

44 ትረካዎች

# ከፍታ

፻፳፱ ገጠመኞችና የረፋዶች

# እፍታ

## 44 ትረካዎች

(በ29 ጋዜጠኞችና ደራስያን የተዘጋጁ)

ፋና ዴሞክራሲ አሳታሚ
አዲስ አበባ

© ፋና ዴሞክራሲ አሳታሚ - 1991

☐ ሽፋን ዲዛይን - አማኑኤል ፒፒኖ

በሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ ታተመ

መታሰቢያነቱ

- ለመንግስቱ ለማ
- ለበአሉ ግርማ
- ለዮሀንስ አድማሱ

# ማውጫ


1. ቢራቢሮ
   ስብሃት ገብረእግዚአብሔር . . . . . . . . . . . . . . 11
2. አውሎ አዲስ አበባ
   ወሰን ዶሚዮስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19
3. ፍርድ
   አንቶን ቼኾቭ (ትርጉም) መኩሪያ መካሻ . . . . . 27
4. የእድሩ ስም ጠሪ
   ተስፋዬ ገብረአብ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 35
5. መቼ ይሆን?
   ደምሴ ፅጌ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 41
6. አሲዳም ዘመን
   ቶማስ አርጋው . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 45
7. ሞገደኛው ጋዜጠኛ
   እሸቱ ተፈራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 51
8. ኬጂቢ በአዲስ አበባ
   ሄኖክ ያሬድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 57
9. የመንግስቱ አባት
   አረፈዓይኔ ሀጐስ . . . . . . . . . . . . . . . . . 67
10. ወፍራምና ቀጭን
    አንቶን ቼኾቭ (ትርጉም) መኩሪያ መካሻ . . . . . 75
11. ፊርአን ሲሶ ዝና
    ስብሀት ገብረእግዚአብሔር . . . . . . . . . . . . . . 81
12. ምንትሴ ቅብጥርሴ
    ደረጀ ደስታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 87

13. በአንድ የበልግ ወራት

ማክሲም ጎርኪይ (ትርጉም) ትእግስት ሀዲይ . . 111

14. የተሻለ ነገር ፍለጋ

ተስፋዬ ገብረአብ . . . . . . . . . . . . . . . 127

15. የማን ዘር ጐመን ዘር

ደረጀ ደስታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 137

16. ኢጋፋሪ እንደሻውና እያ ደብልቡሉ

ስብሀት ገብረእግዚአብሔር . . . . . . . . . . . 147

17. የመተሰ ቀልዶች

ተስፋዬ ገብረአብ . . . . . . . . . . . . . . . . 173

18. ረጅም ሌሊት

የሺጥላ ኮከብ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 179

19. የጆቢ ምስቢር

ሰለሞን ዋስይሁን . . . . . . . . . . . . . . . . 187

20. ፍቅርና ፍቅረኞች

መስፍን ሀብተማርያም . . . . . . . . . . . . . 197

21. ውርርዱ

እንቶን ቼኾቭ (ትርጉም) አፈወርቅ ዘለቀ . . 209

22. ማን ትሆን?

እንቶን ቼኾቭ (ትርጉም) መኩሪያ መካሻ . . 225

23. ሼክስፒራዊ መወድሶች

ተስፋዬ ገሰሰ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 235

24. ሆደባሻው

እንቶን ቼኾቭ (ትርጉም) መኩሪያ መካሻ . . 241

25. ኩቲ

ባሳዝን ደርቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 249

26. በቀል

እንቶን ቼኾቭ (ትርጉም) አፈወርቅ ዘለቀ . . 269

27. ሲባ ላመሉ

አሸቱ ተፈራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 275

28. የሎተሪው ትኬት

29. ፍልቅልቂት ደራርት
አትክልት ሀገገ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 297
30. ማነው ንፁህ ዘር?
እሸቴ ተፈራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 305
31. የመንግስቱ እንጋች ትዝታ
እሸቴ ወንድሙ . . . . . . . . . . . . . . . . . 317
32. ሽሙጥ
ሳሙኤል ተፈራ . . . . . . . . . . . . . . . . . 325
33. በርሜሉ አይሞላም
ተስፋዬ ገብረአብ . . . . . . . . . . . . . . . . 331
34. ትዳር በእደላ
አብዱልቃድር አውልጆ . . . . . . . . . . . . . 343
35. እንደገና እንወለድ
ሲሳይ ንጉሱ . . . . . . . . . . . . . . . . . 347
36. ከአቅም በላይ
አቦነህ አሻግሬ . . . . . . . . . . . . . . . 355
37. አሞራው ሼህ
ይሁን እንዳሻው . . . . . . . . . . . . . . . 361
38. የመቃብር ላይ ፅሁፎች
ኤፍሬም ገብረኢየሱስ . . . . . . . . . . . . . 373
39. ስራ አጡ
አንቶን ቼኾቭ (ትርጉም) መኩሪያ መካሻ . . . 379
40. ይህ አሜሪካ ነው
ተስፋዬ ገብረአብ . . . . . . . . . . . . . . . 387
41. አተርፍ ባይ
ፍሬድሪክ ፎርሰይዝ (ትርጉም) ዝየሁ ዋለልኝ. . . 399
42. አፈርና ሰው
ደረጀ ደስታ . . . . . . . . . . . . . . . . . 405
43. ሀያ ስድስቱና አንድዋ
ማክሲም ጐርኪይ (ትርጉም) ትዕግስት ሁሩይ.. 411
44. ጌታሆይ!
ወሰን ይሄይስ . . . . . . . . . . . . . . . . 439

# ያሳታሚው ማስታወሻ

ስነጽሑፍ ድንበር አያውቅም:: ዓለም ዓቀፋዊ ነው:: ሕይወት በስነጽሑፍ ሲንፀባረቅ እዚህ አገር ያለው የሰው ልጅ ኑሮ የትም አገር ያለውን የሰው ልጅ ልብ ይነካል:: ስለዚህም ነው የዓለም ደራሲያን ማህበር (PEN Ass.) በቻርተሩ ላይ «ስነጽሑፍ ድንበር የለውም» በማለት ያሰፈረው::


እኛም «የጥበብ ቁራጭ የለውም፤ ስነጽሑፍም ድንበር አያውቅም» ብለን፣ ዘመንና ቦታ ያልገደባቸውን ልዩ ልዩ ድርሰቶችን፣ ልቦለዶችን፣ ሐተታዊ መተርኮችን ወዘተ. አሰባስበን «እፍታ» በሚል ርዕስ ለአንባብያን አቅርበናል:: ድርሰቶቹ በማንኛውም የትምህርት ደረጃ የሚገኙ፣ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ግለሰቦችን ልብ የሚነኩ ናቸው ብለን እናምናለን::

እስከዛሬ ድረስ ባለው የኢትዮጵያ የስነጽሑፍ ታሪክ የ29 ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞችን፣ ተርጓሚዎችንና ደራሲዎችን ስራ አሰባስባ ወደ አደባባይ ለመውጣት «እፍታ» የመጀመ ሪያዋ ትመስለናለች:: በዚህ መድብል ከተካተቱት ድርሰቶች መካከል፣ አብዛኞቹ ቀደም ሲል በ«እፎይታ» መፅሄት የታተሙ ቢሆንም፤ ከመፅሄትዋ ስርጭት ክፍ ዝቅ ማለት አንፃር ሲታይ፣ ድርሰቶቹ ሙሉ በሙሉ ከአንባብያን ደርሰዋል ለማለት አያስደፍርም:: ለዚህም ነው ምርጥ ምርጦቹን፣ አሰባስበን በመፅሀፍ መልክ ለማዘጋጀት የፈለግነው:: ወደፊትም ተቀድቶ ከማያልቀው የስነጽሑፍ ባሕራችን እፍታ፣ እፍታውን በ«እፍታ» በኩል ለአንባብያን ለማቅረብ እንሞክራለን:: አንባብያንና የሙያው ባለቤቶች በአድራሻችን ለሚልኩልን አስተያየቶች በቅድሚያ እናመሰግናለን::

ፋና ዴሞክራሲ አሳታሚ



- ኩኩሉ አሰ ዶሮ!
ምን ይሰማ ይሆን ጆሮ?
ዘንድሮ?
ሰካስ ሲነጋ ነው፣
ኩኩሉ ሲል የሰማነው፣
ፀጋ ነው።
(ብዙነሽ በቀለ)



# ቢራቢሮ

## ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

ቢራቢሮ እንደ ደብተር ተከፍታ ደረቷን ለጧት ጸሀይ ሰጥታለች:: ደስ ማለቱ! የጧት ጸሀይ ሙቀቱ::

ሽው ብሎ በላይዋ ላይ አለፈ- አስደንጋጩ የድንቢጥ ጥላ:: ክንፏን ዘግታ! ጸጥ!

ከንድምቢጥ ሆነ ከሌሎቹ የሞት መላእክት ራሷን የምትከላከልበት አንድም መሳሪያ የላት:: ወላ ጥርስ- ወላ

ቀንድ- ወላ መርገዘ:: ምንም!

ምክር ፍለጋ ዶክተር ኤሊ ዘንድ ሄደች:: ዶክተር ኤሊ ጥንት ከነቢዩ ኤልያስ ጋር ነበሩ:: የአበው ጥበብ በድንጋይ ልብሳቸው ሙሉ ተጽፏል እየተባለ ይወራላቸዋል::

ቢራቢሮ ፍርሀቷን ነገረቻቸው:: ፈጣሪ ዘንድ አቤቱታ አቅርቢ አሏትና መንገዱን አመለከቷት::

ቢራቢሮ ጓደኛዋን ሱፍ አበባን ልትሰናበታት ሄደች:: ሱፍ አበባም እንዲህ አለቻት

«አንቺስ ታድለሽ:: ብር! ብለሽ ሄደሽ 'አቤት' ትያለሽ:: እኔ እንዳንቺ ክንፍ ቢኖረኝ ገና ገና ድሮ ሄጄ ነበር፤ ጸሐይዬ ጋ:: አቤት ደስታ! ፀሐይን መጠጋት፤ ጸሐይን መንካት! ለኔ መንግስተ-ሰማያት ነበር! ዳሩ ምን ይሆናል:: ከሩቅ መተያየት ብቻ ሆነ እጣችን:: የአይን ፍቅር::»

ቢራቢሮ ለጓደኛዋ አዘነችላት::

«ለምን አትልኪኝም?» አለቻት «ፈጣሪን ሳገኘው ምን ልበልልሽ?»

«ቀን ቀን ባለሁበት ቆሜ ጸሐይን ስከተል እውላለሁ:: ሌሊት ሌሊት ባለሁበት ተደፍቼ ጸሀይን ስናፍቅ አድራለሁ:: እባክህን እዘንልኝ- ራራልኝ ርህሩህ ነህ ይባላል፤ በይልኝ»

«እሺ» አለችና ቢራቢሮ ሱፍ - አበባ የሰጠቻትን ወለላ እስኪበቃት ጠጥታ መንገዷን ቀጠለች::

ፈጣሪ ዘንድ ስትደርስ በቢራቢርኛ ሰገደችለትና ጉዳይዋን ተናገረች::

«ይህን ሁሉ መንገድ ስትመጪ እነድምቢጥ ወይም ሌሎቹ እንዴት ሳይበሉሽ ቀሩ?» አላት።

«እኔ'ንጃ ። ባያዩኝ ይሆናላ!»

«እንዲህ በቀለማት አሸብርቀሽ እንዴት አያዩሽም?»

«እኔ'ንጃ። ምናልባት የበረራዬ አይነት ይሆናል። ቢራቢሮ ሳልሆን የረገፈና በነፋስ የሚውለበለብ ቅጠል መሳይ ነገር መስያቸው እንደሁ?»

«እሺ። በይ ያውልሽ ያ ትልቅ ቅርጫት። ከውስጡ የፈለግሽውን ሁሉ መሳሪያ ውሰጂ።»

በቢራቢርኛ እጅ ነሳችና ወደ ቅርጫቱ በረረች- እየተጣደፈች። አቤት የመሳሪያዎቹ አይነት! መምረጥ እስኪያስቸግር ድረስ ነበረ። ከብዙ ማመንታት በኋላ ሶስት መሳሪያ መረጠች- የሾሉ ሹላሹል ጥርሶች እና ሲሾል የኖረ ሹል ጦር እና ጨኸት። አስፈሪነቱ ከአንበሳ ጨኸት ሰባት ጊዜ የሚበልጥ ጨኸተ ጨኸት። እነ አዳሜ ድምቢጥን በጨኸተ- ጨኸቷ አስበርግጋ ስታበቃ፤ እድሜ ልኩን ሲሾል በኖረው ጦሯ ከመሬት ሰማዩ ጋር ሰፍታቸው ስታበቃ፤ እንዲያው ለምርቃት ያህል ደሞ በሹላሹል ጥርሶቿ ስትቦጫ ጭቃቸው፣ ይህንና የመሳሰለውን ደጋግ ሀሳብ እያሰበች፤ እየበረረች ወዳገሯ ስትመለስ ራባት።

አንዷ ውብ አበባ- ፈጣሪ ሲያስውባት የከረመ - በደማቅ ቀለሟና በተአምራዊ መአዛዋ ትጣራለች።

«አበባን የፈጠርክ ፈጣሪ! አቤት አፈጣጠሩን ስታውቅበት፤ ኧረ ተመስገን!» እያለች ቢራቢሮ አበባዋ ላይ አረፈች።

ወለላውን ልትጠጣ ብትል ታድያ በየት በኩል? ጥርሶቿ- እንዲያ በጥንቃቄ የመረጠቻቸውና እንዲያ ስትመካባቸው የቆየች ጥርሶቿ አላስጠጣ አሏት፡፡ ይባስ ብለው ደሞ ውቢቱን አበባ ቦጫጨቋት፡፡

«እንዲያውስ ጥርስ ምን ሊያረግልኝ ኖሯል? የኔ ምግብ እንደሆን አይታኝክ፡፡ ለሳቅ ለፈገግታ እንደሆን የኔ ሳቅ ፈገግታዩ ክንፌና በረራዬ ውስጥ ናቸው፡፡ ትርፍ ሸክም!» አለችና እነዚያን የሾሉ ሹላሹል ጥርሶች ወድያ አሽቀንጥራ ጣለቻቸው፡፡

ከአበባዋ ወለላዋን ጠጣችና ጉዞዋን ስትቀጥል «ሆ! ኧረ እንኳንም ጥርስ አልፈጠረልኝ!» አለች፡፡

አገሯ እንደደረሰች መጀመሪያ ያሰበችው ጓደኛዋን ሱፍ አበባን ሳይሆን እንድምቢጥን ነበር፡፡

ሲሾል የኖረ ሹል ጦሯን ወደ ሰማይ አሾለች አመቻቸችና ክንፎቿን እስከጫፍ ዘርግታ ደረቷን ለጸሀይ ሰጥታ ስታበቃ «እነሆ በረከት! እነሆ ቢራቢሮ ለምላ!» አለች በክንፎቿ፣ በቢራቢርኛ እየሳቀች፡፡

ሸው! ብሎ ወረደ - ሞት የተጫነ ድምቢጥ፡፡ ጦሩ ጥልቅ ሲልበት፣ ከህመሙ ይልቅ መገረሙ፣ መደንገጡ ብሶ እዚያው ክንችር አለ፡፡

«አይ አቶ ድምቢጥ! ለካ የተጫንከው የኔን ሳይሆን የራስክነን ሞት ኖሯል! ተመስገን!» እያለች ቢራቢሮ ሆዩ ጦሩን ከድምቢጥየው ሬሳ ላይ ለመንቀል ብትሞክር ብትፍጨረጨር እሷ ትቦጨቅ እንደሆን እንጂ ጦሩ የማይነቃነቅ ሆነ፡፡ ደሞስ የደሙ ክርፋት!

«እንዲያውስ ጦር ምን ሊያረግልኝ ኖሯል? ገድያችው

እንዲህ ከሚገሙኝ፤ እንዲህ እንደሰይጣን ፊስ ከሚከረፉኝ፤ ብቅ ሲሉ ከንፌን እጥፍ አድርጌ አልጠፋባቸውም? ይሻለኛልም ይቀለኛልም» አለችና ጦሩን እዚያው ለድምቢጡ «ማስታወሻ ይሁንልህ ትቼልሀለሁ» እያለች ወደ ሰፈሯ ሄደች::

ውድቅት ነው:: ፍጡራን እንደየፍጥርጥራቸው በየፊናቸው ሲመገቡ አርፍደው፤ እንደ የአይነታቸው ውሀቸውን ጠጥተው፤ በየስፍራቸው እፎይ ብለው በማረፍም በማንቀላፋትም ላይ ናቸው::

ይህን ጊዜ ቢራቢሮ አበባ ላይ ተመቻቸችና ያንን ከአንበሳ ጨኸት ሰባት ጊዜ ጉልቶ የሚጮኸውን አዲስየውን ጩኸቷን ለቀቀችው::

ፍጡራን ከመበርገግ የባሰ በረገጉ:: ብዙ ሯጮች ወለም አላቸው:: ብዙ በራሪዎች ክንፋቸውን ቅርንጫፍ አቆሰላቸው::

ፍጡር ሁሉ በየበረገገበት እንደየፍጥርጥሩ አደፈጠ:: ብዙ ብዙ ቆይቶም በየፊናው አደጋውን ለማየት እዚህም እዚያም ተገላመጠ:: ምንም የለም:: ቀስ በቀስ ወደ የስፍራቸው ተመለሱ::

«እኔ ብቻ ሳልበረግግ» አለች ቢራቢሮ::

«እሱን ተይው! ያልበረገገ የለም» አሉዋት::

«ከኔ በስተቀር»

«ኧረ ባክሽ? አሁንስ አንጎልሽም እንደ በረራሽ አበደ'ንዴ? አንበሳ ራሱ በርግጓል እንኳን አንቺ»

«ሽረሪት ትጠየቅ» አለችና ቢራቢሮ የውልብልብ እየበረረች ሄደች::

... እንግዲህ ሽረሪት ስትበረግግ መብረር ወይ መሮጥ ሳይሆን ጥልቅ! ድብቅ! ሽፍን! ነው:: በዚያ በድርዋ- የምግብ ማግኛ መሳሪያዋ- ልብሷ- ቤትዋ- እንቁላል መጣያዋ- በጥበቧ ከገዛ ውስጧ የፈጠረችው ድርዋ:: የምን ከንቱ ልፋት? ጥበቡን ስጥቷታል:: ታዲያ ከተሸሸገችበት ቀስ ብላ ብቅ ብትል፤ ቢራቢሮ ሆዬ አበባዋ ዙሪያ እየበረረች፣ ራሷን በራሷ እያባረረች በሳቅ ትንከተከታለች- የከንፍ ሳቅ::

«በረራሽ የእብድ መሆኑን አይቻለሁ» አለቻት ሸረሪት «ግን ፍጥረትን በሙሉ የማያስበረግግ ጩኸት ሲያስቅሽ ሰባቴ ነው ያበድሽው፤ እንዴም አይደለ»

«የጮህኩት እኔ ስለሆንኩ ነውኮ!» አለቻት- ቀለማት ክንፎቿን እያክነፈነፈች::

«እየባሰብሽ ሄደ:: ሰባ ጊዜ ሰባት አበድሽ!»

ቢራቢሮ በረራዋን ትታ አበባዋ ላይ ተቀመጠች- ቆመች-ሆነችና፣

«አንቺ ድር ሊኖርሽ ከቻለ እኔ ሃያል- መርእድ- መደንገጽ ጩኸት ሊኖረኝ ለምን አይችልም? ወይስ የተፈጥሮን ምስጢር ሁሉ ታውቂዋለሽ?»

ሸረሪት ብዙ ስለማትንቀሳቀስ በጥሞና ለማሰብ ጊዜ አላት:: ያውም ከድርዋ እኩል ተአምር የሆኑ ሀሳቦች:: እርጋታ አለ ሸረሪት ጋ :: ተረታችን ውስጥ የመነኑት ባህታውያን እርጋታን ለመማር ወደ ሸረሪት ያተኩራሉ:: ለሰባት ሙሉ ሰዓት ያተኩራሉ::

ስለዚህ ሸረሪት በእርጋታ «አሳምኚኝ» አለቻት ቢራቢሮን::

«አዳሜ ፍጡሬ ከብርጎጋዋ ተመልሳ በየስርፋዋ ታርፋለች እማደል? ያን ጊዜ ትኩር ብለሽ እዩኝ- እጮህለሁ- ይበረግጋሉ:: አንቺ ግን ስጮህ እያየሽኝ ስለሚሆን አትደነግጪም»

እንደተባባሉትም ፍጡር ሁላ እንደ የድፍረትዋ፤ በየተራዋ በየስርፋዋ ተመልሳ አረፈች::

ቢራቢሮ ለምናልባቱ ሽረሪትን ለማስጠንቀቅ ጥቂት በራረረች- አበባዋ ላይ ሆነች- እና ድምጹን- ጩኸቱን- ከፈጣሪ ቤት ያመጣችውን - እና እብድም ይጠነቀቃልና በጥንቃቄ የክንፏን ቀለም አስመስላ ክንፏ ላይ ለጥፋ ደብቃ የነበረውን ጩኸት አነሳችና-

አንድ ጊዜ ስትጮኸው ጊዜና ፍጡሬ- አዳሜ እንደ ቅድሙ አይበረግግላችሁም!?

ቢራቢሮ እየበረረች ባበባዋ ዙሪያ በክንፏ ስትስቅ- ስትስቅ- ስትስቅ-

«እሽ! ዝም በይ አንዴ» አለቻት ሸረሪት:: «ሳይመለሱ ስሚኝ፤ ሲመለሱ ምንም እንደ ማናውቅ እናስመስል:: በኋላ በየስርፋቸው ሲያርፉ ጩኸትሽን ስጪኝና አንዴ ልጩኸው»

«እኔ ገና አልጠገብኩትማ!»

«ተይ ተይ ተይ! አንዴ ብቻ? እሺ እንለዋወጥ:: ያንቺን ጩኸት ላንዴ ብቻ ስጪኝ፤ የኔን ድር ጥበብ እሰጥሻለሁ:: አቤት አንዴ ብትወዘወዥው በኔ ድር ሸረሪት በሆንኩ ትይ ነበር::»

እሺ አለቻትና ተለዋወጡ:: ቢራቢሮ በሀር ክር ጥቂት ከተወዛወዘች በኋላ ስለቻትና፣ «አንቺ ድርሽን:: እኔ መሄዴ

ነው» አለቻት፡፡


«እንዴ ሳልጮህባቸው? እሺ ብለሽኝ?»

«ኧረ አስር ጊዜ ጨሄ ተፈለግሽ፡፡ ጨኸቱን መርቂልሻለሁ፡፡»

«ገና አልጠገብኩትም አላልሽም?»

«አሁን ጠገብኩት» አለችና ቢራቢሮ የውልብልብ እየበረረች ሄደች፡፡ «ደሞ ጨኸት ምን ያረግልኛል?» አለች ለራሷ፡፡ «ትርፉ ሽክም!»

ሸረሪትም «ቢራቢሮን ያሳበድክ ተመስገን!» እያለች ጨኸቱን ለእንስሳቱ እያከራየች አድጉን ከበረች፤ ምን መክበር ብቻ ?- ሚሊዮኔር ሆነች፡፡



# አውሎ - አዲስአበባ

## ወሰን ይሄይስ

አውሎ ነፋስ- አውሎ ምድር- አውሎ ባህር- አውሎ ዝናብ- አውሎ ደመና- አውሎ ሰማይ- አውሎ ጨረቃ- አውሎ ከዋክብት- አውሎ ገጠር- አውሎ ከተማ... አውሎ አዲስ አበባ::

አዲስ አበባ የመማሪያ፤ የማስተማሪያ ሰሌዳ፣ የመማሪያ የመመራመሪያ ጣቢያ:: የውቦች ጫፍ፤ የመገናኛ እምብርት፤ የስርጭት ጣቢያ:: የስልጣን ቆብ፤ የግዛት ማእከል:: የአድሀሮት ረግረግ-ማጥ:: የሽንቆሎ ዋሻ:: የምኞት መጋዘን-መፈለጊያ፤

መገናኛ፤ መከማቻ፤ መከፋፈያ። የእለታዊ ህይወት መታዘቢያ፤ ማረጋገጫ፤መዘክሪያ-ስርከ አዲስ።

እስኪ ይሁና! የስምሽ ምልኪ ቢቀና፣ ቢያቀና። ያለጥርጣሬ እምነት የለምና፤ እውነት የለምና! በቸርችል ጐዳና፤ በአብዮት ጐዳና፤ ውስጡን በመርካቶ፣ ወዲያ በቀበና።

እነሆ ከአመታት አንዱም ሊያልቅ ሆነ። የአዲሳባ ምድርም በቀኑ እንቅልፍ የተጫጫናት መሰለች። በየሰው ላይ የተጫጫነ የክብደት ስሜት አሳደረች። ሰማይ ዝቅ ብሎ ምድርን ስለሚጫናት ሰው ሁሉ እንዳይድፈጠፈጥ ተጨንቆ ባላ ለመትከል በመሯሯጥ የደከመ መሰለ። ሁሉም ያለውን ልብስ ደርቦ፣ ደራርቦ ተርመሰመሰ። ሰማይ ሲደማምን ምድርን ለምን እንደሚከረስሰው አይጠየቅም። ትንንሽ መኪናዎች ሲራወጡ ምድርን በአጥለቀለቀው ጭጋግ ውስጥ አፈትልከው ለመውጣት የሚሮጡ ይመስላሉ። ተሽሎከለኩ። ትልልቅ መኪናዎች በጭስ ላይ ጭስ እየተነፈሱ ጮሁ። እንጓቀሱ።

ከላይ ሰማይ የቀን ሌቱን አዝሎ ብልጭ ብሎ እልም እያለ በጩኸት ጉርምርሞች እየተጠራራ ምድርን ያስፈራራል። የሰማይ ነገስታት 'ምታ ነጋሪት፤ ክተት ሰራዊት' ብለዋል። ዲያብሎስ ከግራ ከቀኝ ጆሮ ግንዱ ድረስ ፈገግ ሲል፤ ጥልምያኮስ አጃቢ ሠራዊቱ ሲስቅ ምድር ትንቀጠቀጣለች። ዛፍ ቅጠሉ ፀሐይንና እርጋታን ናፍቆ በወጀቦው ሀይል ይወዛወዛል። አዏራ እየተነሳ ከቦታ ወደቦታ ይበተናል። ፀሐይ የደረሰችበት ጠፍቶ ቀን የሌት ደባል መጥቶባት፣ ሁሉም የአካባቢው ተፈጥሮ ተረብሾ ተደናግጧል። ይህን መደናገጥ ሲያስተውሉት የአዲሳባ

ምድር ዝናብ የምታውቅ አትመስልም:: የአዲሳባ ሰማይም 'ዛሬ የመጨረሻ ነው' የሚል ይመስላል::

ግሩም ነው:: እጅ የለው፤ እግር የለው፤ አፍ የለው፤ ጉሮሮ የለው፤ ሲበላ ሲጠጣ - አናይ አንሰማ - ደንፊ ጭንቅ ነፊ:: አንድ የተፈጥሮ ዘርፍ፤ ዘርፋዘርፍ - ጥቀርሻ የመሰለ - መከራ ያዘለ የአዲሳባ ሰማይ፤ ባልሻ እንደያዘው ሆድ እየጮኸ ይፎክራል፤ ያስፎክራል:: ልጆች ወስፋት ሲወጥራቸው ወይ አንዳች ነፍሳት በትርፍ አለቦታው ሲገላበጥባቸው ሆዳቸው ቅትት ብሎ ያብጥና ውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ:: ያን ጊዜ ሀበሻዋ እናት ለልጇ ጤንነት ስትል የማታደርገው የለም- የጥጥ መዳመጫ ብረቷን ታመጣና ልጇን አንጋላ የአበጠ ሆዱን በቅቤ ወይ በምራቋ እያወዛች ቁልቁል ትዳምጠዋለች:: በሽታው ወርዶ እንዲፈተለክ:: ልጁም ትንሽ ያቃስትና እፎይ ይላል- ከወጣለት:: ካልዳነም ይሞተዋል:: እናትዬዋም የዘሯን የእድሜዋን ታለቅሰዋለች:: ለቀሪ ዘመኗ ተጨማሪ እንጉርጉሮ ይሆናታል::

አይ አዲሳባ! መንገዱ ግም- ቆሻሻ! ቤቱ ውሽልሽል- ደሳሳ! ሰማኝ ተሰማኙ ክሳሳ! ምላስ ብቻ! ማደንቆር ብቻ! ሳቅ ብቻ!...

የተነዳደለ ገላ ሲደመር፤ የቡትቶ ድሪቶ ሲደመር፤ አደንቋሪ የነፍስ አድን ዜማ ይሆናል- ለማኝ:: «እስጠሲታ» ለማኝ:: ባለፀጋ የጣለው ካልሲ፤ የአዲሳባ ለማኝ በኩራት ለሚከናነበው ማባለቻ፤ ድግዳግ ጋቢው ማሟያ ይሆነዋል:: በአገራችን ሰው ለሰው ምን ያህል እንደተጨካከነ፤ ምን ያህል እንደተለያየ፤ ለማሳየት በዋቢነት የተጐለቱ የድሀ ድሆች:: ከቆሻሻ መንገድ ዳር እየተንፏቀቁ የባለፀጐችን የምግብ አምሮት የሚቆልፉ ትርፍ ሰዎች- ትራፊ፣ ትርፍራፊ ሰዎች፤ ከአለም ለምኔዎች ወይ እንዲታዘንላቸው የተፈጠሩ ይሆኑ?

ወይስ ባለፀጋ ፈጣሪውን ለማመስገኛ ማመሳከሪያዎች ያሆኑ?

እውነታቸው የራሳቸው፣ ፍርዳቸው የግላቸው፣ አገራቸው ከርሳቸው፣ የኢይሉት የሌላቸው:: በህብረተሰቡ ሰማይ ውስጥ የሞሉ እብቆች! «ትቢያዎች!» ብቻ ስጡኝ ብቻ ልመና:: እንደቡትቶ የጨርቅ ኳስ መንደር ለመንደር፣ መንገድ ለመንገድ እየተጠለሉ፣ እየተልወሰወሱ ቀኑን ሁሉ የልመና ያደርጉታል:: በነሱ አዘን - በነሱ ዋይታ ስንቱ እስበሱ ተማታ! ሰጥቶ ላይሰጥ፣ አትርፎ ላያተርፍ፣ ስንቱ ጉበዝ ተንገላታ! በመርዝ፣ በጥይት ተመታ!... ደሞ ግድ የላቸው:: አንድ የእለት ጉርሻ ከሰጧቸው:: የእድሜው፣ የሀብቱ፣ የጤናው፣ ልመናቸው:: ይደርስ እንደሁ ምረቃቸው፣ ከልብ እንደሁ ምስጋናቸው:: እንኳን ጉርሰው፣ እንኳን በልተው፣ ሲሸታቸው ሲያሸቷቸው:: ደሞ በዚህ ላይ እርባታቸው:: ሀብት ንብረት እንዳለው ሰው፣ ድሀ ወዳድ - ዘመድ ወዳጅ እንዳለው ሰው:: ወጉ ልምዱ አይቀራቸው:: ያው እንደሰው ተፈጥረው:: ማጨት የለ፣ መታጨት የለ፣ ሠርግ የለ፣ ውል የለ... ደሞስ እንዴት ይኑር? ለምንስ ይኑር? ብለው ብለው አዲሳባን አይጠሉትም ብላችሁ ነው?... ኑሮ፣ ያላየ ይይሽ መባባል ቢሆን ኖሮ ሰው በተፈጥሮው ማን ከማን ያንሳል? ሁሉም ሰው ሁሉንም አርሶ የሚያበላ አፈር ገፊ ገበሬ ነው! ገበሬ ያለ ከአዲሳባ ውጭ! አዲሳባ ውስጥ ማን ኖረ? ማን ሆነ?

አዲሳባ የጉዳንጉድ መንደር ኮ'ናት:: ምን የሌለ ጉድ አለ? የንግዱ ብዛት አጥወልውሎ የማይደፋት? የማይከነትራት? በጢምቢራዋ የማያቆማት? ወይ ራሷ አለመሸጧ!... ያ ሁሉ ትልቅም ትንሽም መኪና መሀሉን እየሰነጠቀ ዳር ዳሩን እምቧለሌ እየዞረ መሄድ አቅቶት

እስተሚያስከልክ ተጭኖ ሲደፈጥጣት ውስጥ እያደረ አለመስመሟ! ምድሪቱ ግን ቻይ ናት- የእስቻላት የተቻላት ከተማ! ይሄ ግን ችሎታ አይደለም። የመጨረሻ ንጉሶች፣ የመጨረሻ ከተማ ሆኖ መቅረት ችሎታ አይደለም። ነው እንዴ?... ደሞ የስሟ ማማር! አማጋ እንደማለት ደብ-ምድር እንደማለት፣ አዲሳባ። ፊንፊኔ። ሸገር። ሁሉም ያው ነው። አዲሳባ የሰው አማጋ ናት! ማስረፊጃ ማዋያ፣ ማቆያ፣ ማገጃ...

ትነሰ ጃርት። የነጋደው እቃ ትርኪ ምርኪው መብዛቱ። ጨለው ቢሏቸው ውድ፣ ስኳር ውድ፣ ዳቦ ውድ፣ እንጨት ውድ፣ ውሀ ውድ፣ እና ውድ ብቻ! ከቆሎ አቅም የሚሸጠው ከሳንቲሙ ቁጥር አይበልጥም። የአስር ሳንቲም አስር ፍሬ። የሃምሳ ሳንቲም ሃምሳ ፍሬ። ችጋር ጠሪ! ሰውስ እንዴት እርጎ በየት በኩል በልቶ ይጠረቃል? ምሳ በልቶ ለእራት መጨነቅ ባለበት፣ እህሉስ እንዴት እርጎ ሰውነት ይሆናል? ሰው ዘንድሮን በማጀቱ ይዞ ከርሞን በቡቃያው ካልተከራራ ምኑን ኖረው ይባላል? ነገር የእድሜ ልክ ስንቅ ይሆናል?

የአድሩስ አይነት፣ የሽቶው አይነት... ሬዲዮው፣ ጋዜጣው፣ በቃ አለባበስን አሳምሮ - ጠረንን አሳምሮ መወዛወዝ ብቻ- እንደባለዛር። ኧረ ባለዛርስ አይነት አለው-እንደ አባይ ጠንቋይ! ከሰው ብዛት የተነሳ በመተፋፈግ እምክ እምክ እንዳይሉ ተብሎ ይሆን የሽቶው ጋጋታ ያስፈለገው? ያፍንጫ ስንቁ በዛከ! ግን ደሞ ቆሻሻ ከዝና፣ ቆሻሻ ተንፍሶ፣ ንጽህና ሽቀጣቸው ቢከላና አለባበሳቸው ቢቆሸሸ ምን ይሆኑ ይሆን? በአንድ ቀን ስደት ሳይሄዱ ይቀራሉ? አዎን ኑሮ በአዲሳባ የእለት ብቻ ናት። ከተመኛ እንደገጠሬ ጉብል እሽሩሩ በሉኝ የሚል የሚመስለው የህይወቱ ዋስትና ባጭሩ የታቀደ ስለሆነ ይሆናል።

የወንበሩ የጠረጴዛው የመደርደሪያው ብዛት:: የዶሴው የወረቀቱ የፋይሉ ብዛት:: የተሰራበት፣ ያልተሰራበት፣ የሚሰራበት፣ የማይሰራበት... የነገር ቋት ብቻ! ወግ ጠራቂ ብቻ! ተማሪው ልቡን እያቋተ እያመረቀዘ እያቀለዘ ይነጉዳል:: እናም የዘላለም መንገደኛው የእውቀት ቅብብሎሽ ሂደት በየመንታ መንገዱ ይገታል፤ ይቀጥናል፤ ይዳከማል:: አስተማሪስ ማዘኑ ይቀራል? አእምሮውስ ስተጨማሪ ፊደሎች እውቀቶች መስላቱ ይቀራል?... ሲሆን ባልሞተ፣ ከሞተም ባልተረሳ- ተማሪ የባላገር አንበሳ፣ የድሆች አንበሳ፣ ጉልበቱ እንኳን ባይኖር በድምጹ ሲያገሳ ለሁሉም ሰው መብት ተነስቶ ሲያስነሳ::

ንግር ከግር ግትር- የማይቀር:: አዲሳባ ስቅል ከተማ:: ተራዋን ቆማ ትጠብቃታለች- ቆመው እንዳሳለፏት:: ነጥቃ ነጥቃ - ሌላውን አድቅቃ አድቅቃ - ለራሷ ተመንጥቃ ተመንጥቃ - እንደተሰረቀ እቃ እድገቷን ለራሷ ደብቃ፣ አምቃ አምቃ... አዎና የከተማ ድፍርስርስ፣ የሁሉም በዋልፈሰስ፣ እሷን ብሎ አዲስ! ደሞ አበባ- ገለባ!

ስሟን አሳምራ፣ ተወይዝራ፣ ሌላው በሰራ እሷ ኮርታ፣ እሷ ከብራ፣ ተንቀባራ:: የውጭውን የውስጡን ቀላቅላ፣ አቀላቅላ፣ ሌላውን በልታ በልታ፣ አስበልታ አስበልታ- ለሳባት ሁላ፣ ለሳማት ሁላ ፊቷን ሰጥታ ሰጥታ፣ ሌላውን አንክራታ ለራሷም ተንክራታ::

አንችን ያቀፈና ባንች የታቀፈ በለፈለፈ፤ የስንቱ ቀልብ ተገፈፈ? የስንቱ ህይወት ተገፈፈ? ቆይ ብቻ! እኔማ አታውቂኝ አላውቅሽ፣ አላቀፍሽኝ አላቀፍኩሽ፤ ደሞም ባውቅሽ ባላውቅሽ ለዚህ አልፈልግሽ - ቢገባሽ ግን እንደሌላው ኑሪ- ስርተሽ ጥረሽ ግረሽ:: አንች ከሌሎቹ

በምን ትለያለሽ? የከተማ ደልቃቃ፣ ቦቃቃ - የድሆች ስቆቃ!...

ደሞ ትሁት ለመምሰል ይታሰባል ሌላውን ለመወከል ይሞከራል:: እንግዳ ሲመጣ ይሳቃል:: ፈገግ ይባላል:: ግትቻ! ውሸት ነው:: መላ ነው፤ ለማጭለግ ነው:: ከየቦታው እየጐረፈ የሚደባለቅሽ ሰውም ሌላውም ጤነኛ ነገር ይዞ አይመጣም::... ውሻ ፎቅ ላይ እየኖረ ሌባ ሊጠብቅ ነው? ድመት ፎቅ ላይ ሆና አይጥ ልታድን ነው? አዲሳባ እንኳን ሰው ከሰው እንስሳው ከእንስሳ ባህሪ የተለየበት ነው:: ድመት በአይጥ አትጫወትም-ራሷ ድመት መጫወቻ ናት:: አይጥ አይታ የማታውቅ ድመትም ሞልታለች:: መስክሩ አትፍሩ:: አሁን የአዲሳባ አንበሳ አንበሳ ነው? አቅሙን አቅም አግዶት!

«ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ፤

አገርም እንደሰው ይናፍቃል ወይ

ብለው ያደነቁሽ ይበቃሻል ወይ?

ወይስ ላክልልሽ እኔም በድርሻዬ፤

ማጠንተ- ዲያብሎስ ኩነኔዬ ብዬ፤

የሳጥናኤል እሳት- ነበልባሌ ብዬ፤ ገለባዬ ብዬ::

አንችም ትኖሪያለሽ እኔም አለሁልሽ፤

ገለሽ ባትጨርሺኝ ሞቼ ባላልቅልሽ፤

እጅሽ ለኛም ገብቶ እስከምታዘብሽ::»

ብዙ ሰው ለምን እንደሚጠላሽ ታውቂያለሽ አይደል አዲሳባ? ስለጠላሽው፤ በቃ የጠላሽው ጠላሽ:: ድሀሽ ጠላሽ:: የኋላ ኋላ በደረመንሽ ተበክሎ በክቶ በመሞቱ ኗሪም ጠላሽ፤ ሟችም ጠላሽ:: ሟች በኑዛዜ ረገመሽ፤ ኗሪም በውርስ

አወገዘሽ፤ ርግማን ይጉዳሻል:: የባሰበት ያጠፋሻል- ይገልሻል:: እኔ ላንች ብዬ ነው:: ለማኘሽ ኑሮሽን ጠላው:: እውሲ ስኳላ! የኳላ ልሴን እውጥቻለሁ::... እህ ማን ይሞክርሽ? ድህነትማ ማን ይወዳል? እና ተይ ድሀ አትናቂ:: ሰው በየቀኑ ምን ልብላ? ምን ልጠጣ? ምን ልልበስ? የታባቱ ልግባ?... እያለ እንደተበጠበጠ እንዴት እድሜውን ይዘልቀዋል? «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» የእህያ ተረት መሰለሽ? ሞኝ አትሁኚ-አህያ ተናግራ ሰው ሰምቷት አያውቅም::

ይሄ «...ትግል አይሞትም» የሚሉ አስተሳሰብሽንም ወዲያ ጣይ:: የነገር ታንቲራ አይረባም:: ትግል ሞተ አልሞተ ለድሀ ርባና የለውም:: ትግል እህል ውሀ ካላስገኘ ፈላጊ የለውም:: ያንች የትግል ጨዋታ ብልጥነት ነው:: ሰው የውን ገሎ ጥሎ፣ ታግሎ ወደቀ ብሎ ማውራት ተሰልችቷል:: እና ሁሉንም አስቢበት:: ለራስሽ እወቂበት ነው የምልሽ:: 'ገሎ ይማርህ' ጨዋታሽን ተይ::

ደሞ ቢሮ- ክራሲ ድሮ - ክራሲ አትበይ:: ማን ፈጠረውና ወዴት ነገር ታላክኪያለሽ? ለነገሩማ አንችኮ ጤና ከአጣሽ ውለሽ አድረሻል:: በይ ችሎቱን ይሰጥሽ፣ ውቃቢ ይቅረብሽ:: ቸር ያበጀን፣ ቸር ያክርመን:: ልባችንን አንድ አፋችንን ባይድ ያርገው፤ ለዚህ እያባብለን:: ያመካክረን እንጅ አያፎካክረን:: ይትቀበሉ አቡነ ዘበሰማያት...



# ፍርድ

**አንቶን ቼኾቭ**

**(ትርጉም) መኩሪያ መካሻ**

«የመቶ አለቃ ፕሪሽቤቭ! መስከረም 3 ቀን፣ የበታችሹም የሆነውን ዥጊንን ሰድበዋል፣ አስፈራርተዋልም። የአምራች ገበሬ ሊቀመንበር የሆኑትን አልያፖቭን፣ የጥበቃ ተመራጩን ኢፍሞቭን፣ ኤግዚቢት መዝጋቢውን ኢቫኖቭን፣ ገቭሪሎቭንና እንዲሁም ስድስት ገበሬዎችን፤ በተለይ እዚህ ላይ ሦስቱ የመጀመሪያዎቹ ሙያዊ ግዴታዎቻቸውን

በሚወጣበት ሰዓት ሰድበዋቸዋል:: ስለዚህ ጥፋተኛነትዎን ያምናሉ?»

ፕሪሽቤብ ግንባሩን ቋጥሮ በተከፋ ስሜት እጁን አወራጨ:: ከመቅጽበትም የድምፁ ቅላጼ ተለወጠ:: በሻከረ ድምፅ እያንዳንዱን ቃል እየረገጠ፣ ልክ ሰው እንደሚያዝ ሆኖ፣ «የተከበረው ፍርድ ቤት! በሕጉ መሠረት የመሥራት ሕጋዊ ኃላፊነት አለብኝ:: ጥፋተኛው እኔ ሳልሆን ስማቸውን የጠራኋቸው ሰዎች ናቸው:: በተጠቀሰው ዕለት ከባለቤቴ ከአፊሳ ጋር በዝምታና በጨዋነት በምዝናናበት ወቅት አወንዙ ዳርቻ የተለያዩ ሰዎች ተሰብስበው አየሁና ጠየቅሁ:: 'ህዝቡ እዚህ የሚሰበሰበው በየትኛው መብቱ ነው? ለምን? ሕዝብ ሥርዓት የለሽ ይሁን! የሚል አንቀጽ በየትኛው የህግ መፅሃፍ ላይ ነው የሰፈረው?' ስለዚህም 'ተበታተን!' ብዬ ትዕዛዝ ሰጥቼ ሕዝቡን ወደየቤቱ በተንኩ:: የጥበቃ ተመራጩንም እየገፈተረ እንዲያባርር አዝዣለሁ::»

«ይፍቀዱልኝና እርስዎ የፖሊስ አዛዥ ወይም የአካባቢ ባለሥልጣን አይደሉም፤ እናም ሕዝቡን መበተን ሥራዎ ነው እንዴ?»

«የእሱ ስራ አይደለም! አይመለከተውም!» የሚል ድምፅ ከፍርድ ቤቱ አዳራሽ የተለያየ አቅጣጫ ተሰማ::

«ሰብአዊነት የለውም ክቡር ፍርድ ቤት! አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ ታገስነው! እሱ ከግዳጅ ከተመለሰ ጀምሮ ከሰፈር ለቅቀን መጥፋት ያስመኘናል:: ሁላችንንም አስቸግሮናል!»

«በትክክል እንደሰሙት ነው ክቡር ፍርድ ቤት!» አሉ ከአካባቢው መስካሪ ሽማግሌዎች አንዱ «ከእሱ ጋር መኖር ፈጽሞ አይቻልም:: እየተንዣዘንም ሆነ ሠርግ ላይ

ወይም ደ'ሞ በዕረፍት ጊዜያችን ይደነፋብናል፣ ይረብሸናል፣ሥርዓት ካላስከበርኩ ይላል:: የልጆቻችንን ጆሮ ይቆነጥጣል፣ ሴቶችን እንደ ጉድ ይገላምጣል-እንዲያውም እማት ሆኖባቸዋል:: . . .አሁን በቅርቡ በየቤቱ ጥግ እየዞረ እንዳይዘፍኑ፣ እሳት እንዳያነዱ ያዛል:: ዘፈን እንዳይዘፈን ግን በሕግ የተደነገገ ነገር የለም...»

«ቆዩኝ እርስዎ ቀጥለው በሰፊው ምስክርነትዎን ይሰጣሉ» ብሎ ክቡር ፍርድ ቤቱ ሽማግሌውን አቋረጣቸውና «አሁን የፕሪሽቤብ ተራ ነው:: ይቀጥሉ ፕሪሽቤብ!»

«አመሰግናለሁ» አለ ሳግ ተናንቆት «የተከበሩ ዳኛ 'ሕዝብን ማባረር ያንተ ሥራ አይደለም' ይባላል. . . ጥሩ! ግን ሥርዓት አልበኝነት መስፈን አለበት? ሕዝቡ እንዳሻው እንዲሆን መፍቀድ አለብን? በዬትኛው ሕግ ነው 'የሕዝብን ፍላጎት ጠብቁ' የሚል የተጻፈው? ይህ እንዲሆን ፈጽሞ አልፈቅድም:: እኔ እነሱን ፈር ካላስያዝኩ ማን እንዲያሲዝ ይጠበቃል? በዚህ መንደር ከእኔ በላይ ሕግ የሚያውቅ ሌላ ሰው የለም፤ ክቡር ሆይ! ከተራ ኃላፊዎች ጋር እንዴት መሥራት እንደሚገባ የማውቅ ሰው ነኝ:: የተከበሩ ዳኛ! ሁሉን ነገር አውቃለሁ:: እኔ ተራ ሰው ሳልሆን የሙት አለቃ ነኝ፣ ሻምበል ለመሆን የተቃረብኩ:: በዋርሶ፣ በጠቅላይ መምሪያ አገልግዬአለሁ፤ ቀጥሎ ደ'ሞ በእሳት አደጋ መከላከያ ውስጥ ነበርኩ፤ በህመም ምክንያት ከእሳት መከላከያው ከወጣሁ በኋላ ለሁለት ዓመታት በወንዶች ጂምናዚየም በጥበቃ ኃላፊነት አገለግያለሁ. . . ማናቸውንም አሰራሮች አውቃለሁ:: ሌላው ተራ ሰው ግን ይህን ሁሉ ስለማይገነዘብ እኔን ማዳመጥ አለበት፤ ለራሱ ጥቅም ሲል:: አንድ አብነት ልጥቀስ . . . ሰዎችን ከአካባቢው በማባርርበት ወቅት ውሃ ውስጥ ሰጥሞ የሞተ ሰው ፋልማው ላይ

አጋጠመኝ:: 'በምን ምክንያት ነው እዚህ የሞተው?' ብዬ ጠየቅሁ:: ለመሆኑ ይህ አግባብ ነው? የአካባቢው የፖሊስ አለቃስ ምን ይሠራል? 'ለምንድነው ለበላይ አለቃህ ሪፖርት ያላቀረብከው?' አልኩት:: ሟች ራሱን በራሱ ገድሎ ይሁን ወይም በሌላ ተገድሎ አይታወቅም:: እንዲያውም የሌላ እጅ ያለበት ይመስላል:: የሚመለከተው የፖሊስ ኃላፊ 'ኻርጊን' ግን ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ ዝም ብሎ ሲጋራውን ያቦናል:: ይህ ምንን ያመለክታል? 'አንተን ብሎ ምክር ሰጭ? እኛ የራሳችንን ሥራ ሳናውቅ ቀርተን ነው?' አለኝ:: እኔ ደግሞ 'አታውቅም! እዚሁ ተቀምጠህ ምንም አላየህም!' አልኩት:: 'በትላንቱ ዕለት ለከተማዋ ፖሊስ ዋና አዛዥ አስታውቂያለሁ' አለኝ:: 'ለምንድነው ለከተማዋ ፖሊስ አዛዥ የምትነግረው? በየትኛው ሕግ መሠረት እንደዚህ ዓይነት ነገር፣ በተለይ ሰው ወንዝ ውስጥ ሞቶ ሲገኝ፣ ሲሰቀልና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የፖሊስ አዛዡ ምን ማድረግ ይችላል? በዚህ ሰዓት ሁኔታው ወንጀል ስለሆነ በፍጥነት ማስተላለፍ ያለብህ ለመርማሪውና ለፍርድ ቤቱ ነው' አልኩት:: 'ከሁሉ በፊት አስቀድመህ ፋይሉን በመክፈት በቀጥታ ጉዳዩን ለተከበረው ፍርድ ቤት መላክ አለብህ?' እሱ ግን የበታች ሹም ነው፤ ዝም ብሎ ይሰማኝና ይስቃል:: ሌሎቹም ሰዎች እንደሱ ናቸው:: ሁሉም ስቀውብኛል:: ክቡር ፍርድ ቤት እነማን እንደሆኑ ምዬ ላሳዮት እችላለሁ:: ይሄው ይሄ ራሱ ኻርጊን ስቋል:: ደግሞ 'ምን ያስገለፍጣችኋል?' ስላቸው የበታች ሹሙ ተነሳና 'ለክቡር ፍርድ ቤቱ እንዲህ ያለውን መግለጽ ተገቢ አይደለም' አለኝ:: በዚህ አባባሉ ብቻ አናደደኝ:: በል ተናገር እንጂ! ሹም ... ይህን አላልክም?» ብሎ ኻርጊንን ጠየቀ::

«ተናግሬያለሁ፡፡»

«'ለፍርድ ቤቱ እንዲህ ያለውን መግለጽ ተገቢ አይደለም' ብለህ በተራው ሕዝብ ፊት መናገርህን ሁሉም ሰምቷል፡፡ ሁሉም በደንብ ሰምቷል ... የተከበሩ ዳኛ ኀፍረትን አናድዶኛል፤ ሌላው ቀርቶ በዚሁ ምክንያት ኪሎዬ እንኳ ቀንሷል፡፡ 'ድገም እስቲ ያልከውን እንደገና!' ብለው መልሶ መላልሶ ይህንኑ ቃል ይደጋግምልኛል ... 'እንዴት ነው ስለ ተከበረው ፍርድ ቤት እንዲህ የምትናገረው? የፖሊስ ሹም ሁነህ ፀረ መንግሥት ትሆናለህ? አ! የተከበረው ፍርድ ቤት፣ በዚህ አባባልህ ክፉ ሀገር ወህኒ ነበር የሚከትህ፤ የተከበረው ፍርድ ቤት በዚህ የፖለቲካ ንግግርህ ዪት እንደሚከትህ ታውቃለህ?' ስለው የበታች ሹም መልሶ 'ፍርድ ቤቱ ከተሰጠው መብት አልፎ ምንም አያደርገኝም፡፡ እነዚህ ጥቃቅን ነገሮች አይመለከቱትም' እንዲህ ብሎ ነው የተዘባነነብኝ፡፡ ሁሉም ሰምቷል፡፡ ... 'ለመሆኑ' አልኩት 'መንግሥትን ማዋረድ ትችላለህ? ወንድም ከእኔ ጋር ቀልድ አያዋጣህም' አልኩት፡፡ በዋርሶና በወንዶች ጂምናዝዩም የጥበቃ ክፍል ኃላፊ ሁኜ በነበረበት ዘመን ትክክል ያልሆኑ ቃላትን ስሰማ ወዲያው ወደ መንገዱ ወጥቼ የጥበቃ ፖሊሶችን ነበር የማፈላልገው፡፡ 'ጥበቃ! ወዲህ ና!' ብዬ የሰማሁትን በሙሉ አስገነዝበዋለሁ፡፡ እዚህ ገጠር ውስጥ ግን ለማን ሪፖርት ማቅረብ ይቻላል? ... አናደደኝ፡፡ የአሁን ዘመን ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም፤ ጥፋተኝነቱንም አይቀበልም፡፡ እኔም በዚህ ጊዜ ለመማታት ሞክሬያለሁ፡፡ ... እርግጥ ይህን ያህል ከበድ ያለ ባይሆንም፣ ክቡር ፍርድ ቤቱን እንዲህ ያለ ቃል እንዳይናገር ለማድረግ ስል ... እኔ የበታች ሹሙን ብሆን ኖሮ .. እ .. የማደርገውን አውቅ ነበር ... ተናድጄ ነበር ክቡር ዳኛ፡፡ በዚህ ዓይነት ታዲያ መማታት ሲያንስ ነው፡፡ ባለጌን ሰው መደብደብ

ካልተቻለማ ሐጢያት ሁኖ ነው መንፈስ ውስጥ የሚቀረው:: ይፍቀዱልኝና አጥፊዎቹን እዚሁ ላሳይ፤ የቢታች ሹሙ፣ ሽማግሌውና ነጭ ለባሾቹ ናቸው:: እርግጥ የቢታች ሹሙን ከሌሎች ጋር ማነጻጸር አይቻልም:: እኔ የማውቀውን ያህል የሚገነዘብ አይደለምና ...»

«እዚህ ላይ- ይህ የእርስዎ ጉዳይ አይደለም!» አሉ ዳኛው::

«ምን?! እንዴት የእኔ ጉዳይ አይሆንም? ተአምር ነው ... ሰው የእኔ ጉዳይ እንዳልሆነ አድርጐ ያምታታል፤ የእኔ ጉዳይ አይደለም?! ምን እንዳደርግ ነው የተፈለገው? እንዳሞግሳቸው? በእርስዎ ፊት 'እንዳንዘፍን ተክለከልን' ብለው ያሳጡኛል፣ የእነሱ ዘፈን ... ትላንት ደግሞ አንድ ወግ አምጥተዋል ... እሳት ከበው የመቀመጥ፤ በጊዜ መተኛት ይገባል:: እነሱ ግን እያሽካኩ ወሬያቸውን ይጠርቃሉ:: በማስታወሻዬ አስፍሬዋለሁ!»

«ምንድነው የጻፉት?»

«እነማን እሳት ከበው እንደሚቀመጡ::»

ፕሪሽቤቭ አንድ የተጨማደደ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ መነጽሩን አድርጐ ማንበብ ጀመረ፣ «እሳት ከበው የተቀመጡ ገበሬዎች፣ ኢቫን ፕሮሆሮቭ፣ ሳቫ ሚኪፎሮቭ፣ ፔትር ፔትሮቭ፣ ሴት ወታደር ሹስትሮቫ፣ ይህቺ ሕጋዊነት ያለው ጋብቻ ሳትመሠርት ከሲመን ኪስሎቭ ዘንድ ገሴ የገባች ነች:: ኢግናት ስቬርቾክ አላፊ አግዳሚውን ተሳዳቢና ሚስቱም ማቭራ ለላቢ ነች፣ በጭለማ እየዞረች ነው የሌላ ሰው ላም የምታልበው ...»

ዳኛው «በቃህ!» ብለው አስቀመጡትና ሌሎች

ምስክሮችን መጠየቅ ቀጠሉ::

ፕሪሽቤብ መነጽሩን ግንባሩ ላይ አስተካክሎ እሱን የደገፉ ያልመሰሉትን ዳኛ በገረሜታ ተመለከተ:: ያጉረጠረጡ አይኖቹ ያበሩሉ፤ አፍንጫውም ቀልቷል:: ዳኛውን፣ ምስክሮችን በአትኩሮት እየተመለከተ፤ ዳኛው ለምን እንደተጨነቁ፣ ከየአቅጣጫው የሚፈነዳው ሣቅና ጉምጉምታ በምን ምክንያት እንደሆነ በማሰብ ግራ ተጋባ:: «የአንድ ወር እሥራት!» የሚለው ፍርድም ለምን እንደተወሰነበት ፈጽሞ ሊገባው አልቻለም::


«ምን አጥፍቼ ነው?!» አለ እጁን እያወራጨ «የምቀጣው በዩትኛው ሕግ መሆኑ ነው?»

አሁን ግልጽ ሆነለት:: ዓለም ለእርሱ ተለውጣበታለች:: ስለዚህ 'በዚህ ዓለም ላይ መኖር አይቻልም ማለት ነው' አለ:: ጭልም ያለና ተስፋ የለሽ ሃሣብ ወጠረው:: ከአዳራሹ ሲወጣ የተሰበሰቡትን ሰዎች ተመለካከተ:: ምን እንደሚናገሩ እንኳ ሊገባው አልቻለም:: ስለዚህ በንዴት:-

«ሕዝብ - ተበታተን! አትሰብሰብ! በየቤትህ ግባ!» እያለ አጉተመተመ::



# መርካቶ



# የእድሩ ስም ጠሪ

ተስፋዬ ገብረአብ

ይህን ታሪክ የነገሩኝ ሁለት ጓደኞቼ ናቸው:: ታሪኩ በዚሁ በአዲስ አበባ ልደታ በተባለ አካባቢ በትክክል የተፈፀመ መሆኑን እየማሉ ነው ያጫወቱኝ:: ለአንባቢ በሚስማማ መልኩ አቅርቤዋለሁ::

እለቱ ሰንበት ነው...

ሰንበት ስለሆነ ነው መሰል ቀብር ላይ በርከት ያለ ሸኚ ተገኝቶአል:: በኦርቶዶክስ ሀይማኖት አማኞች ልማድና

ደንብ መሰረት በቀብር የተገኘና ያልተገኘውን ለማጣራት የስም ጥሪ ይካሄድ ጀመር:: ስም ጠሪው ባሻ መላኩ እርጅና ተጭኖአቸዋል:: እርጅና በብርቱ ክርን የደቆሳቸው ቢሆንም ግን ድምፃቸው እንደ ባቡር ጡሩምባ ነው:: በፀጥተኛው የመቃብር ስፍራ እየተምዘገዘገ ከአስከሬን ሽኚው ጆሮ ይደርሳል::

«አመት ፊትሰወርቅ ሙሉ»

«አቤት!»

«አስር አለቃ እርገጤ ሺባባው»

«አለሁ!»

«ወይዘሮ ከበቡሽ ደሜ»

«አቤት!»

«አቶ ዳኜ ተማም»

ምላሽ አልነበረም::

«አቶ ዳኜ!?» አሉ ስም ጠሪው በድጋሚ::

«አለሁ!... አለሁ! ...» የሚል ድምፅ ተሰማ::

ይህን ጊዜ ሽማግሌው ስም ጠሪ እብድ የሚያህለውን ዶሴ አጥፈው እርሳሳቸውን ጆሮአቸው ላይ ሰክተው ከፊታቸው ለተኰለኰሉት የእድሩ አባላት ማስጠንቀቂያ ይሰጡ ጀመር::

«ስሙኝ ቀባሪዎች! እኔ ላንቃዬ እስቲዘጋ የምጮኸው እንደ ፊልፕስ ሬድዮ ባትሪ ውጩ አይምሰላችሁ:: በዚህ እድር በቀን አንድ ሰው ይሞታል:: በየቀኑ እጮሀለሁ! በ75 ብር ደሞዝ! በ75 ብር ስጮህ መዋሌ ወገኖቼን ልጠቅም ካልሆነ

ገንዘቧ ምን አላት? ስለዚህ ካንድ ጊዜ በላይ አልጠራም! ውርድ ከራሴ:: ቀሪ ተባልሁ ተብሎ ቅያሜ እንዲመጣብኝ፣ ተቀጣሁ ተብሎ ወቀሳ እንዲወርድብኝ አልፈቅድም:: ጆሮአችሁን ተከላችሁ ስማችሁን አዳምጡ:: እኔ የቁራ ዘር የለብኝም:: በሜዳ የሚጮህ ቁራ ነው:: በየባህር ዛፉ፣ በየገደሉ፣ በዋርካ ላይ ተጉልቶ ሲጮህ የሚውል ቁራ ነው:: እኔ ግን ቁራ አይደለሁም» ስም ጠሪው በተጨማደደች መሀረም ግንባራቸው ላይ ያቸፈቸፈውን ላብ አደራረቁና ጥሪውን ቀጠሉ::

«ወይዘሮ የሁዋላሽት አለሙ»

«አለሁ! » አለ የወጣች ወንድ ድምፅ::

«ደ'ሞ አንተ ማነህ?»

«ልጃቸው ነኝ!»

ጥሪው ቀጠለ...

«አቶ ክበደ ማሞ»

ምላሽ የለም:: ቀሪ::

«ፊታውራሪ የሽዋሉል ግርማቸው»

ምላሽ የለም:: ቀሪ::

«እሙት ጌጤ እሸቴ»

«ታመዋል!» የሚል ድምፅ ተሰማ::

«ኰሎኔል ድንበሩ ጣሰው»

«ልጃቸውን የሚድሩት ዛሬ ስለሆነ ፈቃድ ጠይቀዋል» አለ አንድ ጐልማሳ::

«አቶ ተሰማ ታደሰ»

ምላሽ የለም። ቀሬ። የእድሩ ስም ጠሪ ግምባራቸውን በመሀረም እያበሱ ቀና አሉ።

«ስሙኝ ቀባሪዎች! ቀሪ በዝቶአል። እንዴት ነው ነገሩ? አዲስ ድንኳዋን ገዝተን የምረቃ ግብዣ የተባለ ለታ ግን እድርተኛው ግልብጥ ብሎ ነበር የመጣው። ልብ በሉ ያሉን አባላት 315 ናቸው። ያን እለት ግን 327 ሰው ነው የተገኘው። 12 ትርፍ ሰው ነበር። መቼም የቀበርናቸው አባላቶቻችን ሰው ወክለዋል አይባል? ቀብር ሲባል ግን ቀሪ ይበዛል? ይሄ ደግ ነው? ነግ በኔ ነው ቀባሪዎች። ዛሬ ያላቃበርነው ነገ አይቀብረንም። ከነተረቱም 'ቀባሪ አታሳጣኝ' ይባላል ...»

ምክርና ተግሳፁን እንዳበቁ ጥሪውን ቀጠሉ...

«አቶ ሀይለሥላሴ ተካ»

«አቤት»

«ወይዘሮ ኪሮስ ገብሬይ»

«አለሁ!»

«ወይዘሮ አረጋሽ አባተ»

ምላሽ የለም። ቀሬ።

«አቶ ኩራባቸው ታዬ»

«አቤት!»

«መምህር ገረመው ደበላ»

«አቤት!»

«ወይዘሮ የወርቅ ውሀ ታደሰ!»

ምላሽ የለም። የእድሩ ስም ጠሪ ግራ የተጋቡ መሰሉ። በድጋሚ «ወይዘሮ የወርቅ ውሀ! "ሲሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጠሩ። አሁንም ምላሽ አጡ።

«እኒህ ሴት እንኳዋ ከቀብር ቀርተው አያውቁም ነበር። ዛሬ ምን ነካቸው ልጄ?» ብለው አጉተመተሙና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለሶስተኛ ጊዜ ተጣሩ...


« ወይዘሮ የወርቅ ውሀ ታደሰ! ተወካይም ከሌለ ቀሪ ማድረጌ ነው እንግዲህ። ደጋግሜ አልጣራም ብያለሁ! ተናግሬያለሁ። ወይዘሮ የወርቅ ውሀ ታደሰ...»

በዚህ ጊዜ አጠገባቸው ቆሞ የነበረ አንድ ጐልማሳ ሰው ወደ ጆሮአቸው ጠጋ ብሎ አንሾካሾከላቸው።

«ይገለሉት ባሻ። ዛሬ የቀበርነው እኮ ወይዘሮ የወርቅ ውሀን ነው። ማን እንደሞተም አላወቁ ኖሮአል?»



# ደኖች ይጠበቁ



# መቼ ይሆን?

ደምሴ ጽጌ

ለኑሯችን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው ያንድን ነገር ህልውና የምንቀበለው::

ባጋጣሚ ሊሆን የማይችል ነገር ነበር ያጋጠመኝ- ገዋኔ አካባቢ አፋሮች መንደር:: አፋሮች ዘላኖች ናቸው:: አርሰው ሳይሆን ፍየል፣ ከብትና ግመል አርብተው የነሱን ወተት ጠጥተው የሚኖሩ፣ አለባበሳቸው፣ ጎጆ አሰራራቸው፣ አመጋገባቸው፣ ሃይማኖታቸውና አስተሳሰባቸው፣ ባጠቃላይ

አኗኗራቸው አንድ አይነት የሆነ:: መልካቸው ብቻ ነው መለያቸው:: ይሄ እንግዲህ የዘላን ሁሉ መለያ መሆኑ ነው::

ልጅቷ ግን ባጋጣሚ የተለየች ሆና ተወልዳ ኖሯል:: ወይም ከተወለደች በኋላ ልዩ የመሆን መንፈስ ተጠናውቷት:: ከሰዎቿ መሀል ወጥታ በመጀመሪያ ልብሷን፣ ቀይታ አመጋገቧን፣ ቀይታ ሃይማኖቷን፣ ከዚያም አስተሳሰቧን፣ ከርማ ደግሞ የጐሳውን ደንቦች በመጣስ ገዋኔ ብቅ እያለች ሌላ አይነት ኑሮ መምራት ትጀምራለች:: በመጀመሪያ ቤተሰብ ይገስጻል፤ አሻፈረኝ ትላለች:: ጓደኞቿ ይመክሯታል፤ አያገባችሁም ትላለች:: ሽማግሌ ይለክባታል፤ ወይ ፍንክች:: በአፋሮች ደንብ የጐሳው መሪዎች ይሰበሰቡና ውሳኔ ይጥሉባታል::

«ልብሳችንን ናቀች?»

«አዎ!»

«ምግባችንን ናቀች?»

«አዎ!»

«ሃይማኖታችንን ደፈረች?»

«አዎ!»

«ደንባችንን ጣሰች?»

«አዎ!»

«ስለዚህ እሷ የኛ አይደለችም፤ አፋር አይደለችም:: ከኛ ጋራ አትኖርም» ብለው ይወስኑባታል::

ብያኔአቸውን ጥሳ እዚያው እመንደሯ ትኖራለች::

ሸማግሌዎቹ ቆይተው ይሰበሰባሉ:: ሌላ ውሳኔ ይሰጣሉ:: የሞት ፍርድ ይፈረድባታል:: በዚህ የጉሳው ህልውና ይጠበቃል:: የማያስፈለገው ይወገዳል::

* * *

ሀመሮች መሀል ተገኝቼ ነበር- አንድ ወቅት:: ያንዱ አባወራ እንግዳ ሆኜ እቤቱ ገባሁ:: ተጨነቀ፣ ተጠበበ:: እኔን የሚያህል እንግዳ በምን ያስተናግድ? ሀብታም ነው:: በመቶ የሚቆጠሩ ፍየሎችና ከብቶች አሉት:: ግን አንዷን ፍየል ለእንግዳው ለማረድ እንኳን ብቻውን መወሰን አይችልም:: ስለዚህ እቤቱ አስቀምጦኝ ያገር ሽማግሌ ፍለጋ ወጣ:: ጠራቸው:: ተሰበሰቡ፤ ተወያዩ፤ የጉዳዩን ክባድነት ስለተገነዘቡም አንድ ፍየል አርዶ እንዲያስተናግደኝ ፈቀዱለት...

'በራሱ ፍየል?' ትሉ ይሆናል- ይህንን ስትሰሙ:: አዎ በራሱ ፍየል ማዘዝ አይችልም:: በዘላኖች ዘንድ የግልና የወል በውል ተለይተው የሚታወቁበት መስመር ግልጽ አይደለም:: እያንዳንዱ ለራሱም ለሁሉም ነው እሚኖር:: እኔነትና የኔነት በነሱ ዘንድ የሉም:: አያስፈልጉማ!

የዴሞክራሲ አባቶች የሆኑት ግሪኮች ያደረጉትን ደግሞ ላጫውታችሁ:: ሶቅራጥስ የሚባል ታላቅ ፈላስፋና መምህር ነበራቸው:: ግሪኮች በወቅቱ ጌታና ባሪያ ሆነው ነበር የሚኖሩት:: ዴሞክራሲ ለጌቶች ብቻ ነበር:: እንዳሁኑ የመጻፍና የመናገር መብት ነበራቸው::

ሶቅራጥስ እንደልቡ ሲናገር ሲያስተምር ሲጠይቅ የግሪኮችን ኑሮ ሁሉ ጥያቄ ውስጥ አስገባው:: ወጣቶችንም ተጠራጣሪዎች አደረጋቸው:: «አይናችሁን እንጂ ጆሯችሁን አትመኑ» አላቸው:: በዚህም የአቴናን ኑሮ አናጋው::

አዋቂዎች ተሰበሰቡ:: ሶቅራጥስንም ከሰሱት:: 'ወጣቶቻችንን አበላሸ፤ እምነታችንን አናጋ' አሉ:: አሰሩት፤ ለፍርድ አቀርበው የሞት ፍርድ በየኑበት:: መርዝ በጥብጠው ሰጡት:: ጠጥቶት ሞተ:: አላስፈለገማ!

የግሪኮቹ እንዲያ ነበር፤ የአሁኑ ዘመን ዴሞክራሲስ?

«እንደ እኛ አይበላም?»

«አዎ»

«እንደኛ አይለብስም?»

«አዎ»

«እንደኛ አይኖርም?»

«አዎ»

«የራሱ ጉዳይ! እንዳሻው ይኑራ!» ማለትን ይጠይቃል:: እንዳሻው እንዲኖር መፍቀድን የግድ ይላል:: ያኔ ብቻ ነው ዴሞክራሲን ለማጣጣም የምንበቃው::




# አሲዳም ዘመን

ቶማስ አርጋው

ዶሮ ማነቂያ ብቅ ካላችሁ አንድ ረዥም ዘመን ያስቆጠረ የጥንት አዳራሽ ታገኛላችሁ:: ጠጅ ቤት ነው:: የሸበተ:: ማሊዮን ጠጪ ደንበኞቹን ሲያስተናግድ አራት መንግስት ያየ::

እዚህ ጠጅ ቤት ውስጥ ለምን የተሸራረፉና የተገማመሱ፣ የተጣመመሙና የተላላጡ ሰዎች እንደሚበዙ ይገርመኛል:: የአንዳንዶቹ መዘዝ እዚያው ቤት የተፈጠረ ነው:: በጣም አጭር የሚባሉ ሰዎች በአስቂኝ ቁመናቸው ፍንጥር ፍንጥር

ሲሉ የሚታዩት በአብዛኛው ጠጅ ቤት ነው:: ዓይነ ሸውራራ፣ ራሰ ሞላላም የሚበዛው ጠጅ ቤት ነው:: በፕላስተር የተለጣጠፈ ፊት፣ በዱላ የተበደሰ አናት፣ በብዛት ለማየት ዕድሉ ያለው ጠጅ ቤት ነው:: ብቻውን የሚያወራ፣ ሳያውቁት የሚገላምጥ ሞልቷል::

ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ምርምር፣ ቅኔም ሆነ ሙዚቃ በጭንቅላታቸው ቆመው እግራቸው እየተፈራገጠ ፍዳቸውን የሚያዩት ጠጅ ቤት ነው:: ጠብ አጫሪ ተንኮለኛ፣ አስታራቂ ሰላምተኛም እዚህ አሉ::

መምሬ ምንተስኖት ግን የተለዩ ናቸው:: ጠላትም ወዳጅም የላቸውም:: የሚያወሩት ብቻቸውን ስለሆነ ምን ያረግላቸዋል? ቁመተ ዶሮ ናቸው:: እና ዘወትር ተሲያት ላይ ፀብ ይጀምራሉ- ከዘመን ጋር:: ዘመኑን ያዋርዱታል:: እስከ አፍንጫው ያስታጥቁታል:: ጭራቸውን እያወዛወዙ ... ጠጃቸውን እየኮመኮሙ ... እንዲህ ይሉታል::

«እህል በቆርኪ የሚሸጥበት አሲዳም ዘመን፣ መቅኖቢስ የጊዜ አመዳም፣ ቢበሉ አይጠገብ፣ ቢጠጡ አያረካ:: እንዲያው እኔስ ከሁሉ የሚገርመኝ በፊት በፊት ጠዋት የበላሁት ቁርስ ከሆዴ ተከምሮ ምሳና እራት ትዝ የማይለኝ እርቦኝ ሳይሆን ሰው ሲበላ ስመለከት ነበር:: ዛሬ ሁለት እንጀራ ጠዋት ብበላ አራት ሰዓት ሳይሞላ ረሃብ በሰላ ምላሱ ሲልሰኝ አገኘዋለሁ:: እህል ከሆድ የሚነጥቅ ሰላቢ ጊዜ::

«... ድሮ ጠጅ ቤት ገብተን ትግላችን ከንብ ጋር ነበር:: የማሩ ሰፈፍ እንደ ዳቦ ሲገመስ፣ በሽልንግ አራት ብርሌ እስኪያገሳን ጠጥተን ቆረጠኝ የለ ፈለጠኝ፣ ሆዴን የለ እራሴን:: የዛሬ ጠጅ እንደ ጉንዳን የሚሮጠው አናት

ላይ ነው። ዛሬ ቁና ሙሉ ስኳር ታንሮበት ንብ ዘሩ ጠፍቶ፣ ዝንብ እያፏጨብን፣ በሶስት ብር አንዲት ጠርሙስ ጠጅ እንደ መድኃኒት የምንቀምስበት ጊዜ ሲመጣ ምን ታደርገዋለህ? ቢራና ድራፍትንማ እቁብ የበላህ ቀን ካልሆነ የት ትደርስባቸዋለህ?

«... ያለቀለት ጊዜ መሆኑ የማታውቀውክ ሌላው ቀርቶ እንቁላሉ ሲጠበስ መች ብጫ ይሆናል? ልብ ብለው ሲያዩትክ ወተቱም ቢሆን ንጣቱ የድሮው አይደለም። ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው ነው ወይስ ማጭድ ለባሰው ሆድ አታውሰው? በዚያ ላይ ደግሞ ክረምቱ ክረምት አይመስል፤ በጋውም ለዛቢስ። አንዳንዴ ቆመው ሲያስተውሉትክ ውሃውም መልክና ጣዕሙ ከድሮው ተለውጧል። አሁን በሞቴ የአዲሳባ ውሃ ጣዕሙ እንዲህ ነበር?

«... ይሁና ምን ይደረግ! የአስር ሳንቲም አረንቻታ ሁለት ብር ሲገባ፣ የውሃ ጣሙ ቢቀየር ምን ይደንቃል? የተሟጠጠ ገፊ ጊዜ መሆኑ የማታውቀው ህፃናቱ ትናንት ተወልደው በማግስቱ ገርጅፈው ይሸብታሉ፤ ሸንት ቤቱ ዛሬ ቆፍረውት ነገ ይሞላል፣ ቅቤው ሲያነጥሩት ሽታ የለው፤ ቢበሉት አይጥም፣ ቢያስቀምጡት ውሎ አያድር።

«... ሃምሳ ኪሎ ዱቄት ዛሬ ተቦክቶና ተጋግሮ ለነገ ምሳ አይገኝ። ማዕድ የቀለለበት፣ ገበታ መቅኖ ያጣበት ጊዜ! ኧረ ሌላው ቀርቶ ልብ ብለው ሲያዩት አስከሬኑ ለሸክም ሲቀል! ድሮ ቢሆን አንድ አስከሬን በአስር፣ አስራ አምስት ሰው ሸክም ከመሬት አይነሳም ነበር። ዛሬ ያየኸው እንደሆን ሁለት ሰው እንደ ዘንቢል አንጠልጥሎት ነው የሚበረው።

«... ቆመንም ሞተንም ቀትረ ቀላል የሚያደርግ ጊዜ! አይ ጊዜ! ዶሮ እንኳን እራሱዋ ምን ጊዜ እንቁላል ጥላ ምን

ጊዜ እንደምትፈለፍል አይታወቅም፤ የተንቀገዠቀገና አደቡን ያጣ ጊዜ፤ ተዋክቦ የሚያዋክብ ዘመን::

«... ድሮ ቢሆን ዶሮ ወግ ማዕረጉን ተከትላ በቀን አንድ እንቁላል ለመጣል አምጣና አቃስታ፣ እየዞረች ኡኡ! ብላና አሽካክታ ነበር:: እንደ ሰው አራስ ነበር ልጆችዋንም አቅፋ የምታሳድግ:: ዛሬ ያየህ እንደሆን እየሄደች እንቁላሉን ሲሚንቶ ላይ ታፈርጠዋለች:: እርጉም ጊዜ!!

«... ምስጢር በልባችን ውሎ አያድር! ወሸከሬና ፈሽፋሻ የሚያደርግ ጊዜ:: ሰው ቢለብስ አያምርበት:: ለዚያውም ለውርስ የሚበቃ ገንዘብ አውጥቶ፤ ቢበላ አይወዛ፤ የግራው ቀኝ የቀኙ ግራ! ... ኧረ ጉድኮ ነው!! ልብ ብለው ካዳመጡትኮ የመኪናውም ድምፅና ጩኸት ከድሮው ተለውጧል:: በፊት በፊት እርም! እርም! ... እያለ ምድር የሚያንቀጠቅጥ «ዚተዋ» ነበር ግርማ ሞገስ ባለው ሾፌር ሲያጓራና ሲያስገመግምብን የሚውለው:: አሁን አሁን ቀትረ ቀላል፣ ሾካካ ሾፌሮች እንደ አይጥ ከውስጥ ያደፍጡና እንደ እባብ እግርህ ስር ሲደርሱ አልያም ሲጐሽሙህ ካልሆነ በቀር ዱካቸው አይሰማ:: ሾካካ ጊዜ!


«... ደግሞ ፍጥነቱ! ሰኞ ብሎ እርብ ነው! መስከረም ብሎ ታህሳስ ነው፤ መሽ ሲባል ነግቶ ይገኛል፤ ጨረቃዋ ደብዛዛ! ፀሐዩዋ ፈዛዛ፤ መስከረም ጠብቶ አበባ የማይታይበት፤ የልጆቹ ጭፈራ ለዛ የሌለው፤ ወንዱ አበባየሆይ፣ ሴትዋ ሆያሆዬ የሚጨፍሩበት አቅል ያጣ የተገላቢጦሽ ዘመን!»

መምሬ ምንተስኖት ጠጅ ቤቱን የሚሰናበቱት ሲመሽ ነው:: እያጉተመተሙና ዘመንን እየወቀሱ ከጠጅ ቤቱ ብዙም ወደማትርቅ ዛኒጋባቸው ይደርሳሉ:: ባለቤታቸው


እንደርሳቸው አጭር ናቸው:: ልጆች የላቸውም - መሆን ናቸው:: እና ታዲያ ባለቤታቸውም ራት ለማብሰል እሳት እያነደዱ እንዲህ ሲሉ ይሰሙዋቸዋል ...

«የዘንድሮ እሳት ምን መላ አለው? ድሮ ቢሆን አንዴ ካነደዱት እንኳን ድንች ብረት ያቀልጥ ነበር:: የዘንድሮ ነገር! የዛሬ ዘመን ነገር! ድንች ልገዛ ወጣ ብል እንቅፋት አገኘኝ:: የዘንድሮ እንቅፋት እንደ እግር ካገኘ ገሸልጦ ነው የሚጥለው:: ድንጋዩ የሰላ፤ ሚስማሩ የሾለበት ዘመን፤ የዘንድሮ ጨውም ድንጋይ ሆኖአል:: የብር ጨው ለአንድ ድስት ወጥ አይበቃ:: ድሮ ቢሆን የብር ጨው የምንገዛው ለሰርግ አለያም ለተዝካርና ላሰንበቴ ነበር!»

ጊዜ ግን መልስ አይሰጥም:: ዝምታውን ቀጥሎአል ... ሞናልባት የሰዎች 'ሰበብ' ለጊዜ የመዝናኛ ቀልድ ይሆን?



# ተገላቢጦሽ



# ሞገደኛው ጋዜጠኛ

## እሸቱ ተፈራ

በህይወት ስንኖር ጥላና ዱካ ያለንን ያህል፣ ይህችን ዓለም ስንለቅ ደግሞ መጥፎም ይሁን በጐ ትዝታችንን ለሰዎች ጥለን እናልፋለን፡፡ ያለፉ ሰዎችም በተግባራቸው ሲወቀሱ አሊያም ሲሞገሱ ይኖራሉ፡፡

ብቻ ማንም ቢሆን «ባለመታደል» ለሀገሩ ህዝብ ለፊ ትዝታ ወይም ውለታ ትቶ ማለፍ ቢያቅተውም ለኖረበት አካባቢ፣ ለተማረበት ትምህርት ቤት፣ ያም ባይሆን

ስጕረቤቶቹና ለወዳጆቹ ጥሎት የሚያልፈው ነገር አያጣም። የጠፋ ቢጠፋ በአለባበሱ፣ በአረማመዱ፣ በአሳሳቁም ሆነ በአስቃቀሱ «ወይ ጉድ! ቁርጥ እንሴን!» እየተባለ ይታወሳል። በዚህ መነሻ መንግስቱ ገዳሙ ስለሚባለው ሞገደኛ ጋዜጠኛ ጥቂት እናውጋችሁ። መንግስቱ አሁን በሕይወት የለም። አስቂኝና አስገራሚ ገጠመኞቹን ትቶ ያለፈው በሀምሌ ወር ነበር-1968።

መንግሥቱ ገዳሙ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ተወልዶ ጥጃ ሲጠብቅ ያደገ የባላገር ልጅ ነው። በልጅነቱ አባብ ነድፎት ለስድስት ሳምንታት ሕሊናውን ስቶ ከሰነበተ በኋላ ከሞት መትረፉ ይነገራል። ዕድሜው ከፍ ሲልም ወታደርነት ተቀጠረ። በውትድርናው ግን አልገፋበትም።

ከወታደርነቱ ዓለም ወጥቶ ፖስታ፣ ቴሌፎንና ቴሌግራፍ ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጠረ። በስራው ጕበዝ ስለነበርም በዕድገት ወደ ድሬዳዋ ተዛወረ።

ደሞዙ ግን አጥጋቢ አልነበረም። ስለሆነም ስራውን ለቅቆ በእጥፍ ደሞዝ ምድር ባቡር ኩባንያ ይቀጠራል። ፖስታና ቴሌግራፍ ሚኒስቴር ይህን ሲሰማ ወደ ጥንት ስራው በግዳጅ ይመልሰዋል። ሞገደኛው መንግስቱ ግን ለአለቆቹ ውሳኔ የሚመች አልሆነም። 'አለቃም ይሁን ምንዝር በእጁ ከመጥፋቱ በፊት በሰላም አሰናበቱኝ' ብሎ ያስፈራራል ገባ። ሆኖም ይህ ፋከራ ሳያዋጠው ቀረ። ሌላ መላ ደሞ ዘየደ። 'ራሴን እገድላለሁ' ብሎ ማስፈራራት። እንዳጋጣሚ ይህ መላ ያዘለት። መስሪያ ቤቱ «ራስህን ከምትገድል እንለቅሃለን» ብሎ አሰናበተው። ባቡር ኩባንያ ሄዶ ስራውን ይጀምራል። ጥቂት እንደሰራም የኩባንያው ስራ አስኪያጅ እብሪት አስመረረኝ በማለት ስራውን በፈቃዱ ይተዋል። ሰነባብቶም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደህና ደሞዝ

ይተጠራል። ማዕረጉ የመዝገብ ቤት ሹም ነበር። ጥቂት ስርተም ወደትርጉም ክፍል ተዛወረ። ከዚያም ወደ አስተዳደር አካባቢ ስልጣን ብጤ ያገኛል። ሁለት ጊዜ ደህና የደሞዝ ጭማሪ አግኝቷል። ያገኘበት መንገድ ግን ለየት ያለ ነው። ሁለቱም ጭማሪዎች የተገኙት በሕንዳዊው ስራአስኪያጅ ላይ ሸጉጥ በመደገን ነበር። ሶስተኛውን ጭማሪ ናስማስር በመደገን ለማግኘት በመዘጋጀት ላይ እያለ በመካከሉ ሌላ ጉዳይ ተፈጠረ።

ባህል አስከብራለሁ በሚል ምክንያት በርኖስ እየለበሰ ቢሮ መግባት ጀመረ። በዚህም ተከስሶ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በስንት እግዚኦታ በርኖሱን አወለቀ። አያይዞ ግን ባንኩን በጋዜጣ ሙልጭ አድርጎ ተሳደበ። ይባስ ብሎ ንጉሱ የባንኩን አገልግሎት ሊጎበኙ ሲመጡ ተጣጣፊ አልጋ በድብቅ አስገብቶ ክፍሉ ሲጎበኝ ለጥ ብሎ ተኝቶ ተገኘ። ለምን ቢሮ ውስጥ እንደተኛ ቢጠየቅ «አለቆቼ ስራ ስለማይሰጡኝ የምሰራው ስራ ሳይኖር በከንቱ ደሞዝ እንደሚከፈለኝ ለማሳወቅ ነው» ብሎ አረፈ። በዚህ አድራጎቱ አለቆቹ ተበሳጩ። በማግስቱ የስንብት ደብዳቤ በፖሊስ እጅ ደረሰው። ፍርድ ቤት ከሰሰ። መስሪያ ቤቱን ተከራክሮ ረታ፣ ግን ጉዳዩን ተከታትሎ ሳያስፈጽም ማስታወቂያ ሚኒስቴር በጋዜጠኝነት ረቀጠረ።

በጋዜጣ የጀመረው ጽሑፍ ወደደራሲነት አሳደገው። ብዙ የቤሳ መጻሕፍት ደርሶአል።

መንግስቱ ገዳሙ የማተሚያ ቤት ዕዳ መክፈል አቅቶት ሲሰቃይ ከማተሚያ ቤቱ ዕዳ በላይ ሊሸጡ የሚችሉ መጻሕፍቱን ለየድርጅቱ በነፃ ያድል ነበር። ለመጻሕፍት አዟሪዎችም በዱቤ ወይም በነፃ ይሰጣል። የጻፋቸውን መጻሕፍት ይዘት ግን ባብዛኛው አያስታውስም። የመፃህፍቱ ቅጅዎችም ኖረውት አያውቅም።

መንግስቱ ገዳሙ አራት ጊዜ አግብቷል:: አራት ጊዜ ፈትቷል:: ትዳርን ለምርምር የሚጠቀምበት ይመስላል:: የመጀመሪያ ሚስቱ እዚህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ፤ ሁለተኛዩቱ ደህና መተዳደሪያ ያላት ባለሙያ፤ ሶስተኛዩቱ የፈደልን ዓይን ያላየች የከተማ ማይም፣ አራተኛዩቱ ከአቡጊዳ በፊት «ግራን ፕራይመር» ያወቀች፤ በእውቀት የመጠቀች፤ በእንግሊዝኛ መሳቅና ማልቀስ የሚቃጣት ዘመናይ ነበረች:: መንግስቱ ገዳሙ ድንቅ ቤተመ ጻሕፍትም ነበረው:: ለአንድ ዓመት ስራ ሲፈታ ግን መጻሕፍቱን በሙሉ ቸበቸባቸው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመጽሐፍ ደሃ ሆነ::

ሌላው የመንግስቱ ጠባይ አምባጓሮ መውደዱ ነበር:: በዚህም የተነሳ ከመቶ ጊዜ በላይ ተቧቅሷል:: አራት ጊዜ በጩቤ ተወግቷል:: አራት ጊዜ በመኪና ተገጭቷል:: ሃያ ጊዜ በወረበሎች ማጅራቱን ተመትቷል:: እንዲያውም አንድ ጊዜ ሕሊናውን እስኪስት ድረስ ማጅራት መቺዎች ጉዳት አድርሰውበታል:: በቆሻሻ ክምር ላይም አንድ ሙሉ ሌሊት አሳልፏል::

የመንግስቱ ገዳሙ ሕይወት በሙሉ ውጣውረድ የበዛበት ነበር:: የሚሰራቸው ነገሮች አብዛኛዎቹ የሚያስቁም የሚያስደምሙም ነበሩ:: አንድ ጊዜ አንድ ምስኪን ፈረንጅ በ700 ብር ደሞዝ ቀጥሮ ካፖርት እያሸከመ በፒያሳ ይዞር ነበር:: ይህም «ፈረንጅ የአበሻ አሽከር አይሆንም» የሚለውን አመለካከት ለማፍረስ ነው:: በአንድ ወቅት አራት ኪሎ አካባቢ ተወዳጅ ዊስኪ ቤት ነበር አሉ:: ታዲያ የዊስኪ ወዳጆች ቤቱን ካፍ እስከገደፉ እየሞሉት መቀመጫ አይገኝም ነበር:: አንድ ቀን መንግስቱ ከውጭ ጋዜጠኛ ጋር ዊስኪ ለመቀምቀም ወደቡና ቤቱ ቢሄድ እንኳን መቀመጫ መቆሚያም ይጠፋል:: በዚህ ጊዜ አንድ ሐሳብ ይገለጥለታል:: በሩላይ ቆሞ ድንገት አጨበጨበ:: ጠጪው ሁሉ ፀጥ ሲል በወቅቱ የነበሩትን ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድን፣ የፖሊስ ሠራዊት

ጠቅላይ አዛዥ ጀኔራል ይልማ ሽሪቢ'ን፣ የዐጥታ ሹሙን ኮሎኔል ሰለሞን ከድርን የመንግስት ሹሞች መሳደብ ይጀምራል:: ምድረ ጠጪ ያሳፍሰናል በሚል ስጋት ሂሳቡን በቁሙ እየከፈለ ቤቱን ጥሎ ይወጣል:: ቤቱ ጭር ሲል መንግስቱ ከጓደኛው ጋር ምቹ ሶፋ ላይ ተቀምጦ ጨርቅ እስኪሆን ድረስ ዊስኪውን ይቀመቅም ገባ:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ኢሲታሲያ ሮምን እንዲጎበኝ ይጋብዘዋል:: መንግስቱ ቲኬቱንና ፓስፖርቱን እጁ ካስገባና ቪዛውን በምስጢር ካስመታ በኋላ በማግስቱ ለመብረር ሲዘጋጅ በዋዜማው ለማጠለት አለቃው ከሳምንት በኋላ ወደአውሮፓ ለመሄድ ዕድል የገጠመው መሆኑን ገልጦ ያለቃው መልክም ፈቃድና ቡራኬ ካልተሰጠው ሰማይ እንደሚደፋበት አድርጎ አንጀት የሚበላ ደብዳቤ ይጽፋል:: አለቅየውም በጃቸው በመውደቁ ተደስተው «ከማሕደሩ ጋር ተያይዞ ይቀመጥ» የሚል ትእዛዝ ጽፈው ማመልከቻውን ወደመዝገብ ቤት ይሰዱታል:: መንግስቱ እንደተጫወተባቸው አለቃው የነቁት ጧት ለስራ ሲፈልጉት በአንድ ሰዓት ወደ ሮም መብረሩ ሲነገራቸው ነበር::

## የመንግስቱ ገዳሙ ታሪክ ምን ተወርቶ ያልቃል?


አንድ ጊዜ በመስሪያ ቤቱ ግብዣ ላይ የአለቃው አለቃ ባለመገኘታቸው ይወርፋቸዋል:: «ክብረ ነክ» ተብሎ በማግስቱ ኮሚቴ ተቋቁሞ ለፍርድ ይቀርባል:: ጥፋት የፈፀምክበትን ምክንያት አብራራ ተባለ:: ምላሹ 'ሰዎች ገፋፍተውኝ ነው' የሚል ነበር:: እነማን እንደሆኑ ሲጠየቅ ለፍርድ የተሰየሙትን አባላት ስም ይደረድራል:: በዚህ የተነሳ የኮሚቴው አባላት ዳኝነቱን ትተው መንግስቱን ለመደብደብ ከጀሉ:: መንግስቱ ገዳሙ ሮጦ ይወጣል:: የተናደዱት የኮሚቴው አባላት ተከትለው ያበርሩት ገቡ:: መንግስቱ የኮሚቴው አባላት ስሜታቸውን መቆጣጠር የማይችሉ

መሆናቸውን ባደባባይ አሳይቷል።

ሌላ ጊዜ ደግሞ አስመራ ለስራ ጉዳይ ይላካል። ታዲያ በየፖሊስ ጣቢያው ስላሉት ማረፊያ ቤቶች ሁኔታ ለመጻፍ ይፈልጋል። ባለስልጣኖቹን ለማስፈቀድ ቢሞክር ግን አሻፈረኝ ይሉታል። ሞገደኛሙ ጋዜጠኛ ምሽት ላይ አንድ መላ ይገለጽለታል። ወንጀል ሰርቶ ፖሊስ ጣቢያ መታሰር። ስለዚህ አንድ መጠጥ ቤት ይገባና ባዶ ጠርሙሶች እየመረጠ ሰብርብራቸውን ያወጣል። ኡኡታው ይቀልጣል። ፖሊስ እያዳፋ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይወስደዋል። ከሶስት ቀን በኋላ በዋስ ተለቅቆ አዲስ አበባ ሲመለስ ስለአስመራ ፖሊስ ጣቢያዎች በርከት ያሉ መጣጥፎች ጽፏል። ፖሊስ ጣቢያዎችን ለመጐብኘት በማሰብ አዲስ አበባ ላይም ተመሳሳይ አምባጓሮ ፈጥሮ ፖሊስ ጣቢያዎችን በእስረኝነት ጐብኝቷቸዋል።

መንግስቱ በራሱም ላይ መቀለድ ይወድ ነበር። አንድ ጊዜ ሳይሞት ሞቻለሁ ብሎ መስሪያ ቤቱ አስደውሎ የቀብሩ ቦታ (ቀጨኔ መድኃኔዓለም) ለቀስተኛ ተሰብስቦ አስከሬን ሲጠብቅ፣ መንግስቱ ባርኔጣውን ደፍቶ፣ ጥቁር ሱፉን ግጥም አድርጐ ብቅ ይላል። ለቀስተኛውን በመካነ መቃብሩ በመሰብሰቡ አመስግኖ ሳይሞት 'ሞቻለሁ' ያለው በእውነት ቢሞት የቀብሩ ስነስርዓት ምን እንደሚመስል በቁሙ ለማየት ፈልጐ ያደረገው መሆኑን ገልጾ ኀዘንተኛውን ይበትናል።

ስለመንግስቱ ገዳሙ ባሕርይ ብዙ ነገር ለመጻፍ ይቻላል። እንዳይሰለች ግን በዚሁ እንግታው። በአጭሩ የመንግስቱ ገዳሙ ሰብዕና ፈረንጆቹ «ዲቪየንት» አፈንጋጭ የሚሉት ዓይነት ነበር። እኛ ደግሞ ሞገደኛው ጋዜጠኛ ብለነዋል።



# ኬጂቢ በአዲስ አበባ

ሄኖክ ያሬድ

በጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ተከፍቶ በጀኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን በተዘጋውና አስራ ሰባት ደመራዎችን ባስለኮሰው የደርግ ዘመን ውስጥ ገና ያልወጡና ያልታዩ በርካታ የታሪክ ጉዶች አሉ። በተለይ ወታደራዊውን ደርግ 14 ዓመት ሙሉ ያሽከረክር የነበረው መንግስቱ ኃይለማርያም አገሪቱን ከየት አንስቶ የት እንዳደረሳት ማውጋቱ እንዲህ በቀላሉ እሚደፈር ባይሆንም ሌላውን ለጊዜው ትቶ በእጅ የገባውን እያወጉ መቀጠሉ ይመረጣል።

«ፍራንክፈርት አልጋማይኔህ» በተሰኘው አንድ

የጀርመን አሉታዊ ጋዜጣ ላይ ነው ጉዳዩ የተዘከዘከው:: ቅሌቱን ይፋ ያደረጉት ደሞ የምዕራብ ጀርመን ኮሚኒስት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት የሐምበርጉ ሚስተር ፒተር ሹልትዝ ናቸው:: «የ10ኛው የአብዮት በዓል ትዝታ» በሚል ርዕስ የእንግድነት ትዝታቸውን ያሰፈሩት ሚስተር ሹል ትዝ ከ1968-89 ለሀያ አንድ ዓመታት በምዕራብ ጀርመን ኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ ወሳኝ ቦታ የነበራቸው ናቸው:: በዚህም የተነሳ ለፓርቲው ምስረታና ለ10ኛው የአብዮት በዓል አዳማቂነት የተጋበዙ እንግዳ ሆነዋል:: እና ያኔ ነው ያን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የተዋረዱበትን ብሔራዊ ቅሌት ያዩት::

ዘመኑ 1976 ነው:: በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አስከፊው ድርቅና ረሀብ የተከሰተበት ወቅት:: ዓለም ተጨንቆ ተጠቦ ርዳታ ለማድረግ የተንሳሳበት፤ ግብረሰናይ ድርጅቶች ፍጡነ ረድኤት ለማድረግ የተረባረበበት ወቅት :: በአንፃሩ ደሞ አዲሳባ ተሞሽራ ሙሽሮቹን ደርጋውያን ከኢሰፓአኮ ወደ ኢሰፓዊ ቅብዓት ለመለወጥ ሽርጉድ ያለችበት፤ የኢትዮጵያ ከተሞች መኖሪያና የንግድ ተቋማት በአረንጓዴ ብጫ ቀይ ባንዲራ፤ አምፑሎች፤ ፍሎረሰንቶች የተሸቀረቀሩበት፤ ሕንፃዎች ለኢሰፓው ምስረታ ድምቀት በሚሊዮኖች በሚቆጠር ወጪ የታደሱበት ጊዜ ነው:: በባንዲራ ሽያጭም ቀበሌና ነጋዴ ፉክክር የያዙበት:: ቀበሌ በአምስት ብር ሂሳብ ሲቸብችብ ነጋዴም በሁለትና ሶስት ብር አርክሶ ሲሸጥ፤ ክብረ- ባንዲራ የቀለለበት ጊዜ ነበር:: ያ ዘመን ድርቅ እንደሌለ፤ ረሀብ እንዳልሰፈነ ያስተነትን የነበረው «ግንድ አልባሹ» ደርግ ኢሰፓአኮ ለ10ኛው አብዮትና ፓርቲ ምስረታ ጉባኤ አዳራሽ ሲሰራ፤ ጣኦታውያኑን ሐውልት ሲገነባ ለመስተንግዶውም ውስኪ ከአውሮፓ ሲያስገባ የተስተዋለበት ነው::

በ13ኛው ወር በጷጉሜን፤ ኢሰፓአኮን ወደ ኢሰፓ

የሰጠጠው ጉባኤ ከአገር ቤት ተካፋዮች ሌላ ከዓለም ዙሪያ ግብዣ የተደረገላቸው፤ ከምስራቁ ሶሻሊስታዊ ባለጠበሎች እስከ ሶስተኛው ዓለም ግልገሎች፤ ከምዕራብም አናቃሬ ኮሚኒስቶች የተገኙበት ሲሆን፤ የኮሚኒስቱን ዓለም ልዩ አሚያደርገው ከአክራሪዎቹ እስከ ለዘብተኞቹ፣ የተገኙበትና ባንድ መድረክ የተሰባሰቡበት መሆኑ ነው።

የዚህን መድረክ ጉድ የሚገልፀው የሚስተር ሹልትዝ ጽሁፍ የብዙ ኢትዮያውያንን ቀልብ ስቦ እንደነበር የበርሊኑ ጋዜጠኛ ይልማ ሀ/ሚካኤል ጀርመናዊውን መሰረት አድርጐ አንድ ዘገባ አቅርቦ ነበር። በዚህ ዘገባውም ላይ ሚስተር ሹልትዝ በሙያቸው ደራሲ፤ በፖለቲካ አመለካከታቸው ደሞ ኮሚኒስት መሆናቸውን ገልጿል። ይሁን እንጂ የሚስተር ሹልትዝ ኮሚኒስትነት በኮሚኒስትነት ሽፋን እሚካሄደውን ታሪካዊ ቅሌት ከመፃፍ አላገዳቸውም። በዚህ መሰረት ገጠመኞቻቸውን እንዲህ አስፍረዋል።

የሜዲትራንያንን ባህር አቋርጦ፣ የአባይን ወንዝ ተከትሎ፣ አዲስ አበባ ዓለማቀፍ ቦሌ አየር ጣቢያ ያረፈው አውሮፕላን የተነሳው፣ ከቀድሞዋ ምስራቅ ጀርመን ዋና ከተማ ከበርሊን ነበር። አውሮፕላኑ ከጥቂት ሰዓት ጉዞ በኋላ ያፍሪካን ከርባ እየተጠጋ ሲመጣ አንድ በቀድሞው የምስራቅ ጀርመን ኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ ያለምዓቀፍ ግንኙነት ኃላፊ፣ አውሮፕላኑ ውስጥ እየተዘዋዋረ በጀርመንኛ ቋንቋ የምንናገረውንና በአማርኛና በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ ይበተናል የተባለውን ጽሁፍ እንደሰጠኝ እኔው ራሴ የማነበውን በድርጅቴ አመራር ተቀባይነትና ድጋፍ ያገኘውን የኔን ጽሁፍ ግን ወሰደው። አውሮፕላኑ ውስጥ የታደለው ጽሁፍ በተለየ አቀራረብ የተዘጋጀ ሲሆን፤ የኦስትሪያና ዴንማርክ ፤የኖርዌይና ሉክሰምበርግ፤

የእንግሊዝና ቺሊ ወዘተ. ልዑካኖችም እንደእኔው የማያነቡትን ጽሁፍ እንደተቀበሉ በመጥቀስ የሰጠኝ ወረቀት በኢሰፓ ጉባኤ ላይ እንዳነበው ከበላይ የተወሰነ መሆኑን ገለፀልኝ።

ከበላይ አካል የተላከው ጽሁፍ ይዘቱ 'በመልካም ምኞት መግለጫ ጋጋታ ብዛት የተካተተ መሆኑን ማስተር ሹልትዝ ሲገልጹ 'በደስታ መግለጫ ወረቀት የተነሳ የመጀመሪያው አሰመግባባት የሚያሳየው አዝማሚያ ከጽሁፉ እንደምንረዳው የቀድሞው ምስራቅ ጀርመን መሪ ኤሪክ ሆኔከር ከመጋረጃው ጀርባ ተቀምጠው ሁሉምና እያንዳንዱ የሚንቀሳቀስበትን ስንሰለት በጣቶቻቸው እንደበገና ክር የሚደረድሩ መሆናቸውን ያስረዳናል።' ይላሉ።

* * *

በዚያ የባሬ ዘጠኝ ዓመት የተደገሰው ድግስ በዓይነቱም ሆነ በመጠኑ የመስኮቡን፣ የቲራናውን (አልባኒያ)፣ የፔኪንጉን (ቻይና)፣ የፕዮንግያንጉን (ሰሜን ኮሪያ)፣ ኮሚኒስቶች በማሰባሰብ፤ እርስ በርሳቸው የማይግባቡ መሪዎችን አንድ ላይ፤ ባንድ አዳራሽ ውስጥ ያካተተ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ስብሰባ እንደነበረ የፒተር ጽሁፍ ይገልፃል።

አዲሳባን ለዝክረ ታሪክ ፈጥሯታልና 108 የኮሚኒስት ፓርቲ መሪዎችና ተወካዮች፤ 35 የሶስተኛው ዓለም አገሮች፤ ከነዚህም ውስጥ የኬንያውና የዛምቢያው፣ የታንዛኒያውና የአንጐላው፣ የዚምባቡዌውና የሞዛምቢኩ፣ እንዲሁም የደቡብ የመኑና ዛሬ የት እንደደረሱ የማይታወቁ ፕሬዚዳንቶች በአዲሳባው ሸንጐ ወለል ላይ እንደተውረገረጉ ተስተውሏል።

የጸሐፊውን ጉባኤተኛ ድርሳን የበርሊኑ ጋዜጠኛ ሞገድ አሳብሮ እንዳስደመጠው፣ በጉባኤው ወቅት በውሃ ወለድ

ሀገራቸው የነካው፤ ቁመናቸውና ፈገግታቸው ደስ የሚል፣ በዓይናቸው ሰው የሚያባብሉና የሚማርኩ ወጣት የሞስኮ ቆንጆዎችም በአዲሳባ ነበሩ፡፡ እነዚህም ሞስኮባውያን ቆንጆዎች ታዛዥነታቸው ለዝነኛው የሶቪየት ስለላ ድርጅት ለኬጂቢ ብቻ የሆነ፣ በተለይ የኢትዮጵያና የአፍሪካ፣ እንዲሁም አንዳንድ የታወቁ እንግዳ የፖለቲካ መሪዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ፣ በሆነው መንገድ ተጠግተው ጆሮ እንዲጠቡ ለዚህ ዓለማቀፍ የወንዶች ስብሰባ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኮረዳዎች ተሰማርተው እንደነበር ጀርመናዊ ያስታውሳሉ፡፡

በሰበባ ሰበቡ አለቅጥ እንዲራዘም በተደረገው የኢሰፓ መስራች ጉባኤ (ከጳጉሜ1-5) የራሳቸው የግል ወንበር ይዘው የሞስኮን ልዑካን ቡድን መርተው የመጡት ሚስተር ግሪጎሪ ቫሲሊ የቪች ሮማኖቭ ነበሩ፡፡ ሚስተር ሮማኖቭ በጠና ታመው ይሞታሉ ተብለው የሚጠበቁትን የማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊና የሶቪየት መሪ ቼርኔንኮን ይተካሉ ተብለው ይነገርላቸው የነበሩ ሰው ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደሞ በኰሎኔል መንግስቱ ዓይን «ልዩ ወዳጅ» ተብለው የሚጠሩት የሰሜን ኮሪያ ልዑካን መሪ ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ እኚህ ሰው የሶቪየቱ ሮማኖቭ ስራ ምንም አይጥማቸውም፡፡ በዚያ ጧት ጧት በሚደረገው የጉባኤ አዳራሽ ውሎ ሮማኖቭ እሚያደርጉትን ሁሉ እያዩ ይበሳጫሉ፡፡ በርግጥ ከሰዓት በኋላ እንኳ ፋብሪካዎችን በመዞርና በመጎብኘት ሰራተኛውንም በመጨበጥ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ ያም ሆኖ ይህ ከሮማኖቭ ጋር እሚያጋጫቸው ነገር ዘገየ እንጂ አልቀረላቸውም፡፡

ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

ልዩ ወዳጅ ናቸውና ለመንግስቱ የመክፈቻ ንግግሩን እሳቸው እንዲያደርጉ ይመረጣሉ። እንዲያውም ንግግራቸውን ካሰሙ በኋላ የኪም ኢል ሱንግ ፎቶ ያለበትን ቀይ ባንዲራ ለኮሎኔል መንግስቱ ለመሸለም ፍላጎትና እቅድ ነበራቸው። ይህ ዜና በነሮማኖቭና ኤሪክ ሆኔከር ዘንድ እንደተሰማ ትልቅ ሽብር ተፈጠረ። በሶቭየትና ጀርመን ዓይን ክብረነክ የሆነው ቅንብር እንደተደረሰበት ሁሉም ነቅተው፣ እንዲህ ዓይነቱን የሰሜን ኮርያና የመንግስቱ ኃይለማርያም ደፋርነት ፊዕመው እንደ ማ ይቀበሉና ርምጃውንም ለማጨናገፍ ዱለታ እንደያዙ ደራሲው ሹልትዝ ከሁኔታው ጋር ያስታውቁናል።

የአዲስ አበባው ጉባኤ የኢሰፓ ምስረታ የሚባል ሽፋን ይሰጠው እንጂ ከጧቱ ኦፊሴላዊ ስብሰባ በኋላ ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ እንግዶቹ ለምክክርና ለስራም እያሉ ልዩ ስብሰባዎችን ያካሂዱ ነበር። በዚህም ባንዱ የከሰዓት በኋላ ስብሰባ ላይ ነው የሰሜን ኮሪያ ደፋር እርምጃ እንዲከሽፍ የተወሰነው።

የተደረሰበትም ውሳኔ የመክፈቻውን ንግግር የኮሪያው ተጠሪ እንዳያደርጉ ሲሆን፣ ከእርሳቸው በፊት ግን የአፍሪካ መሪዎች ተራ በተራ በመናገር እንዲቀድሟቸው ነበር። በዚህ ርምጃ ነገሮች ተራዝመው፣ አብዛኛው ከተሰጠው ሰዓት በላይ ተናግሮ ጊዜ በመውሰዱ፣ የሰሜን ኮሪያ ልዑክ ማመሻሻው ላይ የንግግሩ ተራ ደረሳቸው። በዛው የዕለቱ አጀንዳ ተዘግቶ በነጋታው የሞስኮው ባለስልጣን ሚስተር ሮማኖቭ የጧቱን ንግግር ከፈቱ። የኮሪያው ሰው ሁሉም በተስማሙበት ውሳኔ መሰረት ከንግግራቸው በኋላ ሊሸልሙ ይዘውት የመጡትን ቀይ ባንዲራ ቦርሳቸው ውስጥ ሲያስቀሩ፣ የሞስኮ ልዑካን መሪ የጻጉሜን 3 መክፈቻ ንግግራቸውን «ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቆራጥ መሪ፣ ዝነኛ የአፍሪካ ልጅና የዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴ ታላቅ ሰው» በማለት

እንዳገባደዱ የሌኒን ምስል የተንደፈበትንና «ያለም ወዛደሮች ተባበሩ» የሚል የተፃፈበትን ቀይ ባንዲራ ለክቡር ሊቀመንበሩ ለኰሎኔል መንግስቱ በራሳቸውና በመንግስታቸው ስም አስረከቡ።

ኰሎኔሉ በደስታ ተቀብለው ሲፈነድቁ፣ ተከፋዩም ደስታውን በጭብጨባ ሲገልጽ፣ ከመትጀበት የከረያው ልዑክ መሪ ብድግ ብለው መድረኩ ላይ በመወርወር ወንድማዊ መሳሳም በተደባለቀው የደስታ መግለጫ፣ የኪም ኢል ሱንግ ምስል የተንደፈበትን ቀይ ባንዲራቸውን በተራቸው መንግስቱ ቀኝ እጅ ላይ አስታቀፉ። መንግስቱ ኃ/ማርያም አንዱን ባንዲራ በግራ እጃቸው ሌላውን በቀኝ ይዘው ሲፈነድቁ 'በዚያ የኮሚኒስቶች ክብርና በመካከላቸውም ያለው አንድነት ግልጽ በሚደረግበት ሰዓት እድሜ ለኬጂቢ' ይላሉ ፀሐፊው 'መድረኩ ላይ የቆመው ፍጡር ባንዲራውን በደስታ ሲያውለበልብ የጉባኤው አዳራሽ መብራት ድርግም ብሎ እንዲጠፋ ተደረገ። ኤሌክትሪክ ተቋረጠ። የድምጽ ማጉያ መሣሪያውም ፀጥ አለ። በባትሪ ድንጋይ ከሚሰራው የፀጥታ ሰዎች መገናኛ መሣሪያ ሁካታ በስተቀር ምንም ነገር ለመስማት አልተቻለም። ከሁለት ሰዓት በላይ ከፈጀው ግርግር በኋላ መድረኩ ላይ ሽብር ፈጥሮ የነበረው ባንዲራና ተሸክሞት የነበረው ሰው (መንግስቱ ኃይለማርያም) በፕሮግራሙ መሰረት ጉባኤው ሲቀጥል በቦታው አልተገኙም።

ከግርግሩ በኋላ የደስታ መግለጫ ንግግሩ ሲጀምር የምስራቅ ጀርመን ኮሚኒስት ፓርቲን ደስታ መሪው ኤሪክ ሆኔከር ሳይሆኑ የቤተመንግስታቸው አገልጋይ የፖሊት ቢሮ አባል ኸረስትሆለር ዳላስ እንዲያነቡ ተደረገ።

የስምንቱ ቀን ጉባኤ በዚህ አላለቀም። ከድርሳነ ሹልትገ

ለመረዳት እንደማቻለው በኢሰፓ ጉባኤ አዳራሽ የተገኙት ሁሉም የዓለም አብዮት ተዋናይ ለመሆን የሚፈልጉ እንደየዘይቤዎቻቸው ራሳቸውን የማያስተዋውቁበት፣ ግንኙነት የማቋጥሩበት፣ በድብቅ ነገሮች የማጠንሰሱበት መድረክ ሆነ:: የማስተር ሹልትዝን ፍርድ እንከተል ካልን አንዳንዶቹ መሪዎች ጥጋበኛ፣ ኩራተኛና የሚጀነኑ ናቸው::

የኩባው የርእዮተ አለም ኃላፊ ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ስዕል የሚያንፀባርቁ ሲሆን፣ ሌላኛውም እንደማስተር ሮማኖቭ መሰላዊ ገጽታ ያላቸውና ይዘውት የመጡትን ኮኛክ መደባበስ የሚወዱ መሆናቸውን ጽሁፉ ያመለክታል:: ማስተር ኤሪክ ሆኒከር ደግሞ ሁሉን የማያነጋግሩና የሚያዳምጡ፣ እንዲያውም ያለም አቀፍ ኮሚኒዝም አፈቀላጤ ለመሆን የሚቃጣቸው ሰው ነበሩ::

ኤሪክ ሆኔከር በንግግራቸው ብቅ ያሉት የካርል ማርክስ ሐውልት በሚመረቅበት ጊዜ ነበር::


ፈረንሳዊው ፀሐፊ ማስተር ሬጂዶብሬ እንደሚሉት ከሆነ ስልጣን ላይ ያሉ የጦር መኰንኖችም ሆኑ ገና ለስልጣን የሚታገሉ ሽምቅ ተዋጊዎች የካርል ማርክስን «ዳስ ካፒታል» እንኳን አንብቦ መረዳት ይቅርና ባይናቸውም ያዩት ጥቂት ናቸው፤ እንደሚሉት ሁሉ ኰሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምም በዚሁ ስብሰባ ላይ ነበር «የማርክ ስ ውድ ተማሪ፤ የአፍሪካ ሌኒን» ተብለው የተሰየሙት::

ሆኔከር የማርክስን ሐውልት ከመመረቃቸው በፊት፣ ኰሎኔል መንግስቱ በአማርኛ የታተመውን «ካፒታል» መጽሀፍ ለእንግዶቹ ያከፋፈሉ ሲሆን፣ እንደሚባለውም መጽሀፉ በአዲሳባ የተጠናቀቀ ሳይሆን ምስራቅ ጀርመን ላይፕዚንግ ከተማ እንደተጠረዘ ጽሁፉ ይገልፃል::


በዚህ የማርክስ ሐውልት ፊት ንግግሩ አልቆ መጋረጃው ሲነሳ ኤሪክ ሆኔከርን ለመርዳት መንግስቱ ኃይለማርያምና ባገራቸው የኮሚኒስት አስተሳሰብ የሚከተሉትን ሰዎች የሚያሳድዱት ኬንያዊው ፕሬዚዳንት ዳንኤል አራፕሞይ ለርዳታ ቀልጠፍ ብለው አጠገባቸው እንደተገኙ ድርሳኑ ያብራራል:: በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካ እግር ሶቭየት ኅብረት፣ በእስራኤል ቦታ ኩባ፣ በምዕራብ ጀርመን ፈንታ ምስራቅ ጀርመን፣ የተተኩባት እንዲያውም ይላል ጽሁፉ ደፍሮ «ኢትዮጵያ የምስራቅ ጀርመን ቅኝ ግዛት» እና የፈለጉትን የሚሰሩባት አገር እንደነበረች ነው:: ሰሜን ኮርያም የመንግስቱን ፎቶ ግራፎች በመሳል፣ የኮሚኒስቶችን ካኪ ልብስና ነጠላ ጫማዎችን ታቀብል እንደነበረ በመጥቀስ፣ ሶቭየት በመሳሪያ፣ ምስራቅ ጀርመን በርዕዮተ ዓለምና በጸጥታ፣ የበላይነቱን ይዛ አገሪቱን ትቆጣጠር እንደነበር ያመለክታል:: 'የላምበርገዝ የቡና ለቀማ ልዑካኖች' በሚለው ሽፋን ስርም አስረኛው ያብዮት በዓል በተሳካ ሁኔታ እንዲፈፀም የምስራቅ ጀርመን ፈጥኖ ደራሽ ወታደሮች በአዲሳባ ተገኝተው እንደነበረ ጽሁፉ ይገልፃል::

መቼስ ምን ይደረጋል? ያ በትልቅ የጦር መሣሪያ ሰልፍ «እድሜ ለመንግስቱ ኃይለማርያም» ተብሎ ባደባባይ የተጮኸበትን የጉባኤው መዝጊያ፣ የአብዮት አደባባይ ትርዒት ሚስተር ሹልትዝ «ሳናስበው ኃይለኛ ነፋስ፣ ዝናብና በረዶ መጥቶ ያን በክርታስ የተሰራ ስገነት ግንጥልጥሉን በማውጣት» እንግዶቹን ዝናብ አርሷቸው እንደበታተናቸው ይገልፃሉ::

በእርግጥ የሆነው ግን ከአዲሳባ ጉባኤ በሁዋላ ስልጣን የያዙት ሚስተር ጐርባቾብ ያቀጣጠሉት እሳትና የለቀቁት አውሎ ነፋስ ሁሉንም ጠራርጐ እንደወሰደ ነው::



# እናት ኢትዮጵያ



# የመንግስቱ አባት

አረፈዐይኔ ሀጎስ

«አቶ ወልደ አማኑኤል፤ አቶ ወልዴና ባሻ ግዛው፣ ደራ በሽፍትነት ቆይተው በመጨረሻ ለንግስት ዘውዲቱ አደሩ:: ጥቂት አመታት በዘበኝነት እንዳገለገሉም ማደሪያ ይሆናቸው ዘንድ ንግስቲቱ አንዳንድ ጋሻ መሬት አዲሳለም ሰጧቸው::

«እንግዲህ እዚያ ሳለን በባህላችን 'ልጅህን ለልጅ' ማለት የነበረ ነውና አባቴ አቶ ወልዴ የጋሼ ወልደአማኑኤልን ልጅ አጩልኝ:: ይሄኔ የጣልያን ጦርነት መጣና ሁሉ ነገር ዲስሚስ (Dismiss) ሆነ::

ዘፈን አይኑር፣ ስርግም ይቅር የሚል ትዕዛዝ ከላይ መጣ:: እንዲህ ስንኖር ሳለ ልጂቱን አንዱ ዲያቆን ያገባና ይወስዳታል:: ዲያቆኑን ደግሞ አንዱ ሹምባሽ ይነጥቀውና መርሃ ቤቴ ላንድ ዓመት ያክል ይቀመጣሉ:: ከዚያም አገሩ ይሂት ሲገባ ወዳዲሳባ ይመጣል::

«እኔ የፓይለቶች አዛዥ ለነበረ ኢጣልያዊ በይነት ተቀጥሬ ደጃች ውቤ ነበርኩ:: ሹምባሽ ሆዬ ልጂቱን ይዞ እዚያው አካባቢ ኖሯል ያረፈው:: ለግብር ውሀ ስትወጣ ከኔ ጋር ግጥምጥም እንላለን:: ይሄኔ ደንግጣ ወደቤት መመለስ:: ያረፈችበት ቤት ሄጄ ባለቤቷን ብጠይቃቸው 'አረ እኔም ጣሳዬ ከጄ ወደቀ፤ የማውቀው ሰው ይመስለኛል' ብላለች አሉኝ:: ተጠርታ ስትመጣ ሆዶ ደነገጠ:: 'የጋሼ ወልደ አማኑኤል ልጅም አይደለሽም ወይ? ያጨሁሽ እኔም አልነበርኩ ወይ?' ስል ጠየቅኋት:: ከዚያማ ተግባባን:: በመጨረሻም 'ከኔ ጋር ትሆኚ ወይስ ከርሱ ጋር ትሄጃለሽ?' አልኋት:: እኔን መረጠች:: አልብሼ ይገርት ገባሁ:: ጠላ ጠጅ ተገዛ:: ስንዘፍን አደርን:: በማግስቱ ሹምባሹ ቡሊሲያ ካራቢኘሪ አምጥቶ አስወሰደን:: ሬዚደንሳ አመለከተ:: እርስዋ መሃል ሆነች:: እኔና እሱ ግራና ቀኝ እንድንቆም ተደረገ:: ዳኛው ምረጪ አላት:: ወደኔ ገልበጥ አለች:: ዳኛውም 'እርሱን ከወደደችውማ በግድ የሚሆን ነገር አይደለምና ሌላ ፈልግ' ብሎ አሰናበተው:: እኔም ይኸኔ ልጂቱን ይዤ ጭልጥ አልኩ::»

«ልጂቱ ስሟ ማነው?»

«ብዙነሽ ተሰማ::»

«የአቶ ወልደ አማኑኤል ልጅ ነች አላሉኝም ኖሯል?»

«አዎ:: ዘንድ ስላደገች ብዙነሽ ወልደ አማኑኤል ነው

የምትባል እንጂ ወላጅ አባቷማ አቶ ተሰማ ናቸው::»

«የደጃዝማች ከበደ ተሰማ ዘመድ ይሆኑ?»

«ኤድያ! እኛ ከነሱ ጋር ምንም ዝምድና የለን:: አቶ ተሰማ ቡልጌ ናቸው:: ጉበዝ የቤተ መንግስት ግንበኛ::»

«በቅርቡ የወጣ አንድ መጽሃፍ ላይ መንግስቱ የጣጢት የልጅ ልጅ መሆኑን አንብቤያለሁ:: ይህስ እውነት ነው?»

ከት ብለው ሳቁና «ሆሆይ! ጣጢት እኮ ሶስት አራት ባሎች የነበሯት ሀብታም ወይዘሮ ነች:: የድሃ ዘር አልነበረችም:: ይሄን ይሄን ተወው፤ ሸዋ ነው የሚያስወራው:: ይልቅ የጀመርኩልህን ልጨርስልህ::»

«በጄ!»

«ልጂቱን ይገሬ ጭልጥ አላልኩልህም? ወዲያውኑ ይህን ልጅ አረገዘች:: የካቲት 1933 መንግስቱ ተወለደ:: የበኩር ልጇ ነው::»

መንግስቱ ከአባቱ ከሀምሳ አለቃ ሃይለማርያም ወልዴ አዲስ አበባ ተወለደ:: ጨርቆስ የቄስ ትምህርቱን ሲከታተል ቆይቶም አባቱ ወደ ጂማ በመዛወራቸው ወደዚያው ሄደ:: ወላጅ እናቱ በ1944 አረፉ::

«ሄርማታ (ሚያዝያ 27) ት/ቤት እስከ ሰባተኛ ክፍል እንደተማረም የመሣሪያ ግምጃ ቤት ወዳዲሳባ ስለጠራኝ በይስካውት አስቀጠርኩት:: ከዚያም ጽህፈት ኮርስ ሰደውት ስድስት ወር ከተማረ በኋላ ሆለታ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ገባ:: የማታ እየተማረም አሥራ ሁለትን ሸፍኗል::»

«ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት 'ኒው ታይምስ' የተባለው የሶቪየት መጽሄት ከዩኒቨርሲቲ በዲግሪ ተመርቋል

ብሎ ጽፏልኮ» አልኳቸው። ስቀው ዝም አሉ።

«አጥፍቶ መጥፋት የተሰኘው መጽሐፍ ጂማ ሳሉ ጠጅ እየጠጡ አምሽተው እንደሚገቡና መንግስቱንም በሞቅታ መንፈስ ይደበድቡት እንደነበረ ይናገራል፣ ዱላ ያበዙበት ጊዜ ነበረ?»

«በሕይወቴ የገረፍኩት አንድ ቀን ብቻ ነው። ያውም ጨዋታ ስለሚወድ አምሽቶ በመምጣቱ ያን ቀን ተገረፈ እንጂ ነክቼውም አላውቅ። ጻሐፊው... ቢሆን ነው እንጂ የምንኖረው ሚሊታሪ ካምፕ ውስጥ ነው። ስለዚህም በ12 ሰዓት ተጠናቅቀን መግባት አለብን። ከዚያም በኋላ ጠባቂ ፖሊስ ይቆማል። በዚያ ላይ ገንዘቡስ ከየት መጥቶ ነው በየቀኑ የሚሰክረው? ደሞዛችን አስር ብርም አልነበር።»

«መንግስቱ በልጅነቱ ምን ዓይነት ባህርይ ነበረው?»

«ቁጡ ነው። ከሰውም አይገጥም ነበር። ፊንጠር ብሎ ነው የሚሄደው። ትምህርት ቤት ሲሄድ ብቻውን ነው የሚሄድ። ከፊቱ ያስቀድማል ወይም ይከተላል እንጂ ከሰው ጐን ለጐን አይሄድም። ኳስ ጨዋታና ስፖርትም ይወድ ነበር። በተለይ በቦክስ ጥሩ ውጤት ያመጣ ነበር።»

«በትምህርቱስ እንዴት ነበር?»

«ጐበዝ ነው»

«እንዴት?»

«ወድቆ አያውቅም»

«ከርስዎስ ጋር የነበራችሁ ግንኙነት እንዴት ነው?»

«በፊት እንኳን ደህና ነበር። መኰንን ከሆነ በኋላ

ግን ሲስተም(System) ለወጠ:: ችሎል አለኝ:: ባዕድ ነው የሚደርስልኝ:: ስለዚህ ምን ያደርጋል ብዬ ተውኩት:: መኮንን ከሆነ ወዲህ ነው የመጣበት::»

«ደርግ ሆኖ ሲመረጥስ ምን ተሰማዎት?»

«ደስ ብሎኝ ነበር:: ከችግር እንዲላቀቅልኝ ነበር ምኞቴ:: በኋላ ግን ራቅሁት:: የገዛ ባልንጀሮቹን መልሶ እንደሚት ይገላል ሰው?! በዚያ ላይ ትዕቢቱ ሌላ ሆነ:: ጋኔን ከተ ሽከሙት ጋር ይጨፈጭፋሉ::»

«ወታደሮቹ ለምን የመረጡት ይመስልዎታል?»

«ግማሾቹ ስለማይወዱት እንዲሞትላቸው መረጡት:: ሌሎቹ ደግሞ 'ላዛገሮቹ የማይ መለስ እሱ ነው:: ጨካኝ እሱ ነው:: ሌሎቹ ፈሳሞች ናቸው' ብለው መረጡት:: በጊዜው ለበታቾቹም ይሟገት ነበር አሉ:: በዚያ ላይ መኮንኖች ከበብ ገብተ ሳይበጠብጥ አይወጣም::»

«ባባትነትዎ ምክር ለግሰውት ያውቃሉ?»

«ከአንድ ሁለት ዓመት በፊት ቢቸግረኝ 'ጠብ ይቅር እርቅ ይውረድ:: ሰውም ልጆቻችንን እየወሰደ አስጨረሰ ብሎ ጠምዶሃልና የሰው ልጅ አታስጨርስ' አልኩት::»

«የቱን ጠብ ማለትዎ ነበር?»

«የኤርትራውን ጦርነት ነዋ! አንተ አታውቅ እንደሁ እንጂ አንድ ነን:: ተዛምደናል፤ አበልጅ የሆንን ሁሉ አለን:: ስለዚህ እነሱንም አታስቀይማቸው:: የሰውም ልጅ እየወሰድክ አታስጨርስ:: እርቅ ይውረድ ልጄ አልኩት::»

«ምን መለሰልዎ?»

«አንተ ምን ታውቃለህ?! ሽማግሌ ነህ፤ አርፈህ ተቀመጥ አለኝ። እኔም ተቀየምኩ ከቤቱ ቀረሁ።»

ጦርነቱ እየገፋ በመምጣቱ ግን ኰሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም በተወለደ በሃምሳ ዓመቱ ስልጣን በያዘ በአስራ ሰባት ዓመቱ ወደሃራሬ (ዚምባብዌ) ኰበለለ።

«መጥፋቱን መቼ ነበር ያወቁት?»

«በራዲዮ ሰማን። እንደሰማን ክው ነበር ያልነው። ገረዶቹ ሁሉ መጥፋቱን አላወቁም ነበር።»

«ቆራጡ መሪ እየተባለ ይወደስኰ ነበር።»

«ለቆራጥነቱማ ቆራጥ ነው።»

«እንዴት ማለት?»

«ክፉ ነዋ! ድንጋይ ራስ»

«ኑሮስ እንዴት ይዞዎታል?»

«ድህነቴ ነው እንጂ የቸገረኝ ምን አለብኝ ብለህ? በፊትም ብቸኛ፤ አሁንም ብቸኛ። መሳሪያ እያደስኩ ኑሮዩን እደጉም ነበር። ሆኖም በግንቦቱ ፍንዳታ መሳሪያ ማደሻው ተቃጠለ። ስራውም ቀረ። በተረፈ እኔ የነሱን ገንዘብ አልከጅል።»

«ሰውስ ምን ይልዎታል?»

«ተወኝ!» አሉና አምሳ አለቃ ከዘራቸው ላይ ጭንቅላታቸውን ደፉ። ቡሽ ባርኔጣ አድርገዋል። ያረጀች ሸሚዝ፤ እንዲሁም ኰትና ሱሪ። ትክዝ ብለው ቆዩ። ደምስራቸው ግንባራቸው ላይ ጐልቶ ይታያል። የ77 ዓመት አዛውንት አይመስሉም።

«ያበሳጨኛል! ብስጭት ብቻ ነው ልጄ:: መረሬ ይሉኛል:: ስሜ ተረስቷል:: ይሄ ሳይሆን ሞቼ ባረፍኩ ነ·ር እላለሁ:: ጧት ማታ እዩዩ ነው፤ እንዳልሰማ ዝም እላለሁ:: እባክህ ተወኝ!»

ለአምሳ አለቃ ኃይለማርያም አዘንኩላቸው:: ይርጋ ዱባለ


«አባት አስወቃሽ ልጅ አይወለድ፤

የሚያስጠራ እንጂ ምንገድ ለምንገድ» እያለ የሚደረድረው ስንኝ ትውስ አለኝ:: ያም ሆኖ ግን እጅግ ያዘንሁት እኚህን አዛውንት በሚያዋርዷቸው ሰዎች ነው:: ይሄኔ ከፊሎቹ «አማልዱኝ!» ሲሏቸው የነበሩ ይሆናሉ:: ቀሪዎቹም ቆዳ አምላኪ ትምክህተኞች::

***

አምሳ አለቃ ኃይለማርያም አሁን በህይወት የሉም:: በ1984 ይህን ቃለምልልስ ከሰጡ በሁዋላ ብዙም ሳይቆዩ አርፈዋል::





# ወፍራምና ቀጭን

## አንቶን ቼኾብ
## (ትርጉም መኩሪያ መካሻ)

በኒኮላየቭስክ ባቡር ጣቢያ ሁለት ጓደኞች ተገናኙ:: አንደኛው ወፍራም ሲሆን ሌላኛው ቀጭን ነው:: ወፍራሙ በባቡር ጣቢያው ውስጥ ተመግቦ መውጣቱ ነበር:: ከንፈሩ በቅቤ አብለጭልጮአል::

የተቀባው የአዶክለ'ኝ ሽቱ ከሩቅ ይጣራል፡፡ ቀጭኑ ገና ከባቡር መውረዱ ስለሆነ በሻንጣዎች፣ በካርቶኖችና በጥቃቅን ቋጠሮዎች ተከቧል፡፡ ከላዩ ላይ የቡና ዝቃጭ ሽታ ይሰነፍጣል፡፡ ከጆርባው ቀጭኑና አገጨዬም ሴት ትታያለች፡፡ ማስቱ ናት፡፡ ቀውላላውና ዓይነ ውሽንግሩ ተማሪ ደግሞ ልጁ ነው፡፡

«ፕሪፍሪያም!» ሲል ጠፍራሙ ሰውዬ ቀጭኑን ተመልክቶ ጮኸ፡፡ «አንተ ነህ ለላ? ወዳጄ! ለመሆኑ ስንት ጊዜ ሆነን ሳንገናኝ?!»

«ወይ እናቴን!» ሲል ቀጭኑም አፀፋ መለሰ፡፡ «ሚሻ! አብሮ አደጌ ሚሻ! ምን እግር ጣለህ?» ሶስቱ አከታትለው ከተሳሳሙ በኋላ ተፋጠው ዓይን ለዓይን ተያዩ፡፡ ዓይናቸው እንባ ያቀረዘዘ ቢሆንም በደስታ ተውጠዋል፡፡

«ወዳጄ ሆይ!» አለ ቀጭኑ ዝምታውን እየገፈፈ፡፡ «ፈፅሞ አልጠበኩም! እስቲ ተመልከተኝ፡፡ እንደጥንቱ ቆንጆ ነህ አሁንም፡፡ አይ አንተ! ለመሆኑ እንዴት ነህ? ሀብት አፈራህ? አገባህ? እኔ እንደሆንኩ እንደምታየኝ ነው - አግብቼያለሁ፡፡ ይህች ማስቱ እኮ ናት፡፡ ሉይዛ ትባላለች፤ ፕሮቴስታንት ናት፡፡ ይህ ደግሞ ልጄ ነው - ናፋናይል ይባላል፡፡ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ ነው፡፡» አያያዘናም ወደ ልጁ ዞር ብሎ

«ናፋናይል ልጄ! ይህ የልጅነት ጓደኛ ነው:: አብረን ነው የተማርነው»

ናፋናይል ጥቂት ካሰበ በኋላ ባርኔጣውን ለሰላምታ አነሳ::

«አንድ ትምህርት ቤት አንድ ላይ ነው የተማርነው» ሲል ቀጠለ ቀጭኑ - «ታስታውሳለህ ያኔ! ተረት ማውራት እወድ ነበር:: መፃህፍቶቹን ባቃጠልኳቸው ጊዜ፤ ሆሆ ... ሆሆ ... ልጆች ነበርን! አትፍራ እንጂ ናፋናይል:: ጠጋ በል፣ ቅረበው:: ይኸውልህ ይህች ሚስቴ ናት - ቫንሴናባህ የተወለደች፣ የፕሮቴስታንት ተከታይ::»

ናፋናይል ጥቂት አሰብ አድርጎ ከአባቱ ጀርባ ተሸሸገ::

«ታዲያስ የጥንቱ ጓደኛዬ፣ ኑሮ እንዴት ነው?» ሲል በግራሞት ወፍራሙ ጠየቀው:: «የት ነው የምትሰራው ወይስ ስራ የለህም?»

«እየሰራሁ ነው ወዳጄ! በኮሌጅ ተቆጣጣሪነት ሁለት ዓመት ጨርሻለሁ:: የስታንስላቭን ሜዳሊያም ተሸልሜያለሁ:: ደሞዙ ግን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ እግዚአብሄር ይሁነን ብቻ:: ሚስቴ ሙዚቃ ታስተምራለች:: እኔም ለተጨማሪ ገበያችን የሲጋራ

ፓኮዎችን እሰራለሁ:: ፓ! እንዴት ያለ ማስቀመጫ ፓኮ! አንዳንድ ሩብል እሸጣቸዋለሁ:: እስርና ከእስር በላይ ፓኮዎች የገዛኝ ቅናሽ ይደረግለታል:: ቀደም ሲል አስተዳደር ክፍል ውስጥ ሰርቼ ነበር፤ አሁን የመምሪያ ኃላፊ አድርገውኛል:: ከእንግዲህ እዚሁ ነው የምሆነው:: አንተስ ታዲያ እንዴት ነው አትፍራ - ተናገር! አማካሪ ነህ? አይደለህም እንዴ!?»

«አይደለም ወዳጄ! ትንሽ ከፍ በል» አለው ወፍራሙ:: «የመንግስት የሚስጢር ክፍል አማካሪ ሆኜ አገለግዬአለሁ:: ለዚህም ሁለት ኮከቦችን ተሸልሜያለሁ»

ቀጭኑ በድንገት ፊቱ አመድ መሰለ:: በቆመበት ክችር አለ:: ፊቱ ከመቅዕበት ተለዋወጠ:: ከፊቱና ከዓይኑ ውስጥ ብልጭታ የሚረጭ መሰለ:: አካሉ እየታጠፈ፣ እየሙዋሸሸና እየጉበጠ ሄደ:: የሚስቱ ሹል አገጭ ይበልጥ ረዘመ::

«የተከበሩ ... ክቡር ... እርስዎን በማግኘቱ ደስታዬ ወሰን የለውም:: ጓዴ ማለት ይቻል ይሆናል፤ ይህን በመሰለ መስሪያ ቤት የሚሰራውን ሰው ግን ... ሂ-ሂ-ሂ»


«በል እንግዲህ ይብቃህ!» አለውና ወፍራሙ እየተኮሳተረ? መንገዱን ቀጠለ:: «ይህ ሁሉ ውዳሴ ምን ያስፈልጋል? እኔ የጥንት የጥዋቱ ጓደኛህ ነኝ፣ ለምን ነው ይህ ሁሉ ማደግደግ ...»

«ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ ምነው ምን አጠፋሁ፣ ምን ነካዎ» እያለ የቀጭኑ ሰውነት እብሮት ሚሽሽ።


ወፍራሙ አንድ ሽንቋጭ ነገር ጣል ሊያደርግ የፈለገ ቢመስልም በቀጭኑ የፊት ገፅ ላይ አክብሮት ይነበብበት ነበር። ወፍራሙ ያሰበውን ከመናገር ከአፉ ላይ መልሶ ወደ ቀጭኑ ዞር አለ። ሊሰናበተውም እጁን ዘረጋ።

ቀጭኑ ግን ሶስት ጣቶቹን አስረዝሞና በመላ አካሉ እያደገደገ እንደ ቻይናዊ ሳቀ። «ሂ-ሂ-ሂ!»

ሚስቱም ተደርባ ፈገግ አለች። ናፋናይል እግሩን ወደኋላ ሰብስቦ በባርኔጣው ሰላምታ ሰጠ። ሶስቱም እጢያቸው ዱብ እንዳለ ተያዩ።



አዳምና ሄዋን ከገነት እንደተወረወሩ



# ፈርኦን ሲሶ ዝና

## ስብሀት ገብረእግዚአብሔር

አቶ አልአዛር (አቶአ) ስርአቱ ያዛል ተብሎ ባነገሱዋቸው በስምንተኛው ቀን ከህልማለም አልቤርጐ ከፍ ብሎ ባለው ትልቁ ዋርካ ስር ችሎት ተቀመጡ።

መጀመርያ ለፍርድ የቀረበው ተከሳሽ አቶ ጲላጦስ የተባለ ግለሰብ።

ከሳሽ፡- የመላው ስምንታገር ሕዝብ ሸማግሌዎች

ክስ፡- አቶ ጲላጦስ ፈርኦን ሲሶ-ዝና ሰባተኛ ሆኖ ነግሶ በነበረባቸው ስምንት አመታት ላደረሰው ግፍ ቅጣቱን እንዲቀበል::

«ምን አይነት ግፍ?» ብለው ጠየቁ አቶ አልአዛር::

ሀ- ሽፋፋ እግር አልወድም እያለ በሀገረ ሲኦል ሲያልፍ ሲያገድም ያጋጠመውን እግረ ሽፋፋ ሁሉ አንድ እግሩን በመጋዝ እያስቆረጠ «አሁን መንሻፈፍ ቀረልህ፤ ዕድሜ ለፈርኦን ሲሶ ዝና በል» እያለ የተሳለቀባቸው ሰዎች::

ኤግዚቢት አንድ አሉና ስምንት እግረ ቆራጣዎች አስገቡ::

እነዚህ ኤግዚቢቶች ሲጠየቁ እውነት በኛደርሶብናል ብለው መሰከሩ «በቃላችንም በእግራችንም እንመሰክራለን» አሉ::

ለ- የምድረ ሲኦል ሳይሆን የጭራቅ አገር ተወላጅ የሆኑ ከፈርኦን ሲሶ–ዝና ስድስተኛ የወረሳቸውን ሰው በላ ቅጥረኛ ወታደሮቹን ለመመገብ በየአንዳንዱ ጭቃ ክልል ያሉ ኗሪዎች ስምንት ስምንት ወጣት ልጆች እንዲያዋጡ በማዘዙ እኛ የመሳው ስምንታገር ሽማግሌዎችም ፈርኦን ሲሶ ዝና ሰባተኛን እንዲህ አልነው::

«ፈርኦን ነህና እንታዘዛለን- ወደድንም ጠላንም::ግን ልብ ብለህ ስማን፤ ወደድክም ጠላህም ህዝብ ነንና»

«ተናገሩ»

**«ያባት በመሆኑ ለጦርነት ልጆች እናዋጣለን እንጂ ለጭራቅ ወታደሮችህ ምግብ ልጆች አዋጡ ምትለን ልጆቻችን ናቸው እንጂ በጉቻችን ወይስ ዶሮዎቻችን**

መስሉህ?»

«አባቶቼ» አለ ፈርኦን ሲሶ-ዝና «ስዩና፣ በላው ጥርስ፣ አሳት ነየው ምን ለየው? በአእምሮዋችን አናስብ እንጂ.»

«በጠለደ አንጀታችን ነው የምናስበው:: ልጆቻችንን ለጭራቅ አንሰጥም»

«የፈርኦን ትእዛዝ ነው!»

«ፈርኦን ነህ እንጂ. እግዚአብሔር አይደለህም»

«እምቢ. አላችሁ በቃ?»

«ከይቅርታ ጋር»

«የመጨረሻ ቃላችሁ ነው?»

«ነው»

ፈርኦን ሲሶ-ዝናም ጭራቅ ወታደሮቹን «አድነህ ብላ» አላቸው:: ስምንት አመት ሙሉ ምድረ ሲኦልን እያደኑ በሉአት::

ኤግዚቢት ሁለት አሉና የስምንት ሰው አጥንት አምጥተው አስቀመጡ:: «የፈርኦን ሲሶ-ዝና ሰባተኛ ጭራቅ ወታደሮች ስጋቸውን በልተው የጣሉት የወጣቶች አጥንት»

ተከሳሽ አቶ ጲላጦስ (ፈርኦን ሲሶ-ዝና) እምነት ክህደት ሲጠየቁ ሽምጥጥ አርገው ካዱ:: «ህዝቤን የሚጠቅም እንጂ. የሚጎዳ ነገር ሰርቼም፣ ተናግሬም፣ አስቤም አላውቅም:: እቺ ጾህይ ትመስክር» አሉ::

ጾህይ ይህን ሰምታ በሳቅ ተንከተከተች:: ግን እንደማታውቀው የሀሐይ ሳቅ አይታይምም አይሰማምም::

አቶ ኮምቡጦር ውሻቸውን ምክር ጠየቁት። አግራቸው አጠገብ ተጋድሞ ሲያዳምጥ ቆይቷል።

«እኔ እምለው» አለ ኮምቡጦር በውሽኛ ፈገግታ «ሰዎች ስትባሉ በጣም ትገርሙኛላችሁ። እሱም እያወቀው እነሱም እያወቁት ከንቱ መካካድ ምን ያረጋል? አሁን እኛ እንስሳት ብንሆን-»

«እሱን ሌላ ጊዜ ትነግረኛለህ። አሁን ወደ ቁም ነገር። እኔን ብትሆን ምን ትፈርዳለህ?»

«አልፈርድም»

«እንዴት?»

«ፍርዱን ለነሱ እተውላቸዋለሁ»

«ብራቮ ኮምቡጦር! አንተ ባትኖረኝ ምን ይውጠኝ ነበር?»

«እሱን ሌላ ጊዜ እነግሮታለሁ። አሁን ወደ ቁም ነገር»

«እናትክን!» አሉት እየሳቁ። ከዚያም አቶ አልአዛር ወደ ስምንታገር ሽማግሌዎች ዞረው፣

«ፍርዱን ለናንተ ትቻለሁ» አሉዋቸው።

የመሳው ስምንታገር ሽማግሌዎች የተከሳሽ ሞክሼ የሆኑትን ዝነኛውን ዳኛ አፈ ፈርኦን ጲላጦስ ጽንፅናዊን ፍርድ ስጡን አሉዋቸው። (የፅንፅንያ ሰዎች ኮስታራዎች ናቸው፣ የፊት ስር ቂጣ እያበሉ ያሳደጉዋቸው።) አፈ ፈርኦን ጲላጦስም በፈርኦን ሲሶ-ዝና ላይ ቅጣት፣ ተራ ቅጣት ሳይሆን አይቀጡ ቅጣት ፈረደበት።

እዚያው እዋርካው አጠገብ ካለው መግደላይት አደባባይ ከስልክ እንጨት ጋር አሰሩት።

በመጀመሪያው ቀን የመጨረሻ ምሳህ ነው ብለው አንድ እንጀራ አበሉት። በሁለተኛው ቀን ግማሽ እንጀራ አበሉት። በሶስተኛው ቀን ኩርማን እንጀራ አበሉት። በአራተኛው ቀን የኩርማን ግማሽ አበሉት። በአምስተኛው ቀን የኩርማን ኩርማን አበሉት። በስድስተኛው ቀን የኩርማን ኩርማን ኩርማን አበሉት። በሰባተኛው ቀን የኩርማን ኩርማን ኩርማን ኩርማን እንደበላህ ቁጠረው አሉት።

በስምንተኛው ቀን ምርጥ ባለሙያ ሴቶች ፈርኦን ሲሶ-ዝና አጠገብ ድስት ጣዱ። ሽንኩርቱ ተቁላላ፣ ቅቤው ተጨመረ፣ ቅመማ ቅመም በየይነቱ እንደ ቅደም ተከተሉ ሲገባ ተዘጋጀ።

ፈርኦን ከረሀቡ ብዛት መቃዠትና ባዶ አፉን ማላመጥ ጀመረ።

የሸማግሌዎቹ ስብሳቢ የእጅ ምልክት ሲሰጡ ኤግዚቢት አንድ ተብለው የመጡት ስምንት እግረ ቆራጦች መጋዝ ይዘው ፈርኦን ሲሶ-ዝና ላይ ተረባረቡበት። «እኛን ምሰል» አሉና አንድ እግሩን በዝግታ ገዝግዘው ቆረጡት።

ከዚያም «የግዘገዘ፣ ተገዘገዘ- አሰየው! ተገዘገዘ» የሚል ትምህርት አዘል መውድስ ዘምረውለት ሲያበቁ እጅ ነስተውት ወደ ኤግዚቢትነታቸው ተመለሱ።

ባለሙያዎቹ ሴቶች የተቆረጠውን እግር ወስደው ክሽን ያለች ሲጋ ወጥ ሰሩ።

ይህ ቀይ ወጥ፣ ሻሽ በመሰለ ነጭ እንጀራ ቀረበለት። ፈርኦን ጥስቅ አርጎ በላ። «እግሬን በላሁ አይባልም፣ እንጀራ በወጥ እንጂ» ብሎ እያሰበ «ደሞ ስበላው እግር እግር አይልም፣ ምግብ ምግብ ነው ሚለው።» በልቶ ሲጨርስ


«ሲ.ር ብህ ተናገር» አለች፡፡

ይህን ባለች በስምንተኛው ሰዓት «ራብኝ» አለ፡፡

ሁለተኛ እግሩን ቆርጠው ወጥ ሰርተው አበሉት፡፡ በልቶ ሲጨርስ «ሲር ብህ ተናገር» አለች፡፡

ሲርበው ተናገረ፡፡ አንድ ጭን ቆርጠው ወጥ ሰርተው አበሉት፡፡

እንዲህ ሲል ፈርኦን ሲሶ-ዝና በየስምንት ሰዓቱ ራብኝ ሲል ከቀረው አካሉ ቆርጠው ወጥ ሰርተው ሲያበሉት ... በልቶ፣ ተበልቶ አልቆ ምላስ ብቻ ቀረች፡፡ እሷም «እኔን ያየህ ተቀጣ» ብላ ስታበቃ «ራብኝ» ብላ ወጥ ተሰርታ ተበላች፡፡ ፈርኦን ሲሶ-ዝና ጥርስ ብቻ ሆኖ ቀረ፡፡ ጥርስ ጥርስን መብላት አለመቻሉ ፈርኦን ሲሶ-ዝናን እጅግ ሲበዛ ቆጨው፡፡



# ምንትሴ ቅብጥርሴ

## ደረጀ ደስታ

ተለቃት ብዙ ቀን፣ እነወጋየሁ ንጋቱ በበቀለብት አገር፣ እነ ሆድ አየሁ ምሽቱ በቅለው ኖሮ ሰዎች ዛሬ እንድን ማንትስ ሲቦጭቁት ሲዘለዝሉት አየሁ። ሥጋው ግን እንዳልጣፈጣቸው ልብ ብያለሁ። ድሮም ቢሆን ጥሩን ሲያሙ እየቋመጡ፣ መጥፎን ሲያሙ እያሸሟጠጡ ነው። ታዲያስ ለሰው ብለው ምንትሴ፣ ለኔ ብለህ ቅብጥርሴ፣ ሆነና ለኔ ብዬ ሰማሁት፤ እንግዲህ የዘመኑ ሰው ምላሱ መንታ፣ አንዱ ለፍቅር አንዱ ላሜታ እንዲሉ እኔ

እንደሰማሁት ስሟቸው::

በመጀመሪያ ጥርቅም አድርገው ጠሉት:: አቤት ጥላቻ! አንዳንዴስ የኪነጥበብ ሰው አይጥላችሁ! ጥላቻቸው ላይን የሚከፋ፣ ላፍንጫ የሚከረፋ ነው:: ድሮ ድሮ ጥላቻዬ ሁሉ በግምት ነበር:: ታዲያ አያቴ ግምት አይወዱም ነበርና «የግምት ግምትማ ፊስም ዳለቻ ነው» ይሉኝ ነበር:: እውነታቸውን ነው:: ዛሬ ግን ጥላቻን በዓይኔ አየሁት:: አሽቀትቅጡት መጥኔ ለኪነት ሰዎች:: ብቻ እናንተ እነዚህ ሁለቱ እንኳ ሲነጋገሩ ልብ ብላችሁ ስሙልኝ! (ወሬው እንዲመቻችሁ በክፍል ክፍል ላድርግላችሁ)

-- 1 --

«አንዳንዴ ሳስበው... ህይወት ሆድ ነው እንዴ?»

«ለምን አልክ?»

«በቃ ሳይፈሳው ሽተተኛ»

«እንዴት?»

«የምትጠላው ሰው ፊሱ ሆዱ ውስጥ እያለ አይሸትህም?»

«ጉድኮ ነው! ታዲያ ህይወት- ሆድ-ፊስ-ምን አገናኛቸው?»

«እንዴ፣ ምን አለያያቸው?»

«የዛሬውስ ነገርህ ምንም አለገባኝም::»

«እውነቴን እኮ ነው»

«እስቲ እውነትህን በለው?»

«ይህ ሰው ክፋቱ አይታይህም፤ ፊሱ አይሸትህም?»

«የቱ?»

«ኧረ ቂስ ይጥራው!»

«እስከዚያው ልጠብቅ?»

«ኧረ ይድፋው!»

«ታዲያ ንገረኛ?»

«እንዲያውም ያው መጣልህ!»

«የታል?»

«ያውልህ?»

«እንዴ! ለካ ቆማጣውን ነው እምትለኝ?»

«ማን አልከው?»

«ቆማጣው!»

«ደሞ እንዲህ ተባለ እንዴ?»

«ሳትሰማው ቀርተህ ነው?»

«ትንሽ ይቀረኛል።»

«ገብቼ ልፈትፍት ያለ እኮ ነው!»

«የት?»

«ኪነጥበብ ቤት!»

«ሌላ ቤት አልገባም?»

«ግማሽ ሆድ ሆነበታ!»

«እንዴ ቁምጥናው ምኑ ነው?»

«ሆዱ!»

(እዚችጋ ትንሽ ይስቁና ከያኒ ነኝ ባዩ ወደ እነሱ ሲመጣ ከመቀመጫቸው- አክብሮት! ይጨብጡታል - ሰላምታ! ይነጋገራሉ- ፈገግታ!

እሱም ቀማጣ ሆዱን እያሻሸ፣ እሚያገዘ እሚግጣቸው ልጆቹን በፍቅር አይን እያየ፣ ያፈቅሩኛል፣ ይወዱኛል እያለ እርዳታ የሚያስፈልገውን የብር ሸክም ሊያቃልል ይሄዳል።

'ውሻ ሆይ የሚሉህን ብትሰማ የሚሰጡህን አትበላም!'

--- 2 ---

እንዲህ እንዲህ እየተባለ ቃል ለቃል፣ ይጨመላለቃል። ወይ ምንትሴው ወይ ቅብርጥሴው ይቀጥላል።

ደሞ ያለም ነገር መጣ ዝም በሉ፤ ሄደ ተናገሩ፤ ነውና እሚቀጥለው ይቀጥላል። ወይ ቅብጥርሴው ወይ ምንትሴው።

«ደሞ እሱን ብሎ...!»

«ምን?»

«ከያኒ?»

«እሱን ተወው፣ ደራሲ ምንትሴ፣ አዘጋጅ ቅብርጥሴ ነው።»

«ግን'ኮ ግርም ይለኛል»

«ከመግረም በላይ እንጂ!»

«ሆድን ሆድ ሲጽፈው እራስ ምን ይበጀው?»

«ደሞ ክፋቱስ!»

«የክፋን ሰው ሆድ ኮሶም አይደርስበት!»

«ደሞ ስም መለዋወጥ!»

«ዘጠኝ በላሊ ፊስ አያስጥልም!»

«ደሞ ያፊኔብሟጊቢው ብዛት!»

«ከብት ባለበት ጅብ አይታጣም!»

«ደሞ... ብቻ ይቅር»

«እሺ! ይቅር በፍቅር።»

«ፍቅሩን እንጂ ተወው፤ ብቻ ይቅር...» እያሉ ይሉት፤ ይሉትና፤ ይሉታል። ደሞ ላፍታ ጥላቻው እንዳይመረቸው ፊኢዋታ ቀየር ያደርጋሉ። መቼም የከንቱ ሰዎች አይደሉ!

-- 3 --

«ብቻ... ጉድ ነው!»

«ሲዳሩ ማልቀስ ልትለኝ ነው?»

«እረ ሳይዳሩም!»

«እሱስ ልክ ነህ፤ ዛሬ ባል ማጊስቱ የት ይገኛል?»

«ነው ብለህ ነው?»

«ታዲያስ?»

«እኔ ግን አለመግባባት ይመስለኛል»

«በምን?»

«በቋንቋ!»

«ቋንቋ ምንድነው?»

«መግባቢያ ነዋ!»

«ሰው ተግባብቷላ?»

«እሱን እንኳ አላውቅም!»

«ታዲያስ?»

«አለና»

«አይ ባቢሎን!»

ይኼኔ አራት ዘፍጥረት ትዝ አይላችሁም? እኔ እንደዚያ ነው ያለኝ። «ኑ እንውረድ፣ አንዱ ያንዱን ነገር እንዳይሰማ ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው» (ዘፍጥረት)

--- 4 ---

ደሞ ውሎ ውሎ ምንትስ ዞሮ ዞሮ ቅብጥርስ ይሆንና መመለሳቸው አይቀር። ግን አመላለሳቸው በቀጥታ አይደለም።

«አዬ ጉድ!»

«አዬ ጉድን አታብላሽ፣ ለባለ ቀን ይሆናል»

«ምን እንዳይመጣ?»

«እንግዲህ ...?»

«ሲነግሩኝ ልስማ?»

«ሳትሸት እንዳትገማ (ከፈለግክ)?»

«እንዳልክ»

«ወደሽ፣ በህይወት ተገደሽ!»

«ህይወትማ ሆድ ነው!»

«ልክ ነህ፣ ከርስ- ለፈርስ - ፈርስ- ለፈስ...»

«ግን እማያስብ ሰው እንዴት ለሆድ?»

«ራስ ስሆድ አሽከር ነው ይባላል::»

«ቢሆንም ቢያንስ... ቢያንስ...?»

«ቢያንስ ምን?»

«ስሰሆድ የሰበከ ሰው...?»

«ምን መሆን አለበት?»

«መሆን የሌለበትን ማወቅ አለበት!»

«ካላወቀስ?»

«ይማራ!»

«ከነማን?»

«ከነ ወጋየሁ»

«እነሱማ ሞቱ»

«ብዙ ወጣቶችም እኮ አሉ»

«እነሱም ተዋጡ»

«በማን?»

«በሆዳሞች!»

«የወጣቶቹ ነገር ግን አይገርምህም?»

«እንዴት?»

«ከአድናቆትም በላይኮ እሚገባቸው አሉ:: ሰው እሚያውቀው ሞኖፖሎቹን ነው::»

አንዳንዱም ወደ ድሮ ብቻ መሮጥ ይቀናዋል:: ደንቆሮ

የድሮን (እሱ ይሰማ የነበረበትን ጊዜ) ዘፈን ይዘፍናል ይባላል:: ብቻ እንዲህ እንዲህ እየተባለ ቃል ለቃል ይጨመላለቃል:: ወይ ምንትሴው፣ ወይ ቅብርጥሴው ይቀጥላል::

እንግዲህ የተጠላ ታምቷል፤ የታማም ተተችቷል:: በዚህ ክፍል ደግሞ ሲታዘንለት ይሞከራል:: ያገኑ ያገኑና ምክንያት ይሹለት ይገባሉ::

--- 5 ---

«ግን ያሳዝናል!»

«ማን?»

«ሆዴ ጉደሎው ሰው!»

«በምኑ?»

«በጉደሎነቱ!»

«ለዚሁም አልተቻለም::»

«እውነቱንኮ ነው!»

«እስቲ እውነትህን በለው?»

«ጉደሎውን ሰው በጉደሎ ማህበረሰብ አስበው!»

«አሰብኩት!»

«አያሳዝንም?»

«መመሳሰል ምኑ ያሳዝናል? ሕግ እኮ ነው::»

«እሱስ ልክ ነህ ታዲያ ምን ይሻላል?»

«ሁለት አማራጮች ያሉ ይመስለኛል!»

«እንስማዋ?»

«ደሙን ከማፍሰስ?ሕጉን ከማፍረስ?»

«ጥሩ ነው እኔም ሁለት ልጨምርና አራት ይሁን»

«እስቲ በላቸው::»

«መልስ አልተሰጠም እና ሁሉም መልስ ነው::»

(አሁን ወደ መጨረሱ የተጠጉ ይመስላሉ:: ነገር ግን ለጥበብ ጉዳይ ይቅርታ ማድረጉ ክብድ ይላቸውና ምንነቴያቸውን መልሰው እንደ አዲስ ይጀምሩታል- እያንገሸገሻቸው::)

— 6 —

«ሆድ እኮ አይነት አለው::»

«ልክ ነህ አለው::»

«ደሞ እንዳሳዩት ነው::»

«ያላሳዩትን አምጡ አይልም::»

«የኔ! ለኔ! የኔ! ለኔ! ማለቱ ብቻ ጥሩ አይደለም::»

«ልክ ነህ:: ሆድ የኔ ነው እየተባለ በቁርጠት ይገድላል::»

«አቤት ደሞ ሆድ ለሆድ ሲዋደዱ»

**«ግም ለግም አብረህ አዝግም ይባል የለ!»**

**«ሆድ ሲጽፍ ሆድ ያዘጋጃል፤ ሆድም ይሰራዋል»**

«ታዲያ ማን ያጣውን?»

«እኔ ግን ያልገባኝ ነገር...»

«ከቻልኩት ላስረዳህ?»

«ለምሳሌ 50 ህሊና ተባብሮ»

«እሺ!»

«አንድ ቲያትር ሲሠራ...»

«የቱን ቲያትር?»

«የሆነውን»

«እሺ!»

«ምን ይሰማዋል?»

«እንደ ቲያትሩም ነዋ!»

«እኮ እንደ ቲያትሩ ቢሆን»

«እንዳለው ድርሻ ይመስለኛል!»

«ተኮታው ወይስ ተቦታው?»

«በሁለቱም ሊሆን ይችላል»

«ታዲያ አንዳንዶ ምን ነካው?»

«ማን?»

«ህምሣው ህሊና?»

«ሣያምስቱ እንኳ ይወጣል።»

«ሣያምስቱስ?»

«ሣያው እሚዋጥ ያገኛል»

«እምስቱስ?»

«ያብዳል!»

«ምን እያለ?»

«አርትን አትመኑ- አብዷል ዘመኑ! እያለ።»

እያሉ ምንትሴ እያሉ ትብጥብርሴ፣ ማለትን ይሉታል። ይሉት ይሉትና መልሰው ይሉታል። ይመላለሱታል።

ምልልስን ያለ ተውኔት፣ ተውኔትን ያለ መድረክ ይሆኑታል። ያለተመልካች ለእግዜር ብቻ ያሳዩታል። ሲያምርባቸው!

***

አሁን ደግሞ «ማነው ምንትስ?» እንበል።

«...እንሱን አርጕብን ጨዋ የሸንጎ የባህል አዋይ.

የሥነ ሥርዓት ደልዳይ,

መራጭ ቆራጭ ቀናን ከአባይ,

ጨዋ መሳይ, ንጹህ መሳይ,

ከኔም ላይሻሉ ደሞ እኔን ምንትስ ባይ?

(ማነው ምንትስ 'እሳት ወይ አበባ' - ጸጋዬ ገብረመድህን)

ፋሲል ሆቴል። ሰለሞን ገባ። አዜብ ሰለመችው። ሰላም አላት። ጂን አዘዘ። አዜብ አመጣችለት። ማን እንደ አዘዘ!

ሙዚቃ በጢ አለ። «አሰው አሰውና ሲደብረው ተኛ» ይላል ዘፈኑ። 'ሶል' ያዳምጣል። በልቡ አዘዛን ያዳምጣል።

አይ አዜብ!

አዜብ ጥሩ ልጅ ነች:: ነጠቃት ቆይቷል:: እዚች ቤት የዛሬ ሶስት ዓመት:: አልተለወጠችም:: ሰው አይለወጥም? ያደራ ዕቃ!

ያኔ... የመጀመሪያው ቀን ሲያውቃት፣ ሲታወቀው፣ ትዝ ይለዋል:-

«አዜዬ»

«ወዬ»

«አይደል ስምሽ?»

«አዎ ነብሴ!»

«ለመሆኑ ብዬሻለሁ?»

«ምኑን ነብሴ?»

«ደስ እንደምትይኝ?»

«አንተ ብቻ አይደለህም!»

«እህሳ?»

«ብዙ ሰው ይለኛል»

«እሯ?»

«ግርምሽ ይሙት!»

«ግርምሽ ደሞ ማነው?»

«ባሌ!»

«መች ያገባሽው?»

«ሳሚ የተወኝ ለታ»

«ሳሚ ለምን ተወሽ?»

«በኤርሚ ጠረጠረኝ»

«ኤርሚ ደሞ ማነው?»

«ወዳጄ!»

«እንዴት እንዴት ይወድሻል?»

«እንደ አስፋው፣ እንደ ታዬ፣ እንደ ፍቅሩ፣ እንደ አምባዬ፣ እንደ ጌትሽ፣ እንደ በቅሽ፣ እንደ...»

«በቃ፣ በቃ ተይው»

«ታዲያ ለምን ጠየቅከኝ?»

«ዝም ብዬ ነው፤ ይልቅ ቁጭ በይ»

«ምን ይገዛ?»

«ደስ ያለሽን»

«ኮኛክ ይገዛ መጣሁ...»

ይዛ መጣች:: አብረው አመሹ::

አብረው አደሩ:: ተፋቀሩ...

እና ዛሬም ጂኑን ይጠጣል::

ሙዚቃ ያዳምጣል:: አዜብን ያላምጣል::

አይ አዜብ!

ሀሳብ ፈረሰኛው ቼ!!

አዜብ ምንድነች?

ሽርሙጣ!

ሽርሙጣ ምንድነው?

አዜብ

ምናኗ ሽርሞጠ?

ሁለመናዋ።

ለመሆኑ እዚህ ለምን መጣሁ?

ልገዛናና።

ከማን ጋር?

ከአዜካ።

አዜካ ምንድነች?

ሽርሙጣ።

እኔስ?

«ማነው ምንትስ» ያለው ማነው?

ጸጋዬ ገብረመድህን፡-

«እና አንዳንዴ፣ አንዳንዴ ብቻ እኔው ከኔው ስመካከር

ከልቤ ጋር ስከራከር

ያው መቸም እኔም እንደሰው የሐቅ ራብ ነፍሴን ሲያመው -

«እኔንስ ያሉትን አሉኝ 'ግን እውነት ምንትስ ማነው'

እያልኩ ነው»

ይኼን እኮ ጺጋዬ አላለም::

ታዲያ ማነው ያለው?

ምንትስ ናት!

እሺ. ይሁን

ሲላስ ምን አለች?

«ያው መቸም እኔም እንደ ሰው፣ አንዳንዴ ሕሊናዬን ሰውነት ሲያምረው፣

ሰብሰብ ብዬ እማስበው፣ ቀድሞስ ቢሆን ለኔ ቢጤ የሔዋን ዘር፣ አዳሜ በኔ ላይ በቀር፣ ለኔ መስከሮ አይናገር፣

ብዬ ከልቤ ስማከር፣ ተጨብጨ እማብላላው

ያው መቸም እኔም እንደሰው

የሐቅ ራብ ነፍሴን ሲያከው፣ ልቤ ልቤን ሲሞግተው...

'እውነት ምንትስ ማነው?' እያለ ነው::»

ሴላስ?

አይ እንግዲህ ይበቃል

አዎ ይበቃል:: ሀሳብ መቼ ያልቃል? ያውም ደሞ ለምንትስ:: እኔ ለሷ አስባለሁ:: እሷ ግን አታስብም:: እንኳን ለኔ ለራሷ! ግን እኔ ብቻ ነኝ እንዴ አሳቢ? ብዙዎቹ ያስባሉ:: አስበውም ይፅፋሉ:: ያለቅሳሉ፤ ያስለቅሳሉ:: ምንትሶቹ ግን አያነቡም፤ አያለቅሱም:: ዝም ብለው ይዘመዘማሉ:: አሁን አሳብ ይብቃ- አለ ሰለሞን::

ሀሳብ ሄዶ ዝምታን ይጠራል፡ ዝምታ ሄዶ ሄዶ ድብርትን ይጠራል፡፡ ድብርት ሄዶ ሄዶ ድንኑን ይጠራል፡፡ ሶል ድጋሚ ጂን አዘዘ፡፡ አዙካ ታዘዘችው፡፡ ማን እንደጂን፡፡ ማን እንደ አዙካ!

ሙዚቃ ቢጤ አለ፡፡ ሶል ያዳምጣል፡፡ ጂኑን ይጠጣል፡፡ አዙካን ያላምጣል፡፡ አይ አዜብ!

ይኼኔኮ ብዙ በሽታ አላት፡፡ አባኮዱ- አባቶራ- አባ ቦምቢ- አባጭሬ- ጂሚ ኤልሣ- ጂሚ ኤድስን ግሳንግሱን... ግን ይኼ ሁሉ ለምን? አዜብ ምናረገች? እኛስ ብንሆን?

«እግዜር ቢተባበር የት ይደረስ ነበር!»

አዜብ መጣች፡፡ አጠገቡ ቁጭ አለች፡፡ ሁሉን ልታስረሳው፡፡ የተረሳች!

«አይ የኔ ነገር ጠፋሁ አይደል?»

«ምንም አይደል!»

«ዛሬ እንዴት በጊዜ መጣህ?»

«ስትናፍቂኝስ?»

«ሸሌ ቀን ቀን ትናፍቃለች?»

«ጨዋታ ቀይሪ!»

«ቀይሬያለሁ»

«አሁን ቀጥይ!»

«ሶልዬኮ ግን ጥፋት አልክ»

«ጠፋሁ እንዴ?»

«ታዲያስ ቆየህኮ»

«ሁሌኮ አይመችም»

«አዎ እንደ ሽርሙጣ»

«ጨዋታ ቀይሪ»

«ቀይሬያለሁ»

«አሁን ቀጥይ»

«ሶልዩ ሙት አሁንስ መረረኝ»

«ምኑ»

«ኑሮው»

«ሱኳር ብይበት»

«ትቀልድብኛለህ አይደል?»

«እኔኮ አይደለሁም»

«ምኑ?»

«የምቀልድብሽ»

«ታዲያ ማነው?»

«የፈጠረሽ ነው»

«እግዜርን ማለትህ ነው?»

«እግዜር ሥራ አላጣም»

«እንዴት?»

«አንቺን ሲያድቦለቡል አይውልማ!»

«አልገባኝም»

«እሱ ቢፈጥርሽ ይገባሽ ነበር»

«ነገርህ ሁሉ ግራ ነው»

«ምን ላድርግ፣ ጊዜው ግራኝ ነው»

«ሞዛዛ እንደሆንክ ግን ታውቃለህ?»

«እስቲ ሙት በይኝ»

«ሶልዩ ሙት!»

«እንዳፍሽ ያርግልኝ»

«ሂድ ሞዛዛ» (ተጠርታ ሄደች)

ስለሞን ብቻውን ነው:: ሙዚቃው እንዳለ ነው:: ሶል ያዳምጣል:: ጂኑን ይጠጣል:: አዙካን ያላምጣል:: አይ አዜብ

ሀሳብ ደግሞ መጣ:: ፈረሰኛው ቼ!!

ምናለ ደራሲ ብሆን?

ለምን?

አዙካን እፅፋት ነበራ?

ከዚያስ?

ዕውነትም ከዚያስ?

አዎ ከዚያስ?

ከዚያማ ትነበባለቻ!

ከዚያስ?

ትታወቃለች!

እሷ ወይስ እኔ?

እሱ ችግር አይፈጥርም

እሺ ይሁን ከዚያስ

ከዚያ በቃ ሰው ሁሉ ይወዳታል። በሕይወት ሳይሆን በመፅሐፍ?

አዎ ስትኖር ሳይሆን ስትፃፍ፤ እሱም እኮ ችግር ነው

ምኑ?

በመፅሐፍ ራሱ ማስወደዱ!

እንዴት?

ትልቅ የደራሲ ችሎታ ይጠይቃላ!

ጥሩ ደራሲ መሆንን?

አዎ ጥሩ ደራሲ መሆንን

አቤት ጣጣዋ

ገና መች አለቀና?

ደሞ ምን ቀረ?

ጥሩ ደራሲም ሲፅፋት?

እሺ ቢፅፋት?

ጥቅሟ ምኑ ላይ ነው?

እንዴት?

እስከዛሬ የተፃፉ ሸርሙጦች ምን ጠቀሙ?

ለማን?

ለአንባቢው!

አዎ እዚያም መሸርሞጥ ነው

አይ ሸርሙጣ! ሲያዩዋት ሸርሙጣ!

ሲጽፏት ሸርሙጣ፣ ስትነበብ ሸርሙጣ

"Once a whore forever a whore"

እስ እሱ ፈረንጅ::

ሀሳብ አያልቅም:: ሰውና ጂን ያልቃል:: ሌላ ጂን አዘዘ:: አዙካ ታዘዘችው:: ማን እንደ ጂን:: ማን እንደ አዙካ!

የሸርሙጣ ነገር ደሞ ሲጀምራት ነው:: ሶልን ልትረሳው ነው:: ወደ እንዱ ሄደች:: ... ሳመች፣ ተሳመች:: ወንበር ሳበች:: ተቀማመጠች:: እንግዲህ ሶል አያት:: ሊቀና ነው እንዴ? አይቀናም::

ሰውዬው ምን አሏል?

ውስኪ.

ሶልስ?

ጂን

ታዲያ ምን አሰቡት?

ሸርሙጣ አሰቡት::

ደሞ እዩዋት ስትገለፍጥ:: ውሻ!

ግን ለምን በውሻ?

ምን ለያቸው?

ውሻክ ታማኝ ነው!

ግን ልክስክስ ነው

ምንድ ነው መልከስከስ?

ጭራ መቁላት

ያኮ ለፍቅር ነው

«ውሻ!» እየተባሉ?

ያ ደሞ ለጥቅም ነው

እና ይቺም ለገንዘብ

ድራሻቸውን ማጥፋት ነበር

የማገዝንላቸው መስሎኝ?

አዘን መች ወደዱ?

«Not tear but sight can touch a harlot»

ብሏል አሉ አንዱ::

እውነቱን ነው ግን... (አዘብ በመኻል መጣች)

ሀሳቡን ሳይጨርስ:: ጂኑን ግን አስጨረሰችው:: ሌላ ቅጂልኝ አላት:: ልታመጣ ሄደች:: አይ አካሄድ! አይ አለባበስ! አንዳንዶስ ሽርሙጣ ትልበስ:: ግን ደግሞ...

ጂኑን አመጣችለት:: አጠገቡም ተቀመጠች:: ደሞ ትንሽ ቆይታ ልትሄድ:: ንፋስና ሽርሙጣ አንድ ናቸው:: ደሞ ማሯን ልታንጠባጥብ ነው «ከጋለሞታ ሴት ከንፈር፣ ማር ይንጠባጠባል» ብሎ የል መፅሐፉ!

«ጠፋሁ አይደል ሶልዬ?»

«እዚያጋ ስታብሪ አይቼሻለሁ»

«ለካ ታየኝ ነበር?»

«ያውም በቅናት»

«ኧረ?»

«ከጁን ይነጥለኝ!»

«ከኔስ?»

«አንቺማ ተነጠልሽ!»

«ደሞ እንዲህ ሆንኩ?»

«ታዲያስ!»

«እንዴት?»

«ውስኪ አማረሽ!»

«ሸርሙጣ እኮ ነኝ!»

«ጨዋታ ቀይሪ»

«አልቀይርም!»

«እንዴት?»

«አትነዝንዘኛ!»

«የዘፈን ዳርዳሩ...»

«ብሬክ ነው!»

«እና?»

«ለቀቅ»

«አልገባኝም!»

«ሚስት አይደለሁም»

«እና»

«አይጨቅጭቅን»

«ይሄ ደሞ ምንኛ ነው»

«ሸርሙጣኛ» (ባስቸኳይ ተጠርታ ሄደች)

ሀሳብ ፈረሰኛ ቼ!!

«ማነው ምነንትስ?»

ይኼማ የጸጋዬ ነው

አይደለም

እንዴት?

እሱ የጠየቀው ከሰው ሰው ነው

ጥያቄ ብቻ?

መልስም ሰጥቷል።

ምን ብሎ?

የአብዬን ወደ እምዬ ብሎ

እና?

ብቻዋን አልሸረሞጠችም

ታዲያ ይኸ ማለትስ?

አንተም ምንትስ ነህ

እኔው?

አዎ አንተም።

እሺ ባይኖሩስ?

እነማ?

ምንትሶቹ!

አሃ!

ምነው?

ነቃሁብህ

እንዴት?

የአንድ ታላቅ ሰው አባባል ትዝ አለኝ

ምን ብሎ ነበር?

«Prostitutes are a necessity without them men would attack respectable women in the street.»

(ሸርሙጦች አስፈላጊዎች ናቸው:: እነርሱ ባይኖሩ ኖሮ፣ ወንዶች መንገድ ላይ የሚዘዋወሩ የተከበሩ ሴቶችን በደፈሩ ነበር::)

እና?

ማነው ምንትስ?



# በአንድ የበልግ ወራት

ማክሲም ጐርኪይ
(ትርጉም) ትዕግስት ህሩይ

አንድ ጊዜ በአንድ የበልግ ወራት በጣም አስቸጋሪ ከሆነና ደስ ከማያሰኝ ሁኔታ ላይ ወድቄ ነበር፡፡ ገና በደረስኩበትና አንድም እንኳ የማውቀው ሰው ባልነበረበት ከተማ ውስጥ ኪሶቼ ቤሳቢስቱ አልባ እኔም መጠጊያ ቢስ ሆኜ ነበር፡፡

በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ውስጥ ከልብሶቼ መካከል

ቢታጠኑ አያጐሉኝም ያልኳቸውን ከሸጥኩ በኋላ ከተማዋን ለቅቄ ኡስትዩ ወደ ምትባል መንደር አቀናሁ:: መንደሪቱ የመርከቦች ማረፊያ ጣቢያ ስለነበረች መርከቦች በሚንቀሳቀሱባቸው ወራቶች ውስጥ የተሟሟቀ የሥራ ሕይወት የሚታይባት ናት:: አሁን ግን ወቅቱ የጥቅምት ወር መጨረሻ ስለነበር ጭር ብላለች::

እርጥቡን አሸዋ በእግሮቼ እየገላለጥኩና በውስጡ የተረፈ ምግብ አገኛለሁ በሚል ተስፋ በዓይኖቼ እየቃኘሁ ጭር ባሉት ሕንጻዎችና መደብሮች መካከል ብቻዬን ስዘዋወር በሀሳቤ አመጣና አወረድ የነበረው ሆድ እስኪሞላ ድረስ በልቶ መጥገብ ምን ያህል ጥሩ መሆኑን ነበር::

ካለው የባሕል ደረጃ አኳያ ከምግብ ርሀብ ይልቅ የመንፈስ ርሀብን ማርካት የቀለለ ነው:: በመንገዶች ላይ ከወዲያ ወዲህ ስትዘዋወሩ በውጭ እይታቸው መጥፎ ናቸው በማይባሉ፣ ስለ ውስጣዊ ገጽታቸው ጥሩነትም ደፍሮ ለመናገር በሚያስችሉ ሕንጻዎች ትከበባላችሁ:: ይህ ሁኔታም በውስጣችሁ ስለአርኪቴክቸር፣ ስለአካባቢ ንጽሕናና ስለሌሎችም ጥበቦች ደስ የሚያሰኝ ስሜትን ይቀሰቅሳል:: በመንገዳችሁም ጥሩ ጥሩ የሙቀት ልብሶችን የለበሱና የእናንተን መኖር አሳዛኝ ሐቅ ለመቀበል ባለመፈለጋቸው ከመንገድ ወጣ ብለው የሚያሳልፏችሁ ትሁት ሰዎች ያጋጥሟችኋል:: በተጨባጭ ሲታይ የተራብ ሰው ከጠገበው ይልቅ የተሻለና ጤናማ የሆነ የመንፈስ ምግብ ያገኛል::

ምሽቱ እየተቃረበ መጣ:: ዝናብ ይዘንባል፣ ከበስተሰሜን በኩል የሚነፍሰው ኃይለኛ ነፋስ በባዶዎቹ መደብሮችና በኪዎስኮች ላይ እያፏጨ አልፎ ከሆቴል ቤቶች የመስኮት እንጨቶች ጋር ይላተማል:: ከወንዙ የሚነሳው ኃይለኛ ማዕበል አረፋ እየደፈቀና ከፍተኛ ድምጽ እያሰማ በዳርቻዎቹ ካለው

አሸዋ ላይ ይንቿቿል:: ነጭ ሰንሰለት መስሎ ወደ ላይ የሚዘለው ማዕበልም አንዱ ሌላውን እየቀደመ፣ አንዱ ሌላውን እየተከተለ ድንግዝግዝ ወዳለው ጨለማ ይጣደፋል... የወንዙ ውኃ የክረምቱን መቃረብ በመፍራት፣ ምናልባትም በዚሁ ሌሊት ከሰሜን የሚነፍሰው ነፋስ ቅዝቃዜውን ሊያወርድበት ስለሚችል በብርድ ከመቆራፈድ ለማምለጥ ወደ ሆነ አቅጣጫ የሚፈተለክ ይመስላል:: ሰማዩ ክብድ፣ ጥቁር፣ ብሷል:: ለእይታ የሚያስቸግሩ የዝናብ ጠብታዎች ያሰዕረፍት ይወርዳሉ:: የከበበኝን አሳዛኝ የተፈጥሮ ገጽታ አጉልተው ያወጡት ደግሞ አስቀያሚ የሆኑት ሁለት ሰባራ ዛፎችና ከእነሱ ሥር ተገልብጦ የወደቀው ጀልባ እይታ ነበሩ::

ተገልብጦ የወደቀውና የተሰረገደው ጀልባ፣ ቅጠሎቻቸውን በቀዝቃዛው ነፋስ የተዘረፉት ዛፎች፣ ሁሉም አሮጌዎችና አሳዛኞች ሆነዋል::... የከበበኝ ሁሉ የፈራረሰ፣ ፍሬ አልባና ሙት ነበር:: ሰማዩ በተራው ያለማቋረጥ ያለቅሳል:: የአካባቢዬ ባዶና ጨለማ መሆን ሁሉንም የሚሞቱ ስላደረጋቸው እኔ ብቻዬን በሕይወት የቀረሁ፣ እኔም ደግሞ በተራዬ ቀዝቃዛ ሞትን የምጠብቅ አስመስሎታል::

በዚያን ጊዜ የአሥራ ሰባት ዓመት ወጣት ነበርኩ:: ጥሩ ዕድሜ ነበር::

በቀዝቃዛው አሸዋ ውስጥ ያለዕረፍት ብዙ ስንዝ ጥርሶቼ ስለርሀቡና ስለብርዱ ክብር ይንቀጫቀጩ ነበር:: ውጤት ባላስገኘ የምግብ ፍለጋ እየማሰንኩ፣ ከመደብሮቹ መካከል ወደ አንዱ ጓሮ በድንገት ዘው አልኩ:: በዚያም በዝናቡ የራስ ቀሚስ የለበሰችና ትከሻዋን ከመሬት አጣብቃ የተደፋች ሴት አየሁ:: ወደ እርሷም ተጠግቼ የምትሠራውን

ተመለከትኩ::

አሸዋውን በእጆቿ እየዛቀች ወደ መደብሩ የሚያስገባ ጉድጓድ ትቆፍራለች::

እኔም ከአጠገቧ ቁጢጥ ብዬ «ምን ሊያደርግልሽ ነው የምትቆፍረው?» በማለት ጠየቅኋት::

እሷም የለሆሳስ ድምጽ አሰምታ በእግሮቿ ቆመች:: ከአጠገቤ ቆማም ፍርሀት በአፈጠጣቸው ዓይኖቿ ስትመለከተኝ፣ በዕድሜዋ አቻዬ የሆነች፣ የሚያባባ፣ ግና ምን ያደርጋል ከሦስት ቦታ ላይ በዘጉኑ ምልክቶች የተዋበ ፊት ያላት ልጃገረድ መሆንዋን ተገነዘብኩ:: ምንም እንኳ የዘጉኑት ምልክቶች እርቀታቸውን የጠበቁ፣ ማለትም የተመጣጠነ መጠን ያላቸው ሁለቱ ከዓይኖቿ ሥር ሌላው ከፍ ያለው ደግሞ በግንባሯ ላይ ከመካፈያው ከፍ ብሎ ያረፈ ቢሆንም የፊቷን እይታ አሳዛኝ አድርገውታል:: የተመጣጠነ እርቀትን የጠበቁ መሆናቸውም ፊቷን የሰውን ልጆች ውበት በማጥፋቱ ጥበብ የረቀቀ ዕውቀት ያካበተ ሰዓሊ የዋለበት አስመስሎታል::

ልጂቱ አተኩራ ተመለከተችኝ፣ ከዓይኖቿ ይነበብ የነበረውም ፍርሀት ቀስ በቀስ ደበዘዘ:: ...በእጆቿ ላይ የነበረውን አሸዋ አራግፋ፣ በእራሷ ላይ ያሰረችውን የጥጥ ሻሽ ካስተካከለች በኋላ ከብርድ እንደመከላከል ብላ፣

«እርቦሀል? መብላት ትፈልጋለህ? አይደለም? ከሆነ በል አንተም ቆፍር፣ የእኔ እጆቼ ደክመዋል::» አለችኝ:: ከዚያም በጭንቅላቷ ወደ መደብሩ እያሳየች፣ «መደብሩ ሥራውን ስላላቆመ ከዚያ ዳቦ አይጠፋም::» በማለት ጠቆመችኝ:: ቁፋሮውን ተያያዝኩት:: እሷም ለትንሽ ጊዜ ያህል ከአጠገቤ ቆማ አያያዜን ካየች በኋላ በጐኔ ሆና ታግዘኝ

ጀመር።

በገዘምቷ ተወጠን ሥራችንን ቀጠልን። በዚያን ጊዜ አዋቂዎች በዘመናችሁ በማንኛውም ጊዜ ማስታወስ አለባችሁ ስለሚሏቸው ስለወንጀለኛ ሕግ፣ ስለሞራል፣ ስለንብረትና ስለሌሎች ጉዳዮች አስታውሼ ነበር ብዬ ለመናገር አልደፍርም። የእውነቱን ለመናገር በዚያን ወቅት ወደ መደብሩ የሚያስገባ ጉድጓድ በመቆፈሩ ተግባር ሙሉ በሙሉ ተወጠር ስለነበር፣ በመደብሩ ውስጥ ምን ይገኝ ይሆን? ከሚለው ሀሳብ በስተቀር ስለሌሎች ነገሮች ማሰቡን ጨርሶ ረስቼው ነበር።

ጨለማ እግሩን ሰደደ። ቀዝቃዛ፣ እርጥብና ብርዳማ የሆነው ጨለማም፣ በተለይ በእኛ አካባቢ ጨርሶ ድቅድቅ አለ። የማዕበሉ ድምፅ ቀደም ሲል ከነበረው ሲቀንስ፣ ዝናቡ በማየሉ በመደብሮቹ ጣውላዎች ላይ የሚያሰማው ድምጽ ኃይልም ፍጥነትም ጨመረ፣ ከሆነ ቦታ የተነፋ የሌሊት ዘበኛ ፊሽካ ተሰማን።

በመካከሉ ዕረዳቱ «ለመሆኑ ቤቱ ሳንቃ አለው ወይስ የለውም» በማለት ቀስ ብላ ጠየቀችኝ። በበኩሌ ስለምን እንደምታወራ ስላልገባኝ ምንም አልተናገርኩም።

«ትሰማኛለህ? መደብሩ ሳንቃ አለው ወይስ የለውም? ነው የምልህ። ሳንቃ ካለው ደግሞ ድካማችን ሁሉ ከንቱ ይሆናል። ጉድጓዱን ከቆፈርን በኋላ ወፋፍራም ሳንቃዎች ቢያጋጥሙን እንዴት አድርገን እንሰብራቸዋለን? የሚሻለው ቁልፉን ብንሰብር ነው... ቁልፉ የሚረባ ዓይነት አይደለም።» አለችኝ።

ጥሩ ጥሩ ሀሳቦች የሴቶችን አእምሮ የሚጐበኙት አልፎ አልፎ ይሁን እንጂ እንደምታዩት ሁሉ

ይጕበኙዋቸዋል። በበኩሌ ምንጊዜም ቢሆን ጥሩ ጥሩ ሀሳቦችን ስለማከብር በሚቻለኝ ሁሉ ሀሳቡን በሥራ ላይ ለማዋል ከመጣር አልቦዝንም።

ቁልፉን ካገኘሁ በኋላ በኃይል ስጕትተው ከነመጠርወሪያው ተነቀለ። ከዚያም ተባባሪዬ በተገኘው ቀዳዳ በኩል ወደ መደብሩ ለመግባት ወዲያውኑ ከመሬት ተደፋች፥ እንደ እባብ ተሳበች። ከዚያ ሁናም፣

«ጕበዝ!» በማለት የተናገረችው የአድናቆት ቃል አስተጋባ።

በግሌ የጥንቶቹን ታዋቂ ተናጋሪዎች ችሎታ ሁሉ ጠቅሎ የያዘ ነው ተብሎ ከሚነገርለት ወንድ ከምሰማው አድናቆትና ሙገሳ ይልቅ አንዲትም ቃል ብትሆን ከሴት የምሰማት ሙገሳ ትበልጥብኛለች። በዚያን ጊዜ ግን ሀሳቤ ያተኮረው በአነስተኛ ነገር ላይ ስለነበር ለወጣቷ የአድናቆት ቃላት ምንም ትኩረት ሳልሰጥ፣ ፍርሀት በሰፈነበት ስሜት በአጭሩ፣

«የሆነ ነገር አለ?» ስል ጠየቅኋት።

እሷም በተለመደ ድምጽ ያገኘችውን ሁሉ ቆጠረችልኝ።

«ጠርሙሶች የያዘ ዘንቢል... ባዶ ጆንያዎች ... ገንጥላ... የብረት ባሊ...»

የጠራችልኝ ሁሉ የማይበላ ስለነበር ጉጉቴና ተስፋዬ ሲከስም ታየኝ... ግን በድንገት ሕይወት ዘርታ በመጮኽ፣

«እሰይ! አገኘሁት...» አለችኝ። እኔም፣

«ምኑን?» አልኳት።

«ዳቦ፣ ክቡን ግን እርሷል... ተቀበለኝ!»

ተንከባሎ ከእግሬ ሥር የወደቀውን ክብ ዳቦ ከተል ብላ ጀግናዋ ተባባሪዬ ከአጠገቤ ስትደርስ፣ እኔ ገና ድሮ ዳቦውን ቆርሼ፣ ከአፌ ጉስጉሼ ማላመጥ ጀምሬአለሁ::

«በላ ስጠኝ?... ከዚህ ቦታ መሄድ አለብን:: ግን ወዴት መሄድ እንችላለን?» ካለች በኋላ በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ዙሪያዋን ቃኘች... ጊዜው ጨለማ፣ እርጥብና በድምፅ የተሞላ ነበር::... በመካከሉም«ከዚያ የተገለበጠ ጀልባ አለ ወደዚያ እንሂድ?» አለች::

«እንሂድ!» አልኳትና ዳቦአችንን እየገመጥን ተጓዝን:: ዝናቡ አይሏል፣ ወንዙ ይደነፋል፣ ከሆነ ሩቅ ቦታ ደግሞ ትልቅና ፍርሀት ምን መሆኑን የማያውቅ ፍጡር፣ አስከፊውን የበልግ ምሽትና እኛንም የምሽቱን ሁለት ጀግኖች ከምንም ሳይቆጥር በማንኛውም ነገርና ፍጡር ላይ በማሾፍ በረጅሙ ያፏጫል:: በፉጨቱ ልቤ ተሸብሯል:: ልቤ ይሸበር እንጂ ዳቦዬን የበላሁት ተንገብግቤ ነበር:: በዚህ ደግሞ ከበስተግራዬ አብራኝ የምትጓዘውም ልጃገረድ ከእኔ የምታንስ አልነበረችም:: በመካከሉ፣

«ስምሽ ማነው?» ስል የጠየቅኋት እንደዘበት ነበር::

«ናታሻ!» አለችኝ እያላመጠች::

ወጣቷን አትኩሬ ስመለከታት ከልቤ ላይ ሕመም ተሰማኝ:: እይታዬን ከፊት ለፊቱ ወደ አለው ጨለማ ስመልስ ደግሞ አሿፊዋ ዕድሌ እንቆቅልሽ የሆነና የቀዘቀዘ ፈገግታ የምታሰየኝ መሰለኝ::

በእንጨቱ ጀልባ ላይ ያለመታከት የሚወርደው ዝናብ የማያሰማው ድምፅ የሐዘን ስሜት ይፈጥራል፣ ንፋሱ ደግሞ በተራው በተገለበጠው ጀልባ ላይ ባገኘው ስንጥቅ

በኩል ሲያፏጭ የሚያንቀሳቅሰው የሆነ ቁራጭ ነገር ሲላተም የሚያሰማው በቅሬታ የተሞላ የመንቃቃት ድምጽ ሰላም ይነሳል:: ከወንዙ የሚመጣው ማዕበል በዳርቻው ላይ ሲንቦጫረቅ የሚያሰማው አንድ ወጥና ተስፋ አስቆራጭ ድምጽ የሚያጉረመርመው፣ ከሚችለው በላይ አስልቺና ከባድ ስለሆነበት፣ እስኪጸየፈው ድረስ ስለጠላው፣ ጥሎት ለመኮብለል ስለሚፈልገው፣ በፈለገው ዓይነት ሁኔታም ስለእሱ መናገር አስፈላጊ ነው ብሎ ስለሚለው ጉዳይ ነበር:: ከዚሁ የመንቦጫረቅ ድምጽ ጋር የዝናቡ ሹክሹክታ አብሮ ተቀላቅሏል:: በተገለበጠው ጀልባ አናት ላይ ደግሞ ብሩህና ሞቃታማው በጋ፣ ከብርዳማው፣ ከጨፈገገውና ከቀዝቃዛው በልግ ጋር በሚያደረጉት ዘላለማዊ መፈራረቅ ከተቀየመውና ከተዳከመው መሬት የሚወጣው ረጅምና ከባድ ትንፋሽ ይንገዋለላል:: ንፋሱም ባዶ በሆነው የወንዝ ዳርቻና አረፋ በሚደፍቀው ወንዝ ላይ የውር ድንብሩን በሚያደርገው ግሥጋሴ የሚያሰማው አሳዛኝ ዜና ቅስም ይሰብራል::

በጀልባው ሥር ያገኘነው የመጠለያ ቦታ ምቾትን የተከላ፣ ጠባብና ቀዝቃዛ ከመሆኑም በላይ በተሸነቆረው ቀዳዳ በኩል ቀዝቃዛ የዝናብ ጠብታዎች ይወርዳሉ፤ ንፋሱም አልተገታ...፤በዝምታ ተውጠን በየተቀመጥንበት ብርዱ ያንቀጠቅጠን ነበር:: በዝያን ሰዓት መተኛት ፈልጌ የነበር መሆኑ አሁንም እንኳ ትዝ ይለኛል:: ናታሻ ጀርባዋን ከጀልባዋ ግድግዳ አስጠግታ ጭብጥብጥ ብላ በመቀመጧ ትንሽ ኳስ መስላለች:: እሷም እግሮቿን በእጆቿ አጥብቃ ይዛ አገጯን ደግሞ በጉልበቶቿ ላይ አሳርፋ ከተቀመጠችበት፣ በፈጠጡ ዓይኖቿ ወደ ወንዙ አትኩራ ስትመለከት እስከ መጨረሻው የተገለጡት ዓይኖቿ ከነጩ ፊቷና ከዓይኖቿ ሥር ከዘሎኑት ምልክቶች ጋር ሲታዩ በጣም ትልልቆች ሆነዋል:: ናታሻ በተቀመጠችበት እንደ ድንጋይ ደርቃለች:: የእሷም ዝምታና

አለመንቀሳቀስ ጕረቤቴን የመናፍሯት ስሜት አሳደረብኝ... እንድትናገር ላደርጋት ፈልጌ ነበር፣ ግን ከየት መጀመር እንዳለብኝ ግር አለኝ።

በመካከሉ እሷው እራሷ መናገር ጀመረች።

«ምን ዓይነት የተረገመች ሕይወት ናት!...» የተናገረችው እርግጥ፣ ጥርት አድርጋ ጥልቅ በሆነ ስሜት ነበር።

አነጋገሯ የቅሬታ አልነበረም። በተናገረቻቸው ቃላቶች ውስጥ የታዘለው ቸልተኝነት ቅሬታን የሚገልጽ አልነበረም። በምትችለው መጠን እስባ አውጥታና አውርዳ ድምጿን ጕላ አድርጋ ከተናገረችው የተረዳሁት ግልጽ ከሆነ ማጠቃለያ የደረሰች መሆኑን ስለነበር፣ እራሴን ቅራኔ ውስጥ ሳላስገባ ለመቃወም አልቻልኩም። ስለሆነም ዝም አልኩ። እሷ ግን የእኔን መኖር እንዳልተገነዘበች ሁሉ እንቅስቃሴ አልባ ሆና እንደተቀመጠች በዚያው ገፋችበት።

«ከሁሉም ለመገላገል በአሉብት ደርቆ መቅረት ይሻል ይሆን?» በማለት ናታሻ የተናገረችው ዝቅ ባለ ድምፅ በሀሳብ ተውጣ ነበር። አሁንም ከተናገረቻቸው ቃላቶች ውስጥ በአንዱም እንኳ ቅሬታ አልተስተጋባም። እሷም በአጠቃላይ ስለሕይወት አውጥታና አውርዳ፣ የእራሷንም ሁኔታ ገምግማ በተረጋጋ መንፈስ የደረሰችበት ማጠቃለያ፣ ሕይወት ከምታደርስባት ግፍና በደል እራሷን ለመከላከል ባሉበት ደርቆ ከመቅረት በስተቀር ሌላ ለማድረግ የምትችለው ነገር አለመኖሩን ነበር።

በበኩሌ ይህን የመሰለውን ግልጽ አስተሳሰብ ስሰማ ልቋቋመው ያልቻልኩት ነገር ተናነቀኝ። በዚህን ሁኔታ በዝምታዬ ከቀጠልኩ ማልቀሴ ላይቀር ሆነ።... ይህ ደግሞ

ከሴት ልጅ ፊት፣ ከዚያም በላይ እሷ ሳታለቅስ ማልቀስ እሳፋሪ ነበር:: በመጨረሻም ከዚህ ለመዳን ስል ላነጋግራት ወሰንኩ::

«ለመሆኑ የመታሽ ማን ነው?» ስል የጠየኳት ከዚህ የተሻለ ጥያቄ ለማሰብ ባለመቻሌ ነበር::

«እንደተለመደው ያው ፖሹ ነዋ!...» የመለሰችልኝ በተረጋጋ ሁኔታ ጉላ ባለ ድምጽ ነበር::

«እሱ ማን ነው?»

«ወዳጄ...ዳቦ ጋጋሪው::...»

«ብዙ ጊዜ ይደበድብሻል?...»

«በስከረ ቁጥር ይመታኛል::...»

ከዚያም፣ ሳላስበው ድንገት ወደ እኔ ተጠግታ በመቀመጥ ስለ እራሷ፣ ስለ ፖሹና በሁለቱ መካከል ስላለው ግንኙነት ታጫውተኝ ጀመር:: ናታሻ፣ እንደምታውቁት ሁሉ፣ «...ከሆኑት ሴቶች መካከል አንዷ» ስትሆን ፖሹ ደግሞ ባለ ቀይ ጺም ዳቦ ጋጋሪ ነው:: አኮርዲዮን ሲጫወት ሌላ ነው:: እሱም ናታሻን ፍለጋ «ወደ ቡና ቤቱ» ይመጣል:: እሷም ፖሹ ደስተኛና ልብሶቹ የፀዱ ስለነበሩ ትወደዋለች:: የኮቱ ዋጋ 15 ሩብል ሲሆን ቦት ጫማው ደግሞ ከለስላሳና ጨምደድ ካለ ቆዳ የተሠራ ነበር:: በእነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ናታሻ ፖሹን ወዳዋለች:: እና እሱም «ልዩ ወዳጇ» ሆኖአል:: ታዲያ «ልዩ ወዳጅዋ» ፖሹ ሌሎቹ ደንበኞቿ ለከረሜላ እያሉ የሚሰጧትን ገንዘብ ነጥቆ በመውሰድ ጠጥቶበት ሲሰክር እሷኑ ይደበድባታል:: ይህም ይሁን ግዴለም የከፋው ነገር የመጣው ዓይኗ እያየ ከሌሎች ሴቶች ጋር መውጣት ሲጀምር ነው::

«ታዲያ በዚህ እንዴት አልከፋ? እኔ ከተቀሩት፣ ከሌሎቹ

የማንስ አይደለሁም!... በእኔ ላይ ማሾፉ ነው... ይህ አረመኔ! ከትላንትና ወዲያ ከቡና ቤቱ ኋላ ፌቃድ ተቀብዬ ወደ እሱ ብሄድ ዱንነን ስከር ብላ ከእሱ ጋር አገኘኋት:: እሱም ጥንብዝ ብሎ ነበር:: ታዲያ ንድድ ብሎኝ አንተ አረመኔ ነህ፣ አረመኔ! አልኩት:: እሱም እንዳልሞት እንዳልድን አድርጎ ደበደበኝ፣ በእግሩ እረገጠኝ፣ ፀጉሬን ጎተተው... ይህም ባልከፋ የለበስኩትን ሁሉ ቀዳደደው... አሁን ምን ልሁን? የቡና ቤቱን ባለቤት ዓይን እንደዚት ሆኜ ነው የማየው? ቀሚሴን፣ ሹራቤን፣ ሁሉንም ነው የቀደደው... ሁሉም አዳዲሶች ነበሩ ... ሻሼንም ከራሴ ላይ ገፎ ጥሎታል... ውይ! የአምላክ ያለህ! አሁን ምን አባቴን ላድርግ?» ያለችው በድንነት፣ ከፍ ባለ፣ በሀዘን በተመላና በጎረነነ ድምጽ ነበር::

የነፋሱ ቅዝቃዜ ከቀድሞው አይሏል:: የእኔም ጥርሶች መንቀጫቀጩን እንደገና ተያይዘውታል:: እሷንም ብርዱ ስላከራመታት ወደ እኔ በጣሙን ተጠግታ ከመቀመጧ የተነሳ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ዓይኖቿ ሲያበሩ ይታዩኝ ነበር::

«እናንተ ወንዶች! ሁላችሁም የተረገማች ናችሁ! ሁላችሁንም በእግሬ ረጋግጬ አካለ ጎዶሎ ነበር የማደርጋችሁ፣ ማንቁርታችሁን ሰንጎ ነበር ማስተንፈስ፣ ... ፖሸነንማ በፊቱ ላይ ነበር የምተፋበት፣... በዚህም ደግሞ አዘኔታ አይሰማኝም ነበር:: ወንዶች ስትባሉ እርጉሞች ናችሁ:: ስትለምኑና ስትለማመጡ እንደ ክፉ ውሻ ጭራችሁን ትቆላላችሁ፣ የምታገዝኑላችሁ ሞኝ ሴት ካጋጠማችሁማ ዓለምን ገዛችሁ ማለት ነው! በዚያው ልክ ደግሞ ሴቲቱ የገጠማት ምን መሆኑን ገና በወጉ ሳታጣራ ድሮ ገና ከጫማችሁ ሥር ጥላችኋታል... እርጉሞች!...»

ያወረደችው ስድብ፣ ዓይነቱ የበዛ ይሁን እንጂ አባባሏ

ከኃይለኛ ስሜት፣ ከቅያሜና ከጥላቻ አልነበረም:: ከስድቦቹ ጋር ይህን አልሰማሁም:: በአጠቃላይ በአነጋገሯ የተረጋጋች፣ ድምጿም የተከፋ ይሁን እንጂ አንድ ወጥ ስለነበር ቅላጼዋ ከምትናገረው ጋር የተጣጣመ አልነበረም::

ይህም ሆኖ አጠቃላይ ሁኔታው፣ ቀደም ሲል በኋላም ዘግየት ብሎ አልፎም እስከ ዛሬ ድረስ ከሰማኋቸውና ከአነበብኳቸው ድንቅና አሳማኝ ናቸው ከሚባሉት ፔሴሚስት ንግግሮችና መጽሐፎች ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ ስሜቴን ነክቶታል:: እንደምትገነዘቡት ሁሉ ይህ ሊሆን የቻለበት አቢይ ምክንያት የሚሞት ሰው ጣር፣ ሞት፣ በትክክልና በሥነጥበባዊ ውበት ከተገለጸባቸው ሥራዎች ይልቅ ሁልጊዜም እውነተኛና ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ነው::

የመጨፍገግና የመክበድ ስሜት ተሰማኝ:: ይህ ስሜት ሊሰማኝ የቻለው ደባሌ ካደረገችው ንግግር ሳይሆን ከብርዱ ነበር:: ቀስ ብዬም በማቃሰት ጥርሶቼን አፋጨሁ::

ከዚያም ከመቅፅበት ሁለት ቀዝቃዛ እጆች ከሰውነቴ አረፉ:: አንዱ አንገቴን ሲዳብስ ሌላው ፊቴን ሲዳስስ፣ በዚያው ጊዜ ውስጥ ደግሞ በአስጨናቂ፣ ለስለስ ባለና በአቆላማጭ ድምጽ፣

«ምን ነካህ? ምን ሆንክ?» የሚል ጥያቄ ቀረበልኝ::

በበኩሌ ይህንን ጥያቄ ያቀረበችልኝ፣ ከደቂቃዎች በፊት ወንዶች ሁሉ የተረገማችሁ ናችሁ በማለት የሁላችንንም ሞት የተመኘችልን ናታሻ ሳትሆን ሌላ ሴት ናት ብዬ ለማለት ዝግጁ ነበርኩ:: ነገር ግን ናታሻ ይህን ሁሉ ቀድማ በመጣደፍና በመቻኮል ንግግሯን ቀጥላ፣

«ምነው ምን ሆንክ? በረደህ? ቆፈን ያዘህ? ምን ዓይነቱ

ነህ ልጄ፣ ዝም ትላለህ? ብርድ የያዘህ መሆኑን ቀደም አርገህ ብትነግረኝ ምን ነበረበት... በል አሁንም ከመሬቱ ላይ ተዘርግተህ ተኛ... እኔም እተኛለሁ... ጠበቅ አርገህ... በል አሁን ይሞቅሀል... በኋላ ደግሞ... ጀርባችንን ገጥመን እንተኛለን... እንደምንም ብለን ሌሊቱን እናሳልፋለን:: ምን ሆነህ ነው? ጠጥተህ ነበር? ለምን ከሥራ አስወጡህ?... ምንም አይደለም!...» አለችኝ::

ናታሻ ልታጽጽናናኝ ... እና መንፈሴን ልታድስልኝ በብዙ ሞከራለች::

ምን ዓይነቱ እርጉም ነኝ? ሕይወትስ ምን ያህል አሹፋብኛለች? እስቲ እናንተም አስቡት? እኔ እኮ በዚያን ሰዓት ስለሰው ልጆች ዕጣ ፈንታ ተጨናቂና ተጠባቢ ሆኜ ማኅበራዊ ሥርዓቱን እንደገና ለመገንባት፣ ስለፖለቲካ ለውጦች የማልም ሰው ነበርኩ:: ይህም ብቻ አይደለም፣ የአስተሳሰብ ጥልቀታቸውን ምናልባትም እራሳቸው ደራሲዎቻቸው በውል ያልተገነዘቧቸውንና የተለያዩ ጠበብት የጻፏቸውን መጻሕፍት አንብ ስለነበር፣ በተቻለኝ ሁሉ እራሴን «ንቃተ ሕሊናው የዳበረ ከፍተኛ ኃይል» ለማድረግ በመዘጋጀት ላይ ነበርኩ:: ጉዳዩ ይህ ሆኖ ሳለ ለአካሌ ሙቀትን የሰጠችው፣ በሕይወት ውስጥ ቦታና ዋጋ የሌላት አካሏን ሸጣ የምትኖር፣ የተከፋች፣ የተደበደበችና ተስፋ የቆረጠች ሴት ሆነች! በእኔ በኩል ግን ከእሷ ቀደም ብዬ እሷ የረዳችኝን ያህል እንኳ እሷን ለመርዳት ጨርሶ አላሰብኩም ነበር::

ወይ ጉድ! በበኩሌ የሆነው ነገር ሁሉ የሆነው በሕልሜ ነው ብሎ ለማሰብ ዝግጁ ነበርኩ::

ግን ደግሞ ይህንን ለማሰብ ጨርሶ አይቻለኝም ነበር::

ምክንያቱም ቀዝቃዛዎቹ የዝናብ ጠብታዎች በላዬ ሲንጠባጠቡ፣ ከደረቱ ላይ ደግሞ የሴት ልጅ ደረት በጣሙን ተጠግቶ ያረፈበት ከመሆኑም በላይ፣ ምንም እንኳ የቮድካ ጠረን ቢታከልበትም ሞቃት የሆነው ትንፋሿ ፊቴን ሲያውደው ይሰማኛል... ሕይወትን የሚያድስ ትንፋሽ፣ ንፋሱ ያፏጫል፣ የዝናቡ ጠብታዎች ጆልባውን ይደበድባሉ፣ ማዕበሉ ይጨፍራል፣ እኛ ሁለታችን ደግሞ ምንም እንኳን እቅፍቅፍ ብለን ብንተኛም ከብርዱ ኃይለኛነት የተነሳ እንንቀጠቀጣለን:: ይህ ሁሉም ተጨባጭ የሆነ እውነታ ነበር:: በግሌም ያንን እውነታ የመሰለ ከባድና አሰቃቂ ሕልም ማንም አይቶ የማያውቅ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ::

ናታሻ ግን በዚሁ ሁሉ ጊዜ ስለሆነ ነገር ታወራኝ ነበር:: አወራሯ ሴቶች ብቻ ሊያደርጉት እንደሚችሉት በቁልምጫና በስሜት ነበር:: የናታሻን የዋህ የቁልምጫ ንግግሮች ተከትሎ በውስጤ አነስተኛ እሳት ተያያዘ፣ ከእሳቱ ሙቀት የተነሳም በልቤ ውስጥ የሆነ ነገር ቀሰጠ::

ታዲያ በዚያን ጊዜ ዓይኖቼን ፈንቅሎ የፈሰሰው እንባ፣ ከዚያ ሌሊት በፊት በልቤ ውስጥ ተከማችቶ የነበረውን ክፋት፣ ናፍቆት፣ ሞኝነትና ቆሻሻ አጥቦ ይዞት ወረደ:: ... ናታሻ ልታረጋጋኝ፣ ልታስደስተኝ በመሞከር፣

«በቃ ተወው! የእኔ ውድ! አታልቅስ፣ በቃ ተወው! በእግዚአብሔር ዕርዳታ ሁሉን ታልፈውና ሥራህን መልሰህ ታገኘዋለህ...» ወዘተ ትለኝ ነበር::

ከዚያም ብዙ ጊዜ ደግማ ደጋግማ ሳመችኝ:: ያለምንም ውጣ ውረድ አሳሳሟ ልባዊና የጋለ ነበር::

እነሱም ለእኔ ሕይወት የለገሰችኝ ከሴት ልጅ ያገኘኋቸው የመጀመሪያዎቹና ከሁሉም የበለጡት መሳሞች ነበሩ::

ምክንያቱም ከዚያ በኋላ ያገኘኋቸው ሁሉ በቀላሉ ያልተገኙና በተጨባጭ ደግሞ ምንም ያላስገኙልኝ ነበሩ::

«በቃህ አታልቅስ! የምትሄድበት ቦታ የሌለህ ከሆንክ እኔ ነገውን የሆነ ቦታ አገኝልሀለሁ...» በሹክሹክታ የነገረችኝን ይህን መሳዩን ማረጋጊያ የሰማሁት በእንቅልፍ ዓለም ውስጥ እንዳለሁ ያህል ሆኘ ነበር::

...እስከ ንጋቱ ድረስ አንዳችን በአንዳችን እቅፍ ውስጥ እንዳለን ተኛን::

ጠዋት ሲነጋ፣ ከጀልባው ሥር ተስበን ወጥተን ወደ ከተማ አመራን... ከዚያም የወዳጅ ሰላምታ ተለዋውጠን ዳግም ላንገናኝ ተለያየን::

በበኩሌ በአንድ የበልግ ወራት የገለጽኩላችሁን ሌሊት አብሬያት ያሳለፍኳትን ውዲቱን ናታሻ ለማግኘት ስድስት ወራት ሙሉ በየመንደሩ ፈልጌአታለሁ:: አላገኘኋትም::

ናታሻ ሞታ ከሆነ ምንኛ ደግ ነገር ነው! የሰላም ዕረፍት ያድርግላት! በሕይወት ያለች ከሆነ ደግሞ ሰላሙን ያውርድላት:: በልቧ ኃጢአትን አስባ አትሽበር፤ በሕይወቷ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አያስከትልም:: ትርፉ ስቃይ ብቻ ይሆንባታል...



# ሙዚቃ



# የተሻለ ኑሮ ፍለጋ

ተስፋዬ ገብረአብ

እንቁጣጣሽና መልአክ በሰርግ ባይጋቡም ባንድ ጣሪያ ስር መኖር ከጀመሩ ውለው አድረዋል:: በመካከላቸው ፍቅር እንጂ ጠብ አይታሰብም:: ታዲያ በአንድ ቅዳሜ ማምሺያ እንደ ወትሮው ቡና ተፈልቶ፣ ጨዋታው ደርቶ፣ ቤታቸው ሞቆ፣ በሳቁና በቀልዱ ደማምቆ፣ ሁሉም ነገር አምሮ ሳለ እንቁጣጣሽ እንዲህ ስትል ያልተለመደ ወግ ጀመረች፣

«መልአከ»

«እንቁዬ»

«አንድ ጠቃሚ ነገር ላማክርህ ፈልጌ ነበር...»

«ምንድነው የኔ ሸጋ?»

«እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፉ ሊደላን አልቻለም:: ያንተ ሰባት መቶ ብር የወር ደሞዝም የበቃችን አይመስለኝም:: ቤት ኪራይ አደቀቀን፣ የታክሲ ወጪ የዋዛ አይደለም:: የጤፍም ዋጋ ናረ:: ኢትዮጵያ ሰርተው የሚሻሻሉበት አገር አልሆነም:: ወደፊት ላሰብ ነው የጋብቻችን ድግስ ይቅርና ሳንቸገር መኖር አቅቶናል:: ድሆች ባንሆንም ሀብታሞችም አደለንም» ብላ በዝምታ ተዋጠች::

እንቁ ሞገስ ቆንጆ ልጅ ናት:: በጣም ቆንጆ ናት:: ያዩዋት ሁሉ ፈዝዘው ይቀራሉ:: አይናቸው ከደማቅ ቁንጅናዋ ጋር አብሮ ይንከራተታል:: ባንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው መልአከ ታዲያ ይህን አሳምሮ ያውቃል:: እሱም እጮኛውን ይወዳታል:: በሙሉ ስምዋ እንቁጣጣሽ ብሎ ጠርቶአት እንኳዋ አያውቅም:: እንቁዬ ነው የሚላት:: ከሰርጋቸው በፊት እነሆ አብረው ነው የሚኖሩት:: አንድ አመት ሞልቶአቸዋል:: ሰርጉ ደግሞ አምስት ወር ብቻ ነው የቀረው:: በሰርጋቸው መቃረቢያ ነበር እንቁ ይህን የኑሮ ችግር ወግ ያነሳችው::

«እንቁዬ...»

«ወዬ የኔ ውድ...»

«ኑሮ ከበደሽ?»

«እንዴት መሰለህ... የቤት እመቤት ሆኜ አላውቅም:: ስኩዋር አለቀ፣ ቅቤ ተወደደ፣ ያልኩበት ቀን አልነበረም:: እንዳልከው ትንሽ ከበደኝ:: ትዳር ፍቅር ብቻ ይመስለኝ ነበር:: ለካስ ፍቅር ብቻ አይደለም:: ኑሮን ማወቅም ነው:: ታዲያ ሰርጋችን እየቀረበ ሲመጣ ፈራሁ:: ትዳር ማለት በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ መቀርቀር መስሎ ተሰማኝ:: ሆኖም 'በሰባት መቶ ብር ደሞዝ ኑሮን እንዴት ነው የምንገፋው?' ብዬ ሳስብ ነው ፍርሀት ያስጨነቀኝ:: ሀብታም ከሆንን ግን ትዳር ፍቅር ብቻ ይሆናል አይደለም?»

«ሊሆን ይችል ይሆናል:: ሆኖም ሀብታም ለመሆን ደግሞ በጣም መስራት ያሻል:: ለምሳሌ የኔ ሰባት መቶ ብር በወር አለ:: አንቺ ስራ ብትይዢና አራት መቶ ወይም ሶስት መቶ ብር ብትጨምሪበት ወደ አንድ ሺህ እንጠጋለን:: በጣም ሳንቀናጣ ብዙም ደሞ ሳይቸግረን መኖር ያስችለናል:: ደሞ ማን ያውቃል? በየመካከሉ የግል ስራዎችን መሞካከር እንጀምር ይሆናል:: የገቢ ምንጫችንን ካሰፋነው ሀብታምነት ቅርብ ነው::»

«የኔ ውድ»

«ወዬ የኔ ሸጋ»

«እኔ ስራ ብይዝ ኑሮዋችን ከፍ የሚል ይመስልሃል?»

«በመጠኑ ይለወጣል!»

«አይምሰልህ?»

«እንዴት የኔ ቆንጆ? ...»

«አንድ ሺህ ብር ምን አላት?»

«የጐረቤታችንን ካየን ምንም የላት:: በራሳችን ጉጆ ዙሪያ

ካሰብን ግን አንድ ሺህ ብር ከፍተኛ ገቢ ነው፡፡»

«ይህን ርእስ ለምን እንዳነሳሁት አውቀሀል?»

«አላወቅሁም እንቁዬ...»

«የተሻለ ኑሮ ፍለጋ... እንድንጀምር ብዬ ነው?»

«ለምሳሌ እንዴት?»

«እኔ ለምን ወደ ውጭ ሀገር አልሄድም?»

«ውጭ ሀገር...»

«አዎ፤ ጀርመን ፍራንክፈርት ላይ አንድ አክስት አለችኝ፡፡ ባለፈው ሳምንት አንተ ለስራ ፊልድ ወጥተህ ሳለ ደውላልኝ ነበር፡፡ ሊወስደኝ እንደሚችል ነገረኝ፡፡ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ሊፈፅመው ይችላል፡፡ የግል ሬስቶራንት ከፍቶአል፡፡»

«የግል ሬስቶራንት?...»

«እኔና አንተ እንፋቀራለን፡፡ ከቶ ማን ያለያየናል፡፡ እኔ በጣም እወድሀለሁ፡፡ አይመስልህም?»

«አዎን ትወጂኛለሽ፡፡ እኔም በጣም አፈቅርሻለሁ፡፡»

«በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አንተን መንጥቄ ወደ ጀርመን ልወስድህ እችላለሁ፡፡ ከዚያም እዚህ ያሰብነውን ሰርጋችንን የጀርመን ሕዝብ ጉድ እስኪል ፍራንክፈርት ላይ እንደግሰዋለን፡፡»

«የጀርመን ህዝብ...» ብሎ ቅጭም አለ፡፡ የመሄድ ከፍተኛ ፍላጐትዋንም ፊትዋ ላይ አነበበ፡፡

«ተጠራጠርከኝ?» አለች አይንዋን እያንከራተተች፡፡

«እምንሻለሁ» ብሎ በጥልቅ ስሜት ውስጥ ሰጠመ::

«አንተ ያልከኝን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ::»

«ባታምኚበትም እኔ ያልኩሽን ልታደርጊ?...»

«አዎ!»

«ጥሩ አይደለም:: እኔና አንቺ መተማመን ነው ያለብን::»

«እኔ እኮ እወድሀለሁ» አለች:: እንባዋም ኰለል ብሎ ወረደ:: ውብትዋ ደመቀ:: መልአክ ተጨነቀ:: የእንቁጣጣሽን እንባ ቀመሰው::

«ስድስት ወር ተለያይተን ሀብታም መሆን ይሻለናል ወይስ እድሜ ልክ በዚህ መልኩ መኖር፤ ምረጥ?»

«ከተቻለ ስድስት ወር መለያየቱ ይሻላል:: ጥያቄው ግን ካልተቻለስ ነው?»

«ለምን አይቻልም?»

«እንጃ!»

«እኔ መቼም አልከዳህም አይደለም?»

«ሙቶ በሙቶ አምንሻለሁ»

«ታዲያ ምን ይሻላል ትላለህ?»

«ሂጂና እንሞክር:: ግን እኔን ወደ ጀርመን ለመውሰድ ከመሞከር አንቺ ጥቂት ሰርተሽ ብትመለሺ ጥሩ አይመስልሽም?»

«ይሄ ደሞ ባጣም የሚጥም ሀሳብ ነው» ብላ በደስታ ጮኸች:: በልዩ ፍቅር ላዩ ላይ ተጠምጥማ ሳመችው::

እየሳመችውም፣

«ስድስት ወር ሙሉ ሌላ እንትን ሳትነካ ትጠብቀኛለህ?»

«አንቺስ?» ሲል በቀልድ ጠየቃት።

እንባዋ ግጥም አለ። እንደገና በፍቅር ተሳሳሙ።

ከሶስት ወራት በሁዋላ እንቁጣጣሽ ኢትዮጵያን ለቀቀች። የጋብቻ ቀለበት አድርገው ነበር የተለያዩት። አምን ተለያዩ። እንቁጣጣሽ አይሮፕላን ውስጥ ስትገባ በእንባ ብዛት አይንዋ ሊፈነዳ ደርሶ ነበር - መልአከ አላስቻለውም። ጉዋደኞቹ እንዳይታዘቡት ሲል ብቻ ግማሽ ሀዘኑን ዋጥ አደረገው። እንቁ ሄደች። እሱ ቦሌ ከአይሮፕላን ጣቢያው ቀረ።

በሰላሳ ሶስተኛው ቀን የናፍቆት ደብዳቤዋ ደረሰው። መልስ ላከላት።

በሀምሳ አራተኛው ቀን ጂንስና ስኒከር ጫማ ላከችለት። በምላሹ ረዘም ያለ የፍቅር ደብዳቤ ላከላት። ከዚያ ወዲያ ድምፅዋም ደብዳቤዋም ቀረ። አራት ወር ጠበቀ። ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ደብዳቤ ላከ። የእንቁ ድምጽ ግን ጠፋ። ተስፋ ቆርጦ ደብዳቤ መላኩን ባቆመ በሁለተኛው አመት ግን ስለእንቁ ወሬ የሚነግረው አንድ ሰው አገኘ። ለስራ ወደ ፍራንክፈርት ተጉዞ የተመለሰ ኖሮአል። በወሬ ወሬ ተነስቶ እንቁጣጣሽ የምትባል አንድ ዘመድ እዚያ ከተማ እንደነበረችው መልአከ ወርወር ያደርጋል። ያ ሰው እንዲህ ሲል ነገረው።

«አ! እንቁ! ዘመድህ ኖራለች? የፍራንክፈርት አበባ! እዚያ ከተማ በሀበሾች ዘንድ ታዋቂ ናት። በአጉትዋ

ሬስቶራንት ትሰራለች፣ ሞዴሊስት ለመሆንም እየሰለጠነች ነው:: ጀርመንን ፈጥና እንደለመደች ይነገርላታል:: በጥቂት ቀናት ውስጥ ብዙ ተግባብተን ነበር:: ሚሊዬነር የመሆን ታላቅ ህልም አላት:: ብዙ እየሰራች ነው::»

መልአከ ማዶ ማዶ የአዲሳባን የክረምት ሰማይ ትክ ብሎ እየተመለከተ እንዲህ ሲል ጠየቀው::

«ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ የምታስብ ይመስልሀል?»

«አዬ ኢትዮጵያ! እንኳዋን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ፣ ኢትዮጵያ የሚባለውን ሀገር ራሱ ረስታዋለች:: ጀርመን ህይወትዋ ሆኗአል::»

መልአከ ይህን ወሬ ከሰማ በሁዋላ ለአንድ ወር ተኩል ያህል ለካራም ሰው ሆነ:: ገንዘቡ ሲሳሳበት ግን ማገናዘብ ጀመረ:: የእንቁን ፍቅር ከልቡ አሽቀንጥሮ መጣል እንደማይችል ቢያወቅም ጨርሶ ላለመውደቅ ሲል ሌላ ትዳር ለመመስረት ወሰነ::

ወደ ዘመዶቹም የገጠር ቀበሌ ሄዶ አንዲት ኰረዳ አጭቶ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ:: ከዚያም ሙሉ ጊዜውን ወደ ስራው በማዘንበል እንቁን ለመርሳት ጥረት ያደርግ ጀመር:: ታዲያ ይህ በሆነ በአራተኛው ወር ስራ ውሎ ሲመለስ ወይኒቱ የተባለችው አዲስዋ ባለቤቱ እንዲህ አለችው::

«አንቱዬ...»

«እባክሽ አንተ በይኝ... ባልሽ ነኝ እኮ::»

«እማላውእበትን?»

«እሺ. ምን ' ድነው?»

«ዛሬም ጮሀ ነበር-- ይቺ ነገረኛዬቱ...»

«ማን ነበር የደወለው?»

«ምናውኤ... ድምጥዋ አይሰማም... ተውጭ ነው አለች...»

«ማናት?... ምን አለችሽ?»

«ዋ እ! ግምኛ ነበርኩ:: ጭንእ... ጭንእ... ቲሰኝ ጊዜ ... እሳቸው ሲገቡ ጩሂ... እኔ አላእም ብዩ... ተውሀዋታ... እማላእበትን?!»

«በይ እሺ ራት አምጪልኝ!» አላት ከእንግዲህ ወደሁዋላ መመለስ እንደማይፈልግ እያውጠነጠነ፤ እንቁ በዚህ ወቅት ለምን እንዳስታወሰችው ግራ እየተጋባም በአሳብ ጭልጥ አለ:: ምንም ይሁን ምን ግን በአንድ ነገር እርግጠኛ ነው:: ከእንቁ ጋር ያለው የእንጀራ ገመድ ተበጥሶአል::


ወይኒቱ ከተዋጠበት ሀሳብ መለሰችው፣

«ዛሬ ቂጣ የለም:: ደሞ እንዳይቆጡኝ:: ሽሮሁን በልተው ነው የሚተኙት»


መልአከ ያልተለመደ አይነት ሳቅ አሰማ:: የዋድላ ደላንታዋ ወይኒቱ በጣም አሳቀችው:: በኑሮ የማደግ ስሜትዋ ከመንደርዋ ዙሪያ እንደማያልፍ እርግጠኛ ነበር:: እናም አንድ ምሳሌ አስታወሰ:: አዎ! ምሳሌው የሰው አይደለም:: የእግዚአብሄር ልጅ ነው:: እየሱስ የተባለው የእግዚአብሄር ልጅ ራሱ ባንድ ወቅት የተናገረው::

«እርሻው ብዙ ሰብል ያስገኘለት አንድ ሀብታም ሰው ነበር:: እርሱም በሀሳቡ ይህን ሁሉ እህል የማከማችበት ስፍራ ስለሌለኝ ምን ላድርግ? እያለ ያሰላስል ነበር:: እንዲህም

አለ የማደርገው ይህ ነው፣ ጎተራዎቼን ሁሉ አፈርስና ሌሎች ትልልቅ ጎተራዎች እሰራለሁ። በዚያ እህሌንና ንብረቴን ሁሉ ሰብስቤ አከማቻለሁ። ከዚህም በኋላ ራሴን አንተ ሰው እነሆ ለብዙ አመት የሚበቃህ ብዙ ሀብት አለህ፤ እንግዲህ እረፍት በማድረግ ተዝናና፣ ብላ ጠጣ፣ ደስ ይበልህ እለዋለሁ አለ። እግዚአብሄር ግን እንዲህ አለው አንተ ሞኝ! ዛሬ በዚህች ሌሊት ነፍስህ ካንተ ትወሰዳለች፤ ታዲያ ይህ ያከማቸኸው ሀብት ሁሉ ለማን ይሆናል?»



# ተገሳቢሎሽ



# የማን ዘር ጐመን ዘር?

## ደረጀ ደስታ

በጥቁርነቴ እኮራለሁ:: በአፍሪካዊነቴማ ለጉድ:: ደሞ ከአፍሪካም የጠራሁ ኢትዮጵያዊ ነኝ:: ማን እንደናት፣ ማን እንዳገር... የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ... ዘመድ ከዘመዱ... ከራስ በላይ ንፋስ... መጥኔ::

ከአገር ዘር- ከዘር ዘመድ- ከዘመድም ቤተሰብ- ከቤተሰብም ራስ... እያለ ውገናው እየጠበበ እየጠበበ ያው አይቀረው 'እኔነት' ከተፍ ይላል::

ለመሆኑ ማነው ዘረኛ? ወገንተኛ? እኔነኛ ልሆን? ማነው የእገሌን ዘር ያልናቀ? የእገሌንስ ዘር ያላወደሰ? ቢያንስ ሳት ብሎት ያላሽሟጠጠ? ያላንጓጠጠ? እጅ ሲያጥረው፣ ጭንቅላት ሲያንሰው፣ በኑሮ ውድድር ተረቶ ማካካሻውን ዘር ያልቆጠረ? ለአሸናፊው ማጣጣያ፣ የማንነት ምርመራ፣ የሐረግ ቆጠራ ያላካሄደ ማነው? መቸም «እኔ በናጼም ቃጥቶኝ አያውቅ» እማል ይበዛልና እንተወው::

ግን ደሞ ለምን እንተወዋለን?

ስንቱን ትተን እንችላለን? በሽታችንም ይኼ ሳይሆን አይቀርም:: እውነት እውነትነቱ ቀርቶ፣ ስምምነት ብቻ ሲሆን አልፎ አልፎ ማመሙ አይቀርም:: እውነት ተደብቆ ውሸት አስማምቶን ስንኖር ሳት ብሎት ወጣ ያለ ቀን ጉድ ይፈላል:: እየፈላም ነው:: እርግጥ ነው እውነት ሁሌ ሊያስማማን አይችልም:: ድርቅ ይልብንና ከእጅም አልፎ እግር እግር ይለናል:: የየዕለት ተራ ግንኙነቶቻችንን እንኳ ብናይ «የሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ» እያደረግን፣ በፈገግታ እየተዳለልን፣ ከእኔነት ይልቅ እኛነትን እየተቸን፣ ይበልጡኑ ደሞ እነሱነትን እያወገዝን እንለያያለን:: ዶሮ ጧት- ዶሮ ቀን- ዶሮ ማታ- ወደ ጉዳያችን እንመለስና ባይሆን እንዲህ እንጠይቅ:: ለመሆኑ ዘረኝነትን በሞኖፖል የያዘ የትኛው ነው?

ነጭ ጥቁርን ይንቃል:: ነጭም ነጭን:: ጥቁርም ጥቁርን እንዲሁ:: ነጭን እማንቅ ጥቁርም ሞልቷል:: አሁን እኛ እነዚያን (እነዚያን ነዋ! እነዚያን?) እንዴት ነው እምናያቸው? ቀድሞ ነገር እኮ ነጭም አይመስሉን:: ኧረ ምን ነጭ፣ ሰዎችም አይመስሉን:: ተዚህም ለየት ብሰው ደሞ ጥቁርም ነጭም

ያልሆኑ፡፡ ሁሉ ለኛ ጠብ ገላጋይነት እሚቃጣቸው፣ እነኚያ ክፍሎች እንደየሁኔታቸው ይናቃሉ፡፡ (በተለይ በእኛ ዘንድ) እንዲያውም ብዙ ጊዜ ከቁጥርም እሚገቡ አይመስለኝም፡፡ ለመናቅም እኮ ከቁጥር መግባት ያስፈልጋል፡፡

ግን ደሞ የዘር ግጭት በዘዴ ካልያዙት ይዳፈናል እንጂ አይጠፋም፡፡ አንድ አሜሪካዊ ፖለቲከኛ እንዳሉት «ዘረኝነት ትላንት- ዘረኝነት ዛሬ- ዘረኝነት ነገ...» ነውና 'ምን አዲስ ነገር አለ?' እንደማለት ነው አባባላቸው፡፡

እንዳንዶቻችን ለግጭት ደንታ ያለንም አንመስልም፡፡ ዘረኝነትን ስንቃወም ዘረኝነትን ይዘን ነው፡፡ ጋርዮሽነትን ይዘን አይደለም፡፡ የቅርብ የቅርቡን እንኳ ትተን ከሩቅ እንጀምር፡፡ «ምሳሌ ስጠኝ እንጂ ምሳሌ አታድርገኝ» ይባል የል! እንደዚያ ነው፡፡ በአሜሪካ ሎስ አንጀለስ የደረሰውን የዘር ጠብ እስኪመለስ ብለን እናስታውስ?፡፡ እዚህ ግቡ እማይባሉ ተራ ፖሊሶች አንዱን ጥቁር አላግባብ ወገሩት፡፡ ይውገሩት ግድየለም፤ ማንም ይወጋገራል፡፡ ግን የእጃቸውን ማግኘት ነበረባቸውና አላገኙም፡፡ ታዲያ ይሄ አያበሳጭም- ያሳርራል እንጂ፡፡

«እና ምን ማድረግ ይበጃል?» አሉ ጥቁሮች፡፡

እንጃ! እሱንም ለማለት ጊዜ የነበራቸው አልመሰሉም፡፡ አጠገባቸው ባለው ሁሉ ነገር መበቀል ነበረባቸውና ያገኙትን ሁሉ አነደዱት፡፡ ሰባበሩት፡፡ የነጭ የነጬን መኪና እያስቆሙ ወገሩት፡፡ 'እነ ከቤ ባጠፉት እየለን ጠፈጠፉት' አይነት፡፡ ታዲያ ነጮቹ አፀፋውን ለመውሰድ አልተቻኮሉም፡፡ ምን አልተቻኮሉም፡፡ ውጤቱ እማያምር በመሆኑ ሰከን ማለቱን

መረጡ:: ጦሱን ስለፈሩ አመዛዘኑ:: ወዲህ ደሞ ላገራቸው ስላሰቡ ኃላፊነት ተሰማቸው:: በአሜሪካ ሲሞጣሞጡና ሲሳሰቁ የነበሩ ሁሉ አፋቸውን ያዙ:: ወዲያውም ጨዋታ ቀየሩ::

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የፊልም ተዋናዩ የጆን ዌይን ዓይነቱ አባባል ትዝ የሚለኝ:: ባንወደውና ባንቀበለውም እንኳ እንዲህ ብሎ ነበር:: «ጥቁሮች ለኃላፊነት መብቃትን እስኪልተማሩ ድረስ በነጮች የበላይነት አምናለሁ::»

እርግጥ ነው ይህ አባባል ጥቁሮች ላይ ብቻ ያነጣጠረ ይምሰል እንጂ የአፍሪካን ትርምስምስ፣ የሱማሊያን ድቁስቁስ፣ የአንጐላንና ላይቤሪያን ጭርስርስ ስናስበው እንዳው ለእነዛ በቴሌቪዥን ከመሞታቸው አምስት ደቂቃ በፊት ለምናያቸው ሕፃናት ሲሉ እንኳ በፍቅር ቢሸናነፉ ማሰኘቱ አይቀርም:: በእነዚህ አገሮች አብዛኛው ጠቡ የዘር ወይም በዚያው አካባቢ በተመሰረተ የፖለቲካ ውገና ላይ የተመሰረተ ነው::

ይህ ሲባል ግን ነጮቹ በዚህ አይታሙም ማለት አይደለም:: ፈጠጥ ብሎ እሚታየውን የዩጐዝላቪያን፣ የራሺያን፣ ተሸጋግረን ውስጡ ውስጡን እያደባ ያለውን የአውሮፓንም ሁኔታ እንኳ ብናይ እንደውም እሱ ሳያስፈራ አይቀርም:: «ስኪን ሄድስ» እየተባሉ ስለሚጠሩት የኒዮናዚ ደጋፊዎች በጀርመን፤ «ሮማን ስኪን ሂድስ እና ሉምባርድ ሊግ» በጣሊያን፣ «የፈረንሳይ ብሔራዊ ግንባር» በፈረንሳይ ወዘተ. ስናይ «የማንዘር ጐመንዘር» ያሰኛል:: ዳር ዳር እየተባለለት ያለው የሰሜን እንግሊዙም መንገድ መንገዱን እያየ ያለ ጉዳይ ይመስላል:: የእስራኤሎችና የአረቦችማ

ዝም ነው::

ይህን ይህን ስናስብ እኛን ንቀው ጨርሰው እነሱ መባላት ከጀመሩ መቸስ ምን ይደረጋል:: ለራሳችን ስንል እየጣፈጥን፣ ተጠፋፍጠን መኖር የግዳችን ነው:: እንዲያውም ጥሩው ዘዴ እሱ ይመስለኛል:: እርግጥ ነው ነጮች ሰው መሆናችንን፣ ዛፍ ላይ አለመኖራችንን፣ እማሊለቅ (ከሰል ቢጤ) ቆዳ የሌለን መሆናችንን ቢያውቁልን ደግ ነው:: ለማመን ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን ያው በተግባር ማሳየት እንጂ ሌላው ዘዴ የትም አያደርስንም:: ትርፉ መዳረቅ ወይም የበለጠ ለስድብና ንቀት መመቻቸት ነው::

እውነቱ ግን ወዲህ ነው:: እነሱም አይጠቁሩ እኛም አንነጣም:: ሊለወጥ እማ.ችል ነገር የለም:: አለ ቢባል ግን መንገዱ ያው ሰልጥኖ፣ በልፅጎ፣ አውቆና ረቆ መገኘት ነው:: አንድ የአገራችን ልቦለድ ገፀ-ባህርይ እንዲህ ብሎ ነበር «መናቅና ማክበር የማንም ሞኖፖል አይደለም:: በግለሰብ፣ በኅብረተሰብ፣ እንዲሁም በብሔሮች ደረጃ የኖረ፣ ያለ፣ የሚኖር ነገር ነው:: እርግጥ ምዕራባውያን የቀረውን ዓለም- ነጭ ያልሆነውን ዘር ሁሉ- ዝቅ አድርገው ያያሉ:: ይኸም የመነጨው ከኃይል፣ ከሀብትና ከሥልጣኔ ደረጃቸው ነው:: እኛ ታዲያ ሁላችንም በአርአያ ሥላሴ የተፈጠርን ስለሆንን እኩል ነንና እባካችሁ እንደ እኩያችሁ ቁጠሩን እያልን ጉንጫችንን እናለፋለን:: መከበርን፣ እንደ እኩያ መቆጠርን ከፈለግን አይለን፣ ሰልጥነንና ከብረን መገኘት አለብን:: ይኸ ብቻ ነው እሚያዋጣው መንገድ::»

ይህ አሳብ እውነትነት ያለው ይመስላል:: ዘር ከልጓም እንዲሉ፣ የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ እንዲሉ፣ የማንዘር

ጉመንዘር እንዲሉ፤ ቤተሰቡ፤ ቤተዘመዱ፤ የሰፈሩ ልጅ፤ የወንዚ ልጅ፤ የባሕሩ ልጅ፤ የውቅያኖስ ልጅ... እንዲሉ መሳሳብ፤ መፈላለግ፤ መሻተት ሁሉም ዘንድ ያለ ነው።

አሁን አገራችን፤ እዚሁ አዲስ አበባችን እንኳ በየራሳቸው ቋንቋ በሚጠቀሙ ክፍሎች ዘንድ ብቻ ያለ ይምሰል እንጂ (ቋንቋው ስለሚያጋልባቸው) አማርኛ ተናጋሪው አማርኛ መናገሩን ብቻ ሽፋን እያደረገ እድሩን፤ እቁቡን፤ ሰበብ አስባቡን እየመነኘ የወንዝነቱን አብሮ ይወጣል። አያስታውቅበትም።

መጠኑ ይለያይ እንጂ ሌላው ቢቀር (እነሱ ራሳቸው ሆቴሎችን እንደሚጠሩት) ምኒልክ ሐውልት አካባቢ ካለው 'የጎንደር ኢምባሲ!' ብንጀምር፤ ለገሀር ስፖርት ኮሚሽን ወረድ ብሎ ያለውን 'ድሬደዋ ኢምባሲ' ጎጃም በረንዳ - የየወንዜው መገናኛ ነው። ወለጌውም ፒያሳና መርካቶ ባሉት ኢምባሲና ቆንስሎች አማካይነት ይገናኛል። ትግሬውም እንዲሁ ጨርቆስና ተክለሃይማኖት ባሉት ኢምባሲዎቹ ይፈላለጋል። ጉራጌውም መርካቶ ባሉት የተባበሩት ድርጅቶቹ ይገናኛል። እቁቡን በየንግዱ እያወራረደ ይጠጣል። ማን ይሆን? የትኛው ይሆን እማይፈላለገው? አዲስ አበቤውም ቢሆን የእናት የአባቱን ወንዝ ቢያገኝ አይምርም። እሚያስከሩ መስሎ ከታየው ይከራል። አልያም ውስጥ ውስጡን ይቆረቆራል። አይደለሁም ቢባል እንኳ «አንተ ማነህ?» መባሉ አይቀርም። ጭፍን አስተያየት በነገሰበት ጊዜ ማን ማንን ያምናል? ሆስፒታል ቢጤ ቢኖር፤ ይህን ነበር መታከም። የሌላኛውንም በሽታ ብቻ ማየትንም ጭምር።

ለማንኛውም እዚሁ እምንኖርባት እምንናቆር ይምሰለን እንጂ

ምንም አንሆን:: በጦርነት ታሪክ የተሸቆጠቆጠች አገር፣ በመከባበር ብቻ ሳይሆን በመገባበር የሰነባበተች አገር፣ የታሪኳ ገዘት ሌላ መልክ ሲይዝባት እርግጥ ነው ቅር ሊላት ይችላል:: መቸስ ምን ይደረግ ትቻለው:: ደሞም ሲያምራት ይቅር:: ፀባችን የውስጥ ነው:: መቸም 'ፀብ የለም' ብለን አንዋሽም:: አለ፤ ግን ይበርዳል:: ካላራገቡት ይሰክናል:: ካላሟረቱበት አገር ሰላም ይሆናል፡ የጭፍን የጅምላ አስተያየት ወይም ግምት ካልወሰዱ እርቅ ይወርዳል:: ደግ ደጉን ካስተዋሉ፣ ከተመኙ፣ ከተማመኑ፣ ፍቅር ይዘንባል:: ማንንም ወገን ቢሆን ቂም አስቋጥሮ ድል ከማድረግ በፍቅር መርታቱ ይመረጣል:: አንድ ነገር አንወሻሽም:: ሁላችንም የኢትዮጵያ ልጆች ነን:: ይህን ስናስብ ግን ኢትዮጵያ እንደ ከዚህ በፊቱ ከልጅ ልጅ ቢለዩ እንዳትሆን እየተጠነቀቀችልን ከሆነ ነው:: እሷ ካላዳላች ልጆቿ ተፋቅቅረው መኖር ይችላሉ:: መብት ሰስተው ግዴታውን አጥብቀው ፍቅር አይገኝም:: አለበለዚያማ የማንዘር ጉመን ዘር ማለቱ ይቀጥላል::

«የብሔራዊነት ስሜት በእኛ ተጽእኖ ብቻ መገለፅ አለበት» ማለትን የመሰለ ጠባብነት ደሞ የለም:: እንዳውም ፊጦ ከሚታየው ይኸኛው የበለጠ አሳፋሪ ነገር ነው:: «ኢትዮጵያዊ» ነን ማለቱ ብቻም አይበቃም:: እንዴት ዓይነት ኢትዮያዊ? እሚለውንም አብረን መመለስ መቻል አለብን:: ይህ ጥያቄ እዚሁ ውስጥ ለውስጥ፣ እዚሁ ባገራችን፣ በጎዳችን ሰው ሳይሰማን እምንመላለሰው ነው:: ገበናችን የኛው ነው:: በደፈናው አፍሪካዊ መባል እንዳልጠቀመን ሁሉ የኛም እንደዚሁ ነው:: ፈረንጆቹ እንደሚሉን

«አፍሪካውያን ለአስር ሺ ዓመታት ውኃ ላይ ሲያፈጡ እየዋሉ አንዲት መርከብ እንኳ መሥራት አልቻሉም» ነውና እንደው በደፈናው «አፍሪካዊ» መባሉ ለከንቱ ውዳሴና ጉራ ካልሆነ የጠቀመን የለም:: አፍሪካም በኛ በልጆቿ አልኮራችም::

በተረፈ ግን አፍሪካዊ ነኝ፣ ወይም ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ ወይም ትግሬ ነኝ፣ ወይም የጠራሁ አማራ ነኝ፣ ወይም በራሴ የገዳ ሲስተም አስተዳደር የኖርኩ የኮራሁ ኦሮሞ ነኝ ወዘተ... መባሉ ብቻውን ምንም አይጠቅምም:: ዋናው ሆኖ መገኘት ነው:: አንዱ የጥንት ፀሐፊ እንዳለው «እሚላስ እሚቀመስ ሳይኖረው ዝርያውን እየጠቀሰ ጉራውን እሚቸረችር ሰው ማለት ድንች ማለት ነው:: ልክ የድንች ድንችነት ከመሬት በታች እንደተቀበረው::»

እኛም ብንሆን እንዲሁ ነን:: ከሁለት ያጣ ባለመሆን ማካካሻውን አንኩራ ባልልም፣ ልመናና ኩራትን እስከመቼ አብረን እንደምናስኬድ አልገባኝም:: ያውም በእኛ ሳይሆን በእነሉሲ እየኮራን:: ለማንኛውም «ኩራት ራት አይሆንም» እንዲሉ ቢያንስ ዛሬን እናሸንፋት::: አለበለዚያ አንዱ እንዳለው «ዘርህን ገበያ ላከውና እሚገዛልህን እየው» እንዲባል ዘር ስንቆጥር ፀሐይ እንዳይጨልም:: እሱ ቀርቷል:: ሌላ ዘፈን ወጥቷል:: የማንዘር ጉመንዘር!

አለበለዚያማ ዘር ልቁጠር-ጉራ ልስፈር- ልሳኔ ልሳንህ-ልብሴ ልብስህ- ይሁንና ልሳንህን ዝጋው ወዘተ... ማለቱ እማይሆን ነው:: አልፎበታል:: እኔ ልወቅልህ፣ እኔ ልቆርቆርልህ እሚል የተኮፋሸ ሞግዚት ዛሬ እሚፈልግ ያለ አይመስለኝም:: ዛሬ እሚፈለገውስ የሥራ ውድድር ነው::

የነበርኩ ነበርኩ ሳይሆን፣ የነኝ ክርክር ነው:: እንግማ ካልሆነ እኔነቴን ልሁን ሲባል ባልተፈራ ባልተጠላ ነበር:: አይሆንም ባይ ተሟዛኝ ካለ ግን ቆሞ መቅረቱ ነው:: እንዲያውም «ቁርበት ምን ያንጓጓህል ቢሉት ባያድለኝ ነው እንጂ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ» አለ እንደሚባለው ወይም «አየወገንህ» ቢሉት «የመቶ አመት ቆዳ ከብት ተራ ቆመ» እንደሚባለው መሳቂያ መሳለቂያ መሆኑ አይቀርም::

አማርኛ መናገር ያልቻለውን ዶክተር አፍ እንዳልፈታ ሕፃን ቆጥሮ ካላዋቂ እሚደመርበትን ጊዜ ከእንግዲህ እሚመርጥ ያለ አይመስለኝም:: ቢያንስ በቋንቋ ሰዎችን የመገመት ልምድ እስካልቀረ ድረስ፣ ድንቁርናን በዘር ማካካስ ከተለመደበት ቦታ ድራሹ እስካልጠፋ ድረስ፣ የልብ አንድነት ሊኖር አይችልም:: ለራሳችሁ እወቁ:: እኛም የኛን እናውቃለን:: ያኔ እንተዋወቃለን:: አብረን በሰላም በአንድነት እንኖራለን:: ዋናው ለዚህ መታገል ነው:: የማንዘር ጉመንዝር!



# ሽሽት



# አጋፋሪ እንደሻውና አያድቡልቡሴ

ስብሐት ገብረእግዚአብሔር

(አጋፋሪ እንደሻው ፉከራቸው «እንደሻው አባ መክት፣ ሽሽት ጋሻው ከሞት ይመክት» መሆኑ እየተስታወሰ።'

አጋፋሪ እንደሻው በስድሳ ስድስት ዓመታቸው የሳምንት ስንቅ የተጫነ በቅሎአቸውን አስከትለው ከቤት የወጡ፣ ሞትን ሲሸሹ፣ ከሞት የሚስጥል ድግምት- ዕፅ፣ ወይም የሆነ ነገር ሲፈልጉ፣ ወይም ሞት የማይደርስበት ስፍራ ሲፈልጉ፣ ምድረ ሀበሻን ሲያዳርሱ ሲከልሱና ሲሰልሱ ሰላሳ ሶስት ዓመት ካስለፉ

በኋላ... በዘጠና ዘጠኝ ዓመታቸው ወደ አዲሳባ ተመለሱ::

በየአውራጃው፣ በየወረዳው፣ በየገዳሙ፣ በየደብሩ (በሹክሹክታ እንንገራችሁና — በየጠንቋይ ቤቱ፣ በየመጣፍ ገላጩ፣ በየኮከብ ቆጣሪው እና በየጠጠር ጣዪ ሳይቀር) ከሞት ማምለጫ ሲፈልጉ ሰላሳ ሶስት ዓመት ካሳለፉ በኋላ የመጨረሻ አዋቂ የተባለው ምን ይነግራቸዋል:-

የሞት መድኃኒት ሊገኝ የሚችለው ባዲሳባ ከተማ በተረት ሰፈር መግደላይት ቤተስኪያን መቃብር ቤት ከሚኖሩ አባ ሽንኩርት ከሚባሉት ባህታዊ ጋር በመመካከር ነው::

«እንሮዬ ያለውን ፍለጋ አገሩን አዳረስኩት?» አሉ አጋፋሪ ለራሳቸው:: ብቻ ያ ሁሉ ጉዞአቸው ምንም ያህል አልቆጫቸው:: እንዲያው ለምናልባቱ ሞትን ማምለጥ ቢያቅታቸው በማለት (ለመጠባበቂ ያህል) በየሄዱበት ዘራቸውን ዘርተዋል:: ከነዙት ሺና ሺ ዘር ስንቱ በቅሎ እንደሆነ ባያውቁም ቅሉ መዝራቱ ራሱ እጅግ በጣም አስደሳች ስለነበረ- ብዙው ባይበቅልም ያን ያህል አያሳስባቸውም::

አጋፋሪ እንደሻው ተረት ሰፈር ደርሰው፣ ሴጣን ቤትን እንደ ወዲህ ትተው የጆሮ ቆራጩን ቤት አልፈው (ጆሮአቸው እንዳይታይ ቀጭን ኩታቸውን በጥንቃቄ ተከናንበው ነው መቸስ የታወቀ ነው) የጭራቁን ግቢ አልፈው መግደላይት የት እንደሆነች ለመጠየቅ ሰው ሲፈልጉ:-

አዩት ዛፍ ስር ራቁቱን ተጋድሞ፣ አላፊ አግዳሚው እንዳያየው ነጠላውን ወደ መንገድ በኩል ጋርዶ:: አጋፋሪ ግን በበቅሎ በመሆናቸው ቁልቁል አዩት::

«ቤቶች!» እንዳይሉ ነጠላ ነው «ነጠላዎች!» እንዳይሉም ስድብ ሊመስል ይችላል፡፡ ስለዚህ «እንዴት ዋላችሁ!» አሉ ባጭሩ፡፡

«እንደነገሩ» አላቸው እሱ በበኩሉ፡፡ «እንዴት ማለት እንደነገሩ?» ቢሉት፣

«እንደሚያዩት ነዋ!»

(እንግዲህ «ወጉሳ መአረጉሳ» ሲለኝ ነው ብለው እያሰቡ)

«እንደማየውማ ነጠላውን መልበስ በተሻለ» አሉት፡፡

«ውስጡን ለማያውቅማ ይመስለዋል»

«ውስጡ ከውጪ የተለየ ነው?»

«ከመለየትም አልፎ ተገላቢጦሽ ነው፡፡»

«እንዴት ነው የተገላበጠው?»

«እሱንማ ለማወቅ ተረቴን፣ እውነቴን በእርጋታ መስማት ያሻል፡፡»

«ረጋ ልበልና ልስማዋ፡፡ ንገረኝ፡፡»

«ዋሸቹ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ» አላቸው፡፡

ውስጡን «እሱን ለሌላ ንገር!» እያሉ «በጀ!» አሉት፡፡

«እሱስ ምንም አልበጀ፡፡ ብቻ ልቀጥልልዎ፡፡ ግን እውነቴ ተረቴ ረዘም ያለ በመሆኑ ከበቅሎዎ ወርደው እዚች ጥላ ሥር አረፍ ብለው ቢያዳምጡኝ ይሻላል ይመስለኛል፡፡»

ወረዱ አጋፋሪ፣ ልጓሙን ገበሬ ተቀበለ፡፡ መጋረጃውን ነጠላ አልፈው «ሰውዬው አጠገብ ተቀመጡ፡፡ ነጠላው ከኮፈ

አግዳሚው ጋርዷቸዋል::

«ሰውዬው» ታሪኩን እንዲህ ሲል እንደገና ጀመረ:: «ዋሸቹ አላውቅም ከተፈጠርኩ፤ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ:: ማክሰኞ የወላጆቹ ሰርግ ተደገሰና ጠላው ተጠምቆ፣ ስንጋው ተጥሎ፣ ሲበላ አደግድጌ ሳሳልፍ አረፈድኩ:: እየተጠጣ ሲዘፈን ብዙ ከቆየ በኋላ ያ የደምቡ ሆነና ነው መሰል (ብራምባር ሰበረልዎ) ብለው መዝፈን ሲጀምሩ ጊዜ እንደማፈር አልኩ:: እውነት ብራምባሩ ገና አሁን ከተሰበረ እኔ ገና አልተወለድኩም፣ የለሁም ማለት ሊሆንብኝ ሆነ:: ቢበዛ ህልም ነኝ፣ ያውም የማን ህልም እንደሆንኩ እንኳን እንጃ ማለት ሊሆንብኝ ሆነ:: ምናልባት እኔ እውነት ተወልጄ ከሆነ ደግሞ ዘፈኑ አባቴን ውሽታም ወይም ውርደታም ወይም ሞኝ ሊያረግብኝ ሆነ:: እናቴንም ውሽታም ነውረኛ ሊያረግብኝ ሆነ:: ሲጨንቀኝ ጊዜ ቀስ ብዬ ከዳሱ ወጣሁ::

«ልክ እኔ ስወጣ እረኛችን ከወድያ መጣና ከሁሉ አብልጬ እምወዳት ላማችን መጥፋትዋን ነገረኝ:: ፍለጋ ተነሳሁ:: አገሩን አዳረስኩ:: ትልልቁ ዛፍ ላይ እየወጣሁ ዙሪያውን ብቃኝ ላሚቱ የለችም:: ያገራችንን ትልቁን ጋራ ወጥቼ ከጫፉ ላይ ያለውን ትልቅ ጥድ ወጥቼ ዙሪያውን ብመለከትም አጣሁት::

«ተስፋ ከመቁረጤ በፊት አንድ ቦታ ልሞክር አልኩና ከሁሉ ዝቅተኛ ሸለቆ ወርጄ እዚያ አንድ እጅግ የጠለቀ ጉድጓድ አለ፤ እጉድጓዱ ገባሁና በመርፌ ቀዳዳ አሻግሬ እመለከታለሁ:-

«ላሚቱን ስምንት ሌቦች ነድተው ወስደዋት ኖሮ፣ እጉንደር ገብተው አርደዋት ሲቀራመቱ ወለል ብለው

ታዩኝ።

«ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ። ዛሬ ማክሰኞ ነው።»

(«አርብ ነው እንጂ» አሉት አጋፋሪ።)

«ለናንተማ አርብ ነው። ለኔ ግን ማክሰኞ ነው። ከማክሰኞ ሳልወጣ ይኸው ሰላሳ ሶስት ዓመት ተንከራተትኩ»

(«ይህ እንዴት ይሆናል?» አሉት አጋፋሪ)

«ልንገርዎት አደል? ሌቦች ሳይበታተኑ ልድረስባቸው አልኩና በፍጥነት ፈረሴ ላይ ወጥቼ እንደ ደራሽ ወንዝ ስጋልብ እንደነፋስ ስሸመጥጥ ከፊት ለፊቴ አንድ ገደል እንደመቀመቅ አፉን ከፍቶ ሊውጠኝ ተዘጋጅቶ ታየኝ። ፈረሴን እየኮረኮርኩትና ባለንጋ ሾጥ እያደረኩት ከዚህኛው አፋፍ ተወረወርን። ፈረስ እንደዚያ ዘሎ ያውቅ አይመስለኝም። ግን አልሆነለትም። ገደል ገባና ተንከታከተ-- ኮርቻው ይዞኝ ተሻገረ።

«ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ።»

(«በጀ» አሉት አጋፋሪ።) ሌቦቹን ደረስኩባቸውና «ላሜን ውሰዱ» አልኳቸው

«እንክፈልህ» አሉኝ «ክፍያ አላውቅም። የምፈልገው ላሜን ነው» አልኳቸው

«መቶ ብር እንክፈልህ ሃያ ላም ይገዛል» አሉኝ

«ሃያ ላም አልፈልግም፣ ላሜን አምጡ»

«እንግድያው ይኸው ቆዳዋን ውሰድ። በስጋዋ ምትክ ስምንታችንም ስምንት ስምንት ፍሬ ጤፍ እንሰጥህ» አሉኝ

«እሺ. አልኩና በቆዳው ከበሮ ሰራሁበት። እውስጡ አንድ ዝምብ ከትቼበት ዛፍ ላይ ሰቀልኩት። ዝምቡ ከውስጥ ከበሮውን እየመታ ዙሪያውን እስከ ሰባት ወንዝ የሚኖሩ ሰዎች ሰባት ዓመት ሙሉ አስክስታ ወረዱበት።

«ዋሸቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ።»

(«እሺ» አሉት አጋፋሪ።)

ሌቦቹን ተሰናበትኩና ጤፌን በስልቻ ተሸክሜ ወዳገሬ ጉዞ ጀመርኩ። ልክ አገሬ ልገባ የስምንት ቀን መንገድ ሲቀረኝ ሀይለኛ ዝናብ ዘነበ። አብረውኝ ይጓዙ የነበሩ መንገደኞች ጉፈሬዬ ስር ተጠልለው ዝናቡን አሳልፉ። ግን ሳላስበው ውሃውን ከጠጉሬ አራገፍኩትና ወንዝ ሆኖ ጠራርጐ ወሰዳቸው።

«ዋሸቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ።»

(«ከዚያስ?» አሉት አጋፋሪ።)

ከዚያ ስልቻዬን ተሸክሜ መንገዴን ስቀጥል፣ ሰዎች ከኋላዬ 'ሰውዬው ጤፍህ ፈሰሰ' ሲሉ ሰማሁ።

ዘወር እላለሁ ጤፌ ድንቅ ሆኖ በቅሏል። እዚያው በዚያው እያየሁት አሸተና እዚያው ለአጨዳ ደረሰ። ታድያ በስላ ማጭድ ብለው ብለው ጨርሶ አልታጨድ አለኝ። በምን ልጨደው ይሆን? እያልኩ ሳስብ ከሩቅ ሁለት አሞራዎች ወደኔ በኩል እየበረሩ ሲመጡ አየሁ።

ጠመንጃዬን አቀባበልኩና አነጣጥሬ ብተኩስ አንደኛው አሞራ ደረቱን መታሁት። እሱ መብረሩን ቀጠለ።

ሁለተኛውን አሞራ ግን የዚያኛው ደም ተፈናጥሮ መታውና ክርብት ብሎ አጠገቤ ወደቀ:: አንድ ላባ ነጭቼ ጤፉን በሱ አጨድኩና ከመርኩት:: አቤት ክምር!

ስምንት በሬ አፈላለግኩና ላሄደው ብሞክር በጭራሽ አልተቻለም:: እንግዲያው እሺ አልኩና ስምንት ቱሀን ጠምጄ ሀይ በል ብለው ስምንት ስልቻ ጤፍ::

ስምንት ወደል አህያ አምጥቼ ልጭናቸው ብል አልቻሉትም:: ወገባቸው ሊሰበር ሆነ:: ዳውላዎቻቸውን አራገፍኩና ስምንት ጉንዳን ፈላልጌ ስምንት ስልቻ ጤፌን እነሱ ላይ ጭኜ መንገዴን ቀጠልኩ:: ዋሸቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ::

(«በጄ» አሉ አጋፋሪ እንደሻው)

የስምንት ቀን ጉዞ አልነበረም የቀረኝ፣ ስምንት ቀን ተጉዤ የት እንደደረስኩ እጠይቃለሁ:: ታዲያ ካገሬ የአስራ ስድስት ቀን ጉዞ ርቀት ላይ ነው ያለሁት::

ይህ ሁሉ- እናም ብዙ የተገላቢጦሽ ነገር- ሲደርስብኝ፣ አስራ አንድ ዓመት አለፈ:: በመጨረሻም ስምንቱን ጉንዳን እየነዳሁ አገሬ ገባሁ:: ቤት እደርሳለሁ:: ዳሱም እንዳለ ነው፣ ዘፈኑም ያው «ብራምባር ሰበረልዎ» ነው:: የማን ሰርግ ነው ብዬ ብጠይቅም ያው የወላጆቼ ሰርግ ነው::

ዋሸቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ::

(«በጄ» አሉ አጋፋሪ እንደሻው)

ተመልሼ ሸሸሁ

ከዚያ በኋላ የደረሰብኝን አንድ ባንድ ብነግርዎ

ማገሰልቸትም ይሆናል ብዙ ስለሆነ ከጉዳይዎ ማስተጓጉልም ይሆናል። ያው ሁሉም ተገላቢጦሽ ነው። ስለዚህ ተረቴ አውነቱ እንዲታይዎ ያህል ዋና ዋናውን ልንገርዎ።

(«እሺ» አሉ አጋፋሪ እንደሻው) ነፋስን መንገድ ላይ አገኘሁትና ውሰደኝ አለምንን አዞረኝ አልኩት። ግዙፎችን አልሸከምም አለኝ።

«የእናቴና ያባቴ ሀርግ ገና እየተደገሰ ነው። ገና ብራምባር ሰበረልዎ እየተዘፈነ ነው። ስለዚህ ገና አልተወለድኩም። እንኳን ልወለድ ገና አልተረገዝኩም። ግዙፍ ብመስልም ገና ረቂቅ ነኝ» አልኩት። እሺ አለኝና አለምን አዞረኝ። ለአሥራ አንድ ዓመት ብዙ ተገላቢጦሽ ነገር ከደረሰብኝ በኋላ፣ በግብፅ አርገን ተመለስንና ነፋስ ካነሳኝ መልሶ አስቀምጦኝ፣ መንገዱን፣ መንፈሱን ቀጠለ።

ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፤ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ።

(«አስቸጋሪ እጣ ነው ያንተስ» አሉ አጋፋሪነታቸው በልባቸው። «ከዚያስ» አሉ ባንደበታቸው፣ ባንድ በኩል «ሰውዬው» እያሳዘናቸው በሌላ በኩል ነገሩን ማመን እያስ ቸገራቸው።»

ከዚያማ አዛውንቱን ተሰናብቼ ወጣሁ፤ አሁንም ካገሬ መውጣት አሰብኝ ብዬ ስሄድ ልክ ካስራ አንድ ዓመት በፊት ንፋስን አገኘሁበት ቦታ፤ ከዚያ በፊት ደግሞ አስራ አንድ ዓመት አስቀድሞ እረኞችን ላሚቱ ጠፋች ያለኝ ቦታ ስደርስ ሞትን ፊት ለፊት አገኘሁት።

(አሁንማ ልባቸው ይመታ ጀመር፤ ያጋፋሪነታቸው «ሰውዬው» ከበሮ በተዘጋበት ዝምብ የመታውን ያህል

ወይም ይብልጥ ይጦታ ጀመር:: «በጂ» አሉ::)

አሁንም ወደ ቤታችን ብሄድ አሁንም ዳስ ያው እንዳለ ነው፣- ትጠሎቹ እንኳ አልጠወለጉም:: ብራምባር ሰበረልዎም እየተዘፈነ ነው:: ሰርጉም ያው ያባቴና የናቴ ነው::

ዋሽዌ አላውቅም ከተፈጠርኩ፤ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ::

(«በጂ ቀጥል» አሉ አጋፋሪነታቸው)

በልቤ አይ አሁንስ ውስጡን ማየት አለብኝ እያልኩ ወደ ዳስ ብገባ፣ በዚህ በኩል ጉረምሳው እየጨፈረ ብራምባር ይዘፍናል፣ በዚህ በኩል አዛውንቱ ጠላ በዋንጫ ፉት እያሉ ያወጋሉ::

ወደ አዛውንቱ ሄድኩና እጅ ብነሳ

«አንተ ሰው ማነህ?» አሉኝ

«እኔ» አልኳቸው

«ከየት መጣህ?»

«ከግብፅ»

«በምን መጣህ?»

«በፍልጥ»

«ምን ይዘህ መጣህ?»

«ጭብጥ ጥጥ»

«በምን አስረህ?»

«በድንጋይ ልጥ»

«ትቀልዳለህ?»

«የምትቀልዱስ እናንተ። ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ አንድ ሠርግ ድግስ ላይ የምትቀመጡ።»

«እና ምን እንጥበስ?»

«ምንም አትጥበሱ። ብቻ ዘፈኑ ሲያበቃ ድግሱ ሲያልቅ ይህንን ጥጥ ለሙሽሪት ስጡልኝ። ለሷም ለባሏም ላማቾቿም ለልጅ ልጆቿም ትፍትልላቸው» አልኩና ከግብፅ በድንጋይ ልጥ ታስሮ በነፋስ ተጭኖ የመጣውን ጭብጥ ጥጥ ሰጥቻቸው ወጣሁ።

ያገሬ ጐረምሳ እየጨፈረ አሁንም «ብራምባር ሰበረልዎ!» እያለ ይዘፍናል።

ዋሽቴ አላውቅም ከተፈጠርኩ፤ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ።

(«አስቸጋሪ እጣ ነው። ያንተስ» አሉ አጋፋሪነታቸው በልባቸው። «ከዚያስ» አሉ ባንደበታቸው። ባንድ በኩል «ሰውዬው» እያሳዘናቸው። በሌላ በኩል ነገሩን ማመን እያስቸገራቸው።)

ከዚያማ አዛውንቱን ተሰናብቼ ወጣሁ። አሁንም ካገሬ መውጣት አለብኝ ብዬ ስሄድ ልክ ካስራ አንድ ዓመት በፊት ንፋስን አገኘሁበት ቦታ፣ ከዚያ በፊት ደግሞ አስራ አንድ ዓመት አስቀድሞ እረኛችን ላሚቱ ጠፋች ያለኝ ቦታ፣ ስደርስ ሞትን ፊት ለፊት አገኘሁ።

(አሁንማ ልባቸው ይመታ ጀመር ያጋፋሪነታቸው — «ሰውዬው» ከበሮ በተዘጋበት ዝምብ የመታውን ያህል ወይም ይበልጥ ይመታ ጀመር። «በጀ» አሉ።)

ሳየው ሞት ግራ የገባው ወይም የጨነቀው መሰለኝ:: ምክንያቱን ብጠይቀው ነገረኝ::

(«ምን ነበር ምክንያቱ?» አሉ አጋፋሪ እየተጣደፉ)

ለካ እሱ አጋፋሪ እንደሻው የተባሉ ሰውዬ ወደ ሰማይ ቤት ለመውሰድ ከላይ ታዞ ኖሮ-

(«እህ?» አሉ እሳቸው፣ ዝም ብሎ መስማቱ ስላልተቻላቸው::)

ሰውዬው ለገዛ ምክንያታቸው ሞትን እምቢ ብለው ኖሮ-

(«እህ?)

እምቢተኝነታቸው በልዩ ልዩ ምክንያት-- ለኔ ባልተነገረኝና በማላውቀው ምክንያት-- አሸንፎት ኖሮ-

(«በጀ ቀጥል» አሉ ኩራ እንደማለት ብለው አጋፋሪነታቸው::)

ፈርቶና አፍሮ ባዶ እጁን ወደ ሰማይ ቤት ሊመለስ ኖሯል::

(«እህ...?» አሉ አጋፋሪ::)

እንግዲህ ምን ልበልዎ? የጨነቀውና የጨነቀው ሲገናኙ የቸገረውም እርጉዝ ያገባል የቸገራትም ስልብ ታገባለች::

(«እሺ» አሉ::)

(«ከዚያስ?» አሉ አጋፋሪ::)

ከዚያማ እኔም በነፋስ ታዝዬ፣ ዓለምን አይቻለሁ፣

ሰማይ ነው የቀረኝ ሞትም ኢጋፋሪን አምጣ ብሎ ታዘዘልና ኢጋፋሪን ይዞ መግባት አለበት- ሰማይ ቤት፡፡»

(«በጀ» አሉ ኢጋፋሪ ድንጋጤ እያገረሸባቸው)

ተስማማና ሞትም ሰማይ ቤት ሊያደርሰኝ፣ እኔም የእምቢተኛውን የኢጋፋሪን መልክና ስም ይዤ ልገባ፡፡

ምን ቸገረኝ፡፡ ምናልባት በኋላ ቢታወቅብኝ እንኳ ገና ባለመወሰዴ የክርስትና ስምም የለኝ፡፡ ከተወሰዱ ሰዎች ቁጥርም አልገባሁ፡፡

(«እሺ» አሉ በትዝብት እያዩት ኢጋፋሪ)

«በኋላ ግን ወደ ምድር ትመልሰኛለህ» አልኩ-ሞትን፡፡

«ወደ ላይ ስመለስ የታዘዝኩትን ሰው ይዤ መሄድ አለብኝ እንጂ ወደታች ስመጣማ ሆረገላዬ ሁልጊዜም ባዶውን ነው፡፡ ስለዚህ በፈለግከው ጊዜ ወደ ምድር እመልስሀለሁ» አለኝ፡፡

በዚህ ተስማምተን ወደ ሰማይ ቤት ሄድኩ፡፡ ባጋፋሪ እንደሻው ስምና መልክ ሰማይ ቤትን አሥራ አንድ ዓመት ሙሉ እየዞርኩ ካየሁና ካጠናሁ በኋላ ሞት አንዱን ለመውሰድ ባዶ ሰረገላውን እየነዳ ሲወርድ አንድ ድብቅ ቦታ ጠበቅሁትና ውሰደኝ አልኩት፡፡ ወደ ምድር ማምጣት ብቻ ሳይሆን እተገናኘንበት መንደሬ ዳር አደረሰኝና ወደ ጉዳዩ ሄደ፡፡

እንግዲህ አሥራ አንድ ዓመት አልፏል ካገሬ ከወጣሁ፡፡ በጠቅላላው ሰላሳ ሶስት ዓመት መሆኑ ነው፡፡

(«በጀ» አሉ ኢጋፋሪ ብዙ ብልሀት በሀሳባቸው እየተሰለፈ፣ ብዙ ምኞት በልባቸው እየተገላበጠ፡፡)

ከሰላሳ ሶስት ዓመት በኋላ ሰማይ ቤትንም ጉብኝቼና አጥንቼ ወደ አገሬ ወደ መንደሬ ስመለስ አሁንም ዳስ ያው ነው «ብራምባር ሰበረልዎም» ይዘፈናል:: ቀኑም ማክሰኞ ነው:: ሰርጉም የናቴና የአባቴ ነው::

(«እዬ») አሉ አጋፋሪነታቸው ለተገላቢጦሹ ሰውዬ ከልባቸው አዘነው:: ይህም ከዕድቅ ተቆጠረላቸው:: መልአኩም ይህን በሰማያዊ መዝገብ አስፈረላቸው:: እሳቸው ግን ዕድቁ ወደ አስማዊ ኑሮ ቢመነዘርላቸው ነበር ፈቃዳቸው::

«ከዚያስ?» አሉ ተገላቢጦሹን ሰው- አጋፋሪነታቸው::

ከዚያማ የመጣው ይምጣ ብዬ ወደዳሱ ገባሁ:: አዛውንቱም መሶቦቹ በነበሩባቸው ዙሪያዎች ጠላ በዋንጫ ፉት እያሉ ያወጋሉ:: አደግድጌ ወደ አዛውንቱ ሄጄ እጅ ብነሳ፤

«ከየት መጣህ?» አሉኝ

«ከሰማይ ቤት» አልኳቸው

«እንደምን እዚያ ደረስክ?»

«በሞት ሁረገላ»

«ከሆነስ ሆነና እግዜርን አይተኸዋል?»

«አዎና!»

«ቀይ ነው ጥቁር?»

«ተከናንቦ ነበር»

«ረጅም ነው አጭር?»

«ቁጭ ብሎ ነበር::»

«አሁን ምን ትፈልጋለህ?» አሉኝ

«የሰርገኞቹ ልጅ እንዲወለድ» አልኳቸው።

«እሱማ ጊዜውን ጠብቆ ነው» አሉኝ።

«እና ጊዜው መቼ ነው?» አልኳቸው።

«እንጃ!»

«በሉ ደህና ሁኑ» አልኳቸውና ወጣሁ።

በመጀመሪያ እረኛውን፣ በኋላ ንፋስን፣ ከዚያም ሞትን ካገኘሁበት ስፍራ ስደርስ ተረትን አገኘሁ። ወደዚህ አመጣኝ። እዚህ አውርዶኝ ሄደ። እርስዎ መጡና፤

«እንዴት ዋላችሁ?» አሉኝ። «ይኸው እንግዲህ እውነቴም ተረቴም አበቃ!» ሲል ደመደመ- ተገላቢጦሽ ሰውዬ።

አጋፋሪ ጥቂት ሲያስቡ ከቆዩ በኋላ እንዲህ አሉ፡-

«ስማኝ ወዳጄ፣ የሞት መድኃኒት ወይም ድግምት ፍለጋ ወደአባ ሽንኩርት መሄዴ ነው። አንተም አብረኸኝ ብትመጣ ጥሩ መሰለኝ። አባ ሽንኩርት ከቻሉና ከፈቀዱ ለኔም የሞት መድኃኒት፣ ላንተም የልደት መድሀኒት ይሰጡናል። አለዚያም እሳቸው ጋ ከደረስን በኋላ ሌላ ብልሀት እንፈልጋለን።»

«አሁን ገና ተናገሩ!»

«እሱስ በፊትም ስናገር ነበር።» አሉት ሳቅ እያሉ «ብቻ ተነስ ነጠላህን አገልድምና፣ ገበሬ ሌላ ልብስ ይፈልግልሀል። ወደ መግደላይት ጓሮ እንሂድ።»

ተነሳ «ሰውዬው» መጋረጃ ሆኖት የነበረውን ነጠላ

አሸረጠ። አጋፋሪም ተነሱ አብረው፤ ወደ አባ ሸንኩርት ሊሄዱ ሆነ።

መልእኩ ይህን ሲመዘግብ፣ አጋፋሪ ከዕድቅ ተቆጠረላቸው። እሳቸው ግን የሚመርጡት ሺ ዕድቅ ወደ አንድ ዓመት ወይም ወደ አንድ ሰዓት አለማዊ ደስታ ቢመነዘርላቸው ነበር...

«ወዳጄ አገርህ መንደርህ የት ነው?» አሉት ሰውዬውን።

«ልክ በትግራይና በጎንደር ድንበር ላይ ነው። ስለዚህ ባንድ ጐኔ ትግሬ ባንድ ጐኔ ጐንደሬ ነኝ። በትግራይ ዘፈን በጐንደር ተረት ነኝ»

«እህ...» አሉ አጋፋሪ ራሳቸውን በአዎንታ እየነቀነቁ «መቼና የት እንደሆነ ረስቶኝ እንጂ በንጉዩ ላይ ከተረት ጐንህ ጋር ካንድም ሁለቴ ተገናኝተናል»

«እርስዎ ተረት ነዎታ?»

«ወይድ! ባለጌ!» አሉ እየገረመሙ። «ተረት ነኝ ብለህ መዋሸትህ አነሰና እኔንም ተረት ልታረገኝ!»

«እኔማ ተረት ነኝ አልኩዎ ኮ ጌታዬ»

«ኧረ ይጐትጐትህ እዚያው! ደሞ ጌታዬ ይለኛል። ተረት ከሆንክ እኔ ለብርቱ ጉዳይ ስሄድ በባዶ ተረት ጊዜዬን ምታጠፋብኝ ለምን?»

«አይቆጡኝና እርስዎም እንደኔ ተረት ነዎት። ልዩነታችን እኔ የቆየሁ ቅርስ ስሆን እርስዎ አዲስ አዝመራ ነዎት እንጂ ተረት ነዎት»

«ኧረ ተረት ሁነህ ቅር እዚያው!»

«እኔማ ተረት ሆኜ ቀርቻለሁ»

«በል ዝም በል አትልከፈኝ፡፡ እኔ ሰው ነኝ'ንጂ ተረት'ማይደለሁ»

«እንግዲያው ተረት ሰፈር ምን ይሰራሉ?»

«እኔማ የሞት መድሀኒት ፍለጋ ስንዝ ሳጠያይቅ ወደዚህ ስላመላከተኝ መጥቼ ነው፡፡ ይልቅ በንትርክ የሰው ጊዜ አታጥፉ፡፡ ትሄድ እንደሆን ተነስ እንሂድ-አባ ሽንኩርት ዘንድ»

አጋፋሪ እንደሻው በትሎአቸው ላይ ተቀምጠው ሲሄዱ ከጉናቸው የሚራመደውን ተገላቢጦሽ ሰውዩ እየተመለከቱ በሀሳባቸው እንዲህ አሉ «እውነት ተረት እሆን እንዴ? ከሆንኩማ ጉድ ተሰርቻለሁ፡፡ (...እንግድያው ሁሉም ተረት ነዋ!...» ብቻ ደሞኮ ተረት ከሆንኩ ከሞት ማምለጥ እችላለሁ ማለት ነው፡፡ ለተረት ምን ተስኖት!... ከሞት ላምልጥ እንጂ ታድያ እንኳን ተረት ለምን ቀልድ አልሆንም? (እንደሻው ግድ አለው?... ዘራፍ) እንደሻው አባ መክት (ሽሽት ጋሻው- ከሞት ይመክት)...»

***

አጋፋሪ እንደሻው ከአቶ ተገላቢጦሽ ጋር አባ ሽንኩርትን ፍለጋ ወደ መግደላይት ቤተክርስቲን ሲሄዱ አያድቡልቡሌን መንገድ ላይ አገኟት፡፡ ተሸክማቸው ከምትሰግረው ጠጂቷ ጋር በሀሳባቸው እያወሩ ሲሄዱ አዩት ከፊት ለፊታቸው፣ ካንገቷ በላይ ሰው፣ ካንገቷ በታች ጋን፡፡ ራሱ ላይ ሽክና ደፍቷል፡፡ እንደ መነኩሴ ቆብ፡፡

እያማተቡ «ስአሰ. ለነ ቅድስት!» እያሉ ልጓም ስበው ከጠጂቱ ወረዱ:: (ሀሳብ ጨረፍ አርጓቸው አለፈ፣ እንዲህ እያለ እሳቸው ሲፈልጋቸው በሁለት እግራቸው፣ ሲፈልጋቸው በጠጂቱ አራት እግር እየተዘዋወሩ ምድረ ሀበሻን ደጋግመው ሲያዳርሱ- ምድሪቱ ያው ሆናም ሺ. ጊዜ ውበት እየለዋወጠች ስታስደስታቸው- ይኽ ሰው ጋን ነገር እንዴት ይሆነው ይሆን? «አቤት አምላኬ ምንኛ ትጨክናለህ! ወይስ ብልሀት ያልከው ይሆን?»

«ጤና ይስጥልኝ» አሉና እጅ ነሱት ሰው-ጋኑን፣ ባለ ሽክና ቆቡን::

«እግዚአብሔር ይመስገን» ሲል ድንግጥ አሉ፣ ፈሩት ድምጹን «እጅ እንዳልነሳዎት እንደሚያዩኝ ነኝ»

«ኧረ ግድ የለም» አሉት በደህና ድምፅ- ውስጡን ግን በፍርሀት ብርድ ብርድ እያላቸው::

«እርስዎማ ግድ የለዎትም!» አለ:: የተናደደ ይመስላል:: «ለመሆኑ ማን እንደሆንኩ አውቀውኛል?»

ከድምጹ ወጥቶ ይህ ነው የማይባል ፍርሀት ነብሳቸውን ወረራት:: መናገር ተሳናቸው::

«'መፍርህ ወመደንግፅ መወርእድ ድምፁ ፍቁር ወልድየ'፣ እንዲል መጽሀፉ» አለ ሰው ጋኛው «ይበሉንጂ ማን እንደሆንኩ አውቀውኛል?»

አጋፋሪ ቢፈሩም፣ ቢርዱም እንደ ምንም ወኔያቸውን እየቀሰቀሱ «ተገናኝተን አናውቅ:: እንዴት ልወቅህ?» አሉት::

«'ወኢአመኑዎ አህዛብ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መጽሐፉ:: እያ ድቡልቡሌ ነኝክ»

ድንገት ፍርሀታቸው እርግፍ እርጕ ተዋቸው፡፡ ሰው-ጋን ገድየውን በስም ስላወቁት ይሆን? «ተውንጂ» አሉት «እያ ድቡልቡሌኮ ድሮ ጥንት ልጆች ሆነን፡፡ የምንሰማው ተረት ነው»

«እኮ! እሱ ራሱ ነኝ እኔ፡፡ እኔ ራሴ ነው እሱ ማለቴ፡፡ አዩት ስጋና ገል እርጕ ፈጥሮ እንዲህ ሲጫወትብኝ? በሱ ቤት እንግዲህ ቅኔ መፍጠሩ ነው – ሰምና ወርቅ ሳይሆን ስጋና ገል፡፡ 'ወአ ድበልበልኩዎ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መጽሐፉ»

«ተውንጂ፡፡ ባይኔ እያየሁህ በጆሮየ እየሰማሁህ ተረት ነኝ ትለኛህ?»

«እርስዎ ራስዎ ምን ሆኑና?»

«ምን ማለትህ ነው? ገልጠህ ተናገር»

«ይህ ያለን ቤት መንደር ምን ይባላል?»

«ተረት ሰፈር»

«እኮ!»

«እኮ ምን?»

«የተረት ሰፈር ሰዎችኮ ተረቶች ነን፡፡ 'ወተረኩዎ አህዛብ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መጽሐፉ»

«አንተ ተረትም፣ ጋንም ትሆናለህ እንጂ እኔ ግን እንደሻው ነኝ፡፡ እንደሻው በልሁ፡፡ በልሁ ድልነሳው፡፡ በል ምንትሆን?»

«እኔማ ምን እሆናለሁ? እርስዎ'ንጂ፡፡ ተረት ባይሆኑ ተረት ሰፈር ውስጥ ካያ ድቡሌ ጋር እንዴት ብለህ ታወሩ

ነበረ? ይቅርታ ግማሽ ገልነቴ አንቱታ አያውቅም:: 'ወኢየአምር ፍቱር ወልድየ' እንዲል መጽሐፉ::»

«ለመሆኑ ተረት ከሆንክ ምን አይነት ተረት ነህ?»

«ሁለት አይነቱ:: «ወክልኤቱ ፍጥረቱ ለፍቱር ወልድየ» እንዲል መጽሐፉ» የጋኑ ጆሮ እሚሆንበት ቦታ የሰው እጅ አለው እያ ድቡሴ:: በጣቶቹ እየቆጠረ «አንደኛው፤ ውጭኛው ተረት ነው - ያ እርስዎ ልጅ ሆነው የሰሙት:: ሁለተኛው ውስጠኛው ተረት ነኝ - ያ እኔ የማውቀኝ»

«እኔ ሁለቱንም አላውቃቸው:: ንገረኝ እስቲ»

«እሱማ እውነቴን ተረቴን ለመስማት እዚች ለምለም ሳር ላይ ቁጭ ብትልስ» አለ በእጁ እያመለከተ 'ወነበረ በባሊሱን ፍቱር ወልድየ' እንዲል መጽሐፉ:: «ወድያውም ሽቅብና ቁልቁል ከመነጋገር-

«መልካም:: መጀመሪያ ይህን ሰው ላስተዋውቅህ:: አቶ ተገላቢጦሽ ይባላል::»

ከተዋወቁ በኋላ ቁጭ ተባለና እያድቡሴ ውጭኛውን ተረት እንዲህ ሲል በማታ እሳት ዳር ተረት ዜማ ጀመረላቸው:-

እንጉዳይ እምትባል ውቢት ነበረች:: እግዜር እጁን ታጥቦ የፈጠራት:: ግና ሳይጣላ አይደግስምና ይህ ውበቷ ሌሎቹ አብረዋት የሚውሉት ሴት ልጆች ልብ ውስጥ የጠቆረ፣ የከረረ ቅናት አሳደረባቸው:: አንድ ቀን እንጉዳይ ውቢቱ በሌለችበት ሌሎቹ ተማከሩና ጨሌዎቻቸውን ካንገታቸው አውልቀው ደበቁ:: በእጃቸው እፍኝ እፍኝ ጠጠር ጨብጠው ሐይቁ ዳር ቆዩና እሷ ስትመጣ ልጆችዬ ዶቃዎቻችንን ውሀው ውስጥ እንወርውር!» ተባባሉና «አንድ-

ሁለት-ሶስት!» ብለው ፈጥነው ጠጠሮቹን ሀይቁ ውስጥ ወረወሯቸው::

እና «እንጉዳይ አንቺስ ጨሌዎችሽን አውልቀሽ ውሀ ውስጥ አትጥይም?» አሉዋት «እኛ እንኳን ሁላችን ጥለን? እንግዲያው ሂጂ ለብቻሽ ከኛ ጋር አትጫወቺም፣ በቃ:: እ-እኛ ደሞ ብትፈልጊ 'አይጥ የት ከርማ መጣች?' እንጫወታለን:: ከኛ ጋር አትጫወቺም? እንደኛ ዶቃዎችሽን ውሀው ውስጥ ጣይና!» ብለው ጨሌዎችዋን አስውልቀው ባህሩ ውስጥ አስወረወሩዋት:: ባዶ አንገትዋን ቀረች::

ይኸኔ ሌሎቹ እየተሳሳቁ ዶቃዎቻቸውን ከየደበቁበት አውጥተው እፊቷ እያወዛወዙ «እንቁልልጭ! እኛ ዶቃችን ይኸው! እኛ ዶቃችን ይኸው!» ብለው ጨሌዎቻቸውን አንገታቸው ላይ አሰሩ::

አለቀሰች:: እንጉዳይ ውቢቱ ተንሰቀሰቀች:: ሳትደርስባቸው ሳትበድላቸው እነሱ ይህን ያህል እንደጠሉዋት ድንገት በማየትዋ እጅጉን ተከፋች:: አንገቱዋን ደፍታ ስታለቅስ እየተሳሳቁ ትተዋት ሄዱ::

ስታለቅስ ሰምቷት አያ ድቡሴ መጣና «ምን ሆነሽ ታለቅሻለሽ እንጉዳይ ውቢት?» አላት:: ነገረችው:: «ዶቃዎችሽን አምጥቼ ብሰጥሽ ሚስት ትሆኚኛለሽ ወይ?» አላት::

ያ ሀዘን ለቅሶዋ ወደ እልህ ተለወጠ:: እሺ አለችው::

አያ ድቡሴ ባህሩን ጭው አርጐ ጠጣውና ጉድጓዱ ባዶውን ቀረ:: እዚያ ታዩ ዶቃዎችዋ የንጉዳይ ውቢቱ:: አያ ድቡሴ አንስቶ ዶቃዎቹን አንገትዋ ላይ አሰረላት::

እንደ አበባ ፈካች:: ፈገግ አለች::

አያ ድቡሴ ልብ ውስጥ ደስታው እንደ ፀሐይ በራ:: ዳሩ ምን ይሆናል? አያ ድቡሴ እንጉዳይ ውቢቱ ቤቶች ዘንድ ልጃችሁን ስጡኝ ብሎ ሽማግሌዎች ቢልክ «እንኳን ልጃችንን ልንድርልህ ቀርቶ፣ እዚች ድርሽ ብትል በነብስህ እወቅበት» አሉና ቤታቸውን በሰባት ዙር አጥር ከበቡት::

መቸስ «ፍቅር ውእቱ» እንዲህል መጽሐፉ አያ ድቡልቡሴ እንጉዳይ ውቢትን ፍለጋ እየተድበለበለ መጣ::

መጣና ውጭኛው ሰባተኛው አጥር ጋ ሆኖ ተጣራ፣

«እንጉዳይ ውቢቱ፣ እንጉዳይ ውቢቱ-

መጣሁልሽ- አንቱ!» አላት:: ለማጥመ ሲባል «አንቱ» አለ እንጂ «መጣሁልሽ እኔ» ማለቱ ነበር::

አሷም ወጥተው ይቀበሉት መስሏት

«አባዬ-ተነሳ ነጠላ-ህን አንሳ» ስትል አባቷ ጋሻ ጦራቸውን አንስተው ወጡ::

(እዚህ ላይ አያ ድቡሴ የተረት ዜማውን ተወውና በንዴት ለነአጋፋሪ ተናገረ:-) «ሊወጉኝ መጡ አባትየው:: አይ ግፍ! ባፈቀርኩ በጦር ሊወጉኝ? ተናደድኩ::»

አያ ድቡሴ ተናደደ አይኑ ተንቦለቦለ::

ጭስስ አለ፣ ካፍንጫው ጪሱ ቡልቅ ቡልቅ አለ::

መጨሱም መናደዱም እስኪያልፍ ትንሽ በዝምታ ተቆየ::

«ምነው አልጨስ፣ ምነው አልናደድ!?» ሲል ቀጠለ አያ ድቡሴ፣ በእሳት ዳር ተረት ዜማ፣ «ምነው አልጨስ፣

ምነው አልናደድ!? ምነው አልጨስ ምነው አልናደድ?! ምነው አል-»

«በል በቃህ ወዳጄ፣ ጨስክ ተናደድክ» ብለው ዝም ሊሉ ሊሰሙት እየፈለጉ እሳቸውም በተረት ዜማው ቀጠሉ «ምን አጨሰህ ምን አና-ደደህ?! ምን ያጨሳል ምን ያናድዳል?! ለምን መጨስ ለምንስ መ-ናደድ?! ምነው መጨስህ መ-»

«አዩት አይደል የመደጋገምን ነገር?» ብሎ ሲያቋርጣቸው እፎይ ብለው ተነፈሱ:: «የኔም የርስዎም የተረትነታችን አንዱ ምልክት ነው::»

«ወዲያ ባክህ! አትድበልበልብን እዚህ!»

«እሺ ይተውት በቃ:: ተረቴን ልቀጥልልዎት»

«እሱኳ ይሻላል»

አባትየው ባልወለደ አንጀታቸው ጨክነው ጦሩን ወረወሩብኝ:: ጋኔ ውስጥ ገብቶ ቀረ፣ ጠፋ:: ጋኔ እንኳን ሊሰበር ንቃትም አልታየበት:: እኔን ፊቴን ያያሉ ደሞ፣ ምንም አልሆንኩም! ደንግጠው ጋሻቸውን ጣሉ:: 'ወፈርህም አህዛብ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መጽሐፉ»

«የቱ መጽሐፍ ነው ግን?»

«ያ ያልተፃፈው»

«ብዙ ነገር ይላል እሱ መፅሐፍ»

«አስተዋይ ነዎት»

«እሺ በል ቀጥልልኝ»

«ስድስቱንም አጥር እያፈራረስኩ ደረስኩ:: ሰባተኛውን ውስጠኛውን አጥር አፍርሼ ስገባ እንጉዳይ ውቢቷ ቆማ ትንቀጠቀጣለች::

«እይኝ እስቲ ፊቴን» አልኳት:: ፈርታ አቀርቅራ ቀረች:: ባገጩዋ ይገፔ ጠምዝዤ አይን ለአይን እንድንተያይ አስገደድኳት:: እንደ መፍዘዝ አለች:: ተያየን:: በፍቅር አይን ያየችኝ መሰለኝ:: ድፈር ድፈር አለኝ::

«ካንገቴ በታች እይኝ» አልኩና በፍቅር እጅ፣ በተስፋ እጅ፣ በፍርሀት እጅ ራሷን ከኋላ ይገፔ አይኗን አሽቆለቆልኩት::

«አይ!!» ብላ ጮኸችና አይኗን በጇ ሸፍና እየተርበተበተች ተንበርክካ ተጣጠፈች:: መሬቱቱን የሙጥኝ አለች::

ለሷም አዝኜላት፣ በእድሌም እያዘንኩ፣ እዚያ ትቻት ወጣሁ- ኮበለልኩ:: ሰላሳ ሶስት አመት ሙሉ ስኮበልል፣ ስንከባለል ይኸው እዚህ ደረስኩ:: ከመንደር ቂሎ ቀጥሎ ያጋጠሙኝ እርስዎ ነዎት»

('ዳኛቸው እንደሚለኝ እኔ ደሞ የመንደር እብድ መሆኔ ይሆንንዴ?» አለች ሀሳባቸው ያጋፋሪ)

«እዩኝ ስቲ በፈጠራችሁ ጌታ» አለ አያ ድቡሌ «መልኬ ለሴት ልጅ ያንሳታል?»

አዩት:: ሰውየው መልኩ እንከን አይወጣለትም::

«እኮ ይናገሩ»

«ካንገት በላይ ሲያዩህ እግዜሩ እጁን ታጥቦ ሲሰራህ የዋለ ነህ»

«እንግዲያው ለምን አልፈለገችኝም?» ጥልቅ ሀዘንና ቁጭት አለ እዚያ ድምፅ ውስጥ «ለምን? ለምን?»

አጋፋሪ በጣም አሳዘናቸውና «ስማኝ ወዳጄ» አሉት «ይኸ አቶ ተገላቢጦሽ የቸገረው ሰው ነው። መወለድን ፍለጋ ሲንከራተት ይኸው ሰላሳ ሶስት አመት ሆነው»

«ወይ አጋጣሚ! እኔ ደሞ በእንጉዳይ ውቤ፥ ፍቅር ስንከራተት ይኸው ሰላሳ ሶስት አመት ሆነኝ»

«ሦስተኛ አጋጣሚ ይኸውልህ። እኔ ደሞ የሞት መድሀኒት ፍለጋ ስዞር ይኸው ሰላሳ ሶስት አመት ሆነኝ»

«አጋጣሚው አልበዛም?» አለ አያ ድቡሴ።

«ይብዛ ግድ የለህም። አባ ሸንኩርትን ታውቃቸዋለህ?»

«ማናቸው?»

«መግደላይት ኋሮ መቃብር ቤት የሚኖሩት የበቁ ባህታዊ ናቸው። ከመብቃቱም አልፈው ከዝጌሩ ጋር ቡና ይጠጣሉ ይባላል። እኔና አቶ ተገላቢጣሽ እሳቸው ዘንድ መሄዳችን ነው። እኔ ምናልባት የሞት መድሀኒት ቢሰጡኝ ብዮ በተስፋ፤ እሱ መወለድ ቢያስችሉት ምናልባት ብሎ በተስፋ። አንተም አብረኸን እንሂድና ሙሉ ሰው ያድርጉኝ ብለህ ለምናቸው።»

«እሺ ይሉኛል?»

«በተስፋ። ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም» አሉት።

«እንዲሁም አያ ድቡልቡሌ» አለ አያ ድቡልቡሌ።

«እንዲያ ነው እንጂ። በሉ እንሂዳ። ሁለተኛውን

ተረትህን እየሄድን ትነግረናለህ»


«እሱስ ይቻል ነበር። እኔ ግን ብቻየን ስሆን ተሽከርክሬ እሄዳለሁ እንጂ ከሰው ጋር ለመሄድ አልችልም። ጋን ገላዬ አይንቀሳቀስም ከሰው ጋር ልሄድ ካልኩ።»

አጋፋሪ ትንሽ አሰቡና «ግድ የለም» አሉ «በጠጂቱ እንጭንሀለን።»


«እርስዎስ?»

«እኔማ በእግሬ ሄዳለሁ» አሉ አጋፋሪ እንደሻው (ይህም በሰማይ ቤት ዕድቅ ሆኖ ተፃፈላቸው። ወደ ምድራዊ እድሜ የሚመነዘር ካልሆነ ግን እሳቸው ምን ተዳቸው?)

እንዲህ ሆነው አምስቱም ወደ መግደላይት አመሩ፡- አንዱ የሞት መድሀኒት ፍለጋ- አንዱ የልደት መድሀኒት ፍለጋ- አንዱ ፍቅርን ፍለጋ- ሁለቱ ግን ለማገልገል ብቻ።



# «መስከረም ሁለት»




# የመቀሌ ቀልዶች

ተስፋዬ ገብረአብ

በመቀሌ ከተማ የቀልድ ነገር ሲነሳ ካሳ ደበስና አስፋቸው ፈቃዱም አብረው ይነሳሉ:: ከማለዳው አራት ሰዓት ጀምሮ የጠላ ገበያ በሚደራባት መቀሌ ቀልድ ትልቅ ስፍራ ይሰጠ ዋል:: ጥርስ የማያስከድኑ ቀልዶችም በጠላ ቤቶችና በአረቂ አዳራሾች ይንቆረቆራሉ:: ሁለቱ የቀልድ አባቶች ዛሬ በህይወት ባይኖሩም የከተማይቱ ነዋሪዎች ግን ያነሳሱዋቸ ዋል:: ጥቂቱን ለአንባቢዎቼ አቅርቤያለሁ:: በአማርኛ ሲቀርቡ ያስቁ ይሆን?

አስፋቸው ፈቃዱ ማመልከቻ በመጻፍ የታወቁ ነበሩ ይባላል:: ታዲያ ከእለታት አንድ ቀን አንዲት የመንደሩ ነዋሪ «ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ይጻፉልኝ» ትላለች::

«ትከፍይኛለሽ?»

«ገንዘብ ስለሌለኝ በነፃ ይጻፉልኝ»

አስፋቸው ተስማምተው የሚከተለውን ማመልከቻ ጻፉላት::

«ለበነፃ ፍርድ ቤት፣

በነፃ፣በነፃ፣ በነፃ:: በነፃ በመሆኑ በነፃ እንዲሆን በነፃ ሆኖአል:: በነፃ ተፅፎአል::

ነፃ::

አመልካች ነፃ::

አመልካችዋ አስፋቸውን አመስግናና መርቃ ከማመልከቻዋ ግርጌም ፊርማ አስቀምጣ ማመልከቻዋን ለፍርድ ቤት አቀረበች:: የደብዳቤውም ታሪክ እነሆ በመላው መቀሌ እስካ ሁን ይነገራል::

* * *

አንድ ጊዜ ደግሞ አስፋቸውን በሬ ስለወጋቸው ክፉኛ ተጐዱ:: ከህመማቸው እንዳገገሙም የበሬውን ባለቤት «ብቆየ ቂም ተነሳስቶ በሬውን ልኮ አስወግቶኛልና ይካሰኝ» ሲሉ ከሰሱ:: አገር ጉድ ብሎ ተሰበሰበ:: ዳኛው ግን «እንስሳ መልእክት መቀበል ስለማይችል አይከስህም» ብለው ጉዳዩን በአንድ ቀን ዘጉት::

በውሳኔ የተከፋት አስፋቸው ታዲያ «ጥይቱ» የሚሉት

ውሻቸውን አስከትለው ባላንጣቸውን አድብተው ይጠብቁ ጀመር:: እናም አንድ ቀን ብቻውን አገኙት:: ውሻውን «ያዘው» ሲሉትም ተወርውሮ የባለበሬውን እግር ይቦጭቀዋል:: በዚህ ተከሰው ፍርድ ቤት ሲቀርቡም የሰጡት መልስ «እንስሳ መልእክት መቀበል አይችልም» የሚል ነበር:: ቅጣቱ ግን አልቀረላቸውም::

* * *

አስፋቸው በደርግ ዘመን ቤታቸው ስለተወረሰባቸው ብዙ ስራዎችን ይሰሩ ነበር:: ቆዳ እያለፉ ይሸጡም ነበር:: አንድ ቀን ታዲያ በአህያቸው ቆዳ ጭነው ወደገበያ ሲያዘግሙ አንዱ «ቆዳ ይሸጣል?» ሲል ይጠይቃቸዋል::

«የለም ሰርቢ ነው» ነበር የአስፋቸው መልስ::

* * *

በመቀሌ ከተማ የታወቁት ነጋዴ የካሳ ደበስም ስም በተደጋጋሚ ይነሳል:: በቀይ ሽብር ዘመን የካሳ ደበስ ሁለት ልጆች የተለያዩ ቦታዎች ይታሰሩባቸዋል:: አንደኛው ልጅ ወህኒ ምርመራ፣ ሌላው እንዳየሱስ በተባለ ሩቅ ያለ ስፍራ:: ይኸኔ ካሳ ደበስ በወቅቱ ለነበሩት ሹም የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉ::

«ያለኝ የምሳ ማመላለሻ ሳህን አንድ ብቻ በመሆኑ፣ ሁለቱ ልጆቼ ከተቻለ በአንድ ላይ ቢታሰሩልኝ:: ካልተቻለ ግን አንደኛው ቢገደል::»

ይህ ደብዳቤ የደረሰው ሹም በደብዳቤው ተገርሞ ሁለቱንም ልጆች ፈታቸው::

* * *

በዚያው ሰሞን መቀሌ ከተማ መጠጥ ቤት ውስጥ አንድ ወታደር ከሲቪሎች ጋር ተጋጭቶ ይቆስላል። በዚህ የተነሳ ከተማዋ ስትታመስ ታድራለች። ወታደሮችም በየቤቱ እየዞሩ ያስሳሉ። ፈታሾቹ ካሳ ደበሳ ቤት እንደደረሱም፣

«ክፈት!» ይላሉ።

«አልከፍትም»

«አንት ቡሽቲ ክፈት!»

«ደግነዋ፣ ቡሽቲ ከመጣችስ እከፍታለሁ»

በዚህ ጊዜ ከፈታሾች አንዱ ካሳ ደበስ መሆናቸውን አውቆ «ያ ቀልደኛ ነው እባካችሁ፣ ተውት» ይላቸዋል። በር ሲደበድብ የቆየው ወታደር «ቆይ አንተ ቡሽቲ ሲነጋ እናገኝሃለን» ብሎአቸው ይሄዳሉ።

ከዚያ ካሳ ደበስ ማልደው ቤተክርስቲያን ሲያስቀድሱ መከፋታቸውን ከፊታቸው ያነበቡ ጐረቤቶች፣ «ምነው ደህናም አላደሩ» ሲሉ ይጠይቋቸዋል።

«ምን ደህና አድራለሁ? ቡሽቲ የምትባል በሽታ ስታስቃየኝ አደረች እንጂ»

* * *

የካሳ ደበስ እዚህ ላይ ይብቃንና ወደ አክሱሙ ቄስ ምህረይ ወልደዮሀንስ እንሂድ።

ምህረይ ወልደዮሀንስ በዘመነ ቀይሽብር የኢዲዩ አባል ተብለው ይታሰራሉ። ፖለቲካ አላውቅም ቢሉም ግን ሰሚ ጠፍቶ ሌትና ቀን ይደበደባሉ። ከሳምንት በሁዋላ ግን «እብድ ናቸው» ተብሎ እንዲፈቱ ተወሰነ። ሲፈቱም በድብደባ በጣም

ተጉድተው ስለነበር የፖሊስ መርማሪው «ሰው ምን ሆኑ ብሎ ቢጠይቆት መኪና ገጨኝ በሉ» ይሉቸዋል። ምህረይ ወልደዮሀንስም ከተለቀቁ በኋላ «መኪና ገጨኝ» እያሉ መናገር ጀመሩ። ታዲያ አንድ ቀን ሰው በተሰበሰበበት እከተማ መሀል ከመርማሪ ፖሊሱ ጋር ይገናኛሉ። ይኸኔ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጣታቸውን ወደ መርማሪው ፖሊስ በመቀሰር «የገጨችኝ መኪና መጥታለች፣ ዘወር በሉ። እንዳትገጫችሁ፤ ገለል በሉ!» አሉ ይባላል።



# ልዩነት?



# ረጅም ሌሊት

## የሺጥላ ኮከብ

ቀንደኛ ጠላቶቼ ሶስት ነገሮች ናቸው:: አይጥ፣ ረጅም ሌሊትና የጣት ቁስል:: ትናንት ምሽት በተለይ የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ ሶስቱም ተረባርበው ሲያሰቃዩኝ ነበር ያደሩት:: ቀንደ-ቢስ ቀንደኞች:: ገና ሰዓቱ ከመንፈቅ- ሌሊት ብዙም ሳይገፋ ስወራጭ የጣት ቁስሌን ግድግዳ ነክቶት ኖሮ ህመሙ አባነነኝ:: ይህንኑ የቆሰለ ጣቴን እሹሩሩ ብዬ መጠዝጠዙ ጋብ ሲልልኝ ተመልሼ ተጋደምኩ:: የቤቴን ስርቻ እያሰሱ በነፃነት የሚሯሯጡትና በሚንጫረር ድምፃቸው ... ምን

ልበል? የሚጠራሩት... ወይም የሚጨቃጨቁ ት... ወይም የሚሞ ጋገሱ·ት... ወይም የሚላቀሱ·ት... ወይም የሚዘፍኑ·ት... ወይም... ቆይ! ይቅር:: ቋንቋቸው ካልገባኝ ለኔ እንደሚሰማኝ ልናገረው እችላለሁ:: የሚሰድቡኝ፣ የሚያድሙብኝ፣ የሚሳሳቁብኝና የሚሳለቁብኝ አይጦች እንቅልፌን አስበርግገው አባረ ሩት:: መብራት አብርቼ ድምፅ ባሰማ፤ ጣውላ ብተሙትም፤ በብሽቀት ባፈጥባቸውና እቃ እያነሳሁ ወደ የአቅጣጫው ብወረውር ባሰባቸው:: ለጥቂት ደቂቃዎች ድምፃቸውን አጥፍ ተው ይቆዩና ይመጣሉ:: እንጃ... ሊያበሽቁኝ ተዘጋጅተው ሳይመጡ አልቀሩም:: አፈጠ ጥኩ፤ እንደገና አፈጠጥኩ:: አፈጠጥኩ ለረጅም ጊዜ! አፈጠጥኩ:: ከንፌሬን ነከስኩባቸው፣ አጉረጠረጥኩባቸው፣ ዛትኩባቸው.. ምነው ቢዋጣልን!? ወይ እነሱ የሰው ልጅ ቋንቋ ቢናገሩና ጉልበት ቢኖራቸው፣ አልያም እኔ የነሱን ቋንቋ ባወቅሁና መሽሎክለክ ወይም ጣራ ላይ መሮጥ በቻልኩ:: የማንግባባ ባላጋራዎች፤ አያሸንፉኝ ወይ አላሸንፋቸው፤መብሸቅ ብቻ::

ግዴላችሁም፤ ጊዜ የአይጥና የጣት ቁስል የቅርብ ጓደኛ ሳይሆን አይቀርም! አለያ ምን እንዲህ አረዘመው? ቶሎ ለምን አይነጋም? ተገላበጥኩ፣ ዓይኖቼን ጨፈንኩ፣ እንቅልፍ ሊያስወስደኝ ይችላል ያልኩትን ሃሳብ ሁሉ ማሰብ ጀመርኩ:: ምንም የለም::

ገልበጥ ብዬ ወደ ጠረጴዛዬ ተመለከትኩ:: አንድ ወደል አይጥ እንደዘረጋሁ ደክሞኝ የተውኩት መፅሃፍ ላይ ይቦርቃል:: ድብብቆሽ እንደሚጫወት ሁሉ ዘሎ ሌሎች ወረቀ ቶች መሃል ይገባል:: ወጥቶ መፅሃፉ ላይ ይቦርቃል:: 'ምን እያለኝ ይሆን?' አልኩኝ በል ቤ:: 'ና! ወንድ ከሆንክ ጫፌን ንካኝ! ሳይለኝ ይቀር ይሆን?'

እንዳሻኝ እቦርቃለሁ! እስኪ ምን ትሆን? የኛ አንባቢ! ያውም ታሪክ ነው የምታነበው? ጅል! ታሪክ ብሎ ነገር! አይጦች ታሪክ ስለሌላቸው ምን የጎደለባቸው መሰለህ? ይወልዳሉ-ያድጋሉ- የበላሉ ይራባሉ- ያረጃሉ:: ከዚያም ይሞታሉ:: ድንገተኛ አደጋና አዳኝም ካገኘ ይገድላቸዋል:: ስለሚገድላቸውም ይሞታሉ:: በቃ! ይሞታሉ:: አይጦችንም በሽታ ይይዛቸዋል፣ ገባህ? ይታመማሉ! እንደናንተ! ይድናሉ- ይሞታሉ!...

...ተመልከቱ እንግዲህ ሃሳብ ይዞኝ ጥርግ ሲል! ሃሳብ ጓደኛ ዬ! ይቀጠላል አይጡ::

...አይጦችም ይርባቸዋል:: ረሃብን ያውቁታል:: ጥጋብንም እንደዚያው:: ጦርነትስ ቢሆን? እኛ አይጦች እንደናንተ ሁሌ አይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች የነጠላ ጠብም ሆነ የቡድን ጦርነት እናካሂዳለን! እናሸንፋለን ወይም እንሸነፋለን:: የተፈጥሮ አደጋም ቢሆን አይምረንም:: ጎርፍ ጠራርጎ ይወስደናል፣ ሰደድ እሳት በየጉድጓዳችን አፍኖ ይፈጀናል:: ንዳድና ውሀ ጥም ያስቃዩናል::

የቡድን... ምንድነው? እናንተ የሕብረተብ አለቃ ወይም መሪ እንደምትሉን ሁሉ እኛም የመንጋ አለቃ አለን:: በእድሜውና በጥንካሬው ከሁላችን ብልጫ ያለው:: ሰነፍና ደካሞችም በመካከላችን ይገኛሉ::

እናንተ ዘንድ ያለው ሁሉ እኛምጋ አለ:: እናንተም ትወልዳላችሁ፣ ትማራላችሁ፣ ትሞታላችሁ:: እኛስ ምን እያደረግን ያለን ይመስላችኋል? እኩል ነን:: ግን እኛ ታሪካ ችንን አናቆይም:: እንዳውም ታሪክ የምንለው ነገር የለንም:: ልጠይቅህና የታሪክ ርባና ምኑ ላይ ነው? ለትምህርትነቱ እንዳትለኝ እስቃለሁ:: የምትማሩ ከሆነ አሁንስ ለምን ታጠፋላችሁ?

ይገርማል፣ ተናጋሪው እኔ ልሁን አይጡ፣ ቋንቋችንም ሰውኛ ይሁን አይጥኛ ሊለይልኝ አልቻለም:: ብቻ ይቀጥላል...

ድንቄም ታሪክ! በዚህ ላይ ይህ ታሪክ እውነት ነው፤ ይህኛው ውሸት ነው ትባባላላችሁ:: እኛ ግን እንዴት እዚህ ላይ እንደምንበልጣችሁ ተመልከት:: አይጦች ዘንድ እውነትና ሃሰት የሉም:: እውነትን ስያሜ አሳጥቶ «እውነት» ያሰኘው የእብለት መኖር ነው:: አንተ «እውነት» እያልክ የምትደረድረው ቅብጥርጥር ፌዕሞ ጉዳዮችን አይደለም:: እዚህ ያለ ው መሆን ነው:: መሆን ትረዳለህ? ሁነት አንድ ገፅታ ብቻ ነው ያለው:: ሆነ-ሆነ-በቃ:: ግን እናንተ ለአንድያው ሁነት ሁለት ገፅታ እየፈጠራችሁና ያንኑ በእልፍ አእላፍ መንገድ እየተረጎማችሁ ትራኮታላችሁ:: ይህ ነው የናንተ ታሪክ እርባና:: እንትፍ!

አይጡ ዲስኩሩን እንደጨረሰ ከጠረጴዛዬ ቱር ብሎ ሲሄድ ወደራሴ ተመለስኩ::

* **

ታሪክ ምንድነው? ታሪክ ለምን ይፃፋል? ታሪክ እንዴትና በነማ መፃፍ አለበት?

«ታሪክ ማለት በአንድ የተወሰነ ስፍራ እና ጊዜ ከሚኖር ሕዝብ፣ የግለሰብ ትገብሮ (Experience) ልምድ የተጠናቀረ ሃተታ ነው» ይላሉ አንዳንዶቹ:: በነኚህ ሰዎች አባባል የአንድ ሰፊ ሃገር ታሪክ የሚገኘው ከሁሉም ግለሰቦች የሕይወት ታሪክ ተለቅሞና ተጠናቅሮ ነው:: ዋስ እጠራለሁ እንጂ በዚህ አልስማማም:: እንዲያማ ከሆነ የሚያገዘ እና የሚጨበጥ ጠፍቶ ታሪክ የሚባል ነገር ከመዝገበ-ቃላት ይፋቃል:: እርግጥ ነው፤ በኔ እምነት በአንድ መልክዓ-ምድራዊ ክልል እና በተመሳሳይ ጊዜ የሚገኙ ህዝቦች በጋራ

በአንድ ሃሳብ ላይ ተባብረው ወይም በሃሳቡ ላይ ልዩነት ፈጥረው የሚያካሂዱት ድርጊት ነው::

ታሪክ ሰዎችን በተቀዳሚነት አይፈልግም፣ ድርጊታቸውን እንጂ:: «በዚህ አገር-ምንትስ-የተሰኘ-ህዝብ ኖረ» ማለት ብቻውን ታሪክ አይደለም:: «...ምንትስ የተሰኘ ህዝብ ከዚህ ተነስቶ እዚያ ሄደ፣ ከዚያኛው ህዝብ ጋር ተዋጋ፣ ተዋግቶም ድል ሆነ» ወዘተ ድርጊቱ ታሪክ ሆነ:: ስለዚህ ታሪክ በጊዜና በቦታ የተከሰሰ የአንድ ሕዝብ ድርጊት ነው::

ግን በአንፃሩ የዚህ ድርጊት ቀስቃሽና በኋላም ቀለሙ-ደማቅ ተጠቃሽ የሚሆኑ ዕድል (ጊዜና ሁኔታ) የረዳቻቸው ጥቂት ግለሰቦች ሲሆኑ ነው የምናይ:: አቲላ በጦረኛነቱ እስከ ዛሬ ስሙን ተክሏል:: በርግጥ ግን ጦረኛው የአቲላ ሰራዊት የሚባለው አንጋችና ታጣቂ ነበረ:: ሩስያና ሁለተኛው የአለም ጦርነት ሲነሱ ስታሊን ግንባር ቀደሙ ተዘካሪ ነው:: ግን ስታሊን የጦርነቱ በለስ ከሆነው ሁልቀ- መሳፍርት ከሆነው ህዝብ ጋር ሲተያይ ብዙ ሊጋነንለት አይገባም::

በየእያንዳንዱ ዘመን የአንድ ሃገር ህዝብ ታሪክ ውስጥ የሚገኙ የጊዜው አንጋፋ ሰዎች ጭራሹን ታሪክ የማበጀቱን ዋነኛ ሚና ከመጫወት አልፈው የታሪኩ ባለቤት ሲሆኑ ይታያሉ:: «...ዳኘው ምኒሊክ ወራሪውን የኢጣሊያ ጦር ድል መትቶ መረብን አሻገረው...» ይኸኔ ለኔ የሚታየኝ አንድ ፈረስ ላይ ቁጭ ብሎ እልፍ የጠላት ወታደርን እንደመንጋ ፍየል ከበስተኋላው የሚያባርር፤ መጠኑ ሰማይ ጥግ የደረሰ፤ የፈረሱ ኮቴ ስፋት በጋሻ የሚተመን ምኒሊክ እንጂ በየፈፋና በየጥሻው ባፍ ጢማቸው ተተክለው የቀሩት የሰው ልጆች አይደሉም:: ድርጊቱ ከተካሄደ በኋላ እነሱ አስፈላጊ አይደሉም:: የታሪክ መሳሪያዎች እንጂ ባለታሪኮች

አይደሉም:: «... አፄ ቴዎድሮስ ራስ አሊን ወጉ...»የዚህ አይነቱ አገላለፅም ከላይኛው የተለየ አይደለም:: ሆኖም በሁለቱም በኩል የሕዝብ መሳሪያነት የተገለፀ ይመስላል::

ታሪክ በሕዝብ ላይ ፊቱን መልሶ ወደ ግለሰቦች የሚያተኩርበት ምክንያት ባያገኝም፣ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በሃገር ታሪክ ውስጥ የሕዝብ ድርሻ የታሪክ መሳሪያ መሆኑ ብቻ ያሳዝነኛል::

ይሁን:: ብቻ ለማንኛውም አንድ ሕዝብ በኖረበት ስፍራ ሁሉ ታሪክ ይኖራል:: ግን ታሪክ ለምን ይፃፋል? ያለፈውን ወደ አሁንታ ለመመለስ? እኛን የኋሊት ወስዶ ጥንት በኖሩ ታላላቅና ስሙ-ጥር ሰዎች ስፍራና ጊዜ እንዲሁም የአኗኗር ሁኔታ ለማኖር? ጦርነታቸውን ሲዋጉ አብረን በሃሳብ እንድንዋጋ ለማድረግ? ለምን? ታሪክ ባይፃፍ ምን ጉዳት ያመጣል?


አይጎዳም ለማለት አልከጅልም፣ እንዲያ ማለት የሚያመጣው ብዙ መዘዝ ሊኖር ይችላልና:: ሆኖም በኔ አስተሳሰብ የታሪክ ጥቅሙ መምህርነቱ ላይ ነው:: ምን ዓይነት መምህር? የሰው ልጅ ካለፉ ስህተቶቹ እንኳ መማር የማይችል ፍጡር መሆኑን የሚያሳይ መምህር:: የመማሩ ፈቃደኛነት ቢኖረው ኖሮ ለሰው ልጅ የአንዲቱ ዘመን የውጣ ውረድ ታሪክ ለስንት ሺህ ዘመናት በበቃች:: ይህ አልሆነም:: ከታሪክ የምናየው መማር አለመቻላችንን ወይም አለመፈለጋችንን ነው:: አይጡ ወይም አይጥኛው ሃሳቤ እውነት አለጉ::

ሌላም ሃሳብ ˈለኝ:: በየሃገሩ የሚካሄደውን ታሪክ የተንተራሰ የሕዝ እንቅስቃሴና የርስ-በርስ እልቂት ስመለከት ታሪክን የማየው እንደ አዋሻኪ ሰው ነው:: ሰው

ባለፈው አይኖርም:: በመጪውም እንደዚያው:: የመኖሪያ ጊዜው አሁን ነው:: ታድያ ታሪክን 'ጎሽ! እሰይ!' ብዬ የምቀበለው ለሰው ልጆች ጥሩ የመግባቢያና የወንድማማችነት መሰረት ሆኖ ሳገኘው ነው:: 'እንዲህ ነበር' የሚባል ታሪክ፣ ደም መቃቢያ ከሆነ እንጦሮጦስ ይውረድ!



በሬ ሆይ በሬ ሆይ
ሞኙ በሬ ሆይ
ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ
እልም ካለው ገደል
ገብተህ ቀረህ ወይ?



# የጆቤ ምስጢር

## ሰለሞን ዋስይሁን

የጆቤ ጉዳይ በጨረፍታም ቢሆን «ወደ ሀብት ጉዞ» የተሰኘውን ተወዳጅ የሬዲዮ ድራማ ሳያስታውስ አይቀርም። ጆቤ ግን ልብ የወለደው የፈለሰመው አይደለም። አይን የማያ ማልል በገሃዱ ዓለም ያለ ታሪከኛ ኮረብታ እንጂ።

የኢጣሊያ ወታደሮች የዘረፉትን ንብረት ሁሉ ባህር አላሻገሩም የሚል ጠንካራ እምነት አለ። በመንግስታቸው ትእዛዝ ይሁን፣ በቡድናዊ ቅንጅት ለመገመት ቢያዳግትም፤ የኢጣሊያ ወታደሮች፤ በወረራው ዘመን፤ ከኢትዮጵያ

መንግስትና ህዝብ የዘረፏቸውን ንብረቶች ቆፍረው የቀበሩበት ቦታዎች እንደሆኑ በእድሜ ባለጠጐች የሚነገርላቸው ስፍራዎች አሉ:: ጆቤ እንግዲህ ከነዚህ ቦታዎች አንዱ መሆኑ ነው::

ጆቤን ከሌሎቹ መሰል ቦታዎች ልዩ የሚያደርገው፤ ለባለሙያ ቀርቶ እንዲሁ ሄዶ ለጐበኘው ተራ ሰው እንኳ፤ የሚሰማውንና የሚያየውን በማገናዘብ የሚያሳድርበት ጥር ጣሬ ብርቱ መሆኑ ነው:: «እውነት እዚህ የኢጣሊያ ወታደሮች የቀበሩት ሀብት ወይም ሌላ ነገር ይኖር ይሆን?» ያሰኛል::

ጆቤ ከሶሬ ወረዳ ከሚያዋስነው ተራራማው የጀጁ ወረዳ ክፍል ውስጥ የሚገኝ መለስተኛ ኮረብታ ነው:: በግዙፍ ተራራ ላይ ያለ ትንሽ ጋራ ጆቤ ላይ ሆነው ወደ ምእራብ ሶሬ ከተማን ሲያዩ ወደ ሰሜን ገደማ መልካሳ፣ ወንጂ፣ ቆቃ፣ ናዝሬት ወለል ብለው ይታያሉ:: በተለይ ምሽት ላይ::

ጆቤ የቅርብ ሩቅ ነው:: ከናዝሬት ከተማ የሶስት ሰዓት አስቸጋሪና አደገኛ የላንድሮቨር ዳገታማ ጉዞ ርቀት ላይ የምትገኘው በአርሲ ዞን የጀጁ ወረዳ ዋና ከተማ አርቦዬ ከገቡ በኋላ ጆቤ ለመድረስ በጋማ ከብት ጋራና ገደሉን እያሳበሩ ወደ አራት ሰዓት ገደማ ሽቅብ ያስኬዳል::

ጆቤ የሄድኩት እግረ መንገዴን እንጂ አስቤበት አልነበረም:: አዲስ አበባ ከመቆርቆሯ በፊት ታንፃ በ1984 ዓ.ም በተቀናቃኝ ፀረ- ህዝብ ኃይሎች በአካባቢው ተቀጣጥሎ በነበረ ው ብጥብጥ የወደመችውን የኮለባ ማርያም ቤተክርስቲያን ቅሪቷን ላይ፣ ገድሏን ልሰማ ነበር- ያቀናሁት::

ጆቤና ኮለባ ማዶ ለማዶ የሚተያዩ ኩታ ገጠም

ቀበሌዎች ሆነው:: ከአንዱ ወደ ሌላው ሃያ ደቂቃ ቢፈጅ ነው:: ኮሰባ ላይ ተቀምጦ ጀቤን ሲቃኙት ገና አዲስ የተላጨ መላጣ ነው የሚመስል:: ፍፁም ደን አልባ ነው ለማለት ይቻላል::

«ጀቤ» የሚለውን ቃሉንም ያወቅሁት እዚያው ጀቤ ከደረስኩ በኋላ ነበር:: ትርጉሙም «ብርቱ፣ ጠንካራ» ማለት እንደሆነ ነው የተነገረኝ:: በኦሮሚኛ!

የግራኝ መሐመድ ፈረስ ከዚያ ኮረብታ ላይ ከአደረበት ቀን ወዲህ ነው ስሙ ጀቤ ስያሜውን ያገኘው- አዛውንቶች እንዳጫወቱኝ::

ፀጉረ ልውጥ መሆኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥርጣሬ ቢያሳድርባቸውም ኋላ ላይ የአካባቢው ሰዎች በፍቅር ነበር ሲያስተናግዱኝ የከረሙት:: በንግግራቸው መሀል በተደጋጋሚ እንደመሀላ፣ እንደ ማረጋገጫ ወይም እንደ ጥያቄ የሚያስገቧት አንድ ቃል ነበረች:: «ጀቤን!» «ጀቤን?» ይላሉ:: አስጐብኚዬን ስለ ጀቤ ያወጋኝ ዘንድ ጠየቅኩት:: ህዝቡ ቅን ነው:: በዙሪያዬ የነበሩት የአካባቢው አዛውንት የጀቤን ገድል እየተቀባበሉ አጫወቱኝ::

የጀቤ ታሪካዊ ምስጢርነት ለጊዜው ለአፍታ ይቆየንና እስቲ ሌላ ገፅታውን እንመልከት:: በእርግጥ ጀቤ የሚገርም ጋራ ነው:: ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ያመልክበታል:: ይምልበታል:: ክርስቲያኖች ጀቤ ላይ አውዱን ጠብቀው መስዋእት የሚያቀርቡላት አድርባ አለቻቸው:: የሼሪያን ህግ ይፃረራል ተብለን ተውነው አሉ እንጂ፤ ሙስሊሞችም ከአም ስት ዓመት በፊት እጅግ ደማቅ የሆነ አምልኮታዊ ስነ ስርዓት የሚካሄድበት «መስጊድ» ብለው የቀለሱት ጐጆ እዚያው ጀቤ ላይ ነበራቸው:: ዛሬም አፅሙ (ቅሪቱ)

ሉስ፡፡ የሚገርመው ነገር የመስጊዱ መዋቅሮች (እንጨቶቹ) እንዳሉ ሳይነኩ መቅረታቸው ነው፡፡ «ደኑ አልቆ የማገዶ፣ የጥጆ መቀለሻ፣ ለሞፈር የሚሆን እንጨት እጦት እንዳለ በሚታይበት በጀቤ አካባቢ፣ የዚህ ቤት ከእነ እንጨቱ እንደቆመ እንዴት ቀረ?» ስል፤ ያገኘሁት ምላሽ፤ ህዝቡ መስጊዱን ቢተወውም መስጊዱ የታነፀበትን እንጨት መንካት ለማንም የጀቤ ሰው የሚደፈር ድርጊት አለመሆኑን ነው፡፡

የጀቤ የአምልኮት ስፍራነት ከተነገረኝ በኋላ ለጥቆ የመጣው ወግ በእጅጉ ያብሰለሰለኝ፤ በውስጡ ይዟል ስለተባለው ምስጢር ነበር፡፡

የጀቤ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ፤ ከ56 (ሃምሳ አምስት) ዓመታት በፊት ኢጣሊያ ኢትዮ ጵያን በወረረችበት ወቅት፣ የኢጣሊያ ወታደሮች ከጀቤ ጋራ ላይ ጉድጓድ አስቆፍረው፣ የተቆፈረውን ጉድጓድ አስገንብተው ውስጡ ምንነቱ ያልታወቀ እቃ ቀብረውበታል፡፡

በወቅቱ ሃያ ዓመት ይሆነኝ ነበር የሚሉት አቶ ኢዳኦ ጉደታ ሲናገሩ «ሁለት ቀን ሙሉ በኃይል አስገድደው ሰብስበውን፤ ትልቅ ጉድጓድ ጀቤ ላይ አስቆፈሩን፡፡ የጉድጓዱ አቆፋፈር የተለየ ነበር፡፡ መጀመሪያ ቀጥታ ወደታች በጥልቀት ቆፈርን፡፡ ከዚያ ደግሞ ወደጐን ቆፍሩ ብለው አዘዙን፡፡ እንደታዘዝነው ከቆፈርን ወዲያ፣ ጉድጓዱ በሲሚንቶና በድንጋይ ተገነባ፡፡ በግንባታው ጊዜ፤ ጣሊያኖቹ በሬዲዮ መገናኛ እየተነጋገሩ ነበር የሚሰ ሩት፡፡ ግንባታው ሲያልቅ 'ከእንግዲህ እዚህ እንዳትደርሱ' ብለው አስጠንቅቀው አባረሩ ን» ይላሉ፡፡

ጉድጓድ ከተቆፈረና በሲሚንቶ ከተገነባ በኋላ፣ ጣሊያኖቹ ለምስጢሩ ቅርበት አላቸው ያሏቸውን ባንዳዎችንና ሌሎች

ሰዎችን ገድለዋልም ይባላል።

ጀቤ ጋራ ላይ ከተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ጣሊያኖች የቀበሩት ምን እንደሆነ የሚያውቅ ሰው በጭራሽ አላገኘሁም። ለመገመት የሚደፍር እንኳ የለም። አዛውንቶቹ እንደሚሉት ከሆነ የተቀበረው እቃ የመጣው በትልቅ የጭነት መኪና ነበር። በዚያን ጊዜ የጀቤ ቀበሌ፤ ቦሎ ከሚሰኘውና ከጀቤ በእግር አንድ ሰዓት ተኩል ገደማ ከሚያስኬደው አነስተኛ ከተማ በሰው ጉልበት ብቻ ተሰርቶ በነበረ የመኪና መንገድ ምንነቱ ያልታወቀ እቃ ያጉዋጉዙ ነበር። ያኔ ጀቤ ላይ የደረሰው የጣሊያኖች መኪና ምናልባት መነሻው ከአዲስ አበባ ቢሆን፤ ከአዲስ አበባ ናዝሬት፤ ከናዝሬት ሶሬ፤ ከሶሬ ቦሎ፤ ከቦሎ ጀቤ እያለ የመ ጣ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

በጊዜው የሃያ አምስት ዓመት ወጣት ነበርኩ የሚሉት አቶ ከማል አማኖ «ጣሊያኖች የቀበሩትን ለማወቅ ባልችልም ሲቀብሩት ግን ተደብቄ በርቀት አይቻለሁ» ይላሉ። «መኪናው ከቦሎ የመጣው በምሽት ነበር። በርካታ የኢጣሊያ ወታደሮች በመኪናው ላይ ተሳፍረው ነበር። ጀቤ እንደደረሱም እቃውን ከመኪናው ላይ እያወረዱ ቀብረው ጨርሰው እስኪሄዱ ድረስ ቆየሁ። በማግስቱ ማለዳ ላይ ተደብቄ ሄጄ አካባቢውን ስመለከት፣ የጀቤ ጋራ ብዙ ቦታ እዚህም እዚያም ተቆፋፍሯል። ብዙ ድንጋይ ተፈነቃቅሏል። አፈሩ ተገለባብጧል። ጣሊያኖቹ ይህንን ያደረጉት ሆን ብለው የቀበሩት ቦታ እንዳይታወቅባቸው የፈፀሙት ነው» የሚሉት አቶ ከማል አማኖ፣ እሁንም ድረስ ቢሆን ቦታውን ማለትም ጣሊያኖች ያመጡትን እቃ የቀበሩበትን ቦታ አስታውሳለሁ ይበሉ እንጂ ቦታውን ለመጠቆም ፈቃደኛ አይደሉም። እንዲያሳዩኝ

ብጠይቃቸውም በተለያዩ ሰበቦች ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡

እነሰም በዛ፣ ጀቤ ጋራ ላይ የተፈፀመ አንድ ነገር አለ ብሎ የሚያስጠረጥር ፍንጭ አለ፣ ይህም ከጋራው እናት ላይ በ15 ሜትር ተራርቀው ካሉት ሰፋፊና ጠፍጣፋ ቋጥኞች ላይ በጥልቀት የተቸከሉት የአራት ሴንቲ ሜትር ዲያሜትር ስፋት ያላቸው የብረት ችካሎች ናቸው፡፡ ችካሎቹ በአካባቢው ህፃናትና ወጣቶች ለቁምነገርም ሆነ ለጨዋታ እየተቀጠቀጡ አሁን ከተቸከሉበት አለት ሰርጉደው ነው የሚገኙት፡፡

ማረጋገጥ አልተቻለም እንጂ፣ በእነዚህ ሁለት የብረት ችካሎች ዙሪያ ከአለቶቹ ላይ የሚታየው ነጭ ድንጋይ ሲሚንቶ እንደሆነ ነው የጀቤ ሰዎች የሚናገሩት፡፡ በእርግጥም 55 ዓመት የቆየን ሲሚንቶ ከድንጋይ ለመለየት ለኔ በጣም ነው ያስቸገረኝ፡፡

እዚህ ላይ ቁም ነገሩ ጣሊያኖች እነዚህን ችካሎች ከአለቱ ላይ ከቶ ለምን ተከሉ ነው፡፡ የጀቤ አዛውንቶች «የብረት ችካሎቹ፣ ንብረቱ የተቀበረበትን ጉድጓድ ለጣሊያኖቹ በዘዴ እንዲያመላክቱ የተተከሉ የምስጢር ምልክቶች ናቸው፡፡» በማለት ነው ስለችካሎቹ የሚያስረዱት፡፡ በእርግጥ ይህ እውነት ከሆነ ጣሊያኖቹ በነዚህ አለቶች ላይ ተመስርቶ በጆሜትሪያዊ ቀመር የጉድጓዱን ቦታ በትክክል የሚጠቁም ካርታ አገራቸው ይዘው እንደገቡ ለመገመት ያደፋፍራል፡፡ ጉድጓዱም የተቆፈረበት ቦታ ከቁፋሮው በፊት አስቀድሞ፣ በቀመር ተሰልቶ የታቀደና የተወሰነም ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

የኢጣሊያ ወታደሮች የዘረፉትን ንብረት ለመቅበር እንዴት ጀቤን መረጡ? ገበሬዎቹ የራሳቸው መላምት አላቸው፡፡ የተለያዩ ማሳመኛዎችንም ያቀርባሉ፡፡ የጀቤ ጋራ

ቀጥ ያለ ዳገት ካለመሆኑ የተነሳ ብዙም ከፍታ ያለው ኮረብታ አይደለም:: ያም ሆኖ ግን በቀላሉ ሊታይና ሊለይ የሚችልበት አቀማመጥና ቅርፅ ያለው ጋራ ነው:: ሌላውና ዋነኛው ነጥብ ጀቤ በዚያን ጊዜ መኪና ሊደርስበት የሚችል መሆኑና ከዚሁ ጋር በእጅጉ ለመኖ ሪያነት የማይጋብዝ የዱርነት ባህርይ ያለው ስፍራ መሆኑ ነው:: የጀቤ አካባቢ መሬት ለመቆፈር አስቸጋሪ ያልሆነ አሸዋማ አፈር መሆኑም አንድ የሚጠቀስ ነጥብ ነው:: የጣሊያን ወታደሮች በወቅቱ በሎ ከተማ ላይ ካምፕ ስለነበራቸው ጀቤን ለማየት በጋራው ዝናና ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ተማርከው መርጠውትም ሊሆን ይችላል::

የጀቤ የታሪክ ምስጢርነት በዚህ አያበቃም:: ቀጣይ ምእራፍ አለው:: ጣሊያን ኢትዮጵያን ለቆ ከሄደ ከብዙ ዓመታት በኋላ የዘውዱ አገዛዝ ወድቆ በደርግ ሊተካ ጥቂት ዓመታት ሲቀሩ ሲሉ፣ ጀቤ አንድ ድርጊት ተፈፀመ::

አንድ ሄሊኮፕተር ከጀቤ ጋራ አናት ላይ ታርፋለች:: «ይህ ድርጊት ሲፈፀም አይተናል» የሚሉ የጀቤ ሰዎች በርካታ ናቸው:: ጊዜው ቀረብ ያለ ስለሆነ «በዚያን ጊዜ ገና ያላገባሁ ጉብል ነበርኩ» የሚሉት የ40 ዓመቱ ጉልማሳ አቶ እሸቱ ዳምጤ «ሄሊኮፕተሩ ጋራው ላይ ካረፈ በኋላ ከውስጡ አበሾችም ነጮችም ነበር የወጡት:: ምን እንደሆነ ያላወቅነው መሳሪያ አንዱ ሰውዬ ይዟል:: መሳሪያውን ወደ አይኑ አስጠግቶ ቁልቁል ወደ ምድር ያስተውል ነበር:: ሌላው ሰውዬ ደግሞ ወረቀት ዘርግቶ ያነብ ነበር» ብለዋል::

የሄሊኮፕተሩ ጀቤ ላይ ማረፍ፣ ብዙ አመላካች ጥያቄዎችን ማጫሩ አይቀርም:: የጀቤ ምስጢር በዘውዱ መንግስት ባለስልጣናት ዘንድ ተደርሶበት፣ በምስጢርነት ተይዞ የነበረ ይሆን? ወይስ እኒያ ሰዎች ሁኔታውን

ይከታተል የነበረ ድርጅት (መ/ቤት) የምሁራን ቡድኖች ነበሩ? ያልተመለሱ ጥያቄዎች ናቸው።

ሄሊኮፕተሯ ስታርፍ የጀቤ ሰው ምን ምላሽ እንደሰጠ አንድ የጀቤ አዛውንት ሲናረገሩ «ከበን እናያቸው ነበር። ከጋራው ተቀብሯል ስለሚባለው ነገር የምናውቀውን ያህል እንድንነግራቸው ጠየቁን። እኛ ግን 'ምንም አናውቅም' ብለን ደበቅናቸው። በመጨረሻ የሚያዩትን ካዩ ወዲያ ብዙም ሳይቆዩ 'ይህንን ቦታ በጭራሽ እንዳትቆፍሩ፤ እጅግ አደገኛ ቦታ ነው' ብለው ደጋግመው አስጠንቅቀውን መንኩራኩራቸውን አስነስተው ሄዱ» ብለ ዋል።

ጀቤ የተቀበረው የተዘረፈ ሀብት ሳይሆን የጦር መሳሪያና ቦንቦች እንደሆኑስ? የጀቤን ዳገት ለመስርሰርና የተቀበረውን እቃ ለማውጣት ማንም ሰው እንዳይደፍር የሄሊኮፕተሯ ሰዎች የፈጠሩት የመከላከያ ተንኮል ብቻ እንደሆንስ?


እቃው የተቀበረበትን ቦታ አውቃለሁ ያሉት አቶ ጀማል አማኖ እና ሌሎችም አንጋፋ የጀቤ ሰዎች ስለ ጀቤ ምስጢር ያንን ያህል እውቀት እያላቸው፤ ፈፅሞ ቦታውን ለመቆፈር እንዳይሞክሩ ያገታቸው ፍርሃት እንዳለ አንዳንድ አዛውንቶች አልሸሸጉም። «ጣሊያን ንብረት ከቀበረ፣ በንብረቱ ላይ ቦምብ ማጥመዱ የማይቀር ነገር ነው» ይላሉ። ሁኔታውን ህገወጥ ድርጊት ከመሆኑ ጋር የተቀበረው እቃ እንደታሰበው ንብረት ቢሆን፤ ዘመድ ከዘመዱ፣ ወዳጅ ከወዳጁ አናቁሮ ደም ያቀባባልም የሚለው ሌላው ተጨማሪ ስጋታቸው ይመስለኛል።

በጥቅሉ የጀቤን ምስጢር ሲሰሙት ተረት ተረት ነው የሚመስለው። የጀቤ ምስጢር እውነት ይሁን ሀሰት፤ ታሪክ ይሁን አፈ-ታሪክ መለየቱ እንግዲህ የሀብት አዳኞች (ትሬዠር-ሀንተርስ) ወይም ያገባናል የሚሉ ባለሙያዎች ፈንታ ይሆናል።

የጀቤን እንቆቅልሽ ለመፍታት ጠንካራ መረጃዎች ያስፈልጋሉ። ስለጀቤ የሚኖረው መረጃ መገኛው ደግሞ እዚያው ጀቤ ነው። ከጀቤ ከጋራው ከራሱና እየደከሙ፣ እየጃጁ፣ እየሞቱ ካሉት የጀቤ አዛውንቶች። ይህ አንድ የሚያስጠነቅቀን ነጥብ አለ። የጀቤ ምስጢር ፍፁም እውነት ቢሆን እንኳ፤ ዓመት በዓመታት በተተካ ቁጥር እውነቱ ተረት እየሆነ ይሄዳል። ታሪኩም አፈ-ታሪክ፡



# ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ



# ፍቅርና ፍቅረኞች

*መስፍን ሀብተማርያም*

በሁለተኛው ዓለም ጦርነት አንድ አስደናቂ ነገር ፖላንድ ውስጥ እንደ ተፈፀመ «ሪደርስ ዳይጀስት» በተባለው መጽሔት ላይ ሰፍሮ ተመልክቻለሁ። የናዚ ጀርመን አምባገነንነት በሰፈነባት አውሮፓ ብዙ ሰዎች በየጊዜው ከአሰቃቂ እስር ቤቶች እየተወሰዱ ይረሸኑ ነበር። እና በአንድ ወቅት ከሁለት መቶ የማያንሱ እስረኞች እንዲወጡ ይታዘዙና ሽማግሌዎቹንና አሮጊቶቹን ትተው ሌሎቹን ሊገድሉ ተዘጋጁ። የሚጠበቀው የኮሎኔሉ ትእዛዝ ብቻ ነበር።

ኮሎኔሉ ትእዛዝ ሊሰጥ ሲል አንድ ከሳሳ ሽማግሌ «እባክህ ኮሉኔል! ፍቀድልኝና ለአንዲት ደቂቃ ልናገር!» ሲሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጠየቁ:: «በል ፈጠን በል ተፈቅዶልሀል» አለው ኮሎኔሉ:: «ያንን ወጣት ተመልከተው» አሉ አዛውንቱ «በአንድ እስር ቤት ለሁለት ዓመት ያህል ኖረናል:: ሚስቱን እንደሚያፈቅር ሌት ከቀን ይነግረኝ ነበር:: ሙሽርነቱን ገና ጠግቦ ሳይጨርስ ነበር የታሰረው:: ስለዚህም ዘወትር ሚስቱን እያነሳ ያለቅሳል፣ ይብሰለሰላል:: ምግቡን እንኳን አጣጥሞ በልቶ አያውቅም:: ፈገግታ ከረሳ ቆይቷል:: ስለዚህ አሁን እንድትፈቅድልኝ የምጠይቅህ... እኔ ሞቴን የምጠብቅ ሽማግሌ ነኝ፣ ሚስቴንና ልጆቼን ቀብሬያለሁ:: እባክህ በሱ ምትክ እኔ ልገደል:: እሱን ግን አንድ ቀን ሚስቱን ለማግኘት በቅቶ ፍቅሩን እንዲጨርስ እድል ስጠው::»

በዚህ አነጋገር ኮሎኔሉ ልቡ ተነክቶ እንባ ተናንቀውና ሊረሽኑ የተወሰነባቸውን ሁሉንም ምሕረት አደረ ገላቸው::

ፍቅር የሚሉት ነገር ይሄን ያስደርጋል? እስኪ ይሄን ትተን ወደ ሌሎቹ አጋጣሚዎች ደግሞ እንለፍ::

አንድ ሰውዬ ነበረ:: ይህ ሰው ሳይቤሪያ አምስት ዓመት ታስሮ በሕይወት መቆየቱ ያስገረማቸው የሶቪዬት ባለስልጣኖች «ሌሎች የእስር ቤት ጓደኞችህ በበረዶ እየተሰቃዩ ሲሞቱ አንተ እንዴት ተቋቋምከው?» ሲሉ ጠየቁት:: «ሚስቴን ሁልጊዜም ስለማስብ ብርዱ እምብዛም አይሰማኝም» በማለት ነበር- እርሱም ምስጢሩን የገለፀላቸው::

ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ በጻፉት «አስደናቂ የፍቅር ታሪኮች» ላይ እንደ ተረኩት አንዲት ሴት እጅግ ከመቅናቷ

የተነሳ ያስበችውንና የፈፀመችውን ብናይ ሌላውን የፍቅር አስደንጋጭ ምንነት ይገለጽልናል:: ሴትዮዋ ወጣቱን በጣም ትወደው ስለነበረ ጊዜ-ሞቷ ሲደርስ «ሌላ ሴት ከምታፈቅረው አብሮኝ ቢሞት ይሻላል? ብላ ጌጣ ጌጧ ካለበት ትልቅ ሳጥን ውስጥ ባሏ እንደተደበቀ ቆልፋበት፣ አብሯት መቃብር ቤት እንዲገባ አድርጋለች:: (በዚያን ዘመን የአውሮፓ ወይዛዝርት ጌጣ ጌጣቸውም አብሮአቸው መቃብር ቤት ይቀመጥ ስለነበር) ወጣቱ እንዴት እንዳልዳነ መጨነቁን ትተን የቅናትን ምንነት በፍቅር ስም ብታዘብ ይሻላል::

ደሞ ሌላ እሚያሳዝን ነገር አለ:: ይኸውም ፍቅር በየመንገዱ ሞልቶና በየደሳሳው ጐጆ ተርፎ ሳለ፣ ፍቅርን አጥብቀው እየፈለጉ መፈቀር የማይሆንላቸው ሰዎች መኖራቸው ነው:: ይሄ ዓይነቱ መጥፎ እጣ በኔ ብጤው ቢደርስ ባያስገርምም፣ በሐብትና በሙያ ዝና ባካበቱ ሰዎች ዘንድ የተፈጥሮ አስቀያሚ እርግማንዋ እጅጉን የሚያይልበት ክስተት መሆኑ አያጠያይቅም:: የታወቀው ኮሜዲያን ቻርሊ ቻፕሊን ሴቶችን ሊወድ በሞከረ ቁጥር እነሱ ኮሜዲያንነቱና አስቂኝ የተፈጥሮ ቅርጹ ላይ ብቻ እያተኮሩ አድናቆታቸውን ሲያሳድዱ፣ በዚያ ተጽዕኖ ፍቅር ሊሰጡት ከቶም ደንታ አልነበራቸውም:: ያንን የሚያህል ዓለም ያደነቀው ፊልም ተዋናይ፣ የምታፈቅረው ሴት አጥቶ፣ ከግማሽ ዕድሜው በላይ በብቸኝነት ኖሮ፣ ኖሮ፣ በሃምሳ አራት ዓመቱ አንዲት የአስራ ስምንት ዓመት ልጅ ወዳው የቀረውን ሕይወቱን አብሮአት በደስታ አሳልፏል:: በፈለጉት ጊዜ አሻፈረኝ ብሎ፣ ባሰኘው ጊዜ ብቻ ከች ይላል ማለት ነው? አይ የሱ ነገር! መሳም የለው::

«ፍቅር ፍቅር አሉት ስሙን አሳንሰው፤

ከድንጋይ ይከብዳል ለተሸከመው ሰው::»

ከተባለለት ወዲያ ኃይለኛነቱ መች ያጠያይቃል!

«አሁን ይሄ እግዚአብሔር ይማራል ወይ ነፍሱ፤

ፍቅርና ትዳርን አርጐት ለየራሱ::» ብሎታል ደሞ ሌላው አዝማሪ:: ብቻ አትደንግጡ! በተለይ ባለትዳሮች፤ እግዚአብሔር በርግጥ አልተሰደበም:: ትዳርም ይፍረስ አልተባለም:: አዚመኛነቱ «ምን ታረገዋለህ?» የሚያሰኝ ዓይነት ነው ለማለት ብቻ ነው፤ ፍቅርን::

ለመሆኑ ፍቅር ምንድነው? አምብሮይስ ቢርስ የተባለ አሜሪካዊ ሐያሲ «የሰይጣኖች መዝገበ ቃላት» (The Devils Dictionary) በተባለው መጽሐፉ «ፍቅር ማለት ሰዎች ነገሮች ሲሳከሉላቸው፣ መንግስተ ሰማያት የገቡ እንዲመስላቸው የሚያደርግ ጊዜያዊ እብደት ነው» ሲል ገልጾታል:: ባለቅኔው ኦስካር ዋይልድ ደግሞ በሌላ መልኩ አይቶ ታል::

«ፍቅር፣ በተለይም ከቆንጆ ሴት ጋር የሚያከንፍ ፍቅር፣ ወርቅ አልፈልግም፣ አልማዝ ካልሆነ በስተቀር የሚባልበት የሰው ልጆች ራስ ማታሊያና ከንቱ ድካም ነው» ብሏል:: «ፍቅረኞች ዓለምን ረስተው ዓለማቸውን የሚቀጩ ይመስላቸዋል እንጂ ዓለም ምን ያህል እንደምትረሳቸው አይታወቃቸውም» በማለት ማቲው አርኖልድ የተባለው ደራሲም ተናግሮለታል::

አዋቂዎቹ ምንም ይበሉ ምንም፣ ፍቅር በአግባቡ ከያዙና ከተያዘ አርኪና ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን:: በአግባቡ ካልተያዘ ግን የንትርክ መድረክ እንደሆነ ይቀራል:: በተለይ መረን-የለሽ ቅናት ከታከለበት ጣዕም ይኖረዋል ተብሎ የሚጠበቅ ሕይወት መራራ ይሆናል:: መቸም ፍቅር ሲባል ቅናት የሚታጣበት ክስተት አይደለም:: በማናቸውም ኅብረተሰብና ባህል ያለ ጉዳይ ነው:: ነገር ግን በኛ ኅብረተሰብ

አንዳንዶ እንደሚታመንበት ቅናት የሌለበት ፍቅር ፍቅር አይደለም ማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሴቶች (ወንዶችም ጭምር) ካልቀኑላቸው የተወደዱ አይመስላቸውም፡፡ እንዲያውም መወደዳቸውን ለማረጋገጥና የመወደድን እሳት ለማራገብ ሲሉ ፍቅረኞቻቸውን ማስቀናት ልማድ የሚያደርጉ አሉ፡፡ አላስፈላጊ ቀናታኛነት መጥፎ ባሕርይ ነው፡፡ መጥፎ ባሕርይነቱን ለማረጋገጥ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም፡፡ ቀናተኛው ሰው፣ ቅናቱን ለመደበቅ የሚያደርገው ጥረት ራሱ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡ በጥቂቱ ለመጥቀስ፣ የዓይን እንቅስቃሴን መለዋወጥ፣ ፊትን ወደሌላ አቅጣጫ ዞር ማድረግ፣ አለበቂ ምክንያት መሳቅ ወይም ፈገግ ማለት፣ ነገር መደጋገም፣ የጨዋታ ርዕስ መለወጥ... እና እነዚህን የመሳሰሉ ሙከራዎች ቅናት እንዳይታወቅ ሲባል ትኩረት ለመስረቅ የሚደረጉ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ሆኖም የመደበቁ ጥረት ሁሌም ይሳካል ማለት አይቻልም፡፡ ያልተለመደ ጠባይ እንቅስቃሴና አነጋገር፣ አመለካከት እዚያው ይጋለጣል፡፡ ፍጹም ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ቅናትማ ነጭናጫና የመሰላቸት ምልክትም ይታይበትና (ዞር በሉ ካጠገቤ አይነት) ወይም ድንገት አፈናጥሮ «አመመኝ ጋደም ልበል» ያሰኝና ለባለ ትዝብት ይዳርጋል፡፡

ቀናተኛ አፍቃሪ (መረን ያጣው) ነገር ፈላጊነቱ አይኖቹ ላይ ያስታውቁበታል፡፡ ገና ውይይት ታክሲ ውስጥ ፍቅረኛውን ይዞ ሲገባ ከተቻለው የአይኗን ማማተር ለመቆጣጠር እሚመቸው ቦታ ያስቀምጣታል፡፡ እፊቷ የተቀመጡትን ተሳፋሪዎች አንድ ባንድ ይቃኛል፡፡ ጉዞው ሁሉ እሷን እያሰበ ነው የሚሆነው፡፡ ማንን ሰላም አለች? ለማን ፈገግ አለች? ምን ታስባለች?... በተለይ ግብዣ ቦታ እንዲህ አይነቱ አፍቃሪ በጨዋታ ላይ ከወቅቱ ሁኔታ በተሳትፎም በሐሳቡም ስለሚለይ በደመቀው ስነ-ስርዓት

ላይ ግር ያለ ድባብ ሊያስከትል ይችላል። ከመጠን ያለፈ ቅናት ትኩረቱ ሁሉ ፍቅር ላይ ስለሚሆን ጨዋታ ከመደጋገም አልፎ ተርፎ ነገሮችን እዛው በዛው ያስረሳል። የመርሳት ነገር ከተነሳ «ከጐረቤት ሰው ጥሪልኝ» ተብላ ስልኩን ከፍቱን እንደተወችውና የመኪና ክላክስ ስትሰማ ሮጣ ጥልቅ ብላ የሄደችው ሴትዮ ሁኔታ ከሰማኋቸው አስገራሚ ነገሮች አንዱ ነው። እንደዚያ ተቻኩላ ስልኩን እንደረሳችው የሄደችው ፍቅረኛዋን ፍለጋ በጉጉት ተመስጣ ስለነበረ ነው አሉ። ኃይለኛ ቀናተኛ ሳትሆን አትቀርም። አለበለዛማ ጤናማ ፍቅር አንድን ምስኪን ስልክ ደዋይ እንዴት እንዲህ ጉድ ሊሰራ ይችላል?!

ሆኖም ይሄንን ሁሉ ተናገርን እንጂ ቅናት በሚያጠቃው አፍቃሪ ላይ ሁል ጊዜም እንፍረድበት ማለታችን አይደለም። አንዳንዱ የማይቆጣጠሩት የተፈጥሮ ጣጣ ስለሚሆን «እግዚኦ ሰውረነ ከመዓቱ» ማለቱ ሳይሻል አይቀርም። ይሄን የሚቃወም ካለ በሰው ሰርግ ላይ የሚጣሉ ወይም ራሳቸው በደገሱት ግብዣ ላይ የሚኩራረፉ ባልና ሚስት እንኳ ሊኖሩ እንደሚችሉ ማወቅ አለበት። መቸም ነገሩ ምን ያህል እንደሚዘገንን ለማንም ግልጽ ነው። በቅናት ያኮረፈ ሰው ያስፈራል። ማስፈራቱን ለመደበቅ የሚያየው መከራ ደሞ ይበልጥ ያስጨንቃል።

ፍቅር የሚሄድበት መንገድ አይታወቅም። አሮጊቷን ከወጣት፣ ሽማግሌውን ከኮረዳ፣ ሊቁን ከመሐይም፣ ሀብታሙን ከድሀ ያቆራኛል። ታዲያ በዚህ ጊዜ የመፈራራቱ ድልድይ የተቻለውን ያህል መጥበቡ አይቀርም። በሌላ በሌላ ሁኔታ ደግሞ የዚያኑ ያህል መቃረንና አለመጣጣም ይኖራል። በአስተሳሰብ፣ በዓላማ፣ በእርካታና በመሳሰለው ሁሉ ያደጉበት ኅብረተሰብ እሴትና እምነት፣ እንዲሁም

የኑሮ መደብ ባልቃ እየገባ ችግር ሲፈጥር ይችላል።

እንዲያ ያሉት ቁርኝቶች ሲታሰቡ ለአጋጣሚው ሰበብ የሚሆኑት ሁኔታዎች ሁሌም ባይሆን አስገራሚ ናቸው። ባልጠበቁት ቦታ፣ ለምሳሌ ታክሲ ወይም አውቶብስ ውስጥ ተያይተው፣ ተዋውቀው ፍቅር ሊጀመርና ለትዳር ሊበቃ ይችላል። መጀመሪያ ተጣልተው በኋላ የሚፋቀሩ፣ ሳይተያዩ በስልክ ተዋውቀው የሚጋቡ... በዝናብ መጠለያ፣ በገበያ፣ በሲኒማ ቤት ሁሉ ቅጽበቱ የሚያገናኛቸው አሉ።

ፍቅርም ሲጀማምር እንዴት እንደ ሚያደርግ የደረሰባቸው ያውቁታል። የዓለምን የዘፈን ግጥሞች ያጣበበው «መናፈቅ» የመጀመሪያውን ደረጃ ሳይዝ አይቀርም። በሀሳብ ፈረስ ጭልጥ ብሎ ወደ ፍቅረኛ መሄድ ወይም ያለፈውን ውሎ አዳር በአይነ ሕሊና ማየትም («ትዝታ» እሚባል ቆንጆ ስም ወጥቶለታል) የሚቀጥለውን ደረጃ ሳይወስድ አይቀርም። ከዚያ ወዲያ ያለውን... እንቅልፍ ማጣቱን፣ ጭንቀት ጥበቱን፣ ራስ ምታቱን፣ ትኩሳቱን፣ ብርዱን፣ ቁርጥማቱን ቤቱ ይቁጠረው። ነገሩ እንደ አፍቃሪውና እንደ ሁኔታው ይለያያል። አንዱ ፍቅርኛው ስትቀርበው እንደ ሙጫ ተጣብቆ ባይላቀቅ ደስ ሲለው፣ ሌላው ሲያገኛት ቀለል ይልለትና ስትርቀው ይንሰቀሰቃል። አንዱ ተውኩ ያለውን ሲጃራ በላይ በላዩ እያቀጣጠለ የክብሪት እንጨት ሲቆራርጥ ይውላል («ሲጃራ እጠጣለሁ ላንቺ ስል ላንቺ ስል፣ በየወረቀቱ አገኘሽ ይመስል») ሌላው እህል አስጠላኝ ይልና የገዛ ጣቱን ጥፍር በጥርሱ መከርከሙን ይያያዘዋል። («ይሄ ፍቅር ማለት ምንኛ ጉድቶኛል፣ ውሀ እንደ ቁም ነገር ስጠጣው ያንቀኛል!»)

ታዲያ ይሄን አልን እንጂ ፍቅር በየደረሰበት አንቆ እሚይዘው አመጣጡን አካሄዱን የሚያውቅ ክፉ በጉውን የለመደ ሁኔታው ከወትሮው ምንም ያህል ለውጥ

የማያመጣበት ሰው እንደሚኖር መዘንጋት የለብንም፡፡ እንዲህ አይነቱ ሰው «እንደ ሁኔታው» ሁሉንም ኮስተር ብሎ ይችለዋል፡፡ ፍቅር ሲመጣ «እሰየው» ሲሄድ ደሞ «ቻው»፡፡

በብዙ አፍቃሪዎች ላይ የጠባይ መለወጥ (ጊዜያዊም ቢሆን) መታየቱ ግን አሌ አሚባል አይደለም፡፡ አንዳንዱ ከመሬት ተነስቶ ዝምተኛ ይሆናል፡፡ ለምን ዝምተኛ እንደሆነ ካጠቃችሁበት ደሞ አለ በቂ ምክንያት በማከታተል ያወራል ወይም ውስጡን የምታዳምጡበት እየመሰለው ይለፈልፋል (በጨዋኸት ሊሆን ይችላል)፡፡ አንዳንዱ የሱን አፍቃሪነት የሚነካካለት ወይም የሚያስታውሰውን መጽሐፍ እየፈለገ ያነባል፡፡ ወሬም ከሆን ከዛ ውጭ ላለው ደንታ አይኖረውም፡፡ የሚያየውና የሚሰማው ሁሉ በዚያ አቅጣጫ እንዲሄድለት ይፍልጋል፡፡ በአፍቃሪ ላይ የሚደርሱ ነገሮች ብዙውን ጊዜ ለራሱ የታወቁት አይመስለኝም፡፡ ለምሳሌ «ፍቅር መሆኑን ያወቅኩት ቆይቼ ነው፡፡ በአንድ ወቅት ዙር ዙር፣ ሂድ ሂድ የሚል ልማድ ተፈጥሮብኝ ነበር» ያለኝ ሰው አለ፡፡ በዚህ ዓይነት የናንተን አላውቅም እንጂ አንድ የሰማይ ስባሪ ሊያህል ምንም የማይቀረው ወደ ሀምሳ ዓመት እድሜ የተቃረበ አዋቂ ሰው፣ ፍቅረኛው ልትለየው ስትል ቀውስነት ሊደርስበት አስፈራርቶት ሳለ «ምን ሆንክ?» ብዬው «ጨቤህ ጨቤህ ይለኛል» ብሎ እንደመለሰልኝ ትዝ ይለኛል፡፡ እና... በእውነቱ ሳቂታው ቁጡ፣ ቀልደኛው አኩራፊ፣ ሰላምተኛው ኩሩ፣ ጉብዙ ፈሪ፣ ትሁቱ ግደለሽ... በተቃራኒው ደግሞ አመንዝራው ጥንቁቅ፣ ሸርዳጁ ገለልተኛ፣ ውሸታሙ እውነተኛ፣ ባለጌው ጨዋ ሲሆን የመቻሉ ጉዳይ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ነገሩን በዚህ ለመግታት... እናንተስ ስታስቡት ለምሳሌ ፍቅር የያዘው ሰው ሞኝ ቢመስል ምን ያስገርማል? ከፍቅረኛው ሌላ ማየት ቢያስጠላውስ እንደት

እንግዳ ነገር ሊሆንባችሁ ይችላል? እሱ ለራሱ የሚያየው ሩቅ ሩቅ... ሌላ ቦታ፣ ሌላ ሁኔታ! ከፍቅረኛው ጋር:: ከሰማው ሙዚቃ በስተቀር ሌላው ጨኸት ሆነብኝ ቢላችሁስ እንዴት ትፈርዱበታላችሁ? እሱ ለራሱ ጆሮው ዝም ብሎ ተገተረ እንጂ የሚሰማው የሩቁን! የአንድ ቀኑን... የዛን ለቱን... የእንትን ጊዜውን...

ፍቅር ጥሩ መኖርንም ይጠይቃል:: ጥሩ ለመኖር ደሞ ብር ያስፈልጋል፤

«ትንሽ ይበቃዋል ለፍቅር መፍረሻ

ስር ስሩን ካልሄደ የገንዘብ ወጌሻ»

ሲል አንድ ጓደኛዬ የጻፈው ያለ ምክንያት አይደለም:: በርግጥ ገንዘብ አጋዥ ኃይል ነው:: በአቅም መጠን ፍላጐት ከተሟላና የጭቅጭቅ በር ከተዘጋ መዋደድ ይለመል ማል:: መግባባትና መተሳሰብ የመንፈስ ጥንካሬና ሀቀኝነት ካልተጨመሩበት ግን ቢለመልምም ለፍሬ አይበቃም:: ትእግስትም የገንዘብን ያህል (እንዲያውም በይበልጥ) ለሰላማዊ ውጼታ፣ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: ገንዘብ ተትረፍርፎ ትእግስት ከጠፋ ውጤቱ ክፉ ይሆናል:: ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ፍቅር ፀብ ነው ብለው የሚያምኑ ይመስል፣ የሚወዷትን የሚገድሉት ትዕግስት በማጣታቸው ነው:: የዚህ መነሾው መረን ያለፈ ሰይጣናዊ ቅናት ብቻ ሳይሆን፣ ራስ መውደድና ስግብግብነት መሆኑ አያጠያይቅም:: በዚህ አጋጣሚ አንዲት ወጣት ሐውልት ላይ የተጻፈ ሁለት መስመር ጠቀስ አድርጌላችሁ ወደ ሚቀጥለው ልለፍ:: ወጣቷ በእድሜ ብዙ በማበልጣት አፍቃሪ ነኝ ባይ የተገደለች ናት:: ጽሑፉ «በእድሜ አባት ሊሆናት በሚችል ሰው በአራት ጥይት ተገደለች» ይላል::

እንዲህ ያለው አሳዛኝ ሁኔታ፣ የሰዎችን ድክመት በጉልህ የሚያሳይ ነው። ይሄ ሲገርመን በአይን ፍቅር መለከፍ አለ። በአይን ፍቅር መለከፍ ሲገርመን፣ በስተርጅና ወጣት መውደድ፣ በወጣትነት ሽማግሌ መውደድ አለ። የገዛ ራስ እስረኛ ሲኮን ደሞ አለ እድሜ መንከሶ ካዩዋት ጋር ሁሉ አይንን እያንከራተቱ መሰቃየት ይኖራል። ቆበቀንጥ ምንኩስና የሚሉት። እሱንስ ጊዜያዊ ፍቅር ብንለው አያስኬድ ይሆን?!


ፍቅር በእውነትም እውር ነው። በገሀድ ያላነጋገሩትን ሰው በሕልማዊ መንፈስ ያገኙት የሚያስመስል፣ ሌላ ተቃራኒ ጾታ አሳቅፎ አብረን ያሉ የሚያስመስል፣ የምትሐተኞች ሁሉ ምትሐተኛ ነው። በአጠቃላይ ሲታይ የማፍቀር ነገር ቦታና ጊዜ አይመርጥም። ተውኔቱን ትቶ ተዋናይቱን መውደድ፣ስራን እርም ብሎ ትቶ አለቃን መውደድ ለመታከም ሄዶ ሐኪሙን፣ ለትምህርት መጥቶ አስተማሪውን... ምኑቅጡ! በዚህ አጋጣሚ ካትሪን ማንስፊልድ የተባለችው ደራሲ አንዲት ወጣት ከእጮኛዋ ጋራ ተቀምጣ ፊልም ስታይ ደስ ያላትን ተዋናይ ደጋግማ እያየች፣ በብርሃን እንቅስቃሴ ብቻ እንዴት ተመስጣ ፍቅር እንደያዛት የሚተርክ አጭር ልቦለድ መጻፏ ትዝ ይለኛል። ማክሲም ጐርኪም ሀያስድስት ስድስት ዳቦ ጋጋሪዎች አንዲትን ሴት በመስኮታቸው በየቀኑ እያዩ እንዴት እንደወደዷትና ስትቀር ቅር እንደሚሰኙ ለዛ ባለው ብእሩ ነድፎታል።

እኔ ደሞ እንደ ዘበት የማደንቀው በኑሮ መደባቸው የሚመሳሰሉ ወይም የሚቀራረቡ ሰዎች የሚቋደሱትን ቅልብጭ ጥፍጥ ያለ ዓይነት ነው። እንዲህ ያለው ፍቅር የአክራሪነት ባሕርይና የልምሰል- ልለወጥ ውጣ ውረድ

የሌለበት ከመሆኑም በላይ በአጉል መቀናጣት የተበከለ አይሆንም:: የጀመርነው ጉዳይ ከሆነ ይሆናል:: ካልሆነም የራሱ ጉዳይ:: በዚህ ዓለም ችላ ባይነት የሚከሽን መዋደድ ይኳል ይሄ ነው:: ለምሳሌ አንድ የትልቅ ቪላ ዘበኛ እንውሰድ:: ብርድ ልብስ ለብሶ አንዳንዴ ነጠላ ስለሚቋጭና ፍልጡን ፈላልጦ ማገዶ ሁሉ ሲያስገባ ውሎ ዱላ ብጤ ይዞ ስለሚንጐራደድ ብቻ ፍቅር የማይዘው እንዳይመስላችሁ:: እንዲያውም እያንዳንዷ የሚቋጯት የነጠላ ቋጭት የግል ትዝታውን የምታስተጋባ ሆና፣ ብርድ ልብሱም በቅዝቃዜ የሚያስቃየው ሆኖ ልታዩት ትችላላችሁ:: እጐኑ ካለው ሌላ ቪላ ቤት የቤተሰብ ልብስ ከምታጥብ ቆንጆ ጋር ምን የመሰለ ፍቅር ሊኖረው ይችላል:: በአታክልት አጥር ቢለያዩም በሳምንታዊ እረፍታቸው በእርካታ ከመክነፍ ማንም አያግዳቸውም:: ከሴሲቱ ዝናብ ካፊያ ጋር ሕልማቸውን እየተያዩ በመነፋፈቅ ብቻም አይወሰኑም:: እሱ በር እየከፈተ እሷም ልብሷን እያሰጣች ለሌላ በማይገባ ቋንቋና ዜማ ድብቅ ምስጢራቸውን ሊወያዩ ይችላሉ::

ታዲያ «ታላላቅ» ፍቅረኞች የሚሰቃዩበት ስነ-ልቦናዊ በሽታ እነዚህን እምብዛም አለመጠናወቱ ምንኛ ደስ ይል መሰላችሁ?! እነሱ ዘንድ ቅናት ማለት በክልላቸው የሚያጤኑት ነገር ነው:: ከክልላቸው ቁጥጥር ውጭ ከሆነ ብዙም አይሰቃዩበትም:: ሂያጁ ቢያልፍ፣ መጪው ይመጣል- ምን ማድረግ ይቻላል ነው ፍልስፍናው:: የቀኑን መርዘም አድካሚ ስራ እየሰሩ፣ መፋቂያ እያኙኩ ወይም እያንጐራጐሩ ማሳለፍ ይቻላል:: የትዝታ አዚም ቢያንቅም አይገላቸውም:: ለአውዳመት የሚገዙትን ጨርቅ ሲያስቡ መዋል ማደሩ ራሱ ቶሎ እንዲያገግሙ ያደርጋቸዋል:: ምነው ፍቅር ሁልጊዜም እንደዚህ በሆነ!

ምንም ይሁን ምንም ፍቅር በአመዛኙ ሲታይ፣ ከአንዳንድ ችግሮቹ በስተቀር ያምራል:: ፍቅር የጥላቻ ተቃራኒ ብቻ አይደለም:: የታላላቅ ስራዎች፣ <ሙያዎች> መወጣጫ፣ የኑሮ እርካታ መገናኛና የሌሎች እሴቶችም ደጀን ነው:: እናትን ከመሳም ተነስቶ በወጣትነት፣ በጉልማሳነት፣ አብቦና አፍርቶ፣ በአዛውንት ደረጃ የልጅ ልጅ ለመሳምም የሚያበቃ ነው:: የፍቅረኞች አኳኋን ጭቅጭቅ በሌለበት ቦታ ሁሉ ደስ ይላል:: ሾላ ወይም ኮተቤ ሲናፈሱ ውለው በሚኒባስ ታክሲ ውስጥ ተዝናንተው፣ በኋላ ቁጭ ብለው በአይናቸው የሚነጋገሩ ጉረምሳና ኮረዳ ፍሜአቸው እምን ይደርስ ይሆን? የሚያሰኙን ለፍቅር ትልቅ ግምት ስለምንሰጥ ነው:: የዚያኑ ያህል ትዳር ያለው ሀብታም ሰው ወድዳ፣ ፍቅር በሷ ብቻ አይሎባት በናፍቆት የገረጣች ሴተኛአዳሪ ስናይ ልባችን የሚነካውም ወሰን የለሽነቱ እያስገረመን ነው::



# ውርርዱ

አንቶን ቼኾብ
ትርጉም - አፈወርቅ ዘለቀ

የፀደዩ ወራት ምሽት ከነጐደ የትየለሌ ቢሆነውም፣ ሽማግሌው የባንክ ባለሙያ ግን እንቅልፍ በዓይኑ አልዞር ብሎት በጥናት ክፍሉ ውስጥ ይንጐራደዳል፡፡ ሕሊናውን እንደዚያ ያናዘዘው ደግሞ ልክ ከዛሬ 15 ዓመት በፊት

ተካፍሎበት በነበረው አንድ የእራት ግብዣ ላይ እንደዋዛ ተነስቶ የነበረ ክርክር ያስከተለው ጦስና መዘዝ ነበር:: ስዚያም ሰጦሩ ክርክር መንስኤው የሞት በቃ ፍርድ ጉዳይ ሲሆን በአብዛኛው የውይይቱ ተሳታፊዎች ዘንድ ይህን ፍርድ የሚደነግገው እንቀጽ ሰብአዊ ርህራሄን የተራቆተ እንደመሆኑ ከማናቸውም መንግስት ሕግ መሰረዝ አለበት የሚል አስተያየት ሰንዝሯል::

እንደ እነርሱም እምነት የሞት ፍርድ በዓለም አቀፍ ደረጃ በእድሜ ልክ እስራት መተካት ነበረበት:: ታዲያ በዚያን መሀል ነበር አንዱ ከመካከላቸው በማፈንገጥ ለየት ያለ አቋሙን ማንፀባረቅ የጀመረው::

«በእርግጥ እኔ የሞት በቃውም ሆነ የእድሜ ልክ እስራቱ ፍርድ ደርሶብኝ አልቀመስኩትም:: ይሁን እንጂ በበኩሌ እንደምገምተው እድሜ ልክ ለእስራት ከመዳረግ ይልቅ አንዴ ሞቶ መገላገሉ ይሻላል ባይ ነኝ:: ስለዚህ ማናቸውም ለሰብአዊ ስሜት ተቆርቋሪ ነኝ የሚል ሊደግፈው የሚገባው ከመቅፅበት ገድሎ የሚያሳርፈውን የሞት ፍርድ እንጂ በስቃይ የሚገዘግዘውን የእድሜ ልክ እስራት መሆን የለበትም!» በማለት ነበር የተናገረው::

ሌላው አዛውንት ደግሞ ከርሱ ቀበል በማድረግ «ሁለቱም ፍርዶች ሥነ ምግባር የጎደላቸው ናቸው»

በማለት ማሳመኛ ነጥባቸውን መደርደር ቀጠለ፡፡ «የሁለቱም ዓላማ ዞሮ ዞሮ ሕይወትን፣ ነፃነትን በመንጠቅ፣ በማሳጣት ላይ ያተኮረ እንደመሆኑ ካንዱ ሌላው ይሻላል ብለን የምናማርጣቸው አይደሉም፡፡ በእኛና ሁለቱም ሊወገዙ ሊወገዱ ይገባል፡፡ ስለምን ሕይወትን የሰጠን እግዚአብሔር እንደመሆኑ ከእርሱ በስተቀር መንግስትም ቢሆን ሊዳፈረው አይገባም» በማለት ደመደመ፡፡ ይሁን እንጂ በእድሜ ለጋ የሆነው የሃያ አምስት አመቱ አማካሪ የበኩሉን አስተያየት ከመሰንዘር አልተቆጠበም ነበር፡፡ እርሱም «በእርግጥ ሁለቱም ፍርዶች ሥነ ምግባር የጎደላቸው ለመሆናቸው ሁላችንም ያመነበት ቢሆንም እንደእኔ የግድ ሆኖ አንዱን ምረጥ ቢባል ያለምንም ማመንታት ምርጫዬ የእድሜ ልክ እስራቱ ይሆናል፡፡ ምንም ቢሆን እስከዘላለሙ ከማሸለብ ለአንዲት ቀንም ቢሆን በሕይወት መቆየቱ ይሻላልና ነው!» ሲል ተናገረ፡፡

እንግዲህ በዚያን አጋጣሚ ነበር ዛሬ በትካዜ የተዋጠው የባንኩ ባለሙያ «ለምን የማታደርገውን ትናገራለህ? አሁን ያልከው ሁሉ ቅጥፈት ለመሆኑ በ2ሚሊዮን ሩብል እወራረዳለሁ፡፡ እድሜ ልክህን ቀርቶ አምስት ዓመት እንኳን በእስር ለመቆት ፈቃደኛ አትሆንም» ሲል ጣልቃ በመግባት የተናገረው፤ የሕግ አማካሪው በተራው «የምር የምትወራረደኝ ከሆነ፣ አምስት አመት ሳይሆን ለአስራ አምስት ዓመት በእስር ለመቆየት

ፈቃደኛ ነኝ» ሲል መለሰለት።

«አስራ አምስት! ያንተ ያለህ» በማለት ጮኸ ባንክኛው፤ ከዚያም ወደ እንግዶቹ በመዞር «የተከበራችሁ እንግዶች ሆይ! 2 ሚሊዮን ሩብል እመድባለሁ» አለ። ወጣቱ የሕግ አማካሪም «አንተ 2 ሚሊዮን መድብ እኔም ነፃነቴን» በማለት በውርርዱ መስማማቱን ገለፀ።

እነሆ ይህ ስብዓዊነት የጎደለው አስገራሚ ውርርድ ተግባራዊ ሆነ። በወቅቱ ብዙ ሚሊዮን ሩብል ያንቀሳቅስ የነበረው ባንክኛ ዛሬ በትዝታ ሰጥሟል።

በምሽቱ የእራት ስነስርአት ላይ ባንክኛው ጠበቃውን በቀልድ መልክ «... ውሳኔህን ብታጤነው መልካም ነው ... ማባፊያው ሳያጥርህ! 2ሚሊዮን ሩብል ለኔ ምኔም አይደለች። አንተ ግን ሶስት ወይም አራት ምርጥ አመታት ከህይወትህ ላይ ልታባክን ነው። ሶስት ወይም አራት አመት ማለቴ ያለ ምክንያት አይደለም። ከዚህ በላይ መቆየት እንደማትችል እርግጠኛ ስለሆንክ እንጂ! ልትገነዘበው የሚገባ ነገር ብቻ በፈቃደኝነት እስረኛ መሆን በህግ ትእዛዝ ከመታሰር የከፋ መሆኑን ነው! እና አሳዝነኸኛል ሀሳብህን ቀይር።» ሲልም ሊያግባባው ሞክሮ ነበር።

እነሆ ዛሬ ከ15 ዓመታት በኋላ በክፍሉ ውስጥ

በመንገራደድ እነዚህን ሁሉ ገጠመኞች በማስታወስ ራሱን ጠየቀ «ለምን ይህንን ውርርድ ተወራረድኩ? ጥቅሙስ ምኑ ላይ ነው? ጠበቃው 15 ዓመታት ከህይወቱ ላይ አባከነ:: እኔም 2 ሚሊዮን ሩብሌን ወረወርኩ:: ይህ ድርጊቱ «የሞት በቃ ፍርድ በአስከፊነቱ ከእድሜ ልክ እስራት ይሻላል የሚለውን የሰዎች አስተሳሰብ ይለውጣልን? » ሲል ራሱን ጠየቀ:: በመጨረሻም «በፍጹም! ሁለቱም የማይረቡ ድርጊቶች ናቸው:: እንደእኔ እንደእኔ የጠበቃው ችኩልነትና ገንዘብ ወዳድነት መዘዝ ነው፣ እነዚህ ሁኔታዎች እንዲከሰቱ ያደረገው::» ሲል ደመደመ::

ባንከኛው ከምሽቱ ግብዣ በኋላ የሆነውን ሁሉ አንድ ባንድ አስታወሰ:: በውርርዳቸው መሰረት በግብዣው ማግስት ወጣቱ ጠበቃ በባንከኛው ግቢ ውስጥ ባለ አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ሆኖ እስራቱን እንዲጀምር ተወሰነ::

በእስር ቆይታው የተጣለበት ማእቀቦች ከተወሰነለት ክልል አለማለፍ፣ ሰዎችን ማየትና ማነጋገር፣ ደብዳቤና ጋዜጣ መቀበል አለመቻል ናቸው:: የተፈቀዱለት ነገሮች ደግሞ የሙዚቃ መሳሪያዎች ማግኘት፣ መፃህፍት ማንበብ፣ ደብዳቤ መፃፍ፣ ወይን ጠጅ መጠጣትና ሲጋራ ማጨስ ይገኙበታል:: ከውጭው

አለም ጋር ያለው ግንኙነት ድምጽ አልባ እንደመሆኑ በስምምነቱ የተፈቀዱለትን ነገሮች ለማግኘት ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀ ትንሽ መስኮት በኩል ማስታወሻ ጽፎ በማስቀመጥ ማግኘት ይችላል::

በተጠቀሰው ውል መሰረት ጠበቃው ለ15 ዓመት ማለትም ከ1870 ህዳር 14 ቀን ከሌሊቱ 6 ሰዓት፣ እስከ 1885 ህዳር 14 ቀን ከሌሊቱ 6:00 ሰዓት ድረስ በእስር የመቆየት ግዴታ አለበት:: ጠበቃው ከዚህ ስምምነት ጥቂት ውልፍት ቢል ወይም ለደቂቃዎች እንደ ቀድሞ ቢወጣ ባንክኛው በውርርድ ይረታል:: ጠበቃውም ቤሳ ቤስቲን አያገኝም::

ከጠበቃው የግል ማስታወሻ እንደምንረዳው በመጀመሪያው አንድ አመት በብቸኝነቱ የተነሳ በጣም ተሰቃይቶ ነበር:: ከተከለለበት ታዛ፣ ቀንም ሆነ ማታ የፒያኖ ድምጽ ይሰማ ነበር::

ከአንድ ዓመት የእስር ቆይታው በኋላ ጠበቃው ወይን ጠጅና ትንባሆ እርም አለ:: ስለውሳኔው በማስታወሻ ደብተሩ ላይ እንደዘገበው 'ወይን ጠጅ ፍላጎትን ያነሳሳል:: ፍላጎት ደግሞ የእስረኛ ቀንደኛ ጠላት ነው:: በተጨማሪም ጥሩ ወይን ጠጅ አለአዳናቂ ለብቻ እንደመጠጣት የሚያስጠላ ነገር የለም:: ትምባሆም የክፍሉን አየር ይበክላል' ሲል አስፍሮ ነበር::

በመጀመሪያው አንድ ዓመት ጠበቃው ቀለል ቀለል ያለ መፃህፍትን ሲያነብ ቆየ:: በሁለተኛው ዓመት ላይ አልፎ አልፎ ከእስር ቤቱ ይሰማ የነበረው የሙዚቃ ድምፅ መሰማት አቆመ:: በምትኩም ጠበቃው መጠቅ፣ መጠቅ ያለ መፃህፍትን መጠየቅ ጀመረ:: በአምስተኛው ዓመት ደግሞ ሙዚቃው እንደገና መሰማት ከመጀመሩም፣ እስረኛው ጠበቃ ወይን ጠጅ ጠየቀ:: በወቅቱ ሁኔታውን ይከታተሉት የነበሩት ዘበኞች እንደገለፁት እስረኛው ዓመቱን ሙሉ ያሳለፈው በመብላት፣ በመጠጣትና በመጋደም ነበር:: ያዛጋል ይነጫነጫል መጽሀፍትን ማንበብ አቁሟል፤ አልፎ አልፎ ምሽት ላይ ለመፃፍ ይቀመጥና ሲጽፍ አድሮ ጠዋት ላይ ቀዳዶ ይጥለዋል:: ካንዴም ሁለቴ ሲያለቅስ ተደምጧል:: በስድስተኛው ዓመት አጋማሽ ላይ እስረኛው የቋንቋ፣ የፍልስፍናና የታሪክ መፃህፍትን እንደጉድ ማጥናቱን ተያያዘው:: ከእስረኛው ፈጣን ንባብ የተነሳ ባንከኛው እስረኛው በጠየቀው መጠን መፃህፍት ማቅረብ ትልቅ ስራ ሆኖበት ነበር::

በቀጣዮቹ አራት አመታት ብቻ ወደ ስድስት ሙቶ የሚጠጉ ዳጐስ ያሉ መፃህፍት በእስረኛው ጥያቄ ቀርበዋል:: ይህም ገደብ የለሹ የመፃህፍት ጥያቄ ከእስረኛው አንድ ለየት ያለ ደብዳቤ እስከተጻፈ ድረስ አላቋረጠም:: የእስረኛው ደብዳቤ መልእክት፣

«የተከበርከው አሳሪዬ ሆይ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በስድስት የተለያዩ ቋንቋዎች ነው የፃፍኳቸው። ለሙያው ጠቢባን አሳይልኝ። አንብበውት ምንም ስህተት ካላገኙበት ድካሜ መና አለመቅረቱን እንድረዳ፣ ከጓሮ አትክልትህ አካባቢ ጠመንጃ አስተኩስልኝ።

«በየትኛውም ዘመን በየትኛውም አገር ያሉ ጠቢብ ንግግራቸው በተለያየ ቋንቋ ነው። ይሁን እንጂ በሁሉም አንደበት ውስጥ አንድ አይነት የእውቀት ነበልባል ይስተዋላል። የሁሉንም ጠቢባን መልእክት መረዳት በመቻሌ የተሰማኝን ደስታ በተረዳህልኝ» የሚል ነበር።

የእስረኛው ፍላጎት ወዲያውኑ ተሟልቶለት በባንከኛው ትእዛዝ ሁለት ጥይቶች ከእስር ቤቱ አካባቢ እንዲተኮሱ ተደረገ።

ከአስረኛው አመት በኋላ ደግሞ ጠበቃው ከንባብ ጠረጴዛው ፊት፣ ያለእንቅስቃሴ ተጉልቶ አዲስ ኪዳንን ሲያነብ የመዋሉ ሁኔታ ለባንከኛው አስገራሚ ነበር የሆነበት። በአራት ዓመታት ውስጥ ስድስት መቶ መፃሕፍት ላስ ያረገ ቀበኛ በውፍረቱም ቢሆን እዚህ ግባ የማይባል፣ መልእክቱም ቢሆን ግልጽ በሆነ መጽሀፍ ላይ አመት ሙሉ መንገታገቱ ከድንቅም ድንቅ ነበር።

ከዚያም በመቀጠል የአዲስ ኪዳን ንባቡ በሀይማኖት ታሪክና በሀይማኖት ፍልስፍና መፃህፍት ተተካ።

ባንከኛው ይህን የመሳሰሉትን የ15 ዓመታት ትዝታዎች አብሰለሰለ:: « ...ነገ ልክ ከሌሊቱ በ6:00 ሰዓት አጅሬ ነፃነቱን ይቀዳጃል:: በውሉ መሰረት እኔም ሁለት ሚልዮን ሩብሌን ቁጭ ማድረግ ሊኖርብኝ ነው:: ያን ካደረኩ ደግሞ አለቀልኝ ማለት ነው:: ላንዴም ለሁሌም ባዶ እጄን አጨብጭቤ መቅረቴ ነው» አለ በልቡ::

የዛሬ አስራ አምስት አመት ሩብል ጠጠሩ የነበረው ባንከኛ ቁማርና በስተርጅናም ያለቀቀው ሴሰኝነት ተደማምረው ስራውን አሽመድምደው መና አስቀርተውታል::

«ያ የተረገመ ውርርድ »በማለት አጉተመተመ:: ተስፋ በመቁረጥ ደግሞ «ምነው በሞተና በተገላገልኩት! ደግሞም እኮ ገና አርባ አመቱ ነው:: የመጨረሻ ጥሪቴን አሟጦ ይወስዳል፣ ህይወትን ያጣጥምበታል፣ ቁማር ይጫወትበታል:: እኔ ሆዬ ግን በዚያን ጊዜ እንደቀናተኛ ለማኝ ማፍጠጥ ነው:: 'ለደስተኛ ህይወቴ ባለውለታ ነህ፣ እስቲ ትንሽ ልርዳህ' የሚለውን የእርሱን ዲስኩር በየቀኑ መስማት ሊኖርብኝ ነው::

በፍፁም የማልታገሰው ነው:: 'ከዚህ ውርደት ማምለጫው መንገድ አንድ ነው:: እስረኛውን ገድሎ መገላገል' በማለት ከውሳኔ ደረሰ::

ሰዓቱ ልክ ከሌሊቱ 9 ሰዓት ሆኗል:: ከባንከኛው በቀር ሁሉም ተኝተዋል:: ከዚያም ለአስራአምስት ዓመት ያልተከፈተውን የእስር ቤት ቁልፍ ከካዝናው አውጥቶ ድምፅ ሳያሰማ ከቤቱ ወጣ::


በዝናቡ ውስጥ ተጉዞ ወደ እስር ቤቱ ሲጠጋ ጠባቂውን ዘበኛ ሁለቴ ተጣራ:: ሆኖም ምላሽ አላገኘም:: ከሚወርደው የዝናብ ወጨፎ ለመሸሸ ከአንዱ ጥግ ተኝቷል ማለት ነው ሲል አሰበ::

«ብርታቱ ኖሮኝ እስረኛውን ብገድል የመጀመሪያ ተጠርጣሪ የሚሆነው እርሱ ይሆናል» ሲል ራሱን አደፋፈረ::

ወደ እስር ቤቷ መተላለፊያ ገባ:: በሩ የታሸገበት ወረቀት አልተላጠም፣ በመስኮቱ በኩል አሾልኮ ማየት ጀመረ:: በክፍሉ ውስጥ ደብዛዛ የሻማ ብርሃን ይታያል:: እስረኛው ጀርባውን ለመስኮቱ ሰጥቶ ተቀምጧል:: ወንበር፣ ጠረጴዛውና ምንጣፉ ሳይቀር መጽሃፍ በመጽሃፍ ሆኗል::

አምስት ደቂቃ አለፈ፣ እስረኛው አንዴም ዞር አላለ:: የአስራ አምስት አመቱ እስራት አለእንቅስቃሴ መቀመጥን አስለምዶታል::

ሽማግሌው ባንከኛ የእስር ቤቱን መስኮት በጣቱ



ቢሆንኳኳም ከወደ እስረኛው ግን የአፀፋ መልስ አልተሰማም። ይኼኔ ባንከኛው በሩ የታሸገበትን ባለማህተም ወረቀት ቀዶ በሩን በቁልፍ ከፈተ። ይሁን እንጂ ባንከኛው እንደጠበቀው እስረኛው እራታውን አላተለጠም። ለ3 ደቂቃ ያህል ትንፋሹን ውጦ ቢጠብቅም ሁሉም ነገር እንደበፊቱ በፀጥታ የተሞላ ነበር። ያንጊዜም ለመግባት ወሰነ።

እንደገባ ከጠረጴዛው ፊት ለፊት የተመለከተው ሰውዬ ከሰው የተለየ ሆነበት። ሥጋው አልቆ አጥንቱ ብቻ ነው የቀረው፤ ፊቱ ከመገርጣቱ ብዛት ወደ ቢጫ የተቀየሩት ጉንጮቹ ተሰርጉደዋል። ባጠቃላይ ለማየት የማይዘገንን ሆኗል። የፀጉሩን መሸበት የፊቱን መጎሳቆል ያየ ተመልካች ሰውዬው ገና 40 ዓመቱ ነው ቢባል ለማመን ያስቸግረዋል።

እስረኛው ካቀረቀረበት ጠረጴዛ ላይ ከፊት ለፊቱ የሆነ ነገር የተጻፈበት ወረቀት ተቀምጧል።

«ምስኪኑ ዲያብሎስ ተኝቷል፤ ይኼኔ ሚሊዮን ሩብሉን እያለመ ይሆናል» ሲል አሰበ። በመቀጠልም «ይህን በቁሙ የሞተ፤ አልጋው ላይ ወርውሬ በትራስ ባፍነው ጥንቃቄ የተመላበት ምርመራ እንኳን ሊደርስበት አይችልም። ለማንኛውም ከእርምጃዬ በፊት የጻፈውን መልእክት ላንብብ» ብሎ ወረቀቱን አነሳ።

«... ነገ እኩለ ሌሊት ላይ ነፃነቴን እቀዳጃለሁ:: ከሰው የመደባለቅ መብቴም ይከበርልኛል:: ይሁን እንጂ ይህን ክፍል ከመልቀቁ፣ ፀሀይንም ከማየቴ በፊት ላንተ ጥቂት መልእክት ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ... በራሴ የጠራ አእምሮ፣ ሁሉን በሚያውቅ እግዚአብሔር ፊት ነፃነት፣ ህይወትና ጤንነት ባጠቃላይ እስከዛሬ ባነበብኳቸው መፅሃፎች ውስጥ የተጠቀሱት የምድር በረከቶች ምኔም እንዳልሆኑ ልገልጽልህ እወዳለሁ::

«ለአስራ አምስት አመታት ምድራዊ ህይወትን አጠናኋት:: በርግጥ ለዚህን ያህል ጊዜ ውጪውን ዓለምም ሆነ ሰዎችን ባላይም፣ በላክልኝ መፅሀፎች ውስጥ ከሚንፀባረቁት ገፀ ባሕርያት ጋር፣ በምናቤ አብሬአቸው ወይን ጠጅ ኰምኩሜአለሁ፣ መዝሙር ዘምሬአለሁ፣ አደን አድኜአለሁ፣ ቆነጃጅት አፍቅሬአለሁ፣ በረጃጅም - ተራሮች ላይ ሆኜ - የፀሀይን አወጣጥና አገባብ አይቻለሁ፤ በውቅያኖሶችና በተራሮች አድማስ ፀሀይ ስትወጣና ስትገባ የምትፈጥረውን ወርቃማ ውበት አድንቄአለሁ፤ መብረቅ ደመናዎችን ሲያተራምስ ታዝቤአለሁ:: ባጠቃላይ አለምና በውስጧ የሚካሄዱትን ትርምሶች አንድ ሳይቀር በመፅሀፎችህ ውስጥ ተካፍዬባቸዋለሁ፤ ሌላው ቀርቶ ቆንጆዬ ሰይጣን ክንፍ ላይ ተንጠላጥያለሁ::

«መፅሀፍቶችህ የመንፈስ ተሀድሶ ሰጥተውኛል - ለዘመናት በሰው ልጆች የተካበተ እውቀት በጭንቅላቴ ታጭቋል:: እርግጠኛ ነኝ አሁን በእውቀት ካንተ የተሻልኩ ነኝ::


«... አንተ ግን እብድ ነህ! ስለዚህ የተሳሳተ መንገድ መረጥክ:: በእውነት - ቦታ ሀሰትን፣ በውበት ፋንታ አስቀያሚነትን ለማስቀደም ወሰንክ:: በሆነ አጋጣሚ ብርቱካንና ትርንጐ እንሸላሊትና እንቁራሪት ቢያፈሩ፣ ጽጌሬዳዎች በመዓዛቸው በማወድ ፋንታ እንዳላበው ፈረስ ቢከረፉ፡ የምትደነቀውን ያህል እኔም ባንተ ተደንቄአለሁ:: መንግስተ ሰማያትን በምድራዊ ዓለም በመለወጥህ!

«ይህንንም በግልፅ ትረዳው ዘንድ፣ ከእለታት አንድ ቀን እንደገነት ፀጋ እቆጥረው የነበረውን ሁለት ሚሊዮን ሩብል ትቼልሀለሁ:: በሁለት ሚሊዮን ሩብል ላይ ያለኝን መብት በፈቃዴ አንስቻለሁ:: ለዚህም ስል ከውርርዱ ሰዓት አምስት ደቂቃ ቀድሜ በመውጣት ውለታውን በገዛ እጄ አፈርሳለሁ::»

ባንከኛው ደብዳቤውን አንብቦ እንደጨረሰ ወረቀቷን አስቀመጠና የእስረኛውን ራስ ስሞ አለቀሰ:: ከዚያም ከታዛዋ ወጥቶ ወደ ክፍሉ በመሄድ ከአልጋው

ላይ ተጋደመ:: ይሁን እንጂ በኪሳራው ወቅት እንኳን ያልተሰማው ስሜት ስላደረበት፣ ከሰውነቱ መራድና ሊቆጣጠረው ካልቻለው እንባ የተነሳ ለረጅም ጊዜ ማሽለብ ተሳነው::

በነጋታው ዘበኛው ሲሮጥ መጥቶ ያ ጉደኛ እስረኛ የታሰረባትን ክፍል መስኮት ሰብሮ በመውጣት መሰወሩን ነገረው:: ባንከኛውም ከሰራተኞቹ ጋር በመሆን ወደዚያች ክፍል ወዲያውኑ በመሄድ የእስረኛውን ማምለጥ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን አሰባሰበ:: በተጨማሪም ማናቸውንም ሀሜታ ልታስወግድለት የምትችለውን ያቺን ወረቀት ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ በካዝናው ውስጥ ቆለፈባት::



# ትብብር



# ማን ትሆን?

## አንቶን ቼኾብ
## (ትርጉም) መኩሪያ መካሻ

«እወድሃለሁ፣ አንተ ህይወቴ፣ ደስታዬና ሁሉም ነገሬ ነህ! ለአይን እውጣነቴ ይቅርታ ይደረግልኝና እንዲህ በፍቅርህ እየተሰቃየሁ ዝም ማለትን አልችልም። ዛሬ ማምሻውን ሁለት ሰዓት ላይ በተለመደው ሥፍራ እንገናኝ፣ ስሜን መጻፉ ትርፍ ነገር ስለሆነ ትቼዋለሁ። ለማንኛውም ስለራሴ ልንገርህ- ወጣትና ቆንጆ ነኝ ብዬ አስባለሁ። ሌላስ

ምን ልጨምር?»

ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ደብዳቤ ፓቬል ኢቫኖቪች ቭሆድሴቭ ካነበበ በኋላ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ እየታወሰው ትከሻውን ነቀነቀ፤ ሳይታወቀው ግንባሩንም መታ አደረገ::

«ምን ዓይነት ጽሑፍ ነው?» ብሎ አሰበ:: እኔ ባለትዳር ነኝ:: በድንነት ደግሞ እንዲህ አይነቱ የዱብ ዕዳ ደብዳቤ! ማን ጻፈው ይሆን?»

ፓቬል ኢቫኖቪች ደብዳቤውን ደጋግሞ አነበበና ምራቁን ተፋ::

«እወድሃለሁ»... የሚለውን ቃል በውስጡ እየደጋገመ «ምን አይነቷን ወጣት አገኘሁ?! ስለዚህ ካንቺ ጋር ለመገናኘት እሮጣለሁ ማለት ነው... ወይኔ እናቴን- ከእንዲህ አይነቷ Fleur d'amour (የፍቅር አበባ) ከተለየሁ ብዙ ጊዜዬ ነው:: ምናልባትም በስህተት የደረሰኝ እድል ይሆናል:: አቤት ሴት! አምላኬ ይቅር በለኝ! እንዲህ አይነቱን ደብዳቤ ለማያውቁት ሰው መጻፍ! ያውም ሳገባ ወንድ ምን ይባላል? መቼም ግጥጥ ያለ ሞራለ ቢስነት ነው!»

በዚህ በስምንት ዓመት የትዳር ዘመኑ ፓቬል ኢቫኖቪች ከእንዲህ አይነቱ ስሜት የራቀና ከደስታ መግለጫዎች በስተቀር ይህን መሰል ደብዳቤ ደርሶት አያውቅም:: በራሱም ላይ ለመናደድ አልፈለገም፤ ግን የደረሰው ደብዳቤ ትኩረቱን ከመሳቡም በላይ በጣም አሳስቦታል::

ደብዳቤውን ካገኘ ከአንድ ሰዓት በኋላ ሶፋው ላይ ጋደም ብሎ ያስብ ገባ:-

«እኔ ጕረምሣ አይደለሁም፤ ወደዚህ የእብድ ቀጠሮ ቦታ የምሄድ? ቢሆንም ማን እንደፃፈ ማወቁ ግን አስፈላጊ ነው:: እም... መቼም የእጅ ጽሑፉ የሴት እንደሚመስል እርግጠኛ ነኝ:: ደብዳቤው ግልጽነት ያለውና ከልብ የመነጨ ስለሆነ ቀልድ ነው ለማለት ያጠራጥረኛል ... ምናልባትም አንዲት ወፈፌ ወይም ባልቴት የፃፈችው ቢሆንስ? ባልቴቶች እንኳ ሃሣበ ልሎችና የማይታመን ነገርም የሚጽፉ ናቸው:: ብቻ እንዲያው ግን ማን ልትሆን ትችላለች?»

ይህን ዓይነት ጥያቄ መመለሱ ከባድ ነው - ለፓቬል ኢቫኖቪች:: በአካባቢው ከሚስቱ በስተቀር በኡቫኖቪች ዘንድ የምትታወቅ ሴት ስለሌለች::

ግራ ገባው... «እወድሃለሁ» ... ምን ማለት ነው? ከመቼው ልትወደኝ ቻለች? የምትገርም ሴት ነች! የወደደችኝ ምንም መጨበጫ ሳይኖራት ነው፣ እኔ ምን ዓይነት ሰው እንደሆንኩ ሳታውቀኝ ... በሁለትና ሶስት እይታ ብቻ የምትወድ ከሆነ ወጣትና ፍቅር አዋቂ መሆን አለባት ማለት ነው ... ግን ... ማን ትሆን?

በድንገት ፓቬል ኢቫኖቪች አንድ ነገር ታወሰው:: ለካስ ትላንት በመዝናኛው ሥፍራ ሲዘዋወር አንዲት ደማቅ ሰማያዊ ቀሚስ ከለበሰች ባለወርቅማ ፀጉር፣ ወጣት ሴት ጋር በተደጋጋሚ ተያይተው ነበር:: ባለወርቅማ ፀጉራሟ ሴት ተመልክታው ኖሮ እሱ መዝናኛ ወንበሮቹ ላይ እንደተቀመጠ፣ ከእሱ ጐን ተቀምጣ ነበር ...

«እሷ ትሆን?» ብሎ አሰበ ኢቫኖቪች:: ሊሆን አይችልም! ይህች የማትገኝና የማትጨብጥ ፍጥረት እኔን መሰል ዘባተሎ ሽማግሌ ልታፈቅር? ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!

ፓቬል ኢቫኖቪች በምሣ ሰዓት ላይ ሚስቱን አትኩሮ

እየተመለከተ እንደሚከተለው ያስብ ጀመር:- «እሷ እንደሣፈችው ከሆነ ቆንጆና ጥሩ ሴት እንደሆነች ገልፃለች... ይህ ማለት አርጊት አይደለችም ማለት ነው... እኮ! እንደ እውነቱ ከሆነ እኔም ብሆን ለመወደድ የማልበቃ ሽማግሌና መጥፎ ሰው አይደለሁም:: ... ሚስቱም ትወደኛለች! እንደነዴ ደሞ ፍቅር ክፉ ነው፣ ፍየልንም ያስወድዳል አይደል? ...»

- «ስለምን እያሰብክ ነው?» አለችው ሚስቱ::

- «እንዲሁ ነው ትንሽ ራሴን አሞኛል» ብሎ መለሰ ፓቬል አፈር ብሎ::

ከምሣ በኋላ ወደ አልጋው ሄዶ ተጋመደና ከመተኛት ይልቅ በሃሣብ ይቆዝም ጀመር:: «ይኸኔ እሷ ወደ ቀጠሮው ቦታ እንደምሄድ ተስፋ ታደርግ ይሆን? እብድ ነች ማለት ነው! እ...ያ ካልተገኘሁ መቼም በንዴት ትንጨረጨራለች! ... እኔ ፈጽሞ አልሄድም! ... ይቅርባት!»

«እንዲሁ ሁኔታውን ለማወቅ ያህል ልሂድ ይሆን እንዴ?» አለ ፓቬል ከራሱ ጋር እየተሟገተ:: ምን ዓይነት ፍጥረት እንደሆነች ሄጄ ልመልከት... መመልከቱ ጥሩ ሳይሆን አይቀርም! መቼም የሚያስቅ ነው! የተፈጠረው ሁናቴ በእውነት ከተፈፀመ ለምን አያስቅ?»

ከመኝታው ተነስቶ መለባበሱን ቀጠለ::

- «ወዴት ነው የምትጣደፈው?» ብላ ጠየቀችው ሚስቱ፤ ዘመነኛ ክራቫቱንና ንፁህ ልብሱን ሲለብስ ተመልክታ::

- «ትንሽ ዞር ዞር ማለት እፈልጋለሁ ... ራሴን በጣም አመመኝ ... ኡፍፍ ...»

ፓቬል ኢቫኖቪች እየተጣደፈ ሰዓቱን አክብሮ ወደ ቀጠሮው ሥፍራ አመራ:: ፀሐይዋ እየደከመች ስትሄድ የዛፎቹን ጥላ ተከትሎ በአካባቢው የሚዝናኑ ሰዎች ቁመና እየታየው፣ ልቡ ከውስጥ ፈንቅሎ የሚወጣ ያህል መምታት ጀመረ::

«ከነዚህ ውስጥ የትኛዋ ትሆን? እያለ የሚያያቸውን ሰዎች አትኩሮ ተመለከተ- ባለወርቃማ ፀጉሯን ሴት ግን አላያትም... እም... እሷ የዓፌችው ከሆነ መቀመጫው ላይ ትቀመጣለች...»

የሚዝናኑት ሰዎች ወደ ሜዳው ላይ ወጡ... ከነዚህም ውስጥ ያቺ የሚያስባት ሴት ትታያለች... ፈራ-ተባ እያለ ቀስ ብሎ ወደ እሷ ዘንድ አመራ:: በመነቃነቅ ላይ ሳለ «እኔ እንደሆንኩ ወደ ቀጠሮው ቦታ አልሄድ ...እባክህ በድፍረት ወደፊት ቀጥል! ምንስ ይሆናል ተገናኝተን ብንነጋገር?

...ምንም አይሆንም!» እያለ ራሱን በሃሣብ እያስጨነቀ ወደፊት ተንቃነቀ::

የፓቬል ኢቫኖቪች ልብ በጣም መምታቱን ቀጠለ... በድንገት ስለቀጠረችው ሴት የተለየ አስተያየትና ስሜት በአእምሮው መጣ... በሃሣቡ ባለወርቃማዋና ደማቅ ሰማያዊ ቀሚስ የለበሰች፣ ቀጥያለ አፍንጫ ያላት ሴት ታየችው... ፍቅሯን ለመግለጽ እየፈራች፣ ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠና ፈራ ተባ እያለች ወደ እሱ ዘንድ የምታመራ አድርጐ በሃሣቡ አንገዋለላት... ትኩስ ትንፋሿ እየገፈተረው ጥምጥም የምትልበት ሴት ታየችው::

«አይ የእኔ ነገር... እኔ እንደሆንኩ ባለትዳር ነኝ... ቢሆንስ ደሞ? ምንም የለበትም?» የሚለውንና እንደ ሃጢአት የቆጠረውን ስሜቱን ከአእምሮው እያስወገደ፣ በህይወቱ

ውስጥ ምን አይነት ፍጡር እንደሆነች ሳላውቅ መሞት የለብኝም፣ ደግሞስ በሕይወቱ አንዴ ይህን ብሞክር ምን አለበት? ማስቱስ... ከእሷስ ጋር እንዴት ልሆን ነው? እግዚአብሔር በሚያውቀው፣ ይኸው ስምንት ዓመት ሙሉ እሷን ሽፍጪያት አላውቅም... ስምንት ዓመት ሙሉ በቅንነት አብሬያት የኖርኩ ነኝ! ለእሷም ቢሆን ደስ ላይላት ይችላል... ስለዚህ ብለውጣትስ?»

እየተንቀጠቀጠና ትንፋሹ ቁጥር ቁጥር እያለ ወደ ቀጠሮው ሥፍራ አመራ:: ወፍ ዘራሹን የወይን ዛፍ ተታከ እየተመለከተ «ማንም የለም መሰል...» ብሎ አሰበ ለራሱ ወደ ቀጠሮው ቦታ እየሄደ:: ወዲያው ደግሞ የሰው ጥላ ታየው::

ጥላው ለካስ የወንድ ነበር... ወደ ጥላው በትኩረት ቢያይ፣ ያ አብሮት የሚኖረው ቀርሣው ሚቲያ ብቻ ነው::

«አንተ ነህ እንዴ?» አለው በተዘበራረቀ ቋንቋ፤ ባርኔጣውን አውልቆ እየተቀመጠ::

«አዎን እኔ ነኝ» አለው ተማሪ ሚቲያ::

አንድ ሁለት ደቂቃ ያህል በዝምታ አለፈ::

«ይቅርታ አድርጉልኝ ፓቬል ኢቫኖቪች» ብሎ ጀመረ ሚቲያ፣ ቀጠለና «ለመመረቂያ ጽሑፌ በጥልቀት መዘጋጀት ስለአለብኝ ብቸኝነትን መርጬያለሁና ቢሄዱልኝ ጥሩ ነው...»

«አንተው ራስህ ወዲያ ወደጨለማው ሥፍራ ሂድ!» ብሎ ፓቬል ኢቫኖቪች አምባረቀበት «እንዲያውም ንፁህ አየር ላይ ተቀምጦ ማሰብ ይቀላል... እኔ ግን እዚህ

ወንበር ላይ ትንሽ ላርፍ እፈልጋለሁ... ሙቀትም የለውም...»

«እርስዎም ይረፉ! እኔም መመረቂያዬን ላስብበት...» ብሎ አጉተመተመ ሚቲያ- ከስፍራው ላለመነቃነቅ ወስኖ::

እንደገና ዝምታው ሰፈነ... ጆሮውን አቁሞ የሚከታተለው ፓቬል ኢቫኖቪች ኮቴ ሰማ:: በድንገት ታዲያ ለቅሶ በተቀላቀለበት ድምፅ፣

«እባክህ ሚቲያ፤ አንተ ልጅ ስለሆንክ እኔን ማክበር አለብህ... አሞኛል... ስለዚህ ማረፍ እፈልጋለሁ፤ ሂድልኝ!»

«ይህማ ስግብግብነት ነው... እርስዎ ብቻ እዚህ የሚቆዩበት ምክንያቱ ምንድነው? ከመርህ አንፃር ፈጽሞ አልሄድም...»

«እባክህ ልመናዬን ስማኝ! እኔ የፈለከትን ያህል ስግብግብ፣ ግትር ወይም ወናፍ ልሁን፣እባክህ ልመናዬን ስማኝ... በሕይወቴ ዛሬ ገና ነው ያስቸገርኩህ ደግሞም አክብረኝ!...»

ሚቲያ በእንቢታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ... በዚህ ጊዜ ፓቬል ኢቫኖቪች በውስጡ እየበገነ 'ምን አይነቱ ከብት ነው... እሱ እያለማ ቀጠሮው ሊካሄድ አይችልም! ፈጽሞ እሱ እያለ አይሆንም!'

«ስማኝ ሚቲያ... ለመጨረሻ ጊዜ ልለምንህ፣ አንተ አዋቂ፣ሰብአዊነት የሚሰማህ የተማርክ ልጅ መሆንህን እስቲ አስመስክር!»

«ምን ማለትዎ እንደሆነ ሊገባኝ አይችልም» ብሎ ትከሻውን አማታ ተማሪው:: ቀጥሎም «አልሄድም ደሞ! አዎን አልሄድም:: ከመርህ አኳያ ከዚች ቦታ አልነቃነቅም::»

በዚህ ጭቅጭቅ መሃል ወደ መቀመጫቸው አንዲት ሴት ብቅ አለች::

ሚቲያንና ፓቬል ኢቫኖቪችን ተመልክታ ከቁብ ሳትቆጥራቸው ውልብ አለች::

«በቃ ሄደች! ማለት ነው» ብሎ አሰበ ኢቫኖቪች በመጥፎ አይነት ሚቲያን እየተመለከተ:: «ይህን ባለጌ ልጅ ተመልክታ ሄደች ማለት ነው:: ዋጋ አጣ በቃ»

ትንሽ ከጠበቀ በኋላ ባርኔጣውን እያደረገ ከተቀመጠበት ተነስቶ እንዲህ አለ፣

«አንተ ከብት፣ባለጌና ተንኮለኛ ነህ! አዎ! ከብት ነህ! ብልግና ነው...ደደብነት! ከአሁን በኋላ ግንኙነታችን ተቋርጧል::»

«በጣም ደስ ይለኛል!» አለ ሚቲያም እየተነሣ፣ ባርኔጣውን እያደረገ «እስከ እለተ ሞቴ ድረስ የማልረሣውን በደል ነው የፈፀሙብኝ!»

ፓቬል ኢቫኖቪች ከመቀመጫው ሥፍራ በንዴት ተነስቶ በፍጥነት ወደ ቤቱ ውስጥ ገባ... ለእራት የተዘጋጀው የጠረጴዛ አቀማመጥ ደስ አላሰኘውም::

«በህይወቴ ውስጥ አንድ ጊዜ ቢገጥመኝም ሁኔታው ሳይሣካ ቀረ፣ አጨናገፈኝ፤ ከአሁን በኋላ እሷም ብትሆን ሞራሏ ተነክቷል...ተገድላለች ማለት ነው!»

እራት እንደቀረበም ፓቬል ኢቫኖቪችና ሚቲያ የቀረበላቸው ምግብ እየተመለከቱ አኰረፉ... ሁለቱም ከአንጀታቸው ተጣልተዋል::

«ምነው ትስቂያለሽ? ዕብድ ብቻ ነው ካለ ምክንያት

የሚስቅ!» አላት ኢቫኖቪች ሚስቱን::

የተከፋውን የባሏን ፊት እየተመለከተች፣ «ዛሬ ጥዋት የምን ደብዳቤ ነው የደረሰህ?» ስትል ጠየቀችው::


- «እኔ!?... እኔ ምንም አይነት ...» ብሎ እንደማያውቅ ሆነባት::

- «እንዴ! ተናገር እንጂ! እውን ደርሶሃል አይደል? አረፈው በቃ፣ እኔ ነኝ ደብዳቤውን የላኩልህ፤ እውነቴን ነው፣ እኔ ነኝ! ሃ.ሃ.ሃ.ሃ.!»

ፓቬል ኢቫኖቪች አጉንብሶ ሳህኑ ላይ አቀረቀረና «ደስ የማይል ቀልድ ነው» እያለ አጉተመተመ::

- «ምን ላድርግ ታዲያ? እስቲ አንተው ፍረድ... ወለሉን ማጠብ ነበረብኝ:: ታዲያ እንዴት አድርጌ ከቤት ላስወጣችሁ? በዚህ ዘዴ ብቻ ነው መጠቀም የምችለው... ታዲያ አትቀየመኝ፣ ጅሎ... በቀጠሮህ ሥፍራ ብቸኛ እንዳትሆን ብዬ ሚቲያንም ያንኑ መሰል ደብዳቤ ልኬለታለሁ! ሚቲያ ለመሆኑ እቀጠሮው ቦታ ነበርክ?»

- ሚቲያም በሃፍረት አቀርቅሮ ከዚያ ሰዓት በኋላ ፓቬል ኢቫኖቪችን በመጥፎ ስሜት ከማየት ተቆጠበ::



# ሙታንን ሙታን ይቀብሯቸዋል



# ሼክስፒራዊ መወድሶች

ተስፋዬ ገሰሰ

## ለሴተ-ላጤ

ያ'ርባ ክረምት እርሻ፣ አርሶት ግንባርሽን፣
የጠፋ ማሳ አድርጎት፣ ለሙን ውበትሽን፣
የወጣትነትሽ፣ የ'ሽትነት ለዛ፣
ተሟጥጦ ያልቅና፣ ሲደርቅ እንደ ጤዛ፣
የት ገባ ብትባይ? ያ ሁሉ ደም ግባት?

ያ ሁሉ ቂን-ቂን ያ ሁሉ ማንጓት?
«ተመልከተው ዓይኔን
ሽንጥና ዳሌዩን- አሁንም ያንጓል!»
ማለቱ ቅር ይላል::
ነገር ግን ብትዩ «ደምግባቴን ወርሳ
ያቺውና ልጁ የኔን ውበት ለብሳ!»
ምንኛ ባስከራሽ ስምሽን ባስጠራ
ስላስተላለፍሺው ውበትሽን ባደራ
ደምን ሲቀዘቅዝ ደምን የሚያሞቀው
ዳግመኛ መወለድ ልጅ የወለደ ሰው!

## ለወንደ-ላጤ

ፊትህን እይና፣ በመስታወት ፊት
እንዲህ በል ንገረው «አንተ የኔው ፊት
አሁን ነው መተግበር ሌላ ፊት መስራት!
አሁን ካልተካኸው ሳትጨራመት
ተጠምኘተህ ማጣት የናት ምርቃት!
መች ጠፋና ነው የድንግል መሬት?
ዘር እማይቀበል ፍሬ ለማፍራት?
ወይስ? ራስክን ቆጥበህ እስከ መቃብር
ፍሬ ማፍራት ጠላህ ሳትዘራ ዘር?

አንተ ነህ የ'ናትህ የፊት መስታወት
አንጸባራቂዋ የስጋ ውበት!
እድሜህም እንዲሁ ያንተ መስታወት
ዐይንህም በዐይንህ የምታይበት፡፡
ልረሳ ካልክ ግን ልሁን አልባሌ
ስትኖርም ባተሌ ስትሞት ባተሌ!

## ሙግት

ዐይኔና ልቤ ተጋጩ
ባንቺ ላይ ተፋጩ፡፡
ዐይኔ ፍቅሬን ባየች
ምስሏን ቀድማ በቀረጸች
ማሕደሯ እኔ ነኝ አለች፡፡
ልቤ ተቃወመች
ዐይን ብቻ ባየች
ልብ ብላ ካላስተዋለች
ምኑን ማሕደሯ ሆነች?
ተያይዘው ራስ ችሎት ወጡ፣
እውነቱን ሊያፍረጠርጡ፡፡
«በለሃ ልበልሃ!» አለች ዐይን፣
«ያልታየሽን ነገር እንደምን ልታቂው»

«ያላወቅሽውን አገር እንዴት ልትናፍቂው?»
«በለሃ ልበልሃ!» መለሰች ልብ፣
«ሙዚቃን አይተሽ ነው ያወቅሺው?»
ፍትህና ዲሞክራሲን የናፈቅሺው፣
የትአባሽ አይተሺው?»
ራስ ፍርድ ሰጠ፣
አንዱን ካንዱ ሳያበላልጠ፣
ፍርድ፣
«ዐይኔም ውጪያዊውን ያዝ
ልቤም ውስጣዊውን ግዝ።
ዐይኔ ሆይ አያስትሽ ቁልጭልጩ።
ልቤ ሆይ ረጋ በይ፣
እንዲያው አትደልቂ ባደባባይ!
እርግት ያለ ወተት እንዲወጣው ቅቤ
እርግት በሉልኝ ዐይኔም ሆንሽ ልቤ

## ኳተና

ውሎዬን ስኳትን ሲመሽ እደክምና
መተኛት እሻለሁ እፎይ ልል ልዝናና።
ግና ጋደም እንዳልሁ ናላዬን ነሳና
እገሰግሳለሁ በሃሳብ ጉዳና።

ወዳንቺ እንዛለሁ ዐይኔ ተንቀልጦ
ጨለማውን ዘልቆ በስውሩ ፈጥጦ!
ምስልሽ ተደቅኖ ታይሻለች ነፍሴ
ዓይኔ ባያይሽም በመንፈስ ፋኖሴ::
ታዲያ እንደንቆጳዚዮን ታበሪልኛለሽ::
የሻሸረው ቅስሜን ታድሺልኛለሽ::
አምን ሌሊቱ እንደመዐልት ብርሃን ይለብስና
ልረፍ ያለው ልቤ ኳተና እንደገና!
እነሆ በቀን አካላቴ በሌሊት አንጒሌ
ባንቺ የተነሳ ሲኳትኑ ሁሉ!!

## እንቆቅልሽ:-
## ምን አውቅልሽ?

እንዳበደ ውሻ የሚያቅነዘንዘው
እንደተለከፈ የሚቅበዘበዘው
የምኞት ትፍስህት ኀብስተ- ሰማዩ
የ'ልም እንጀራ ቅገ'ት ሐሳዊ- ሲሳዩ...
....................ማነው?....................
ሳያረጉት በፊት አስምሎ አስገዝቶ
ባወገዙት ሰፈር ወስዶና ጉልቶ::
የተናገሩበት ያፍ ምራቅ ሳይደርቅ

አስገብቶ ከማጥ የሚያጨማልቅ...

......................ማነው?.....................

አቤት መጣፈጡ! ብለው አጣጥመው

አክ- እንትፍ የሚሉት ሲጨርሱ አንቅረው

የጣፈጠ መስሎ እንደማር ወተት

ጉሮሮ እሚሰካ የፀፀት አጥንት...

......................ማነው?.....................

ግፊቱ ደመነፍስ የሚያብር መንፈስ

በውርደት ጢሻ ውስጥ ክትቶ ሚያልኮሰኩስ

ኤድስ ማይበግረው ክርክር ቢሉት በጥስ

ማር የተቀባ ሬት ነው እረ እንዲያው አያድርስ

......................እህስ?.........................

መልስ፡- ሕዝብ- ዓለም ያውቀዋል ቅንዝረ ፍትወትን

የነፍስን ገሀነም የስጋ ገነትን፡፡

ሁሉን የሚለውስ ስም-አጥፊው ጥቀርሻ

ካልጋ ሲሉት ካመድ ቅንዝር አባግርሻ!



# ሆደባሻው

## አንቶን ቼኾቭ
## (ትርጉም) መኩሪያ መካሻ

የአንድ ብረታ ብረት ፋብሪካ የበላይ አለቃ ነው- ኢቫን ካርሎቪች:: የፋብሪካው ባለቤት አንድ ጉዳይ እንዲያስፈጽም ወደ ትቪር ከተማ ልኮት ነበር:: በተላከበትም ጉዳይ አራት ወራት ያህል በመቆየቱ ወጣት ሚስቱ ናፈቀችው:: ናፍቆቱ ሲፀናበት፣ የምግብ ፍላጎቱ

ሳይቀር እየቀነሰ መጣ:: እንደማልቀስም ሲዳዳው ከረመ:: ናፍቆቱን ስላልቻለው ወደ ሞስኮ ለመመለስ ወሰነ:: በመመለሻው እለት አይኑን ጨፍኖ በምን መልኩ ወደቤቱ እንደሚገባ፣ የቤት ሰራተኛው ማሪያ እንዴት በሩን እንደምትከፍትለት፣ ሚስቱ ናታሻ እንዴት ትከሻው ላይ ውድቅ ብላ በናፍቆት እንደምትቀበለው እያሰበ እብስ አለ:: መለስ አለና «እኢስ አትጠብቀኝም» አለ ለራሱ:: «ደግሞ አለመጠበቋም በጣም ጥሩ ነው:: ያልተጠበቀ ደስታ ሊገኝበት ይችላልና::»

በማታው ባቡር ሞስኮ ደረሰ:: የባቡር ጣቢያው ሰራተኛ ሻንጣዎቹን እስከሚያወርድለት እዚያው ቡና ቤት ውስጥ ሁለት ጠርሙስ ቢራ ተጉነጨ ... ቢራዎቹን ከወሳሰደ በኋላ ፍፁም ደግነት ተሰማው:: እቃዎቹን ከባቡር ጣቢያው በሰራተኛ አሸክሞ ሲሄድም ይለፈልፍ ነበር::

«አንተ ኩሊ! ጥሩ ኩሊ ነህ ... ሩሲያኖችን እወዳቸዋለሁ! አንተ ሩሲያ፣ ሚስቴ ሩስያዊ፣ እኔም ራሴ ሩሲያዊ ... አባቴ ጀርመናዊ ቢሆንም እኔ ግን ሩሲያዊ ነኝ ... እንዲያውም ከጀርመን ጋር መፋለም እፈልጋለሁ ...»

... ልክ እንዳሰበው በሩን የከፈተችለት ሰራተኛው ማሪያ ነበረች::

ሻንጣውን ለማሪያ እየሰጠ «አንቺ ሩሲያዊት ፣ እኔ ሩሲያዊ ... ሁላችንም የሩሲያ ዜጎች፣ የሩሲያ ቋንቋ የምንናገር ...» እያለ ከፈነደቀ በሁዋላ «ለመሆኑ የት አለች

ናታሻ?!» ሲል ጠየቀ፡፡

«ተኝታለች»

«ደህና፣ አትቀስቅሺያት፡፡ ኡስስስ ... እኔ ራሴ እቀሰቅሳታለሁ ... ሳታስበው አስደነግጣትና አስደስታታለሁ ... ኡስስስ! ... »

ማሪያ ሻንጣዎቹን ይዛ ወደ ኩሽናው ገባች፡፡

ኢቫን ካርሎቪች ፊቱ በደስታ ፈክቶና እጁን እያሻሸ፣ እንዲሁም በአይኑ ወዲያና ወዲህ እያማተረ ወደ መኝታ ቤቱ በር ዘለቀ፡፡ በዝግታ በሩን ከፈተው፡፡ መኝታ ክፍሉ ጭለማና ፀጥ ያለ ነው፡፡

'አሁን አስደነግጣታለሁ' ብሎ አሰበ ኢቫን ካርሎቪች ክብሪቱን ለኩሶ ...

የክብሪት እንጨት እያነደደ አንድ ነገር ታየው፡፡ ወደ ግድግዳው ጥግ ባለው አልጋ ላይ አንዲት ሴት ጭንቅላቷን ተሸፋፍና ተኝታለች፡፡ ከሰውነት ክፍሏ የሚታይ ነገር ቢኖር ተረከዟ ብቻ ነው፡፡ በሌላኛው አልጋ ላይ ደግሞ አንድ ግብዳ፣ ጨብራራና ሪዛም ወንድ ተጋድሟል፡፡

ኢቫን ካርሎቪች አይኑን ማመን አቅቶት ሌላ ክብሪት ጫረ ... አከታተለም፡፡ አምስት እንጨት ክብሪቶችን ለኳኮሰ፡፡ የማይታመነው ስእል አእምሮውን ወጠረው፡፡

አስፈሪና አሳፋሪ ነበር:: እግሩ ተብረከረከ፣ጀርባውን እንዳች ቅዝቃዜ ቀሰፈው:: ያ የጠጣው ቢራ ባንዴ ጭንቅላቱ ላይ ወጣ፣ ስሜቱ ተገለባበጠ:: መጀመሪያ ላይ የመጣለት ስሜት ወንድየውን - ወንበር እንስቶ ጭንቅላቱን መፈጥፍጥ ሲሆን፣ ያችን ከሀዲ ሚስቱን ደግሞ ተረከዟን ይዞ እርቃኗን በማንጠልጠል በመስኮት በኩል መወርወርና እሷም እየጮኸች ድልድዩ ስር ስትወሸቅ ማየት ነው::

«አ! አይሆንም! ያንሳቸዋል!» ብሎ ጥቂት ካሰበ በኋላ «መጀመሪያ ሁለቱንም አያይዤ አስራቸዋለሁ:: ከዚያም ፖሊስና ዘመዶቻቸውን ጠርቼ እገድላቸዋለሁ» የሚል ውሳኔ ላይ ደረሰ::

ካፖርቱን ደረበ መንገድ ላይ ወጣ:: ምርር ብሎ ማልቀስ ጀመረ:: እየተንሰቀሰቀም ስለ ሰዎች ክፋትት አሰበ ... ይህች ተረከ፯ ተገልጦ አልጋው ላይ የተጋደመችው ሴት (ሚስቱ ላለማለት) ከዚህ በፊት ምስኪን ልብስ ሰፊ ነበረች:: ዛሬ ግን ደስተኛና በአመት 750 ሩብል የሚከፈለው፣ የተማረ - አለቃ ሚስት ሆናለች:: ቀድሞ ከርታታና እንደ ቤት ሰራተኛ ቡትቶ ለባሽ ነበረች:: «እድሜ ለእኔ ትበል! ዛሬማ ዜንጦና በፋብሪካችን ውስጥ ሳይቀር 'አንቱ' የተባለች ሰው ሁናለች ...» አለ ካርሎቪች::

ኢቫን ካርሌቪች፣ «ሴቶች ምን አይነት መሰሪና አታላይ ናቸው!» እያለ በመንገድ ላይ ሲሄድ፣ እውነትም 'ሴትና እባብ' አለና አሰበ:: ድምፁን ዝቅ አድርጐ «ለምን ሩሲያዊት አገባሁ?

ሩሲያውያን ጥሩ ሰዎች አይደሉም! ከሩሲያኖች ጋር መፋለም አለብኝ፣ ይህቺ ሰይጣናም!» እያለ ለራሱ አጉተመተመ::

አረፍ ብሎ ትንሽ አሰበና «የሚደንቅ ነው:: በጨብራራው ሰውዬ ለውጣኛለች ማለት ነው! ይኸኔ እኮ ኪሱ ውስጥ እንኳ ዱንቡሎ የሌለው ነው! ወይኔ ካርሌቪች! እኔኮ የተረገምኩ ሰው ነኝ::» አለ::

ካርሎቪች አይኑን ጠራርጐ ወደ አንድ አነስተኛ ምግብ ቤት ገባ::

«እስቲ ወረቀትና ብእር ስጠኝ!» ብሎ አስተናጋጁን ጠየቀ::

በንዴት ፈረስ ላይ ሁኖ - «ለመፃፍ ፈልጋለሁ!» ብሎ ደብደቤውን ይሸቀሽቀው ገባ::

እጁ እየተንቀጠቀጠ ስርፑሆቭ ከተማ ውስጥ ለሚኖሩት ለሚስቱ ወላጆች በፃፈው ደብዳቤ - አንድ የተማረ የፋብሪካ አለቃ ከዚች አይነቷ ጋጠ - ወጥ ሴት ጋር መኖር እንደማይቻለው፣ ቤተሰቦቿም ሆኑ ልጃቸው አሳሞች ስለሆኑ ካርሎቪች «ወደ ፈለገው መሄድ ይችላል ...» ካለ በኋላ በማጠቃለያው ወላጆቿ ከጨብራራ ፀጉራሙ ሰውዬ ጋር ደብለው እንዲወስዷትና ሊገድላቸው ያልፈለገውም እጁን ላለማበላሸት ሲል መሆኑን ገልጾ ደብዳቤውን ደመደመ::

ከምግብ ቤቱ ወጣና ፖስታውን ከተተ:: እስከ ጥዋቱ

አራት ሰአትም በየከተማው ሲዘዋወር በሀዘን ተወጥሮ ነበር:: ምስኪኑ ካርሎቪች በሀሳብ ብቻ ክስትና ጥውልግ አለ:: «ሕይወት - መራር፣ የእጣ ጥንቅር ነች:: ለእኔ የጠመመችና የረከሰች ሁናለች» እያለ ሚስቱንም ሆነ ያንን 'ፀጉራም' ሰው ላለመበቀል ወሰነ:: ማድረግ የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፣ በግድየለሽነት በመተው ሚስቱን መቅጣት እንደሆነ ቁርጥ ሃሳብ አደረገ::

«ሄጄ ሁሉን ነገር አስረዳታለሁ» አለና ወደ ቤቱ አመራ:: በመንገድ ላይ «ሕይወቱን አጠፋለሁ ... ከዚያ ጨብራራ ፀጉራም ሰው ጋር ተደስታ ትኑርበት፣ ከእንግዲህ አልረብሻትም ...» እያለ ራሱ እንዴት እንደሚሞትና ሚስቱም ሀሊናዋ ተጨንቆ በሀዘን ስትቆራመድ ታየው::

«ንብረቱንም ቢሆን በሙሉ አስቀርላታለሁ፤ አዎን! አስቀርላታለሁ» አለ እቤቱ ደርሶ መጥሪያ - ደወል እያሰማ «እስቲ ያ ጨብራራ ከእኔ ሲሻል እናያለን፣ እስቲ እሱም በአመት 750 ሩብል እየሰራ ሲያስገባ እናያለን!» እያለ ሲያጉተመትም የቤት ሰራተኛው 'ማሪያ' በሩን ከፈተችለት:: ስታየውም በጣሙን ተደናገጠች::

ካፖርቱን እንኳ ሳያወልቅ - «እስቲ ናታሻን ጥሪያት! ላነጋግራት እፈልጋለሁ ...» አለ እንዳኮረፈ::

ከደቂቃ በኋላ ሚስቱ ናታሻ በባዶ እግሯ ኢቫን ካርሎቪች ፊት በመገረም ቀረበች:: ካርሌቪች እያለቀሰና ሁለት እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ እንዲህ ማለት ጀመረ

«ሁሉን ነገር አውቄያለሁ! እኔን ማታለል አይቻልም! በገዛ አይኔ ያንን ሪዛም ከብት መሳይ ተመልክቼያለሁ!» እያለ አንባረቀባት::

«አበድክ እንዴ! ምነው እንዲህ ትጮሃለህ? በሰላም ያረፉትን ሰዎች አትረብሽ!» አለችው፤ ናታሻ በተራዋ ጮክ ብላ፣

«ያን ዳለቻ ዱሪዬ ነው የምትይው!»

«አንተን እኮ ነው የምለው! አትጩህ! ሰክረ እንግዲህ - ይጮሃል! ሂድና ተኛ!»

«ከዚያ ከጩብራራ ጋር በአንድ አልጋ ላይ ልተኛ? አላደርገውም! ሂጂልኝ!»

«አብደሃል ማለት ነው?» ተናደደች ናታሻ:: «እኛ ቤት ያረፉ ሰዎች አሉ! መኝታ ቤታችን ውስጥ አናጢው ከሚስቱ ጋር ተኝቷል::»

በተደናገጠ ሁናቴ - «ኤ ... ኤ፣! የትኛው አናጢ?»

«ጩብራራው አናጢ - ከሚስቱ ጋር:: ለወር በአራት ሩብል ሂሳብ፣ ክፍሉን አከራይቻቸ ዋለሁ ... አትጩህባቸው ትቀሰቅሳቸዋለህ!»


ጀርመናዊው አይኑን አጥርቶ ሚስቱን በአትኩሮት ተመለከታት፣ ከዚያም አንገቱን ደፍቶ ቀስ ብሎ አፋዋጨ ...

«አሁን ገባኝ ... » አለ ለራሱ፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጀርመናዊው መንፈስ ተረጋጋ። ኢቫን ካርሎቪች አሁን በደስታ ተሞላ፡፡

«አንቺ ሩሲያዊት፣ ሰራተኛዬ ሩሲያዊት፣ እኔም ሩሲያዊ ... ሁላችንም ሩሲያዊ ቋንቋ ያለን ... አናጢውም ጥሩ አናጢ፣ እንዲያውም ሄጄ እቅፍ አደርገዋለሁ ... ፋብሪካችንም ጥሩ ፋብሪካ ነው ... ሩሲያ እጅግ ያማረች ምድር ናት ... እኔም ከጀርመን ጋር እፋለማለሁ ...»

*ይህ አጭር ልብወለድ ድርሰት (እ.ኤ.አ. በ1883) በሚፃፍበት ወቅት በጋዜጦች ላይ ጀርመን ወታደራዊ ዝግጅት እንደምታደርግና ጦርነት ሲነሳ እንደሚችል ስጋት የነበረበት ዘመን ነው፡፡*



# ኩቲ

## ባሳዝን ደርቤ

መቼም በኛ ሰፈር ኩቲን የሚያክል ጉበዝ ውሻ ይገኛል ማለት ዘበት ነው፡፡ እንዲያው የዝርያ ነገር ሆነና ኩቲ ተባለ እንጂ ሺ መልስ ሺ መክት አሰግድ አናጋው... ቢባል አይበዛበትም ነበር፡፡ ኩቲ የኔ ውሻ ያየውን የሰማውንና የፈለገውን ሳይደብቅ ልቅም አድርጐ ይነግረኛል፡፡ እኔና ኩቲ በቋንቋ ስንግባባ የጉድ ነው፡፡ ታዲያ ኩቲ ከቡችላነቱ አንስቶ ይጮሃል! ይጮሃል፡፡

«ተው እንጂ ኩቲ ለሆነ ላልሆነው ለምን ትጮሃለህ?» እለዋለሁ፡፡

«ሰዎችም እኮ ከኛ በላይ ለመጮህ እየፈለጋችሁ ይሉኝታ ወይም ፍርሃት እየለጉማችሁ ነው ጪሂ የማትመስሉ! የጉንዳኑ ነገር ትዝ አይልህም ጌታዬ?» አለኝ እንዳልቀየመው እጫማዬ ላይ በልፊያ ዓይነት እየተንከባለለ፡፡ -ትዝ አለኝ፡፡

አንድ ጊዜ ኩቲ እሪታውን በድንገት ይለቀዋል፡፡ ማልቀሱ እንጂ መጮሁ እንዳልሆነ የገባኝ ባለቤቱ ፈጥኜ ደረስኩለት፡፡ ከኩቲ ማደሪያ አጠገብ የረጠበ መሬት ሽንቁሮ የፈላ ጉንዳን የሰራ አካላቱን ይለመዝገው ይዟል፡፡ ጉበዙ ኩቲ ይደነፋል፤ ይዘላል፤ ይፍርጣል፡፡ ጉንዳን ላይሸሽ፣ ላይደነግጥ፣ ከንቱ ልፋት፡፡ ጉንዳኑን አራግፌ አረጋጋሁት፡፡ ያሰኔ ማን አለው?

ሆኖም ኩቲን አዳንኩ ብዬ በገላጋይነት ስንጐዳጐድ፤ ጉንዳኑ አይገቡ ገብቶ እኔንም አንጐዳጐደኝ፡፡ ቁንጥጫው እውስጠኛው ነፍሴ ድረስ ዘልቆ ሲያንገበግበኝ እሪታዬን ልለቀው ቃጣኝና ወንድ መሆኔ ታስቦኝ አምቄ ቻልኩት፡፡ አይወንድ እቴ! ለነገሩማ እዚያው ወንድነቴ አጠገብ አይደል የለመዘገኝ፤ ጉንዳኑ፡፡

እንግዲህ ኩቲ ሲነከስ ያለ ይሉኝታ የበቃውን ያህል ጮኸ፡፡ እኔም አጉል ስፍራ ተነከስኩ፡፡ ግን ጩኸቴን ዋጥኩት፡፡ በዚህ አድራጐት ማንኛችን ልክ እንደሆን

መከራ-ከሩ ይቆየንና ኩ-ቲ የተናገረው ግን እብለት የለበትም።። የኔ ውሻ መቼ ይዋሻል ደርሶ? ይጮሃል... ይጮሃል...

«ለምን ትጮሃለህ? ትፈራለህ እንዴ?» ስለው «መጮህ ስላለብኝ ነው የምጮኸው ለፍርሃት እንኳ ሰዎችን የሚያክል የለም። የገዛ ሥራችሁ ፍርሃት ይለቅባችኋል። ደግሞ ብልጦች ናችሁ። ለምሳሌ እኔ ሌሊቱን ሙሉ ስጮህ አንተ ያልሰማህ ትመስልና ታደፍጣለህ። አንዳንዴ ሲነጋጋ ሲያውም ሽጉጥ ደግነህ በርህን በቀስታ ትከፍታለህ- 'አለሁ' ለማለት ያህል። ይህ ሐሰት ነው፤ ጌታዬ?» ይለኛል።

እውነቱን ነው፤ ኩቲ። ጩኸቱ ሲበዛብኝ ዛሬ ወደሰላም ሰፈር ሰተት ብሎ የተመለሰ ሽጉጤን በማስፈራሪያነት ጩብጬ ብቅማለቴ እርግጥ ነው።

«ስማ ኩቲ፤ ለመሆኑ ከምታየውና ከምትሰማው የቱ ይበዛል ትላለህ?»

«የምሰማው ልክና መልክ የለውም፤ በማየቱም በኩል ሰው ከሰው ተደብቆ ጨለማን ተተግኖ የሚሠራውን ወንጀል ለመመልከት ከሰው የተሻለ እድል አለኝ፤ ዞሮ ዞሮ ለማየውም ሆነ ለምሰማው እኩል እጮሃለሁ»

«ለአየኸውስ በጄ፣ ለአልታየ ጉዳይ ለምን ትጮሃለህ?»

«በመሠረቱ እኛ ውሾች ለምንሰማው ነገር መጮህ ባህላችን ነው። በጣም የሚገርመው ሰዎች ላልታየ፣ ላልሆነና ልኩ ላልታወቀ ወይም ከአሉባልታነት ለማያልፍ

አርቲቡርቲ ነገር በጭንቀትና በሹክሹክታ ስትታመሱ ማየታችን ነው:: ይቅርታ ጌታዬ፣ የአንተ ጠርጣሪነት ግን አይከፋም...» ይለኝና ጩኸቱን ይቀጥላል::

ያኔ በ1969-70 ሰው ሰራሽ ሞት በቀይ ሽብር ተመስሎ፣ ጆምበር በጠለቀች ቁጥር የትም እየገባ ያዳምን ልጅ አጅና እግሩን እየቀየደና አንደቡቱን እየሸበበ፣ ወደ መቃብር ሲነዳ ኩቲ የኔ ውሻ ከሰው ተሽሎ፤

«እሪ ያገር ያለህ! ሰው ሆይ ተጠራራና ዝርያህን አድን! ... እያለ ሲጮህ ያልሰማው ባይኖርም የነቃለት የለም::

«ስማ ጌታዬ! እኛ ውሾች በታማኝነትም ቢሆን ከአንዳንድ ሰዎች ልቀን የተገኘንበት ታሪክ ተመዝግቧል:: ፍቅርና መታመን ተፈጥሮ ያደለን ፀጋ ነው:: አያሌ ውሾች ከሚያፈቅሯቸው ጌቶቻቸው መቃብር ላይ አንነሳም እያሉ ለህልፈት ተዳርገው፣ ታማኝነት የውሾች ባህል መሆኑን አረጋግጠዋል:: ሰዎች ግን እርስ በርሳችሁ ስትሰዳደቡ

«ውሻ፣ ከዳተኛ፣ ልክስክስ፣ ምናምንቴ...» እያላችሁ የመጥፎ ምሳሌ ታደርጉናላችሁ:: እናንተ ግን በእምነታችሁ ሸርታታነትና በጥቅም ፍለጋ በህይወታችሁ ጭምር ስትከዳዱ ወቃሽም ሆነ ሰዳቢ የለባችሁም እንጂ፣ በውሻ ፈንታ ወይም ከውሻ በላይ መረገምና መወገዝ የእናንተ እጣ ሊሆን ቡተገባ ነበር:: እኛ ውሾች ለድሃም ሆነ ለሃብታም እኩል እናድራለን:: ፀጉረ ልውጥ ሲሆንብን በሁሉም ላይ እኩል እንጮሃለን እንጂ እንደናንተ ባለፀጋውን ለይተን 'ነወር፣ ነወር' ለማለት ጉብ

ቂጥ አናውቅም:: የክብር፣ የንቀት፣ የአድልዎ ቋንቋ ከኛ ሰፈር የለም» እያለ ይነግረኛል::

ኩቲ የኔ ውሻ ደፋሩ፣ ደጉ፣ ታማኙ፣ የዋሁ ይጮሃል፣ ይጮሃል::

«ምነው?» እለዋለሁ በዚያው በቋንቋችን::

«ከርቀት ተኩስ ሰማሁ» ይለኛል::

«ከኛ ደጅ ካልተተኰሰ በቀር ታዲያ ምን አሰጋህ? አርፈህ ግቢውን ጠብቅ» እለዋለሁ::

«በሩቅ የተጀመረ ከቅርብ እንደሚደርስ ከኔ የተሻለ ጌታዬ የምታውቅ ይመስለኛል:: እየህ እኔ ጦርነት እፈራለሁ:: ጦርነት ከተቀሰቀሰ ሰዎች ለኛ ተገን መሆናችሁ ቀርቶ ቀድማችሁ ታልቃላችሁ:: ከእንስሳት እንሻላለን እያላችሁ ስትኩራሩ፣ ስትሞጋገሱ ትክርሙና በማ ከያው ጦርነት አብቅላችሁ ትፋጃላችሁ:: ያኔ ጦሳችሁ ለኛም ይተርፍና መአት ይወርድ ብናል::

«ስትዋጉም ፈሪዎች ናችሁ:: ማዶ ለማዶ ትሆኑና ጥበባችን ነው በምትሉት መሳሪያ ስትዋጉ እናንተ በናንተ ላይ የወረወራችሁት የፈሪና የጨካኝ በትር እናንተን እየሳተ ወይም አብሮ እኛንም እንዳልነበርን ያደርጋል::

«በትር ያማዘዘው ልዩነታችሁ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ወይም የባህልና የሃይማኖት ካልሆነም የዘር ጣጣ፣

በማናውቀውና ጉዳያችን ባልሆነ መዘገዘ በናንተው ዳፋ እንረግፋለን:: ለእናንተ ሲለቀስ፣ የኛው ሞት በእናንተው አባባል «የውሻ ሞት» ሆኖ ይቀራል:: የተረፍነውም ፍርፋሪ የሚጥልልን አጥተን በረሃብ እናልቃለን:: እንዲያም ሲል ከሰው ጋር የሰው ፍርፋሪ ለመቧገት ከስደት ጉዳና ገብተን ስንንከላወስ የትም እንወድቃለን::

«ምን አማራጭ አለን? ዝርያችን ከአውሬነት የዱር ኑሮ ወጥቶ ሰውን ከተጠጋ አያሌ ሺ. አመታት አልፈዋል:: ከሰው ብንውልም ቅሉ ሰው መሆን አልቻልንም:: ስልህ ግን የሰውን ምስጢርና ገመና ልቅም አድርገን እናውቃለን:: ቂም የቋጠረ ልቡን ከፊቱ ንባብ ላይ በቀላሉ እየተረዳን እግዚአ ለምህረቱ እያልን እንጮሃለን:: ሰውን በተንኰለኛ ገጹ ባየነው ጊዜማ የኛው ውሻ ሆኖ መፈጠር ይወደዳል እንላለን::

«ተግባባን ጌታዬ! አብዛኛው የቀን፣ የሌሊት ጩኸታችን ጦርነት እንዳይሆን እግዚአ ለፈጣሪ ማለታችን ነው:: ሰዎችን ከሁሉም በላይ የምንታዘባችሁና የምንንቃችሁ የራሳችሁን ዝርያ ለማጥፋት ጦርነት ተንኩሳችሁ ስትፋጁ ነው:: የትም ሊያደርስ የሚችለውን የሰላም ጉዳና እየተዋችሁ ጦርነትን እንደአቋራጭ መንገድ ትከተሉና ለፍጥረታት ሁሉ ማብቂያ የሌለው መከራ ታመጣላችሁ:: ለነገሩ እኛም አልፎ አልፎ አምባጓሮ እየፈጠርን እርስ በርስ መናከሳችን ባይቀርም፣ ጥሉ ወዲያው ይበርድና ይረሳል:: ሌላ ጊዜ

ብንናከስም ዛሬ ተፈጥሮ፣ ዛሬውኑ በሚጠሩ ጉዳይ እንጂ እንደናንተ በዋለ ባደረ ቂም አይደለም:: የኛ ግጭት አሸንፈንም ይሁን ተሸንፈን ወይም ደክመንና ሰልችተን በቅጽበት ያበቃል እንጂ ጦሱ ለሌላ ዝርያ እስኪ ተርፍ አይቀጥልም:: ታዲያ ሰዎች፤

'ዘላለም እንደውሻ መናከስ ...' እያላችሁ ስትዘባበቱ እጅግ ይገርመናል- እኛ ውሾች:: አለ እንጂ የእናንተ ጉድ! ስንቱ ሚሊዮን ዝርያችሁን አፈር የመለሰበት ጦርነት:: ስንቱን የሰው ልጅ፣ እጅ እግሩን አሳጥቶ በእንፉቅቅ እያስኬደ ህይወትን የሚያስረግም:: ከእልቂትና ከጉዳት መማር ተስኖ፣ ለጠቅላላ ውድመት የሚሽቀዳደም እስገራሚ ፍጥረት ከእናንተ በላይ ምድር አላፈራችም:: የኛ ጠብ ቂም በቀል የለውም:: ሁላችንም መጮህ ስላለብን እንጮሃለን:: የዚያኛው ግቢ ውሻ ሲጮህ እኔ ዝም አልልም:: ሰው ግን የወዲያ ማዶ አምሳያው በእሳት ሲጋይ እያወቀ፣ በአላየሁም ባይነት ከራሱ ህሊና ሊደበቅ በማይቻለው ከንቱ ማስመሰል ይማስናል:: ብቻ ሰው ሲባል ቂምና ጥላቻን ሰንቆ በክፋት ጉዳና መጓዝ ከጀመረ ከስህተቱ ሊመለስ የማይፈቅድ አስቸጋሪ ፍጥረት ነው:: አዬ ሰው!!» አለ ኩቲ በምሬት::

«በሰው ዘር ላይ ጥላቻ አለህ ማለት ነው ኩቲ?» አልኩት::

«ከባድ ጥያቂ አመጣህብኝ ጌታዬ:: ለመሆኑ

የትኛውን ሰው ነው የምትለኝ? ሰው እኮ ሁሉም ነገር ማለት ነው:: ሰው ለበጐ ሥራ ከቆመ ከእግዚአብሔር ለጥቆ ያለውን የደግነት ሥፍራ ይይዛል:: የጥፋቱን ጐዳና ከተከተለም የዲያቢሎስ አምሳያ ሆኖ ይገኛል:: ታዲያ የትኛውን ማለትህ ነው? ስለአንተ ብትጠይቀኝ አሳምሬ መናገር እችላለሁ:: ለምሳሌ እኔን ትጠደኛለህ:: ከመውደድህ ላይ ግን ብልጠት አለበት:: ግቢህ እንዲታፈርና ሌባ አጥር ሰርስሮ እንዳይዘልቅ እንጂ ከዚህ አያልፍም ውዴታህ::

«ብዙ ጊዜ ታዝቤሃለሁ:: ከጨዋታችን መጀመሪያ ላይ እንደነገርኩህ ላየሁትም ሆነ ለሰማሁት የድረስልኝ ጩኸቴን ሳሰማህ፣ ከሚስትህ ታቅፈህ የምታደፍጥበት ጊዜ ይበዛል:: ባለቤትህ የኔ እመቤት ደግሞ መሸቀርቀር ታበዛለች:: የሸቶዋ ጠረን ስታልፍ ስታገድም በዚችው ጐራዳ አፍንጫዬ እየገባ ያስነጥሰኛል:: ታዲያ ቅናት ነው መሰለኝ ነጋ ጠባ ስትነዛነዙ እሰማለሁ...» አለ::

«በቃ! በቃ! አበዛኸው ኩቲ! በሰው ትዳር መሃል አንተን ምን ዶለህ? እንዲህ ያለ ወሬህን እጅሪት ብትሰማ ወገብህ እስኪለመጥ በፍልጥ ታንቆራጥጥሃለች ዋ!» አልኩና ተቆጣሁት::

«እሺ ጌታዬ፣ እሱን እንለፈውና ከጀመርን አይቀር ስለጐረቤቶቻችን ላውጋህ:: ከኛ ለጥቆ ቤት የሠራው ሰውዬ ስግብግብ ነው:: አጥሩን ወዲህ እያንፏቀቀ ወሰን ይገፋል::

ቆሻሻውንም ወዲሁ ይደፋል። ከአንተ ቤት ቡና ይጠጣል፣ ከሱ ቤት አይጠራህም፤ አንተ ታከብረዋለህ፣ እሱ ይንቅሃል፤ አንተንማ ባይንቅ እኔን አይመታኝም ነበር። የላይኛው ግቢ ባለቤት ደግሞ ከአንገታቸው ተጐንብሰው የጦርነትን ነገር ያቶስቱሳሉ። ሲያስጠሉ!! እሳቸውን ሳይነካ ድብልቅልቁ የወጣ ጦርነት ቢሆን ይወዳሉ። ደግሞ ፈሪ ናቸው። እንኳንስ መሳሪያ አንስተው ሊዋጉ ይቅርና ጓደኛዬ ውሻቸው ሲጮህ ጨርሶ ብቅ አይሉም። አንዳንድ ሰሞንማ እራሳቸው በፈጠሩት የምኞት ሽብር እየበረገጉ ከቤታቸው ይወጡና ከዘመድ አድረው ይመለሳሉ። ጦርነትን በመሰለ መቅሰፍት ሌላው ጋይቶ እንዲያልቅና ምድር እንዲሰፋቸው የሚመኙ የሰላም ምቀኛ ናቸው።

«ደላላው ጐረቤታችን ደግሞ እጥብ ያሉ ጮሌ ናቸው። አሮጌውን አዲስ፤ ርካሹን ውድ፣ ትንሹን ትልቅ፣ መጥፎውን ጥሩ ያደርጉና በሌላቸው ትህትና ከአንገት በላይ ስቀው እያሳሳቁ በሚሰሩት ሁሉ ወደ ኪሳቸው የሚገባ የማያጡ ናቸው። ጅል ተገኝቶ ወደገበያው የሚነዳ ከሆነ፣ ጦርነትንም ከመደለል አይመለሱም። ኧረ ስንቱ ጌታዬ» አለ ኩቲ።

«ኩቲ በቃህ! ይኸኛውም በሰው የግል ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ሃሜትን ማራባት ነው። ሆድ የሚያሻክር ሰብቅ ነው። አንተ ግቢውን ከመጠበቅ ወዲያ የሚያገባህ ጉዳይ የለም- እሺ!» አልኩና ወረፍኩት።

ይጮሃል... ይጮሃል-- ኩቲ የኔ ውሻ፡፡

«ደግሞ ዛሬ ምን ሆንክ?» እለዋለሁ፡፡

«መጮህ ስላለብኝ ነው የምጮኸው፡፡ አንተ'ማ ምን ተዳህ? አደብ ተላብሰህ ተኛ እንጂ ጌታዬ» ይለኛል፡፡

«አብረን እንጩህ ነው የምትለኝ?» ስለው፤

«ሰዎች እኮ ኩሩ ናቸው፡፡ እናንተ ድምጻችሁ ሳይሰማ ነው የምትጮሁ፡፡ አዲስ ሰበብ ስታገኙ ግን የብዙ ጊዜ እምቃችሁን ትጮሁና ታስወጣላችሁ፡፡ ዘንድሮ ለሆነው ግድ ባይኖራችሁም አምና ለሞተው ማልቀሻ ሰበብ ይሆናችኋል፡፡ ግን ተለቀሰም፣ ተዘፈነ፤ ተሳቀም፣ ተኮረፈ፤ መሆን ያለበት ከመሆን ይቀራል ማለት ዘበት ነው» ይለኛል፡፡

«ኩቲ ለመሆኑ የጊዜውን እንቅስቃሴ እንዴት ታየዋለህ?» እልኩት፡፡

ትንሽ ሲያስብ ቆየና፤

«አዲስ ዘመን ተጀምሯል፡፡ አሁን ያለው ሁናቴ በደጋፊ ወይም በተቋዋሚ ተጽእኖ ሥር ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡ ይልቁንም መሆን ያለበት እየሆነ ነው እላለሁ፡፡ በተለይ በአንድ ጉዳይ በጣም እርግጠኛነኝ፡፡ ለበጐ ግብ ተነስተናል የሚሉ ሁሉ እስከ ወዲያኛው ሊጓዙበት የሚችሉ ጥርጊያ መንገድ ለመበጀቱ በእማኝነት ልጠራም፤ ልቆምም እችላሁ» አለኝ በሙሉ ልብ፡፡

«ነገሮች ሁሉ እርጋታና ስክነት ያገኙ አስመስለህ እንዴት ትናገራለህ? ጋዜጣና መጽሔቱ ሁሉ መንግሥትን ሲሳደብና ሲያማርር እየዋለ... ያለፈው መንግሥት ተከብሮ ነበር የሚኖር...» አልኩት፡፡

«እሄሄ! እንዴት ሻል? ድንቄም ተከብሮ መኖር!...» በማለት ያቺኑ ከኔ የቀዳትን የለበጣ ሳቀብኝና፤

«...ያለፈው መንግሥት በገዳይነቱ ተፈርቶ እንጂ ተከብሮ እንዳልኖረ ልቦናህ እያወቀ ባታላግጥ ይሻላል ጌታዬ፡፡ በዚያ የጽልመት ዘመን እንደዛሬው ያለ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ቢታይ ኖሮ አገሩ ከዛሬው ሚሊዮን ጊዜ በላይ መንግሥት ተብየውን በተሳደበ ነበር፡፡ በዚያ የፍዳ ዘመን ዴሞክራሲ ቢኖርማ አንድ ሙሉ ትውልድ ከምድር በታች የመውደቅ መዓት ባልወረደበት ነበር፡፡ እልቂቱም ለዴሞክራሲ ነበርና ዴሞክራሲን አብቅሏል ዛሬ፡፡ የዴሞክራሲ ጥማት ሲያንገበግበው ለኖረ አገር፣ ጋዜጣና መጽሔት እንደ እንጉዳይ ፈልቶ የፈለገውን ለማለት መቻል ሺዎች በጀግንነት የወደቁለት ድል ነው...ለዚህም ነው አዲስ ዘመን ተጀምሯል ማለቴ፡፡ተግባባን ይሆን ጌታዬ?» አለኝ ኩቲ፡፡

«ኩቲ ሲበዛ ወሬ ለመድክ እኮ!» አልኩት ነገሩ ገርሞኝ፡፡

«ውሎዬ ከማን ጋር ሆነና— ከሰው አይደል!»፡፡

«ስመሆኑ ዋናው ፍላጐትህ ምንድነው?»::

«ሰላምና ጥጋብን አጥብቄ እፈልጋለሁ:: እንጀራ እንኳንስ ለሰው ልጅ ለውሻ ተርፏል የሚባልበትን የጥጋብ ዘመን ሞት ሳይቀድመኝ ማየት እሻለሁ:: ከሁሉም በፊት ግን ዘላቂ ሰላም እንዲወርድ ለፈጣሪ ጩኸቱን አሰማለሁ:: ሰላም ከሌለ እንኳንስ የእንስሳት ፍላጐት የሰው ልጆችም እቅድ ምኞት ሆኖ ይቀራል»

ታዲያ ኩቲ ይጮሃል፤ ይጮሃል::

በተለይ በ1983 የግንቦት ወር ሊጋመስ ጥቂት ሲቀረው ከፋኛ ጮኸ ኩቲ::

«ኧረ ተው ኩቲ! እንቅልፍ አትንሳኝ! ዛሬ ደግሞ ምን ነካህ?» አልኩት::

«ጉድ መባል የሚያንሰው ጉድ ፈልቷል አባክህ! መንግሥቱ አገር ጥሎ ሸሸ!!» አለኝ::

«ታዲያ አንተ ምን ቸገረህ? እኔ እያለሁልህ፣ የሱ ውሾች ይጨነቁ እንጂ» አልኩት::

«ሁሉንም የሱ ውሻ ሊያደርግ አልነበር ምኞቱ፤ ጊዜ በጊዜው ከዳው እንጂ:: ኧረ ጉድ ነው! እንዴት መሪ ይፈረጥጣል?! 'እኔ ቆራጡ ፈሪ አልወድም!! ፈሪ ፈሪውን በጥይት በልልኝ!! በጠላቶቼ ላይ ሞትን እየዘራሁ በእናት አገሬ ምድር ጥርኝ አፈር እሆናለሁ::' እያለ ፋከራው አገር ሲያደናቁር የከረመ «ጀግና» እንኳንስ የሰው ልጅ ውሻ

በማይሰማው አሾላለክ ኰቴውን አጥፍቶ ፈረጠጠ።

«ፈሪ የማይወደውን «ቆራጥ» ፈሪና ፍርሃትን እንደረገመና እንዳወገዘ፣ግን ጉበኞችን እንደፈጀ የኖረውን «የቴዎድሮስ ምትክ» ፍርሃት እስከ ደቡብ አፍሪካ ጫፍ ይዞት ነጉደ። ከዚያም ወዲያ ርቆ ቢሸሽ ባልጠላ ነበር-መሬት ክብ ስለሆነች አዙሪ አራት ኪሎ እንዳትመልሰው ፈርቶ እንጂ። ፈረጠጠ፣ ለአንተም በምሳ ሰዓት የመሸሹን መርዶ ራዲዮ ያረዳሃል...» አለኝ ኩቲ የኔ ውሻ፣ ከአገር ቀድሞ የሰማውን።

«ተው እንጂ ኩቲ! በቋንቋ ከተግባባን አይቀር ብለህ በነገር አትንካኝ!! የመንግሥቱ ሽሽት ለኔ መርዶ ይሁን የምሥራች ለይተህ የምታውቅም፣ የሚያገባህም አይመስለኝም» አልኩት።

«እስቲ ይሁን» አለና በምጸት ዓይነት ያስተውለኝ ገባ እንጂ ክርክር ሊገጥመኝ አልወደደም፣ ኩቲ።

የ«ቆራጡ» ሽሽት እርግጥ መሆኑ ሲታወቅ፣ ለሳሎኔ ግርማ ሞገስ ይበጅ መስሎኝ የሰቀልኩትን ፎቶግራፉን አውጥቼ ስወረውር፣ ባይናገረኝም በትዝብት ዓይን ይመለከተኝ ነበር ኩቲ።

ግንቦት 20/1983 ጉህ ሲቀድ አቅራቢያም ኩቲ ጨኸቱን አቀለጠው።

«ወይ ጣጣ! ዛሬ ደግሞ ምን ነካህ?» አልኩት።

«ወያኔዎቹ በዚህ በኩል እየገሰገሱ አራት ኪሎ ገቡልህ!» አለኝ::

«እውነት አየሃቸው?» አልኩት::

«በሚገባ አየኋቸው! ጠመንጃና ቦምብ ታጥቀዋል፤ ሁሉም ልጅ እግሮች ናቸው:: ፀጉረ ልውጥ ስለሆኑብኝ፣ ለወጉ ያህል በውሸነቱ ጮህኩባቸው እንጂ ነገረ- ሥራቸው ደስ ብሎኛል:: እነሱ ግን ባገር ምድር ያለው ውሻ ቢንጫጫ ጉዳያቸው አይደለም:: ወደፊት እያሉ ወደፊት ከመራመድ በቀር ቆመው ሲያመነቱ አላየኋቸውም::»

ኩቲ አልዋሸኝም:: ትንፋሼን አጥፍቼ በጭላንጭል አጮልቄ ያየሁትን እውነት ነው የነገረኝ::

«ታዲያ እንዲህ የሚገሰግሱት የት ለመድረስ ይመስልሃል?» አልኩት::

«በእርግጥ ሁነኛ መድረሻውን የሚያውቀው ተንገፍ ነው:: ከመንደር ሆኖ መገመቱ ቢያስቸግርም ሊሆን የሚችል አስተያየት መሰንዘሩም ክፋት አይኖረውም:: ይቺን አገር ከወደቀችበት የችግር አረንቋ ለማውጣት እንደ አነሳሳቸው ገና የትየለሌ ይጓዛሉ እንጂ አራት ኪሎ መድረስ የመጨረሻው ግባቸው ሊሆን አይችልም» አለኝ::

«ኩቲ የለም! የለም! በምትናገረው ሁሉ ክፉኛ ጠረጠርኩህ:: በዚህ ጥያቄ ላይ ቀድመህ የተዘጋጀህ ይመስለኛል:: እንዲያውም አባል ሳትሆን አልቀረህም»

አልኩት::

«አባል መሆን እኮ ተራ ፎርማሊቲ ነው:: ቁም ነገሩ በእውነተኛ ነገር ከማመኑ ላይ ይመስለኛል:: ደግሞም እንኳንስ እኔ ህይወትን ከሰው ልጅ በቅርብ የምጋራው፣ መላው የእንስሳ ዝርያ ለሰላም ደህንነት አባል ቢሆን ቢያንስ እንጂ አይበዛም» አለኝ ፍርጥም ብሎ::

«ስማ ኩቲ፣ አንተ እንደምትነግረኝም ሆነ ከሁናቴዎች እንደምረዳው ከግንቦት 20/1983 ማለዳ ወዲህ ያለፈው አብቅቶ አዲስ ታሪክ ተጀምሯል:: ታዲያ በበፊት ኑሮህ የሚቆጭህ ነገር ይኖር ይሆን» አልኩት::

«አዎ በግልጽ የሚቆጨኝ ነገር አለ:: ዛሬ እንደማየው ከኛ የማይሻሉ ሰዎች ነበሩ አገር ሲገዙ የኖሩት:: ታዲያ በዚያ የፍዳ ዘመን ከዛሬው በላይ መጮህ ነበረብኝ:: እንዲያ ባለማድረጌ ይቆጨኛል...» አለኝ::

«ኩቲ ለመሆኑ ይህ ነገር እንደሚሆን አስቀድመህ ትገምት ነበር?»

«አሳምሬ እገምት ነበር:: ገገሮች የነሱን መሸነፍ እንደ ተረት ቆጥረው አገር ሲያደነቁሩ ቢከርሙም፣ ዛሬ የሆነው ሊሆን እንደሚችል ጠረኑ ይሸተኝ ነበር»

«ታዲያ ለምን አስቀድመህ አልነገርከኝም ነበር?»

«አዬ ጌታዬ! እንዳትቀየመኝ እንጂ አንተ እኮ

እንኳንስ ውሻ፣ ሰው ቢነግርህ የማትሰማ ግትር ነህ። ለነገሩ ታማኝነቱን ለመግለጽ ካልሆነ በቀር ብነግርህም ባልነግርህም በማይሆነው ጉዳይ ላይ ለውጥ አያመጣም ነበር» አለኝ ከምሩ።

በዝምታ ሳስተውለው ቆየሁና፤

«ወያኔዎቹን አትፈራቸውም ኩቱ?» አልኩት።

«ጌታዬ እኔ የማላውቀው ኃጢያት ካለብህ አንተ ፍራቸው» አለኝና ጩኸቱን ቀጠለ።

«ኩቱ እረ በፈጠረህ እረፍ! እኔ ትንሽም ብትሆን ነገር ብጤ አለችብኝ፤ ያደፈጥኩበትን ቦታ በጩኸትህ አታመላክትብኝ እባክህ!!» እያልኩ ተማፀንኩት፤ በዚያው የግል ቋንቋችን።

«ያለህበትን የሚጠቁም ምግባርህ እንጂ የኔ ጩኸት አይመስለኝም። ተደብቆ መቆየት እንጂ ማምለጥ የሚቻል አይሆንም። ለማንኛውም ትክክለኛ እማኝህ ውስጥህ ብቻ ነውና ከዚህ ውጭ በሆነ ጉዳይ ሕሊናህ እየበረገገ ሥጋት አይጉዳህ… እኔ በውሻነቴ መርጫህ ስላለብኝ እጮሃለሁ። መደበቅ፣ መያዝ፣ መታገት፣ ክስ፣ ማስረጃ፣ እርቅ… እየተባለ ባለፈ ጉዳይ ላይ እንደናንተ ጠያቂና ተጠያቂ የሚባል ጣጣ በውሾች ባህል ጨርሶ የለም። ደስ አይልም ጌታዬ? ብቻ ምነው ውሻ ሆኘ በተፈጠርኩ እንዳትለኝ እንጂ። ከፈለግህ አብረን እንጩህ። ጩኸት ፋይዳ የለውም የምትለው ፍልስፍና በውሾች ሰፈር ሃሪም ዓይነት ነገር ስለሆነ እጮሃለሁ!» አለና ጩኸቱ ባሰበት።

የኩቴ ነገር ገረመኝ:: አንዳንዱ አባባሉ ሲያበረታኝ፣ ሌላው ያስፈራኛል:: የውሻዬን ንግግር እያውጠነጠንኩ ጭነት የሚሞላ «ሠርቶ አደር» ጋዜጣ የክት ከሆነበት ጓዳ አውጥቼ ክብሬት ስጭርበት፤

«ይኸ ያልታደለ ጋዜጣ፣ ከግድግዳ ላይለጠፍ፣ እቃ ላይጠቀለልበት፣ በክብር ስም እስረኛ ሆኖ ኖረ:: በመጨረሻም የሳት አደጋ ላይጠራለት ሆኖ በክብሬት ነደደ:: ምናለበት ለሥጋ ቤት ብትሸጠው? ደግሞስ ከምኑ ለማምለጥ ብለህ ይሆን ወረቀት የምታቃጥል?» አለኝ:: መልስ አልነበረኝም ለኩቴ ጥያቄ::

· «ኩቴ አታስፈራራኝ እንጂ፣ ገራገሩን ብንነጋገር ይሻላል:: በእርግጥ በውሻነትህ እንደልብህ መጮህ ብትችልም ነገር ከተፈለገ አይጠፋም-- ዋ!!» አልኩት::

«ምን ኃጢያት ይኖርብኝ ጌታዬ?» አለኝ ድንጋጤ እየታየበት::

«ያኔ በ1970 የፀደይ ወር፣ አንድ ታጋይ የፋሺስቶችን እስር ቤት ሰብሮ ሞትን ለማምለጥ በኛ ጓሮ ሲወድቅ፣ ሲነሳ ጩኸህ ማሲያዝክን ዘነጋኸው እንዴ?»

ሃሳብ ወደዚያ የእልቂት ዘመን ይዞት ነጕደና ዝምታ አፈዘዘው::

«ልክ ነህ ጌታዬ፣ የሰዎች ብልጫችሁ ከዚሁ ላይ ነው:: ሕሊናችሁ በልግም ካልታወከ በቀር ከማድረጋች

በፊት ታጣራላችሁ:: ቢያንስ ትገምታላችሁ:: እኔ ሠፈራችን እንዳይደፈር በውሻነቴ ዱካውን ለጥቂ ስጮህ፣ የሞት አጃቢዎች ደርሰው ያን ያልታደለ ፍጡር የመትረፍ፡ ሙከራ አመከኑበት:: ታዲያ ሌባ መስሎኝ እንጂ በእውነቱ ማንንም ወግኘ አልነበረም» አለ::

«መስሎኝ ነው ማለት ካዋጣማ ሥጋት የለም» አልኩት::

«የምን ሥጋት አመጣህብኝ ጌታዬ? እኔ እኮ ውሻ ነኝ:: ሸር ስሌለበትና በአጋጣሚ ለተፈፀመ ጉዳይ መሸበሩ አጉል ስለሆነ አልሰጋም:: አይመስልህም ጌታዬ?» አለና ሲጠይቀኝ ከዝምታ በቀር ቃል አልተነፈስኩም::

«ተከፋህ እንዴ ጌታዬ?» አለና፤

«እሽሩሩ ጊዜ... ዘመን እሽሩሩ፤

ባይሳካልኝም እንደ ሰው መኖሩ::

እምብዛም አይከፋኝ ማደሩ ከታዛ፤

እንዳይርቀኝ ብቻ የሰላም መዓዛ...»

በማለት እያንጐራጐረ ያስደስተኝ ገባ::

ኩቲ እርጅና እየተጫጫነው መጮሁን ተወ:: እንዲያም ሆኖ የልቡን ሳይነግረኝ አይውልም::

«...አዲስ የሰላም ዘመን በመጀመሩ፣ ሕዝቦች ከጦርነት

መዓት እየወጡ፣ የማኅበራዊ እድገት ጉዳናን በመያዝ ላይ ይገኛሉ። ግንቦት ሃያ ገና ከማለዳው የተጀመረው ጉዞ የሚደርስበትን ብሩህ ግብ ከሰማይ ቤት ሆኜ ቁልቁል ለማስተዋል ዘላለማዊ እድል አለኝ...» እያለ በጣእር የተናገረው የመጨረሻ ቃሉን አስደምጦኝም ባለፈው ሳምንት የተፈጥሮ ሞቱን ሞተ። የኩቴ ነፍስ በሰማይ ቤት ደህና ሥፍራ አታጣም- ጨኸት ካላስኮነነ በቀር።



ሰካራም ቤት አይሰራም



# በቀል

## አንቶን ቼኾብ
## (ትርጉም) አፈወርቅ ዘለቀ

ከተሜው ሊብ ሳቪች በመሀከለኛ ኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ጐልማሳ ነው:: ድንቡሽ ያለች ቆንጅዬ ሚስት አለችው:: አንድቀን በጓደኛው የልደት በዓል ላይ ተገኝቶ ቁማር ሲቆምር አረፈደና መበላቱ ቢበዛበት፣ ከንፈሩ በጥም ቢደርቅበት፣ ትንሽ ከወደ አረቂው ልጐንጭ ብሎ ከቁማሩ ላይ ተነሳ::

እየተጀነነም በሚደንሱት ወጣቶች መሀል አቋርጦ፣

ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍል አመራ። በዚያው በትንሿ በር ሾልኮ ወደ መጠጥ ክፍሏ ገባ። በያይነቱ ከተደረደሩት መጠጦች ቮድካ መርጦ ቀዳና ባንድ ትንፋሽ ጅው አድርጎ፣ በሹካ እየወጋጋ እማበላ ሲቀማምስ ከወዲያኛው ክፍል አንድ የማያውቀውን ድምጽ ሰማ።

«...እሺ ይሁን፣ ብቻ መቼ እናድርገው?» የሚል በጉጉትና በመቋመጥ ስሜት የተወጠረ የሴት ድምጽ ነበር።

«ሚስቴ ናት» አለ ድምጿን ወዲያውኑ ለይቶ፤ <ከማን ጋር ትሆን?> ሲል ራሱን ጠየቀ «ደስ ባለሽ ጊዜ፣ የኔ ቆንጆ» የሚል መረዋ ድምጽ መልስ ሰጣት፤ ድምጹ ቀጠለ «ብቻ ዛሬ አይሣካም፤ ነገም ቢሆን ሙሉቀን ስጣደፍ ነው የምውለው..»

«ዶ/ግትያሬብ ነው» ሲል ሲብ ሣቢች ከጓደኞቹ አንዱ መሆኑን አረጋገጠ። «አውሬ! አባብላው ይሆናል። ፊት አሳይታው መሆን አለበት። ... እንዴት ያለችዋ ሴሰኛ ናት ጃል! አንዲት ቀን እንኳን ያለወሲብ መቆየት የማይሆንላት።»

ባለመረዋ ድምጹ የሙዚቃ ቅላጼ ባለው ቃና ማውራቱን ቀጠለ፣

«... እንዳልኩሽ ነገ ሙሉ ቀን አይመቸኝም፤ ፈቃድሽ ቢሆን ነገ ማስታወሻ ብትጽፊልኝ ደስ ይለኛል። ለመልእክቱ የራሳችንን ዘዴ እንቀይሳለን። ... በፖስታ ቤት በኩል መጠቀም አደገኛ ነው። ምክንያቱም አሮጌ የቱርክ ዶሮ የመሰለ ባልሽ ከፖስተኛው ሊጠልፈው ይችላልና ነው። ነንቴም የሚላከው መልእክተኛ በሌለሁበት በባለቤቴ እጅ ወድቆ መዘዝ ያስከትላል። በአሽከር ብልከውም ችግሩ ያው ነው፣ ወዘናዛዛው ባልሽ ተቀብሎ ሊያየው ይችላል።

... ስመሆኑ አሁን ምን እየሰራ ነው? እዚያው ቁማሩ ላይ ይሆን?» ሲል ጠየቃት:: «አዎ! ሁሌም መበላት የማይሰለቸው ጅል» አለች መልሳ::

«በቁማር ባያድለው በፍቅረኛ አድሎታል» ብሎ ሣቀ::፣ ውዶ ሌላውን እንተውና ይህን ብሩህ ሀሳቤን አድምጭኝ:: ነገ ልክ ከቀኑ 6:00 ሰዓት ላይ ተቆጣጣሪውን ለመገናኘት በመናፈሻው መሀል ስለማልፍ፣ ከ6:00 ሰዓት ትንሽ ቀደም ብለሽ መልእክቱን እመናፈሻው ውስጥ ከወይኑ በግራ በኩል ባለው የእብነበረድ ገንቦ ውስጥ አኑሪልኝ:: ምርጥ ሃሣብ! ያ ጅላጅል ባልሽም ሆነ ሚስቱ አይነቁብንም ማለት ነው:: የዘየድነው ብልሃት ቢፃፍ ጥሩ የፍቅር ገድል ይወጣዋል:: ... ታዲያስ ፍቅሬ! ታረጊው የለ?»

ሌብ ሣቪች አንድ ብርጭቆ ቮድካውን ደግሞ ጨለጠና ወደ ቁማሩ አመራ:: ከሚስቱ ያለሌኑት ተግባር ይልቅ ከውሽማዋ ጋር የሰደቡት ስድብ ዘልቆ ተሰምቶት ኖሮ፣ አንገበገበው::

«... ምን የማይረባ ፍጡር ነው፤ ዴግትያሬቭ ብሎ ሰው» ሲል አሰበ ሌብ ሳቪች:: በእለቱ የተበላውን ገንዘብ እየመዘገበ:: «ስንገናኝ እንደደህና ወዳጅ እየቀላመደ ከኋላዬ ጉርጓድ ይምስልኛል:: እኔ ጋር ሲሆን 'ውድ ጓደኛዬ' ሲለኝ ቆይቶ፣ ከጀርባዬ ወዘፈዛፋ፣ ጅላጅል፣ አርጌ ዶሮ እያለ ይሞልጨኛል! ...»

መበላቱ በጨመረ ቁጥር ጥቃቱ ይበልጥ እየተሰማው መጣ:: ድንገት አፈፍ ብሎ ተነሣና፣ «ግድ የለም፣ ወዘፍዛፋነቱን አሣይሃለሁ» ሲል አጠገቡ በሌለው ጠላቱ ላይ ዛተ::

በአራት ስነስርዓቱ ላይ ሌብ ሳቪች የዴግትያሬቭን

ፊት ማየት አስጠላው:: በዚያ ላይ ለማስመሰል የሚያደርገው መቀላመዱና የሚስቱ ደርሶ ጨዋ መሃይነት ተደማምሮ ብስጭቱን አባብሰውበት አመሸ::

ግብግቡ ተጠናቆ ወደቤት ሲመለስ፣ ሌቭ ማቪች በንዴት እንደጦፈ ነበር:: ንዴትና ስቃዩን እንደምንም ታግሶ ወደመኝታው ቢያመራም የሚስቱን ሹክሹክታና የውሽማዋን ስድቦች ጅላጅል ... ላፍታም ሊረሳቸው አልቻለም::

«... ባደባባይ በጥፊ ባጮልኩት ኖሮ» ሲል ተቆጨ:: መፋለምም ከጀለው:: ደብዳቤ የሚጠብቅበት የእብነበረድ ገንቦ ውስጥ ዓይነምድር፣ ወይም ሌላ የሚገማ ነገር ፈልጎ፣ ወይም ደግሞ የሞተ አይጥ ሊያስጨብጠው አሰበ:: የሚስቱን ደብዳቤ ወስዶ በምትኩ እገንቦው ውስጥ ሌላ ... የስድብ ደብዳቤ ለማስቀመጥ አሰበ::

ሌቭ ማቪች እነዚህንና ሌሎች ሊፈጽም ያቀዳቸውን መቋጫ የሌላቸው የተንኮል አይነቶችን እያሰመና እያውጠነጠነ ፈካ አለ::

በድንገት ግንባሩን መታ መታ አድርጎ ... 'ብራቮ አገኘኋት' ብሎ በደስታ ፈነደቀ:: ምርጥ ሀሳብ .. ድንቅ ፈጠራ!

ሚስቱ በሰላም እንቅልፏን ስትለጥጥ ወደ ጠረጴዛው ሄዶ የሚከተለውን አቀለመ:: የእጅ ጽሁፏን ለውጦ አንዳንድ የፊደል ግድፈቶችን በማከል፣

«ለነጋዴው ዱሊኖቭ፣ በዛሬዋ እለት ማለትም መስከረም 12 ልክ በ6:00 ሰዓት፣ 200 ሩብል እመናፈሻው ውስጥ ከወይኑ አፀድ በስተግራ ባለው የእብነበረድ ገንቦ

ውስጥ ካላኖርክ የእቃ መጋዘንህ ይጋያል፣ አንተም ትገደላለህ»

ደብዳቤው ተፃፈ:: ሌብ ሣቢች በደስታ ጮቤ ረገጠ::

እጆቹን እያፋተገም «አይ ፈጠራ! ሰይጣን እራሱ እንኳን ቢሆን ከዚህ የተሻለ በቀል ሊያስብ አይችልም:: ነጋዴው ሆዬ ገና ደብዳቤዋን እንዳነበበ ለፖሊስ ያመለክታል:: ፖሊሶች ደግሞ ሰዋራ ቦታ ተደብቀው ይጠብቁታል:: አጅሬ ያጅሬትን ደብዳቤ አገኘሁ ሲል እጅ ከፍንጅ ቀጨም! ያረጉልኛላ!... ጉዳዩ እስኪጣራ አንጀቴን ያርሱልኛል:: ... ወንዳታ!»

ሌብ ሣቢች ቱምብሩን ፖስታው ላይ ለጥፎ ራሱ ፖስታ ቤት አደረሰው:: ከዚያ መልስ አስደሣች ህልሞቹን አየ:: የሰላም እንቅልፉንም ለጠጠ::

ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነቃ የማታውን ድንቅ የፈጠራ ችሎታውን እያስታወሰ ተደሰተ:: ከደስታው ብዛት የእምነተ ቢስ ሚስቱን አንገጭ በፍቅር ቆንጠር ሊያደርግ ዳዳው::

በድል አድራጊነት ስሜት እየነጠረ ወደ ስራ ሲሄድ እግረመንገዱን ጣውንቱ ዬግትያሬብ በወጥመድ ሲወድቅ የሚደርስበትን ስቃይ በሀሳብ እየቃኘ በደስታ ተፍነከነከ::

የጠላቱን ስቃይ ለማየት የናፈቀው ሌብ ሣቢች የስራ ሰዓት ማብቂያ እስኪደርስ አላስችል ብሎት ገና አምስት ሰዓት ሣይሆን ከስራ ወጥቶ ወደመናፈሻው ተጣደፈ::

'አሃ!' አለ፣ በርካታ ፖሊሶቹን እመናፈሻው አካባቢ በማየቱ:: '... ቀድመው ሌባ ለመያዝ ተንቀሳቅሰዋል ማለት ነው' ሲል አሰበ::

እሱም ሁኔታውን በአይኑ ለመከታተል እንዲቻለው ከቁጥቋጦው ስር ተወሸቀ:: የሌብ ሣቢች ችኮላና መቁነጥነጥ

ሰብቻው ነው።

ልክ 6:00 ሰዓት ሲሆን፣ ዴግትያሬቭ የሀር ባርኔጣውን ደፍቶ በጥሩ አለባበስና ንቃት በተሞላው አካሄድ ሲጋራውን እያቦነነ ብቅ አለ።


«አሁን ጅላጅል፣ ወዘፍዛፋ ... ብለህ ከተሳለቅህበት ሰው ዋጋህን ታገኛለህ። ጠብቀኝ ብቻ» አለ ሊብ ሣቢች በሆሣቡ- እመሸገበት ጉድባ ውስጥ እንደተጉለተ።

ሌብ ሣቢች ከተወሸቀበት ሆኖ አንገቱን አስግጎ ሁኔታውን ሲከታተል። ወጣቱ ዲግቴያሬቭ ወደ እብነበረዷ ገንቦ እጁን እንደዋዛ ጣል አርጎ አንድ ፖስታ ይዞ ወጣ። ትከሻውን ከፍ ዝቅ አርጎ ፖስታውን በመገረም ተመለከተው። እያመነታ ከፈተው። እውስጡ ሁለት ባለ መቶ ብር ኖቶች!

ዴግትያሬቭ ለደቂቃዎች ተገትሮ የብር ኖቶቹን ከፈታተሸ በኋላ «ተመስገን» ብሎ ወደኪሱ ከተታቸው።

ምስኪኑ ሊብ ሣቢች የጣውንቱ የደስታ «ተመስገን» በጆሮው ሽው አለበት። የዛን ቀን ምሽት ሌብ ሣቢች እነጋዴው ዱሉኖቭ ሱቅ ትይዩ ቆሞ፣ እመልካች ጣቱን ቀስሮ፣ የስድብ ውርጅብኙን ሲያወርደው አመሸ።

«ቦቅቧቃ፣ ቡካታም፣ ልበ ቢስ፣ ቡከን? ዘረጥራጤ ...» እያለ።



# ሌባ ሳመሉ

እሸቱ ተፈራ

«ሌባ ሳመሉ ዳቦ ይልሳል» የሚለውን አባባል የስነ-ልቡና ጠበብት ክሌፕቶማኒያ ይሉታል፡፡ ይህም ለግለሰቡ ምንም ጠቀሜታ የሌለውን እቃ በመስረቅ የሚገኝ የመንፈስ ርካታ ነው፡፡ ድርጊቱ ግለሰቡ በሕፃንነት ዘመኑ ልቡናው የተመኘውን ነገር ሳያገኝ በመቅረቱ የተነሳ፣ ለዚያ ማካካሻ የሚፈፀም ተግባር ሲሆን፣ ሕመምተኛውም ትንሽ ትልቅ ሳይል ያገኘውን ነገር ሁሉ ነው የሚመነትፍ፡፡፡ ግለሰቡ በሀብት የከበረ ወይም በስልጣን ከፍ ያለ፣ አሊያም የሰከነ

ምሁር ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ይሰርቃል- ከእርሟ ቤሳ ምላሿ እስከ ወርቅ:: በዚያን ጊዜ የሚሰማው የመንፈስ ደስታ ወሰን የለውም:: ራሱን እንደታላቅ ጠቢብ አድርጎ ይቆጥራል:: ከተራው ሊባ የሚለየውም፣ የሰረቀውን እቃ አለመሸጡና ለኑሮው አስፈላጊ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን መስረቁ ላይ ነው::

ለአብነት ያህል የአንዲት የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ (ስነ-ልቡና) ምሁርን ድርጊት እንመልከት:: ታሪኳን ራሷ ትተርክልናለች::

ያለ ክፍያ ቁሳቁስ ማግኘትን ያህል በዓለም ላይ የሚያረካኝ ነገር የለም:: በየምሽቱ ፈጣሪዬን ከዚህ ልማድ እንዲገላግለኝ እለምነዋለሁ:: ሲነጋ ግን ሱቅ እገባና ባንኮኒ ተደግፌ ለመስረቅ አደባለሁ:: የሰረቅሁት እቃ ዋጋ 50 ብር ሲሞላ፣ ስርቆቱን አቆማለሁ በማለት ለራሴ ቃል ገብቻለሁ::

ዛሬ ጥቅምት 2 ነው:: በደስታ ሰክሬያለሁ:: ያስደሰተኝም ጉዳይ 25 ብር የሚያወጣ ቁሳቁስ መስረቄ ነው:: አንዳንዶቹ እቃዎች ዋጋ ሲኖራቸው፣ ቀሪዎቹ ግን በነፃቢታደሉም እንኳ ወሳጅ አያገኙም:: ቁምነገሩ ግን ሰው ሳያይህ መመንተፍ መቻሉ ላይ ነው! ዛሬ ከሰረቅኋቸው እቃዎች አንዱ ከመዳብ የተሰራ ቀለበት ነው:: ቤቴ ግን ከወርቅ የተሰሩ ቀለበቶች ሞልተውኛል:: ሌላው የሰረቅሁት እቃ ደግሞ ካውያ ያቃጠለው ውስጥ ልብስ ነው::

ብዙ ጊዜ የምሰርቃቸው ዕቃዎች ግን በጣም ጥቃቅን የሆኑና በመዳፌ ውስጥ፣ በሳንቲም መያዣ ቦርሳ ወይም በመሐረቤ ውስጥ ሊደበቁ የሚችሉትን ቁሳቁሶች ነው::

ሆኖም ዛሬ አንድ ፒጃማ ከነፓኮው መስረቅ ችያለሁ። ከሁለት ወር በፊት ሙታንቲ መስረቅ አስፈርቶኝ መተዌ የቆጨኝ። የልምድ ማነስ ባይሆን ኖሮ ጉዳዩ በጣም ቀላል ኖሯል ለካ!

ደወሉ ተደወለ፤ ክፍል ልገባ ነው። የማስተምረው ስለልማድ ነው። በቦርሳዬ ውስጥ የሰረቅኋቸው ቁሳቁሶች ግጥም ብለዋል። እያስተማርሁ ሳለሁ ህሊናዬ 'አንች ሞሽላቃ ሌባ!' ይለኝ ነበር። ጥርሴን ነክሼ እንደምንም ክፍለ ጊዜውን ጨረስኩ።

«እቤቴ ገብቼ የሰረቅኳቸውን እቃዎች ስመለከት በትምህርት ቤት ያለኝ ትልቅ ስምና የበሸቀጠው የግል ሕይወቴ ድቅን ስላሉብኝ ሰዲቃ መታኝ። ተማሪዎቼ 'መልክሽ የሞናሊዛ፣ አለባበስሽም ሽክ ያለ፣ የስክንሽ ምሁር ነሽ' ሲሉኝ 'ዋ ሞላጫ ሌባ መሆኔን ብታውቁ ኖሮ ...' እል ነበር በሆዴ።

ጥቅምት 4፤ ሀምሳ ብር የሚያወጣ ቁሳቁስ እንደሰረቅሁ ይህን ተግባሬን እርግፍ አድርጌ እተወዋለሁ ያልኩት ሴትዮ አሁን ጣራውን ወደ 100 ብር ከፍ አደረግሁት። የምሰርቃቸውን እቃዎች ዋጋ ሁልጊዜ እመዘግባለሁ። «መዝገቡ ሽልቀቃ» የተሰኘውን ይህን ፋይሌን ሳየውም የለበጣ ሳቅ እስቃለሁ።

ጥቅምት 9፤ ለአንድ ሳምንት ከኮሌጁ ግቢ አልወጣሁም። ፍላጎቴን ለመግታት ስጣጣር ነው የሰነበትኩት። ዛሬ ግን ተረትቻለሁ። ከተማ የሚያስኬደኝ አንዳችም ምክንያት የለም። ግን እሔዳለሁ። ባንኮኒ ላይ ማድባቱ፣ ጊዜ ማባከኑ፣ መሸማቀቁ፣ ቅራቅንቦ መስረቁ ያሰለቻል። ቢሆንም ውልፍቱን ማርካቱ ደግሞ ያስደስታል። ስለዚህ ሄጄ አደባለሁ።

ኅዳር 11፤ ዛሬ በቀላሉ የሚወሰድ እቃ አግኝቻለሁ። መውሰድ እንጂ መስረቅ ማለቱን አልሻም። ዛሬ የወሰድሁት

የዘፈን ሽክላ ነው። እቤቱ ግን ለልጅ ልጅ የሚተርፉ ሽክላዎች ሞልተውኛል። ዛሬ የመነተፋነት እቃ ዋጋ የ100 ብር ጣሪያዬን አሳልፎኛል። ስለዚህም የገንዘቡን ጣሪያ ከፍ ማድረግ ሊኖርብኝ ነው።

ዛሬ እለተ አኩቴት (የምስጋና ቀን) ነው። መደብሮች በሙሉ ተዘግተዋል። ደስ አለኝ። በዓል ሆኖ ሱቆች ካልተዘጉ ለስርቆት መስማራቴ የማይቀር ነበርና። ስራ በዝቶ መፈናፈኛ ሳጣም የስርቆቱ ነገር ይረሳል። ስሞኑም የፈተና ወቅት በመሆኑ ነበር እንግዲህ ለሁለት ሳምንታት ከቤቴ ሳልወጣ መሰንበቴ።

ኅዳር 30፤ ዛሬ በጧት ተነስቼ ከተማ ወረድሁ። የተለመደ ሙጭለፋዬን ለማከናወን በየመደብሩ ስዞር ስለዋልኩኝ ደካክሜያለሁ። በጣም ነው የደከመኝ። እንዲያውም ታምሜያለሁ መሰል። ዶክተሬ የትምህርት ቤት ስራ ስለበዛብሽ ነው የታመምሽው ባይ ነው። ነገሩ ግን ወዲህ ነው። ቀኑን ሙሉ ስዞር ውዬ ለመስረቅ ባለመቻሌ ስለተበሳጨሁ ነው ለበሽታ የተዳረግሁት።

ታህሳስ 3፤ ዛሬ ከተማ መውጣት አምሮኛል። ብቻዬን ለመሄድ ግን አልፈለግሁም። ብቻዬን ከሆንኩ 'ስረቂ ስረቂ' የሚለው አመሌ ይነሳብኛል። ከሰው ጋር ከሆንኩ ግን አልሰርቅም። ስለዚህ አንዲቷን መምህርት አብራኝ እንድትሄድ ጠየቅኋት። ፈቃደኛ ነበረች። ሆኖም ሱቅ ስንገባ አላስችል ስላለኝ በንንቴ ሸፍኜ የሚያማምሩ ብዮችን ሰረቅሁ። ለምን ይህን ለውርደት የሚዳርግ ነገር እንደምሰራ አይገባኝም። በወር የማገኘው 6250 ብር ደሞዝ አንቀባሮ ነው የሚያኖረኝ። ትርኪ ምርኪ ስሰርቅ ከተያዝኩ ግን በራሴም ሆነ በዩኒቨርሲቲው ላይ ታላቅ ውርደት ነው

የምፈጥር፡፡ ያም ሆኖ ግን ላለመስረቅ ብታገልም አልቻልኩም፡፡ ራሴን ተወዳዳሪ እንደማይገኝለት ድንቅ ሌባ ስለምቆጥር ተራውን ሌባ ከመጠን በላይ ነው የምጠየፈው፡፡

ታህሳስ 5፤ ዛሬ አንድ ሱቅ ገብቼ የምታምር የሐር ስካርቭ መነተፍኩ፡፡ ለነገሩማ ቤቴ ሁለት ግሩም ስካርፎች አሉኝ፡፡ ሻጮቹ በስራ መጠመዳቸውን ሳይ ወደ መደርደሪያው አቀናሁ፡፡ አንድ ሽማች አጠገቤ አለ፡፡ እቃ የሚመርጥ ይመስላል፡፡ የወረቀት መያዥዬን ጣል አደረግሁና ስካርፉን እጄ መሀል አስገባሁ፡፡ ከዚያም ወደ መውጫው በር መጓዝ ጀመርኩ፡፡ አጠገቤ የነበረው ሽማች ተከትሎኛል፡፡ ከመደብሩ ልወጣ ስል የአንድ ሰው መዳፍ ትከሻዬ ላይ አረፈ፡፡ 'ይቅርታ እመቤቴ፣ አንድ ነገር የወሰድሽ መስሎኛል' አለኝ፡፡ ለካስ ሽማች የመሰለኝ የመደብሩ ተቆጣጣሪ ኖሯል፡፡ 'ወደ ቢሮ ቅደሚ' ሲለኝ 'ንጹህ ስለሆንኩ አታስቸግሩኝ' በማለት አፈጠጥኩ፡፡ እጄን ጠምዝዞ ወደ ፊት ወሰደኝ፡፡ አንዱ ጉረኛ ቢሮው ውስጥ ጉብ ብሏል፡፡

በሐሰት መወንጀሌን ለማስረዳት ስሞክር 'ቅጥፈትሽን አቁሚ' ሲል አምባረቀብኝ፡፡ ተቆጣጣሪው ኪሴን ቦርሳዬንና የወረቀት መያገዬን በረበረ፡፡ ከሰዓት በኋላ የሰረቅኋቸው እቃዎች በሙሉ ተጉለጉሉ፡፡ በገንዘቤ የገዛኋቸው ናቸው በማለት ድርቅ አልኩ፡፡ ደረሰኝ አሳዩ ሲሉኝ አመዴ ቡን አለ፡፡

በመጀመሪያ ስምና አድራሻዬን ላለመንገር ሞከርሁ፡፡ በኋላ ግን እስር ቤት እንደምላክና በፖሊስም እንደምመረመር ሲገልፅልኝ አድራሻዬን ተናገርኩ፡፡ ምሁር ወይዘሮ፤ አለ ሰውዬው፡፡ ቦርሳዬ ውስጥ የባንክ ደብተሬን አገኙት፡፡ በርካታ ገንዘብ እንዳለኝ ያሳያል፡፡ «ይህ ሁሉ ገንዘብ እያለሽ ነው፣ እንዲህ ዓይነቱ ቅሌት ውስጥ የምትዘፈቂው?» ሲል

አፈጠጡብኝ፡፡ ከዚያም ስርቆት መፈፀሜን የሚያረጋግጥ ሰነድ አስፈረመኝ፡፡ ላብ አሰመጠኝ፡፡ ቀጥሎ ምን እንደሚያደርገኝ ስላላወቅሁ ተጨነቅሁ፡፡ 'በይ የእቃውን ዋጋ ክፈይ' ሲለኝ ትልቅ እፎይታ ተሰማኝ፡፡ ቁሳቁሶቹ ላይጠቅሙኝ ገንዘቤን ከሰከስኩ፡፡

እንደተሸማቀቅሁ ከመደብሩ ወጥቼ ወደፊት ገሰገስኩ፡፡ የተገረፍሁ ያህል ቀጠቀጠኝ፡፡ ወንጀሌ እሌብነቴ ማረጋገጫ ወረቀት ላይ ሰፍሮ በስራ አስኪያጁ ቢሮ ተቀምጧል፡፡ እቤቴ እንደገባሁ በእለቱ የሰረቅኳቸውን ቁሳቁሶች ሽንት ቤት ውስጥ ወረወርኳቸው፡፡ በስርቆት የተገኙ የሚያሸማቅቁ እቃዎች ናቸውና አስጠሉኝ፡፡

አሁንም ደቅቄያለሁ፡፡ የፈፀምኩት ወንጀል ይቆጠቁጠኛል፡፡ መንፈሴ ተረብሿል፡፡ እንቅልፍ በዓይኔ አልዞር ስላለ የእንቅልፍ ኪኒን ዋጥሁ፡፡ ዶክተሬ ካዘዘልኝ በላይ ነበር የዋጥሁት፡፡

ታህሳስ 6፤ አንድ ሽምገል ያለ ዶክተር ፊልጌ ስለ ሁኔታዬ አነጋገርኩት፡፡ ምክር ቢጤ ሰጥቶ ብዙ ገንዘብ አስከፈለኝ፡፡ ታህሳስ 5፤ ስርቆት ያካሄድኩት በአእምሮ ሕመም የተነሳ መሆኑንም የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ሰጠኝ፡፡ ያን ይገኙ ትላንት ሰነድ ወዳስፈረመኝ ስራ አስኪያጅ ገሰገስኩ፡፡ ወረቀቱን ሲያይ አዘነልኝ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰረቅሁ መሰለው፡፡ ልማደኛ መንታፊ መሆኔን አላወቀም፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ሌባ መሆኔን ማመን አለብኝ፤ ስንት ጊዜ ራሴን አታልላለሁ፤ «ከዚህ አጸያፊ ተግባር ራሴን መቆጠብ አለብኝ» የሚል ሐሳብ ያብሰለስለኝ ገባ፡፡ ለአንድ ሳምንት ያህል አንዳችም ነገር አልሰረቅሁም፡፡

ታህሳስ 17፤ ዝንጥ ብዬ ወደ መደብሩ ስራ አስኪያጅ በመሄድ ያስፈረመኝን ስነድ ለማስቀደድ ፈለግሁ:: ስራ አስኪያጁም በርግጥ በዚያን እለት ታማ ነበር የሚል እምነት ስላደረበት በፈገግታ ተቀበለኝ:: እኔም ድርጊቴ ስላሳፈረኝ ስራዬን በፈቃዴ ለመልቀቅና አገር ጥዬ ለመጥፋት ማሰቤን አጫወትኩት:: «ስለ ስርቆትሽ ማንም የሚያውቅ ስለማይኖር አትጨነቂ» ሲል አበረታታኝ:: ወረቀቱን አውጥቶም እፊቴ በጫጭቆ ጣለው:: ብጭቅጫቂውን ለቃቅሜ እኪሴ ከተትሁት:: ከተቀመጥኩበት ስነሳ ብርክ ያዘኝ:: ስራ አስኪያጁ ደገፍ አደረገኝ:: እቤቴ ስገባ ተንበርክኬ አምላኬን አመሰገንኩ::

ታህሳስ 24፤ ሌብነቴን እርግፍ አድርጌ የተውኩ ስለመሰለኝ ተደስቼ ነበር:: ዳሩ ግን የመስረቅ አመሌ ሳይታሰብ ተነሳብኝ:: ዛሬ የሙዚቃ ሸክላ ልገዛ ሱቅ ገብቼ በርከት ያሉ የሙዚቃ ሸክላዎችን ሰርቄ ወጣሁ:: በሩ አጠገብ የነበረው ባለሱቅ 'እሜቴ የፈለጉትን ሁሉ አገኙ?' ሲል ጠየቀኝ?:: አስተያየቱ ግን አላማረኝም:: ፈገግታዬን ግቼው ፈጠን ብዬ ወጣሁ:: ፍርሀት ወረረኝ::

ጥር 8፤ ከገና እረፍት በኋላ ገበያ አልወጣሁም- የመስረቅ በሽታዬ እንዳይነሳብኝ በመስጋት:: ዛሬ ግን የሙዚቃ መምህሩ ስለታመመ የሙዚቃ ሸክላዎችን እንድገዛለት ኮሌጁ ጠየቀኝ:: ለኮሌጁ የሚሆነውን ሸክላ ከገዛሁ በኋላ ግን «ስረቂ» የሚለው አባዜዬ ተነሳብኝ:: ስለዚህም በርከት ያሉ ሸክላዎችን መነተፍኩ:: ልወጣ ስል የሽያጭ ሰራተኛው ብዙ ሸክላዎች ይዘሻል እሳ አለኝ:: በስሕተት የሰራሁት በማስመሰል ያልተከፈለባቸውን ሸክላዎች ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩ:: ሰውዬው ግን አልተታለለም:: 'በእውነቱ ትላንትና የፈፀምሽውን በሙሉ ተመልክቻለሁ:: ሰው ፊት አላዋርድሽም ብዬ ነው ችላ ያልኩሽ' አለኝ:: ከመደብሩ በርሬ ወጣሁ::

ጥር 10፤ ሁለት ቀናት አለፉ:: የሽክላ መደብሩ ለመስሪያ ቤቱ ደብዳቤ አልጻፈም:: ተመስገን አልኩ:: ሲባንቴን ለማጋለጥ ለጋዜጦች ወሬውን እስተላልፈውስ እንደሆነ የሚል ጭንቀት አደረብኝ:: ስለዚህም የእለቱን ጋዜጦች በጥንቃቄ አነበብኩ:: አንቀጠቀጠኝ:: እህል ውሀ መቅመስ ተሳነኝ:: ጥርጣሬና ፍርሀት በልቶ ጨረሰኝ:: ከሰዓት በኋላ የደንብ ልብስ የለበሱ ፖሊሶች ትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ አየሁ:: እንጠልጥለው ሊወስዱኝ የመጡ ስለመሰለኝ ፍርሀት አብረከረከኝ:: ደግነቱ ፖሊሶች አልነበሩም፤የእሳት አደጋ ሰራተኞች እንጂ:: ጉንበስ ብዬ መሬቱን ሳምኩ:: ፈጣሪዬን ከዚህ መጥፎ ልምድ እንዲገላግለኝም ተሳልኩ::

ጥር 11፤ ህሊናዬ አላሳርፍሽ አለኝ:: ስለዚህም ለሙዚቃ ቤቱ የሽክላዎቹን ዋጋ በፖስታ ቤት ላኩለት:: ከሌሎች ቦታዎች ለሰረቅኋቸው እቃዎችም ክፍያዎችን በፖስታ ቤት በኩል ሰደድሁ:: ዛሬ የሰላም እንቅልፍ እንደሚወስደኝ ተስፋ አደርጋለሁ::


ጥር 12፤ ዛሬ ደግሞ የሰረቅኋቸውን እቃዎች ዝርዝር የያዘውን መዝገብ እሳት ለቀቅሁበት:: ያለኝን ክብር ከምስርቃቸው ቁሳቁሶች ጋር ሳወዳድር ሀፍረት ያሸማቅቀኛል:: 'ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል' የሚለውን አባባል አጥብቄ እያሰላሰልሁት ነው:: ከዛሬ ጀምሮ በምንተፋ ተግባር ላይ ላልሰማራም ማልሁ::ሁለት ጊዜ ስሰርቅ ተይዤያለሁ:: ሶስተኛ ጊዜ ከተያዝኩ ዘብጥያ መውረዱ የማይቀር ነው:: ከእስራቱ የውርደቱ! ምንተፋዬን ከቀጠልኩም ጤንነቴ መቃወሱ አይቀርም:: አላፊ አግዳሚው 'ሽልቃቂቷ መጣች' በማለት መግቢያ መውጫ እንደሚያሳጣኝ የታወቀ ነው:: ኃዘኑ ለልቤ ተሰማኝ:: እንባዬ ኮለል ብሎ ወረደ::

አሁን ስርቆቴን አቁሜያለሁ:: እንቅልፍ በደንብ ይወስደኛል:: የእንቅልፍ ኪኒን መቃሜንም አቁሜያለሁ:: ስርቆት ካቆምኩ እነሆ ድፍን አንድ ዓመት ሞላኝ:: ፀፀቱ ግን አሁንም እያንገበገበኝ ነው:: ሞላጫ ሌባ ነበርኩ:: የፈለግሁትን ሽፋን ብሰጠውም ሀቁ ግን ሌባ መሆኔ ነበር:: 'ርግማን' ነው:: ልክፍት ነው::»

***

ይህን መሰሉ በሽታ የተጠናወታቸው ሰዎች በሀገራችንም ሞልተዋል:: ሲጋራ የማያጨሱ ሰዎች በብዙ መቶ የሚቆጠሩ መለኮሻዎችን (ላይተሮችን) ሰርቀው ያከማቻሉ:: አንድ መስመር የማይጽፉ አመለኞችም ብዙ የጭቃ ቀለምና ብእሮች ከጓደኞቻቸውና ከየቢሮው እየመነተፉ ይቀብራሉ:: ለቁጥር የሚታክቱ መሐረቦች ያከማቻሉ:: ጥቅም የማይሰጧቸውን ቁልፎችና የቁልፍ መያዣዎች ያግበሰብሳሉ:: ሚስት ሳይኖራቸው የፀጉር መያዣ ይሞጨልፋሉ:: የኃዘን ቤት አንኩላ ሳይቀር ያጨልጋሉ:: ወዘተ...

እነዚህ ሰዎች በክሌፕቶማኒያ በሽታ የተለከፉ ናቸው:: እርዳታ ያስፈልጋቸዋል:: ይህን መሳይ አመል ያለባቸው ሰዎች የስነ አእምሮ ሐኪም እንዲያነጋግሩ መገፋፋት ይገባናል:: የሚሳቅ ባቸው ሳይሆኑ የሚታዘንላቸው ናቸው:: አመሉ ያለባችሁም የስነ-ልቡናና የስነ- አእምሮ ባለሙያ አማክሩ:: አለበለዚያ መዋረድ ይመጣል::



# ምኞት



# የሎተሪው ቲኬት

## አንቶን ቼኾቭ
## (ትርጉም) ቴዎድሮስ ሙላቱ

በየአመቱ በሚያገኘው ደህና ገቢ ከቤተሰቡ ጋር ተደላድሎ የሚኖረውና የመካከለኛው መደብ አባል የሆነው ኢቫን ዲሚትሪች፤ ከእራት በኋላ ሶፋው ላይ ተቀምጦ ጋዜጣ ማንበቡን ተያያዘው:: ይህን ያየች ሚስቱ እራት የተበላበትን ጠረጴዛ እየወላወለች «አይ የኔ ነገር... የዛሬውን ጋዜጣ ማየቱን እርስት አላደርገው መሰለህ? እስቲ የሎተሪው እጣ ወጥቶ እንደሆን ተመልከተው::» አለችው::

«ሎተሪው ወጥቷል ግን ያንቺ ትኬት ጊዜው አላለፈም?» አለ ኢቫን ዲሚትሪች።

«አላለፈም። የሚወጣው ማክሰኞ እንደሆነ አውቃለሁ።»

«ቁጥሩ ስንት ነበር?»

«ዋናው ቁጥር 9499 ሲሆን መለያው 26 ነው።»

«9499 እና 26 ... እንዬዋ» አለ ኢቫን ዲሚትሪች፣ በመሰረቱ ሎተሪ ለሚያመጣው እድል የተሻለ ሕይወት «እመሰርታለሁ» ወይም «ያልፍልኛል» ብሎ አያምንም። ትኬቱንም አይገዛም። ሚስቱ እንደምትገዛ ቢያውቅም ሎተሪ በሚወጣ ጊዜ እንኳን እንዲች ብሎ ዝርዝሩን መመልከት አይወድም። አሁን ግን ጋዜጣው አይኑ ስር ስለሆነ፣ ሚስቱ ስለጠየቀችውና ምንም ማድረግ ስለማይችል፤ አሸናፊዎቹ የሎተሪ ቁጥሮች ቁልቁል ከተደረደሩበት አምድ ባለቤቱ የነገረችውን ቁጥር ለመቃኘት ሌባ ጣቱን ቀስሮ ባይኑ በመከተል ወደ ታች ወረደ። ከመጀመሪያው ተርታ ብዙም ሳይርቅ ቀልድ እንጂ እውነት በማይመስል ዓይኑ በቁጥር 9499 ተጠለፈ። ዓይኑን ማመን አስቸገረው። ያልጠበቀው በመሆኑም ደነገጠ። የሎተሪውን ቁጥር እስከመጨረሻው አይቶ አልጨረሰም። 9499 ወከክ ስላደረገው ጋዜጣውን ወደ ጉልበቱ ለቀቀው፤ ቀዝቃዛ ውሀ የተቸለሰበት መሰለው። ቅዝቃዜ የእምብርቱን ጫፍ ተሰማው። መናገር የለም። መተንፈስ ብቻ ...! ምን አይነት አስቸጋሪ፣ አስጨናቂና ጣፋጭ ነገር ነው ...?

«ማሻ ደስታውን እንዴት ትችይዋለሽ? ቁጥር 9499 ወጥቷል» አለ ኢቫን ዲሜትሪች ደስታ ባደረቀው ድምፅ።

ማሻ ክው አለች። ዓይኖቿን አፍጥጣ ተመለከተችው። የሚቀልድባት መሰላት። በአድናቆትና በደስታ መመስጡን

የሚመስክረው ፊቱ እንደማይቀልድ አረጋገጠላት፡፡ እሷም ፊቷ ተሰጠ፡፡ ደስታው አገረጣት፣ ያጣጠፈችውን የጠረጴዛ ጨርቅ መወርወሯና በደስታ ጭምር መጮኋ አንድ ነበር፡፡ «9499!» አለችው፡፡

«እንዴታ! ይሄውልሽ»

«የቲኬቱስ ቁጥር? 26 ...!»

«አው! ለካስ እሱም አለ? ምናለፋሽ ... እሱም አለ፡፡ ግን ... እኔ የምልሽ ... የሆነው ሆኖ ...» እያለ ኢቫን ዲሚትሪች የሚብለጨለጭ እቃ እንዳሳዩት ሕፃን፣ ስሜት የራቀው ፈገግታ ለሚስቱ ለማሻ አሳያት፡፡ እሷም በደስታ ተፍለቀለቀች፡፡ የምታየው ቁጥር እርሱን እንዳረካው ሁሉ እርሷንም ፍንድቅድቅ ስላደረጋት፣ የቲኬቱን መለያ ቁጥር ማየቱ አስፈላጊነት እስከዚህም ሆነ፡፡ መቸም ቢሆን ሊሆን በሚችል ነገር መፈንደቅን ቀርቶ መስከርንም የመሰለ ነገር የለም፡፡

«ዋናው ቁጥር የራሳችን ነው፡፡» አለ ኢቫን ዲሚትሪች፡- ከረዥም ፀጥታ በኋላ፡፡ «ለመሆኑ ለማሸነፉ ሰፊ እድል አለን፡፡ በርግጥ እድል! ... ቀሪው ቁጥርም ቢሆን ይኖራል፡፡ አትቸኩይ»

«ደህና በደምብ እየው»

«ትንሽ ታገሽኝ፡፡ .. ቁጥሩ የወጣው ከመጀመሪያው መስመር ቀጥሎ ሁለተኛው ላይነው፡፡ ስለዚህም ስጦታው ሰባ አምስት ሺ ብር መሆኑ ነው፡፡ ፓ! ይሄስ ገንዘብ አይደለም፣ ሀይል ነው፣ ካፒታል!» አለ ኢቫን ዲሚትሪች፡፡

ባልና ሚስቱ በዝምታ ተውጠው ቀሩ፡፡ በመሀከላቸው ድምፅ የለም፡፡ ብቻ ውስጡን በደስታ ይፍነከነካሉ፣ ከላይ

ይስቃሉ፤ ድምፅ የሌለው ሳቅ። ለማሸነፍ ያላቸው እድል በሩን ከፍቷል። ሁለቱም ቢሆኑ ይህን ያህል ገንዘብ ምኔም ቢሆን ይደርሰናል ብለውም ሆነ አስበው አያውቁም። አሁንም ቢሆን ሰባ አምስት ሺ. ብርን ያህል ገንዘብ ቢመጣ ምን እንደሚያደረጉበት፣ ምን እንደሚገዙበትና ወዴት እንደሚሄዱበት አላሰቡም። በሀሳባቸው የሚመላለሰው 9499 እና 75,000 የሚለው አሐዝን ብቻ ነው። በምናባቸው ርቀው በመሄድ የየራሳቸውን የሀሳብ ስእል መመልከትም ገና አልጀመሩም።

ኢቫን ዲሚትሪች ጋዜጣውን ይዞ ካንዱ የግድግዳው ማእዘን ወደ ሌላው ሲንጐራደድና በመጀመሪያ ደረጃ ደስታው ሲናውዝ ከቆየ በኋላ ቀስ በቀስ ስለ ወደፊቱ ማሰብና ማሰላሰል ያዘ። «ካሸነፍን ኮ» አለ ኢቫን ዲሚትሪች። «... አዲስ ህይወት! ከፍተኛ ለውጥ ነው። ግን ትኬቱ ያንቺ ሆነ እንጂ የኔ ቢሆን ኖሮ ምን ነበር መሰለሽ የማደርገው? በመጀመሪያ ደረጃ ሀያ አምስቱን ሺ. እርስት ገዝቼ ቋሚ ንብረት ላይ አውለዋለሁ። አስር ሺውን ደግሞ ላስቸኳይ ወጪ ማለትም ላንዳንድ የቤት እቃ ግዥ ... ለመንጓጓዝ ... ለእዳ ክፍያና ለመሳሰለው ካደርግሁት በኋላ ቀሪውን አርባ ሺ. ብር ባንክ አስቀምጬ ወለድ እልጥ ነበር» ሲል ከፈገግታ ጋር «እርስት? ... እሱን እውነት ብለሃል» አለች ባለቤቱ፤ እጅዋን ጭኗ ላይ ጣል አድርጋ በመቀመጫዋ ጫፍ ሶፋው ጠርዝ ላይ ቂጽ ብላ እንደ ተቀመጠች።

ኢቫን ዲሚትሪች ቀጠለ። «እርስቱን ቱላ ወይም ኦርዮል ክፍለ ሀገር ሄዶ መግዛት ... ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ በጋውን የምናሳልፍበት ቪላ እንደማያስፈልገን ማወቅ ይገባል። በተፈጥሮ ልምላሜ መደሰት ይቻላል። እርስቱ ግን ሁልጊዜ ገንዘብ የሚያስገኝ ቋሚ የገቢ ምንጭ ነው።»

ካለ በኋላ እጅግ ማራኪ የሆኑ ተድላና ደስታን የሚያበስሩ ስእሎች በአይነ ሕሊናው እየተፈራረቁ ይታዩት ጀመር:: የሚታየው ስእል አንዱ ከሌላው ይበልጣል:: ከፊተኛው ይልቅ የሚቀጥለው ኪናዊ ዜማና ጣእም አለው:: በምናብ በሚታየው በእያንዳንዱ ስእልና ትእይንት እየረካ የቅድሙ ቅዝቃዜ እየለቀቀው እንዲያውም እየሞቀው መጣ:: - ሞቀው እስኪያልበው::

በበጋው ወራት ሙቀት ያስቸግራል:: እንደበረዶ የቀዘቀዘ ሾርባ ያስፈልጋል:: ያንን ከወሰደ በኋላ ከምንጨ ዳር ካለው ለምለም ሳር ላይ ጋለል ብሎ ይዝናናል:: ሕፃናት ልጆቹም አረንጓዴው መስክ ላይ ይቦርቃሉ፤ ይጫወታሉ:: አንዱን ሲያነሱ ሌላውን ይጥላሉ:: ሁሉንም ማየት ያስደስታል:: ጊዜው ግን ሞቃት ነው:: ... የሚያሳስበውና የሚያስጨንቀው ነገር የለም:: አሁንማ ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ፣ ነው:: እንኳን ዛሬ ነገ ተነገወዲያም ወደ ቢሮ ላይሄድ ይችላል:: ጋደም ካለበት ተነስቶ እየተጀነነ በእርሻው አጠገብ ወዳለው ክምር ይሄዳል ወይም መረባቸውን ወደወንዙ እየወረወሩ አሳ የሚያሰግሩ ገበሬዎችን ይመለከታል:: በክራት ...

ፀሐይቱ ወደ ምእራብ አድማስ ስታዘቀዝቅ፣ ጌታው ኢቫን ዲሜትሪች ልብሱን ሁሉ ያወላልቅና በውስጥ ሱሪ ብቻ እንደሆነ ፎጣውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ባንድ እጁ ሳሙና ይዞ በሌላው እጁ ደረቱን እያፍተለተለ ይሄድና ገላውን ለመታጠብ ወደ ውሃው ... ወደ ወንዙ ... ይገባል:: ውሀው ውስጥ እያለ አካላቱን በሳሙና ይመታል:: ... በእጁ እየጨለፈ ወደ ሰውነቱ የሚረጨው ውሀ አረፋውን ይዞ ይሄዳል:: ... እንዲ የውሀውን አካሄድ ሌላም ጊዜ ዳርቻዎቹን ይቃኛል:: ትንንሽ ዓሳዎች ብቅ ጥልቅ እያሉ

ሲራወጡ ... የጅረቱ ዳር አረንጓዴ ተክሎች እናታቸውን እያነቃነቁ ሲወዛወዙ ሲያይ፣ እንደርሱ ተደስተው በዳንስ የሚያጅቡት ይመስለዋል:: ብቻውን ፈገግ ይላል:: መንፈሱ ይታደሳል:: ገላውን ከታጠበ በኋላ የሚጐነጨው አርጐና ቅባት አክል የተደረገበት ሻይ ተቀምጦ ይጠብቀዋል:: ሕይወቱ በእርካታ ትመላለች::

አንዳንዴም አመሻሹ ላይ ካንዳንድ ጐረቤቶች ጋር ሽርሽር ይወጣል:: - ደስታን ለመጋራት ...

ኢቫን ዲሚትሪች ይህን ከመሰለው አስደሳች ምናባዊ ዓለም አልተመለሰም ነበር:: በዓይነ - ሕሊናው የሚፈራረቀውንም ትእይንት አላዳረሰም:: ሚስቱም በበኩሏ ድምጿን አጥፍታ የራሷን ህልም ይዛለች:: እሷም ብትሆን ለምታልመው ሁሉ ከፍ ያለ የደስታ ስሜት ከደሟ ተቀላቅሎ በሰራ አከላቷ መሽከርከር ላይ እንዳለ ፊቷ ይመሰክራል:: ሁለቱም በየራሳቸው አስደሳች ሕልም ውስጥ እንዳሉ ነበር፤ አፏን ነጠቅ ያደረገው:: «እውነት ብለሃል፤ ርስት መግዛት ጥሩ ነው» አለች ማሻ::

ኢቫን ዲሚትሪች፣ ባለቤቱ ማሻ የተናገረችውን ከልብ አላደመጠም:: ከሚዋኝበት ጣፋጭ ሕይወት ከላበት የሀሳብ ውቅያኖስ በቀላሉ የሚወጣ ሰውም አልነበረም:: በቅዱስ ማርቲን በጋ ወራትና በመኸሩ ዝናም እንደዚሁም በቀዝቃዛው አየር ተመስጧል:: እንኳንስ የማሻን ድምፅ መድፍ ቢተኰስም አይሰማም:: - በሀሳብ ርቋል:: ነጉዷል:: በነዚያ ወራት ረጃጅም የእግር ጉዞዎችን በማድረግና በየአመሻሹ በመንሸራሸር አልተወሰነም:: - ሌላም ብዙ የሚታየው አለ::

በመኸሩ ወራት ብርድና ውርጭ ሲያስቸግረው፣ የአትክልትና ጮማ ሾርባ (ሙቀት እንዲሰጠው) ድርግም

የደርግና በቍጥቍጥ ሳይሆን በስፊው ...! በትልቅ ብርጭቆ ከመቀመጫ የሚያስነሳ ቮድካ ይከለብስበታል። ሰውነቱ ጋል፣ ደሙ ሞቅ ይላል። ቮድካው ከልቡ ካልደረሰም ምን ይቸግረዋል? ያሻውን አማርጦ ይጎነጫል። የራት ሰዓት ሲደርስ ሽታው ከሩቅ የሚጣራ ምግብ ከፊቱ ይቀርብለትና እንዲያስተናግደው ይጠይቀዋል። ጌታው ኢቫን ዲሚትሪችም ያቺን እንክት አድርጎ ሲያበቃ ቀበቶውን ፈትቶ እግሩን ይዘረጋና ሶፋው ላይ ፈስስ ነው። ከዚያ መጽሔት ብጤ አንስቶ ወደ ሰማይ እያየ ፊቱን በወረቀት ጋርዶ ጽሑፉን እያነበበ ይዝናናል። መጭው አዲስ ሕይወት ከዚህ የበለጠም ስሜትና ትርጉም ይሰጠዋል።

አስደሳቹ ወራት ሲያልፍ፡ አሰልቺው ወቅት ይከተላል። ከበጋው ቀጥሎ የሚወጣው ደመናማና ጭጋግማ የአየር ጠባይ ነው ። ጭጋጉ ምድሪቱን፣ ደመናው ሰማዩን ይከድናሉ። ሌት ተቀን ይዘንባል። ንፋሱ ከባድና ቅዝቃዜ አዘል ነው። ከቤት መውጣት አይቻልም። ሽርሽር የለመደ እግር ግድግዳ መሀል ይታሰራል። የውጭው ዓለም ቢናፍቅ እንኳ እንዲትን በመስኮት በኩል ወጣ ከማድረግ ሌላ እድል የለም። በመስኮት ማየት ብቻ ደግሞ አያረካውም። ተፈጥሮ ውበት ሲርቃት ሕይወትም ትሰለቻለች። በዚህን ጊዜ ወዴት ይኬዳል?

ኢቫን ዲሚትሪች፣ በዚህ አይነት ማሰላሰሉን ቆም አድርጎ ላንድ አፍታ ሚስቱቱን ተመለከታት። ሁሉም የሰከንዶች የአእምሮ ክንውን ነበር። «ስሚ ማሻ! አዲሱ ሕይወታችንን ስንመሰርትኮ፣ እንዳንዴም አየር መለወጥ ያስፈልጋል። ወደ ውጭ አገር መሄድም ይኖርብናል። ገባሽ?» ብሎ፤ በመኸሩ ወራት መጨረሻ ወደ ደቡብ ፈረንሳይ ... ወደ ኢጣሊያና ... ወደ ሕንድ አገር መሄድ እንዴት ጥሩ

እንደማይሆን ማሰብ ቀጠለ፡፡

«ያኔማ እኔም ወደ ውጪ አገር እሔዳለሁ፡፡ ግን ለምን ቁጥሩን በደንብ አታይውም? በሞቴ ... እየው እስቲ» አለችው ባለቤቱ፡፡

«ታገኘሽ» አለ ኢቫን ዲሚትሪች፤ እሷ የምትለውን መፈፀም ወይም የያዘውን ሀሳብ ማቋረጥ አልፈለገም ነበር፡፡ እሷም ወደ ውጭ አገር ለመሄድ የማሰቧ ነገር በጣም ከነከነው፡፡ «ምን ልትሰራ ትሔዳለች?» አለ፡፡ ብርሀን ወደ ተናኘባቸው ወደነዚያ የፈረንሳይና የኢጣሊያ ውብ ከተሞች ሚስቱን ይዞ መሄድ ደስታ እንደማያስገኝ ታየው፡፡ አዲስ ነገር ስለሌለበት፣ ሁሉቱም ስለሚያውቁት፣ ስለልጆች ጉዳይና ስለ አለፈ ሕይወት እያነሱ በየጉዳናው ማውራት መንፈስን ከማሰልቸት ሌላ የሚፈጥረው ነገር አይኖርም፡፡ ስለዚህ ለርሱ ብቻውን እንደመሄድ የሚያረካ አይገኝም፡፡ ሚስቱ ኰተቷን አክታ በባቡር ሲጓዙ ገና ብዙ ጣጣ ታመጣለች፡፡ «ባቡሩ አንገላታኝ፣ ራስ ምታት ለቀቀብኝ፣ ብዙ ገንዘብ አወጣሁ» እያለች ልትነጫነጭ ነው፡፡ በዚያ ላይ በጉዟቸው ፍጻሜ የፈላ ውሃ፣ ዳቦ፣ ቅቤ ሌላም ፍለጋ መሯሯጥ አለ፡፡ እራት ሲቀርብ የሆቴሉ ዋጋ ውድነት እስደንግጧት «አልበላም» እያለች ማስቸገሯም አይቀርም፡፡

በዓይኑ ገርመም አደረጋት፡፡ «የምትሔደው እኔኑ ለማስቸገር ነው» በሚል ስሜት ደግሞም .. እሷ የበላይነቱን እንደምትነጥቀው ታየው፡፡ «አዎ» አለ «የሎተሪው ቲኬት ገንዘቡም የራሷ ነው፡፡ ቢሆንም ምን ልታደረግ ትሄዳለች? እኔኑ ለመቆጣጠር ነው፡፡ መች አጣሁት? ካረፍኩበት ሆቴል ሌላ ውልፍት እንድል አታደርገኝም፡፡ ስንት ውቦች በሞሉባቸው ከተሞች ታስሬ ልቀመጥ ...? አይሆንም! የማይሆን ነገር ነው፡፡» አለ በሃሳቡ - ባለቤቱን ምንም

አልተናገረም። ብቻ አንድ ሃሳብ መጣበት።

በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አእምሮው በሚስቱ እያረጀች መሄድ ላይ አተኮረ። እንደ እምቡጥ ጽጌረዳ የሚያንጓጓ ውበቷ እየረገፈ፣ የመማረክ ሃይሏ እየደከመ መጥቷል። ውሎዋ ማእድቤት ነው። ጢት የተነሳች አዚያው ማጀቷ ውስጥ ስታንጐዳጉድ ይመሽላታል። ጠረኗም ጭስ ጭስ ማለት ጀምሯል። ሰውነቷ እየደከመ ነው። እንደከዋክብት ያበሩ የነበሩት አይኖቿም ዛሬ ማንንም አያስደንግጡም። እርሱ ግን እያደር ወጣት፣ እያደር አሸት፣ እያደር ልጅ ነው። ሰውነቱ እያሞላ፣ መልኩ እያማረ፣ ቁመናው እየተስተካከለ ይሄዳል። ቢፈልግ ከቆንጆዎች መሃል ቆንጆ መርጦ ልጃገረዷን በወግ በማእረግ፣ በሠርግና በሆታ ያገባል።

«በርግጥ ይህ ሁሉ ከንቱና አልባሌ ነገር ነው።» አለ በሃሳቡ ግን ... ወደ ውጭ አገር መሄድ ምን ያደርግላታል? እሺ ትሂድ፤ እኔም ልስማማ፣ ውጤቱ ምንድነው? እንደ እውነቱ ከሆነ ኔኘልስም ሆነ ክሊን ሁሉም ለርሷ አንድ ናቸው። ያም ሆነ ይህ እኔን መከተል አለባት። እኔም ብሆን የርሷ ጥገኛ መሆኔ ነው። ሳይታሰብ አዱኛ ስገደላት። ገንዘቡ የሷ ሆነ የምትቀመስ ግን አይመስለኝም። ልክ ገንዘቡ እጅዋ እንደገባ ስርቻ እንደምትቀረቅረው አውቃለሁ። ያኔ ፀባይ ማሳመር ሊኖርብኝ ነው። ኡድያ! ግን እዎ ... እንደምንም ባስወጣትም ሌላ ችግር መፍጠሩም አይቀርም። እርሷ ለራሷ ሺ በክንፉ ...»

ኢቫን ዲሚትሪች ባለቤቱ ያሏትን የዘመድ አዝማድ ብዛት ማስብ ገባ። ሕይወት ፊቷን ያዞረችባቸው እንግልቱ እኅቶቿ፣ ወንድሞቿ፣ እህቶቿ፣ እናቷ ሆኑ አባቷ

«የሎተሪ እጣ ደረሳቸው» ማለትን በሰሙ ጊዜ፣ ነገ ዛሬ ሳይሉ እየተስገበገቡ ይመጣሉ:: ግማሾቹ ልብሳቸውን እንኳ መቀየር ያልቻሉ፣ ወጣ ሲሉ የሚለብሱት የሌላቸው ናቸው:: አንዳንዶቹም የተቃጠለ ዘይት የተነከሩ በሚመስሉ ባዳደፉ ልብሳቸው ታጅለው ነው የሚሄዱት:: አመጣጣቸውም ለምን እንደሆነ ይታወቃል:: ያው ለልመናና ችግር አውርቶ፣ እርጥባን ለመጠየቅ ነው:: የምንበላው አጥተን ... ለበሽታ ተዳረግን ... አቅም ከድቶን ... በመጨረሻ ገንዘብ አምጡ ነዋ! ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? እነርሱ እንደሆኑ በቃኝና ተመስገን አያውቁ! ጥቂት ሲሰጧቸው ብዙ ይጠይቃሉ:: እስከናካቴው «የለም የተባሉ እንደሆነማ መዓተ - እርግማኑን ያወርዱታል:: ያማርራሉ:: ምሬት እጣ ፈንታቸው መሆኑን ረስተው፤ የሰው እጣ እንካፈል ይላሉ! መጥኔ! »


ኢቫን ዲሚትሪች በዚህ አልተወሰነም:: መለስ ብሎ የራሱንም ዘመዶች መልክ አስታወሰ::

የሚያምረው ሳይሆን ማስጠሎ ፊታቸው መጣበት:: የተጨማደደ ቆዳ... የተሰነጣጠቀ ተረከዝ... አቧራና ጭቃ ያጠመቀው ቅልጥም... «ፑ! ለካስ እንዲህ ዓይነቶች ኖረዋል» በማለት አሰበ:: ሚስቱንም አያት! ከሌሎች የተለየች አልሆነልህ አለችው:: ገንዘቡን ወስዳ ስትቀረቅር እየታየው «ጨቅ! » አላት፤ በልቡ::

በደንብ አያት፤ ባለቤቱን:: አሁን በፈገግታ አይደለም፤ የጥላቻ አይኑን ነው የተከለባት:: እሷም እየችው፤ ልክ እንደርሱ በቁጣና በጥላቻ አስተያየት:: እርሷም የራሷ የቀን ሕልም ነበራት:: የራሷ እቅድና የሕይወት ገጽታ! የባሏ እቅድና ሕልምም ምን እንደሆነ በሚገባ ለመረዳት አላዳገታትም:: የሎተሪው ቲኬት አሸናፊ በመሆን የተገኘውን ገንዘብ

በመጀመሪያ የሚዘርፉት ማ እንደሚሆን አውቃለች፡፡ አስተያየቷ ራሱ «በሌሎች ሰዎች ኪሣራ አስደሳች ሕይወት ማለም በጣም ጥሩ ነው፡፡ አይደለም እንዴ?» ነበር የሚለው፡፡

ባለቤቱም፤ አመለካከቷ ምን ምስጢር እንዳለው ወዲያውኑ ተረዳ፡፡ የልቡንም ሁሉ እንደነቃችበት ስለአወቀ ጥላቻው ይብሱን ገነነ፡፡ ደረቱ እስኪበተን እልህ ተናነቀው፡፡ ግን ትዝብትና ጥላቻ የሚንቦገቦግበት አይኗን ለመሸሽ ያህል ብቻ የጋዜጣውን አራተኛ ገጽ ገልበጥ አድርጎ ቁጥሩን በፍጥነት ተመለከተው፡፡ የሆነው ይሁንና መጨረሻው ምን ይሆን?» በሚል፡፡ ጉድ ፈላ!! የታተመውና የተነበበው የርሱን ሀሳብ አልተከተለም፡፡ አሸናፊው ቁጥር፣ ሴሪ 9499 ቁጥር 46 እንጂ 9499 ቁጥር 26 አይደለም፡፡



# ፊልም ቀራጭ



# ፍልቅልቂቱ ደራርቱ

**አታክልት ሀገገ**

ደራርቱ ቱሉ ዓለማቀፋዊ ውድድር የጀመረችው በ1981 ኖርዌይ ላይ ሲሆን ከዚያ ወዲህ ዝናዋ ከግብፅ እስከ ሞሪሽስ፤ ከቡልጋሪያ እስከ ስፓኝ ተናኝቷል። በኢንተርናሽናል ውድድሮች 13 የወርቅ ሜዳልያ አግኝታለች። የአያሌ የብርና የነሀስ ሜዳልያዎች ባለቤትም ናት። ደራርቱ የኦሊምፒክን የወርቅ ሜዳልያ በማግኘት የመጀመሪያይቱ ሴት አትሌታችን ናት። ይህች ሻምፒዮን ከባርሴሎና ድል በሁዋላ በሰጠችው መግለጫ «አበበ ቢቂላ በማራቶን ሩጫ

ለኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳልያ ያስገኘ የመጀመሪያው ወንድ አትሌት ነው። እኔ ደግሞ የመጀመሪያዋ ሴት አትሌት ነኝ» ብላለች፤ በዚህ ታላቅና ደማቅ ድል አገሯን አስጠርታለች። ሕዝቧን አኩርታለች። በተለይ ገና ከማጀት ላልወጡት የዖታ ጓደኞቿ፣ የጀግንነት አርማ የድል ተምሳሌት፣ የዕናት አርአያ ሆናለች።

«ለዚህ ታላቅ ድል እንድበቃ ከመጀመሪያው ኮትኩተው ያሳደጉኝ ባሻ በየነ አያና ናቸው። እሳቸው ከአርሲ ወደ አዲስ አበባ አምጥተው ባያወዳድሩኝ ኖሮ ለዚህ ታላቅ ድል አልበ ቃም ነበር» ትላለች ደራርቱ። በባርሴሎና ኦሊምፒክ 10ሺ ሜትሩን 3.06.02 በሆነ ጊዜ ነው የጨረሰችው። ይህም ለራሷ አዲስ ክብረወሰን ነው።

ጀግናዋ ደራርቱ አሁን የ21 ዓመት ወጣት ናት። በተደጋጋሚ ቢነበብም እንኳ ከቶ የማይሰለቸውን የባርሴሎና ድል ማግስት ቃለ ምልልስ ከነለዛው እነሆ!

«የኦሊምፒክ ወርቅ ሜዳሊያ በማግኘትሽ የተሰማሽን ደስታ እንዴት ብትገልጪው ነው አብዛኛው ሰው ሊረዳልሽ የሚችለው?»

«እኔንጃ። በጣም ነው ደስ ያለኝ። መግለፅ ያቅተኛል በቃ፤ ደስታ ነው።»

«ራስሽን ከአበበ ቢቂላ፣ ከማሞ ወልዴና ከምሩፅ ይፍጠር ጋር እንዴት ነው የምታነፃፅሪው?»

«እነሱን በታሪክ ነው የማውቃቸው። እነሱን የመሆን ምኞት ያደረብኝ በተለይ ስለምሩፅ ስሰማ ነው። ምሩፅ ዘዴኛና ፈጣን ሯጭ ነው ሲባል እሰማ ነበር። አሁንም የውጭ ጋዜጠኞች 'የምሩፅ ይፍጠርን ዘዴ ነው

የተማርሺው?' እያሉ ይጠይቁኛል::»

«ከመንግስት የተፈቀደልሽ ሽልማት በቂ ነው?»

«እዎ! አገሬ አቅሟ የፈቀደላትን አድርጋልኛለች:: ደስ ብሎኝ ነው ሁሉን ነገር የተቀበልኩት:: የተሰጠኝ ክብር ራሱ በገንዘብ የማይተመን ታላቅ ሀብት ነው::»

«ገንዘቡን ምን ልታደርጊበት አስበሻል?»

«ቤተሰቤን እረዳበታለሁ ብዬ ነው ያሰብኩት፤ እስካሁን ሌላ የተለየ ዕቅድ አላወጣሁም::»

«'ደራርቱ' ተብለሽ ስትጠሪ ነው ደስ የሚልሽ ወይስ 'ሻለቃ ደራርቱ?' »

«'ደራርቱ' ስባል ነው ደስ የሚለኝ::»

«ሹመቱን አልወደድሺውም ማለት ነው?»

«እንደዚያ ሳይሆን እፍራለሁ:: ሳቁ ይመጣብኛል::»

«'ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ ዘንድ ቀርበሽ በተሸለምሽበት ጊዜ 'ፕሬዚዳንቱ ምን አሉሽ?»

«ስለውድድሩ ሁኔታ ጠየቁኝ:: ከዚያም 'እኛ ምንጊዜም ከጐናችሁ ነን፤ እናንተ ብቻ በርቱ፤ ከዚህ የበለጠ ውጤት እንደምታመጡ እተማመናለሁ' አሉኝ:: ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራትም 'እንደድሮ አይደለም:: አይዟችሁ፤ ችግር ካለ በተቻለ አቅም ለመፍታት እንሞክራለን:: ለሚቀጥለው ኦሊምፒክ በደንብ ተዘጋጁ:: አራት ዓመት ማለት አራት ቀን ማለት ነው:: መበርታት ያስፈልጋል' አሉኝ:: ፕሬዚዳንት መለስ ጐን ቆሜ በነበረበት ጊዜም 'ፕሬዚዳንቱ 'እኚያ እናትሽ ናቸው? ለምን አትጠሪያቸውም?' ስላሉኝ እናቴንና አባቴን

ጠርቼ አስተዋውቄያችዋለሁ::»

«ከአቶ ሀሰን ሺፋ ተሰጠሽ የተባለው 'ልዩ ሽልማት' ምንድን ነው?»

«የባርሴሎና ኦሊምፒክ አርማ ያለው ሀብል ነው:: ስልሳ ግራም ወርቅ::»

«ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው ብለሽ ታምኚያለሽ?»

«ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው ብዬ መናገር ይከብደኛል:: ሆኖም እነሱ የማይችሉትን እኛ እንሰራለን፤ እኛ የማንችለውን እነሱ ይሰራሉ:: እኛ ሴቶች ትንሽ የሚቀረን ይመስለኛል::»

«ተፎካካሪዎችሽ በሙሉ ለምልክት ብቻ የምትሆን ቁራጣ ካናቴራ (ጃፖኒ) ለብሰው ሲወዳደሩ፣ አንቺ ግን በዚያ ወበቅ ከውስጥ ድፍን ካናቴራ ከላይ ደግሞ ሌላ ካናቴራ የደረብሽው ለምንድነው?»

«እምና ጃፓን ላይ ስወዳደር ጃፖኒ ብቻ ለብሼ ነበር:: ግን ውጋት ያዘኝና ስምንተኛ ወጣሁ:: አሁንም ያንኑ ፈርቼ ነው የደራረብኩት:: እዚህ ስንለማመድም ደርበን ነው:: ጃፖኒ አንለብስም::»

«'እንጀራ በወጥ እበላለሁ:: በሶም እየበጠበጥኩ እጠጣለሁ እንጂ የፈረንጅ ምግብ አልቀምስም' ብለሽ ነበር፤ ኢትዮጵያን ሄራልድ ላይ እንዳነበብኩት:: ስለማይስማማሽ ነው?»

«አልቀምስም ማለቴ እንኳን አይደለም:: ማንም ሰው የአገሩን ምግብ ነው የሚወደው:: ውጭ አገር ሄጄ ምግብ አልስማማም ካለኝ በሶዬን በጥብጬ እጠጣለሁ::»

«ስፖርተኛ በመሆንሽ የቤተሰብ ተፅዕኖ ይደረግብሽ እንደነበር በአንድ ወቅት ገልፀሻል። አሁንስ ምን ይሉሻል?»

«እንደ'ት መሰለህ፤ እድገቴ ገጠር ነው። ቤተሰቦቼም ገበሬዎች ናቸው። ስለዚህ 'ሴት እንዴት ቁምጣ ትለብሳለች። እንዴት የወንድ ስራ ትሰራለች' ይሉኝ ነበር። ይህ ካለማወቅ የመነጨ ነው። አሁን ግን ያበረታቱኛል። የሞራል ድጋፍም ይሰጡኛል። ደስ ይላቸዋል።»

«ጋዜጠኛ ፍቅሩ ኪዳኔ ባርሴሎና አግኝቶሽ ነበር?»

«አዎን፤ አግኝቶኛል። ባለፈው ዓመትም ቶክዮ ላይ ውጋት ይዞኝ ስምንተኛ ስወጣ እዚያው ነበር። ባርሴሎና ስገባ እንዳገኘኝ 'አሁንስ እንዴት ነሽ? ተሻለሽ ወይ' በማለት ጠይቆኝ ነበር። ጤንነቴ የተሟላ ስላልመሰለውም ፈርቶ ነበር። 'እንግሊዛዊትዋ ሊን ጆንግስ ኃይለኛ ስለሆነች እንደምንም ተከተያት' ብሎ መከረኝ። ከድል በኋላም 'ጥሩ ነው የሮጥሺው ደስ ብሎኛል' ብሎ የባርሴሎና ኦሊምፒክ አርማ ያለበትን የእጅ ሰዓት ሸለመኝ። 'ሌሎቹንም ሴቶች በርቱ በያቸው' ነው ያለኝ።»

«ከድል በኋላ ስታዲዮሙ ውስጥ ባንዲራ ሲያለብሱሽ ከነበሩት ሰዎች ቱታ የለበሰው ሰውዬ ሲያንቅሽ የፈለገ ነበር የመሰለው። ሰውዬው ምን ልሁን ነበር የሚለው?»

«የኛው ልጅ ነው። ከደስታ ብዛት የሚያደርገው ጠፍቶት ነው የሚራወጠው።»

«አዲስ አበባ እንደገባሽ አየር ማረፊያው ውስጥ ምን ጠፍቶብሽ ነው ከተዘጋጀልሽ ልዩ መኪና ወርደሽ ወዲያና ወዲህ ስትሯሯጪ የነበረው?»

«ጓዜን የሚሰበስብልኝ ሰው ስላልነበረ እሱን ለመረከብ

ነበር የተረራረጥኩት፡፡»

«ኦሊምፒክ መንደር ውስጥ ሳለሽ ያጋጠመሽ ልዩ ነገር ነበር?»

«ፈረንጆቹ ሃያ አራት ሰዓት ይበሉ ነበር፡፡ ነፃ ስለሆኑ ይጫወታሉ፤ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፡፡ አትሌቶቹም እጅብ ብለው ይገባሉ፤ ይወጣሉ፡፡ ይህ ለኔ አዲስ ነበር፡፡»

«ከዓለም አትሌቶች በጣም የምታደንቂያት ሴት አትሌት ማንች?»

«ደቡብ አፍሪካዊቷን ኤሌና ማየር፣ ያልታወቀች ተወዳዳሪ ሆና ሳለ ሁለተኛ በመውጣቷ አደንቂታለሁ፡፡ ሶስተኛ የወጣችው አሜሪካዊትም ከክሮስ ካንትሪ (አገር አቋራጭ) ወደ ትራክ በሆረች፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ድል ማግኘቷ የሚያስመሰግናት ነው፡፡ በወለደች በዘጠነኛው ወሯ ተወዳድራ አንደኛ የወጣችው ሚክግሊን ሲገዛም የምትደነቅ ናት፡፡ ሉቺያ ይስሀቅንና ትዕግስት ጥሩዳንም የተቻላቸውን ሁሉ በማድረጋቸው አደንቃቸዋለሁ፡፡»

«የባርሴሎናውን ድል በአትላንታ የምትደግሚው ይመስልሻል?»

«ሰላምና ጤና ካለ ምንም የሚያግደኝ ሀይል የለም፡፡ እግዚሀር ለዚያ ያብቃኝጂ፡፡»

«ከኦሊምፒኩ የወርቅ ሜዳሊያሽ በላይ የምታፈቅሪው አለ?»

«አዎን፤ አሰልጣኜን፡፡ ለዚህ ድል ያበቁኝ እሳቸው ናቸው፡፡ በቶኪዮው ውድድር በደረሰብኝ ህመም ምክንያት ኦፕራሲዮን እንድደረግ ታዞ ነበር፡፡ በዚያ ላይ ጭንቀቱ


ደግሞ የበለጠ አስቸግሮኝ ነበር። እርሳቸው ግን እንደ ሀኪም ሆነው አያሹ አድነውኛል። እንደወንድም፣ እንደሐኪም፣ እንደአባትም ናቸው አሰልጣኝ ወልደመስቀል ኮስትሬ፤ በጣም እወዳቸዋለሁ።»

«ግን እውነት ከሜዳልያው አብልጠሽ ነው የምትወጂያቸው?»


«(በሳቅ ፍንድት ብላ) ከሜዳልያው የበለጠ እንኳ አልወዳቸውም።»

«ይህን መድረክ ምን መልዕክት ልታስተላልፊበት ትፈልጊያለሽ?»

«እንግዲህ ስለህዝባችን ልንገርህ። ሕዝቡ በጣም ከባድ ፍቅርና ደስታ ነው ያሳደረብኝ። እንዳሸነፍኩ ወዲያውኑ ሰዎች 'አገርሽ እንደገባሽ ሕዝቡ እንዴት ነው የሚቀበልሽ? ምን ያደርግልሻል?' እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ሲጠይቁኝ 'ሕዝቡ በደስታና በዕልልታ ነው የሚቀበለኝ' እላቸው ነበር። ግን በልቤ እንደዚያ ይደረግልኛል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ሕዝቡ ግን 'ውጣ' ሳይባል በየመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ደስታውንና ፍቅሩን በገለፀልኝ ጊዜ ልገልፀው የማልችለው ደስታ ነው የተሰማኝ። የጣት ቀለበታቸውን ሳይቀር እያወለቁ የሰጡኝ አሉ። እቤቴ ድረስ እየመጡም የወርቅ ስጦታ ያበረከቱልኝ አሉ። ባጠቃላይ ብቻ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍ ያለ ምስጋና አቅርብልኝ።»



# ፍቅር ወይስ ልዩነት?



# ማነው ንፁህ ዘር?

## እሸቱ ተፈራ

«ሳፊ ኦሮሞ ነኝ» አለ አንዱ በቴሌቪዥን። «የጠራሁ አማራ» «ንጹህ ትግሬ» ወዘተ... ነኝ የሚሉም በርካታ ሰዎች በየስፍራው እናገኛለን። ወገኖች ካልሆን በስተቀር «ንጹህ» የሚለውን ቃል ፈፅሞ ልናነሳው ባልተገባም ነበር- «ንጹህ» ነን ካልን፣ ሌላ «የቆሸሸ» አለ ማለታችን ይሆናልና።

ፈረንጆች እንደሆን ሁላችንንም «ምጥማጦች» ነው የሚሉን። ታዲያ አሁን የኛን ዘር ቀጠራ ምን ይሉታል?

ካሁኑ ካልተጠነቀቅንስ ወደዘረኝነት ማምራታችን ይቀራል? የዚህ ዓይነቱ የዘረኝነት ልክፍት የተጠናወታቸው ናዚዎች ባንድ ወቅት ንጹሁ የሰው ልጅ ዘር የአርያን ዘር ብቻ ነው ብለው ተነሱ:: እነዚህ እብዶች ባገራቸው ላይ ያደረሱትን ውርደት ዓለሙ ሁሉ ያውቀዋል::

የኔ አነሳስ ዘረኝነት ቅጡን ሲያጣ የሚያስከትለውን አበሳ ቅልብጭ አድርጋ የምታሳይ ያንዲት ሴት እውነተኛ ታሪክ ላጫውታችሁ ነው::

አገሩ ጀርመን ነበር:: መጋቢት 26 ቀን፣ 1945 እ.አ.አ ቆጣጠር::

የአሜሪካ ወታደሮች በባቫሪያ በኩል ጦርነቱ እየገፉ ስቴይንሆሪንግ እምትባል አነስተኛ ከተማ ደረሱ:: ከተማይቱ ከሙኒክ 20 ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ ናት:: ጀርመኖቹ ከ36 ሰዓታት በፊት ጥለዋት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ፈርጥጠዋል:: አሜሪካኖቹ ታንኮቻቸውን በዋናው አደባባይ አቁመው ከተማዋን ማሰስ ጀመሩ:: ወዲያው አንዱ ቃኝ ቡድን ውብና ንጹህ ፎቅ አገኙ:: ያማሩ የቢሮ እቃዎችና ትሙክ-ትሙክ የሚሉ ምንጣፎች አሉት:: እድሜያቸው ከሶስት ዓመት ያልበለጠ 350 ሕፃናትም አልጋቸው ውስጥ ነበሩ:: ጥቂት ሞግዚቶች አብረዋቸው አሉ:: አስተዳዳሪዎቹ ወንዶች በሙሉ ሸሽተዋል::

ጫጫታው አያድርስ ነው:: አብዛኞቹ ሕፃናት ያለቅሳሉ:: የሚላስ የሚቀመሰውን ሁሉ የሆስፒታሉ ሰራተኞች ይዘውት ስለሸሹ ህፃናቱ ለሁለት ቀን ምግብ በማጣታቸው በጣም ተርበዋል::

አሜሪካኖቹ የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ:: ንጹህ ወተት ግን አልነበራቸውም:: በአጋጣሚ ግን አንድ ላሀን አገኙና

ከአንድ ገበሬ ጋር አስተዋወቋቸው:: ትንሽ መኪና ስለነበረችው አሜሪካኖች ቤንዚን ሰጡትና በየመንደሩ እየዞረ ወተትና ዳቦ ቃርሞ ለሕፃናቱ አመጣላቸው::

ትልቁ ችግር ግን ሕፃናቱ የማን መሆናቸውን ማረጋገጡ ላይ ነበር:: ሞግዚቶቹም ቢሆኑ ብዙ ሊረዱ አልቻሉም::

ቤቱ «ንጹሀን ዘሮች» የሚፈለፈሉበት «የሕይወት ምንጭ» በመባል የሚታወቀው በናዚዎች የሚካሄድ ተቋም መሆኑን ግን ጠቁመዋል:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይህ ተቋም ብዙም የተጠና አይመስልም:: ናዚዎች ስለህብረተሰብ አኗኗር ከነደፉት እቅድ ውስጥ በደንብ ያልተፈተሸ ጉዳይ ነው:: ስንት ሕፃናት በዚህ ቤት ውስጥ እንደተወለዱ አይታወቅም:: ጦርነቱ ካበቃ በኋላ በተጠናቀረው ስታቲስቲክስ መሰረት ቢያንስ 12ሺ ሕፃናት በዚህ ተቋም ውስጥ ተወልደዋል:: በተቋሙ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሁሉ ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ ራሳቸውን ስለሸሸጉና ሕፃናቱም የሚያስታውሱት ነገር ስለሌለ ግን ብዙ ጠቃሚ መረጃዎች ተዳፍነው ቀርተዋል:: በዚህች ከተማ ውስጥ ከ15 የማያንሱ የሕፃናት ማሳደጊያ ሆስፒታሎች ነበሩ::

ሌበንስቦርን የተባለው ሆስፒታል የተቋቋመው በፍሬዴሪክ ሂምለር እ.አ.አ በ1935 ሲሆን ዓላማውም ብዙ «ምርጥ» የሆኑ የኤስ.ኤስ (የመረጃ ፖሊሶች) ልጆችን በገንዘብ እየደጐሙ ማሳደግ ነበር- ንጹሁን የአርያን ዘር ለማራባት በሂትለር በኩል የሚካሄደው ፖሊሲ መተግበሪያ አንድ አካል መሆኑ ነው:: በርሱ አስተሳሰብ የጀርመን ሕዝብ ከሌላው ጋር በመጋባቱ በግብረ ሰዶም፣ በውርጃና በአመንዝራነትም ምክንያት ንጹህ ዘርነቱን አጥቷል:: ይህ

ደግሞ ጀርመንን በንጹሕ ዘር የመገንባቱን ተግባር ያደናቅፍበታል:: ስለዚህም የጌታውን ሀሳብ ለማሳካት የሚጥረው ሂምለር፣ ይህን ጉዳይ ሊያስተካክል ተነሳ:: ሂምለር ፍጹም ታዛዥነትንና ጀግንነትን እንዲሁም የተለያየ የዓይንና የፀጉር ቀለም ያላቸውን ሰዎች በማጋባት የተፈለገውን ቀለም ለማግኘት እንደሚቻል ሁሉ ምርጥ ዘር የመፍጠሩ ተግባርም ያንኑ ያህል ይቀላል የሚል ቅዠት ነበረው:: እንዲያውም ትርኪ ሚርኪ የሆኑትን አይሁዶች፣ ጂፕሲዎች፣ ምግባረ ብልሹዎችና ደካሞችን ካስወገድን ጀርመን የምርጥ ዘሮች ሀገር ትሆናለች ብሎ ያምናል::

ይህንኑ ቅዠቱን ለመተግበርም ሂምለር ትእዛዙን ያሻገጉደጉደው ጀመር:: የኤስኤስ አባሎች ከሚስቶቻቸውም ይሁን ከጋብቻ ውጭ ብዙ ልጆች እንዲወልዱ መመሪያ ሰጠ:: ቀጥሎም የጀርመን ሴቶች ብዙ ሕፃናት መውለድ እንዳለባቸው ወሰነ:: በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይማሩ የነበሩ ልጃገረዶች ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የሚያደርጉትን ዝግጅት ትተው በርካታ ልጆች ለመውለድ እንዲዘጋጁ አዘዘ:: ብዙ ልጆች የወለዱ እናቶች ሜዳሊያ እንዲሰጣቸውና በየመንገዱም የናዚ ፓርቲ ወጣት አባሎች የክብር ሰላምታ እንዲሰጧቸው ተደረገ::

በተከታዩ ዓመት በየአነስተኛ ከተሞች ውስጥ ሌበንስቦርኖች ከነሙሉ ድርጅታቸው ተከፈቱ:: የናዚ ፓርቲ አባሎች ተቋሞቹን በተቆጣጣሪነት እንዲያስተዳድሩ ሲመደቡ የምስጢር ፖሊሶች ደግሞ አካባቢውን እንዲጠብቁ ተደረገ::

ዋነኛው ጥንቃቄ እናቲቱ ንጹሕ ጀርመን መሆኗን ሳያስልሱ መቆጣጠሩ ላይ ነው:: የሴቲቱ ዝርያዎች ረጅም ዘመን መኖር የሚችሉ መሆናቸው፣ በሽታ መቋቋም ይችሉ

እንደሆነና በምን ምክንያት እንደሞቱ ታሪካቸው በጥንቃቄ ይመረመራል:: ፍጹማዊቱ ጀርመናዊት ሴት የምትባለውም ወርቃማ (blonde) ፀጉርና ሰፋ ያለ ዳሌ ያላት ናት:: ሽንቃጣነትና ምግብ አለመድፈር የሚወደድ አልነበረም:: መኳኳልማ ጀርመናዊነትን እንደመካድ ይቆጠራል::

ሌበንስቦርን ገብተው መውለድ የሚፈልጉ ሁሉ ተቀባይነት ያገኛሉ ማለት አይደለም:: በ1930ዎቹ መጨረሻ ካመለከቱት ነፍሰጡሮች 40 በመቶው ተቀባይነት አላገኙም ነበር:: ምርጥ ዘር ለማፍራት ባብዛኛው የሚመረጡት ከጋብቻ ውጪ የሚደቅሉት እናቶች ሲሆኑ እርግዝናቸው በግልጽ መታወቅ እንደጀመረም ወደ ሌበንስቦርን ይወሰዳሉ:: እዚያም ሳሉ ልዩ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል:: ተራዎቹ ጀርመናውያት በሕልማቸው እንኳን የማይመጡባቸውን ዓይነት ምግቦች ይመገባሉ::

የሕፃናት መሰየሚያ የሚባል ልዩ ቀንም በሂምለር ተፈጥሮ ነበር:: ይህም በዓል ክርስትናን ለማስቀረት ታስቦ የተጀመረ ሲሆን፣ በእለቱ ወላጆች በናዚ ባንዲራ ስር ይንበረከኩና የኤስ.ኤስ ሹሞችን ዲስኩር ይሰማሉ:: ከዚህ በኋላ እናቶች ልጆቻቸውን በእንክብካቤ እንደሚያሳድጉ ቃል ገብተው ሕፃናቶቻቸውን ይዘው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ:: ወላጆች የሌሏቸውን ልጆች ደግሞ የናዚ አባሎች በማደጐ ወይም በጉዲፈቻ ወስደው እንዲያሳድጓአቸው ይደረጋል:: ይህ ሁሉ ግን የሚደረገው በምስጢር ነው::

የሕፃናቱ መኖሪያ የሂምለር የቀን ተቀን ክትትል የማይለየው ስፍራ ነው:: እያንዳንዷን ጥቃቅን ጉዳይ ሳይቀር ይከታተል ነበር:: የልጆቹ ወላጆችና ሕፃናቱ የሚያሳዩአቸውን ባህርይ፣ የበታቾቹ ሪፖርት እንዲያደርጉለት አዝዟል::

በተመቸው ጊዜም እያንዳንዱን «ልዩ» ሕፃን ይጎበኛል:: ለልደት በዓላቸውም አንዳንድ ሻማ በነፍስ ወከፍ ያበራላቸዋል:: በሂምለር ልደት ቀን ለተወለዱት ደግሞ የተለየ እንክብካቤ ያደርግላቸዋል:: የልደት ስጦታ ያቀርብላቸዋል:: አስተዳደጋቸውን፣ ውበታቸውን፣ ታዛዥነታቸውንና ጠባያቸውን ይከታተላል::

የተወለደው ሕፃን የምርጥ ዘርን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑም በየጊዜው ይገመገማል:: በድርጅቱ የሚገኙትን ሕፃናት የ«ምርጥ ዘር» ኢክስፐርቶች በየጊዜው ይመረምሯቸዋል:: ንጹህ የሚባለውም ዘር ረጅም፣ ራሰ ትልቅ፣ ፊተ ጠባብ፣ ጉንጮቹ የተስተካከሉ፣ ስንደዶ አፍንጫ፣ ዞማ ፀጉር፣ ሰማያዊ ወይም ግራጫ ዓይኖችና ፀአዳ ቆዳ ያለው ነው:: በመጀመሪያው አካባቢ የኤስኤስ አባል ከሆነ አባትና ከተመረጠች ሴት የተወለዱ ሕፃናት ንጹሕ እንደሆኑ ይቆጠር ነበር:: ነገር ግን ጦርነቱ እየገፋ ሲሄድ ንጹሕ የአርያን ዝርያ ያላቸውን ሴቶች በገፍ ፈቃድ ማግኘት አዳጋች ሆነ:: በመሆኑም ሂምለር እንዳለመው ተቋሙ ብዙ ሕፃናትን ሊያሳድግ አልቻለም:: ስለዚህም ሂምለር ሌላ የምርጥ ዘር ማበራከቻ ዘዴ ቀየሰ:: ከሚሽን ተቋቋመናም የኤስኤስ ወታደሮች እድሜያቸው 30 ሲሞላ የግድ እንዲያገቡ ተወሰነ:: ሚስቶቻቸው ወዲያውኑ ካልፀነሱም ወደ ሐኪም ተልከው እንዲመረመሩ መመሪያ ተሰጠ::

ከዚህም በተጨማሪ ከሌሎች ሀገሮች ሕፃናትን የማፈን ተግባር ተጀመረ:: ይህንን ተግባር ሂምለር «የጠፉ ዘሮችን ፍለጋና ግብረ ሕጽበት» ሲል ሰየመው:: በዚህ እቅድ መሰረት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሕፃናት ከየቦታው ታፍነው ተወሰዱ- ቁጠራቸው ይህ ነው ብሎ በውል ለመናገር ግን አይቻልም::

ጀርመኖች ምስራቅ አውሮፓን፣ ፈረንሳይና የስካንዲኔቪያን ሀገሮችን በወረሩ ጊዜ የ«ንፁሁን ዘር» የሚመስሉ ወጣቶችን እንዲከታተሉ ታዘው ነበር። ለዚህም ሲባል «ቡናማ መነኩሲቶች» የሚባል ቡድን ተቋቋመ። የናዚ እምነት ተከታይ የሆኑ ሴቶች የመነኩሲቶችን ቡናማ ቀሚስ ለብሰው፣ ነጭ ኮሌታ አድርገውና ግራጫ ካፖርት አጥልቀው፣ ምግብ በመያዝ የተራቡ ሕፃናትን ማደን ጀመሩ። ስለወላጆቻቸው ጥቂት ከጠየቁና ቀርበው ሲያዩዋቸው ምርጥ ዘሮች መስለው ከታዩአቸውም ተጠልፈው በባቡር ወደ ጀርመን ይላካሉ።

ጀርመን ከገቡ በኋላ ለሂምለር ኤክስፐርቶች ይሰጣሉ። እድሜያቸው ከስድስት ዓመት መብለጥ የለበትም። ኤክስፐርቶቹ ጠቅላላ የአካል ምርመራ ያደርጉላቸውና የዓይናቸውንና የፀጉራቸውን ቀለም፣ የራሳቸው ቅርፅና ቁመታቸውን በደንብ ይለካሉ። የአርያን ዘርን መስፈርት ካሟሉ የጀርመናዊነት መብት ይሰጣቸዋል። ከዚህ በኋላ ጀርመናዊ ስምና መታወቂያ ይታደላቸዋል። ትእዛዝን አሜን ብሎ የመቀበልም ትምህርት ይሰጣቸዋል። ወንዶቹ ወታደራዊ ስልፍ እንዲማሩና የኤስ.ኤስ ዓርማን እንዲለዩ ይደረጋሉ። የእናታቸውን ቋንቋ እርግፍ አድርገው ያልተውቱ በጀርመንኛ ብቻ መናገር እስኪጀምሩ ድረስ አይቀጡ ቅጣት ይቀጣሉ።

ያም ቢሆን እነዚህ እድለኛ ናቸው ማለት ይቻላል። ሂምለር ባስተላለፈው ትእዛዝ መሰረት በሌበንስቦርን ከነበሩት ሕፃናት ውስጥ «መናኛ» የተባሉት ይፈጁ ጀመር። ከጀርመናውያት የተወለዱ ቢሆኑም አካለስንኩላን የሆኑትና ከውጭ ታፍነው ከመጡ በኋላ፣ የንፁሁን ዘር መስፈርት

ያላሟሉት እየተመረጡ ጠንከር ያሉት ወደ ግዳጅ ስራ ካምፕ ሲላኩ፣ ደካሞቹና ጨቅላዎቹ ደግሞ ወደ ሕፃናት ማረጃ «ቂራ» ተወሰዱ:: ከፍ ከፍ ያሉት ወደ ሎድ (ፖላንድ) ካምፕ ተልከው በረሀብና በቅዝቃዜ ሲሞቱ ቀሪዎቹ በካርቶን ሳጥን እየታሸጉ እሳት ተለቀቀባቸው:: ሌሎቹም ከነሕይወታቸው ኖራ የተሞላ ጉድጓድ ውስጥ እየተጨመሩ ተገደሉ::

ጦርነቱ በ1945 ቢያበቃም የቀይ መስቀል ማኅበር የሕፃናቱን ወላጆች ለማግኘት ወይም ወላጆቻቸው የሞቱባቸው መሆናቸውን ለማረጋገጠ ድፍን ዓመት ፈጅቶበታል:: በተለይ ከፖላንድ ታፍነው የመጡትን ሕፃናት ወላጆች ማግኘቱ እምብዛም አልተሳካም:: ሃያ በመቶውን ብቻ ነበር ማግኘት የተቻለው:: በርግጥ ከጦርነቱ በኋላ አንዳንድ ፖላንዳውያን ወደ ጀርመን ተሻግረው ልጆቻቸውን አግኝተዋል:: ይህም ግን ችግር መፍጠሩ አልቀረም:: ልጆቹ ፍፁም «ጀርመናውያን» ስለሆኑ፣ ከጀርመንኛ በስተቀር ካለ መናገራቸውም ሌላ በተጨማሪ ስለወላጆቻቸውም የማያውቁት ነገር ባለመኖሩ፣ ከጀርመን መውጣትን አልፈቀዱም:: ወላጆቻቸውም ባዶ እጃቸውን ተመለሱ:: እዚህ ላይ እንግዲህ የሂምለርና የኤስ.ኤስ ፕላን ሰራ ማለት ነው:: ከፋና በጉውን የማያውቁትን እምበቃቅላ ሕፃናት እነሂትለር እንደፓስተር ኢንስቲትዩት ጥንቸሎች፣ ለምርምር አዋሏቸው፣ እንደ ጭዳ በግ አረዷቸው::

ከዚህ መዓት ከተረፉት ውስጥ አንዷት ለ18 ወራት በሌበንስቦርን ውስጥ የነበረች ሴት ታሪኳን በቅርቡ ዓለም እንዲያውቀው አድርጋለች:: ሬኔት ትባላለች:: ሙሉ ስሟ እንዲገለጥ አትፈልግም:: ዛሬ በኮሎኝ ከተማ የታሪክ መምህርት ናት:: እድሜዋ ሃምሳዎቹ ውስጥ ነው:: ታሪኳም ልዩና አሳዛኝ ነው:: ይህንኑ ታሪኳንም ለማጠናከር ሃምሳ ዓመት ፈጅቶባታል::

የሬኔታ እናት ኮሎኝ ባንክ ውስጥ በፀሐፊነት ስትሰራ አንድ ከፍተኛ የኤስ.ኤስ ሹም ይወዳጃታል:: ሰውዬው ባለትዳርና የስምንት ልጆች አባት ነበር:: ወጣቷ ፀሐፊ ልጅ ለመውለድ አስባ ትገናኘው ወይም ጊዜያዊ ደስታን ፈልጋ በውል አይታወቅም:: ብቻ ወዲያውኑ ፀነሰች:: ወዳጇ የኤ.ስ.ኤ.ስ ሹምም በምቾት ወደምትያዝበት ወደ ሴቴይንሆሪንግ ወሰዳት:: እዚያ የሄደችው እርግዝናዋ ከመግፋቱ በፊት ነበር:: ስለዚህም ጓደኞቿ መፀነሷን አላወቁም:: በ1941 እንደተገላገለችም ጥቂት ሳምንታት ቆይታ 700 ኪሎ ሜትር ወደ ሚርቀው መስሪያ ቤቷ ወደ ኮሎኝ ተመለሰች:: በዚያን ወቅት ከነበሩበት ከተማ መቀየር ስለማይፈቀድ፣ ልጇ ወዳለችበት ከተማ መዛወር ባለመቻልዋም ነበር ልጇን ለሌበንስቦርን ሞግዚቶች ጥላ መሄድ የተገደደችው:: ሆኖም በየጊዜው ፈቃድ እየወሰደች ልጇን ትጎበኛት ነበር:: ሬኔት 18 ወር ሲሞላት፣ ለማደጐ ተሰጥታ ስትኖር በ1944 ግን የሬኔት እናት ቤት በቦምብ ስለጋየ ወደ ባቫሪያ የመቀየር እድል ገጠማት:: በዚህን ጊዜም ተገናኙ::

የሬኔት አባት ግን ልጁን የማየት እድል አላገኘም:: በመጀመሪያ ወደ ስቴይንሆሪንግ ለመሄድ ፈቃድ ጠይቆ ተከለከለ:: በሁለተኛው ጊዜ ተሳክቶለት ልጁን ለመጠየቅ ቢጓዝም ልጅቱ ለማደጐ እናት ተሰጥታ ስለነበር ሊያገኛት አልቻለም:: ሬኔት ስለ ስቴይንሆሪንግ የምታስታውሰው ምንም ነገር የለም:: ስላለፈው ሕይወቷ ብዙ ለመናገር ፈቃደኛ አልነበረችም:: ስለዚህም ሬኔት ብዙ የጦርነቱን ወቅት መዛግብት ማገላበጥ ነበረባት::

ሬኔት ካደገች በኋላ የአባቷን ማንነት ለማወቅ መጣር ጀመረች:: እናቷ አባትሽ ትልቅ የኤስ.ኤስ ሹም ነበር፣

በጦርነት ላይ ሞቷል:: ምናልባትም በሩሲያ ጦር ግንባር ሳይሆን አይቀርም ያረፈው፤' ከማለት በስተቀር የተብራራ መልስ ሰጥታት አታውቅም:: ይህ ሬኔት ስላባቷ ለማወቅ ያላትን ጉጉት ይበልጥ አናረው:: ስለዚህም አባቷ ለእናቷ የፃፋቸውን 83 ደብዳቤዎች እንድታሳያት አጥብቃ በመለመን እጇ አስገባች:: አንድ ባንድ አነበበቻቸው:: ደብዳቤዎቹ ስለ ስራው የሚሰጡት ምንም ፍንጭ የለም:: የአስር አመት ልጅ ሳለች ግን አንዲት አክስቷ መጥታ ወሰደቻት:: ከአባቷ ዘመዶችም ጋር አስተዋወቀቻት:: የአባቷ ዘመዶች በበጐ ዓይን ቢመለከቷትም ሬኔትን መልካም ስሜት አልተሰማትም:: የናቷ ወገኖች በበኩላቸው ገሸሽ በማድረግ የቀዘቀዘ ስሜት ያሳይዋታል:: ሬኔት አንድ ምስጢር ቢኖር ነው ብላ ደመደመች::

ስለዚህም ፍተሻዋን ቀጠለች:: «የመጀመሪያው ፍንጭ በ1979 ተገኘ:: ያኔ እድሜዬ 38 ነበር:: አንድ ትንሽ መጽሐፍ አገኘሁ:: ከቼኮዝሎቫኪያ የጭነት መኪና ላይ የተገኘ ነበር:: በውስጡ የጀርመን መኰንኖች ስም ዝርዝር አለበት:: በጦርነቱ ጊዜ የሰሩት ድርጊትም በሙሉ ተዘርዝሯል:: አዎን አባቴ የገደላቸውም ሰዎች ብዛት ዝርዝር ቀርቧል:: ወደ ማጐሪያ ካምፕ የላካቸው ጂፕሲዎች ስም በዝርዝር ሰፍሯል:: ከዚህ በኋላ ነበር 'ስለአባቴ ተግባር በዝርዝር ማወቅ አለብኝ' ብዬ ታጥቄ የተነሳሁት:: በርካታ መዛግብ ቶችንና ጋዜጦችን ፈተሸኩ::

«ቀስ በቀስ ሐቁን ተረዳሁ:: አባቴ ተራ የኤስ.ኤስ አባል አልነበረም- የሂምለር ቀኝ እጅ እንጂ:: ስሙም ፍሬደሪክ ጆኬልን ሲሆን የፖሊስ ሠራዊትና በሰሜን ሩስያ የሚገኙ የምስጢር ፖሊሶች አዛዥ ነበር:: በጭፍጨፋው ፕሮግራም በግድያ ካምፖቹ፣ በመስቀሉና በማስሩ ተግባር

ላይ ሙሉ በሙሉ ነው የተሳተፈው፡፡ እጁ በደም የተነከረ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ ወደ ጦርነቱ ማብቂያ ገደማም ተይዞ ራሱ መስሪያ ቤት አጠገብ በሚገኘው አደባባይ ላይ መሰቀሉን ደረስኩበት፡፡»

ሬኔት ይህን እንደተረዳች በሃዘን ማእበል ተዋጠች፡፡ ጀርመን ጦርነቱን ብታሸንፍ ኖሮ ሬኔት ለእናት ሀገር ጀርመን፣ ንጹህ (ምርጥ) ዝርያዎችን እየፈለፈለች የምትኖር፣ የርቢ ላም መሆኗ ሲታሰባት ይዘገንናታል፡፡ «የናቴ ወገኖች ለምን ፊት እንደሚነሱኝ፣ የአባቴ ወገኖች አስተያየት ደግሞ ለምን ለየት እንደሚል፣ በሚገባ ተገነዘብኩ፡፡ አባቴን ስለምመስል ነገረ ስራሽ ሁሉ ቁርጥ ያባትሽን ነው ይሉኛል፡፡ ይህ ነው መድረሻ ያሳጣኝ፡፡ እኔ እሱን አለመሆኔን ለማሳመን ስንት ውጣ ውረድ ደረሰብኝ፡፡ አባቴ የፈፀማቸውን አሰቃቂ ድርጊቶች እንደሁ በደም አልወረስኳቸው፡፡ እኔ የራሴ ስብዕና ያለኝ ንጹህ ግለሰብ መሆኔ ሊታወቅልኝ ይገባል» በማለት ሬኔት በምሬት ትናገራለች፡፡



## የክብር እንግዶች ለምን ይዘገያሉ?



# የመንግሥቱ አንጋች ትዝታ

እሸቱ ወንድሙ

ከራሴ ልጀምር፤ የኃይለ ስላሴ ልዩ ዘብ የነበረው የክብር ዘበኛ ከፈረሰ በኋላ በክብር ዘበኛው መልክ የተቋቋመ ልዩ የደርግ ጥበቃ ጦር መመስረት ነበረበትና ከሌላው ጦር በተለየ የኮማንዶና የጥበቃ ትምህርት ተከታትዬ ቤተ-መንግስት ውስጥ በነበረው ስፔሻል ፎርስ ውስጥ በአንጋችነት ተመደብኩ:: ቤተ መንግስት ስገባ የንጉሳውያን ወይም የልዑላን ኑሮ ይገጥመኛል ብዬ ባልመኝም፣ የአጋፋሪነቱ ግን አይቀርብኝም ብዬ ነበር፤ ግን አልሆነም:: ስራዬን ልዩና የተለየ አድርጋችሁ የምትጠብቁ

ካላችሁ አትሳሳቱ! ተግባሬ ጥበቃ፣ አጀባ፣ በከፍተኛ ደረጃ ፀረ-አብዮተኞች ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩትን የማጐሪያ ስፍራ ማከማቸት ነው::

በዚህ ግቢ ባሳለፍኩት ጊዜ ብዙ ነገር አይቻለሁ፤ ታዝቤያለሁም:: ራሴም ለራሴው ስግቼ ያለሁ:: የገዛ ጓደኞቼን ተጠራጥሬያለሁ:: በተለይ በየዕለቱ የሚለዋወጠው የጥበቃ ቦታ ባለመተማመንና ለሚስጥር ጥበቃው ብቻ ሳይሆን እርስ በርስም ያቆላልፈን ነበርና ነው:: አንዱ በሌላው ላይ ሹክ ማለቱ ሳይበቃው፣ ምን እንዳሰበ እንኳ ስለሚጠቁምበት ስርዓቱ ጥብቅ ነበር:: የተባልነውን መፈጸምም ግዴታ::

ሁሌም ግዳጅንን መወጣት ነው:: ትእዛዝ፤ በአንደኛ ደረጃ ተጠንቀቅ መታሰር ብቻ፤ «የወቅቱ ችግር ነው፣ ሀገሪቱ በውጪም በውስጥም በፀረ-ሕዝቦች ተወጥራለች» ይባላል::

ይህ በንዲህ እንዳለ አንድ ቀን አዲስ ትእዛዝ መጣ:: በወቅቱ የቤተ መንግስቱ ጥበቃ ክፍል ዘመቻ መኰንን የነበረው ሻለቃ እሸቱ ገብረሕይወት «ጓድ ሊቀመንበር ወደ ምርመራው ክፍል በጧት ስለሚሄዱ ተዘጋጁ!» አለን:: 'በነገው እለት ከበድ ያለች ነገር መኖር አለባት' አልኩኝ ለራሴ:: ሊቀመንበር መንግሥቱን አጅቤ ለማምጣት በነጋታው መሄዶ አልቀረም:: ሊቀመንበሩ በሰዓቱ ተዘጋጅቶ ይጠብቀን ስለነበረም በክብር አጅበነው እምርመራዋ ክፍል አደረስነው:: ከዚያም ከጓዶቼ ጋራ ሆኜ የጥበቃ ስራዬን እዚያው ቀጠልሁ::

ያቺ ምርመራ ክፍል ብሩህ አእምሮ ያለውን ስንቱን ወጣትና የተከተልነው መንገድ ትክክል አይደለም ብለው

የተቃወሙ የደርግ አባሎችን እምሽክ አድርጋ የበላች ነች። ብዙዎች በዚህች ክፍል ውስጥ ተንገላተዋል፤ የፊጥኝ ታስረው ተገርፈዋል። ይህች የሞት ቤት ዛሬም እማኝ ሆና ተገትራ ትገኛለች።

ወደዚች ክፍል ነበር መንግስቱ ዘልቆ የገባው። ፍርደ-ገምድሉ ዳኛና የሲኦል ቤቱ ተገናኙ። አንድ መነጽር ያደረገና በውል የማላውቀው ሰው ለመንግስቱ አንድ ደብዳቤ ሰጠው። መንግስቱ ወገቡ ላይ ከታጠቀው ሽጉጥ በተጨማሪ ብእር መሰል ሽጉጥ ነበረውና በቀኝ እጁ የያዘውን ይህን ሽጉጥ ወደግራ እጁ አዛውሮ ለፊርማ ብዕሩን አወጣ። ፊርማውንም አስቀመጠ- የሞት ፊርማ!

ይህች ዕለት ግን እንዲሁ በፊርማ ብቻ ነበር ያለፈችው። እኔም የተለመደውን ጥበቃዬን ቀጠልኩ። ሆኖም በቤተ-መንግሥቱ ውስጥ ውጥረት ሰፍኖ ነበር። በነጋታው የተለመደው አሰልቺ የደርግ ስብሰባ ተጠራ። መቸም በስብሰባ የተወለደ መንግስት፣ ስብሰባ ይወዳልና ስብሰባ ሆነ። የደርግ አባሎች ተሰበሰቡ። ተረኛ መኮንኑም የዕለቱ ጥበቃ እንዲጠናከር ቀጭን ትዕዛዝ ሰጠ። እኔም ጥበቃዬን ቀጠልኩ። ስድስት ሰዓት ያህል የፈጀው ስብሰባ ተበተነ። ጥበቃው ቀጥሏል።

ታንኮችና መትረየሶች ሳይቀሩ ከእኛው ጋር አፍጠው አደሩ።

አይነጋ የለም ነጋ። የቃኝ የሙቶ አዛዥ የነበረው ሻምበል ዓለሙ ደቻሳ ለግዳጅ ብቁ ለማድረግ መትረየስ የተጠመደባቸውን ጂፖች ወደ ቤተ መንግስቱ ጋራዥ ይዞአቸው ሄደ። ጂፖቹ የመጀመሪያ ደረጃ ጥገና (ሰርቪስ) ተደረጉላቸው ተወልውለው መጡ። የውጭ ሀገር መሪዎችን

በክብር የማይኖቡ ሳይሆኑ አካባቢውን «ከፀረ-ሕዝቦች» የሚጠብቁ፣ የውጭ ኃይል ቢመጣ አፋቸውን ከፍተው የአረር ነዳድ የሚያዘንቡ ናቸው። አራት ተጨማሪ ሽንጣም የደርግ ጽህፈት ቤት ላንድሮቨሮችም ተጨምረው በቃ በቃቸውን ይዘዋል።

የቤተ መንግስቱ ተራ አንጋች ስንዳዩ እጅግም ትኩረት የሰጠው አይመስልም። «ያለ ምንም ደም፣ እንክፏ ይውደም!» እያለ ይዘምራል። ይዘምራል እንጂ ትርጉሙንስ አያውቀውም፤ ሊያውቅም አይችልም። ያሁኑም ግርግር ታዲያ በየዕለቱ የሚደረግ ትርኢት ነውና ከመጤፍ አልቆጠረውም። እንዲያውም በጥበቃ ሥራ ላይ የቀረነው ብቻ ስንቀር፣ የማይመለከታቸው በድራቶት ተከስ እንደ ሾተል ቀጥ ያለ ዩኒፎርማቸውንና ከሥሩ'SF ምልክትን መሬት ላይ እየከተበ የሚሄድ ጫማቸውን፣ የሰውን መልክ እስከሚያሳይ ድረስ ወልውለውት እስከ ክንዳቸው ድረስ ፋቲጋቸውን አጥፌው የፈረጠመ ጡንቻቸውን እያሳዩ፣ ሲንጐማለሉ ያስፈራሉ። ነፍስ በላዎች ናቸው። በሰልፍ ሆነው ወደፊታቸው ያመራሉ። እነሱም ሌላ ግዳጅ በሌላ ጊዜ ለመወጣት።

ሻለቃ እሸቱ ገብረሕይወት ልዩ ኃላፊነት ያለበትን ሥራውን ያከናውናል። ዝምተኛና ድብቅ ሰው ነው፤ ሥጉና ጠንቃቃ። የምሽቱ የጥር ወር አየር ለእሱ አይሞቀውም፣ አይቀዘቅዘውም። ስለተፈጥሮ፣ ስለነፋሻ አየር፣ የማሰቢያ ጊዜ የለውም። ጥበቃ ብቻ! ግዳጅ ብቻ! በእጁ ትንሽ የመገናኛ ሬዲዮ ይዞ መመሪያ ያስተላልፋል፤ መመሪያ ይቀበላል። ወዲያው ጄኔራል (በኋላ ነው ጄኔራል የሆነው) ጌታቸው ሺበሺ በነጭ ፔጆ 504 ከተፍ አሉ። የተጣደፈ ይመስላል። ሻለቃ እሸቱ የትዕዛዝ ወረቀት ተቀብሎ ወደ

ቆሙት መኪናዎች በመሄድ ለሶስቱ ጂፖች አለቆች ትዕዛዝ አከፋፈለ::

በርግጥም ወረቀቱ የውሳኔ ወረቀት ነበር:: መንግስቱ ኃይለ ማርያም የፈረመበትና አንድ ዓይነት አስቸኳይ ትዕዛዝ የያዘ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ:: ትንሽ እንደ ቆየ አንዱ ጂፕ በላንድሮቨሩ ተከታይነት በአራት ኪሎ በር አድርጎ ወደ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ፣ ሁለተኛው ጂፕና ላንድሮቨር ወደ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት፣ ሶስተኛው ጂፕና ላንድሮቨር ወደ ወታደራዊ ፖሊስ እስር ቤት ተፈተለኩ:: ለምን ይሆን ይሄ ሁሉ ሩጫ?

ከዚህ ሰዓት በኋላ ቤተ መንግስት የሞት መንፈስ ያንገዠበበበት የመቃብር ስፍራ መሰለ:: የፍራቻ ፀጥታ ሰፍኗል፤ ጭለማ ነግሷል:: የእኛ የአንጋቾቹ ጥበቃም ተጠናክሯል:: የሚደረገውን ሁሉ በንቃት እየተከታተልን ነበር::

«መንግስቱ የት ገባ?» ትሉኝ ይሆናል:: መንግስቱማ ከዘራውንና የመገናኛ ሬዲዮኑን ይዞ ወደ ደርጎች ክበብ ገብቷል:: ሰውነቱን የበረደው- ስሜቱን የጨፈገገው ይመስላል:: ስለዚህ መጠጥ አስፈልጎታል:: እሱነቱን የሚያደፋፍርለት ፣ሙቀት የሚሰጥ፣ የጨፈገገ ስሜቱን የሚገልጽለት፣ ኮስተር ያለ መጠጥ! ጂን ቀረበለት:: ያኔ ጂን ይወዳል:: ዊንስተን ሲጋራማ ሕይወቱ ነው:: ደረቅ ጂኑን በአንድ ትንፋሽ ጨለጠ፣ ዊንስተን ሲጋራውን መማግ ቀጠለ:: ከምሽቱ አራት ሰዓት አልፏል::

እሽቱ ለጥበቃ ሥራ ከመጣደፋ በቀር አረፍ ብሎ እንኳ አላጣጣውም:: «ሞአ! ሞአ! (አሸናፊ! አሸናፊ!») የሚል የዕለቱ የግዳጅ ሚስጢር ስም ተደጋግሞ በእሽቱ እንደበት ተጠራ:: ሞአም (መንግስቱ መሆኑ ነው) «ይሰማኛል ቀጥል!» አለው::

«እህሉን ስመውቃት አቅርበናል»

«እኔ ስመጣ ይወቃል?»

«ውጪ ውጪ» ትዕዛዙ አበቃ።

ያስቀመጠውን ደረቅ ጂን ስመጨረሻ ጊዜ ጨለጠ። ስው በላ ከዘራውን፣ ብዕር መስል ሽጉጡን። የመገናኛ ሬድዮኑን ይዞ ወደ «መውቂያው» ቦታ ቀጠለ። እኛም ፈንጠር ፈንጠር ብለን ተከተልነው።

«የመውቂያው» ቦታ ፀጥ ረጭ ብሏል። የሬዲዮ ንግግሮች እንኳ አሁን ቆመዋል። ፀጥታው ከጨለማው ጋር እየተጋገዘ የፍራቻ አዚሙን በአካባቢው ላይ አጥልቷል። የሚናገር የሚጋገር የለም። እኔም እብስ ካልኩበት የፀጥታ ባህር ውስጥ የነቃሁት የሻለቃ አሸቱን «ከእንግዲህ አታስፈልጉም! ወደ አቀበቱ ላይ ተመለሱ!» የሚለውን ደረቅ ትዕዛዝ በሰማሁ ጊዜ ነው።

ትዕዛዝ፤ትዕዛዝ ነው። የነገሩን ሁኔታ እዚያው ሁኜ ስመከታተል ብፈልግም አልቻልኩም። እያማረኝ ሊቀርብኝ ሆነ። ቢሆንም ወደታዘዝነው ሥፍራ ተመልሰን ሄድን።

ዋነኛው ትርዒት ተጀመረ። ምንም ጨለማ ቢሆን፣ በቤተ መንግስቱ ዙሪያ የተተከሉት መብራቶች ውጋጋን ዛሬ ላቀረብኩት ምስክርነት የሐቅ ውጋጋን ሆነው ረዱኝ። ትኩረቱ ትዕይንቱ ላይ ተነጣጥሮ ቀረ። አንድ ሰው ተይዞ ወደ ትልቅ የጥድ ዛፍ ስር ቀረበ። «ምን ሊያደርጉት ይሆን?» እያልኩ ስከተል የጥዱን ግንድ አስታቀፉት። ዓይኔን ማመን አቃተኝ። የምመለከተውን ሁሉ አሳንሶ የሚያሳየኝ አይኔ መሆን አለበት ብዬ ስለሰጋሁ ዓይኔን የግድ በልጥጬ በትኩረት ተመለከትኩ። ምንም ለውጥ ግን አላመጣሁም።

የማየው ነገር ከበፊቱ አልተለየም::

መንግስቱ ድምጽ አለባውን ከዘራ እያነሳ ያነጣጥራል እንጂ በከዘራው አይማታም:: ያነጣጥራል:: ግንዱ ላይ እየመጡ የሚለጠፉት እስረኞች አሁንም ይወድቃሉ:: በጣም አነስተኛ የሆነ «ጦሽ!» የሚል የአለንጋ ድምጽ ሰማሁ:: በዚህ ዓይነት ዑደቱ ቀጠለ:: «ጉድ ነው!» አልኩ ለራሴ:: እኔ የማውቀው ከዘራ አባቶች ደከም ሲሉ ለምርኩዝነት የሚጠቀሙበትን እንጂ ከዘራው ድምጽ አልባ ጠመንጃ መሆኑን አላወቅሁም:: ራሴን ማመን አልቻልኩም:: ሆኖም ከስር ሰዎች ተረፍርፈዋል:: ያ ሰው በላ የቤተ መንግስት ቄሳር «በከዘራው» ጉድ ሰረቶአቸዋል::

ያየሁት እንግዲህ ይህን ነበር:: የምሽቱ ትርዒትም በዚሁ ተፈፀመ::

በማግስቱ ድግሱ ተጧጧፈ:: ትላንት የሞት አዚም ያጠላበት ቤት፣ መንግስት ምንም የተለየ አስከፊ ድርጊት እንዳልተፈፀመበት፣ አድብቶ ተራውን ለአስረሽ ምቺው ለቀቀ:: ማምሻውን በደርጉች ክበብ ግብዣው ጦፈ:: አንዱ ጠርሙስ ሲጋባ ሌላው ይከተላል:: ብርጭቆ እየተጋጨ «ድል ለአብዮታችን! ነጭ ሽብር ይደመሰሳል» እየተባለ መጠጡና ምግቡ ይጓዛል:: «አብዮታውያን» እየተያዩ ይሳሳቃሉ:: «ቁጡው መንግስቱ! ቆራጡ መንግስቱ! አብዮታዊው መንግስቱም» ምንም ዓይነት ወንጀል እንዳልፈፀመ ነጭ ጥርሱን ብልጭ እያደረገ፣ ትላንት በሰራው ስራ ሆዱ ይሳለቃል:: በነጋታው ጥር 26ቀን፣ 1969 «አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል! ሕዝቡን ሲከፋፍሉት የቆዩ ቀን ደኛ ፀረ-አብዮተኞች አብዮታዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል!» ተብሎ በግልጽ ተለፈፈ::

ወገኖቼ በድህነት ከንፈር መምጠጥ ብቻ እርባና እንደሌለው በመረዳቴ ነው ይህን የአንድ ሌሊቱን ግድያ ወደ ኋላ ተመልሼ ትውስታዬን የለገስኳችሁ፡፡

እንዲህ ዓይነቱ አረመኔያዊ ድርጊት ወደፊት እንዳይደገም በመፈለጌ ነው ይህን ምስክርነት መስጠቴ፡፡ በሰላም ተፋቅረን የተለያዩ ሀሳቦችን ተለዋውጠን እንድንኖር እሻለሁ፡፡ ለዚህም ነው የትላንቱን መራር ነገር ዛሬ ማቅረቤ፡፡





# ሽሙጥ

ሳሙኤል ተፈራ

«...ይኸኛውንስ መንግሥት እንዴት ታየዋለህ ገ'ገን?» ብዬ ስጠይቀው ገበርዲን ካባውን አስተካክሎ በግዕዝ ተንተባተበ «እንግዲህ ንጉሥ ከሥልጣኑ ሲወርድ የድሮ የቀድሞ ማእረጉን ገፎ እያንቋሸሸ ይናገራል:: የበሰበሰው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት አላለም መንግሥቱ ኃይለማርያም? እርሱን ደግሞ ያባረረው ፋሽስቱ አለው... እንግዲህ ልጄ ሆይ! መንግሥቱ ኃይለማርያምን በማመለከት ከሁሉም ነገር ነጻ ነው:: ትሰማኛለህ አንተ ልጅ? ኮሎኔሉ ከሁሉ ነገር ነጻ! ነጻ! ለምንም ነገር ተጠያቂ አይደለም»

አለኝ::

በጣም ገረመኝና«... ደርግ አልነበረክ? ከስልጣኑም ሆነ ከክብሩ አልተካፈልክ... ርስትህን ቀማህ... ቪላዎችህን ወረሰህ፣ ልጆችህን ገደላቸው፤ እንዴት ይህን ነፍስ ገዳይ ነጻ ነው ትላለህ ዛሬ?» ብዬ ሳልጨርስ በፈገዝ እንደበት «... አይ አንተ ሕጻን፣ ለመፍረድ አትቸኩል:: ትዝ ይለኛል፤ ጃንሆይ መኳንንቱን፣ መሳፍንቱን? ንጉሳዊ ቤተሰቦችን ሰብስበው 'ርስት ለሕዝቡ ይሰጥ' ሲሉ.. ሁሉም 'እንዴት ተደርጐ? የማይሆን ነገር አይናገሩ!' አሉአቸው- ካሰ ራስ እምሩ በስተቀር:: ታዲያ ጃንሆይ ተናደው 'ነጣቂ ይዘዝባችሁ!' ብለው በዚያች አጭር ቁመታቸው ፍንጥር! እንጥር! እያሉ ወጡ:: እንዳሉትም ደርግ መጣና ወረሰው::»

«እውነት ይህንን ብለው ነበር?» አልኩት::

«ቤተ መዘክር ማነው የምትሉት? ኮሌጅ ኢኒቨርሲቲ ሰነዱ ይገኛል:: እና ሲወረስ ንዋዩን እግዚአብሔር ሰጠኝ፣ መልሶ ወሰደ አልኩ» አለና ዝም አለ::

ጥቂት ቆየሁና «ታዲያ መንግሥቱ ይህንን ሁሉ ሕዝብ አስገድሎ እንዴት ነጻ ነው ትለኛለህ?»

«ሎቱ ቴዎድሮስ አይበልጥም... ቴዎድሮስ ክርስቲያን አይሉት አረመኔ፣ እንደ ኔሮን ቄሳር... ክርስቲያኑን ቤት ውስጥ አጉሮ በእሳት ያቃጠለ... በገደል የወረወረ... የእስላሙን እጅ ቆርጦ አንገቱ ላይ እንደ ዲሪ ያሰረ... ሐጂ ሁሴን ኸብሪል ይመስክሩዋ!»

«ደግሞ ማነው ኸብሪሉ?»

«በ1881 ዓ.ም የተወለደ ወሎዬ... የእስላም ሐጂ ...

ትንቢት ተናጋሪ... ስለ መንግሥቱ ኃይለማርያም የተነበዬ... አጤ ኃይለ ሥላሴ አርባ ዓመት ትገዛለች... ትንሽ በመሆኗ አትናቋት... መጨረሻዋ ግን የከፋ ... ሮጥ! ሮጥ! ሮጥ! የሚል ወጥቶ አደር (ወታደር) ከዙፋንዋ ይገለብጣታል:: እርሱም ደርግ ይሰኛል ...»

«ገርን ነግሬህ የለም በትንቢት እንደማልስማማ? ይልቅስ ስለ መንግሥቱ ነጻ ነው ያልክበትን ምክንያት ንገረኝ::»

ሰገነቱ ላይ ነበረና እንደ እሳት ነበልባል የሚያንጸባርቁ አይኖቹን ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት አተኩሮ እያየ

«መልካም የሕይወት ጨዋታ! የክብር ጨዋታ! የሞት ጨዋታ! የዘመን ጨዋታ...

...የትናንቶቹ የት ሄዱ? ቢባል እዚህ ነበሩ! ከደመናው ጋር ሄዱ! ብን አሉ! ከንፋሱ ጋር ጨዋታቸውን ጨርሰው ሃሌ ሉያ ብለው ምድሪቱን ተሰናብተው ሄዱ:: እኔ ብቻ ለወሬ ነጋሪ ቀረሁ ...

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ስምንተኛ ክፍልም አልጨረሰም ይላሉ:: ሆኖም ሻለቃ ማእረግ ደረሰ... ከመንገሱ በፊት ምኞቱ ምን ነበረ? ብትለኝ ሐረርጌ የነበርኩኝ ጊዜ አውቀዋለሁ.. እኔም ግምጃ ቤት አልነበርኩም! ቆዳው ጥቁር ስለነበረ «ባሪቾ» እንለው ነበር ለማቆላመጥ:: ተጫዋች አስቂኝ ነበር::

«አንዲት መሸታ ቤት ነበረች:: እዚያ አየው ነበር:: ብቻውን በበሩ ትይዩ ግራ እግሩን ግድግዳው ላይ አስደግፎ ኡዞ አረቂውን ይጠጣል:: ማንም ዞር ብሎ አያየው:: ብቻውን የሚጠጣ፣ ብቻውን የሚራመድ፣ ደፋር ነው:: እጅብ ብሎ የሚሄድ ፈሪ ነው:: አነር ብቻውን ይሄዳልና! መንግሥቱ

በቅዠት ውስጥ የነበረ፣ በሕልሙ የሚኖር፣ ሕልሙ ሆኖ ቅዠቱ ግልጽ ያልሆነለት ሆኖአልና 66 መጣ።

«እርሱና መንግሥቱ ገሙቹ የአንበሳውን ክፍለ ጦር እንዲወክሉ ተመረጡ። ሻለቃው ለክብር ሲል በሞቱ ተወራረደ፤ ማለት እዚህ ጨዋታ ውስጥ ዘው ብዬ እገባለሁ ብሎ ከራሱ ጋራ ቃል ኪዳን ገባ። እራሱ እንዳለው... ከዘለዓለም ባርነት የአንድ ቀን ነጻነት! ይቺ ቃል እውነተኛው ቃሉ ነበረች። በአርአያም አረጋገጣት። ፊቱ የቆሙትን ሁሉ ደመሰሰ... አማን እምደምን በኤርትራ ምክንያት ገደለው ... ተፈሪ በንቲን በኢህአፓ። ታዲያ አጥናፉ ይህንን ሲሰማ 'ይኸ ሰው ጨረሰን አይደለም እንዴ!?' ስለአለ እርሱንም ገደለው። ክብሩን ለራሱ ጠቅልሎ ያዘ» አለና ጸጥ አለ።

አሰብኩኝ። «የክብር ጨዋታ!» ማን መንግሥ የማይፈልግ አለ? የመንግሥ እድል በሯን ከከፈተች? ናፖሊዮን እንዳለው «የወደቀ ዘውድ አገኘሁ በራሴ ደፋሁት» ንጉሥነስ ማን ይጠዳል? እያልኩ አሰብኩኝ። ከዘለዓለም ባርነት ያንድ ቀን ነጻነት!! እውነቱን ነው፤ የተመኘውንስ አሳክቷል። አስራ አራት ዓመት በኢትዮጵያ ላይ ነገሰ። የልቡን ፈጸመ። ምኞት ተፈጸመች። ሕልም እውነት ሆነ፤ ማለት እንዲህ ነው እንጂ!! እያልኩ ሳሰላስል ገርን፤

«የሚጠጣ አለህ ልበል?»

«የለም... ካለውህ በስተቀር» አልኩት።

«ደህና! ቡና አስፈላ፣ እጣንም አስጭስ» አለኝ። ከአክስቴ ከእመቤት ሆይ ተበድሬ እንግዳ ተቀባይቱን ሞግዚቷን ቡና ታፈላ ዘንድ አዘዝኩኝ።

ከሰገነቱ ወደ ቤት ስንገባ «ኖር! ኖር! ኖር!» አለች አክስቴ፣

«በእግዜር» ብለን ቁጭ አልን፡፡

ሞግዚቷ በፍጥነት ጉዝጓዙን ጎዘጎዘች፡፡ እጣኑንም አጨሰች፣ ቡናውም መቆላት ጀመረ፡፡ እመቤት ሆይ ያው የተለመደውን ጥቁር በጥቁር ለብሳለች፡፡ አይኗን በአንድ ቦታ ተክላ ጾጥ ብላለች፡፡ ገርንም የእጣኑን ፈለግ እየተከተለ ከጢሱ ጋር የግል ንግግር የሚያደርግ ይመስላል፡፡ ትንሽ እንደቆየን የበሩ ደወል ተደወለ፡፡

«ዕጣን አመሳከተ፣ ብሎ የለ ቅዱስ ያሬድ» ሲል፣

«ቡና ሲቆላ የሚመጣ እንግዳ የሚወዱት ሰው ነው» አለች አክስቴ፡፡

«ገርን» አልኩት፡፡

«ምንድነው?»

«አንዴ የፓርቲው ምስረታ ጊዜ የአፍሪካ መሪዎች በበዓሉ ላይ ነበሩ፡፡ የዛምቢያው መሪ ኬኔት ካውንዳ ምን አሰው መሰለህ?! 'እናመልክዎታለን!' ወደ እንግዶቹ ዞር ብሎም 'አንድ መሪ! አንዲት ኢትዮጵያ!' ብለው እንዲጮሁ አደረጋቸው» አልኩት፡፡

«...ታዲያ ይህ ሰው ምን አጠፋ!? በቅዠት ላይ ቅዠት፤ ሰው ሰውን ያሳብደዋል፡ ያልሆነውን ነህ ይሉታል፡፡ እኛስ ብንሆን ጃንሆይን 'ቅዱስ! መልአክ! ጸሐዩ ንጉሥ' ብለን አልነበረም?! ጋሻ ጃግሬና አጋፋሪ የማይቀባጥረው ነገር የለም- ለመሾም፡፡ ለሌላ ጉዳይ እንኳን አይደለም! ምስሉ በያለበት ተሰቀለ! ጣኦት ሆነ! ምን ይሆናል የንጉሥነት ክብር ሳያገኝ፣ በመኪናው ውስጥ ተወሽቆ! እንደ ጃንሆይ በግልጽ ሳይጓዝ ...


እንደ ተሸማቀቀ ከዛሩ ብንን ሲል 'እውነት ኢትዮጵያ ላይ ነግሼ ነበር? ታዲያ ለምን ሲገሉኝ ይፈልጋሉ? ምን አጠፋሁና?' ...» እንዳለ ቡናውን ፉት ብሎ «እያቱ አሁንም ሆስታ አለች ሲሉ ሰምቼአለሁ፤ ቀንጆዬ ብልጥ:: የእመቤቱ (ንግሥት ዘውዲቱ) ዣንጥላ ያዥ ነበረች:: ብልጥ ስለሆነች ጦጢት ነው የምንላት... የጦጢት የልጅ ልጅ በቀትር በሮቢላኑ ጭልጥ ብሎ ጠፋ! ዱሮም ወሮበላ ነበረና:: እንግዲህ ልጁ ሆይ በዛር ውስጥ እያለ ቢገድል፣ ቢያስር፣ ቢበድል ትፈርድበታለህ? በፊቱ ተሰብስበው የነበሩት ናቸው ጥፋተኞቹ... ብቻ ምን ያደርጋል? እነርሱም ባለዛር ናቸው...» አለና ዝም አለ::

እመቤት ሆይ ቀጥላ «ይህን የገባር ልጅ አንዳንዴ አልፈርድበትም:: እግዚአብሔር የኛን ግፍ አይቶ 'ካለ ሰለሞን ዘር በስተቀር ንጹህ የለም' ስንል፣ ስንመካ፣ ስንወጠር አምላክ የልባችንን እብሪት አይቶ የምንንቀውን አነገሰብን::»

«ባያመልጥ ኑሮ እንደ ላይቤሪያው መሪ ሳሙኤል ዶ በካራ ተቆራርጦ መንገድ ዳር ይወረወር ነበር:: ግን ለምን ቴዎድሮስን እንደምሳሌ ይጠራ ነበር?» ዣንን ጠየቅሁት::

«ቴዎድሮስ ዙሪያው ገደል ሆነበት:: በዚያች ሰዓት መልአክ መጥቶ ና አድንሃለሁ» ቢለው ቴዎድሮስ በክንፉ ላይ ተንጠልጥሎ በጠፋ ነበር:: መንግሥቱ ድንገት ክብር አገኘ:: በድንገት ጥሏት ጠፋ ...»

እመቤት ቀጥላ «እንግዲህ ገብርኤል መሸሸጊያ እንደ ሰጠው (ጋብርዬል ሮበርት ሙጋቤን ማለቷ ነው) እሱ ይጠብቀው... እሳልፎ ከሰጠን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ዘቅዝቀን እንሰቅለዋለን:: ያ ለገሡ አስፋው ብቻ ያለማምለጡ::»



# በርሜሉ አይሞላም

## ተስፋዬ ገብረአብ

ድንገት የቅርብ ወዳጄ ለመሆን ስለበቃ አንድ ጉረቤቴ ላውጋችሁ:: ሚካኤል ይባላል፡፡ ሰዎች ግን ባጭሩ ማይክ ይሉታል:: እድሜው ከአርባ አምስት አይበልጥም:: ቁመናው መለሎ፤ መልከ ቀና፣ ጨዋታው ቀልብን የሚሰርቅ አይነት ነው:: የዚህን ሰው ሙሉ ታሪክ ለማውጋት ገፅ ስለማይበቃኝና አሰልቺም እንዳይሆን ትረካዬን እንዲያው እንደነገሩ ከመካከሉ ላይ መጀመሩን እመርጣለሁ::

ጊዜው ከዛሬ ሶስት አመት በፊት ነው። የአመቱ አጋማሽ። እለተ ቅዳሜ። እንደወትሮው አመሻሽቴ ወደ መኖሪያ ቤቴ ስገባ ሰራተኛዬ በጣም ተጣድፋ፣

«ማይክ ቀኑን ሙሉ ሲፈልግህ ነው የዋለው። ከመሽ እንኳዋ ሰባት ጊዜ ሰው ላከ» አለቺኝ።

«ምን ሆነ!?» አልኩዋት ደንግጬ። ለስራ ጉዳይ ደሴ መሄዱን አውቅ ስለነበር አደጋ የደረሰበት ነበር እየመሰለኝ።

«ኧረ ምንም አልሆነ። ግብገና ቢጤ መሰለኝ። ከደሴ ሚስት ይዞ መጥቶአል። ጉረቤቱን በጠቅላላ ራት ጋብዞአል» ስትለኝ ፈገግ ለማለት ተገደድኩ።

ለነገሩ ደስ ነበር ያለኝ። ጣሊያን ሀገር ያለች ፍቅረኛውን እያነሳ ሲብከነከን ነበር የኖረው። ባገኘኝ ቁጥር ስምዋን አንስቶ ከማወደስ ወደሁዋላ አይልም። ብስለትዋ - ብልህነትዋ - ደምግባትዋ - አስተዋይነትዋ - ሀቀኝነትዋ - ታማኝነትዋ - አፍቃሪነትዋ - ሩህሩህነትዋ - ቆራጥነትዋ - ቅንነትዋ - ቅጥነትዋ - ሀገር ወዳድነትዋ - ቁጡነትዋ (ሲመጣባት) - እያለ መከራ አሳይቶኝ ነበር። በቦታ ርቀት ተለያየን እንጂ በመካከላችን የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እንከን የለም፤ ፍቅራችን እንደሰብለ ወንጌልና በዛብህ ነው እያለ ፍዳ አሳይቶኝ ነበር። እንግዲህ ጉጉ ለመቀለስ ከበቃ ተመስገን ነው ብዬ አሰብኩ።

የደስታው ተካፋይ ለመሆንም እየተጣደፍኩ ወደ

መኖሪያ ቤቱ ሄድኩ:: ቤቱ ሞቆ ጠበቀኝ:: የሳንቃው ወለል ላይ ቀጤማና ቢጫ አበባ ተነስንሶ አሸብርቆአል:: ቤቱ የእሰተ - እንቆጣጣሽን ጠረን ይዞአል፣

ማይክ ገና ሲያየኝ ብድግ ብሎ አቅፎ ሳመኝ:: በዚያ ስፌድ መዳፉ ጀርባዬን እየጠበጠበ፣

«እኔ ወንድምህ፣ እቴጌ ጣይቱን የመሰለችውን ከደሴ ይገፍ ከተፍ ነዋ! ከእንግዲህ ጥፍጥ ያለች ቆንጆዬ ኑሮ ብቻ ነው የምፈልገው:: አይመስልህም?» ሲል ወተወተኝ::

ተስማማሁ:: ወስዶም አስተዋወቀኝ:: ደነገጥሁ:: በጣም ደነገጥሁ:: ትንሽ ልጅ ናት:: ከአስራ ስድስት አመት አይበልጣትም:: ፈገግታ የሚቀናት ውብ ልጅ ናት::

ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ፣

«በእድሜ በጣም ትራራቃላችሁ» አልኩት::

ማይክ ይህን አስተያየቴን ተቃወመ:: «እድሜ ምንድነው?» ሲል አፋጠጠብኝ::

እንዲያውም ሊያሳምነኝ ቀርጦ ተነሳ፣

«ፍቅርን እድሜ፣ ሀይማኖት፣ የፖለቲካ ልዩነት፣ ዘርና ቀለም አያግደውም» በሚለው የመንደርደሪያ ሃሳብ ጀምሮ፣ የግማሽ ሰአት ትምህርታዊ ማብራሪያ ሰጠኝ:: ትምህርቱን በፀጋ ተቀብዬ ወሬ ለመለወጥ ያህል፣

«ጣሊያን ሀገር ያለችው ፍቅረኛህ ተረሳች ማለት ነዋ!»

የሚል ወግ ቢጤ ጣል አደረግሁ፣

ማይክ ምላሽ ለመስጠት ተጣደፈ፣

«እስካሁን ሳታገባ ትቀራለች ብለህ ነው? ዞረም ቀረ ግን ይህቺን ከዚያች ማወዳደር ከቶ አይቻልም። ይህቺ እኮ ንፁህ - ቅን - ብልህ - መልከመልካም - ደግ - አዛኝ - የዋህ - ጣፋጭ - ቁጥብ ናት። የዚያች ልብ ግን አይገኝም። ወላዋይ ነበረች።»

ከልቤ ሳቅሁ። ማይክ ሊያሳምነኝ ይጥር ገባ።

«እውነቱን ነው... ምንም አላጋነንኩም» ብሎ ሲጀምር አቋረጥኩት።

«የጣልያንዋ ጉዋደኛህ ታማኝ እንደነበረች ደጋግመህ አጫውተኸኛል» ብዬ አፋጠጥኩት።

«ምን መሰለህ?» አለኝ ማይክ «... ታማኝነት ሊኖራት ይችላል። ግን ታማኝነት ብቻውን ምን ይፈይዳል? ድመትም ታማኝ ልትሆን ትችላለች። ማወዳደሪያችን ታማኝነት ብቻ ሊሆን አይገባውም። ይህቺኮ መልአክ ናት። አይቶህ አትጠግባትም። ይህን እድል ማግኘቴ ደግሞ ፀጋ ነው»

«ቀደም ሲልም ጣልያን ስላለችው ጓደኛህ ውበት ሚሊዮን ጊዜ ነው እያደነቀህ የነገርከኝ» አልኩት።

«ምን ዋጋ አለው ታዲያ? ውበት ብቻውን ለግርግዳ ጌጥነት ነው የሚያገለግለው። ያቺ ሰው ውብ ብትሆንም

መንቻካ ነበረች:: ብዙ ጊዜ እንጋጭ ነበር:: በወሬ ጨርሶ ተጣጥመን አናውቅም::»

«ጨዋታዋና ለዛዋ ማር ነው ብለኸኝ አልነበር እንዴ?» ብዬ በነገር ወጋ አደረግሁት::

ማይክ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣

«ጨዋታዋ መልካም ሊሆን ይችላል:: ግን የሰው ልጅ እድሜ ልኩን ሲጫወት ይኖራል እንዴ?» ሲል ጠየቀኝ::

«የተማረች ናት ብለኸኝ ነበር:: አንተም ከፍተኛ ምሁር እንደመሆንህ ቁምነገሩ ላይም ልትግባቡ እንደምትችሉ ነበር የሚገባኝ::»

«እንዳልከው ከፍተኛ ምሁር መሆኔ ግልፅ ነው» ካለ በሁዋላ ድምፁን ረገጥ አድርጎ «...ትዳር መመስረት ግን የምርምር ጣቢያ ማቋቋም ማለት አይደለም:: ከተዋደድክ ይበቃል:: ትኖራለህ:: ትዳር የተማረ የሰው ሀይል የሚፈልግ ዘመናዊ ኩባንያ አይደለም:: መመዘኛው መፋቀር ብቻ ነው:: በቃ:: ከጐርኪይ መፅሀፍ ላይ ያገኘሁትን አንድ ቁም ነገር ልንገርህ ያታው ወንድ ለሆነ ለአንድ ለፍቶ አዳሪ ዜጋ፣ በዚህ አለም ላይ የሚያስፈልጉት ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው:: ጠማማ ጉጆና ሴት:: ሌላ ቦታ ያነበብኩትን ደግሞ ልንገርህ፣ የሰው ልጆች በሶስት ይከፈላሉ፤ ወንድ፤ ሴት፤ የተማረች ሴት:: ተግባባን? ስለዚህ ወስኛለሁ:: እግዚአብሄር ደሴ ላይ እንደፈጠራት ካገኘሁዋት ከዚህች ቅን ሴት ጋር አብሬ ልኖር

ቆርጭያለሁ።»

የባጥ የቆጡን ስንቀበጣጥር ቆየንና ራት ቢጤ ቀማምሰ ለመሄድ ተነሳሁ። ማይክ በእርግጥም በደሴዋ ጉብል የአካል ውበት ተማርኮአል። በየደቂቃው እንደ አሽንጉሊት ይነካካታል። በፈገግታ ተጥለቅልቆ በሞቀ የወደፊት የትዳር ህይወት ህልም ተውጦ፤ ፈገዞ በተስፋ እያያት ይፈነድቃል። ትእግስት ማጣቱን አስተዋልኩ። ለራት በጠራቸው እንግዶች ፊት ደጋግሞ ሲስማት ተጋባዡ እየተጠቃቀሰ፤ እየተጕሻሸመ ይስቃል። ጠጉሩ ላይና ጢሙ ላይ የነበሩትን የሽበት ዘለላዎች አጣሁዋቸው። ወጣት ይመስል ዘንድ በጥቁር ቀለም አመሳስሎአቸው ኖሮአል። እንዲሁ አመሻሽተን ተለያየን፤

በሁለተኛው ወር ግን ያልታሰበ ሁኔታ ተፈጠረ። አንድ ማክሰኞ እለት ማምሻውን ማይክ ጋን ጋን እየሸተተ ድንገት ቤቴ ከተፍ አለ። ፊቱ የተጠበሰ ጉበት መስሎአል። ከባድ ችግር እንደገጠመው ለመረዳት አላዳገተኝም።

«ባለቤትህ ደህናም አይደለች!?» ነበር ያልኩት ተሽቀዳድሜ።

ማይክ ግን ለጥያቄዬ ምላሽ በመስጠት ፈንታ ግንባሩን ጉልበቶቹ መካከል ቀብሮ ደጋግሞ ፊቱን ይሞዠርቅ ጀመር። ተስፋ መቁረጥ ገፅታው ላይ አነበብኩበት። ተጕሳቁሎአል፤

«ምን ሆነሀል ማይክ!?» ብዬ የገጠመውን ችግር ይነግረኝ ዘንድ ወተወትኩት፡፡ ትክሻውን ይዤ አርገፈገፍኩት፡፡ በመጨረሻ ችግሩን ተነፈሰ፣

«ያቺን ውጫጭ ለእናቷ አስረክቤ መጣሁ!» ብሎ ዱብ እዳ አወረደብኝ፡፡ በርጋታ ወደ መቀመጫዬ ተመለስኩ፡፡ ቃል አልተነፈስኩም፡፡ ዳሩ እሱም ወሬውን ከጀመረ ወዲያ በሩ እንደ ስለተከፈተለት የገጠመውን ችግርና የፈፀመውን ለመዘብዘብ ጉትጉዋች አላስፈለገውም፣

«... ምንም ላደርግ አልቻልኩም» ሲል ቀጠለ ማብራሪያውን «ከሁለት ነገሮች አንዱን መምረጥ ነበረብኝ፡፡ ጨርቋን ጥዬ ማበድ፣ አሊያ ለእናትዋ ወስዶ ማስረከብ፡፡ ስማኝ ውድ ወዳጄ፣ በዚህ እድሜዬ ማበድ አለብኝ? ጉልማሳ ነኝ፡፡ ተምሬያለሁ፡፡ ከፍተኛ ምሁር እንደመሆኔም ሀገሪቱ ከኔ እያሌ ቁምነገሮችን ትጠብቃለች፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜና ወቅት ከህፃናት ጋር በጠጠር ቅልልቦሽ ብጫወት የታሪክ ተወቃሽ አልሆንም? ንገረኝ? አስተያየት እንድትሰጠኝ ደሞ እሻለሁ፡፡»

«በምንድነው ያልተግባባችሁት?» ስል ጠየቅሁት፡፡

«በምንም ነገር መግባባት አልቻልንም» ሲል ጮኸ፡፡ «... እንዲያውም እኔን ለማሳበድ ሆን ብላ የተላከች ልትሆን ትችላለች፡፡ እግዜር ያሳይህ ... ማታ ማታ ትልቁ መዝናኛዋ የኔን ሽበት መቁጠር ነው፡፡ እኔ ስናደድ ደሞ እሷ ትደሰታለች፡፡ በሰው ንዴት የምትደሰት እባብ ናት፡፡ እንባዋ ጉንጩዋን

እስኪያስብሳት ድረስ ትስቃለች፡፡ እኔ ደግሞ ማንም እንዲቀልድብኝ አልፈልግም፡፡ ተቀልዶብኝም አያውቅም፡፡ ወደፊትም ማንም ቢሆን፣ በምንም መልኩ ይቀለድብኝ ዘንድ አልፈቅድም፡፡ አቋሜ ይኼው ነው፡፡»

«ይኸው የሽበት ቀጠሮ ጉዳይ ብቻ ነው ያጣላችሁ?»

«ምን ይሄ ብቻ፡፡ በየቀኑ ንትርክ ነው፡፡ ገና ወፍ ላይጮህ ተነስታ ዛሬ ባቡር ማየት እፈልጋለሁ ትለኛለች፡፡ እግዜር ያሳይህ፣ ይሄ አንካሳ በቅሎ የመሰለ ባቡር ምኑ ይታያል? በርግጥ ባቡር በደሴ በኩል ስለማያልፍ ባቡር ማየት ሊያጓጓት ይችል ይሆናል፡፡ ግን እኔን የሚያህል ትልቅ ሰው፣ ሹካ የምታክል ሴት ልጅ አንጠልጥሎ አሮጌ ባቡር ሲያስጎበኝ ሰው ቢያይ ምን ይላል?»

«ይሄም ቢሆን ለፀብ የሚያበቃ አይደለም» አልኩት፡፡ ማይክ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ቁልቁል እያየኝ ይጮህብኝ ጀመር፣

«ከዚህ በላይ ምን ልሁን? ከስራ ስመለስ ከሰፈር ህፃናት ጋር ተሰብስባ በጠጠር ቅልልቦሽ ስትጫወት ሁለት ጊዜ ያዝኩዋት፡፡ ገና ስታየኝ ደግሞ እንደቢራቢሮ በራ ትደበቃለች፡፡ ወጥ ቤት ካርቶን ውስጥ ገብታ ተሸሽጋ፣ እሷን ፈልጌ ለማግኘት አታምነኝም አርባ ደቂቃ ወሰደብኝ፡፡ እኔ አባት ነኝ ባል? 'ለምን ትሸሽያለሽ?' ስላት 'ፈርቼ' ትለኛለች፡፡ እኔ ምኔ ያስፈራል? አውሬ ነኝ? ጉርጥ ነኝ?

እኔ ተናካሽ ውሻ ነኝ የምትፈራኝ? ምን ለማለት ፈልጋ ነው? በስዋ ምክንያት የሌለብኝን የበሽታ አይነት ጨመርኩ:: የግራ ጉኔን ቀስፎ የሚይዝ ህመም በአንድ ወር ውስጥ ሸመትኩ:: ስለዚህ ወደፊት ልፈፅም ያሰብኩትን ጋብቻ ሰርዤ፣ አንጠልጥዬ ደሴ ወስጄ ለእናትዋ አስረክቤያታለሁ:: ቢሻቸው ይክሰሱኝ:: ካሳ ከተጠየቅሁም እከፍላለሁ:: ከስዋ ጋር ከምኖር ግን ወህኒ ብወርድ እመርጣለሁ:: በዚህ እድሜዬ ለምን ልቃጠል? ገና የአርባ አራት አመት ሰው ነኝ:: ከእንግዲህ ብዙ መኖር እችላለሁ::እዚህ አገር በጥሩ ሁኔታ ራሱን የጠበቀ ሰው እስከ ሰባ መዝለቅ ይችላል:: ሰማንያ ድረስ በጤና የሚቆዩም ሞልተዋል...»

ይህ ሁኔታ በተፈፀመበት ሰሞን ከከተማ ውጪ ለስራ ወጣ ብዬ ሰነበትኩ:: ከስድስት ወራት ቆይታ በሁዋላ ስመለስ ማይክ ቤቱን ለመልቀቅ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን ሰማሁ:: ቤቱን የሚለቅበትን ምክንያት ግን የሚያውቅ እንደሌለ ሰራተኛዬ አወጋቺኝ:: ጉዳዩ ስለከነከነኝ በቁሜ ወደ ማይክ ቤት ጉራ አልኩ:: በርግጥም የቤት እቃዎቹ በካርቶን ተጠርዘው ተቀምጠዋል:: ማይክ ገና ሲያየኝ ከተቀመጠበት ብድግ አለ፣

«እንኩዋን አገኘሁህ፤ ሳልሰናበትህ እሄዳለሁ የሚል ስጋት ነበረኝ::» ካለ በሁዋላ የሞቀ ሰላምታ አቅርቦልኝ እንድቀመጥ ጋበዘኝ:: ቤቱን የሚለቅበትን ምክንያትም ያወጋኝ ጀመር:: አሁንም በተስፋ ተሞልቶአል:: በራስ

የመተማመን መንፈስ አልተነካም። እንደተለመደው እሱ ሲናገር እኔ አዳምጥ ጀመር፣

«... እነሆ በመጨረሻ ግጣሜን አገኘሁ» ብሎ ነበር የጀመረው «... አዎን ይህቺ ስክን ያለች ናት። ለጋብቻ የሰከነ ፍቱን ነው። ያቺ ውጪጭ ጨርቁን ልታስጥለኝ ነበር ያሰበችው - አልተሳካላትም። እግዜሩም ሳይደግስ አልተጣላኝም። የአሁንዋ ግን በውነቱ የተመረቀች ናት። ምራቋን የዋጠች ነጋዴ ናት። የግል ቤት አላት።ሁለት መኪና አላት። ብስል ሰው ነች። የተማረች ባትሆንም ከህይወት ብዙ ልምድ ቀስማለች። በርግጥ እድሜዋ ሄዶአል። የኔም ቢሆን ግን ተራምዶአል። ለኔ ግን ጥሩ ትመስለኛለች። አንዱን መኪና እንደምትሰጠኝ ነግራኛለች። ይሄ ትልቅ እድል ነው። ከዚህ በላይ ምን እፈልጋለሁ? በርግጥ ትንሽ ቆምጨጭ ያለች ናት።አንዳንዴ ትቆጣለች።...»


«ይሄ ነገር አላማረኝም፤ ወደ ሌላ ሀሁት ውስጥ እንዳትገባ? ነፃነቷን ተገፈፍክ፤ ጁኒ ቁልቁዋል የመሳሰሉ ሰበቦችን እንዳታበዛ» ስል ምክር ቢጤ ጣል አደረግሁለት።

ማይክ ግን አልተቀበለኝም።


«... አይምሰልህ» ሲል ምክሬን አጣጣለው «... ምቾት ካለ ፍቅር አለ። ሰዎችን የሚያጣላው ድህነት ነው። ዞረም ቀረ ይቺ የምልህ ሰው፣ ያን ያህልም በእድሜ የገፋች አይደለችም። ሀምሳ ቢሆናት ነው። በልጅነትዋ የነበራት

ውበትም ቢሆን ጨርሶ አልጠፋም:: የውበትዋ አሻራ ገፅታዋ ላይ ደብዝዞም ቢሆን ይታያል:: ዋናው ደግሞ መግባባት ነው:: በዚህ ላይ እንደምታውቀው እኔ የማደርገውን በትክክል የምገነዘብ ሰው ነኝ:: ብዙውን ጊዜ አሻግሬ ነው የማየው:: አይመስልህም?»

በዚሁ ተለያየን:: ከዚያ ወዲያም ጨርሶ አጊኝቼው አላውቅም:: አገኘው ዘንድ ግን እመኛለሁ:: ማይክን ሳስታውስም ሁለት ነገሮችን አያይዤ አስባለሁ:: ትእግስትና ተስፋ:: ማይክ ትእግስት የለውም:: ብቻ ዘወትር በተስፋ ይሞላል:: ዳሩ ግን ትእግስት ባልታከለበት፣ በተስፋ ብቻ መሞላት ወደ ተበሳ በርሜል ውሀ እንደመገልበጥ ይቆጠራል:: በርሜሉም ለዘልአለሙ አይሞላም...



# የመስተንግዶ ልዩነት



# ትዳር በእደሳ

## ከአብዱል ቃድር አውልጆ

በ1969 ከሶማሊያ ጋር ግጭት በመፈጠሩ፣ ከወሎ አውራጃዎች አምስት ሻለቃ የሚሆኑ አርሶ አደሮች ታፍሰው ያንድ ወር ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ ለሶስት ወራት ብቻ እንደሚቆዩ ተገልጦላቸው፣ ለጥበቃ ጉዳዬ አውራጃ ተሰማሩ:: ግና ሶስቱ ወራት ተረሳና እስከ 1972 ከሶስት ዓመታት በላይ ቆዩ:: ከዚያ በሁዋላ ግን የአካባቢው ሁኔታ በመረጋጋቱ የመመለስ ተስፋቸው እንደገና

ለመለመ:: የወቅቱ ባለስልጣኖችም ከጉዴ በስተ ምዕራብ ዋቢ ወንዝ ዳርቻ አማገኘው ሜዳ ላይ ሰብስበዋቸው፣ መሳሪያቸውን እንዲያስረክቡ ጠየቋቸው:: Cክክቡ እንዳበቃም ለአይን በሚታክተው አውላላ ሜዳ ላይ ሰፍረው በአምራችነት እንዲኖሩ መወሰኑ ተገለጠላቸው::

ገበሬዎቹ ማሊሻዎች ያልጠበቁት ነገር በመወሰኑ ቅሬታቸውን በተለያየ መንገድ መግለጽ ጀመሩ:: «ግዳጃችንን ስለ ፈጸምን፣ ወደ ልጆቻችን መልሱን»

«ለውትድርና ተግባር እንጂ ለርሻ ስራ ስላልመጣን አናርስም» በማለትም አመፅ ቀሰቀሱ::

በሁለተኛው ቀን ጉዴ የሚገኘው መደበኛ ሰራዊት ተንቀሳቅሶ አማጽያኑን በታንክና አየር መቃወሚያ ከብቧቸው አደረ::

ንጋቱ ላይ መደበኛው ሰራዊት ሁሉንም ከተኙበት እየቀሰቀሰ ሰባሰባቸው:: በሄሊኮፕተር የመጣው የሻለቃ ማዕረግ ያደረገ የደርግ መኮንንም ፀረ-ሰፈራ የሆኑትን አሳልፈው እንዲሰጡ በቁጣ አዘዛቸው:: ዳሩ ግን ጥያቄው የሁሉም ስለነበረ የሚጋለጥ ሰው ጠፋ:: ይኸኔ ሻለቃው ወታደሮቹ የመሰሏቸውን አስራ አምስት ሰዎች እንዲያቀርቡ አዘዘ:: እነሱም አይናቸው ያረፈባቸውን አውጥተው አሰለፉ:: ሻለቃው ጸረ-አምራች ስለመሆናቸው አጭር ንግግር ካሰማ በኋላም እተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በመትረየስ ታጨዱ:: ከዚያም መኮንኑ «አሁንስ አልሰፍርም የሚል አለ?» ብሎ

አፈጠጠባቸው።

«ማስቶቻችን!» የሚል ድምፅ ከቤቱ ተስተጋባ።

«ይመጡላችኋል» ተባሉና በአምስት መንደሮች፣ ማለትም ኢረር፣ ጆረር፣ ፋፌም፣ ወልወልና መሸኮኬ እንዲሰፍሩ ተደረገ። ሆኖም የጠየቁት ሳይፈጸምላቸው ሁለት ዓመት በማለፉ እንደገና አመጽ ተቀሰቀሰ፤

«ማስቶቻችንን!»

በዚህን ጊዜ ግን ደርግ ሃይል አልተጠቀመም። ይልቁንም «ባለቤቶቻችሁ መጥተዋልና ተስልፋችሁ ተቀበሉአቸው» ስለተባሉ እየፈነደቁ ተሰለፉ። ሆኖም የወንዶቹ ቁጥር ከሴቶቹ ስለሚበልጥ፣ ሽሚያና ብጥብጥ እንዳይፈጠር በመስጋት በቅደም ተከተላቸው መሰረት ጠመንጃ የያዙ ሰዎች ሚስቶች አደሏቸው። የደረሰው ደረሰው፤ ያልቀናውም ቀረበት። በቃ!

እንባ የሚራጩትን ሴቶች ግን ዞር ብሎ ያያቸውም አልነበረም። ወይዛዝርቱ ተረብሸዋል። መውጫ ቀዳዳ የሚፈልጉ ይመስላሉ። ዙሪያውን ቢቃኙት ግን በወታደርና በዋቢ ወንዝ የታጠረ በመሆኑ፣ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም። አካፋና ዶማ ታድሏቸው በትጋት እንዲሰሩ ታዘዙ። እንቢተኞች ከወታደራዊ ቅጣት እስከ እርጩሚ ያለችዋን ስለሚቀምሱም ቀናደፋ ማለቱ የግድ ሆነ። እጅግ የተማረሩቱ፣ ከአፍ እስከ ገደፉ የሞላው ዋቢ ወንዝ ውስጥ ሰጠሙ። ሌሎች በተለያዩ ዘዴዎች ሊሾልኩ

የሞከሩም በአውሬ ተበሉ። ቀሪዎቹ የደርግ ወታደር የጥይት ራት ሆኑ።

ታዲያ እኒህ እህቶቻችን ከየት እንደታፈኑ ያውቃሉ? ጉዳዩ እንዲህ ነው። ለድሬዳዋና ሐረር ከተማ ስራ ፈላጊዎች ማስታወቂያ እንዲወጣ ይደረጋል። ክፍት የስራ ቦታዎቹም ለሴቶች ብቻ መሆናቸው ስለተጠቀሰ፣ እስራ ሁለተኛ ክፍልን ያጠናቀቁ በርካታ ኰረዳዎች ይመዘገባሉ። በተጨማሪም ለሴተኛ አዳሪዎች ሌላ ማስታወቂያ ይወጣና በርካታዎቹ ይመዘገባሉ። ደርጉም ባንድነት ይሰበስብና በአይሮፕላን ጭኖ ጉዶ ይወስዳቸዋል። ከጉዶም በትራክተሮች ተጭነው ከተጓዙ በኋላ፣ በሁለት ረድፍ ተሰልፈው ታደሉ።



# እንደገና እንወለድ

**ሲሳይ ንጉሱ**

መቼም ሞታችንን መካድ አይቻልም። በከተሞት ክልል ተሰባስበን ለመንግስት አፍንጫ የቀረብን አብዛኛዎቻችን በቁማችን ሞተን ቆይተናል። አሟሟታችን «ዘመናዊ» በመሆኑ አይታወቀንም። ደግሞም ሬሳ ሳጥን ውስጥ አልገባንም። ሰብአዊ መብታችን ተረግጦ፣ ሰብዓዊ መብቶችን ብንረግጥም፣ ህሊናችን ተሸጦ፣ የሌሎችን ህሊና ብናሸጥም ውሸት ተምረን፣ ለሌሎች ውሸት ብናስተምርም፣ ስርቆትንና ክህደትን ተከነን፣ ሌሎች እንዲካኑበት ብናደርግም፣ ታውረን

ሌሎችን ብናውርም፣ ተዋርደን ሌሎችን ብናዋርድም... ይህንና የመሳሰለውን ሁሉ ብናደርግም፣ መብላት መጠጣታችን፣ መተኛት መነሳታችን፣ መቆም- መራመዳችን አልቀረም:: ይህ ነበር የቆምን ያስመሰለን:: መርጠን መብላት ሳይሆን ማግበስበሳችን፣ መተኛት ሳይሆን ማንቀላፋታችን፣ መራመድ ሳይሆን መንሳፈፋችን ሲወደስ ደግሞ ሞታችንን ዘመናዊ ያደርገዋል:: ህሊና ከበሰበሰና አጥንት ውስጥ ውስጡን ከፈራረሰ በኋላ፣ ቆዳን የቆዳ ስፌት እያሰበሱ ማጊያጌጥና ስጋን በስጋ ለማቆየት ማግበስበስ ዘመኑ የወለደው ዘመናዊ ሞት ነው::

«አልሞትንም» የምንል ከተሜዎች እንኖር ይሆናል:: በእርግጥም ደግሞ ያልሞቱ ጥቂት ንፁህን ይኖራሉ:: ይህንን ማወቅ የምንችለው ራሳችን፣ ለራሳችን ቅንና ግልጽ ሆነን፣ ራሳችንን ሚዛን ላይ አስቀምጠን ያየነው እንደሆነ ነው:: ያልተሸራረፈ ሚዛን መጠቀምም ያስፈልጋል::

የህይወት ጥማታችን ምን ነበር? የህያውነት መመዘኛችን ምን ነበር? ስለሌሎች ያለን ግምት እንዴት ነበር? ኑሮን ለማሟላት የምንፈልገው በምን መልኩ ነበር? በላባችን? በደማችን? ወይንስ በሌሎች ላብና ደም? ወይንስ በስርቆት? ለህሊናችን ወይንስ ለስጋችን አድረናል? ለሃገርና ለወገን በነበረን ፍቅር ላይ ምን ያህል እርግጠኞች ነበርን? በርካታ ጥያቄዎች ለየራሳችን አቅርበን ሚዛን ላይ ልንወጣ እንችላለን::

አስራ ሰባት የወሬ አመታት ሲያልፉ ምላስ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ቆይቷል:: ባዶ መፈክር አንግበን፣ ባዶ ጩኸት ስንጮህ፣ ምድሪቷ በድምጻችን ድርቀት ተሰነጣጥቃ ባድማ ሆናለች:: ምላስ በፈጠነ ቁጥር እግርና እጆች ሽባ እየሆኑ ሄዱ:: ከማምረት ይልቅ ማውራት ተመረጠ:: የሚያሸም፣

የሚያስመርጥ፣ የሚያበላ፣ የሚያጠጣ፣ የሚያኰራ ምላስ ሆኖ ተገኘ፡፡ አሳብቶ መብላት፣ ለፍልፎ መብላት፣ አቃጥሮ መብላት፣ እስከተቻለ ድረስ ሙያ ምናባቱ! ከዚህም ወዲያ ሙያ ለአሳር ነው! ምላስ የሌላቸው ዝም በማለታቸው እንደወንጀለኛ ተቆጥረው ውስጥ ውስጡን ሲታሹ ኖሩ፡፡ ለህሊናቸውና ለሙያቸው ያደሩ ሁሉ ተባረሩ፡፡ የተቀሩቱም በሙያቸው ላይ ምላስ እንዲቀጥሉ ተመከሩ፡፡ እናም ብዙ የእርሻ ካድሬዎች የህክምና ካድሬዎች የምህንድስና ካድሬዎች የኪነ ጥበብ ካድሬዎች፣ ወዘተ ተፈጠሩ፡፡ መለፍለፍ የቻልነውን አስለፈለፉ፣ መለፍለፍ ያልቻልነውን አንገት አስደፉ፣ በዚህም «ጥበባቸው» ምድሪቷን ባዶ አድርገው አለፉ፡፡

የሚሰሩ እጆች ተባርረው፣ የሚሰርቁ እጆች፣ የሚራመዱ እግሮች ተባርረው፣ የሚንሳፈፉ እግሮች፣ ሲፈጠሩ ንግዳችንም አየር በአየር ሆነ፡፡ ወደታች ማየት አስጠላን፤ ወደ ላይ እንዳንጋጠጥን ቀረን፡፡ ወደላይ! ወደላይ! ወደላይ! ከስልጣን ኮርቻ ላይ፣ ከጥቅም ኮርቻ ላይ፣ ከንቅዘት ኮርቻ ላይ መቀመጥ በአየር ላይ!... ለነገሩ ወደታች ምን የሚታይ ነገር አለ? የተጐሳቆለ፣ አንገቱን የደፋ፣ መፈጠሩን የጠላ፣ ኑሮ የከበደውና ከባዶው መሬት ጋር የሚታገል ሕዝብ ነው ወደታች የሚታየው፡፡ ይህንን ረግጦ በላዩ ላይ ቆሞ ወደላይ መመልከቱና አየር ላይ መንገዱ ነበር የተመረጠው፡፡ ቀን አልፎ ቀን ተተክቶ የላዩ ወደታች እስኪገነደስ ድረስ ያ ምስቅልቅልና ተስፋ የሚያስቆርጥ ጊዜ የዊሊያም በትለር ይትስን ግጥም ያስታውሰን ነበር፡፡

ስፋት ባለው ዙሪያ በመብረር

አዳኝ ወፍ ለአደን ሲሽከረከር

የአዳኝ ወፍ አዳኝ መኖሩን

መገንዘብ አልቻለም ጭራሹን...

ነገሮች ወደጉን ወደቁ

አልተቻለም ምስሶአቸውን ማጥበቁ

ስርዓተ- አልበኝነት በዓለም ነገሰ

በደም የጠቆረ ሞገድ ተርመሰመሰ

የንፁህን አምባ ደፈረሰ።

መጥፎዎች በጋለ ስሜት ሲቁነጠነጡ

ጥሩዎች ግን መላ እምነታቸውን አጡ።

አየር ላይ ቢንሳፈፉም የመሬትን ስበት መፍራት አይቀርም። ፍርሀት ደግሞ አምባገነንትን ይፈጥራል። አምባገነንም ብቻውን አይቆምም። ጡንቻውን የሚያሳዩ ብዙ ጡንቻዎች፣ ምላሱን የሚያሳዩ ብዙ ምላሶች፣ ድንፋታውን ያሳዩ ብዙ ደንፊዎች፣ ዙሪያውን ከብበው «አጀብ- አጀብ!» ይሉታል፤ ያጨበጭቡለታል።

ጭብጨባቸው ከፍ ባለ ቁጥር የራሳቸውን ጆሮ ያደነቁራል። በቃ! ከዚያ በኋላ ከወደታች ምንም አይሰሙም። እሪ ቢባል! ዋይታ ቢቀልጥ የሰቆቃ ድምጽ ቢያስተጋባ፣ አይሰማቸውም። ከአየር ላይ ያገኙትን አየር ላይ እየተቃመሱ፣ ምላስ ለምላስ እየተላላሱ፣ ከንፈር ለከንፈር እየተናከሱ... የሚፈሩትን የመሬት ስበት ከርቀት ይገረምሙታል። የተፈጥሮ ሕግ ስለሆነ የመሬት ስበቱ አይቀርም። ወደአፈር መልሶ አፈር ያለብሳቸዋል፤ አለበሳቸው።

ለዚህ ሁሉ ጥፋት ምክንያቱ ስርዓቱ ነበር ብለናል።

ይሁን ግድየለም! አሁን ያ ስርዓት አልፏል። እኛ እንደ አዲስ እንወለድና መጪውን ስርዓት የራሳችን እናድርገው። ዛሬ ጉህ እየቀደደ ነው። ጭለማው ለብርሀን ቦታውን የለቀቀ ይመስላል። የጭለማና የብርሀን መፈራረቅ ዲያሌክቲካዊ ዑደት ምንጊዜም የማይቀር ቢሆንም ከእንግዲህ ሕይወታችንን የሚያጨልም ጭለማ እንፈልግም። አሮጌው ባቡር በጭለማ ውስጥ ሲያልፍ አይተናል። በውድም ይሁን በግድ ብዙ ሰዎችን አሳፍሮ ነበር። የአምባገነኑ ሹፌር አንዳድ ያላማራቸው በጊዜ ወረዱ። አንዳንዶቹም ፉርጉዎች በየመንገዱ ተሰባበሩ። የተቀሩት እስከመጨረሻው ተጉዘው፣ የመጨረሻቸውን አገኙ።

አሁን ደግሞ አዲሱ ባቡር ብርሀናዊውን መንገድ ይዞ ተነስቷል። በብርሀናዊው መንገድ ይቀጥል ይሆን? ወይንስ ጭለማ ውስጥ ገብቶ ይጠፋ ይሆን? ገና ከጅምሩ ይህን መተንበይ ያስቸግራል። የቡናን ጣዕም በጀበናው ዓይነት መለየት አይቻልም። ፈልቶ፣ ከለል ብሎ ሰክኖ፣ ተቀድቶ ሲቀመስ ነው ጣዕሙ የሚታወቀው። ያም ሆነ ይህ አዲሱን ባቡር የምንሳፈር እኛ ራሳችን፤ ከዳር ሆነን የምናጨበጭብ እኛ ራሳችን፣ የባቡሩን መስመር በግልጽ የምንቃወም እኛ ራሳችን። ተደብቀን የምናማም እኛ ራሳችን፤ ወይንም ደግሞ ዝም ብለን የምንመለከት እኛ ራሳችን። ይህ ሁሉ መብታችን ነው። ይህን መብታችንን አስከብረን ለመጠቀም መጀመሪያ ራሳችንን እንደገና እንውለድ።

እንዴት?


እንዲህ!

መጀመሪያ አዕምሮአችንን ለአዳዲስ ሀሳቦች ክፍት እናድርግ። ዓይናችንን እንግለጥ። ጆሮአችንንም እናሰማው።


ከዚያ በኋላ እናስብ:: እናመዛዝን፤ እናንጠርጥር፣ እናብጠርጥር:: በዚህ መልክ ልደታችንን ካከበርን በኋላ ቢሻን እንደግፍ፤ ቢሻን እንቃወም፤ ቢሻን እንውደድ፤ ቢሻን እንጥላ:: ህዝባዊ ስመሆናችን፣ ሰብዓዊ ስመሆናችን ሕሊና ስመሆናችን፣ መጀመሪያ እርግጠኞች እንሁን:: በዚህ እርግጠኛ ከሆንን ለተሰ ማኒትም ሆነ ለአሸናፊነት ጥርጣሬ ሊኖረን አይገባም:: ነገር ግን ጭንቅላታችን ሁሉንም ነገር ከውጭ አንጥሮ ከመለሰ አሎሎ መሆኑ ነው፤ ዓይናችንም ብልቃጥ፤ ጆሮአችንም እንቅብ:: አስተሳሰባችንም ጭፍንና ድፍን ይሆናል:: ይህን አዘማማጊያ መጠንቀቅ ያሻል:: መጥፎ ነው፤ ሳያስቡት ያደድባል:: ሳይፈልጉ ያስገድዳል:: ያለምክንያት ያሳምፃል፤ እያደር ያሳብዳል:: ከበረታም እንደቀድሞው በቁም ይገድላል:: እና ዝም ብለን እንደግፍ፤ ዝም ብለን እንቃወም፤ ዝም ብለን ዝም እንበል:: ለተቃውሟችንም፣ ለድጋፋችንም፣ ለዝምታችንም ምክንያት ይኑረን:: ሰብአዊ ፍጡር መሆናችንን በምክንያት አሳይተን ሰብዓዊ ግምት፣ ሰብዓዊ ፍርድ እንስጥ:: የጊዜ ሁኔታና የአየር ጸባይ መለወጡ አይቀርም:: እየተለወጠ በመሄድ ላይ ይመስላል:: እንደተልባ የሚንጣጣ ምላስና ለባዶ መፈክር ሽቅብ የሚወረወር እንደበት ቦታ ሊኖራቸው አይገባም:: ሕዝብን ንቀው፣ ከሕዝብ በላይ ሆነው የሚጫወቱት የአየር ላይ ጨዋታ ለዘለቄታው እንደማያዋጣ አይተናል:: የነዚህ ድምር ውጤት አጠቃላይ ውድቀት መሆኑንም በሚገባ ተረድተናል:: ወደኋላ አንመለስም:: አሁን ስራ! ስራ! ስራ፤ ጉልበት ለስራ፣ አእምሮ ለስራ፣ ምላስ ለስራ! አየር በአየሩን ትተን፣ ወደ ምድር ወርደን እንነግድ:: ሽቅብ ወደላይ ብቻ ያንጋጠጠ፣ አንገትና አይናችንንም ወደታች እናሳየው:: ስርቆት ይቅርብን፤ ሰርተን ሀብት እናፍራ፤ ሁሉንም በስራ! እንደ ገና እንወለድ::

መሸፋፈን የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል:: የአዕምሮ ፋክክርን፣ የችሎታ ፋክክርን፣ የዕምነት ፋክክርን ጊዜው ይጠይቃል:: ውድድሮችና ፋክክሮች በግላጭ ተካሂደው፣ አሸናፊና ተሸናፊ በግላጭ ተፋጭተው፣ ግልጽ ዳኝነት ማግኘት አለባቸው:: ጉበዝ ያሸንፋል፤ ሰነፉ ይሸነፋል:: የሰራ ይበላል፤ ያልሰራ ጾሙን ያድራል:: እንደገና በመወለዱ ሂደት ውስጥ ካለፍን፣ ከዚህ ውጭ መሆን አንችልም:: እንደነበርን እንኖራለን የምንል ግብዞች ካለን ተሳስተናል::

የሌሎችን ሀሳብ አንናቅ:: የኛ ብቻ ይደመጥ አንበል:: መደማመጥንና ሀሳብ መለዋወጥን እንደ አዲስ ባህል እንልመደው:: አዲስ የስራ ባህል እንልመድ:: አዲስ የመፈቃቀር ባህል እንገንባና በዚያ ውስጥ እንለፍ:: ራሳችንን አክብረን፣ የሌሎችንም ሰብዓዊ መብት እናክብር:: መታፈንን እንደማንፈልግ ሁሉ ሌሎችንም አናፍን:: ተራርቀን በማንራራቅበት፣ ተለያይተን በማንለያይበት፣ በዚች ምድር ምን ጊዜም በሰላም አብሮ መኖርን እንሻ:: ልዩነቶችን እናጥብብ:: ዘመኑ የፈጠራቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ የመገናኛ ዘዴዎችና ድንበር ዘለል ምርምሮች፣ ተራርቀንም ሆነ ተለያይተን እንዳንቀር ያስገድዱናል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ስልጣኔያችን፣ ተፈጥሮአዊ ልዩነቶችን አቻችሎ ሰብዓዊ አንድነቶችን ማጠናከር አለበት::



# ሲሞዚን በአዲሳባ



# ከአቅም በላይ

## አቦነህ አሻግሬ

ዝነኛው ሳይንቲስትና አካዳሚሺያን ሺሚት (1891-1956 እ.ኤ.አ) የአስራ አራት ዓመት ወጣት ሳለ፣ በቀሪው የህይወት ዘመኑ የሚያነባቸውን መፃህፍት፣ የሚያጠናውን ሳይንስ፣ በምርምርና ጥናት መፍትሄ የሚሻላቸውን ችግሮችና ሌሎች ሊያከናውናቸው የሚገባቸውን ተግባራት በመዘርዘር እቅድ አወጣ፡፡ ይህን ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈጅበትን ጊዜ ሲያሰላም ዘጠኝ መቶ ዓመታት የሚፈጅበት ሆነ፡፡ እንደገና

ፕሮግራሙን በማጠጋጋትና በማጨናነቅ ሲነድፈው አምስት መቶ ዓመት የማይጠይቅ ሆነ፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ አጣብቦ ሲከልሰው በአንድ መቶ ሃምሳ ዓመታት ሊጠናቀቅ እንደሚችል ገመተ፡፡

ሺሚት የህይወት ዘመኑን እያንዳንዷን ደቂቃ በእቅድ በመምራትና፣ ያለ የሌለ አቅሙን በስራ ላይ በማዋል በሰላሳ አምስት ዓመት እድሜው ውስጥ የአንድ መቶ ሃምሳ ዓመት እቅዱን ከግቡ አድርሶ በሞት ተለየ፡፡

ከሺሚት ምሳሌነት አንድ የምንረዳው ነገር አለ፡፡ ይኸውም በመጨረሻው አቅም መስራት በራስ ውስጥ ታምቆ ያለን ፍሬያማ ክምችት ሙሉ በሙሉ ለማውጣት አይነተኛ መንገድ መሆኑን ነው፡፡

በዚህ ምሳሌ ወደማጠቃለያ ከመዝለል እንቆጠብና ሌላ ጠቃሚ ምሳሌ ደግሞ እንመልከት፡፡ እንግሊዛዊው የታሪክና የስነ ህብረተሰብ ምሁር ሔንሪ ቶማስ በክል፣ የአስራ ስምንት ዓመት ወጣት ሳለ፣ ስለዓለም ስልጣኔ ታሪክ ሊፅፍ ወሰነ፡፡ እንዲህ አይነቱን ታላቅና ለፋ ስራ ለመስራት በተፈጥሮአዊ ሳይንስ፣ በተለያየ ቋንቋ፣ በታሪክ፣ በህግና በዓለም ስነ- ፅሁፍ የጠለቀ እውቀት ተክኖ መገኘትን በመጠየቁ በክል ይህንን ሁሉ ለማጥናት ቆርጦ ተነሳ፡፡ አብዛኛውን ጊዜውን በመፃፊያ ክፍሉ ውስጥ በመወሰኑ ከነአካቴው ከሰው ጋር ከመገናኘትና ማህበራዊ ጭውውት ከማድረግ ራቀ፡፡ ከስነ- ጥበብና ከሙዚቃ ተለየ፡፡ ከሞዛርትና

ከቤተሆቨን ሊለይ እንኳ አይችልም ነበር፡፡ ወደ ቲያትርና የስዕል ኤግዚቢሽን አይደርስም፡፡ ይወደው ከነበረው የቼስ ጨዋታም ተገለለ፡፡

ይህ ከፍተኛ ጥረት ግን ፍሬ አፍርቶለታል፡፡ በክል አስራ ዘጠኝ ቋንቋዎችን አጠና፡፡ ከሚነጋገርበት ደረጃ ላይ ባይደርስም ለስራው የሚያስፈልጉትን ሀሳቦች በንባብ ከሚረዳበት ደረጃ ላይ አደረሱት፡፡ ውሎ ሲያድር ግን ሊሰራው ያቀደው ስራ እጅግ ሰፊና ከቶ ሊጠናቀቅ የማይችል መሆኑን ተረዳ፡፡ «የሰው ልጅ ስልጣኔ ታሪክ» በሚል ሊፅፍ የነበረውን ሰፊ ርዕስ አጥብቦ ስለ አውሮፓ ስልጣኔ ታሪክ ብቻ መፃፍ ጀመረ፡፡ ቆይቶ ሲያስበው ይህም የማይቻለው ሆኖ ተገኘ፡፡ በመጨረሻው ላይ «የእንግሊዝ ስልጣኔ ታሪክ» ወደሚለው ርዕስ ወረደ፡፡ ታሪኩን በአስራ አምስት ጥራዝ ሊያጠቃልልም እቅድ አወጣ፡፡ ምን ያደርጋል ታዲያ፣ ሁለት ጥራዝ ብቻ እንደጨረሰ በ41 ዓመቱ ሞተ፡፡ ያሰመውን ሳያጠናቅቅ ስራው ቀድሞ አጠናቀቀው፡፡

ታዲያ እንዲህ አይነቱ ጭንቀት አስፈላጊ ነበር? አልነበረም፡፡ በአኳያውም በአነስተኛ ጥረት መወሰን ደግ አይደለም፡፡

እንጉልን በበቂ ሁኔታ አለማሰራት እድገቱን ቀስ በቀስ ማቀጨጭ ነው፡፡ የማሰብ ችሎታውን ውስን አድርጎ ለችግሮች መፍትሄ የሚሰጥበትን የአፍላቂነት ኃይሉን መግታት ነው፡፡ የአፍላቂነት ኃይል መዳከምና ሃሳበ ውስንነት

ደግሞ ጠንክሮ ለመስራት ብርታት የሚጐላቸው ሰዎች ባህርይ ነው።

በረቀቀና የሰከነ እቅድ ከሚመሩ ታታሪ ተማሪዎች ይልቅ፤ አነስተኛ ጥረት የሚያሳዩ ተማሪዎች የበለጠ የድካምና የጭንቀት ስሜት እንደሚታይባቸው የስነ አእምሮ ጥናት ያመለክታል።

የሰው ልጅ ስራው የሚጠይቀውን ያህል አእምሮውን ሊያሰራው ይገባል- ባቅሙ፣ በልኩ። እዚህ ላይ «የአንድ ሰው ልኩ እንዴት ይታወቃል» የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ይህን በወጉ ያልመለሰ ታታሪ፣ በአስቃቂ ጭንቀትና ድካም ህይወቱን አልፍቶ አላፊ ይሆናል።

ሌላው ነጥብ ደግሞ፣ ስለእያንዳንዱ ሰውና ህይወት ጉዳይ ነው። መቼም የአብዛኛዎች ታላላቅ ሰዎች ህይወት በከባድ ትግል የተመላ ነው። ችሎታውን እስከመጨረሻ ልኩ በመጠቀምና በመንፈስ-ቆራጥነታቸው እጅግ በርካታ መሰናክሎችን እየተጋፈጠ በአሸናፊነት ይወጣሉ፤ ዓላማቸውን ከግቡ ያደርሳሉ።

በሌላ አንጻር ደግሞ ህይወታቸው ከእንዲህ አይነቱ ውጣ ውረድ እንዲነፃ «እጣ ፈንታቸው» የሆነ ሰዎች የችሎታቸውን ክምችት በተግባር ላይ ሳያውሉ እየቀሩ ሊደርሱበት ወደሚችሉት ውጤታማ እርከን ሳይቀርቡ ከታች ይቀራሉ።


ታዲያ ከግብ፣ ውጤትና ድል የሚያደርሰው

በመሰናክል የተሞላ ውስብስብና አስቸጋሪው ሂደት የሚወገዝ ነው ወይንስ የሚወደስ? የሚወደስ ነው:: እንዲህ ሲባል ግን ወደ አንድ የታለመ ግብ ለመድረስ፣ በግለሰብ የሚፈጠር ሰው ሰራሽ መሰናክልን የግድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ማለትም አይደለም:: በእርግጥ ራስን ለመፈተን እንዲህ ማድረግ አንዳንዴ ጠቀሜታ አለው:: ማንም ሰው ቢሆን በህይወቱ ውስጥ ከመሰናክል ነፃ ሆኖ አይኖርም:: መሰናክሉን ለማስወገድ ሁኔታው በሚያስገድድበት ወቅት ግን ዳር ዳር እያለ ከችግሩ የሚያመልጥበትን ቀላል ዘዴ ከመፈላለግ ይልቅ ያለ የሌለ ኃይሉን በማጠናከር የመሰናክሉን መረብ በጣጥሶና በታትኖ በድል አድራጊነት መወጣት ተገቢ ነው::

እያንዳንዱ ሰው ለክቡር ዓላማና እሴት ሲል ትግልን የሚያጣጥምበትን ህዋሱን ማጐልበት ይኖርበታል:: (ማርች 1988፣ በእንግሊዝኛ ከታተመው ስፑትኒክ መፅሄት የተወሰደ)



# የወጥ ቤት ሙዚቃ




# አሞራው ሼህ

ይሁን እንደሻው

በረሀ ዞረው፣ ገዳማትን አዳርሰው፣ በመጨረሻም 'በል ሂድና ልጆች አስተምረህ አውጣ፤ እሱ ነው የተሰጠህ ኑሮ፣ ተብዬ ማህተም ተሰጥቶኝ መጣሁ። ይኸው የታዘዝኩትንም እየፈፀምኩ ነው» የሚሉት አባ ልጆች በማስተማር የሚተዳደሩና በአንዲት ዛኒጋባ ውስጥ በቤት ቁጥር «00» የሚኖሩ መነኩሴ ናቸው (የቤት ቁጥር ስለሌላቸው ዜሮ ዜሮ ብለውታል- እሳቸው።)

«የምን ማህተም አባ?» ስላቸው «የደም ማህተም

ነዋ! የክርስቶስ የግራ ጐኑ» አሉ። እድሜአቸው ወደ 75 ይገመታል። መንግሥት ሰማያትን እንደ ሚወርሱ ቅንጣት ታህል አይጠራጠሩም።

የፋሲካ እለት አገኘሁዋቸውና «ምነው የከፋዎት ይመስላሉ አባ?» አልኳቸው።

«ማነው የሚከፋው? እኔ አሞራው ሼህ? አታየውም እንዴ? ዛሬ ፋሲካ በየሁሉ ቤት አስረሽ ምቺው ነው- ሰርግና ምላሽ! ቤቱን አታየውም፣ እና ሆኖ?... ከየህ የዶሮ ወጡ፣ ወዲህ በኩል ጠላው... እክክክ!» ... ምን ተሰምቷል እኔ ቤት? ሄድኳ ስተት ብዬ!»

«የት?»

«ላይ ቤት ነዋ!»

«እሺ» አልኳቸው፤ በምናብ ላይ ቤት አብሬአቸው እየሄድኩ።

«እዛ ስደርስ ሱራፌል የእሳት ሰይፋን - ሰባት ጊዜ የሚያበራውን መዝዞ 'ወዴት ነው?' አለ እየቃጣብኝ። አብርሀምስ ነህ? አዳምስ ነህ? ኧረ ለመሆኑ ማንስ ነህ አንተ? እነሱ ሳይገቡ የምትገባ?» አለ ልገባ መስሎት።

«የሰም ጌታዬ ጋ ነኝ» አልኩት።

«ለምን?»

«ላመለክት!»

ይዞኝ ገባ። እሱ ቁጭ ብሎ ነበር ከመንበሩ። እሱን እሱን ሳይ ሱራፌል ወደኔ እየት አድርጎ፣

«አታውቀውም እንዴ?» አለ።

«ኧረ አውቀዋለሁ!»

«ጉንበስ አትልም እንጂ ታዲያ?»

«እሺ ይኸው» (ከወገባቸው ጉበደድ ብለው እጅ እየነሱ) አጨንቁሮ እየኝና፣

«ከየት ነው የመጣኸው?» ሲል፣

«ከታች ቤት» አልኩት።

«ለመሆኑ እዛ ተርቢ አብልተኸኛል? ታርገቢ አልብሰኸኛል?» አለኝ።

«እሄሄ! አንተ ትቀልዳለህ። እኔ የምበላው ድርቆሽ አሮብኛል አንተ ተርቢ አብልተኸኛል ወይ ትላለህ» ስለው ተቆጣ። «በል ወደዛ ማረፊያ ቤት አስገባው» አለው ሲራፌልን። «ወደ ጨለማው አይደለም ታዲያ» አለው አዝኖልኝ። «እውነቱን በነገርኩት ልታሰር? እኔን በራብኝ?»

«በሉ እነሆ» ብዬ በጃቸው አስጨበጥኳቸው።

«ምንድነው?»

«እህ ሞኒ ነዋ! እነሆ በረከት!»

«ለካስ አንተን ልኮልኝ ነው በል እዛው ሂድ! ምን ትመላለሳለህ? ያለኝ... ይሄን አዘጋጅቶልኝ ኖሯል! አይ እንግዲህ ምን አለብኝ። አሁን ሄጄ ማራቶ (ማራቶን ጠጅ ቤት ነው) አራቱን ተው፣ተው ነው»

«ገና ስገባ 'ኖር! ኖር! አባ መጡ አባ መጡ!' ነው ። ወደ ኋላዩ የምለው የለም አይደል? ሁሉ እኔን ሲያይ ይደሰታል። ጨዋታዬን ይወዱታል። ያም ያም ውሰድ

ውሰድ ነው- ያስተማርኳቸው ሁሉ፡፡ ከደከመኝም ጊዮርጊስን ጠርቼ 'በል አባክህ አፈናጠህ አድርሰኝ' እለዋለሁ፡፡ እዚሁ · ያደርሰኛል፣ እንደፈረደበት፡፡ ሙክት አይደል አይሰባ፡፡ ኋላ ምን ሲሰራ ኖሯል?... ከተፍ ይልና 'ዝም ብለህ እየደባለቅህ፣ ከዛም ከዛም እየቃረምክ፣ ትግት ትግትና መከራ ታሳያለህ፤ በል ተነስ' ብሎ አፈናጦ ያደርሰኛል፡፡ እኛን ለማገልገል አይደል መቼስ? አንዳንዴ እዛ ቁጭ እንዳልኩ በዚያ ሲያልፍ አንጆቱ አይጨክን አይደል? ብቅ ብሎ ያየኝና 'አይበቃህም እንዴ? አትነሳም?' ይለኛል፡፡

'እረ እሺ!' ብድግ ነው፡፡ እኔ አሞራው ሼህ! እናንተ ሁሉአችሁ እያላችሁልኝ ምን እንዳይቸግረኝ ብለህ? እልል በቅምጤ ነው?» አሉ እኚህ መዓተኛ አባ፡፡

***

አቡነ ተክልዬ፣ በመልካም ሥነ ምግባር፣ በበጐ አሳቢነት ይመሰላሉ፡፡ ቆሪጥ ደግሞ በመጥፎ አሳቢነት፣ በክፋትና ተንኮል ይመሰላል፡፡ የኔታ ጐራድ 'ሲሉ መጥፎ ተግባር፣ ሴጣናዊ ድርጊትንና እኩይ የሚሉትን ሲያመለክቱ ነው፡፡ ታዲያ አባ ስለ አገራችን መንግሥታትም አጫውተውኝ ነበር፡፡

«ጣልያኖች መቼም እንደገቡ ቢሸፍቱ ነው የገሰገሱት፡፡ የዋዛ አስማተኞች አይደሉም፡፡ የሚያህላቸው የለም፤ የሚደርስባቸው፡፡ ሄዱና ይሄን ምድረ አጋንንት 'እዚህታጅበህ ትዶልታለህ፡፡ በል ከዚህ ተነስ' አሏቸው፡፡ አሥራ አራት ነበሩ፡፡ 'ደሞ የት ልትሰዱን ነው?' ሲሏቸው 'እዛው ለቂ ደምበል ነዋ!' ብለው ከባሕሩ ከተቷቸው፡፡

ጐራድ ብቻ እምቢ አላቸው፡፡ 'ለራሴ እጅ የለኝ፣ እግር የለኝ፤ ቤት ጠባቂ ነኝ አልሄድም' አላቸው፡፡ ተስማምተህ ትኖር እንደሁ ኑር፤ እለዛ የነሱን ቀን ነው ምንሰጥህ ብለው

ሲያስፈራሩት፤ እነሱን ተቀበለ:: ታዲያ ምን ይላቸዋል፤ መከራ ነው:: 'ፈሳችሁን እንዳላስረጫችሁ' ቢላቸው ደሞ፤ ለዚህ ፈሽፋሽ ሕዝብ ነው ተስማምተህ አልኖር የምትለው?» አሉት:: እርሱም አምስት ዓመት ይበቃችኋል አላቸው::

ጀነራሉ 'ወይድ! አንተ ነህ ያልከው? ዋ! ነግሬንሃል:: አላርፍ ካልክ እዛው ጢው ጢዋ ባሕር ከተንህ አርክን እንዳትበላ' ሲሉት ጊዜ ግን 'የለም ኩስቶ ቦና ቦና:: ተውት እውነቱን ነው» አለ::

ያው አምስት ዓመት ሙሉ ፈሳችንን አስረጨን:: ከዛ ይሄ አርበኛ ከየጫካው ከየበረሃው ብቅ አለና 'መጣሁልህ! እስቲ የቷ ባክ ትገባ? እነሆ በረከት!' እያለ ይሄን ሰላቶ መድረሻ አሳጣው:: ጃንሆይ ሲገቡም «እንኳን ገባህ!» ብሎ ጉራድ በደህና ተቀበላቸው:: ከዛማ ምናለ ወዳጅ ሆኑ:: ከዛ ያው ይገብሩለት ጀመር:: ጉራድም 'እስከ ፍፃሜው ምንም የለብህ:: ግዛ ንዳ' አላቸው:: ያው ዝም ብለው እየገበሩ መንዳት ሆነ:: ኋላ ጉራድ ማጉረምረም አመጣ:: 'እንግዲህ የኔና ያንተ ወዳጅነት ምንድረስ ነው?' አሉት- ሄዱና ጃንሆይ:: 'እንግዲህ ወዳጅነታችንን ካልክ፤ የድሃ ደም ጉፍንኖኛልና የዘመዶችህን አግባልኝ' አላቸው::

«የባሮች ደም አንሶ ደሞ ወደ ዘመዶቼ ዞርክ? ለዚህም ደርሰሃል» አሉት::

«ወይ ጉድ! የድሃ ደም ሲጉፈንነኝስ? እኔ ንክችም አላደርግ::»

«አይ! የዘመዶቼንስ ምን በወጣኝ» ሲሉት «አይ ወዳጄ እንግዲህ ነገርኩህ:: ትሰማ እንደሁ ስማ:: የድሃ ደም ጉፍንኖኛል አልኩህ::»

«ኧረ ተው እንደበፊቱ ይሻለናል» ቢሉት ዝም ጉራድ:: ሆድና ጀርባ ሆነ::

«እሺ. ማብቂያዬን ንገረኝ፣ መጨረሻዬን»

«ምን መጨረሻ አለህ? እምቢ ካልክ ታገኛታለህ:: የቀበርካትን ሳትበላ እየተንኳኳህ 'ትወርዳታለህ' አላቸው:: ወረዷ ይኸው:: የት ይግቡ፤ የት መች ተገኝተው!»

«እኔንማ አይወደኝም» አሉ አባ::

«ማነው የማይወድዎ?»

«ጉራድ ነዋ ... አጅሬ ጉራድ! እንዴት ተደርጐ? 'አንተ አትግብር:: ምን ልታደርግ ነው የምትመጣው?' ይለኛል:: 'ደሞ ከኔም ያምርሃል? መንበሩን ያዝ ቢሉኝ እምቢ ያልኩት ይሄን ጠልቼ አይደል?' እለዋለሁ:: አንዋደድም፣ እኔና እሱ:: እንተያይ የለ? ሥራውን እገልጥበታለሁ:: እነ መንግሥቱ እያሉለት እሱ ምን ቸገረው? ሸረኮች:: አንጋች አልነበረ የጃንሆይ? ከዛች አይለይም:: ልጥፍ ብሎ ኮረጆ ኮረጆና 'እነሆ በረከት' ብሎ ፈነገላቸውና ሄዶ ፊጥ አለ::

ከሞቱ በኋላም ነገር እንዳይመጣብኝ ብሎ፣ ወደጉራድ ዘንድ ይሄድና «መጣሁልህ!» ይለዋል::

«በላ ግብሩን አንጣ! ምን እንደማያውቅ ትሆናለህ? ጋሻ ጃግሬም አልነበርክ?» ቢለው፣ «እንዴታ! ያልከኝን ሁሉ እፈፅማለሁ» በማለቱ ጉራድም እልል በቅምጤ አለ::

«በል ቶሎ!»

«እሺ. እኮ አልኩህ! የሚያደርጉትን አደርግልሃለሁ:: ምን ትፈልጋለህ?»

«የሰ፤ አንተ አጥፍ ነው የምትገብር... እዩህ ላይ እንስማማ::» ተስማሙ ሁለቱ::

«በል የጠጣት ደም አግባልኝ» አለው:: ያው ጠጣቱን እያነቀ በየባቡር መንገዱ አርዶ አርዶ ፈጀው - አባ ነው እያለ:: እኔንም አባ (ኢህአፓ) ነህ ብሎ ለጕራድ ሊገብረኝ ነበር መንግሥቱ:: 'ኧረ እኔ አባ አይደለሁም፤ አባ ኪዳነ ማርያም ነኝ ብዬ መስታወቂያዬን አውጥቼ- እነሆ በረከት-ስላቸው ተውኝና አለፉ:: ዳንሁ:: አይ መንግሥቱ፤ እኔማ ያ ገብርኤል በዛ በሰይፉ አንገቱን ብሎ ይደፋልኛል፣ እያልኩ ፀሎቴን ብይዝ በየት ተብሎ? እንዲያው ዝም ዝም:: ቀጣው እኮ እንዲህ አልነበረም:: ማነው እፊቱ ይቆም ነበር?

መቆጣት ነው ደርሶ:: በግራ እጁ ጕራዶውን አፈፍ፣ መዘዝ ነው:: ሚካኤል ነው የዋህ:: የሚካኤል ለት ነው እንዱ ገበሬ (ገና እኮ ጠፍ ሳይንጫጫ ነው) ይሄን መሬት ይዞ አሳሩን ያበላዋል:: ሚካኤል ታዲያ በዚያ ሲያልፍ፣ እንደኔ ክንፉን ሸሽጕና ሥጋ ለባሽ መስሎ ያየዋል:: 'አንተ ሰው' አለው፤ እዛ ደንግጦ እንደቆመ ገበሬው፤'ቀኑን ረስተህ ነው ወይስ ምንድ ነው?'

'አይ፤ እኔ መቼስ እየራበኝ እያለ ሲወተፈተፍ 'በል ግዴለም አንተ አስኮናኝ! እኔ እንዳየሁህ ብቻ ገብርኤል እንዳያይህ' አለውና እልፍ እንዳለ፣ ከየት መጣ ሳይባል ገብርኤል ዱብ አለና ሰይፉንም አልመዘዘ በመብረቁ መታው::

«የሰውዬው መጨረሻስ እንዴት ሆነ? የመንግሥቱ?» ብዬ ጠየቅኋቸው አባን:

«ያው ቀንየት አመለጠ! ምን ትጠይቀኛለህ፤ ያዋጁን

በጆሮ? አሁን እያረሰ ይበላል:: እሱ ዘመድ አይልምን አይል ብዙ ገብሯል:: ቤተክርስቲያን አያውቅ፣ ምን አያውቅ:: ማታ ማታ አየር ላንስ እያለ መገስገስ ነው አዳሩን:: መች ይለይና ከቢሽፍቱ? ምን እንዳይነካው ነው? የሕፃናት ሁሉ አስገብቷል:: ጉራድን እንደሁ በደንብ አጥግቦታል፣ መቼስ:: 'በል ሁለት ዓመት ቀሪ ነበረህ ይቅርብህ:: መስዋእት ነው የሚያረገህ:: ጫጭንና ሹልክ በል' ሲለው 'እኔ እዚህ ነው የምሞተው እዋጋለሁ' አለ:: 'የምን እሞታለሁ' ነው:: ሹልክ አትልም? ሰው ልታስፈጅ ነው? ባለተሮች መጥተዋል:: ልቀቅና ወደ ምትኬድበት ሂደህ፣ ያጠራቀምከውን ዝም ብለህ አትበላም?' ቢለው:: 'እረ እውነክን ነው!' ብሎ ጫጫኑና ሹልክ ነዋ አጅሬ! በዘንግ መጡዋ አዲሶቹ:: 'እንዴት ዋላችሁ?' ብለው ዘው:: ድምጽ የለ፣ ምን የለ:: እረ እነዚህንም ባላስለመደብን አጅሬ ጉራድ!»

አባ የሌሊት ሕይወታቸውንም እንዲህ ሲሉ አጫውተውኛል::

«በውድቅት ሌሊት እኮ ነው:: ይመጣና...ኳኳ!»

«ማነህ?»

«መቻ አጣኸውና ነው? ይልቅስ ተነስ እንሂድ እላይ ቤት ተጠርተሃል»

«እዚህ ነው የታዘዝከው?»

«አዎ»

«እኔ እንደሁ አንተ ጠርተኸኝ አልሄድ:: ራሴ እውቄ እመጣለሁ:: ፀሎትህን ከገፋህ ትደፍናታለህ ብሎኛል:: መቶዋን ሳልደፍን አልመጣት!»

በራፍ ላይ እንደ ጅብራ ተገትሮ ኳኳ!...

«ወየው ጉድ! ሙት አመት ሲሞላኝ ነው እያልኩህ! እናንተ የፈለጋችሁ ጊዜ ብቻ ማን አለና:: ሄድ አትቁም፣ ይልቅ አጣራ»

«አይሞግቱኝ አባ! ተጠርተዋል» ይለኛል እንደጅብራ ተገትሮ::

«እባክህ ወዳጄ ካንተ እኩል አውቀዋለሁ መዝገቡን:: ቀና ብለህ አታይም ዜሮ ዜሮ (00) ነው የሚል:: ቀበሌ ያልተመዘገበ፣ ከናንተ ሲኖር ነው?»

ሌሊት ሌሊት መቸ እንቅልፍ ይወስደኝ መሰለህ:: ስሚገት ነው የማድረው::

«ይልቅ ሌሎች እንዳያመልጡህ:: የታዘዝክበት አትኬድም?» እያልኩ ሁሌ እንደመራሁት ነው:: እስከመቼ እየመራሁት እዘልቀዋለሁ::

«በዘመነ ማቴዎስ ያዘኝ፣ ያኔ እግሬን ተሰብሬ አልተኛሁም? የፋሲካለት ለካስ አድፍጦ ኖሯል፤ አጅሬ ሆፍ፣ ሆፍ እያለ ክንፉን አንከርፎ ሲንጋፈፍ መጣታ:: ያበቃልኝ መስሎት ጉፈፍ ጉፈፍ እያለ መጣ:: ሰተት ብሎ ገባና ክንፉን አጠላብኝ - ላዬ ላይ ሊከመር ብኝ:: እኔም አደፈጥኩ:: እኔ አሞራው ሼህ! ጉሮሮውን እንቅ! ልቀቅ፣ አለቅም ትንንቅ:: መች የዋዛ ነው? ታገለኝ... እከክ! እኔ አሞራው ሼህ! ከዋው! መዋው! ሰዋው! - ደገምኩበት:: ለቀቀኝ:: ሃፍ፣ ሃፍ ብሎ እስከለከና ጥሎኝ ኡፍ! ሄዶ የጐረቤት በር ያንኳኳል:: ትንሽ አሻሹዮኝ ነበር:: ፀሎቴን ደጋገምኩና ጋደም እንዳልኩ፣ የጐረቤቱ ለቅሶ አነቃኝ:: ለቅሶ ነው የቀሰቀሰኝ:: ብቅ ስል ሲያንኳኳ ከነበረበት ቤት

ውስጥ ነው:: ለካስ አንጠልጥሎ ይዞት ሄዶ ኖሮ ደረት ጥለው ያለቅሳሉ::»

«የመነኩሴት ቤት ንብረትምን ጥለው ነው?»

«የምን ቤት ንብረት? እኔ የወጣሁት በልጅነቴ፤ ገዳም የገባሁ በልጅነቴ... አይ አንተ? ልትፈታተነኝ ነው:: እኔ ከሴት ጉያ ደርሼም አላቅ:: ከወጣሁበት ደግሞ አልገባሁበትም:: እኔ ያንተ አባት፣ ያልዞርኩበት ገዳም የለም:: እኔ አሞራው ሼህ! በቀኝ እጄ ዶማ፣ በግራ እጄ መቁጠሪያ ነው የነበረ:: አትክልቱ እንዲህ አይደለም መቸስ:: በወዲህ ቡናው፣ በዛ ጫቱ»

«ጫት?»

«ያውም የወይን ከንፈር የመሰፈለ ነዋ:: እህ!? ምን መሆንህ ነው? መብቂያችን በምን ሆነና ነው:: በሱም አይዶል ከላይ መገናኛችን? ታዲያ ምን ያደርጋል? ምድረ መነኩሴ እየተንጋፈፈ 'ይሄ መነኩሴ ጫት ይቅማል' እያለ መንሾካሾክ ሆነ:: ሄደውም ከሰሱ፤ ለደብሩ አለቃ:: ሲገሰግስ ወደኔ መጣና 'ምነው አባ ይሄን የሠይጣን ሥራ?' አለ እየተቆጣ:: እኔ ቆጤ ላይ ተመቻችቼ ቁጭ ብዬአለሁ ለሱባኤ:: «እህ! እስክንድር ከላይ ይዞት የመጣ እፀ መሰወር አይዶል? ምኑ ነው የሠይጣን ሥራ? ቡናውስ ምንድነው? ሁሉስ ቅጠል አይዶል? ያሁሉ ደጋግ ሰውስ የበቃው... ቅጠል በልቶ፣ ጤዛ ልሶ አይደል? ይሄኮ የእስክንድር ስጦታ ነው:: እስክንድር ፈረስዋን በንስር ቢያስጠቃት ክንፍ ያለው ፈረስ ተወለደ:: የተንጣለለ ትልቅ የግንብ ግቢ አሳጥሮ፣ ይሄን ባለክንፍ ፈረስ ይለቀዋል:: ፈረሱም ተመቸው አነጠነጠ:: ዳንኮላ ሲሆን ጊዜ እስቲ ልሞክረው ይልና ጉብ አለበት:: ፈረሱም ምን መጣብኝ፣ ይልና ያባቱን ይዞ ሐፍ ወደሰማይ:: ይዞትም

ከገነት ጥልቅ፤ እስክንድር ሆዬ 'ምን አገር ገባሁ' ብሎ ዱብ ይልና ከገነት ዛፍ ላይ ያስረዋል፡፡

«ማንህ አንተ? እነ አብርሃም እነአዳም፣ ደጋጎቹ ሳይገቡ አንተ በጥበብ ልትገባ!» ብሎ የእሳት ሰይፉን ሲመዘው፣ እስክንድር ደንብሮ ፈረሱ ላይ ዘሎ ወጣበት፡፡ ፈረሱ ደግሞ 'ምን መጣብኝ?' ብሎ የታሰረበትን የገነት ዛፍ ምንግል አድርጎ ቁልቁል! እነሆ ዱብ እዚህ፡፡ ከዛ ለኛ ተረፈ ይኸው፡፡ በአንድ በኩል ቡናው፤ በሌላ በኩል የትምባሆ ቅጠሉ - ሰይጣን ኮትኩቶ ያበቀለው፣ በተጨማሪም ይኸው እኛ የምንበቃበት ሰፀ መስውር፡፡ ታዲያ ሌላ በምን ልንበቃ ኖሯል? እሱ በባለክንፍ ፈረሱ በረረ፡፡ እኛስ በምን እንብረር? አመጣልና ሳተናው እስክንድር! ማቆጥቆጫችንን- የእፀ መሰውሩን ተክል፡፡ ከእንግዲህ ምን አለብን? ክንፋችንን አብቅለን እንደልባችን መብረር ነው!»


«የደብሩ አለቃ ታዲያ ምን አሉዎት?»

«ምን ይሉኛል፡፡ 'ይልቅ ና ቁጭ በልና አቆጥቁጥ' አልኩት፡፡ 'ኧረ! ኧረ! ጉድ ሳይሰማ አይታደርም!' አሉና ሆፍ! አሉ፡፡ ሂድ ምን ችገረኝ? እኔ እንደሁ ክንፌን አቆጠቁጣለሁ» አልኳ፡፡

«ታዲያ በየት በኩል? ምድረ መነኩሴ ካባውን ለብሶ እየተግበሰበሰ፣ ለፍቼ ያበቀልኩትን ቡናዬን እንደ አባቱ ማሳ መሸምጠጥ፡፡ ምን ብዬ ልጣላ? የመጣሁት ከፈጣሪ ልታረቅ፡፡ ደግሞ ለሠይጣን ቀዳዳ ልክፈት? እይ! ምነው እቴ! ያውላችሁ!» ብዬ ሁሉንም ተውኩላቸውና ለመንገዴ ቀጠፍ፣ ቀጠፍ አድርጌ፣ ያጋዘን ደበሎዬን እንደለበስኩ ከተፍ አዲሳባ! ይኸው እዚህ የልጆች ፊስ እየታጠንኩ

አለሁ:: ፊደል አስቆጥር ብዬ እዚህ አዲሳባ ከመጣሁ ነው፣ አቆጥቁጦ የነበረውን ክንፌን የተነጨሁት:: እዛ ሳለሁ እኔ አጦራው ሺህ ከዋው! መዋው! ሰዋው! ብዬ እርግፍ አደርግና ሽቅብ ህእ! ነበር» አሉ- እንደመብረር እየቃጣቸው::

በንስርና ፈረስ ልጅ ክንፍ ሳይሆን በገዛ ክንፋቸው በረው ሽቅብ ገብተው፣ ገነት፣ ሰላስ ቅጠላት ሳያመጡልን ይቀራሉ? ሙት አሙቷን እስኪደፍኑ ገና ሀያ አምስት አመት አለን:: ማን ያውቃል ያባ ኪዳነ ማርያምን መጨረሻ? እንዲያውስ መጨረሻ ይኖራቸው ብላችሁ?



# የመቃብር ላይ ጽሑፎች

## ኤፍሬም ገብረየሱስ

ከጥቂት ዓመታት በፊት አርኪዎሎጂስቶች ከአያሌ ዘመናት በፊት በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጠ የተቀበረን ንጉሥ አገኙተዋል። በጣቱ ቀለበትም ላይ «ሁሉም ያልፋል፣ ከእግዚአብሔር መንግስት በቀር» የሚል ተቀርጿል። በርግጥ ሁሉም ያልፋል- ከስምና ከእግዚአብሔር መንግሥት በቀር።

ታላቁ አሌክሳንደር ከፍተኛ ምኞት ነበረው- ዓለምን አንድ አድርጐ የመግዛት። ብዙ ሺ ሰራዊት አልቆበትና

በርካታ ንብረት አውድሞም ምኞቱ ከሞላ ጐደል ተሳክቶለት ነበር፡፡ ሆኖም በድሉ ዋዜማ ዘመቻ ሳለ ባጋጠመው ሕመም የተነሳ ሞተ፡፡ ሞት አፋፍ ላይ ሳለ ታዲያ «ከዚህ ሁሉ ድካም በኋላ ቤሳ ቤስቲን ሳልይዝ መሞቴን ዓለም እንዲያውቅልኝ አንድ እጄን ከመቃብር ውጪ አድርጋችሁ ቅበሩኝ» በማለት ተናዞ ነበር፡፡

«መልካም ስም ከመልካም ሽቶ ይበልጣል» ብሎአል ጠቢቡ፡፡ ሕይወት ብዙ ውጣ ውረድ አለባት፡፡ ለተሻለ ኑሮ ብርቱ ጥረት ያስፈልጋል፡፡ መልካም ስምምታዲያ በዋዛ አይገኝም፡፡ በዚች ዓለም ላይ ከኖርን፣ ቢያንስም ቢበዛ አሻራችን ቢያንስ በቤተሰባችን ላይ ማረፉ አይቀርም፡፡ ስለዚህም «አንቱ» የሚያሰኘንንና ከዓለማችን ባለውለታዎች ተርታ የሚያሰልፈንን ጠፈፍ ያለ ተግባር ለመከወን እንጣር፡፡ ስማችን በሰዎች ልብ ውስጥ ጭምር እንጂ በሐውልት ላይ ብቻ ተጽፎ ሊቀር አይገባምና፡፡ ይሁንና ሐውልቶች ላይ የሚጻፉ ጽሁፎችንስ በጥሞና ተመልክተው ያውቃሉ? ልብ አላሏቸው ይሆናል ብዬ፣ የውጪዎቹንም ሆነ ያገራችንን የመቃብር ላይ ጽሁፎች ባጭሩ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ፡፡

«ሟች ምን ሲሰራ እንደኖረ የሚያውቁት ፈጣሪውና ዘመዶቹ ብቻ ናቸው፡፡ የተንከል ጽዋው ሞልቶ የፈሰስ፣ ሰው ጤፉ፣ ቀምነገር ጭንቁ፣ እንደነበረ ግን መቃብሩን ያየ ሁሉ አይጠራጠርም፡፡ ከምድራችን ሲሰናበት እፎይታ የተሰማቸው ዘመዶቹ መቃብሩ ላይ፤

«መልካም ያላደረገ እዚህ ያርፋል፡፡ በየሄደበት የሰራውን ማን ያውቃል? ጠያቂም የለው ተረስቷል» ሲሉ ጻፉ፡፡

አንዱ ደግሞ እጅግ ታታሪና የተዋጣለት ፀሐፊ ተውኔት ነበር፡፡ እሱን የማያውቅ ቢኖር የለየለት መሀይም

ወይም እብድ ነው። ሼክስፒር ይባላል። ሐውልቱ ላይ የተፃፈው ቃዲያ፤

«ክቡራን ወዳጆቼ ለየሱስ ብላችሁ

ከዚህ ቅንጣት አፈር አትቆንጥሩለት እባካችሁ።

እነህን ድንጋዮችም ያልነካ ይመስገን

አጥንቶቼን የሚነካ ሁሉ የተረገመ ይሁን» ይላል።

ገዛም ብትል መቀጮ የሚጣልባት የሚመስላት ዓይነት አሉብላቢት ነበረች። እንደ ተንጣጣች ነው ነግቶ የሚመሽላት። ምላሷን እረፍት እንደናፈቀው ነበር መቃብር የወረደችው። በአሉብላቢት ምላሷ ክፉኛ የተጠበሱት ቀባሪዎቿ ቃዲያ በመታሰቢያ ሐውልቷ ላይ፤

«ማስዝ አራቦላ እዚህ አርፋለች። ወደ ትቢያነትም ትለወጣለች። በወርሀ ማያዝያ ነው በሞት የተነጠቀች። ያን ጊዜም ነበር አፏን የያዘች» በማለት ጻፉባት።

እ.ኤ.አ በ1799 ሌክሲንግተን ማሳቹሴትስ ባለች ግሪን ቢሌጅ ውስጥ ለሰባ ሰባቱ ደቂቃ «የለውጥ ጦረኞች» ክብር በተቀረፀው ሐውልት ላይ፤

«ጸንታችሁ ቁሙ

ካልነኳችሁ አትንኩ።

ነገር ግን ጦርነት ፈላጊዎች ከሆኑ፣ ውጊያችሁን ከዚሁ ጀምሩ» የሚል ተፅፏል።

የተጠረበ እምነበረድ ቀርቶ ፍልጥ እንጨት እንኳ ለማስታወሻ ሊቆምለት የማይገባ ነበር። የብርሴ አንገትንና የብርጭቆ ኳኳታን ከልጆቹ አብልጦ የሚወድ። እምላኩም

ሆዱ ነበር። አጅሬ ውብ ዓለማችንን ሲሰናበት ያደረገውን ንግግርም በትእዛዙ መሠረት መቃብሩ ላይ ሰፍሮለት ይገኛል።

«ክቡር አንባቢ ሆይ፤

ያገኘሁትን ስበላ ስጠጣ ኖርኩኝ፤ አሁን በተራዬ እኔም በትል እየተበላሁ ነኝ»

ጀግኖች ናቸው። በውጊያ ላይ ሳሉም ነበር ማንነታቸውን ለመለየት እስኪያዳግት ድረስ የተበላሹት። ለነሀ ሙታን «ያልታወቀው ወታደር» የተሰኘ ሀውልት ቆሞላቸዋል። በላዩም፤

«ከእግዚአብሔር በቀር፣

ማንም የማያውቀው ወታደር፣

እዚህ አርፏል በክብር» የሚል ተጽፎላቸዋል።

ለናቱ ላረቁ ነው። ጠዋት ማታ እንደጨለጠ፤ ጤንነቱንና ክብሩን ነስቶ እንደተሰፋደደ ኖሮ በመሞቱ፤

«ሚስተር አዳም እዚህ አርፏል። የሸቃቀለውን ሲጠጣበት ከርሞ፤ ለስንቱ እሚበቃውን አረቄ ለብቻው ግፎ፤

ዳግመኛ እንዳይሸቅል ሞት አጋድሞት

በሽክም ነው እዚህ የደረሰው» ሲሉ ወዳጆቹ ሀውልቱ ላይ ፃፉ።


ጀግናው ሌ/ኮሎኔል አብዲሳ አጋ መቃብር ላይ እንደተፃፈው «ሰው ምን ጀግና ቢሆን መልአከ-ሞትን ድል ማድረግ አይቻለውምና መዘጋጀት ያሻል።»

በርግጥ ባገራችን ባሉ መቃብሮች ላይ ክፉ ነገር ተፅፎ


ኣይቼ አላውቅም:: «ሙት ወቃሽ» ባለመኖሩ ሚች የሰይጣን ቁራጭ ቢሆንም እንኳን፣ ያልፈፀመውን ገድል ፈጥሮ፣ ለቤተሰቡ አሳቢ፣ ለእምነቱ ጠበቃ፣ ያገሩ ጀግና፣ የድሆች አባት እንደነበረ ይታተታል:: ግና ያልፈፀምነውን ጀብዱ ለመታሰቢያችን ብናጽፍ፣ በወንጀለኛነት ባያስጠይቀንም፣ ግብዝ መሆናችንን ይመሰክ ርብናል::

ምናልባት ለፍተን ጠብ ላይልልንና ዝነኞችም ላንሆን እንችላለን:: ሆኖም መልካም ስራን ብቻ እንስራ፣ እንትጋ:: ብንመሰገንም ባንመሰገንም የሰውን ልጅ ኑሮ ለማጣፈጥ እንጣር:: ስንቶች እንሆን በሕይወታችን ፀሐይ መጥለቂ ላይ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ «መልካሙን ገድል ተጋደልኩ፤ ኃይማኖቴን ጠበቅኩ፤ ሩጫዬንም ፈፀምኩ» ማለት የምንችል?




# ታላቅ ቅናሽ



# ሥራ አጡ


አንቶን ቼኾብ

(ትርጉም) መኩሪያ መካሻ


በሕግ ትምህርት የዲፕሎማ ምሩቅ የሆነው ፐርፐልኪን ክፍሉ ውስጥ ሆኖ የሚከተለውን ይጽፍ ጀመር፡-

ውድ አጎቴ ኢቫን ኒኮላየቪች! ከዚያ ካጻፍክልኝ የድጋፍ ደብዳቤህና ምክርህ ጋር የሎስ ያንሳህ! ተከብሬና ለቀኝነቴን እንደያዝኩ ሥራ ፈት ሁኜ ብቀር ይሻለኝ ነበር፣ በእንዲህ ዓይነቱ ቁሻሻ ውስጥ ገብቼ ከመንቦጫረቅ ይልቅ።

እንዲያውም አንተ ነህ በደብዳቤህና በምክርችህ ገፋፍተህ ለዚህ የዳረከኝ:: ዓሣ በልቶ እንደ ተመረዘ ሰው ሁኚልሀለሁ:: እጅግ በጣም ይዘገንናል:: የደረሰብኝን የአእምሮ ብክለት በቮድካ፣ በእንቅልፍ ወይም በሌላ መንፈስ አዳሽ ስሜት ማስወገድ አይቻለኝም:: አየህ አጐቴ! ምንም እንኳ ምራቅህን ዋጥ ያደረክ ሰው ብትሆንም ትልቁ ክብት ማለት አንተ ነህ:: ለምንድነው አስቀድመህ እንዲህ ዓይነቱ ዕኩይ ነገር እንደሚገጥመኝ ያላስጠነቀቅከኝ?! ያሳፍራል::

የደረሰብኝን መከራ ሁሉ እዘረዝርልሃለሁ:: እስቲ ይህን ደብዳቤዬን አንብብና የሠራኸኝ በደል እንኳ ይሰማህ:: ይኸውልህ፣ የጻፍክልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በመጀመሪያ ይገቤ ባብኮብ ወዳልከኝ ሰው አመራሁ:: በባቡር መንገድ አስተዳደር ጽ/ቤት ውስጥ አገኘሁት:: ይህ ሰንዘሮ፣ ራሰ በራና አመዳም ሽማግሌ ክብ ጺሙን ተላጭቶ ተኮፍሷል:: የላይኛው ከንፈሩ ወደ ቀኝ፣የታችኛው ደሞ ወደ ግራ ተጣሟል:: ለየት ባለ ወንበሩ ላይ ተሰጥጦ ጋዜጣ ያነባል::

በረኸርሙ አግዳሚ ወንበር ላይ ደግሞ ዳጐስ ያለ መጽሐፍ የያዙ ሴቶች እንደ አፓሎን[1] ከበውት ተቀምጠዋል:: ሴቶቹ በእንግዶች ተራ መጠበቂያው ላይ የተቀመጡ ሽቅርቅሮች ናቸው:: እነዚህን ተመልክቶ ከድሆች ማመልከቻ ጋር ሲያስተያያቸው አእምሮን ይፈታተናል:: ለመሆኑ እነዚህ እዚህ ምን ይሠራሉ? አባታቸውን ወይም አጐታቸውን ነው የሚንከባከቡት? ወይስ የሂሳብ ሠራተኛ ማማሚያዎች ናቸው? ብቻ ኋላ ላይ እንደተረዳሁት እነሱ ምንም አይሰሩም፤ እንዲያውም

---

1 - (አፖሎ - በጥንት የግሪክ ሀተታ መናፍስት (mythology) የዜናስ ልጅ)

ሥራቸው የሚሸፈነው ራሳቸውን መግለጽ በማይችሉ ከ10 እስከ 15 ሩብል በወር በሚከፈላቸው ሠራተኞች ነው አሉ:: ለዚያ ለባብኩሽ ደብዳቤህን ሰጥቼው ነበር፤ ተቀመጥ እንኳ ሳይለኝ ነው መነጽሩን አድርጎ ደብዳቤውን ቀስ ብሎ ማንበብ የጀመረው:: «አጐትህ ክፍት ቦታ እየጠየቁልህ ነው» አለኝ መላጣውን እየጠራረገ:: ክፍት ቦታ እንደሆን የለንም፤ በቅርቡም መኖሩን እጠራጠራለሁ፣ ለማንኛውም ግን ለአያትህ ስል እሞክራለሁ... ይህንኑ ለዋና ሥራ አስኪያጅ አስታውቃለሁ:: ምናልባትም የሆነ ቦታ እናገኝልህ ይሆናል አለኝ::

በዚህ ጊዜ ከደስታ የተነሳ መዝለል ነው የቀረኝ:: «ግን አንተ ልጅ! ይህ ቦታ የተያዘው ለአጐትህ ብቻ ነው፣ ከእሱ የተቀበልኩት ምንም ነገር የለም፣ ቦታው ላንተ መቼም... እንደሚታወቀው... መቼም ታስመሰግነኛለህ ብዬ አስባለሁ... ተገቢውን ግን ማድረግ ይገባሃል... መቼም የምልህ ሳይገባህ አይቀርም አይደል?... ሲለኝ በጣም ተናደድኩ::

አንተ ግን እንዲያው በባዶ ይህን ክፍት የስራ ቦታ እንደማይሰጡኝና መክፈልም እንዳለብኝ አላስጠነቀቅከኝም:: ይህ ዓይነቱ ግዥና ሽያጭ በይፋ መፈጸሙን ትንፍሽ ያላልከኝ ምን ሁነህ ነው?

አጐቴ ዋ! በተለይማ ያ ባብኩሽ በሴቶች ፊት ያለኝ ነገር በጣሙን ነው ያናደደኝ:: ቀጥታ እኔው ጉቦ የተቀበልኩ ያህል ተሰማኝ:: ፊቴ ተለዋወጠ፣ ዓይኔን ጋረደኝ፣ በመጨረሻም ሃያ የሚሆኑ የሚያሾካኩ ሴቶች ዓይን ተከትሎኝ ወደ መውጫያው በር ሸኘኝ:: ከፊት ለፊቴ የሆነች አስደንጋጭና ቀጫጫ ሴት እያንሾካሾከች ካለ ባብኩሽ ባዶ ቦታ ላገኝልህ እችላለሁ... አምስት ድፍኑን አስጨብጠኝና

ወደ ሳሃር ሚዶቪች ላቅርብህ፣ እሳቸው እዚህ ባይኖሩም ቦታ ያገኙልሃል፤ ደግሞ እኮ ብዙ እያስከፍሉህም ያው ለመጀመሪያው ዓመት ግማሽ ደሞዝህን ብቻ ነው የምትለቀው አለችኝ።

ፊቷ ላይ መትፋት ያስፈልግ ነበረ፤ ግን አመስግኜና አእምሮዬ በሁኔታው ተናግቶ ቀጥታ ወደ ሽማኬቪች አመራሁ። ይህ ሰው ልስልስ፣ ደዘደገና ዓይነ-ሎልሚላ ነው። ዓይኑ በቅባት ርሷል። የወንድምህ ልጅ መሆኔን ሲያውቅ ከመጠን በላይ ፈንጥዞ የሚሆነውን አሳጣው። ሥራውን አቆመና ሻይ ጋበዘኝ። እንደት ያለ ሰው ነው? ፍጥጥ ብሎ እየተመለከተኝ ካንተ ጋር የምንመሳሰልበትን ምልክት ይፈልግ ገባ። አንተንማ ያስታወሰው በዕንባ ነው። የመጣሁበትን ምክንያ ስነግረው ትከሻዬን መታ፣መታ እያደረገ አበረታታኝና «ስለ ሥራዬ መናገር ስልችቶኛል... ሥራ መቼም ይበዛብኛል። ሥራ እንደ ድብ ወደ ዱር ገብቶ የሚሸሽግ ቢሆን ኖሮ በምን ዕድሌ» ብሎኝ «ለመሆኑ ምሣህን ዬት ነው የምትበላው? ሌላ ፕሮግራም ከሌለህ ወደ ፓልኪን ሆቴል እንሂድ! እዚያ ትንሽ እንጨዋወታለን» አለኝ።

በደብዳቤዬም ውስጥ የፓልኪንን የሆቴል የሂሣብ ደረሰኝ እንድታየው ልኬልሃለሁ። በደረሰኙ ላይ የምታየው 76 ሩብል ጓደኛህ ሽማኬቪች የበላበትና የጠጣበት ነው። ታዲያ እኮ ሂሣቡን የሸፈንኩት እኔው ነኝ። ከፓልኪን ሆቴል ቀጥሎ ሽማኬቪች ወደ ትያትር ቤት ወሰደኝ። የመግቢያ ትኬቱን ግን የገዛሁት እኔ ነኝ። ከዚህ ሌላ ምን ልጨምርልህ? ከትያትር በኋላ ያንተው «አታላይ» ከተማው ውስጥ እንድንዘዋወር ነግሮኝ ነበር። ግን እኔ ሙልጩን ስለወጣሁ አልተቀበልኩትም። ሽማኬቪች ከእኔ ሲለይ ላንተ የከበረ

ሁሳምታ እንዳቀርብለትና ክፍት የሥራ ቦታም ከአምስት ወራት በፊት እንደማያገኝልኝ ነገረው ብሎኝ ሊለየኝ ተነሳ::

ቀጥሎ ሆዴ ላይ መታ፣መታ እያደረገኝና እየቀለደ «ቦታውን በዋዛ አልሰጥህም፤ እንዳንተ ላለው የዩኒቨርስቲ ምሩቅ በእኛ መሥሪያ ቤት ውስጥ መሥራት ለምን ይጠቅምሀና ነው? ገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ መቀጠር ይሻልህ ነበር!» አለኝ:: እኔ ግን ስለ ገንዘብ ሚኒስቴር ክፍት ቦታማ ካንተ በላይ አውቃለሁ አልኩት በውስጤ::

ሦስተኛውን ደብዳቤህን ይዤ ወደ ክርስትና ልጅህ ሃላቶብ ነው ያመራሁት፤ ወደ ዥቮድሮ- ሃምስክ ባቡር ጣቢያ መሥሪያ ቤት:: እዚያ የሚገርም ነገር ተፈጠረ:: እነዚያን ባብኮብና ሽማኬቪች የተባሉትን ሰዎች ሽክ ብለው ባንድ ላይ አገኘኋቸው:: መቼም ደግሜ ደጋግሜ እረግምሃለሁ- የሎስ ያንሳህ! ከመጠን በላይ ተናድጄያለሁ:: ደግሞም በዚህ የምትወቀሰው አንተው ነህ:: ያንተን ሃላቶብ አላገኙሁትም:: የሆነ አንድ አዲኮሎኖብ የተባለ ሰው ነው የተቀበለኝ:: ቀጫጫ፣ ደረቅና ቀላጢ መሳይ ነው:: እኔ ክፍት የሥራ ቦታ እንደምፈልግ ሲያውቅ እንድቀመጥ ፈቀደልኝና በዛሬ ጊዜ በምን ዓይነት ችግር ክፍት ቦታ ሊገኝ እንደሚችል ሲዘበዝብልኝ ቆየ:: ከረኸርም ገለጻዎቹ በኋላም ስራ እንደሚያፈላልግልኝ ቃል ገባልኝ፤ አበረታታኝ:: እኔ ታዲያ ጉቦ እንደማይሰጥ ሰው ሁኜ እየተሰናበትኩት ገንዘብ መዳፌ ውስጥ ይዤ ተጠጋሁት::

አንድ ድንገተኛ ተቀባይ እጅ ሲነካካኝ ይታወቀኛል:: ፊቱ ሁሉ ጥርስ መስሎ እንደገና ቃል ገባልኝ:: ግን ታዲያ አዲኮሎኖብ ማንም በማያይበት ደረጃ ላይ ሁኖ ፊራ ተባ እያለ ሌላ ሰው እንዳያየው ይቅበጠበጥ ነበር:: ከዚያም

እንተመተመ... «በታውን ቃል እገባልሀለሁ፤ ግን የምሥጋና ዋጋ አልቀበልም... ፈጽሞ! ፈጽሞ! አይሆንም! አይሆንም! አትቀየመኝ...»

የእጁን ጭብጥ መዳፌ ላይ አስቀምጦ ገንዘቤን መለሰ። የመለሰልኝ ግን እራቱን ሩብል ሣይሆን ሦስቱን ብቻ ነው። ምን ዓይነት ትንግርት ነው?! የሆነ ተአምራዊ ነገር ተሠርቶ መሆን አለበት እንጂ የእኔዎቹ አራቶች እንዴት ወደ ሶስቶች ይቀየራሉ? ይደንቃል።

ይልቅስ ለግሪዛዱቦቭ ያደረስኩት አራተኛ ደብዳቤህ ከሌሎቹ በአንጻራዊነት ሲታይ ንፁህና ትክክለኛ ይመስለኛል። ወጣት፣ መልከመልካምና አለባበሰ ጽዱህ ሰው ነው። ሰልቸት ያለና ፍቅር አልባ አቀባበል ያድርግልኝ እንጂ ትሁት ነው። ከእሱ ጋር ባደረኩት ውይይት ዩኒቨርስቲ እንደጨረሰና በእነሱ ዘመን ለቁራሽ ዳቦ ሲል በረዶ ውስጥ እንደገባ ዓሣ ያላየው መከራ እንደሌለ ነገረኝ። ለጥያቄዎቼ በከፍተኛ ስሜት ተጨንቆልኝ «ከሁሉም በላይ የተማሩ ሠራተኞችን ማግኘት ስመኘው የነበረ ነው...» አለኝ። ግን እኮ ሦስቱ አመላልሶኛል፣ ሦስቱንም ጊዜ ግን ምንም የተለየ ነገር አልነገረኝም። ለስለስ ብሎ ከጥያቄዎቼ ሁሉ ይሙለጨለጭ ነበር።


ዛሬም ወደ ግሪዛዱቦቭ ዘንድ እራቴ ተመላለስኩ... እንደከዚህ ቀደሙ ለስለስ ቢልም ግና የሰጠኝ ልዩ መልስ አልነበረም። በጣም አስገርሞኛል?... ስለ ዕውነት ለመናገር እኔን ከዚህ ዓይነቱ ጋር ያያያዘከኝ አንተው ነህ።

አይሄ! አሁንስ የሚሆነው ይሁን ብዬ ወስኜያለሁ። በሕይወቴ ውስጥ ይህን መሞከሬ ጥሩ ነው። ስሜቴ ሁሉ መቀመቅ ገብቷል። አልቻልኩበትም፣ የጉቦ አሰጣጥ


ጥበቡንም አላወቅኩበትም:: ፊቴ በፍርሃት ቀልቶና ሰውነቴ ተንቀጥቅጦ ለዘመናት ያጠራቀምኩትን ከኪሴ አውጥቼ ግሪዛዱቦቭ ሳያየኝ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩ:: እንደ ዕድል ሆኖ ግሪዛዱቦቭ ጠረጴዛው ላይ መጽሐፍት ሲያስቀምጥ ያስቀመጥኳቸውን ገንዘቦች ሸፈናቸው:: ሳይሳካልኝ ቀረ፣ግሪዛዱቦቭ ገንዘቦቹን አላየም ማለት ነው::

ገንዘቦች ወረቀት ውስጥ ተደብቀው ሊጠፉ ይችላሉ ወይም የቢሮ አፅጂዎች ይመነትፉታል:: መቼም እሱ አይቶት ቢሆን ሊሰድበኝ ይችላል ብዬ እገምታለሁ:: አጐቴ Mon Oncle በዚህ ሁኔታ ገንዘቦቹ ጠፍተዋል ማለት ነው:: ያሳዝናል! አንተም በተረገመው ምክርህ አናደኸኛል ... በል! ደብዳቤዬን ማቋረጤ ነው:: የሆነ ሰው በሬን እያንኳኳ ስለሆነ:: በሩን ከፈትኩ ...

ይኸውልህ አሁን ከግሪዛዱቦቭ ደብዳቤ ደረሰኝ:: በወር 60 ሩብል የሚገኝበት የንግድ ዕቃዎች ቁጥጥር ክፍል ውስጥ ክፍት የሥራ ቦታ እንዳለ ጻፈልኝ:: ይህ ከሆነ ጠረጴዛው ላይ የተውኩለትን ገንዘብ አግኝቷል ማለት አይደል?



ስራ ከምፈታ ...



# «ይህ አሜሪካ ነው»

. ተስፋዬ ገብረአብ

አሜሪካን ረጋ ብሎ ለሚያስተውላት ውብም አስቀያሚም ናት፡፡ ለቸኰለ ግን ውብ ብቻ ናት፡፡ አልቸኰልኩምና በሶስት ወር ውስጥ፣ ጓዳ ጐድጓዳዋን ሁሉ ለማስተዋል የበቃሁ ይመ ስለኛል፡፡

ዋሽንግተን ዲሲን ላይ ላይዋን፣ ሲያትልን /ዋሽንግተን ስቴት/ ግን የነዋሪውን ያህል አወቅኋት፡፡

ሲያትል ውብ ናት፡፡ የዋሽንግተን ስቴት ትልቅዋ ከተማ

ሲ.ያትል የበረዶአማው አላስካና የካናዳዋ ባንኩቨር ጐረቤትም ናት። አየርዋ ተስማሚ ነው። የሰላማዊ ውቅያኖስ ማዕበል ሲያጫውታት ይውላል። በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ሀይቆች የተሞላችው ውብ ከተማ የመላው አሜሪካ ነጭ ባልቴቶች መሰብሰቢ ናት። አሰልቺው ነገር የባልቴቶችና የሽማግሌዎች ቁጥር መብዛት ነው። አውቶቡስ ስጠብቅ ያገኘሁዋት አንዲት አሮጊት፡-

«ከየት ነህ?» ስትል ጠየቀቺኝ። መቼም ወሬ ሲወዱ ለጉድ ነው። እንዳንዱም ለሚያዳምጣቸው ሰው የአውቶቡሱን መሳፈሪያ እስከመነፈል ይደርሳሉ።

«ከኢትዮጵያ ነኝ» ካልኩ በኋላ «አንቺስ?» አልኳት።

«የትውልድ ስፍራዬ ቨርጂኒያ ነው። ሲያትል 60 ዓመት ኖሬአያለሁ» ብላ ባለቀ ጥርስዋ ሳቀች።

«አሁን እድሜሽ ስንት ነው?» ስል የጠቅሁዋት።

«ዘጠና ሶስት» አለች።

ባልቴቷ ጠንካራ ናት። ያለ ደጋፊ ነበር የምትራመደው።

«እድለኛ ነሽ!» ካልኳት በሁዋላ «ባሳለፍሽው ረጅም ዘመን ውስጥ ትዝ የሚልሽ ጥሩ ነገር ምንድነው?» ስል ጠየቅሁዋት።

«ሶስተኛውን ቦይፍሬንዶን ከቶ አልረሳውም። ጥሩ ፍቅር አሳይቶኛል» ብላ በሀሳብ ባህር ውስጥ ሰጠመች። ወሬውን ወደፍቅር ታሪክዋ ስለመራችልኝ ደስ ብሎኝ አንድ ማወቅ የምፍልገውን ጥያቄ አነሳሁባት።

«አሜሪካ ውስጥ ፍቺ የሚበዛው ለምንድነው?»

አሮጊትዋ ሳቀች::

«ምክንያቱማ ግልፅ ነው» አለችኝ::

«ምንድነው?»

«This is America»

እየቆየሁ የተረዳሁት አሮጊትዋ ያለቺኝን ነው:: 'ይህ አሜሪካ ነው' የሚለው ንግግር በጣም ተለምዶአል:: ለደስታውም ለችግሩም ምላሹ «This is America» የሚል ነው:: አሜሪካ ታዲያ ምንድናት?

አሜሪካ ውስጥ ሁሉንም መሆን፣ ሁሉንም ማድረግ ይቻላል:: አሜሪካ ባህል የለም፣ ፍቅር የለም፣ ማህበራዊ ህይወት የለም:: ገንዘብ ግን አለ:: ገንዘብ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይቻላል:: አሜሪካ ማለት አንድ ሰው «ብቻውን» የሚኖርበት አገር ማለት ነው:: ጐረቤት የለም:: ዘመድ የለም:: ጓደኛ የለም:: ገንዘብ አለ:: የአሜሪካ ብር ሊገዛው ያልቻለው ነገር ቢኖር ፍቅርን ነው:: ያቺ አሮጊት በ93 ዓመቷ ትገዛ የሚላት፣ እውነተኛ ፍቅር ያሳያት አንድ ጐልማሳ ብቻ ነው:: ፍቅር በአሜሪካ ብርቅ ነውና::

ሲያትል ውብ ናት ብዬ ጀምሬ ነበር:: አዎን ውብ ናት:: ስለ አሜሪካ መንገዶች፣ የመገናኛ አውታሮች፣ ትምህርት ቤቶች፣ እንዴት መግለፅ ይቻላል? ከኛ ኑሮ ጋር ከቶ አይገናኝም:: የምግብ ዋጋ ርካሽ መሆኑ ትልቁ ጥሩ ነገር ነው:: ቤት ኪራይ አለማጣት (ኪራዩ ቢወደድም) ሌላው እድገት ሲሆን ማቀዝቀዣ በየቤቱ ማግኘት መቻል ደግሞ የተሟላ ኑሮ ወደመኖር ያደርሳል:: ሰው እንደልቡ ስራ አግኝቶ፣ ጥሩ መመገብ፣ በጥሩ ቤት መኖርና ሰውነቱን

በየእለቱ መታጠብ ከቻለ፣ ትልቅ የእድገት ደረጃ ይመስላል:: ይህም ብቻ አይደለም:: ስሙን በእንግሊዝኛ መፃፍና ማንበብ የቻለ የፋብሪካ ስራ ሰርቶ ማደርና፤ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥም መኪና መግዛት ይችላል:: መማር የፈለገ መማር፤ ማበድ የፈለገ ደግሞ ማበድ የሚችልበት አገር ቢኖር አሜሪካ ነው::

እግዚአብሄርም ሰይጣንም ያሉበት አገር ቢኖር አሜሪካ ነው:: ዛሬ ከስራው የተባረረ ሰው፣ ነገ ሌላ ስራ ማግኘት የሚችልበት አገር አሜሪካ ብቻ ሳይሆን አይቀርም:: ስልጣኔውን አይቶ መጥገብ አይቻልም:: ቆሻሻ በየመንገድ አለመጣል ስልጣኔ ነው፤ የትራፊክ ህግ ማክበር፤ መብትና ግዴታን ማወቅ፤ የመታወቂያ ወረቀት በግማሽ ሰዓት ውስጥ ማግኘት መቻል፤ ፖስታ በየቤቱ መታደሉ፣ ቴሌፎን እያንዳንዱ ሰው በየቤቱ የፈለገውን ያህል ማስገባት መቻሉ፤ ሰራተኛ እንጂ ወሬኛ አለመከበሩ፣ እድገትና ስልጣኔ ነው:: ስራ አለመናቁም የእድገት ምልክት ነው:: ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ «ዝቅተኛ ስራ» ይሰራሉ የሚለው ትችት ቦታ እንደሌለው የሚታወቀው አሜሪካንን ማየት ሲቻል ብቻ ነው::

ዝቅተኛ ስራ ማለት ታክሲ መንዳት ነው የሚሉ ይኖሩ ይሆናል:: ኢትዮጵያውን ከዚህ ሄደው የሚሰሩት ትልቁ ስራ ታክሲ መንዳት ነው:: በቀን ከ100 ዶላር በላይም ያገኙበታል:: መኪና መጠበቅ ዝቅተኛ ስራ ነው የሚሉ ይኖራሉ:: ይህ ስራ በቀላሉ አይገኝም:: ይህን ስራ የሚሰሩ ሰዎች በቀን እስከ 100 ዶላር ያገኛሉ:: የጃጁ አሮጊቶችና ሽማግሌዎችን መጠበቅም ትልቅ ስራ ነው:: ሰዎቹን ከመመገብ ጀምሮ ጢም እስከመላጨት ድረስ ያለው ስራ በርካታ ኢትዮጵያውያን የሚሰሩትና ትርፍ ሰዓትን ጨምሮ በቀን እስከ 150 ዶላር የሚያገኙበት ስራ ነው:: ሌላው የፅዳት ስራ ነው:: ዝቅተኛ ስራዎች የሚባሉትም ይህን መሰል ስራዎች ናቸው:: ግን

የተዋረዱ ስራዎች ናቸውን? «ጠራዳ» የሚል ትዕል የሚሰጠው ስራስ ይኖር ይሆን?

የአሜሪካ ትልቁ ውበት እዚህ ላይ ነው:: የ95 ሞደል ዘመናዊ መኪናውን እያሽከረከረ ዕዳት የሚሰራውን ሰው ለማንቋሸሽ መሞከር፣ ራስን ማታለል ብቻ ነው የሚሆነው:: እዚያ ስራ ክቡር ነው:: አሜሪካ አሳፋሪው ስራ መለመን ነው:: ነጭ ለማኞችን ተመል ክቼያለሁ:: መለመን ስለሚያስፈራቸው «ስራ እፈልጋለሁ» የሚል ዕሁፍ ደረታቸው ላይ ለጥፈው ነው የሚለምኑት። ስራ በዘቶ፣ ስራተኛ እንዲጠረ፣ ስለሚታወቅ የሚለማቸው የለም እንጂ:: አሜሪካ ስራ አለ፣ ገንዘብ አለ፣ ጥሩ ኑሮም አለ:: ችግሩና የአሜሪካ አስቀያሚነት የሚጀምረው ከስራ መልስ ነው:: ከስራ መልስ አሜሪካ ታገጣለች::

እያንዳንዱ የግለኝነትን ርችት በየቤቱ ይተኩሳል:: በሩን ዘግቶ ብቻውን ገንዘቡን ይቆጥራል:: ሚስቱንም ስለማያምናት ለኪሱ መቆለፊያ ጉዋንንቸር ይገዛል:: ባልና ሚስት ገንዘብ ያዋጡና ማቀዝቀዣውን ይሞላሉ:: ቢታመሙም ከየራሳቸው ነው ከፍለ ው የሚታከሙት:: ልብሳቸውን ራሳቸው ይገዛሉ:: ቤት ኪራይ አዋጥተው ይከፍላሉ:: የደባል ያህል እንኳ መግባባት ያቅታቸዋል:: አሜሪካኖች ሲጋቡ የሚሰነዝሩዋት አንድ ቀልድ አለች «የፍቺያችንን ወረቀት ፈረምን» የምትል::

ብዙዎች ስለ አሜሪካ ሲገልፁ «በአሜሪካ ገንዘብና ክብር አለ:: ማህበራ ህይወት ግን የለም» ሲሉ ደፋፍነው ያቀርቡታል:: በዝርዝር ሲቀርብ በተገባ ነበር::

ከአንድ ኢትዮጵያ ጋር ተዋውቄ ነበር:: ዘጠኝ ዓመት ሲያትል ተቀምጦአል:: ሁለት ታክሲዎች አሉት:: ሰውየው

44 ዓመቱ ነው። ባንክ 60ሺ. ዶላር አስቀምጦአል። ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ፍላጐት የለውም። አልወለደም፤ ሚስት ማግባትም አይፈልግም። ከተጣላን ንብረቴን ትካፈለኛለች፤ ብሎ ይፈራል። ስለዚህ በቀን ሶስት ሰዓት ብቻ እየተኛ፣ ሌላውን ጊዜውን በመስራት ያሳልፋል። ዜና አያዳምጥም፤ አይማርም፤ አይዝናናም። ሌላው ቀርቶ መርከብ ጥቂት ዶላር ከፍሎ በፓስፊክ ውቅያኖስ ላይ በመንሸራሸር እንኳ ንፁህ አየር ተመግቦ አያውቅም።

«የደስታህ ምንጭ ምንድነው?» አልኩት፣

«ብዙ ገንዘብ አለኝ» ሲል ነበር የመለሰልኝ። ገንዘቡ ግን ባንክ ነው ያለው። የዚህ ሰው ታሪክ አሳዛኝ የሚሆነው ገንዘቡን ለማንም ሳይናዘዝ ድንገት ከሞተ ነው።

አሜሪካ ውስጥ ገንዘብና ክብር ቢኖርም በጭንቀት የተሞሉ ሰዎች እያሌ ናቸው። እንደ ከእይናቸው የማይለይ ጥቂት አይደሉም። በሚያጠራቅሙት ገንዘብ ይጨነቃሉ፤ በባልና ሚስት መካከል ያለው ትስስር፣ የወሲብ ወይም የጥቅም እንጂ እውነተኛ ፍቅር ስላልሆነ ይጨነቃሉ። ስራቸው ስለማያደክማቸው፣ ሳይማሩ በመቅረታቸውና እድሜያቸው በመግፋቱ ይጨነቃሉ፤ ወገኖቻቸውን እየናፈቁ ይጨነቃሉ፤ የጭንቀት ምክንያቶች ብዙ ናቸው።

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የያዙትን ይዘው ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ይመኛሉ። ሆኖም ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ በቂ ኢንፎርሜሽን ስለሌላቸው በስጋት ይዋኘቃሉ። ድህነቱ፣ የትራፊክ መጨናነቁ፣ የቤት እጥረትና ቢሮክራሲው ያስፈራቸዋል። አሜሪካ ገንዘብ ለመሰ ብሰብ እንጂ ለኑሮ ተስማሚ አለመሆንዋን የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። አሜሪካ ውስጥ ብዙዎች ትዳር መያዝ የማይፈልጉበትና

የልጅ ፍቅርም የሌላቸው ለምን እንደሆነ የጠየቅሁት አንድ ግለሰብ እንዳብራራልኝ፣

«በርግጥ ሁሉም ትዳር አይፈልግም ማለት አይቻልም:: ጥሩ ትዳር መስርተው፣ ልጆች ወልደው በጨዋ ደንብ የሚያሳድጉ የሀገራችን ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም:: ባጠቃላይ ሲታይ ግን ትዳርና ልጅን የመሸሽ ዝንባሌ አለ:: ይህን የሚያደርገው ስርዓቱ ነው:: ነገ ሲል ፖሊስ ዘንድ የሚከሰኝን ልጅ ለምን እወልዳለሁ? ከ18 ዓመቱ በሁዋላም አባትነቱን ይክዳል:: ታዲያ ምን አለፋኝም» የሚሉ አሉ:: የልጅ ጉዳይ ከተነሳ፣ አንድ ገጠመኝ ላውጋችሁ፤ በቤቱ እንጀራ መመገብ የሚያዘወትር አንድ ሀበሻ ነበር:: ልጁ ግን ያን እንጀራ በመጥላቱ «ሀምበርገር ይገዛልኝ» ይለዋል:: አባት ሊያግባባው ሞከረ:: እንጀራ የሀገራችን ባህላዊ ምግብ እንደሆነና ሊወደው፣ ሊለምደው እንደሚገባ ይደሰኩራል:: ልጅ አሻፈረኝ ይላል:: አባት ተቆጣ፣ «ወደድክም ጠላህም ትበላለህ» ይለዋል:: ልጅ ስልክ አንስቶ «911» ደወለ:: ፖሊስ ጡሩንባውን እያጮኸ ከተፍ:: ልጅ «የማልፈልገውን ምግብ እንድበላ አስገደዱኝ» ብሎ እንጀራውን ለፖሊስ ያሳያል:: ፖሊሶች እንጀራው እንዲመረመር በመቀስ ለናሙና ቆርጠው ይወስዳሉ:: የስንዴና የጤፍ እንጀራ ነበር:: አባት ተጠየቀ፣ ስለ ባህላዊው ምግብ አብራራ:: የተወሰነው ውሳኔ፤ «ልጁ ያሻውን የመመገብ መብት አለው» የሚል ሲሆን፤ አባት የልጁን ፍላጐት ማሙዋላት ካልቻለ ደግሞ ልጁ አሜሪካዊ በመሆኑ መብቱ ተጠብቆለት መንግስት ያሳድገዋል:: አባት ምን ይበል? የሚገርመው ደግሞ ልጅ መብቱን በማስከበሩ እየፈነጠዘ፤ ጥቂት ሲናገሩት ወደ ቴሌፎን መሮጡ ነው:: ለልጁ ጨዋታ ነው:: ለአባት ግን የአባት የልጅ ግንኙነት

ሻክሮበት በውስጡ ቆሽቱ እያረረ ልጁን እየተለማመጠ ይኖራል። አሜሪካ የተወለዱ ልጆች ትምህርት ቤት ሲሄዱ መጀመሪያ የሚማሩት «አሜሪካዊ» መሆናቸውና መብታቸው ሲደፈር ለፖሊስ «911» መደወል እንደሚችሉ ነው።

አሜሪካ ላይ ሴቶች ያላቸውን መብት በመጥላትም በብቸኝነት የሚኖሩ አሉ። ይህም ቢብራራ መልካም ነው። የሚስት መብት ከባል ትንሽ ላቅ ይላል ልበል? ባልና ሚስት ሲጋጩ ባል ከቤት የመውጣት ግዴታ አለበት። ታዲያ ይህን መሰል ሁኔታ ያጋጠመው ሀበሻ «ወይኔ ሰውየው! ኢትዮጵያ ቢሆን ኖሮ በጥፊ ወልውዬ እለቃት ነበር» ሲል ሰምቼዋለሁ። የሀበሻ ወንድነት ባህሪው ገፋፍቶት ሚስቱን ቃሪያ ጥፊ ያቀመሰ አንድ ሀበሻ ወህኒ መውረዱን አውቃለሁ። ወህኒ ደግሞ ሶዶማውያን ደፈሩት። ከእስር ቤት ሲወጣ አበደ። አሁን በሲያትል ጐዳናዎች ላይ ጠጉሩን አንጨብርሮ እየለፈለፈ ይታያል። ታማኝነትና ፍቅር ስለሌለ ላለመከዳት ሲሉ ብቸኝነታቸውን የሚመርጡም አሉ። በየቦታው መጨፈሩን ወደውት ትዳር የማይዙም አሉ። አሜሪካ ውስጥ በገፍ የሚሸጡትን አርተፊሻል በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የሴትና የወንድ ብልቶችን ከ50-120 ዶላር እየገዙ ያንን፤ «በቂ ነው» ብለው የተቀበሉም መኖራቸውን አብራርተውልኛል።

ይህ ከተነሳ ስለፍቅር መደብር (Love boutique) ጥቂት ልናገር። የወንድና የሴት ብልቶች መሸጫ ሱቅ ነው። ማየት ማመን ነውና ገብቼ ሁሉንም ካየሁ በሁዋላ ሻጩን ማብራሪያ ጠየቅሁት። እንዲህ አለኝ።

«እነኚህ ሴቶች እጅግ ታማኞች ናቸው። አይክዱህም። ከኤድስ ነፃ ናቸው። እየወፈሩ አያስቸግሩህም። መርጠህ ታገባለህ። ከ16 ዓመት ኮረዳ ጀምሮ አሉ። በኤሌክትሪክ

ስለሚሰሩ የድካም ስሜት አይሰማቸውም:: የፈለግኸውን ስም ልታወጣላቸው ትችላለህ:: አይከ ሱህም:: የእድሜ ልክ ሚስት አገኘህ ማለት ነው::» ሲል ሊያግባባኝ ሞከረ:: አያይዞም «እንዲት ደምበኛችን በዓፊችልን ደብዳቤ ከናንተ ሉቅ የገዛሁትን ባሌን ወድጄዋለሁ:: በፊት ከነበሩኝ ባሎች ሁሉ የተሻለ ነው:: ለኔ ያለውንም ፍቅር አድንቄዋለሁ ብላናለች::»

ይህን ስሰማ ለጆሮዬና ለዓይኔ ቀፎኝ ነበር:: እየቆየ ግን የተለመደ ተራ ነገር ሆነብኝ:: እንዲያውም አንድ ሀንዳዊ የገዛትን «ሚስቱን» ሲያደንቃት ሰማሁ::

ከአሜሪካ መጥፎውን ትቶ፤ ደግ ደጉን መማርና መቅሰም ካልተቻለ አደገኛ ነው:: ተደጋግሞ ሲነገር የማይሰለቸውና የሚያጉዋጉዋው እንቁ የስራ ባህላቸው ነው:: የህዝቡ የስራ ባህል ያጉዋጉዋል:: ሰው የሚከበረው በስራው እንጂ በክራቫቱ አይደለም:: ሰነፍ ስራው ላይ አይቆይም፤ ይባረራል:: ጉበዝ ደግሞ ወፍራም ክፍያና ክብር ያገኛል:: ስለዚህ ሁሉም ጠንካራ ስራተኛ ለመሆን ይጥራል:: በህዝቡም ዘንድ ሆነ በምሁራኑ አካባቢ ያለው የማይደግ ጉጉት አስደናቂ ነው::

ሁልጊዜ ለለውጥ ዝግጁ ናቸው:: ከፋብሪካዎች የሚወጡት ምርቶች ተሻሽለው በወጡ ቁጥር ያን ማሻሻል ያመጣ ሰው ለዚያ እቃ ባለ መብት (patented) ስለሚሆን እጅግ ሀብታም ይሆናል:: ሌሎችም ከእርሳስ ጀምሮ የተሻለ ምርት ለማውጣት ይጥራሉ:: የመጨረሻ እድገት ወይም መሻሻል የሚል እምነት የለም:: ሁልጊዜ ለውጥ፤ ዘወትር መሻሻል አለ:: የተሻለ መንገድ፣ ቤት፣ መኪና፣ ጠረጴዛ፣ ድስት ይሰራሉ:: ይህን ሳስተውል ስለ ሀገራችን አሰብኩ::

በማንኛውም ስራ ላይ ለማሻሻል ወይም ለውጥ ለማሳ የት ያለን ሞራል የደከመ ሆኖ አገኘሁት። በትንሹ የመርካት ዝንባሌያችን እድገታችንን ሳይገትተው አልቀረም።

ኢትዮጵያ ሳለ በአንድ የመንግስት ድርጅት ውስጥ በመካኒክነት ይሰራ የነበረ አንድ ግለሰብ ስለ ስራ ባህል ሲገልፅልኝ «ኢትዮጵያ ሳለሁ በምሰራበት መስሪያ ቤት ውስጥ ማኪና እንድሰራ ሲሰጠኝ መጀመሪያ ጋቢና ገብቼ ሁለት ሰዓት ያህል እተኛለሁ። ከዚያ ቱታ ቀይሬ እያፏጨሁ መስራት እጀምራለሁ። የስራ ሰዓት ሊያልቅ ሁለት ሰዓት ሲቀር ቱታ አውልቄ መታጠብ እጀምራለሁ። እዚህ ግን የመታጠቢያ ጊዜ ከስራ ሰዓት ውጪ ነው። ጥሩ ይከፍሉኛል። በደንብ እሰራለሁ። የሚገርምህ ከስራ ወጥቼ ምግቤን አበስላለሁ፣ ቤቱን አፀዳለሁ፣ ፀሎት አደርሳለሁ»

የአሜሪካ የቀብር ስርዓትም ድንቅ ነው። በአንድ ቀብር ላይ ተገኝቼ ነበር። ሁለት ሴቶች አባታቸው ሞቶ እየቀበሩ ነበር። ገንዘብ ከተከፈላቸው ቀባሪዎች ሌላ አንድ ሰው የለም። ታላቅ የምትመስለው ሴት እንዲህ ስትል ሰማሁዋት፣

«He was stupid»

«Not very much» አለች ታናሿ። አባታቸውን ቀበሩት። መኪናቸውን አስነስተው ነጎዱ። እኔ ብቻ ቀረሁ። ለሰውየው ላለቅስለት ፈልጌ ነበር። ልጆቹ ጨካኞች መስለው ታዩኝ። እየቆየሁ ግን 'የቀባሪ ጋጋታ ስራ ከማስፈታት በቀር ምን ይጠቅማል?' የሚል ሀሳብ መጣብኝ። ለሞተው ሁሉ ተላቅሶ ይቻላል? የሚደገፍ ባህል መስሎ ተሰማኝ።

አሁን ሲያትል ውብ ናት... ለስድስት ሺዎቹ

ኢትዮጵያውያንም ምቹ ናት። መልካም ማህበራዊ ህይወት አይኑራቸው እንጂ በልተው፣ ጠጥተው፣ጥሩ ኑሮ ኖረው ዘመዶ ቻቸውን አግዘው መኖር ይችላሉ። ይህ ብቻውን ግን ህይወት አይደለም። ብር ሲገዛው የማይችለው ብዙ ነገር አለ። ከወገን ጋር መኖርንና ፍቅርን ገንዘብ አይገዛውም። የራስ ህዝብ ሁልጊዜ የራስ ነው። ሌሎች ህዝቦች ደግሞ ሁልጊዜ የሌሎች ናቸው። እነሱ ሲስቁ የሳቁበትን ምክንያት ለማወቅ እየተጨነቁ መኖር ከባድ ነው። አሳሳቃቸው፤ ለቅሶአቸው፤ ሁልጊዜ የሌላ ነው። የኛ አይደለም። ለሰው ልጅ ትልቁ ሀብት ደግሞ የኔ የሚለው ነገር ሲኖረው ይመስለኛል።

እንዳልኩት አሜሪካ ጥሩ ናት.. ኢትዮጵያ ውስጥ ከመኖር አሜሪካ መኖር የበለጠ ይመቻል። ችግሩ ቁሳዊ ምቾት የመንፈስ ምግብ መሆን አለመቻሉ። ነው። ታዲያ መፍትሄው ምንድነው? የአሜሪካን ኤምባሲን ማስጨነቅ ወይስ የራስን አገር ምቹ ማድረግ?


ኢትዮጵያ ምቹ መሆን የምትችል ሀገር ናትን? መልሱ ግልፅ ነው። በስራ ካላደግናት ምቹ ናት። አሜሪካ በስራ የተገነባች አገር መሆንዋ ይታወሳል። ህዝቡ ስራ አይንቅም። ስለክብር መነካት ወይም ስለአያቶቱ ታሪክ ለማውራት ጊዜ የለውም። ይሰራል... ይሰራል... ይሰራል... ስራ ማንንም አልገደለም። ይልቁንም አገርን የሚገድል ወሬ ነው። ባህላችንን መለስ ብለን ስናየው ደግሞ ከስራ ይልቅ በጦርነት የታጨቀ ነው።

. «እዚህ ስንት ክብር የነበራቸው ሰዎች አሜሪካ ሄደው ታክሲ ይነዳሉ» ብለው ያሽሙዋጠጡ አንድ ሰው አውቃለሁ። እኚህ ሰው የመዝገብ ቤት ኃላፊ ናቸው።

የሚገርመው ግን የሚጠብቁትን መዝገብ ከአቡዋራ እንኳ ማዳን አልቻሉም፡፡ ከራቫታቸው ላይ ግን የአቧራ ጠብታ አይገኝም፡፡ ክብርና ኩራት፡፡

አሜሪካ ምቹ ናት፡፡ ሆኖም ወርቅማነትዋና ምቾትዋ የሚገኘው ላብ በማፍሰስ ነው፡፡ አሜሪካ ውስጥ እያንዳንዱዋ ሳንቲም የላብ ውጤት ናት፤ አሜሪካ ውስጥ የመንግስት ጥገኛ ጥቂት ነው፡፡ በመንግስት ማሳበብ ስህተት መሆኑን አሜሪካ ታስገነዝባለች፡፡ ስራ የመፍጠር አቅማችንና የስራ ባህላችን ሲሻሻል እድገታችን ፈጣን ይሆናል፡፡ ካልሰራን ታሪክ ነን፡፡

ያ ቀን ቅርብ ይሆን? ጠንክረን ከሰራን ቅርብ፣ በጣም ቅርብ ነው፡፡



# አተርፍ ባይ

ፍሬድሪክ ፎርሰይዝ

(ትርጉም) ገበየሁ ዋለልኝ

ማርክ ሳንደርሰን ሴቶችን ይወዳል:: ቢጠሩት የማይሰማ ቱጃር ስለነበር የፈለገውን ለማግኘት አይቸግረውም:: ዕድሜው ወደ አርባው ግድም የተቃረበ ቢሆንም ሴቶችን የሚማርክ ቁመናው አልሸሸውም:: አላገባም:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አንዲት ጥሩ የትዳር ጓደኛ እንደምታስፈልገው እየተረዳ መጥቷል:: መርጦ ማግኘት ይችላል:: ግን እሱ የሚፈ ልገው አንዲት ልጆች የምወልድለትና ለትዳር ተስማሚ የሆነች ነበር::

የሚፈልገውን በትክክል ያውቃል። ሆኖም ባለፉት ጥቂት ዓመታት የሚፈልጋት ሴት ልታጋጥመው አልቻለችም። በመጨረሻ ተስፋው ሊሟጠጥ ሲቃረብ በአንድ የምሽት ግብዣ ላይ ሲመኘው የነበረው ደረሰለት። መመዘኛውን ከምታሙዋላ ኩሪዳ ጋር ተዋወቀ።

በግብዣው ላይ በአብዛኛው ዘንድ (ዓይኑ ያረፈባትን ሴት ጨምሮ) የሳንደርስን ማንነት በሚገባ የታወቀ ስለነበር ማንኛውንም ሰው በቀላሉ ቀርቦ ለማነጋገር ሰፊ እድል ነበረው። ወዲያው ተጠግቶ አነጋገራት። በቀላሉ ከሰው ጋር መስማማት የምትችል ሴት ሆናም አገኛት። ጭውውታቸውን ያላንዳች ችግር ቀጠሉ። ሳንደርስን ስለ አገሩ ስለ ለንደን፣ አጫወታት። እሷም ከባሏ ጋር ስለምትኖርባት በስፔን ወደብ ዳርቻ ስለምትገኘው አንድ ትንሽ ከተማ አወጋችው። ለንደን የመጣችው ቤተሰቧን ለመጠየቅና ወዲያውም የቀድሞ የትምህርት ቤት ጓደኛዋ ባደረገላት ጥሪ መሰረት ሳምንት ያህል ጊዜ ከእርሱ ጋር ለማሳለፍ እንደሆነ በተጨማሪ ገለጸችለት። በፓርቲው ማብቂያ ላይ ሳንደርስን የራት ግብዣ አቀረበላት። በደስታም ተቀበለችው።

ጠንካራ ግንኙነት ለመመስረት አንድ ሳምንት ብዙ አይደለም። ሆኖም አንድን ሰው በመጠኑም ቢሆን ለማወቅ ያስችላል። በተከታዩ ቀን ግብዣውን አክብራ በስፍራው ተገኘች። እየተመገቡም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይታቸውን ቀጠሉ። ቀደም ሲል ሲጐበኙት ከነበሩት ሴቶች በብዙ ነገር ልቃ አገኛት። ለሚጠይቃት ጥያቄ የምትሰጠው መልስና በጨዋታቸው መሐል የምታቀርባቸው ፍሬ ነገሮች ጠለቅ ያሉ ነበሩ። ይህም ለእርሷ ያለውን ፍቅርና አክብሮት በይበልጥ ከፍ አደረገው። ሳንደርስንም በበኩሉ ስለ ራሱና ስለሚያካሂደው የስራ እንቅስቃሴ በሰፊው አጫወታት።

ጭውውታቸው ሬስቶራንቱ እስኪዘጋ ቀጠለ። በመጨረሻም ወደ መኖሪያ ቤቱ ቢሄዱ ጭውውታቸው ሊቀጥል እንደሚችል ሐሳብ አቀረበ። ጥሪውን ቅር በማይለው መንገድ ሳትቀበል ቀረች። ለሁለተኛ ጊዜም በመሄጃዋ ቀን ዋዜማ ማታ ተገናኙ። የተገናኙት በጓደኛዋ መኖሪያ አቅራቢያ በሚገኝ የሕዝብ መናፈሻ ውስጥ ነበር። ደጋግመው ከተሳሳሙ በኋላ ጭውውታቸውን ጀመሩ።

«ለምን ባልሽን ፈትሽ አንጋባም?» በማለት ሳምንት ሙሉ ሲያስጨንቀው የቆየውን ሐሳቡን ገለጠላት።

«ፈጽሞ አላደርገውም» በማለት መለሰችለት።

«እወድሻለሁ። እኔ የምፈልግሽ ለጊዜው ሳይሆን ለዘለቄታው ነው። የፈለግሽውንም አደርግልሻለሁ።»

«በእርግጥ የፈለግሁትን ልታደርግልኝ ትችላለህ። ብቻ የእኔና የአንተ ነገር እስከዚህ መድረስም የለበትም ነበር። መጀመሪያውኑ ፍላጐትህን ተረድቼ አንተን ማየቴን ማቋረጥ ነበረብኝ።»

«ትንሽ እንኳን አትወጂም?» ሳንደርሰን ጠየቃት።

«በዚህ ጉዳይ ላይ ለመናገር በጣም ከባድ ነው» በማለት መለሰችለት።

«አሁን ወይም ምንጊዜም ልትወጂኝ አትችይም?»

«ሌሎች ስለአንተ የሚናገሩትና እኔ ደግሞ ቀርቤ ያየሁት እጅግ የተራራቀ ሆኖአግኝቼዋለሁ። ልወድህ እችላለሁ ወይም አልችልም ነበር»

«ታዲያ ለምን ባልሽን ፈትተሽ አታገቢኝም?»

«እማይሆን ነገር ነው። ባለቤቴን እንዴ

እኘብቼዋለሁ:: ልለየው አልችልም»

«እሱ ያለውን እኔ ላቀርብ የማልችለው ምን ነገር አለ?»

«ምንም የለም:: ብቻ ባለቤቴ የእኔ የቅርብ እርዳታ ያስፈልገዋል::»

«ለእኔም ያስፈልገኛል::»

«አንተ ያለ እኔ በቀላሉ መኖር ትችላለህ:: እሱ ግን ያለ እኔ ለመኖር ፈጽሞ አይችልም»

«አንጀላ፤ አንቺ እንደምትይው አይደለም:: እኔ በጣም ነው የምወድሽ:: እንደዚህ ዓይነት ሁኔታም ገጥሞኝ አያውቅም::»

«ደጋግሜ ልገልጽልህ ብዙ ሞክሬ ነበር:: ነገር ግን አንተ በጭራሽ የተረዳህልኝ አልመሰለኝም፤ ለባለቤቴ ልክ እንደሚተነፍሰው አየር አስፈልገዋለሁ::»

«ሞት ነዋ ከእርሱ የሚለይሽ?»

«አዎን፤ እንደእሱ መሆኑ ነው:: አዝናለሁ ባለትዳርነኘ:: የእኔና የአንተ ግንኙነት ከእንግዲህ እዚህ ላይ ማብቃት አለበት::» በማለት ተሰነባብተው ተለያዩ::

አንጀላ ሁሌተኛ እንደማታየው ቁርጡን ነግራው ብትለየውም ቅሉ፣ ሳንደርስን እሷን የማግኘት ፍላጐቱ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መጣ:: ሐሳቡንም ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ዘዴዎችን ማውጠንጠን ጀመረ:: በመጨረሻም አንጀላን ለማግኘት ባለቤቷን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን አምኖበት እቅዱን በተግባር ለመተርጐም ቆርጦ ተነሳ:: በመጀመሪያ በቅጥረኛ ወታደርነት በብዙ ሀገሮች ከሰራ በኋላ፣ ስለዚሁ አይነት ተግባርም ብዙ መጻህፍት ከጻፈ ግለሰብ ጋር ተገናኝቶ ችግሩን አዋየው::

«ግድያውን በቀላሉ ለማከናወን የሚችል ግለሰብ ማግኘት ይቻላል:: ከእኔ ጋር ከብዙ ዓመታት በፊት የሰራ አንድ ሰው አውቃለሁ:: አሁን ይህንኑ ስራ ይስራ አይስራ አላውቅም:: ለሁሉም ግለሰቡን ማግኘት አለብኝ» በማለት የቀድሞው የግዥ ወታደር ከነገረው በኋላ ጉዳዩን ተከታትሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚያስታውቀው ተስፋ ሰጠው:: ሳንደርሰንም ግለሰቡ ለሰጠው ዕርዳታ የመጀመሪያ ክፍያ 250 ፓውንድ ሰጥቶት ቀሪውን 250 ፓውንድ ደግሞ ቅጥር ነፍሰ ገዳዩን ሲያገኝ እንደሚያስረክበው ቃል ገብቶለት ተለያዩ::

በሳምንቱ ሳንደርሰን ከቅጥር ነፍሰ ገዳዩ ጋር ተገናኘ::

«ስንት ጊዜ ይፈጅብሃል?» ሳንደርሰን ጠየቀ::

«ከሁለት እስከ ሶስት ሳምንታት»

«ግድያው ያለ አንዳች ፍንጭ መከናወን አለበት:: ተጠንቀቅ:: እንደ መንደር ልክስክስ ሌባ ስርቆት ዓይነት የተድበሰበሰ እንዳይሆን» በማለት ሳንደርሰን አስጠነቀቀ::

«እርስዎ ለዝናዎት እንደሚያስቡ ሁሉ እኔም ለሕይወቴ ወይም ለ30 ዓመቱ እስራት አስባለሁ:: ስለዚህ ግድያው ያለ ምንም ፍንጭ ይከናወናል:: በመጨረሻም ሳንደርሰን የመጀመሪያው ክፍያ የሆነውን 250 ፓውንድ ለቅጥር ነፍሰ ገዳዩ አስረክቦት ተለያዩ::

ከአንድ ወር በኋላ በተወሰነው ሰዓት ሳንደርሰን በቴሌፎን ከቅጥር ነፍሰ ገዳዩ ጋር ተነጋገረ::

ከዚያም ስለግድያው አፈጻጸም በሰፊው ለመነጋገርና ቀሪውንም ገንዘብ ለመረካከብ በአንድ ፀጥ ባለ ቦታ ተገናኙ::

«ምንም ችግር አልገጠመህም?»

«ቀላል ነበር። እንዲሞት የፈለጉት ሰው በትክክል ሞቷል። ሁለት ጥይት በደረቱ፣ አንድ በግንባሩ።»

«ማንም ሰው አላየህም?»

«ማንም አላየኝም.... ብቻ... ብቻ... በስፍራው ከባድ ዝናም ስለነበረ ወደ መጨረሻው ላይ የሟቹ ሰውነት በወደቀበት ቦታ ቁጭ ብዬ አንድ ሰው አይቶኛል»

ሳንደርሰን በፍርሃት ተውጦ ዓይኑን ፍጥጥ አድርጎ ገዳዩን ተመለከተ።

«ማን?» ጠየቀ ሳንደርሰን።


«አንዲት ሴት» በማለት ገዳዩ መለሰ።

ወዲያው ሳንደርሰን ስለ አንጀላ ትዝ ከሚሉትና በተገናኙበት ወቅት ከማረኩት ምልክቶች ጥቂቶቹን በመጥቀስ ጠየቀው።

«ረጅም- ጥቁር ፀጉር ያላት?»

«አዎን፣ በጣም ደስ የምትል ሴት ናት» በማለት መለሰለት ነፍሰ ገዳዩ።

ሳንደርሰን ፊቱ ከቀድሞው የበለጠ የተለዋወጠ። ከድንጋጤውም የተነሳ በጣም ተሸበረ። ነፍሰ ገዳዩም የሳንደርሰንን ትክሻ መታ መታ እያደረገ «አይዞዎ፣ ምንም የሚያሳስብ ነገር የለም። ምንም ፍንጭ አልተውኩም። እሷንም ገድያታለሁ።» አለው።



# አፈርና ሰው

## ደረጀ ደስታ

'አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ' ይላል መጽሐፉ:: ያን ባላገር ፏሪ መሬት ቆፋሪ ስለምን ገበሬ ትሉታላችሁ? ይልቁንስ 'አፈር ገፊ' አትሉትምን? ይላልም መፅሐፉ- አፈርና ሰው::

የሆነ ሆኖ፣ ያን አፈር ገፊ ፍጡር አየሁት:: ደቡብን ምስራቁን ምዕራቡን ሁሉ አውቀው ነበር:: ግና ሰሜኑ ቀርቶኝ ነበር:: እሱንም አየሁት:: አሁን ስላገሬ አፈር ገፊ አንዳች ነገር ማለት የምችል መሰለኝ:: በተለይ ያን የአማራ

ቆፍጣና ገበሬ፤ ጉጃም ድረስ አየሁት። ሲያውም ጫፍ ጫፉን። ገለቱ ካሉኝ ግን ደፍሬ የማደርገው አይመስለኝም። ያስፈራል። ሰው ራሱ አፈር ይመስላል፤ አፈርና ሰው።

አባይን እስኪሻገሩና አባይን ተሻግረው ያለውን አፈር ሁሉ አየሁት። በሙሉ ታርሷል፣ ጤፍ በጤፍ ነው። «በሬው ያርሳል፣ ምርቱን አህያው ያፍሳል» እንዲሉ፣ መርካቶዎች የጉጃም ቀቤ፣ ወዘተ... የሚሉት በሬው ባረሰ ነው። እነሱ አህያ የሆኑት ለካንስ የማይደርቅ ምንጭ አግኝተው ኑሯልና!

የጥጋቤ ዘፋኞች «እህህ ጉጃም እንዴት ነሽ፣ ማር የሞላብሽ» የሚሉን አለዋዛ ዋዛ ጉጃም አያወዛ ሆኖ ነውና። አፈርና ሰው።

ጉጃም ገበሬ፤ ደጀንም ያለው፣ ማርቆስም ያለው፤ ዳንግላም ያለው፣ ቆላ ደጋሞትም ሆነ አገው ምድር ያለው፣ ሞጣና ብቸና ያለው፤ ባህርዳርም ያለው ያው አንድ ነው። አፈር ይገፋል። አፈር ይመስላል።

ምርቱ ግን የትናየት ነው። ድካምና ልፋቱም የትናየት ነው። ጉስቁልናውም እንዲሁ ለሱ ቅርቡ ያው አፈሩ ነው። አፈር ይገፋል ራሱም አፈር ይመስላል ጥንት ከዚህ በላይ ምንም ሲሆን ስለማይችል፣ ያው እንዲሁ አፈር ሲፈጠር አፈር እንደነበረ ሁሉ አሁንም አፈር ነው። ልብ ኖሮት ልብ ብሎ ላየው ሰው፤ ያ ገበሬ ማለት በሰው ቅርጽ የሚንቀሳቀስ አፈር ማለት ነው። ልብሱ ደሞ የአፈሮች ሁሉ አፈር ነው። ቁምጣውም ያው ነው። እግሩም እንደዚሁ የአፈር አንኳር ነው። በእጆቹ- እጅ መባል ስላለበት ነው እንጂ ከእግር አይለይም- ጥፍሮች ውስጥ ያሉት አፈሮች በውሃ ቢቦኩ ግማሽ ቤት ይመረጋሉ። አፈርና ሰው።

አንድ አፈር ገፊ አፈር ተሸካሚ ገበሬ ላይ ዝናብ ቢዘንብ

ውጤቱ መጨቅየት ነው፡፡ ሰው ሲጨቀይ ምን ይመስላል? የሰው መጨቅየት ማለትስ ምን ማለት ይሆናል? እስከዛሬ ያልተደረሰበት ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ለማንኛውም ግን ከሳዩ ላይ አፈር መግፋት ያልቻለ ገበሬ፣ መሬት ላይ ያለውን አፈር መግፋት ምን ይባላል? አፈርና ሰው፡፡

ይኼ ኢትዮጵያዊ አፈር ገፊ፣ አፈር ተሸካሚ ገበሬ፣ እንዲህ አፈርን የሙጥኝ ብሎ የመኖሩ ሚስጥር ምንድነው? አፈሩን ወዶት ወይስ አፈሩ አለቅ ብሎት? ደሞስ አፈር ገፍቶ አፈር ለብሶ ስንት ትውልድ አኑሯል? ሌላው ቢቀር ስንት ልጆቹን ከአፈር አሳቋል? ስንቶቹስ ልጆቹ ይህን ከውለታ ቆጥረው ከራሳቸው የተራገፈውን አፈር ከወላጆቻቸው ለማራገፍ ጥረዋል? ይህን ጥያቄ ብዙዎቹ አይወዱትም፡፡ ምክንያቱም የመልሱ መልስ፣ ከአፈር ካላደባለቀ አያግባባምና ነው፤ አፈርና ሰው፡፡

ለምሳሌ አፈር ገፊው ይህ አይነት ታሪክ አለን ይላል፡፡ «እርግጥ ነው ከአፈር ተፈጥረናል፡፡ አፈር ፈጭተን፤ እሱኑ አቡክተን፣ ጭቃ አድርገን አድገናል፡፡ ደሞ እሱኑ ገፍተን፤ ከሱው ቀምሰን፤ አብዛኛውን አብልተን፣ በተቀረው ተበልተን፣ ባልተቀረው ደሞ ተረስተን ኖረናል፡፡ እናም ደሞ ሰው ነንና ወደአፈር እንመለሳለን፡፡ አፈርን እንደወረስን ሁሉ አፈርን አውርሰን እንሄዳለን፡፡ የእስከዛሬው ታሪካችን ይኸው ነው፡፡

«በርግጥ፤ በርግጥ ብዙ ጣልቃ ገብ ታሪኮች አሉን፡፡ ታሪኮቹ ግን በአብዛኛው የእኛ አይደሉም፡፡ የናንተ ናቸው፡፡ ባለታሪኮቹ ከአፈር ተፈጥራችሁ፣ አፈር ሳትገፉ፣ ባቋራጭ ወደ አፈር የምትመለሱት ወይም በአፈር ግፊት አድጋችሁ፣ አፈርን የረሳችሁ ወገኖች ናችሁ፡፡ አዎ ታሪከኞች እናንተ

ናችሁ:: ከአፈር መግፋት ውጪ ያለው ታሪክ ሁሉ የእናንተ ነው:: ሌላው ቀርቶ የገዛ አፈራችን ሊቆች፣ ኤክስፐርቶች እናንተ ናችሁ:: እኛ የምናውቀው አፈር ገፍቶ ማረስ ብቻ ነው:: የተቀረውን የአፍም ሆነ የወረቀት እርሻ እምትችሉበት ግን እናንተ ናችሁ:: ግን በአፍ የሚገፋው አፈር አቧራ፣ በወረቀት የሚገፋ ው ትቢያ፣ መሆኑን ማን በነገራችሁ? ለነገሩ ለዚህ ለዚህ እናንተ አትተናነሱምና እናንተው እዚያው ተነጋገሩ፤ በተረፈ እኛን ለአፈሩ::» አፈርና ሰው::

ይኸው ሰሜነኛ አፈር፣ ገፈ ከደቡብኛው ወይም ከምስራቅ ምዕራብኛው በምን ይለያል? እነ ሱም አፈር እሱም አፈር ናቸው:: አንድ ባሕርዳረኛ ወጣት ስለዚህ ሲያጫውተኝ እንዲህ አለኝ:-

«እየው እንግዲህ፣ የዚህ የሰሜኑ ገበሬ ይህን ይመስላል:: ወደላይ (ወደጐንደርና ወደ ትግራይ ማለቱ ነው) ብትሄድ ደግሞ ከዚህ ይብሳል:: የበለጠ አፈር ይመስላል:: አሁን እዚህ መጥተህ በዓይንህ ተዘዋውረህ እንዳየኸው ይሄ አማራው አፈር ገፈ ይኸን ይመስ ላል:: ምርቱ ደሞ እንዳየኸው ነው:: ጐጆም ውስጥ ባዶ መሬት አታይም:: ከሰሜነኞቹ ሁሉ ጐጃምን የሚያህል አምራች አታገኝም:: ግን ሰዎቹ እንደምታያቸው ናቸው- አፈር ይመስላሉ:: ሁለመናቸው አፈር ነው:: ግን ሁሉም አፈር ገፈ (በሌላውም ክልል ያለው) ይኸን ይኸን ቢያስብላቸው ጥሩ ነው:: ታውቃለህ ይኸ አፈር ገፈ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አፈር ገፈ ሁሉ እንደሱው የሚኖር መሆኑን ነው የሚያውቀው:: ታችኛው ግን ይኸ አይሰማውም:: እዚህ ያለው አፈር ገፈን፣ አፈር በመግፋቱ ሳይሆን በገዥነቱ፣ በተንደላቃቂነቱ ነው የሚያስበው... ታዲያ ምን ያደርጋል? ይህ ልዩነት የብዙዎቹ መጠቀሚያ ሆነ:: ከፊሎቹ የበታች

ሆንናል' ብለው ሲጠሉት፣ ሌሎቹ የራሱ ወገኖች 'ደሞ የዘነዩ ነን' ብለው አፈር መግፋቱን ደብቀው ይመክሩበታል:: አፈርነቱን ሳይሆን ያሸከሙትን መመጻደቂያ ዘር ቆጥረው ይነግዱበታል:: ለዚህ ንግዳቸውም የለበሰውን አፈር እንዲበላ ያነሳሱታል:: እና እንደኔ እንደኔ የችግራችን አንዱ ምንጭ ይኼ ይኼ ነው ብሏል::» አፈርና ሰው::

በተቀረው ግን ይኼ የአባይ ዳር ገበሬ፣ ይኼ የጣና አገር ገበሬ፣ የመሬቱን አፈር ሁላ እያጠበ ከሚሄደው ውሃ እንኳ ለራሱ አፈር ማጠቢያ እሚሆን አላገኘም:: እንኳን ለመታ ጠቢያ:: ለመጠጫ እንኳ ቢሆን 'የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው' መባሉ እውነት ነው:: ማን ይጥለፍለት? ሌላው ቀርቶ 'እኔ አፈር አልገፋም' ባይዋ ተቀላቢዋ ባህርዳር እንኳ፣ እዚያው ጣናን ተንተርሳ የውሃ እጥረት አለባት:: እሳት ካየው ምን ለየው? እንዲሉ እሷም በአቧራ ተሞልታ:: ያን አፈር አሻሽላ ትቅመዋለች:: ሁለት እርምጃት ተራምዶ ጫኜማ ማስ ጠረግ የባህርዳር ከተማ ነዋሪ ግዴታ ነው:: የቤቱ ጣሪያ ሁሉ አፈር፣ ቤቱ ሁሉ አፈር፣ መንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱት ሕጻናት ሁሉ አፈር፣ ዛፎችና መንግዶች ሁሉ አፈር በአፈር ናቸው:: እንዳንዴማ የትኛው ከተሜ፣ የትኛው ባላገር መሆኑን ለመለየት ያስቸግራል:: የአማራውን ክልል በዘመናዊነቱ እወክላለሁ ባይዋ ባህርዳር ራሷ እንዲህ መሆኗ ይገር ማል:: አባይ ራሱ፣ ጣና ራሱ በላይዋ ላይ ቢከለበስባት እንኳ እንዲህ በቀላሉ የምትለ ቀለቅ አትመስልም:: ደሞም በአፈሩ ተገርመው ሳያበቁ የምስኪኑ እንደ አፈር መብዛት ሌላ ገረሜታ ፈጥሯል:: አፈርና ሰው::

ብቻ እንዲያው በደፈናው ግን የጐጃሙ ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ አፈር ገፊ እጣ ተመሳሳይነት

ይገርማል:: 'የባሰ አለና አገርህን አትልቀቅ' ቢባልም ባይባልም፤ አፈርና ሰው ተደበላልቆ፣ ታዝሎ፣ ተዛዝሎ መኖሩ የሚገርም ነው:: በሌላ በኩልም ውጫዊ አካሉ አፈር ይሁን እንጂ ውስጡ ብሩህ ነው:: ሕይወቱ የድህነት ስለመሆኑ እኔ ከተሜው ልንገረው እንጂ ለሱ ግን ቀጥ ያለና የተለመደ ነው:: አሳዛኙ ነገር ግን እንደሱ ውጫዊ አካል፣ ውስጣዊ አካሌ ያልፀዳው እኔ፣ ባለ አቧራማው አእምሮ፣ ከአፈር ሳላወጣው አፈር ነህ እያልኩ ማስቸገሬ ነው:: ወይም የሱን ሳይሆን የመሬቱን ለምለምነት እያደነቅኩ መመጻደቄ ነው:: ለሶስትሺ ዘመንም ይሁን ለመቶ ዓመት የታሪኩ ስሌት የአፈር ለባሹን የሰቆቃ ታሪክ የማሳጠርና የማስረዘም ካልሆነ፣ አፈር ገፊው እንደሆነ ያው አፈር ገፊ ነው:: አፈርና ሰው::



# ሃያ ስድስቶቹና አንዷ

ማክሲም ጐርኪይ
(ትርጉም) በትዕግሥት ህሩይ

በቀዝቃዛ ምድር ቤት ውስጥ ታጉረን ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ ሊጥ እያቦካን ብስኩት ስንጋግር የምንውል ሃያ ስድስት ሰዎች ማለትም ሃያ ስድስት ሕያው ማሽኖች ነበርን፡፡ ከምድር ቤታችን መስኮት ትይዩ የሚታየው ጉዳጓድ በሸክላ የተገነባ ቢሆንም ከአባቢው ቅዝቃዜ የተነሳ አረንጓዴ የድንጋይ ሽበት ለብሷል፡፡ የመስኮቱ ክፈፍ ከበስተ ውጭ በኩል በብረት መረብ ተሸፍኗል፡፡ የፀሐይ ብርሃንም

በተከማቸው አዋራ የተሸፈነውን መስተዋት አልፎ ከእኛ አይደርስም። የብስኩት ቤቱም ባለንብረት ከምንጋግረው ብስኩት ለለማኞችና ከጓደኞቻችን መካከል ሥራ አጥተው ለሚንገዋለሉትና ለተራቡት እንዳንሰጥ መስኮቱን በብረት አስከርችሞታል። እኛንም አጭበርባሪዎች ብሎ ሰይሞናል። ለምላችን የሚሰጠን በሥጋ ፈንታ የበሰበሰ የበሬ ጨጓራ ነበር።

በዚያ በጣም ዝቅ ያለና የሚከብድ፣ በጥቀርሻና በሸረሪት ድር የተሸፈነ ጣሪያ ባለው የድንጋይ ሳጥን ክፍላችን ውስጥ የነበረን ሕይወት የተጨናነቀና የታፈነ ነበር። በደነደነውና በተለያዩ ቆሻሻዎች በተዥጎረጎረው ግድግዳ ተከቦ መኖሩ ከጭንቀትና ከበሽታ ላይ ይጥላል። ጠዋት ማለዳ ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት እንቅልፋችንን ሳንጨርስ ተነስተን፣ እኛ ተኝተን ሳለ የተነሱት ጓደኞቻችን ካቦኩት ሊጥ ብስኩት መሥራታችንን እንቀጥላለን ከጠዋት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ድረስም ከፊሎቻችን እንደላስቲክ የሚሳበውን ሊጥ ስናሽ፣ በተቀመጥንበት እንደድንጋይ ደርቆ ላለመቅረት ስንናጥ፣ የተቀሩት ደግሞ ሊጥ ሲያቦኩ ይውላሉ። ብስኩት በሚቀቀልበት ትልቅ ማሰሮ ውስጥ ሲፈላ የሚውለው ውኃ በሀሳብና በሐዘን ተውጦ ሲንተከተክ፣ የብስኩት ጋጋሪው ትልቅ ማንኪያ ደግሞ የሚያሙለጨለጩትንና የተቀቀሉትን የሊጥ ቁርጥራጮች ወደጋለው ምድጃ ያስዕረፍት ያግዛል።

ከጠዋት እስከ ማታ ድረስም ከምድጃው በአንድ ወገን እንጨት ሲነድ ይውላል። የሚንቀለቀለው የእሳት ነበልባል ነፀብራቅም በመጋገሪያው ቤት ግድግዳ ላይ ሲንደፋደፍ በእኛ ላይ የሚያሾፍና የሚስቅ ይመስላል። ትልቁ ምድጃ በተረት የሚነገርንና ቅርፁ የተበላሸ ጭንቅላት ያለውን

ልዩ ፍጡር ያስታውሳል:: ይህም ልዩ ፍጡር በድንገት ከወለሉ ሥር በርግዶ በመውጣት እሳት የሚንቀለቀልበት መንጋጋውን፣ ትናጋው እስኪታይ ድረስ ከፍቶ በላያችን ላይ ሙቀት እየተፋ፣ ማለቂያ የሌለውን ሥራችንን ከግንባሩ ላይ በጐደጐዱትና በእየር የተሞሉ በሚመስሉት ሁለት ጥቋቁር ጉድጓዶች የሚመለከት ይመስላል:: እነኚህም ሁለት በአየር የተሞሉት ጥልቅ ጉድጓዶች ለልዩ ፍጡሩ የዓይን ያህል ቢሆኑም ሐዘኔታና ስሜት የለሾች ነበሩ:: እነኚህም ዓይኖች አዘውትረው በተለመደው ዓይነት የክፋትና የጥላቻ አመለካከት ያዩን፣ በቀዘቀዘውና በተናቀው ጥበባቸውም ይንቁን ነበር::

በየቀኑ ከውጭ በመጫሚያችን ተሸክመን በምናመጣው አቧራና ቆሻሻ እንዲሁም ከምድር ቤቱ ሙቀት የተነሣ እምቅ እምቅ በሚሸተው ክፍል ውስጥ ላባችንን የምናንጠባጥብበትን ሊጥ እያሻሸን የብስኩት ቅርጽ እናወጣለን:: በሥራችን ላይ የመረረ ጥላቻ አድሮብናል:: እኛም የሠራነውን ጨርሶ በልተን አናውቅም:: ከምንጋግረው ብስኩት ይልቅ ጥቁር ዳቦ እንመርጣለን:: ከረጅሙ ጠረጴዛ ግራና ቀኝ ዘጠኝ ዘጠኝ ሰዎች አንዳችን በአንዳችን ትይዩ በረድፍ ተቀምጠን እጆቻችንንና ጣቶቻችንን በደመ ነፍስ በማንቀሳቀስ የተላመ ድነውን ሥራ ለብዙ ሰዓታት እንሠራለን:: ከሥራው ጋር በጣም ከመላመዳችን የተነሣም እንቅስቃሴአችንን አናጤነውም:: አንዳችን አንዳችንን አተኩረን ከመመልከታችን የተነሣ በጓደኞቻችን ፊት ላይ ያሉትን መስመሮች አጥርተን አውቀናቸዋል:: የምንነጋገርበት ጉዳይ ስላልነበረን ካልተሰዳደብን በስተቀር በዝምታ መቀመጡን ተላምደነዋል:: ምንጊዜም ቢሆን

ደግሞ ጓደኛ የሆነን ሰው ለመስደብ ምክንያት አይታጣም:: ይህም ሆኖ የምንሰዳደበው አልፎ አልፎ ነበር:: ለመሆኑ አንድ ሰው በከፊል ሙት ከሆነ፣ እንደ ድንጋይ ደርቆ ከተጐሰተ፣ ስሜቶቹ ሁሉ ከባድ በሆነ ሥራ ከተድፈጠፈጡ ስለምን ተጠያቂ ሆኖ ለስድብ ይደርሳል? ዝምታ ደግሞ አስፈሪና አስጨናቂ የሚሆነው ለመናገር የሚፈልጉትን ሁሉ ተናግረው በተጨማሪ የሚናገሩት ለሌላቸው ነው:: ንግግራቸውን ገና ላልጀመሩ ሰዎች ግን ዝምታ ተራና ቀላል ጉዳይ ነው::

አልፎ አልፎ እንዘፍን፣ እናንጐራጉር ነበር:: አጀማመራችንም እንደሚከተለው ነበር:: በሥራ መሃል ከመካከላችን አንዱ እንደ ደከመ ፈረስ በረጅሙ ተንፍሶ፣ በረጅሙ ከሚ ጐተቱት ዘፈኖች አንዱን በለሆሳስ ማንጐራጐር ይጀምራል:: እንጉርጉሮዎቻች ንም፣የሚያንጐራጉሯቸውን ሰዎች ጭንቀትና ትካዜ የሚያቃልሉ ዓይነቶች ነበሩ:: መነሻው ላይ ከመካከላችን አንዱ ሲያንጐራጉር የቀረነው በፀጥታ እናዳምጠዋለን:: የጓደኛችን የብቻ እንጉርጉሮም፣ በቀዝቃዛው የበልግ ሌሊት፣ የጠቆረው ሰማይ በምድር ላይ በሚንጠለጠልበት ወቅት በሜዳ ላይ እንደሚነድ አነስተኛ እሳት፣ ጐልቶ በመሰማት እያጉረመረመ ወደ ምድር ቤቱ የከበደ ጣሪያ ይወጣል:: ጥቂት ቆይቶ አንጐራጓሪው ሌላ ጓደኛ ያገኛል:: ሁለቱ ድምፆች በአንድነት ሆነውም በለሰለሰና በሐዘን ስሜት እያንጐራጐሩ በጠባቧ ጉድጓዳችን ውስጥ ይንሣፈፋሉ:: ከዚያም በድንገት የተበራከቱ ድምጾች እንጉርጉሮውን በማጀብ አንጐራጓሪዎች ይሆናሉ:: በዚህን ጊዜ እንጉርጉሮው ደምቆ በመሰማት እንደማዕበል ይጠነክራል፣ ጥርት ብሎ ጐልቶ ሲሰማም የድንጋይ እሥር ቤታችንን ጠቋቁርና ከባድ ግድግዳዎች ገለል ያደርጋቸዋል::

በመጨረሻም ሃያ ስድስታችንም በአንድ ላይ እናንጐራጉራለን:: ተደጋጋሚ ልምምድ ያደረግን በመሆኑም የተዋጣለት አንድ ወጥ ድምፃችን ጮክ ብሎ ሲያንጐራጉር የሥራ ክፍላችንን ስለሚሞላት ክፍሉ ለእንጉርጉሮው ይጠባል:: እንጉርጉሮውም ከድንጋይ ግድግዳ ጋር ተላትሞ ሲመለስ የማቃሳት ድምጽ አስምቶ ያለቅሣል:: ይህም የሐዘን ስሜት ስለሚቀሰቅስና የቆየ ቁስልን ስለሚነካካ የልብን ውስጥ ሕመም ይቀሰቅሳል፣ መንፈስንም ያስጨንቃል:: በዚህ መካከል አንጐርጓሪዎቹ በረጅሙ እንተነፍሳለን:: ከመካከላችን አንዱ አብሮ ማንጐራጐሩን ይተውና ጓደኞቹ ስናንጐራጉር ጊዜውን ወስዶ ያዳምጣል፣ ብሎም ድምፁን ከአንጐራጓሪዎቹ ድምፅ ጋር አስተባብሮ እንደገና በአንድ ላይ ማንጐራጐሩን ይቀጥላል:: ሌላው ደግሞ ከሐዘን ስሜት የተነሣ በረጅሙ ተንፍሶ ዓይኖቹን ከድኖ አብሮ ያንራጉራል:: ምናልባትም ይኸኛው የጐረነነውና በድምፆች ማዕበል የተመላው እንጉርጉሮ፣ በዓይነ ሕሊናው ድቅን የሚልበትንና ወደ ሩቅ ቦታ የሚወስደውን ብሩህ ጐዳና እያስቃኘ እራሱን የዚያ መንገድ ተጓገር አድርጐ እንዲመለከት ያደርገው ይሆናል::

የምድጃው ነበልባል አሁንም ይንቀለቀላል፣ የብስኩት ጋጋሪው ትልቅ ማንኪያም እንደ ሸማኔ መወርወሪያ ከወዲያ ወዲህ ይላል:: በትልቅ ማሰሮ ውስጥ ያለው ውኃ ይፍለቀለቃል፣ በግድግዳው ላይ የሚንፀባረቀው የእሳት ነበልባል፣ በገዘምታ ተወጦ ከማሾፍና ከመሣቅ አልተገታም::... እኛም የእኛ ባልሆኑ ቃላት አማካይነት የባሮችን ሐዘን፣ ሕያው የሆኑና ከፀሐይ ብርሃን የተከለሉን ሰዎች ከባድና አደንዛዥ ሰቆቃ በማንጐራጐር እንተነፍሰዋለን:: በዚህ ዓይነት ሃያ ስድስት ሆነን ከድንጋይ

በተሰራ ትልቅ ሕንጻ ምድር ቤት ውስጥ ስንኖር፣ የሕንጻው ሦስት ፎቆች በሙሉ በቀጥታ በእኛ ትከሻ ላይ የተገነቡ ያህል መኖር ከባድ ሆኖብን ነበር።

ነገር ግን ለእኛ ከአንገርጋሮአችን በተጨማሪ ለሁላችንም ጥሩ የሆነና ሁላችንም የምንወደው ምናልባትም ለእኛ ፀሐይን የተካ ነው ብለን የምንለው አንድ ሌላ ነገር ነበረን። በምንኖርበት ሕንጻ፣ በሁለተኛው ፎቅ ላይ የወርቀዘቦ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ይኖራሉ። በዚያም ከሚሰሩት ብዙ ሴቶች መካከል አንዷ የአሥራ ስድስት ዓመቷ የቤት ሠራተኛ ታንያ ነበረች። በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ትንሽ ቀለመ ሮዝ የሆነና በፈገግታ የተሞላው ፊት ወደ ምንሠራበት ክፍል የሚያስገባው በር ከመሀሉ ተከፍቶ የገባለትን መስተዋት ተጠግቶ «እስረኞች ብስኩት ስጡኝ?» በማለት በሰማያዊ ደስተኛ ዓይኖቹ እየተመለከተን በሚያቃጭልና በሚያቀላምጥ ድምፅ ይጣራል።

እኛም ወደዚያ ጉልህ ድምጽ መለስ በማለት በደስታና በፍቅር፣ እያየ አርኪ ፈገግታ የሚመግበንን የልጃገረዲቱን ፊት እንመለከታለን። ለእኛም በመስተዋቱ ላይ የተደፈ ጠጠውን አፍንጫ፣ ከሮዝ ከናፍርት መካከል የተደረደሩትን ትናንሽና ነጫጭ ጥርሶች እንዲሁም ግልጽ የሆነውን ፈገግታ መመልከት ከፍተኛ ደስታን ያስገኝልን ነበር። በሩን ከፍቶ እሷን ወደ ውስጥ ለማስገባት ሁላችንም በአንድ ላይ እንረባረባለን። በሩ ሲከፈትም ደስተኛዋና ውዷ ታንያ ወደ ውስጥ ትገባና ሽርጧን አስቀምጣ፣ ጭንቅላቷን ወደ አንድ ወገን ዘንበል አድርጋ ከፊት ለፊታችን በመቆም የማያቋርጥ ፈገግታ ትመግበናለች። ረጅሙና በወፍራሙ የተጉነጉነው ዞማ ፀጉሯ ትከሻዋን ተሻግሮ ከጡቶቿ ላይ አርፏል። እኛም ቆሻሻ፣ አስቀያሚና አፀያፊ የሆንን ሰዎች

ታንያን የምንመለከታት ከታች ወደላይ ነበር። የምንገኝበት ክፍል መግቢያ በር ከወለሉ አራት ደረጃዎች ወደላይ ከፍ ያለ ስለነበር የምንመለከታት ጭንቅላታችንን ወደላይ አቅንተን ነበር። «ታንያን እንደምን አደርሽ?» «መልካም ጠዋት!» በማለት የምናነጋግራት ለእሷ ብቻ በምናገኛቸው ልዩ ቃላት በመጠቀም ነበር። ከእሷ ጋር በምንነጋገርበት ወቅት ድምፃችን የለሰለሰ ቀልዳችን ለዛ ያለው ይሆናል። በአጠቃላይ ለእሷ ያለን አመለካከት ከሁሉ የተለየ ነው። ዳቦ ጋጋሪውም በተለይ ለእሷ፣ በረጅሙ ማንኪያ መርጦ የሚያወጣቸውን ጥሩ ሆነው ተጠብሰው የበሰሉ ቀጋ የመሰሉትን ብስኩቶች እንደዘበት ወደ ሽርጧ ወርወር ያደርጋቸ ዋል።

ከዚያም ሁላችንም በአንድ ላይ «ባለቤቱ እንዳያይሽ ተጠንቀቂ፣» በማለት እናሳስባታለን። እሷም የመስሪ ሳቅ ስቃ፣ በደስታ በተመላ ድምፅ ጮክ ብላ፣

«እስረኞች ደህና ሁኑ!» በማለት እንደ ትንሽ አይጥ በፍጥነት ትሰወራለች።

ሁሉም በዚሁ ያበቃል። ነገር ግን እሷ ከሄደች በኋላ እርስ በእርሳችን ስለእሷ ብዙ እናወራለን። የምናወራውም ያው ትላንትናና ከዚያም በፊት ስለእሷ ያወራነውን ነበር። ምክንያቱም እሷም ሆነች እኛ እንዲሁም የምንገኝበት አካባቢ ትላንትናና ከዚያም በፊት ከነበረው ያልተለወጠ በመሆኑ ነው። ለሰው ልጅ በሕይወቱ፣ የሚኖርበት አካባቢ አለመለወጥና በዚያው መርጋት በጣሙን ከባድና አሰልቺ ይሆንበታል። ይህን መሳዩም ሁኔታ መንፈሱን ሳይገልበት ቢቀር እንኳ ሕይወቱን በገፋቁጥር በየአካባቢው እንቅስቃሴ አልባ መሆን የበለጠ አሰልቺ ይሆንበታል።

እኛም ዘወትር ስለሴቶች የምንናገራቸውን አፀያፊ ቃላቶች መስማት፡ አልፎ አልፎ ለእኛው ለእራሳችን እንኳ ይሰቀጥጠናል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ምናልባትም እኛ የምናውቃቸው ሴቶች ከዚህ የተሻለ የማይገባቸው ስለሆኑ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ስለታንያ ክፉ ነገር ጨርሶ ተናግረን አናውቅም፡፡ ከመካከላችንም አንዳችን እንኳ እሷን ለመንካት እጃችንን አልዘረጋንም፡፡ ታንያም ከእኛ እንደበት አልባሌ ቀልዶች ሲነገሩ ሰምታ አታውቅም፡፡ ለዚህም ምክንያት የሆነው ታንያ ከሰማይ እንደወደቀ ኮከብ ለቅጽበት ታይታ ወዲያውኑ የምትሰወር፣ ከእኛም ጋር ለረጅም ጊዜ የማትቆይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ትንሽና በጣም ቆንጆ ስለሆነች፣ ቆንጆ የሆነ ነገር ሁሉ ደግሞ በባለጌ ሰዎች ዘንድ እንኳ የሚከበር የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምንም እንኳ ሥራችን ቅስም የሚሰብር ሆኖ የአህያ ያህል ያደደበን ቢሆንም ሰዎች እንደሆንን ያለን በመሆኑ፣ እንደማንኛውም ሰው የምንንበረከከለት የሆነ ነገር ሳይኖረን ለመኖር አለመቻላችን ነው፡፡ በእኛ አካባቢ ከእሷ የተሻለ ማንም አልነበረም፡፡ በዚያ ሕንፃ ውስጥ በእሥርቶች የሚቆጠሩ ሌሎች ነዋሪዎች ቢኖሩም ከታንያ በስተቀር እኛን በምድር ቤት ውስጥ የምንኖረውን ሰዎች ነገሬ ያለን አልነበረም፡፡ በመጨረሻም ምናል ባትም ይህ ዋናው ምክንያት ሊሆን ይችላል፣ ታንያ የእኛ ናት ብለን የምንላትና ለመኖርም የቻለችው በእኛ ብስኩት ነው ብለን በማመናችን ነው፡፡ ለእሷም ትኩስ የሆኑ ብስኩቶችን መስጠትን ግዴታችን አድርገን ስለወሰድነው ይህንኑ ተግባር ለምናምንበትና ላመለክነው ኃይል በየዕለቱ የምናቀርበው መስዋዕት አድርገን ቆጥረነዋል፡፡ ይህም የእኛ የተቀደሰ ተግባር እኛን ከታንያ ጋር የበለጠ አቀራረበን፡፡ ለታንያ ብስኩቶቹን ከመስጠት በተጨማሪ ብዙ ምክሮችን እንመክራታለን፡፡ የሙቀት ልብስ እንድትለብስ፣ በደረጃው ላይ እንዳትሮጥ፣ ከባድ የሆነ የግንድ እንጨት እንዳትሸከም እንመክራት ነበር፡፡

እሷም ምክራችንን ፈገግ ብላ ብታዳምጥም ቅሉ፣ በምክሮቻችንን ከመሳቅ በስተቀር በተግባር አላዋለቻቸውም:: በዚህ ደግሞ እኛም አልተቀየምንም፣ ለእኛ ዋናው ነገር ስለሷ የምንጨነቅና የምናስብ መሆናችንን ማሣወቁ ብቻ ነበር::

ታንያ ብዙ ጊዜ አንድ አንድ ነገሮችን እንድናደርግላት ትጠይቀናለች:: ለምሳሌ ከምድር ቤት ያለውን የዕቃ ቤት እስቾጋሪ በር እንድንከፍላት፣ እንጨት እንድንፈልጥላት፣ ... እኛም እነኚህንና ሌሎቹንም እሷ የጠየቀቻቸውን ሥራዎች ሁሉ በደስታ እንዲያውም በተለየ ክብር ከውነንላታል::

ነገር ግን ከመካከላችን አንዱ ታንያን፣ ያለች የሌለችውን አንዲት ሸሚዝ እንድ ትጠቃቅምለት ቢጠይቃት በንቀት ዓይን ተመልክታ፣

«ይኼ ነው የቀረው፣ እጠቃቅማለሁ እንጂ እንዴታ!» አለችው::

እኛም ሁኔታው በደረሰበት ጓደኛችን ስቀን፣ ዳግመኛ ይህን አድርጊልን ላንላት በዚሁ አበቃን:: ታንያን ሁላችንም እንወዳታለን፣ ከዚህም ሁሉንም መረዳት ይቻላል:: የሰው ልጅ ሁል ጊዜ ፍቅሩን በሆነ ሰው ወይም ነገር ላይ ለመጣል ይፈልጋል:: ምንም እንኳ ይህ ሁኔታ የወደዱትን ቅርብና ውድ የሆነውን ሕይወት ሊያጠፉ፣ ሊያበላሽ አልፎም ሊመርዘው የሚችል ቢሆንም እንኳ ያደርገዋል:: ምክንያቱም የሚወድ፣ የሚወደውን የሚወድ እንጂ የሚያከብር ስላልሆነ ነው:: እኛም ከእሷ በስተቀር ሌላ የምንወደው ማንም ስላልነበረን ታንያን የግድ መውደድ ነበረብን::

አንድ ጊዜ ከመካከላችን አንዱ በድንገት ተነስቶ ነገሩን

በማመዛዘን እንዲህ ሲል ተናገረ፣

«ለምንድን ነው ይህችን ልጅ የምናሞላቅቃት? ምን የተለየ ነገር አየንባት? ስለምንስ ነው በእሷ ብዙ ጊዜ የምናጠፋው?»

ይህን ለመናገር የወሰነውን ሰው ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ስሜት ዝም አሰኘነው:: በእኛ በኩል የምንወደው ነገር እንዲኖረን አስፈልጎን ነበር:: አገኘተን ወደድነው:: እኛ ሃያ ስድስታችንም የምንወደው ነገር እንዲኖረን አስፈልጎን ነበር:: አገኘተን ወደድነው:: እኛ ሃያ ስድስታችንም የምንወደው መሆናችን ደግሞ ለእያንዳንዳችን ግልፅ ስለነበር ለእኛ የቅዱሳን ቅዱስ ሆነ:: ይህ በመሆኑም ማንኛውም የዚህ ተቃራኒ የሆነ ሁሉ የእኛ ጠላት ነበር:: እኛ ወደነዋል:: ምናልባትም የወደድነው በተጨባጭ ጥሩ ያልሆነውን ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን እኛ ሃያ ስድስት ስለሆን፣ ለእኛ ወድ ሆኖ የኀ ኘው በሌሎች ዘንድ የተቀደሰ ሆኖ እንዲታይ እንሻለን::

የእኛ ፍቅር ከጥላቻ ያላነሰ ከባድ ነበር:: ስለሆነም መሰለኝ አንዳንድ በራሳቸው ተኩራርተው ሌሎችን የሚንቁ ሰዎች ከእኛ ፍቅር ይልቅ ጥላቻችን የተሻለ መሆኑን የሚያረጋግጡት:: ታዲያ ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ ለምን ከእኛ አይርቁም?

የብስኩት ቤቱ ባለንብረት ከብስኩት መጋገሪያው በተጨማሪ የዳቦ ቤትም ነበረው:: የዳቦ ቤቱም በዚያው ሕንፃ፣ በዚያው ጉድጓድ ውስጥ ግን በሌላው ወገን የሚገኝ ሲሆን ከእኛ የሚለየው በግድግዳ ነው:: ዳቦ ጋጋሪዎቹ አራት ብቻ ሲሆኑ፣ ሥራቸውን ከእኛ የበለጠ ንፁሕ አድርገው ስለሚገምቱት ገለል አድርገውናል:: ከዚህ ጋርም አያይዘው

እራሳቸውን ከእኛ የተሻሉ አድርገው ስለቆጠሩ ወደ ሥራ ቦታችን አይመጡም። በቅጥር ግቢው ውስጥ ስንገናኝም በንቀት እየተመለከቱ ይሳለቁብናል። እኛም በበኩላችንም ወደእነሱ አንሄድም። ባለቤትየውም ዳቦ ይሰርቁብኛል ብሎ ስለሚፈራ ወደዚህ እንዳንሄድ ከልክሎናል።

የዳቦ ጋጋሪዎቹ ሥራ ከእኛ የቀለለ፣ የሚያገኙት ገንዘብ ከእኛው የበለጠ፣ የሚመገቡት ምግብ ከእኛ የተሻለ፣ የሚሰሩበት ክፍል ደግሞ ሰፋ ያለና በቂ ብርሃን የሚያገኝ፣ ንጽሕናቸውንና ጤናቸው የተጠበቀ፣ በአጠቃላይ ይዞታቸው ከእኛው ተቃራኒ ስለነበር እንቀናባቸዋለን እንጂ አንወዳቸውም። እኛ ሁላችንም ፊታችን የገረጣ ሲሆን ከመካከላችን ሶስቱን ቂጢኝ፣ ጥቂቶቹን እከክ ይዟቸዋል። አንዱ ደግሞ ከቁርጥማት ሕመም የተነሣ ጨርሶ ጉብጧል። ዳቦ ጋጋሪቹ በበዓልና በዕረፍት ቀናት ኮት ለብሰው ሲጥ ሲጥ የሚል ገምባሌ ጫማ አድርገው በከተማው የመናፈሻ ቦታ ይንሸራሸራሉ። ከመካከላቸው ሁለቱ አኮርዲዮን ነበራቸው። እኛ ግን የቆሸሸ ጨርቃ ጨርቅ ስለምንለብስና ጫማችን የተቀዳደደ ወይም በሲባጐ የተያያዘ ስለነበር ወደከተማው የመናፈሻ ቦታ እንዳንገባ በፖሊስ እንከለከላለን። ታዲያ በዚህ ዓይነት ዳቦ ጋጋሪዎቹን ልንወዳቸው እንችላለን?

አንድ ቀን ዋናው ዳቦ ጋጋሪ በመስከሩ የንብረቱ ባለቤት ከሥራው ያሰናበተውና በምትኩም ሌላ የቀጠረ መሆኑን ሰማን። አዲስ የተቀጠረውም ሰው የሐር ሰደርያ የሚለብስና የወርቅ ማሰሪያ የወርቅ የሆነ ሰዓት የሚያደርግ ወታደር ነበር። እኛም ስለሰውዬው ተሽሞንሟኝነት ብዙ በመስማታችን እሱን ለማየት በጣሙን ጓጓን። ድንገት በግቢው ውስጥ ብናገኘው ከሚል ተስፋም እንዳችን

አንዳችንን እየተከተልን ወጣ ገባ ማለት አበዛን:: ግና እሱ እራሱ ከምንሰራበት ቦታ ሳናስበው በድንገት መጣ:: በጫማው ጫፍ በሩን ገፋ አድርጎ በመክፈት የከፈተውን በር ሳይዘጋ ከደጃፉ ላይ ቆሞ በፈገግታ፤

«ሰላም እንደምንአላችሁ?» አለን:: በሩን ሳይዘጋው ከደጃፉ ላይ በመቆሙ ከውጭ የነፈሰው ቀዝቃዛ አየር ከእግሩ ሥር ሲንገዋለል የጨፈገገ ደመና መሰለ:: ከዚያው ከደጃፉ ላይ በመቆሙም የሚመለከተን ከላይ ወደታች ነበር:: ከታች ሆነን ስንመለከተው አገጩና ጠቅለል ጠቅለል ካለው ሪዙ ሥር የተደረደሩት ትላልቅና ቢጫ ጥርሶቹ ያንፀባርቃሉ:: የለበሳት ሰደርያ እውነትም የተለየች ነበረች:: ሰማያዊ መደብ ያላት ሆና የተለያዩ ቀለማት ያላቸው አበቦች የተጠለፉባት፣ የምታንፀባርቅና ቁልፎቿ ከተለየ ቀይ ድንጋይ የተሰሩ ነበረች:: የተባለውም ባለወርቅ ማሰሪያ የእጅ ሰዓት ተደርጓል::

ወታደሩ፣ የተዋበ፣ ዘለግ ያለ ቁመና ያለው፣ ጤናማ፣ ጉንጮቹ የበሰለ ቲማቲም የመሰሉ፣ ትላልቅና ብሩህ ዓይኖቹ ደግሞ በደግ የሚመለከቱ፣ በፍቅር ስሜትና በግልጽ የሚያዩ ናቸው:: በእራሱ ላይ ነጭ፣ በአሚዶ በደንብ የተተኮሰ ደረቅ ቆብ ደፍቷል:: ያደረገው የወቅቱን ሞድ የጠበቀ ባቱ ድረስ ወጥ የሆነው ገንባሌ ጫማ በደንብ ተጠርጎ ያንፀባርቃል:: በላዩ ላይ ለመሄላ የሚታይ የቆሻሻ ነጥብ አልነበረም::

የእኛው ጋጋሪ በሥርዓት በሩን እንዲዘጋ በጠየቀው መሠረት ሳይጣደፍ ረጋ ብሎ የተጠየቀውን ካደረገ በኋላ ስለብስኩት ቤቱ ባለቤት መጠየቅ ጀመረ:: እኛም አንዳችንን አንዳችን እያቋረጠን፣ ሰውዬው ሰውን በቁሙ የሚያልብ፣ ሞሽላቃ፣ አረመኔ፣ ሰውን ለማሰቃየት የተፈጠረ፣ ... ወዘተ በማለት ስለሰውዬው መናገር የሚቻለውንና መነገር ያለበትን፣

እዚህ ላይ ግን በጽሑፍ ማስፈሩ አስፈላጊ ያልሆነውን ሁሉ ነገር ነው፡፡

- ወታደሩም ሪዙን እያሻሸ፣ እኛንም በብሩህ ዓይኖቹ እየተመለከተ በጥሞና አዳመጠን፡፡

ከዚያም ድንገት፣ «እዚህ እናንተ ዘንድ ብዙ ሴቶች አሉ?» ሲል ጠየቀን፡፡

ከመካከላችን ጥቂቶቹ የአክብሮት ፈገግታ ሲያሳዩ የቀሩት ፊት ተለዋወጠ፡፡ አንደኛው ግን ለወታደሩ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያህል፣ «ዘጠኝ ሴቶች አሉ፡፡» ሲል መለሰለት፡፡

እሱም በዓይኖቹ ጠቀስ አድርጎ፣ «ትጠቀሙባቸዋላችሁ?» በማለት ጠየቀን፡፡ በነገሩ ሳቅን፣ በለሆሳስ የእረፍት ሳቅ ሳቅን፡፡ ከመካከላችንም አብዛኞቻችን ለወታደሩ እኛም እንደእሱ ደፋር ወጣቶች መሆናችንን ለማሳየት ፈልገን ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን ለማድረግ ማንም ሳይችል ቀረ፡፡ ከመካከላችን አንዱ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ዝቅ ባለ ድምፅ፣

«እነሱ የእኛ አይደሉም፡፡» አለው፡፡

«ግልጽ ነው፣ የእናንተም ሊሆኑ አይችሉም!» በማለት ትክ ብሎ እየተመለከተን በእርግጠኝነት ተናገረ፡፡ ከዚያም አያይዞ፣ «እናንተ ከመመዘኛው አትደርሱም... ቁመናችሁ አይመጥንም... ሴቶች ደግሞ የወንድን ገጽታ ይወዳሉ... ቁመናና ዛላው ያማረ እንዲሆን - ይሻሉ ... ሥርዓት ያለው እንዲሆን፤ በነገራችን ላይ ሴት ልጅ ጉልበት ላለው ጉብዝ ትንበረከካለች፡፡ እጁ እውነተኛ የወንድ እጅ እንዲሆን ትሻለች! ይህን የመሰለ ክንደ እንዲኖረው ትፈልጋለች፡፡» አለን፡፡

ብሎም የሸሚዙ እጀታ እክርን ድረስ የተጠቀለለውን ቀኝ እጁን ከኪሱ አውጥቶ ለእኛ ለማሣየት ከፍ አድርጐ ያዘው፡፡ የቀኝ እጁም ነጭና ጠንካራ ከመሆኑም በላይ በሚያንፀባርቅ ወርቃማ ፀጉር ተሸፍኗል፡፡

«የእግሩ፣ የደረቱ፣ በአጠቃላይ የሰውነቱ ፈርጣማነት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ለቁመናው ተስማሚ የሆነ ጥሩ ልብስ መልበስ አለበት፡፡ ለምሳሌ እኔን ሴቶች ይወዱኛል፡፡ እኔ እነሱን አልጠራም፣ አልጠብቅም፣ እነሱ እራሳቸው በአንድ ጊዜ አምስት ሆነው ነው ከትከሻዬ የሚንጠላጠሉት፡፡»

ወታደሩ በአጠገቡ ከነበረው የፋርኖ ዱቄት ጆንያ ላይ ተቀምጦ ሴቶች እንዴት እንደሚወዱትና እሱም እንዴት አድርጐ በድፍረት እንደሚያስተናግዳቸው በሰፊው አወጋን፡፡ በመጨረሻም ተነስቶ ሄደ፡፡ የከፈተው በር ሲጢጥ የሚል ድምፅ አሰምቶ ተዘጋ፡፡ እኛም ለረጅም ጊዜ ፀጥታ በሰፈነበት ክፍላችን ውስጥ ስለ ሰውዬውና ስለ አጫወተን ታሪኮች በዝምታ ተውጠን አሰብን፡፡

ከዚያም በድንገት ሁላችንም መናገር ጀመርን፡፡ ከውይይታችንም ሰውየውን ሁላችንም የወደድነው መሆኑን ተገነዘብን፡፡ ሰውየው ተራ የሆነ መልካም ሰው ነበር፡፡

መጥቶ ተቀመጠ፡፡ ተጫውቶ ሄደ፡፡ ይህን በመሰለ የወዳጅነት መንፈስ ወደ እኛ ማንም አልመጣም፣ ይህን በመሰለ ስሜትም ከእኛ ጋር ማንም አልተወያየም፡፡ እኛም ስለሰውዬው፣ ወደፊትም ወርቀ ዘቦ ሰሪዎቹን ሴቶች በመማረክ ስለሚያንጋጥመው መልካም ውጤት ሁሉ አወራን ወርቀ ዘቦ ሰሪዎቹ ሴቶች ከእኛ ጋር በደጃፍ ሲገናኙ በቁጣ ከንፈራቸውን ነክሰው ገለል የሚያደርጉን ወይም

ደግሞ ጨርሶ በመንገዳቸው ላይ እንደሌለን ሁሉ በላያችን ላይ የሚያልፉ ናቸው። እኛም እነሱን በክረምቱ ወራት ለየት ያለ የክረምት ቆብ ደፍተው ፀጉራም ካፖርት ደርበው፣ በበጋ ወቅት ደግሞ በአበቦች ያጌጡ ዝርግ ባርኔጣዎች አድርገውና በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቁ ገርንጥላዎች ዘርግተው በቅጥር ግቢው ውስጥ ሲዘዋወሩና በመስኮታችን አጠገብ ሲያልፉ እየተመለከትን በማድነቅ ብቻ የተወሰንን ነን። ግን ደግሞ እርስ በእርሳችን ስለ እነሱ የምናወራውን፣ በአጋጣሚ ሰምተው ቢሆን ኖሮ ጨርቃቸውን ጥለው ያብዱ ነበር።

«በነገራችን ላይ... ሰውዬው የእኛዋን ታንያን እንዳያበላሽብን እሰጋለሁ!» ሲል ዋናው ጋጋሪ ጭንቀቱን አሳወቀን። በሰማናቸው ቃላት ተደናግጠን ሁላችንም ዝም አልን። ወታደሩ ታንያን በግዙፉና በአማረው ሰውነቱ ከእኛ የጋረዳት ይመስል ስለእሷ ማውሳቱን ረስተነዋል። በመካከላችን ጩኸት የነገሰበት ጭቅጭቅ ተነሳ። አንዱ ወገን ታንያ ጨርሶ ከዚያ የሚያደርስ ድርጊት አትፈጽምም ሲል፣ ሌላው በወታደሩ ቁመና መማረኳ የማይቀር ነው ብሎ ሲያረጋግጥ ሦስተኛው ወገን ደግሞ ለምናልባቱ ወታደሩ ከታንያ መቀራረብ ከጀመረ የጉን አጥንቱን ማድቀቅ ነው የሚል ሃሳብ አቀረበ። በመጨረሻም ሁላችንም በአንድነት ወታደሩንና ታንያን በዓይነ ቁራኛ ለመከታተል፣ ለታንያ ደግሞ ከሰውዬው እንድትጠነቀቅ ለመንገር ወሰንን። በዚህ ጭቅጭቁ አበቃ።

የአንድ ወር ያህል ጊዜ አለፈ። ወታደሩ ዳቦ መጋገሩን፣ ከወርቀ ዘቦ ሠራዎቹ ሴቶች ጋር መውጣቱ ቀጠለ። ወደኛዋ የብስኩት መጋገሪያም አዘውትሮ ይመጣጣል። ሴቶችን በተመለከተ ስለተቀዳጃቸው ድሎች

ግን ምንም አይናገርም:: ብቻ ጢሙን እያሻሸ ከንፈሩን በመምጠጥ ከግራ ቀኝ ያጣምመዋል::

ታንያ እንደ ወትሮዋ በየዕለቱ ጠዋት ጠዋት ወደ እኛ «ብስኩት ጋጋሪዎች» በማለት ትመጣለች:: እንደተለመደው ሁሉ ደስተኛ፣ ውድና ከእኛም የቀረበች ነበረች:: በእኛ በኩል ከእሷ ጋር ስለወታደሩ ለመነጋገር ሞክረን ነበር:: ነገር ግን እሷ ለወታደሩ «ዓይነ ፈጣጣ ጥጃ» የሚልና ሌሎችም አስቂኝ ስሞች ስለአወጣችለት መንፈሳችን ተሰበሰበ:: ወርቀ ዘቦ ሠሪዎቹ ሴቶችም ከወታደሩ ሲጣበቁ እያየን በእኛዋ ኩረዳ ኩራን::

ታንያ ስለ እሱ የነበራት አመለካከት የእኛን መንፈስ አነሳሳው፣ እሷን ተከትለን እኛም ወታደሩን በንቀት መመልከት ጀመርን:: እሷንም ከቀድሞ የበለጠ ወደድናት:: በየጠዋቱም በከፍተኛ ደስታና ፍፁም በሆነ ስሜት እንቀበላት ነበር::

አንድ ቀን ወታደሩ ትንሽ ሞቅ ብሎት ሳለ ወደ እኛ ብቅ ብሎ መቀመጫ ከያዘ በኋላ መሳቅ ጀመረ:: እኛም የሚያስቀው ጉዳይ ምን መሆኑን ስለጠየቅነው የሚከተለውን መልስ ሰጠን::

«በእኔ የተነሳ ሁለቱ ሴቶች ሊዳና ግሩሻ ተደባደቡ:: አቤት እንዴት አድርገው እርስ በእርስ ተቦጫጨቁ! ተሞነጫጨሩ! ሃ! ሃ! ሃ! አንደኛዋ የሌላዋን ፀጉር ጨምዳ ይዛ ከመሬት ላይ አንደባለለቻት:: ከዚያም ከላይዋ ላይ ወጥታ ጉብ አለችባት... ሃ! ሃ! ሃ! ከዚያም ፊታቸውን ተሞነጫጨሩ... አንዷ የሌላዋን ልብስ ብጭቅጭቁን አወጡት... በጣም አስቂኝ ነበር! ለምንድን ነው ሴቶች በወጉ የማይደባደቡት? ለምንድን ነው የሚሞነጫጨሩት?»

ወታደሩ በአግዳሚው ወንበር ላይ ተቀምጧል:: ጤናማ፣

ንፋሕና በሕይወቱ ደስተኛ የሆነ ሰው ነው:: ያለማቋረጥ ይስቃል:: እኛ ደግሞ በዝምታ ተውጠናል:: ለምን እንደሆን እንጃ ሰውየው እንደ ወትሮው ደስ የሚለን ዓይነት ሰው አልሆነም::

«ለምን ይሆን ሴቶችን በተመለከተ እንዲህ ዕድለኛ ሰው የሆንኩት? አስቂኝ ነው! አንዴ ከጠቀስኩ ሁሉ ነገር ወዲያው ዝግጁ ይሆናል!»

በሚያንፀባርቁ ፀጉሮች የተሸፈኑትን ነጫጭ እጆቹን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ መልሶ ከጉልበቱ ላይ ሲጥላቸው የበረታ የጥፊ ድምጽ አሰሙ:: እኛንም ደስታና መገረም በተመላበት አመለካከት አተኩሮ ተመለከተን:: እሱም ቢሆን ከሴቶች ጋር ባለው ግንኙነት ዘወትር መልካም ዕድል የሚያጋጥመው በመሆኑ በጣሙን ተገርሟል:: ሙሉት ያለው ቀይ ፊቱ እርካታ ማግኘቱን የሚገልጽ የደስታ ስሜትን ያንፀባርቃል:: ምላሱም ያለዕረፍት ከናፍሮቹን ይቃኛል::

የእኛ ጋጋሪ የመጋገሪያውን ረጅም ማንኪያ በቁጣና በኃይል ወደ ምድጃው ወርውሮ በማፌዝ እንዲህ አለው፣«ትናንሽ የጥድ ችግኞችን ነቅሎ መጣል ጉራ የሚያስነዛ ታላቅ ተግባር አይደለም:: የዝግባ ዛፍን ግን ምን እንደምታደርግ ለማየት እጓጓለሁ::»

«ምን አልክ? ከእኔ ጋር ነው የምትነጋገረው?» በማለት ወታደሩ ጠየቀ::

«አዎን! ከአንተ ጋር...»

«ምንድን ነው ያልከው?»

«ምንም አይደለም... እርሳው::»

«የለም የለም ቆይ ነገሩ ምንድን ነው? የትኛውን ዝግባ ነው የምትለኝ?»

የእኛው ጋጋሪ ወዲያውኑ መልስ አልሰጠም:: በረጅሙ ማንኪያው የተቀቀሉትን ብስኩቶች ሰብስቦ ወደ ምድጃው፣ የበሰሉትን ደግሞ ተሸርቦ በተዘጋጀ ድር ላይ የሚያን ጠለጥሏቸው ልጆች ከመሬት ተቀምጠው ወደ ሚጠባበቁበት መወርወሩን ቀጥሏል:: በዚህ መካከል ዋናው ጋጋሪ ወታደሩንም ሆነ ከእሱ ጋር የተለዋወጡትን ነገር ዘንግ ቶታል:: ነገር ግን ወታደሩ ካላሰበው ጭንቀት ላይ በመውደቁ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ምድጃው አመራ:: ወደ ምድጃው የቀረበው በድንገት ስለነበር ፍጥነቱን ጠብቆ ወዲያ ወዲህ በሚለው ረጅም የመጋገሪያ ማንኪያ ደረቱ ላይ ሊመታና አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችል ነበር::

«የለም! የለም! የጀመርከውን ጨርስ ማን ናት እሷ? አስቀይመኸኛል... እኔን ልትቋቋም የምትችል አንድም ሴት የለችም! የተናገርካቸው ቃላት በጣሙን አስቀይመውኛል!» አለው::

እውነትም ወታደሩ ከአንጀቱ ተቀይሞ ነበር:: ምናልባትም ይህ ሰው እራሱን የሚያከብርበት፣ ሴቶችን ለመማረክ ካለው ችሎታ በስተቀር ሌላ ምንም ሕያው የሆነ ነገር የሌለው ይሆናል:: እራሱን ሕያው እንደሆነ ሰው አድርጐ ለመቁጠር ያስቻለውም ይህ ብቻ ነበር ለማለት ያስደፍራል::

ለአንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ አለን የሚሉት ዋና ነገር የአእምሮ ወይም የአካል በሽታን ይሆናል:: ለእነዚህ መሳይ ሰዎችም ሁኔታው የመኖራቸው ምክንያት ስለሚሆን ምንም እንኳን በሕመሙ የሚሰቃዩ ቢሆንም ቅሉ የሚኖሩት ደግሞ ይህንኑ ተስፋ አድርገው ስለሆነ ሕመማቸውን

በተመለከተ ያላቸውን ቅሬታ ለሌሎች ያሰማል። በዚህም ቅርባቸው የሆኑ ሰዎችን አትኩሮት ያገኙበታል፣ የሌሎችን አዘኔታ ያግበሰብሱበታል። ከዚህ በስተቀር በሕይወት ውስጥ ሌላ ምንም ነገር ስለሌላቸው ከበሽታው ተፈውሰው ቢድኑ ዕጣ ፈንታቸውን የሚረግሙ ዕድለቢሶች ይሆናሉ። ለዚህም ምክንያቱ በሕይወታቸው ውስጥ አለን የሚሉትን ነገር ማጣታቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጅ ሕይወት ጨርሶ ባዶ ስለሚሆን፣ ያለፍላጎቱ ለጉድለቱ ዋጋ ለመስጠትና ለዚያም ሲል ለመኖር ይገደዳል።

ወታደሩ በነገሩ ተቆጥቶ በጋጋሪው ላይ ተነሳበት፣«የለም? ማን መሆኗን መናገር አለብህ?»

«መናገር አለብኝ?» አለ ጋጋሪው በድንገት ፊቱን ወደ እሱ መልሶ፣

«አዎን!»

«እንግዲያው እሷ ናት! ሞክር...»

«እኔን?»

«አዎን አንተን!»

«እሷን? ይኼማ ተራ ነገር ነው።»

«እናያለን!»

«አዎን!አሳይሃለሁ! ሃ! ሃ!»

«እሷ አንተን...»

«ከወር በላይ አይወስድም!»

«አይ አንተ ጉረኛ! ልታይ ልታይ ባይ ነህ!

አይደለህም?»

«ሁለት ሳምንት ብቻ ከዚያ በኋላ ቃንያ ማን መሆኗን አሳይሃለሁ።»

«አሁን ውጣ... ሥራ ላይ አታስቸግረኝ።»

«ሁለት ሳምንት ከዚያ በኋላ ሁሉም ይሆናል! አይ አንተ!...»

«ውጣልኝ ብያለሁ!»

ጋጋሪው በድንገት ተቆጥቶ የመጋገሪያውን ትልቅ ማንኪያ አሸቀንጥሮ ወረወረው። ወታደሩ በሁኔታው ተገርሞ አፈገፈገ፣ ከዚያም በዝምታ ተውጦ ሁላችንንም ከተመ ለከተን በኋላ በለሆላስ ግን በቁጭት «ጥሩ ነው» ብሎን ወጣ።

በእኛ በኩል በጉዳዩ ስሜት አድሮብን ስለነበር ያዳመጥነው በፀጥታ ተውጠን ነበር። ነገር ግን ወታደሩ ከወጣ በኋላ ሁላችንንም ነፍስ ዘርተን በመጯጯኸ ጭቅጭቅ ጀመርን።

ከመካከላችን አንዱ ጋጋሪውን፣ «ፖቬል፣ የጀመርከውን ሥራ ጥሩ አይደለም።» ቢለው «ሥራህን ቀጥል።» ሲል መለሰለት።

በበኩላችን ወታደሩ ክብሩ ስለተነካበት ቃንያ አደጋ ላይ መሆኗን ተገንዝበናል። ምንም እንኳ ሁላችንም ይህን የተረዳን ቢሆንም ቅሉ፣ በዚያው መጠን ደግሞ ምን ይሆን? የሚለውን ለማወቅ በጣም ጓጉተናል። ለመሆኑ ቃንያ ወታደሩን ተቋቁማ ትመልሰው ይሆን? ሁላችንም በዚህ እርግጠኞች በመሆን፣

ቃንካ? ትቋቋመዋለች! እሷ እንዲህ የዋዛ ሰው አይደለችም! በማለት ተጯጯኸን

ሁላችንም በጣም አድርገን የጓጓነው የአማልክታችንን ጥንካሬ ለመፈተን ነበር፡፡ እርስ በእርሳችንም ስንወያይ በእርግጠኝነት የእኛ አማልክት ከአማልክት ሁሉ ጠንካራ ስለሆነች ከዚህ ሁኔታ በአሸናፊነት ትወጣለች ተባባልን፡፡ መጨረሻ ላይ ግን ወታደሩን በበቂ ያነሳሳነው መስሎ ስላልታየን ውርርዱን ይረሳው ይሆናል ብለን ፈራን፡፡ ስለሆነም የስውየውን የራስ ወዳድነት ስሜት ጥሩ አድርጎ መነካካትና መቆስቆስ አስፈላጊ ነው ብለን አመንን፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም በእኛ በኩል ከዚህ ቀደም ያልኖርነውን፣ የተለየ ውጥረት የሰፈነበትንና የነርብ ሕዋሶቻችንን ያስጨነቀ ሕይወት መኖር ጀመርን፡፡ ያለማቋረጥም ለተከታታይ ቀናት ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ እርስ በእርሳችን ብዙ ተጨቃጨቅን፡፡ ሁላችንም ከቀድሞው በበለጠ አዋቂዎች ሆነን ብዙና በተሻለ አኳኋን መናገር ጀመርን፡፡ እልፍ አልፎ ግን ታንያን ከጕናችን በመደራደሪያ ነጥብነት ይዘን ከሰይጣን ጋር የምንጫወት ይመስለን ነበር፡፡ በዚህ መካከል ከዳቦ ጋጋሪዎቹ «ወታደሩ ታንያን ለማሽኮርመም» ማቀዱን ስንሰማ ከመጠን በላይ በሆነ ደስታ ተዋጥን፡፡ሕይወታችንም ተለውጦ በጉጉት የተመላ ሆነ፡፡ የእኛንም በሁኔታው መነሳሳት የተገነዘበው ባለንብረት በአጋጣሚው ተጠቅሞ በየቀኑ ይቦካ የነበረው ሊ.ጥ 14 ፑድ መጨመሩን አላጤነውም፡፡ በሥራ ብዛት የመዳከሙ ነገር ተረሳን የታንያ ስም ሙሉ ቀን ከአፋችን አልለይ አለ፡፡ በየቀኑ ጠዋት ጠዋትም መምጣቷን የምንጠባበቀው በታላቅ ጉጉት ሆነ፡፡ እልፍ አልፎም ታንያ ወደ እኛ ስትመጣ ያች የምናውቃት ታንያ ሳትሆን ሌላ፣ ለየት ያለች ብትሆንስ የሚል ሃሳብ በአእምሮአችን ይንገዋለል ገባ፡፡

ይህም ሆኖ ለታንያ ስለተፈጠረው ሁኔታ ምንም

አልነገራትም፡፡ ስትመጣም እንደወ ትሮው በፍቅርና በጥሩ ስሜት ከመቀበል በስተቀር ስለምንም ነገር አልጠየቅናትም፡፡ ነገር ግን እኛ ከታንያ ጋር በነበረን ግንኙነት ላይ አዲስና ለቀድሞው ባእድ የሆነ ስሜት አድሮብናል፡፡ ያደረብንም ስሜት እንደ ብረት ቢላዋ የሾለና የቀዘቀዘ፣ ከዚያም አልፎ ኃይለኛ ጉጉትን ያዘለ ነበር፡፡

ከቀናቶቹ በአንዱ ማለዳ ላይ የዕለት ስራውን የጀመረው ጋጋሪ «ወንድሞቼ! ዛሬ የተሰጠን የጊዜ ገደብ ያበቃል!» በማለት ሁኔታውን አስታወሰን፡፡

እኛም ብንሆን ያለ እሱ አስተዋሽነት ጊዜው መድረሱን አውቀን የነበረ ቢሆንም እሱ ካስታወሰን በኋላ ደግሞ የበለጠ ንቃት አሳየን፡፡

እሱም አያይዞ፣«በደንብ ተመልከቷት ... አሁን ትመጣለች» አለን፡፡ ከመካከላችንም አንዱ በቅሬታ በተመላ ድምጽ፣

«ለመሆኑ ሁኔታው በዓይን የሚታይ ነው!» አለው፡፡

እንደገና በመካከላችን መጯጯኽ የበዛበት ጭቅጭቅ ተነሳ፡፡ የዛሬው እለት ሁላችንም በውስጣችን ካለው ምርጡን ያኖርንበት ምርጥ እቃ፣ ምን ያህል ንፁሕና እራሱን ከቆሻሻ የጠበቀ መሆኑን የምናውቅበት የመጨረሻ ቀን ነው ተባባልን፡፡

በዚያን እለት ጠዋት ነበር የምንጫወተው ከፍተኛ ጨዋታ አማልክታችንን ጨርሶ ሊያጠፋብን የሚችል መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገነዘብነው፡፡ ባለፉት ቀናት ውስጥ ያለማቋረጥ የሰማነው ወታደሩ ያለመታከት ታንያን የሚከታተላትና የሚነዘንዛት መሆኑን ነበር፡፡ ከእኛ በኩል

ግን ለምን እንደሆነ እንጃ አንድም ሰው እሷ ስለእሱ ምን እንደምታስብ አልጠየቃትም። እሷም ዘወትር ጠዋት እንደተለመደው ከእኛ ዘንድ መጥታ ብስኩት ስትወስድ፣ ለእኛ ያችው የተለመደችው የወትሮዋ ታንያ ነበረች።

በዚያን ቀን ማለዳም እንደተለመደው ሁሉ በጠዋት ድምጿን ሰማን። ታንያም፣ «ሰላም! እስረኞች! መጥቻለሁ!» አለችን።

እኛም ተቻኩለን ወደ ውስጥ ካስገባናት በኋላ ከተለመደው ተቃራኒ በሆነ ፀጥታ ተቀበልናት። ሁላችንም ዓይኖቻችን ተጉልጉለው እስኪወጡ ድረስ አፈጠጥን እንጂ ከእሷ ጋር ስለምን ማውራት እንዳለብን ወይም ደግሞ ታንያን ስለምን እንደምንጠይቃት አላወቅንም ነበር። በአጭሩ ግራ ተጋባን። ሁላችንም ከፊት ለፊቷ በዝምታ ተውጠን ቆምን። እሷም ባልተለመደው አቀባበላችን መደነቋን አልደበቀችም። በድንገትም ፊቷ ተለዋውጦ አመድ ስትለብስ አየናት። በሁኔታውም ተደናግጣ በተጨነቀ ድምጽ፣

«ምነው ሁላችሁም ተለወጣችሁ?» አለች፣

«አንችስ?» በማለት ጋጋሪው ዓይኖቹን በእሷ ላይ እንደተከለ በጨፈገገው ድምጽ ጠየቃት።

«እኔ ምንሆንኩ?» አለች ታንያ፣

«ምንም!»

«ደህና እንግዳው ብስኩቶቹን ቶሎ ስጡኝ...» አለች። ከዚህ በፊት እንደዚህ አስቸኩላን አታውቅም።

ጋጋሪው ዓይኖቹን በእሷ ላይ እንደተከለ፣ «በቂ

ጊዜ አለሽ» አላት። በዚህ ጊዜ ሳይታሰብ በሩን ከፍታ ተሰወረች።

ጋጋሪው የመጋገሪያውን ትልቅ ማንኪያ አንስቶ በረጋ ሁኔታ ወደ ምድጃው በማምራት፣ «ወታደሩ ጉዳዩን ፈጽሟል ማለት ነው። ክፉ ሰው» አለ። እኛም እንደ በግ መንጋ እርስ በእርስ እየተጋፋን ወደ ጠረጴዛችን ሄደን በፀጥታ ተቀመጥን። ደከምከም ባለ መንፈስም ሥራችንን ጀመርን። በዚህን ጊዜ ከመካከላችን አንዱ፣

«ምናልባት ጉዳዩ አልተፈጸመ እንደሁ...» ሲል ተናገረ። ጋጋሪውም፣ «በላ ቀጥል ተናገር» በማለት ጮኸበት።

ጋጋሪው ሁላችንም የምናምንበትን፣ ከሁላችን የበለጠ አዋቂ ሰው ነበር። ይህም በመሆኑ ከጩኸቱ የተረዳነው በወታደሩ ድል አድራጊነት የአመነበት መሆኑ ስለነበር ከባድ ሐዘን ተሰማን... ተረበሽን...።

ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን ማለትም በምሳ ሰዓት ላይ ወታደሩ ወደ እኛ መጣ። እሱም እንደተለመደው ሁሉ ንጹሕና ሽክ ያለ ነበር። ወታደሩ እንደወትሮው በቀጥታ ዓይኖቻችንን ትክ ብሎ ተመለከተን። ለእኛ ግን እሱን ትክ ብሎ መመልከቱ አስጨነቀን።

«ታዲያስ ክቡራን፣ የወታደሩን ድፍረት እንዳሳያችሁ ትሻላችሁ?» ሲል በተኩራራ መንፈስ ጠየቀን። አያይዞም «እንግዲያው ወደ መተላለፊያው ውጡና በየቀዳዳው ተመልከቱ... ግልጽ ነው?» አለን።

እኛም ወደ ውጭ በሚያወጣው ኮሪደር የሳንቃ ግድግዳ ቀዳዳዎች አማካይነት ለመመልከት አንዳችን በአንዳችን ላይ ተደራረብን። ብዙም አልጠበቅንም። ታንያ በፍጥነት

እየተራመደች መጣች። የቀለጠውን በረዶና የቆሸሸውን ክምችት በእመርታ እየዘለለችም ግቢውን አቋርጣ በማለፍ ከምድር ቤቱ በር ገብታ ተሰወረች። ከፊቷ ላይ በሃሳብ መዋጧ ይነበባል። ከዚያም ወታደሩ እጆቹን በኪሶቹ ከቶ ሪዙን እያንቀሳቀሰ፣ እሱም በእመርታ እየተራመደና እያፏጨ አልፎ ሄዶ ወደዚያ ገባ።

ዝናብ ይጥል ነበር። እኛም የዝናብ ጠብታዎች በተቋጠረው ውኃ ላይ ሲያርፉ፣ የእነሱ ግፊት ደግሞ በተራው የተቋጠረውን ውኃ በትናንሽና ቀጫጭን ቦዩች እንዲወርድ ሲያደርገው ተመለከትን። ቀኑ የጨፈገገው፣ የቀዘቀዘና ጭር ያለው ነበር። በቤቱ ጣሪያ ላይ በረዶ እንደተጋገረ ነው። በመሬት ላይ ያለው ግን መቅለጥ ስለጀመረ በየቦታው የቆሸሸ ውኃ ቋጠሮ ይታያል። በጣሪያው ላይ ያለውም በረዶ ቢሆን በመጠቋቆሩ ጣሪያው በቆሻሻ ተሸፍኗል። ቀጥ ብሎ የሚወርደው ዝናብ ድምጽ የሐዘን ነበር። ቀኑ ቀዝቃዛ ስለነበር በርዶናል፣ መጠበቁም ሰልችቶናል።

በመጀመሪያ ከምድር ቤቱ የወጣው ወታደሩ ነበር። እሱም ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ ረጋ ብሎ እጆቹን ከኪሶቹ ከቶ ሪዙን እያነቃነቀ ግቢውን አልፎ ሄደ።

ቀጠል አርጋ ታንያ ወጣች። ዓይኖቿ... ደስታና ፍስሐ ያንጸባርቃሉ፣ ከናፍሮቿ ፈገግ ብለዋል። እሷም በሕልም ዓለም ውስጥ እንዳለች ሁሉ እየተወዛወዘች እርግጠኛ ባልሆነ እርምጃ ወደፊት አመራች።

በእኛ በኩል ይህን ሁኔታ በዝምታ ማለፍ አልቻልንም። ሁላችንም በአንድ ጊዜ ወደ በሩ አመራን። በርግደንም ወደ ውጭ ወጥተን፣ በታንያ ላይ አፏጨንባት፣ ጭካኔን

ባስተጋባ ድምጽ ጮኸንባት፣ በአረመኔነት ተረባረብንባት።

እሷም እኛን ስታይ ከመደንገጧ የተነሳ ከቆሻሻ ውስጥ እንደቆመች ድርቅ ብላ ቀረች። ዙሪያዋን ከበንም በክፉ ዓይን እያየን በጣም አሳፋሪ የሆኑ ስድቦችን አወረድንባት።

ይህን ያደረግነው ከከበብናትና ከከበባው አምልጣ ወደትም ለመሄድ እንደማትችል ካረጋገጥን በኋላ ሳንጮኽ፣ ሳንቻኮል፣ ረጋ ብለን ነበር። ስለከበብናትም ያሻንን ያህል ጊዜ ወስደን አሾፍንባት። ለምን እንደሆን አላውቅም አልደበደብናትም። እሷም ከመካከላችን ቆማ ጭንቅላቷን እንዴ ወዲህ እንዴ ወዲያ ዘንበል እያደረገች ያወረድንባትን የስድብ መዓት ትሰማ ነበር። እኛም አራስ ነብር ሆነን በአለን ኃይል ሁሉ ወራዳና መርዛማ ቃላቶቻችንን አወረድንባት።

ከታንያ ፊት ላይ ሕይወት ደበዘዘች። ከደቂቃ በፊት ደስተኞች የነበሩት ሰማያዊ ዓይኖቿ ፈጠጡ፣ ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ አለ፣ ከንፈሮቿ ተንቀጠቀጡ።

እኛም ታንያን ከበን የእኛ የሆነን ነገር ዘርፋናለችና ቂም በቀላችንን ተወጣን። እሷ የእኛ ነበረች። እኛም ያለ የሌለንን መልካም ስሜት ሁሉ ለእሷ አድርገነው ነበር። እርግጥ ይህ መልካም ስሜት የምስኪኖች ብጫቂ ነገር ሊሆን ይችላል። ቢሆንም ያንኑ ለእሷ ሰጥተን ነበር። ይህም ሆኖ እኛ ሃያ ስድስት እሷ ግን አንድ ብቻ ስለሆነች ያደረሰችብንን በደል የሚመጥን የበቀል እርምጃ ለመውሰድ አልቻልንም። እንዴት አድርገን ሰደብናት...! ታንያ በዝምታ ተውጣ፣ ጭካኔ በተመላበት እይታ አተኩራ ስትመለከተን ሰውነቷ በሙሉ ይርድ ነበር።

እኛ ሳቅን፣ አሽካካን፣ አፌዝንባት... ከየት እንደመጡ

የማናውቃቸው ሰዎችም ከበቡን... ከመካከላችን አንዱ የታንያን ኮት ጉንተል አደረገ::

በድንገት ዓይኖቿ ብርሃን ፈነጠቀ፤ ሳትቸኩል ረጋ ብላ እጆቿን በማንሳት ፀጉሯን አስተካከለች:: ከዚያም ጮክ ብላ ግን እርጋታ በሰፈነበት ሁኔታ በቀጥታ ፊት ለፊት እያየችን፣

«አይ እናንተ ዕድለ ቢስ የሆናችሁ እስረኞች!» አለችን:: ከዚያም ጨርሶ በቦታው፣ በመንገዱ ላይ እንደሌለን ሁሉ በቀጥታ ወደ እኛ መጣች:: እኛም በመንገዱ ላይ አልቆምንም፣ በመንገዷም አልተጋረጥንም::

ከከበባችን ከወጣች በኋላ ወደ ኋላ መለስ ብላ ሳትመለከተን ወደፊት እየተጓዘች ድምጿን ከፍ አድርጋ በኩራትና በንቀት፣

«አይ እናንተ! ምናምንቴዎች! ወራዶች!» ብላ ሰደበችን:: እኛም በግቢው መካከል ከቁሻሻው ውስጥ እንደቆምን ቀረን:: ዝናብ ይጥላል:: ፀሐይ በቦታው የለችም:: ሰማዩም ጥቁር ግራጫ ቀለም ተላብሷል::

በመጨረሻም ፀጥ ብለን ወደ ቀዝቃዛዋ የድንጋይ ሳጥናችን ተመለስን:: እንደቀድሞው ሁሉ በክፍላችን መስኮት በኩል የፀሐይ ብርሃን ጨርሶ አልፈነጠቀም፣ ታንያም ከዚያ በኋላ አልመጣችም::



# ሸር - እንደሸረሪት



# ጌታ ሆይ

. ወሰን ይሄይስ

«ከዚህ ከምድር ላይ ሽቅብ የሚታየው ሰማይ ሁሉ፤ ከአድማስ እስከ አድማስ፤ ከጠፈር እስከ ጠፈር፣ ኩታ ገጠሙ ሁሉ ግንባርህ የሆነ አምላክ ሆይ፤ በአንድ በፀሀይ ወይ በጨረቃ አሊያም በፈረቃ ዐይንህ የምታይ አምላክ ሆይ፤ በሰው አካል በሰው አምሳል፣ ሌላው ዐይንህ የታል? ወይስ ሌላው አይንህ ሌላ ያያል? አንተ ምን ይገድሃል! ወደሰማየ ሰማያት እንዲያይ አድርገኸው ቢሆንስ- ይሄኑ የአንዱን ዐይንህን የወዲያኛውን ጉን::

«እንዲያው ለነገሩ አብዩ፣ የአሰምሮን አቅም ሰጥቶ፣ የሰውን ልጅ የሚያለያይ ዘረኛ ብሂልን ምን መቋጫ ለማስህለታል? አዎ አንተማ ሰው በሃሳቡ ምንም እንዳይገደው ፈቃድህን መርቀህ ወይም ረግመህ ትተህለታል:: ምድራዊ ቁሳዊ ህይወቱን መደለያ ኑሮ መዕውተኸዋል:: ክብር ምስጋና ይግባህ:: ሰው ያንተ ድሃ፣ ያንተ ለማኝ፣ ባዶነትንና ምሉዕነትን በባዶ ጊዜ ለዘንታለም እያመሳከረ፣ እያቻቻለ፣ መሆንንና አለመሆንን ይኖራል:: ይቅናው ያስችለው ዓሜን!!

«ጥንት አማኝ አልነበረህም ይባላል:: በዚችው ዓለም የድሮ ምድር ላይ፣ የድሮ ሰዎችን ሰብከህ እንደነበረም ይነገራል:: ምስጋና ይግባህ ገለታ የድረስህና ዛሬ አሳማኝ ሞልቷል:: በስምህ የሰበከ ሁሉ ተከታይ አያጣም:: ጦሙን አያድርም:: ገዳም ንጉስ ነህ:: ግን ዛሬ አማኝ መኖሩን እንጃ:: ለማሳመን እንጂ ለማመን የሚንበረከክ መኖሩን እንጃ:: ታምር ገላጩ በዛና የእምነት አንድነት ታጣ:: ከስምህ እስከ ስርዓትህ ልዩነቶች በዙ:: ወይ ድሮውኑ ብዙ ነበራችሁ ይሆን? እና የኛው የቱ ነህ? የመቅደሱ ነህ የመስጊዱ?... ወይስ አንድም የትየለሌም ነህ? ናችሁ? እና ሰባኪም ተሰባኪም ሁሉ ከንቱ ይሆኑ? ከእያንዳንዱ እንደየእምነቱ እንደየዕናቱ (እንደየፀሎቱ) ይሆን የዘመናችን ምልዐተ ጉድለቱ?

«ደማቅ፣ ብልጭልጭና ኅርንገርገር ልብሶች የለበሱና ውድ ዋጋ ያላቸው ምልክቶች የሚጠቀሙ፤ በልዩነታቸው ግርማ ሞገስ የሚያስፈሩ ጌጣ- ጌጦች የሚሸለሙ ሁሉ ያንተ መላክተኞች ናቸውን? ነጭ በነጭ ለብሰው፣ አልባብ፣ አልባብ እየሸተቱ፤ ጫጉት ቅመጠ በስምህ እውቀታቸውን የሚያስሙ፤ የድሮ ቋንቋና መፃህፍትን የሚያወድሱ፤ እውን ያንተ ነቢዮች ናቸውን? እውን አንተ ያለቀሳውስት ያለሼኮች

የለህምን? እውን ኢየሩሳሌምን ያልሳመ፣ መዲናን ያልጐበኘ ... ብለሃልን? ጠያቂህን ይቅር በለው ጌታዬ። አውሊያስ ምንድነው ፈጣሪ ሆይ? ስራቱ ከአንተ ነው ከሌላ?

«ሠይጣን ከአንተ የተሰጠረ ነውን? አንተን አምነን በራሳችን እንመካ ዘንድ ባለጋራህን ያዝልን። ርኩሳን መናፍስትን ከልጆችህ መኖሪያ ውጭ አርጋቸውና አስደስተን። የእድሜ ገደብንም ከእህልም ከውሃም፣ከጤናም፣ ቁጥጥር አንፃልን። ሲሳያችንንም አታበላልጥብን፤ አታቀናናን። አዎ አታታግለን። ሰላምን አድለን።

«እንድያው አንድ ነገር ደግሞ አለ- ያንተ ነው እያሉ የሚሸጡት ስዕል ጉዳይ። ልብህን ከልብስህ ውጭ አርገውት ነው እንጂ፣ የጠጉርህ ማማር፣ የወዘናህ ማማር። ኧረ በጣሙን ሸጋ ነህ። ያንተ ማማር ለኛ ክብራችን ይሁንልና!! ይኼኔኮ ሠይጣን ጠጉሩም የማያምር፣ ንጣትም የሌለው ወዘናም፣ የሌለው ይሆናል- የታባቱ! ድሮውንስ ፈረንጅነትን ከየታባቱ ያመጣዋል?!»

«ግን ደሞ ፀጉርህም መልክህም ከጥቁር ዘር አምሳያም የለው። እኛ ጥቁሮች ንጣትን እንደማንፈልግ አውቀህ ያረግኸው ይሆናል። ወይም እነዚያ ነጮች ጥቁረትን እንደማይፈልጉ አውቀህ ያረግኸው ይሆናል። ወይ ደሞ ዲያብሎስ ሲባረር ወደዛሬው የጥቁሮች አህጉር ዘልቆ ከሰይጣን ተራብቶ ይሆን? እንዲህስ አይሁን አደራ! እንዲህ ከሆነማ ዘርዓ ጥቁር ወደ አንተ ውዴታ ለመድረስ መቻሉን እንጃለት።

«ያንተ ረቂቅነት ግን አይመረመርም። ጥቁሮችን ፈልጐ አግኝቶ ስለ አንተ ሰብኮ በስምህ ቅኝ ግዛትን የአስፋፋው ዘርዓ- ነጭ፣ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረሱ ምን ጥርጥር

አለበት። በምድርም በሰማይም የምታሸር፣ ታላቅ ንጉስነትህን ከነሱ የበለጠ ያስተምር ዘንድ ማን ይቻለዋል? ለዚያውምኮ ጥቁሮች እንሰበክም ብለው ሰይጣናዊ ጦርነት አውጀው፣ የገደሏቸው ሰማዕታት ፈረንጆችም ይኖራሉ።»


«በዚህ በዚህ የተነሳ መጪው የጥፋት ዘመን ለመላው ዘርዓ ሰብ ሳይሆን ለጥቁሮች ሳይሆን ይቀራል? ጥቁር ህዝብ ያሳዝናል። የቅጣቱ አቅጣጫስ ሳይበዛበት ይቀራል- ቅጣት የአቅም ሳይሆን፣ የፈጣሪ ቁጣ ብቻ ከሆነ!»

«እንዲያውማ የሰው ልጅ ከዝንጀሮ ዘር የመጣ ነው የሚባለውም ቅጥፈት ነው። ጥቁሮችን ለመንካትም ለማግባባትም የተባለ ሳይሆን አይቀርም። ጥቁር የርኩስ መንፈስ የሰይጣን ዘር ነው እንዳይሉት ለቅዱስ መንፈስ ስብከታቸው የማይመች ሆኖባቸው ይሆናል። የሚገርመው የጥንታዊ ሰው ዘር የሚባለው የሚገኘው ሁልጊዜ በጥቁሮች አገር መሆኑ ነው። እምና የዝንጀሮ አፅም እየለቃቀሙ አያቶቻችንን አገኙልን ለመባል ያሉት ይሆናል። ቢሆንም ከሰይጣን ዘርነት ይሻላል ብለው የዘር- ሀረግ ግንድ መስገሳቸው ከሆነ ይሁን። ደሞ ሌላ መዘዝ እንዳያስከትሉ እንጅ።


«እና ጥቁር ሁልጊዜ የጥንታዊነቱ ታሪክ እየተመረመረ ይኖረዋል። ለዛሬ እደግ ተመንደግ፣ ተስማማ የሚለው ግን የለም። ጥንትነቱን ለመፈለግ ጉድጓድ ሲምስ ፈረንጁ ትንቢቱን እውን ለማድረግ ሸቅብ ይፈተለካል። ጥቁር ዛሬነቱን ከትላንትነቱ እያስተሀቀረ ሲፅናና፣ ነጭ ዛሬነቱን ከነገነቱ እያስተያዬ ይቦርቃል። የጥቁር ዛሬ ለነጭ ትላንቱ ቢሆን፣ የነጭ ዛሬ፣ ለጥቁር ከርሞው ይሆናል። እስኪ ይሁና።

«ግን ፈረንጆች አምላካችንን ቀምተውን ቢሆንሳ? ሰይጣንኮ ጥበብን ይወዳልም፣ ያውቃልም፣ ይመራመራልም ይባላል:: እንዲህ ከሆነ እኛ ደጐች ደጋጐች እንሆናለን:: የነጮች ሰይጣናዊ ምርምርና ግኝት ሁሉ በጥቁሮች ጾም ጸሎት ሊደመሰስ ይገደዳል:: የሰዎችን ጥበበኛነትና ምርምር የማያወግዘው፣ ነጮች የሚሰብኩበት፣ ጥቁሮች የሚሰ በኩበት አገላብጦ መዛኙ አምላክ ለኛ ይፈርድልን ይሆናል:: ኧረ አርግልን ጌታዬ!! ኧረ አዘዋውረው እባክህ! ኧረ ነጩ ይጥቆር! ኧረ ጥቁሩ ይንጣ! እርስ-በርስ አባልተው ሊጨርሱን ሆነኮ!...


«ጌታ ሆይ! ኧረ አንተ ረዝቀን:: እድሜውን፣ ጤናውን፣ ሀብቱን፣ ሰላሙን፣ ፍቅሩን፣ ምክሩን እውቀቱን አንተ ለግሰን፣ እባክህ:: የጦር መሳሪያ ማረሻና ወገል ይሁን እባክህ:: የጦርሰው ሰርቶ እንዲበላ አርገው እባክህ:: መምጫህ የማይታወቅ አምላክ ሆይ! ክፉችንን አርቅልን:: ርዳታህን አቅርብልን:: አንተ አበርታን:: በተረፈ አንተው ሙላበት- አሜን::»




# ፃም ስዘልዓለም ይኑር



# እኩልነት በምን?



# ከማን አንሼ



# ናፍቆት - ምንጣፍ እስኪደርስ

# አንባቢያን ሆይ!

«ፋና ዴሞክራሲ አሳታሚ» ስለዚህ መፅሀፍ ያላችሁን አስተያየት ብትገልፁለት በደስታ ይቀበላል::

አድራሻ - 12682

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

301
~~338~~/2000
636/93

ዋጋው ብር 15.00